# ከምድራዊነታችን ባሻገር

## ሦስተኛ መጽሐፍ

## ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ - ማስታወሻና ማስተዋያ

መ. ኃ. መስቀል (ዶ/ር)

# ጸሎት

አቤቱ ፈጣሪአችን አምላካችን ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ!
የእውር ሰውን ልቦና ባለ አይን ከሚያየው የበለጠ እንዲያይ
ማድረግ የምትችል አንተ ነህና፤
ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን የሚጠቅም ሆኖ ይጨረስ ዘንድ፥
ስለአንተ ፈቃድ እለምናለሁ።
አሜን።

Copyright © 2020 by M.H. Meskale (PHD)

መልሶ የማሳተም መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ሁሉ ለመንፈሳዊ እና ለበጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚሰጥ፥ ለድኩማንም መርጃ የሚውል ይሁን።

# መታሰቢያ

**ለባለቤቴ እና ለልጆቼ**

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ እዚህ ያደረሰኝን ፈጣሪ አምላኬን በከፍተኛ ደረጃ አመሰግነዋለሁ። በእውነት ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን የጨለመውን የሚያበራ፥ ቀናውንም መንገድ የሚያሳይ፥ እኔ በእውቀት ሳይሆን፥ በብዙ ዓመታት ጥረትና በጸሎት የተጋሁበትን ሥራ አይቶ እርሱ እንደረዳኝ አምኛለሁ፤ የተማመንኩበት አምላኬ አላሳፈረኝም።

በአካላዊነት የማትታየው ባለቤቴን እና በኑሮዬ ደስ እንዲለኝ የሚያደርጉኝ ልጆቼን  በጣም አመሰግናለሁ። ለደገፉኝ ለኔ ዘመዶችና ለባለቤቴ ዘመዶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቅርብም ሆነ በሩቅ ሆናችሁ በመንፈስ ላልተለያችሁኝ ወገኖቼ ሁሉ ሙሉ ምስጋናዬን ከመንፈሳዊ ፍቅር ጋር አስተላልፋለሁ።

በከፊልም ሆነ በብዛት መንፈሳዊ ትምህርትን ላስተማሩኝ (ለሰበኩኝ) ኦርቶዶክሶች፥ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። የሁላችንም ሕይወት በምድር ላይ እክል እንዳይበዛበት መንፈሳዊነትን የሚያስተምሩ፥ የሚያጽናኑ፥ የሚመክሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።

በእርማትም ሆነ አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ፥ በተለይም ለወንድሜ ለአዲስ አለሙ እና ለጓደኛዬ ለተስፋየሱስ መንግሥቱ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

# የአጻጻፍ መመሪያዎች

ይህ መጽሐፍ ለምሁራኑ እንዲሁም ለሠፊው ሕዝብ ቀላል ምንባብ እንዲሆን የሚከተሉትን የአጻጻፍ መመሪያዎች ተከትሏል፡-

- በተቻለ መጠን አረፍተ ነገሮችን በማሳጠር፥ በቀላል አማርኛ ተዘጋጅቷል።
- ከተጠቀሱት ዋቢ መጻሕፍት ሌላ፥ የድረ ገጽ ምንጮችና ተጨማሪ ማብራሪያዎች በግርጌ ማስታወሻዎች (foot notes) እንዲያመላክቱ ተደርጓል።
- አንዳንድ ቃላት በትእምርተ ጥቅስ (quotation mark) የታጠሩት፥ አረፍተነገሩ ከሚያመለክተው ውጪ ሌላም ትርጉም ሊሰጠው ስለሚችል የመጽሐፉ ስሜት እንዲጠበቅ ሲባል ነው ትእምርተ ጥቅስ ያስፈለገው። ለምሳሌ፡- በሥጋም በመንፈስም "አንድ" ነን ሲል፥ "አንድ" የሚለው ቃል አንጻራዊ ስለሆነ ለአረፍተነገሩ የተለያየ ፍቺ ይሰጠዋል - ሰውን ሁሉ "አንድ" ሊያስመስለው ይችላል - ሳይሆን።
- አንዳንድ ቃላት በመጥበቅም ሆነ በመላላት ሲነገሩ የተለያየ (አሻሚ) ፍቺ እየሰጡ እንዳያደናግሩ፡- አልፎ አልፎ (እንደየአስፈላጊነቱ፥ አሻሚ ፍቺ እንዳይኖር) አንዳንድ ሆሄዎች ላይ በመጥበቅ መነገር ሲኖርባቸው ከሥራቸው ተሰርዞባቸዋል። ለምሳሌ፥ አልለይህም (ሰረዙ አንድ ሆሄ ላይ ብቻ ነው)፤ አይገባም (ሰረዙ ሦስት ሆሄዎች ላይ ነው)። ይህ የተደረገው፥ በተለይ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ሆኖ፥ ወይንም በውጭ አገር ብዙ ስለቆዩ፥ ወይንም ከዛ ስለተወለዱ፥ የአማርኛን ስነጽሐ#ፍ ምንባብ ላልተለማመዱ አንባቢያን እንዲቀላቸው ለማድረግ ነው እንጂ፥ በዚህ ረገድ የአማርኛን ስነጽሑፍ ለማሻሻል ታስቦ አይደለም።
- ከመደበኛው የአጻጻፍ ዘዴ ወጣ ቢልም፥ ልክ እንደ ንግግር ሆኖ ቀለል ይል ዘንድ፥ ነጠላ ሰርዞች በዛ ብለውበት ይሆናል።
- ብዙሓኑ ሲያነቡት "የማውቀውን ቀስቅስ እንጂ አትንገረኝ.." እንዳይሉ፥ በተቻለ መጠን ገኃድ የሆኑ ሃሳቦች መጠቀሳቸው ለአንዳንድ የአስተሳሰብ ዘገባዎች የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፥ ተወግደዋል።

- የወንድ  ጾታ ብቻ አልፎ አልፎ ቢጠቀስ፥ የሴትን ጾታም በውስጠ ታዊቂነት አብሮ በማጠቃለል ነው።
- አንባቢ ዘና ብሎ እንዲያነብ፥ ጠለቅ ያሉ ሃሳቦችን ለማፍታታት፥ በዚያውም መጽሐፉ የራሱ የሆነ ጣዕም እንዲኖረው ለማድረግ፥ አልፎ አልፎ ግጥሞች ታክለውበታል።
- በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሃይማኖት ነክ ጉዳዮች አላማ፥ ከመንፈሳዊ ይዘታቸው አልፈው፥ በማንንም ሃይማኖት ላይ ነቀፊታ - አጉል ትችት ወይም የግል ስሜትን ለማንጸባረቅ አይደለም።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተጠቀሱት፥ አንዳንድ ሃሳቦችን ለማብራራት ነው እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያመለክተው መንፈሳዊ ትርጉም ጋር ለማመሳሰል አይደለም።
- አንዳንድ ፖለቲካዊ  ወይንም ሃይማኖታዊ አመለካከቶች ሲብራሩ፥ የሚያነበው ሁሉ ከራሱ ሃሳብ ርቆ የሚሄድ ባለ አንድ አቅጣጫ አክራሪ ሃሳብ እንዳይጎላበትና እንዳይሰናከል ጥንቃቄ ተደርጓል። ምናልባት በግላጭ ወይንም በድብቅ ወገናዊነት ቢታይባቸው፥ የአንባቢ ይቅርታ ይጠየቃል።
- ይህ መጽሐፍ፥ አንዳንድ እስከ ዛሬ ያልተደረሰባቸውን ፍሬ ሃሳቦች ስለሚያካትት፥ ለወደፊት ትኩረት እንዲሰጣቸው በማሰብ፥ እጅግ በተቃለለ መንገድም ቢሆን፥ ደራሲው የራሱን ነፃ አስተያየት ከመሰንዘር አልተቆጠበም።

# መቅድም

ታግሶ ይህንን ያህል በምድር ላቆየኝ ሉላዊ ሕብረተሰብ፥ ወደማልመለስበት ስሄድ የምተወውን ማዘጋጀት ግዴታዬ መስሎኛል። ማንም ሰው የሚሠራው ሥራ ሁሉ ጥሩ ብቻ ወይንም መጥፎ ብቻ መሆኑን ሳያውቅ ነው የሚሠራው። እኔም አላወቅሁም ብዬ መሥራቴን አላቆምኩም።

መጻሕፍትን የመጻፍ ሥራ ከመጀሩ በፊት፥ "ለመሆኑ እኔስ ማነኝና? ምንስ አውቄ? እንዴትስ ብደፍር?.. እስቲ እራሴን በቅድሚያ ልመርምር...." በማለት የምድራዊነቴን እና የነፍሴን (የመንፈሴን) ጉዳይ ሳሰላስል የተጻፈው፥ "ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት" በሚል ርዕስ ከአንደኛው መጽሐፍ መጨረሺያ እንደ አባሪ ቀርቧል።

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በተለይ ሃይማኖተኞች ሃይማኖታዊ እምነቶቻቸውን በሳይንሱ እያገናዘቡ፥ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ የበለጠ እንዲያደንቁ፤ ሳይንቲስቶችም ተፈጥሮን ሲመራመሩ፥ የሚያውቁትንም ሆነ የማያውቁትን፥ የሚያዩትንም ሆነ የማያዩትን የሚያጠቃልል፥ አንድ መለኮታዊ ኃይል መኖር እንዳለበት እንዲያገናዝቡበት ነው።

ምድር ክብ አይደለችም ብለው ሲከራከሩ የነበሩ፥ አሁን አለምን ሲዞሩ ክብነቷን እንዳመኑ ሁሉ፥ ሳይንስ የማናውቀውን በመግለጡ፥ የእግዚአብሔርን ሥራ የበለጠ እንድናውቅ የሚረዳን፥ በእርሱም ያለንን እምነት እንዲጠናከር የሚያደርግ እንጂ፥ የሃይማኖት፥ የእምነታችንም ጠላት ሊሆን አይችልም። ሆኖም፥ ሳይንስ ምድራዊ ኑሮአችንን ቢያመቻችልን፥ በፍቅርና በመከባበር ተስማምተን እንድንኖር አያስተምርም፤ ለሕብረታችን፥ ለአንድነታችን እና ለሰላማችን የሚጠቅመውን ሁሉ የሚያስተምር ሃይማኖት ስለሆነ፥ የመንፈሳዊነታችንን ነገር መመረመር፥ ሳይንስ ለሰው ልጅ የጠቀመውን ያህል፥ ወይንም ከዚያ በላይ ሊጠቅም ይችላል።

በዚህ መጽሐፍ፥ ስለ ጠፈራችን እና ስለ ምድራችን፥ ከቀረቡት ሳይንሳዊ ዘገባዎች ጋር፥ የሰውን ልጅ ሥጋዊና መንፈሳዊ ጉዞ ለመግለጽ የተሞከረው፥ ሁሉም የሚያያዝ በመሆኑ ነው። በሚገባ ቋንቋ ከቀረበለት፥ ማንም ሰው መጠነኛ መሠረታዊ ሳይንሳዊ እውቀት ሊኖረው ይችላል። ሆኖም፥ በዚህ መጽሐፍ የተካተቱ ሳይንሳዊ ዘገባዎች፥ በተጠቀሱት አርእስቶች ላይ ማንም ሰው መጠነኛ መሠረታዊ ሳይንሳዊ

እውቀትና ግንዛቤ ለመስረጽ ያህል ነው እንጂ፥ እንዳንድ አርእስቶች ለደራሲውም ሆነ ለሌሎች እጅግ የሚከብዱ ናቸው።

ሳይንስ ያልደረሰባቸውን ጉዳዮች ሳይንሳዊ ባልሆነ ሃሳብ (አስተያየት) ለማግኘት መሞከር ትክክል አይደለም የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ መጽሐፍ ላይ ሂስ ሊኖር የሚችለውም በዚሁ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፥ ለየት ያለ መንገድ ቢኖር፥ እርሱም በኋላ ሲመረመር፥ ከአንዳንድ አሮጌ ሳይንስ የተሻለ ሊሆን ይችላል። ሁሉንም በትእግስት ይመለከቷል።

ከተያያዝነው ሰፊ አርእስት አንጻር፥ የምናውቀውንና ልናውቅ የማንችለውን ሁሉ - ነው፤ ይመስላል፤ ይሆናል፤ ብሎ በመነካካት የተደረገው ገለጻ ሁሉ፥ ዛሬም ሆነ ለወደፊት የሚታከልበትን እውነት በመተማመን ነው። በተለይም አንዳንድ ጽንሰ ሃሳቦች ሳይንሳዊ መልክ ይዘው፥ ሃይማኖትንም አስታከው መቅረባቸው፥ አንባቢያን በበለጠ እየተመራመሩ፥ በግል የሚያምኑበትን ለማጠናከር እንዲረዳቸው ስለሆነ፥ ወጣት ተማሪዎችም ለወደፊት ሳይንቲስቶች ቢሆኑ፥ በእግዚአብሔር የሚኖራቸውን እምነት የሚያጠናክር እንዲሆንላቸው ታስቧል።

በተጨማሪ፥ ስለ ሰው ዘር፥ ስለ ስደቱ፥ ስለ ኢትዮጵያችንም በመጠቃቀስ፥ የሕዝቦችን አጠቃላይ ታሪክ በሳይንሳዊ እይታ ለመግለጽ ተሞክሯል። ስለዚህ፥ ይህ መጽሐፍ በእጃችሁ የገባ፥ በውስጣችሁ ያለው እውነት እንዳይበረዝባችሁ እየተጠነቀቃችሁ፥ ሁሉንም እንደ ፍጹማዊ እውነት ሳትቆጥሩ፥ በእናንተው እንደተጻፉ እየቆጠራችሁ፥ ከአበቦች መካከል ጣፋጩን ጭርቃ እንደሚቀስሙ ወፎች፥ ወይንም ከጭቃ ውስጥ የጠፋ ወርቅ እንደሚፈልግ ሰው ሆናችሁ አንብቡ። ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን የጨለመውን የሚያበራ፥ ቀናውንም መንገድ የሚያሳይ፥ ለሁሉም እንደየሁኔታው ይገልጥለታል።

**<u>የአንደኛው መጽሐፍ ይዘት - ከግለሰብ እስከ አገር - ማስታወሻና ማስተዋያ፡</u>**

አባቶች/እናቶች በበኩላችን የሄድንበትን ጎዳና፥ ያሳለፍነውን ክፉውንም ደጉንም ጊዜ ለልጆቻችን እንድናሳውቅ፤ ለሁላችንም ቢሆን እንደ ማስታወሻ፥ እንደ ማስተዋያም እንዲሆን በማሰብ ተዘጋጀ።

ይህ መጽሐፍ በወታደራዊው አገዛዝ (ደርግ) ዘመን፥ ደራሲው በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ውስጥ የነበረውን ወቅታዊ አብዮታዊ ተሳትፎ፥ በዚያውም ስለ አገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ እና በኢሕአፓ ውስጥም ስለተፈጠረው ውስጣዊ የፖለቲካዊ ውዝግብ ያወሳል። በመጨረሻም፥ ኢትዮጵያችን ካሁን ቀደም

የገጠሟት ችግሮች እንዳይደጋገሙባት በመምከር፥ በነፃነትና በእኩልነት አንድነታችንን እንድንገነባ ያሳስባል።

**<u>የሁለተኛው መጽሐፍ ይዘት - ሁሉም ለአንድነት - ማስታወሻና ማስተዋያ ግጥሞች፡</u>**

“ከምድራዊነታችን ባሻገር” በሚል አቢይ ርዕስ ሥር ከተዘጋጁት ሌሎች መጻሕፍት የተጠቀሱ አንዳንድ “ጠቃሚ” ሃሳቦችን በስእሎችና በግጥሞች ያጠናክራል። ግጥሞቹ የተዘጋጁት በስሜቶች ብቻ የሚገባን ከሚመስለን ጋር መቆየታችንን ለማስታወሻ፥ መሠረታዊ ጥያቄዎቻችንንም ለማሰላሰል እንዲረዳን ሲሆን፥ በአጠቃላይ የግጥሞቹ ይዘት በኢትዮጵያችንም ሆነ በተቀረው አለማችን ውስጥ ግለሰብአዊ፥ ቤተሰብአዊና ሕብረተሰብአዊ ኑሮአችንን ይመለከታል፤ ትኩርት በምድራዊ ኑሮ ብቻ እንዳይሆንም የሰውን መንፈሳዊ ጠባይ አጉልቶ ለማሳየት ይሞክራል።

**<u>የአራተኛው መጽሐፍ ይዘት - መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ፡</u>**

ለብዙዎች - ሃሳቦችን ከመጋበዝ (ከማስረጽ) አልፎ፥ የሚያሳውቀው ነገር ባይኖረውም፥ ከምናየው አለም የማናየውን አለም ለማየት ስንሞክር የሚታሰበንን (ፍቅር፥ ደስታ፥ ሃይማኖታዊ - መንፈሳዊ ስሜት..) የሚጠቃቅስ፤ ሁሉም የገዛ እምነቱን ይዞ እንዲጸና ለየት ባለ መልክ የሚያሳስብ ነው ይህ መጽሐፍ።

**<u>ሁሉም ለአንድነት - ድረገጽ፡</u>**

ቀደም ሲል፥ ሁሉም ለአንድነት በሚል መርሆ፥ የሚከተለው ድረገጽ ተዘጋጅቶ አያሌ ግለሰቦች በአለም ዙሪያ ተመልክተውታል። ጽሑፎቹ ሁሉ፥ ከስዕሎቹም ጋር ሆነው “ከምድራዊነታችን ባሻገር” የተሰኘውን አቢይ አርእስት ባይመጥኑት ይቅርታ።

<u>https://www.amharicbooksforunity.org/</u>

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ምስጋና፡ | | iv |
| የአጻጻፍ መመሪያዎች፡ | | v |
| መቅድም፡ | | vii |
| ማውጫ፡ | | x |
| | | |
| መግቢያ፡ | | 1 |
| ምዕራፍ አንድ፡ | ሳይንስ እና መንፈሳዊነት - መንደርደሪያ፡ | 3 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ | ስለ ጠፈር፡ | 13 |
| ምዕራፍ ሦስት፡ | የጠፈር መሰብሰብ፡ | 39 |
| ምዕራፍ አራት፡ | ምድራችን - መሬታችን፥ ባህራችን፥ አየራችን፡ | 55 |
| ምዕራፍ አምስት፡ | ምድራዊ አካላዊ ሕያዋን፡ | 73 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ | ዝግመተ ለውጥ እና ፍጥረት፡ | 87 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ | ፍጥረት ከምናየው ሁሉ ባሻገር፡ | 129 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ | ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና፡ | 149 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ | ፍጥረታችን እና ስደቶቻችን፡ | 163 |
| ምዕራፍ አስር፡ | ምድራዊት ምድራችን - ሰማያዊ፡ | 211 |
| የቃላት ትርጉም እና ተጨማሪ ማብራሪያ፡ | | 225 |
| አባሪ፡ (የጊዜ እርከኖች - እንደ ምድራዊ አቆጣጠር) | | 237 |
| ዋቢ መጻሕፍት: (ለአራቱም መጻሕፍት) | | 239 |

# መግቢያ

በዚህ መጽሐፍ አካላዊ ተፈጥሮ ከመጀመሩ በፊትም ሌላ አካላዊ ያልሆነ አለም ነበረ በማለት ይነሳና፥ "አካላዊ ተፈጥሮ ከየት ተጀመረ? ይህች ምድር ከመፈጠሯ በፊት ጀምሮ እንዴት ነበር? ከተፈጠረች በኋላስ? ይህች ምድር (መሬቷ፥ ውሃውና አየሩ) እና በውስጧ ያሉ ሁሉ እንዴት እዚህ ደረሱ?" በማለት ይመራመራል።

ሳይንስና ሃይማኖት በፍልስፍና ደረጃ ተደጋጋፊዎች ሊሆኑም ስለሚችሉ፥ በተለይ የሳይንስ ተማሪዎች ከሚማሩት ሳይንስ ጋር ሃይማኖታዊ ፍልስፍናዊ አመለካከቶችንም ቢያክሉበት፥ የበለጠው እውቀት ከዚያ እንደሚገኝ ያስገነዝብ ይሆናል። ሳይንስና ሃይማኖት የተለያየ የአመለካከት ክልል ቢኖራቸውም፥ ሳይንስ - በተለይም የስነ ምድር (ጂኦሎጂ) ትምህርት ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንጂ የሚያርቅ አለመሆኑን - በእውነት የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ የበለጠ እንድናደንቅ የሚረዳ መሆኑን ለመግለጽ ተሞክሯል። ከእግዚአብሔር ምስክሮች መካከል የጠፈር አካላት በእውነት የሚደነቁ መሆናቸውን ከቀረበው ሳይንሳዊ ገለጻ መረዳት ይቻላል።

እነሆ! በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፥ ሊቃውንት ይቀበሉት ዘንድ የማይደፍሩትን በድፍረት ያስቀመጥናቸውን ሁሉ አንባቢ በትእግስት እንደሚከታተላቸው ተስፋ እናደርጋለን። አልፎ አልፎ ከአቅም በላይ የሚመስል፥ ከስሜት ብዛት ወይንም ከተደበቀ ውስጣዊ እውነት ግፊት የተነሳ፥ የድፍረት አነጋገር (እጅግ የመጠቀ ነጻ አስተያየት) ቢታይ፥ ያ፥ ብዙ ከማይሰማው፥ ብዙ ከማይነገረውም በስተጀርባ አንባቢ በትእግስት እንዲከታተለው ፍንጭ ለመስጠት ያህል ነው።

ይህ መጽሕፍ ተፈጥሮአዊ እድገት በአካላዊነቱ ከፍጥረትና ከዝግመተ ለውጥ (evolution) እንዴት ተለይቶ ይታያል? በማለት አንዳንድ መሠረታዊ ሃይማኖታዊ ጥያቄዎችን በሳይንሳዊ አመለካከት ይተነትናል፤ እንዲሁም ለአንዳንድ መሠረታዊ ሳይንሳዊ ጥያቄዎች ጥንቃቄ የተመላበት ሃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) አስተያየት ይሰነዝራል።

በመቀጠልም ፍጥረታችን እና ስደቶቻችን እንዲሁም ሥልጣኔዎቻችንን በተመለከተ፥ አንዳንድ ሕዝቦች በምድር ዙሪያ የተንከራተቱበትን፥ ሌሎችም ሳይንቀሳቀሱ የቆዩበትን ምክንያት ይገልጻል።

በተለያዩ የጂኦግራፊ ሁኔታዎች ምክንያት፥ በሰዎች መካከል ስነአይምሮአዊ፥ ባህላዊ፥ አካላዊ፥ ወዘተ.. ልዩነቶች ቢፈጠሩም፥ እነኚህን ልዩነቶች ደምስሶ አንድ ወጥ

አስተሳሰብ የሚያመጣ ውስጣዊ መንፈሳዊ ጠባይ፤ ምድራዊ ችግሮችንም ለመቋቋም የሚያስችል እምነት (ሃይማኖት) አለን። ይልቅስ ይህንን የመሰባሰብን ክስተት የሚያባብስ የመንፈሳዊነት እድገታችንን ጉዳይ በበለጠ እናጥናው በማለት ይደመድማል።

*መልካም ምንባብ*

# ምዕራፍ አንድ

## ሳይንስ እና መንፈሳዊነት - መንደርደሪያ

ከመቶ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ፥ እንዲሁም በሌሎች ብዙ አገሮች፥ ዘመናዊው ትምህርት (በተለይም ሳይንስ) እንደ ሰይጣን ትምህርት ይቆጠር ነበር። በአውሮፓም ቢሆን፥ ሳይንስና ሃይማኖት በጠላትነት ይተያዩ ነበር። በዚያን ጊዜ የነበረው፥ እስከ ግድያ የደረሰ ተቃርኖ፥ እስከ አሁን ድረስ ፈጽሞ አልጠፋም። ሆኖም፥ የሰውን ኑሮ ለማቃለል ሳይንስ ያደረገው እርምጃ ለመንፈሳዊው ሕይወታችን ባይጠቅምም፥ ለአካላዊው ሕይወታችን የሚጠቅም መሆኑ ገሃድ እየሆነ ስለመጣ፥ ሳይንስ በብዙሃን ዘንድ ተወዳጅነትን እና አድናቆትን ለማትረፍ በቅቷል።

ሳይንስ በአካላዊ መረጃ የተረጋገጠ እውነት ቢሆንም፥ ከአንጻራዊነት አልተላቀቀም። ነገር ግን፥ የሳይንስን አንጻራዊነት የእውነትንም አንጻራዊነት መመልከት ያቃታቸው አንዳንድ ሰዎች ሳይንሳዊ የሆነውን ሁሉ፥ እንደ ፍጹማዊ እውነት እየተመለከቱ፥ ሳይንስን እንደ እምነት ወስደውታል። አንዳንድ የሃይማኖት ሊቃውንትም በሳይንስ ውስጥ አያሌ ጉድለቶች መኖራቸውን ካለመገንዘብ የተነሳ፥ ሃይማኖትን ወደሳይንስ ለማስጠጋት ሲሉ የራሳቸውን እውነት እየለቀቁ ሲሰነካከሉ ተመልክተናል።

አንዳንድ ሳይንሳዊ እውነቶች እየተጠናከሩ መጥተው፥ ከአንጻራዊነት አልፈው ወደ ፍጹማዊ እውነትነት እየተሸጋገሩ የመጡ ስለሚመስሉ ብዙዎቻችን ወደ ሳይንስ እንሳባለን። ይህ መልካም ነው፤ ግን ብዙ ፍጹማዊ የሚመስሉ እውነቶች፥ ከፊትለፊታቸው የተሻለ እውነት ሲጋረጥባቸው፥ እነርሱም ከአንፃራዊነት አያመልጡም። በእርግጥ በሳይንስ ውስጥ ብዙ የጎሉ እውነቶች በመኖራቸው፥ ሰዎችም እነኚህን እውነቶች ተምረው ስላወቁ፥ ብዙዎቻችንን እውነት አቀራርቦናል። በአንጻሩ፥ ሰዎች በሳይንስ አንድ አይነት አስተሳሰብ የሚኖራቸውን ያህል በሃይማኖትም አንድ አይነት አስተሳሰብ ሊኖራቸው አልተቻለም።

ሳይንስ እውነትን ከአካላዊው አለም አውጥቶ በእጅ የሚያስጨብጥ፥ በአይን የሚያሳይ ሲሆን፥ ሃይማኖት ግን እውነትን አካላዊ ካልሆነው አለም አውጥቶ በአይምሮ የሚሰርጽ፥ በአይነ ልቦና የሚያሳይ ነው። እነኚህ በሳይንስና በሃይማኖት

መካከል ያሉ መሠረታዊ ልዩነቶች ናቸው። ሰዎችም ከነኚህ መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ፥ የአስተሳሰብ ዝንባሌዎቻቸው ካንዱ ወደሌላው እየሄዱባቸው ከፉኛ ይቸገራሉ። እንዳውም እንዳንድ ጊዜ፥ አንዳንድ ግለሰቦች ሃይማኖትን ሲዘልፉ፥ ሳይንሱን ያመጡና ይገረግዱበታል። ለምሳሌ፥ “ማርያም ድንግል ናት፥ ..ክርስቶስ በተዘጋ በር አልፎ ገባ....አገሊት ጸበል ጠጥታ ከበሽታዋ ተፈወሰች፥..ወዘተ...” ሲባል፥ በሳይንስ የማይቻለውን፥ በእምነትም እንደማይቻል ቆጥረው፥ “እንዴ ይኸማ ሊሆን አይችልም፥” ይላሉ።

ሆኖም፥ ልዩነት የሚኖረው ገና ከመነሻቸው መሆኑ ከታወቀ፥ ሁለቱንም እንደየግል‌ጋሎታቸው እየመዘኑ መጠቀም እንደሚቻል ማገናዘብ አያቅትም።

የሰው የኑሮ እድገቱ በአካላዊነቱ እንዲሁም በመንፈሳዊነቱ ስለሆነ፥ በሁለቱም አቅጣጫ ታላቅ የእድገት እመርታ ታይቷል። የሚሠራው ተሠርቷል፤ የሚታሰበውም ታስቧል፥ የሚታመነውም ታምኗል። የቀረ ምንም የለም ለማለት ባይሆንም፥ “ከዚህ የሚከተለው ምንድነው?” ብለን መጠየቃችን አይቀርምና፤ ለዚህ ነው ብዙ ማወቅን የምንሻ።

ሰው በሥጋው ቢደላውም፥ መንፈሳዊነቱን የሚያረካለት “ነገር” ካላገኘ ሕይወቱ የተሟላ አይሆንለትም። በሳይንስ መራቀቅ ከመንፈሳዊነት ጋር አብሮ ካልሆነ በስተቀር፥ የኋላ ኋላ የሰውን ልጅ ሰይጣናዊ ሥራ እንዲሠራ የሚያደርገው ሁኔታ ሊመጣ ይችላል ተብሎ ይታሰባል (ይፈራል)። ምንድነው መፍትሔው?

ሳይንቲስቶች ስለ ሃይማኖት ቢያውቁ፥ በበለጠ ለሳይንስ ምርምር የሚጠቅማቸው መሆኑን፥ እንዲሁም ሃይማኖተኞች ስለ ሳይንስ ቢያውቁ፥ በበለጠ ለሃይማኖት ምርምር የሚጠቅማቸው መሆኑን፥ አብራርተው ለመግለጽ የደፈሩ ጥቂቶች ናቸው። መጠነኛ የሳይንስ እውቀትና መጠነኛ መንፈሳዊ እውቀት ያላቸው አንዳንድ ግለሰቦች ግን፥ እውነት እውነት ከሆነ፥ ለሰው ሁሉ አንድ ወጥ መሆን አለበት - ሳይንስና ሃይማኖት ቢያንስ በፍልስፍና አንጻር መቀራረብ አለባቸው ይላሉ።

ታላላቅ መንፈሳዊ አባቶችና ታላላቅ ሳይንቲስቶች ግን፥ የሰው አይምሮ በአካላዊውና በመንፈሳዊው አለም መካከል ሲመላለስ፥ መንገዱን አንድ ወጥ ለማድረግ አልሞከሩም፤ የማይዘለቅበትን ነካክቶ ነገር ከማበላሸት ቁጭ ብሎ ማየት ይሻላል ብለው ይሆናል። ሆኖም፥ ቢሳካም ባይሳካም፥ በዚህ አንጻር፥ የደከሙ ሌሎች ብዙዎች ይኖራሉ።

ይህንን ቁስ አካላዊ ባለ ሕይወት (living thing) እና ሕይወት አልባ (non living thing) አለም በጥልቀት ሊረዱ የቻሉት ሙሉ ጊዜአቸውን በምርምር የሚያጠፉ ሳይንቲስቶች ናቸው። እነርሱ ቁስ አካላዊ ስላልሆነውና ስለመንፈሳዊው

አለም ማሰቢያ ጊዜ የላቸውም። የሁለቱን አለማት ግንኙነትና ልዩነት መመራመርም ጊዜ ማጥፋት ነው የሚመስላቸው።

እንዲሁም፥ ከልጅነት እስከ እውቀት፥ ስለ መንፈሳዊው አለም ሲማሩና ሲመራመሩ የኖሩ ታላላቅ መንፈሳውያን፥ ዘመናዊውን ትምህርት ተምረው፥ በሳይንስ ምርምር ብዙ ጊዜ አጥፍተው፥ እንደ ታላላቅ ሳይንቲስቶች ለመቆጠር እድሜ አልፈቀደላቸውም። ስለዚህ፥ በተጠቀሱት አበይት ምክንያቶች እና በሌሎችም ያልተጠቀሱ ምክንያቶች የተነሳ፥ የታላላቅ ሳይንቲስቶችና የታላላቅ መንፈሳውያን አለም እየተራራቀ መጣ።

የሰው ልጅ አዝማሚያው የራሱን ጥፋት የሚያመጣ መሆኑን ከጥንት ጀምሮ መንፈሳውያን እንዳሳሰቡ ነው። ሃይማኖተኞች (አይሁዶች፥ ክርስቲያኖች፥ እስላሞች..ወዘተ.) ሁሉም በበኩላቸው የሰውን ልጅ ከጥፋት የሚያድን፥ እውነትን ግልጥልጥ አድርጎ የሚያሳውቅ "ነቢይ" እንደሚመጣ ያምናሉ። ይህ ለወደፊት ይመጣል ብለው ሰዎች የሚጠባበቁት "ነቢይ" የሰውን በአካላዊነት መቆየት የሚያሰማምር ከሆነ፥ የሳይንስ ጠላት ሊሆን አይችልም፤ የሳይንስ አስፈላጊነት የሚያከትመው ሰውን ከአካላዊነቱ ለይቶ በመንፈሱ ብቻ የሚያስኖረው ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነውና። ይህ የሚሆነው ደግሞ ይህች ምድር ጭራሹኑ ስትጠፋ (ሕይወት ሁሉ ውድም ሲል) ነው። በሁለቱም አቅጣጫ የሩቁን ወደፊት አላወቅነውም። ግን በአሁኑ (በጊዜአችን) ለምን ሳይንስን የመንፈሳዊነታችን ጠላት አደረግነው?

- በሳይንስ የተገኘ ቁስአካላዊ እድገት የሰውን ልጅ ከመንፈሳዊነቱ ስላራቀው ነው?
- ሳይንስ የሚያስተምረው ስለሚታየው አለም ስለሆነና፥ የማይታየውን እንደሌለ ስለሚቆጥረው ነው?
- ሃይማኖት እምነት እንጂ በላቦራቷር የሚፈተን፥ በሥጋዊ አይምሮም ተመርምሮ የሚደረስበት ስላልሆነ፥ ሁለቱ ምንጊዜም የማይጣጣሙ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው?
- የሳይንስና የሃይማኖት መንገድ የተለያየ በመሆኑና፥ የሰውን ልጅ በሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች መምራት ስለማይቻል ነው?
- በእርግጥ ሳይንስና ሃይማኖትን ለማቀራረብ መሞከር የሚታየውን አለም ወደማይታየው፥ የማይታየውንም ወደሚታየው ለማስገባት እንደመሞከር ሊቆጠር ይችላል። ይህ "አካላዊ" የሆነው አይምሮአችን ምድቡ ከሁለት

አለም ላንዱ ብቻ ቢሆን መልካም፤ ግን ወደ ሁለቱም አለም የሚያስገባን እሱ (አይምሮአችን) አይደለም እንዴ?

- ከሁለቱም አለም ተስማምተን እንድንዘልቅ ለማድረግ - ይህ ከሆነ የአይምሮአችን ሥራ፥ እኛ ሳይንስን የበላይ አድርገን ሃይማኖትን የናቅንበት ምክንያቱ ምንድነው?
- ሃይማኖት ሁሉ ስነ አመክንዮ የሚጎድለው ስለሚመስለን ነው?
- የሃይማኖት ስነ አመክንዮ የተለየ ስለሆነና፥ እንጎላችን ሁለት የተለያዩ ስነአመክኖአዊ አስተሳሰቦችን ማስተናገድ ስለሚቸግረው ነው?
- ሳይንስ በየጊዜው የሚታደስ (ዘመናዊ)፥ ሃይማኖት ግን ቢታደስም ከደረቅ እምነት የማይላቀቅ (ጊዜ ያለፈበት) በመሆኑ ነው?
- እኛ እራሳችን የሃይማኖት እውቀት ስለጎደለን ይሆን?
- ሃይማኖት እና ሳይንስ ተቃራኒዎች ስለሆኑ፥ ወደ አንዱ መቅረብ፥ ከሌላው መራቅ ስለሚመስለን ነው?
- ኮሙኒስት የሆነ እግዚአብሔርን መካድ እንደሚኖርበት፥ ሳይንቲስት የሆነም እንደዛው መሆን አለበት?

አዎ! ሁላችንም በተናጠል ስንኖር፥ መንፈሳዊ አንድነትም ስለሚጎድለን፥ የምንኖርበት አካላዊ አለማችን አንዳንዴ ባይተዋር እየሆነችብን፥ የመኖራችን ሕልውና በደንብ የማይታወቅ - አጠራጣሪ ይሆንብናል፤ ለዚህም ይሆናል፥ ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊ ፍልስፍናዎች በኛ አለም ውስጥ የማይዋሃዱት።

በየጊዜው ከምናውቀው እየተነሳን ወደ እምነት ስንገባ፥ እውቀታችን ከማናውቀው ሁሉ ጋር መሆኑን እንዘነጋለን። ለምሳሌ፥ ዳርዊን ሰዎች በፈጣሪያቸው እንዳያምኑ የሚያደርግ ገለጻ አቀነባብሮ ስላስቀመጠ፥ ይህም እንደ ሳይንስ በመቆጠሩ፥ የተቀረውን ሳይንስ ሁሉ የሃይማኖት ጠላት አስመስሎታል። ነገር ግን እውነትን ብቻ ለሚመረምር አይምሮ፥ ሳይንስ የተባለ ሁሉ ፍጹማዊ እውነት አለመሆኑን መገንዘብ አያቅትም። እስቲ ሁሉንም በገዛ አይምሮአችን እንፈትን፤ በሳይንቲስቶች ወይንም በሃይማኖት ሊቃውንት የአስተሳሰብ ተጽንኦ ሳንበገር።

ለምሳሌ፡- በሳይንስ መሬት ከተፈጠረች ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው ጊዜ አራት ነጥብ ተኩል ቢሊዎን ዓመታት ነው ቢባል፥ ይህ ፍጹማዊ እውነት ባይሆንም፥ ወደ ፍጹማዊ እውነት የሚቀርብ እውነት መሆኑን፤ ይህም ከሃይማኖታችን ጋር ምንም ቅራኔ እንደሌለው ማገናዘብ እንደማያዳግት በዚህ መጽሐፍ እናያለን።

በአንጻሩም፥ መሬት ከተፈጠረች ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው ጊዜ ሰባት ሺህ ዓመታት ነው ቢባል፥ ይህ ከፍጹማዊ እውነት የራቀ ስለመሆኑ፥ መጠነኛ የሳይንስ

እውቀት የቀሰመ ሃይማኖተኛ ሊገነዘበው ይችላል። ይህንን ጉዳይ በሃይማኖታዊ ፍልስፍና ለተመለከተውና በእግዚአብሔር ዘለአለማዊነት (አልፋና ኦሜጋ) ለሚያምን ሰው፥ ነገሮችንም በጠባቡ ለማይመለከት፥ ምንም የሳይንስ እውቀት ባይኖረውም እንኳን፥ መሬት ከተፈጠረች ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው ጊዜ ሰባት ሺህ ዓመት ብቻ ነው ብሎ ድርቅ ከማለት ይድናል። እንዳውም፥ ከዚህ ይልቅ፥ ሰው ይህች መሬት ከመፈጠሯ በፊት፥ (ከአራት ነጥብ ተኩል ቢሊዎን ዓመታት በፊት) ተፈጥሯል ብሎ ማሰብ ይቀላል።

ታዲያ፥ በሁሉም አቅጣጫ ጥልቅ እውቀት ባይኖረንም፥ ይህንን እና የመሳሰለውን የስነ አመክንዮ አስተሳሰብ ብንመለከት አይከፋም። የዘመኑ ሰው እውነት ወደሆነው ሁሉ (ወደ ሳይንስም ቢሆን፥ ወደ ሃይማኖትም ቢሆን) ለመቅረብ ያስፈልጋል። መነሻው እውነት ካልሆነ፥ መጨረሻውም እውነት አይሆንምና፤ እውነት መሆኑ ካልተረጋገጠ እምነት ልነሳ የሚል ሰው መጨረሻውም ያልተረጋገጠ ይሆንብኛል ብሎ መጠራጠር አይቀርለትም። የዘመኑም ወጣት ከእናትና አባቱ እምነት (ሃይማኖት) የሚሸሸው በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርምና፤ የዚህም መጽሐፍ አንዱ አላማ፥ አንዳንድ የሃይማኖት ምሁራን፥ ለብዙሐኑ አይምሮ ዘልቆ የማይገባውን እየመዘኑ፥ ቢሰብኩ እንደሚሻል ለመምከር ነው።

ባሁኑ ጊዜ ታላላቅ ሳይንቲስቶችና ፈላስፋዎች አጠቃላይ እውቀቶችን እያገናኙ ያሳድጋሉ፤ ግን በሳይንስ የመራቀቃቸውን ያህል፥ መንፈሳዊ እውቀቶችን በማሳደግ የሚደረስበትን ሥፍራ ማየት አልቻሉም (በአስተሳሰባቸው ከምድራዊነታቸው ለቀው መሄድ አልቻሉም)። ሆኖም፥ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያችን አያሌ የበቁ ሊቃውንት እንዳሏት አይካድም። በሃይማኖት ላይ ጥርጣሬ የሚያበዙት ግን፥ በብዛት ተማርን (አወቅን) ከሚሉት ውስጥ ነው። ግን የሚገርመው፥ የነርሱን ጥርጣሬ የሚያስወግዱላቸው የእውቀት ስጦታዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ተቀምጠዋል።

ዛሬ ከፍተኛ (ጥልቅ) የሚባል እውቀት ሁሉ ለወደፊት ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ መሆኑ ይቀርና የጋርዮሽ ይሆናል፤ አሁንም እየሆነ ነው ያለው። ለዚህም ምክንያቱ፥ በጠፈር ውስጥ የሚከናወነው ሁሉ፥ አካላዊው ከመንፈሳዊው ጋር ሳይነጣጠል አብሮ የሚሄድ በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም (ይህንንም በሰፊው እንመለከታለን)።

ሳይንሳዊ እውቀት እንዲህ ያደገው በውስጡ ምንም መንፈሳዊነት ሳይኖረው እንዳይመስለን። ከሁለት ዘርፎች (ሳይንስና ሃይማኖት) የምናገኛቸው እውቀቶች ናቸው የሰውን ልጅ ወደ አጠቃላይ የጋራ ግንዛቤ እየመሩ ያሉት። ስለዚህ፥ ሳይንስን ከሃይማኖትና ከመንፈሳዊነት ጋር የሚያጣምር ትምህርት ቢኖር፥ ይህ ትምህርት የሰው

ልጅ በመሠረታዊ ጠባዩ (በተፈጥሮው) ሥጋዊና መንፈሳዊ መሆኑን ስለሚያመለክት፥ ደስ የሚል መሆን አለበት። ይህ ነው በእውቀትና በጥበብ መታነጽ ማለት፤ ለሰው ሁሉ የሚበጀው።

ሳይንቲስቶች (በፈጣሪያችን የሚያምኑ፥ የማያምኑትም)፥ በአጠቃላይ ሰማይ - ጠፈር ውስጥ ተፈጥሮ የራሱን ሕግ ተከትሎ ሲንቀሳቀስ፥ በውስጡ ለውጥን የሚያስከትሉ ሌሎች ለውጦች በተለያየ ረድፍ (ኬሚካል፥ ፊዚካል፥ ባዮሎጂካቻል...) እየተካሄደ፥ ይህም እንዲሁ እየቀጠለ እዚህ ደርሰናል በማለት፥ ሃይማኖተኞች የመጀመሪያው ፍጥረት የሚሉትን፥ እነርሱ ወደ ፕላኔቶችና ጨረቃዎች እየተጓዙ ካለመሰልቸት በከፍተኛ ደረጃ ይመራመሩበታል። በጊዜ ውስጥ ወደ ኋላ ተጉዘን፥ ያ የመጀመሪያው ሕይወት  እንዴት እንደተጀመረ እንመራመር ይላሉ።

በፕላኔቶች ወይም ጨረቃዎች ወስጥ፥ አሁን ወይንም ቀደም ሲል በውስጣቸው ሕይወት መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ ብዙ የጠፈር ምርምር ይካሄዳል።  በአንጻሩ የሰብአዊነት አካላዊ ጎኑ እየተጎዳ  ምድር አስጨናቂ ስትሆን፥ ይህ በየጊዜው ለምርምር የሚወጣው ገንዘብ አግባብ አይደለም የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

በኛ መሬት ላይ ሕይወት ተፈጥሮ የተገባደደ ስለሆነ፥ ስለመጀመሪያው ፍጥረት የምናገኘው መረጃ ሁሉ ተደምስሶብናል፤ ነገር ግን በሌሎች የጠፈር አካሎች ውስጥ ለሕይወት መፈጠር አመቺ ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ፥ እና የሕይወትም መኖር ከታየ፥ ይህ የኛ የጠፈር ምርምር፡-

ሀ) ስለ ፍጥረታት ሁሉ መነሻ እንድናወቅ ያስችለናል፤

ለ) ይህንን ካወቅን፥ እኛም ከየት እንደመጣንና ወዴት እንደምንሄድም ያሳውቀናል በማለት፡-

1) በሌሎች የጠፈር አካሎች ውስጥ ለሕይወት መፈጠር አመቺ ሁኔታ (ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ) መኖር/አለመኖሩን ማወቅ፤
2) ከዚሁ ጋር ተያይዞ፥ በሌሎች የጠፈር አለማት፥ ሕዋሳት ቢኖሩና ቅሪተ አካላቸው (fossil) በዝቅጠ አለት sedimentary rock) ውስጥ ተመዝግቦ ቢገኝ፥ ያንን መመርመር፤
3) ከዝቅጠ አለቶቹ ውስጥ በሚገኙ ተለዋዋጭ ንዑስ አካላት (isotopes) በቅድመ ዘመናት ስለነበረው የአየር ሙቀትና የመሳሰሉትን ማጥናት፤
4) ሌሎችም ለኛ ባልተነገሩን ምክንያቶች፥ ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ ምርምር ይካሄዳል።

ለዚችው ለምድራችን የሚጠቅመንን ጥናት እየመሩ ከዚህ ያደረሱን እንደ NASA ያሉ ሳይንሳዊ ድርጅቶች በመኖራቸው ምድራዊ ኑሮአችን ተሻሽሏል። እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ እንድናይለት ስለሚፈልግ፥ የሚያስብ አይምሮ ስለሰጠን ማወቅ የሚገባንን ሁሉ ስናውቅ ቆይተናል። ሳይንስን ለተጨባጭ ማስረጃነቱ፥ ሃይማኖትን ለእምነት፥ ፍልስፍናን ለሕይወታችን የኑሮ መመሪያ እያደረግን ወደፊት እንጓዛለን። ለዚህ ያበቃን አምላክ ይክበር ይመስገን።

ሳይንስ ለምድራዊ እድገታችን ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ በጣም የሚያሳዝነው፥ ሳይንስ ካለ መንፈሳዊነት ለሰውም ለእንስሳትም ሕልውና አይበጅም። እንደገናም፥ ሰውንም ምድሪቱንም የሚያድናት ሳይንስ ነው፣ ይህም ከመንፈሳዊነት ጋር ሲሆን ነው እንጂ ብቻውን አይደለም።

ተፈጥሮ (ሰውም ጭምር) መንፈሳዊነት በሌለው ደረቅ ምድራዊ የሳይንስ እውቀት ላይ የተመሠረተ "ሥልጣኔ" ምክንያት እየተጎዳ ነው። ልክ እንደ ሰው ይህችም ምድር እየታመመች ነው። መንፈሳዊ ጎኗን ባለማየታችን፥ ካለ አግባብ ቦጠቦጥናት። የተፈጥሮአዊ አካባቢዋ ሁሉ ለርሷ በማይስማማ ሁኔታ ተበለሻሸ፤ ከርሰ ሰውነቷም በመርዝ ተበከለ። ይህ ሁሉ የሳይንቲስቶች መንፈሳዊ አለመሆን (እምነት ማጣትም) ያስከተለው ሊሆን ይችላል፤ ካለ መንፈሳዊነት ሳይንስ ጨካኝ - አረመኔ ነውና።

መንፈሳዊነት ርህራሄን ይሰርጻል። ከራሳችን አልፈን ምድሪቱን በርህራሄ ብንመለከታት፥ እርሷ ስትታመም ዝም አንልም። እርሷን በፍቅር መንከባከብ ስንጀምር በጎ ትሆናለች፤ እኛም ቶሎ ከመጥፋት እንድናለን።

እኛ የተፈጠርነው ከተፈጥሮ ጋር ስምም ሆነን እንድንኖር ነው እንጂ፥ እኛ ከተፈጥሮ በላይ ሆነን፥ የፈለግነውን እያደረግን የሌላውን ፍጡር የመኖር መብት ልናሳጣ አይደለም። ተፈጥሮ በታላቅ ትእግስቷ የምታስተምረን ካልገባን፥ እራሳችንን ነው የምንጎዳው።

ሃብትን ለማካበት ሲል፥ የአካባቢን ተፈጥሮ ሆን ብሎ የሚጎዳ ድህነትን ለወደፊቱ ትውልድ ያስተላልፋል። እንዲሁም፥ በግለሰቦች ጫንቃ ላይ ኑሮውን የሚያደላድል የራሱን ሕይወት ከሌላው አስበልጧል። በዚህች ምድር ላይ አንዱ ወገን (ግለሰብ) ሌላውን ሳይጎዳ፥ ምድሪቱንም ሳያጨናንቃት በሰላም መኖር ይችላል።

አንዳንዶች (ሳይንቲስቶች፥ ፖለቲከኞች - የአገር መሪዎችና አስተዳዳሪዎች) መንፈሳዊ ባለመሆናቸው ምድራዊ እውቀትን በጠባቡ ወስዱት፤ አርቆ ማሰብ ስለተሳናቸው፥ ለሚሠሩት ሥራ ሁሉ የሚያስከትለውን ውጤት እየመዘኑ፥ ጥቅሙና ጉዳቱን እያወዳደሩ፥ ጎጂውን እያዳከሙ ጠቃሚውን እያጎለበቱ መራመድ

አቃታቸው። ሃይማኖት (መንፈሳዊነትም) ስለሌላቸውም ለገንዘብ፥ ለግል ጥቅምና ለምድራዊ ክብር ሲስገበገቡ፥ ለወደፊቱ ትውልድ አላሰቡለትም።

እንዲሁም እንዳንድ ሳይንቲስቶች የሚደክሙባቸው ሳይንሳዊ ምርምሮችና ጥናቶች፥ ለገንዘብ፥ ለግል ጥቅም፥ ለክብር፥ ለስልጣን እና የፖለቲካ መወጣጫ እንዲያገለግሉ እየተደረጉ፥ ብዙ እውነቶችን ከተራው ሰው ሲደብቁ ተመልክተናል።

በተቃራኒውም፥ በእውነት ለእውነት ብቻ የቆሙ፤ እንጸድቃለን ወይም እንኮነናለን፥ እንበለጽጋለን ወይንም እንደኸያለን ብለው ሳይሆን፥ እውነትን ብቻ ሲፈልጉ የሚደክሙ መንፈሳውያን ሳይንቲስቶች እየበዙ ነው፤ የሰው ልጅ እውቀት ሁሉ የእግዚአብሔር - ከእግዚአብሔር የሚመጣ መሆኑን አውቀዋልና።

“..በልባቸው ጥበበኞች በሆኑት ሁሉ ጥበብን አኖርሁ።” ዘጸ.31፥7

ለወደፊት ሕዝቦች ሁሉ በአንድ ላይ እንዲኖሩ፥ እንዲሠሩ፥ እንዲያስቡም የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል (ተፈጥሯልም)። ለወደፊት በምድር ላይ የጋራ ችግር ሲበዛ፥ ሰዎች ከምንጊዜውም የበለጠ ካልተቀራረቡ በስተቀር፥ የጋራ ችግር በተናጠል የማይቃለል ይሆናል። በየጊዜው እየጨመረ በሚሄደው የሕዝብ ቁጥር ብዛት አንጻር፥ የሚበላ ሲጠፋ፥ የአየር ለውጦችና ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች አካባቢያችንን ለኑሮ አስቸጋሪ ሲያደርጉት፥ በሰው እና ከሰው በመጡ በካዮች (waste) የምድር አየሯ፥ ውሃዋና አፈሯም ሲበከል፥ የሰው ጤንነትና ኢኮኖሚ በምድር የመቆያ ጊዜያችንን ሲያሳጥረው፤ ሁላችንም በአለም አቀፍ ደረጃ በጋራ ማሰብና፥ መሥራት ተገቢያችን (የውዴታ ግዴታችን) መሆኑ ግልጽ ይሆናል።

ሰዎችን ከሞላ ጎደል እርስበርስ ያቀራረባቸው፥ በመጀመሪያ ሃይማኖት፥ ቀጥሎም ሳይንስ ሲሆን፥ የዛሬ ዘመን ሰው ከነኚህ ከሁለቱ ርቆ የትም አይደርስ። ይህ የዘመኑ ሥልጣኔ - ዘመናዊ ኑሮአችን ከዚህ አደረሰን። ግን የተፈጥሮ አደጋ ሲመጣ፥ የሌሊት ወፍ መብራት ሲበራባት ምንም ማድረግ እንደማትችል ሆና ሽምቅቅ እንደምትል እንሆናለን።

በከፍተኛ የስነ ምድር (ጂኦሎጂ) ትምህርት የዘለቁ እጅግ ብዙ ሳይንቲስቶች በሰዎች ላይ ሊደርስ የሚችል ተፈጥሮአዊ ጥቃት ተለይቶ የሚታወቅ መሆኑን ደጋግመው ነግረውናል። ግን፥ በምድር ላይ ስለሚፈጸም አደጋ በቅድሚያ ስለማወቅ ጉዳይ፥ እራሱን ቀና አድርጎ ሰማይ ሰማዩን ከሚያይ ሰው ይልቅ፥ እራሳቸውን ወደ መሬት ደፍተው ምድርን ብቻ እያስተዋሉ የሚኖሩ እንስሳት እንደሚሻሉ ተመልክተናል። እንስሳት ተፈጥሮን ስለሚያዳምጡ ተፈጥሮአዊ አደጋ ከመምጣቱ በፊት ስለሚታወቃቸው የበኩላቸውን እርምጃ ይወስዳሉ። አንዳንድ ጊዜም እኛን ለማዳን ሲሉ በተለያየ መንገድ ይነግሩናል።

መጮህ እንጂ ማዳመጥ የማንወድ እኛ ግን፥ ላለመበለጥ ስንል አንሰማቸውም። ከተፈጥሮ በላይ የሆን እየመሰለን፥ ተፈጥሮን በቁጥጥራችን እናውላለን ብለንም ፎክረናል።

አዬ!..ትእቢት፥ እራስን ወዳድነት እና የሥልጣን ጥም ስላለብን ከእንስሳት በልጠን ተፈጥሮን ማዳመጥ አቃተን። በመንፈሳዊነታችን ጥሩነታችንን ብናጎለብት ኖሮ፥ ከተፈጥሮ የሚመጣውን ድምጽ እያዳመጥን ኑሮአችንን ማሻሻል ባላቃተን ነበር። ሱናሜ (የውቅያኖስ ውሃ ወደ ላይ ከፍ እንዲል የሚያደርግ የመሬት መዛባት በተፈጠረበት ወቅት፥ የባህር ሞገድ መሬትን ሲሸፍን) በሰዎች ላይ ጥቃት ስለማምጣቱ የተነበየ ሳይንቲስት አልነበረም።

ነገር ግን፥ እንስሳት እና፥ የእንስሳትን የጠባያት መለዋወጥ በመከተል፥ አንዳንድ ነገዶች ወደ ከፍተኛ ሥፍራ አስቀድመው ስለሸሹ ራሳቸውን አድነዋል። ሱናሜ እና ተመሳሳይ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ የምድር እንቅስቃሴዎች ምንጊዜም እንደሚኖሩ አውቀናል፤ ለምንድነው ሳይንስ ከፍ ብሎ የማይሻገርና ከጥፋት በፊት ሰዎችን አስጠንቅቆ የማያድን።

የዘመኑ ሳይንቲስቶች ከሄኖክና ከኖህ የበለጠ ለሰው ልጅ ጠቅመውታል? ሄኖክ "ስለ ሰማይ መስኮቶች (Atmospheric windows) እና የመሳሰሉት፥ አንዳንድ ሳይንሳዊ ጥንስሶችን ቢጠቁመን፥ ዋናው ትምህርቱ፥ "ከሁሉ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን ጽድቁን እሹ፤ ኃጢአት አትሥሩ" ነው..።

በኖህ በኩልም ለትውልድ ትውልድ የተላለፈ ምድራዊ ሥልጣኔ ይኖራል (በምዕራፍ ዘጠኝ እንደተገለጸው)። ሆኖም፥ ዋናው ከኖህ የምንማረው ዋነኛ ትምህርት፥ ኃጢአት አለመሥራት፥ እግዚአብሔርን መፍራት፥ ምስጋና እና ስለ የድኅነት ተስፋን ነው።

የሚያሳዝነው፥ በመንፈሳዊነታቸው - ግብረገብነታቸውና ሞራላቸው እጅግ ዝቅ ያሉ ሳይንቲስቶች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ ነው። የመማራቸውንና የማወቃቸውን ያህል፥ ሰብአዊ ትህትና የጎደላቸው፥ በምድራዊነታቸው ተጠምደው፥ ለገንዘብና ለምድራዊ ክብር የሚስገበገቡ ሳይንቲስቶች ብዙዎች ናቸው።

ሳይንስ ከመንፈሳዊነት ሲማር፥ በሁለት አቅጣጫ ስፋትና ጥልቀት ያገኛል (በምድራዊና በሰማያዊ)። ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ሳይንስን እየቀደመ በመምጣቱም ነው በሳይንስ የሉም የምንላቸውን ነገሮች ሁሉ መኖራቸው የታወቀ።

ለሰው አይምሮ ሃይማኖት ብቻውን አይበቃውም፤ ሳይንስም ብቻውን ሲሆን ወደ ሩቅ የሚወስደው "ነገር" ይጎድልበታል። ለምሳሌ፥ በሳይንስ አለም እጅግ ታዋቂ

የሆነው አይሳክ ኒውተን፥ በሂሳብ ስልት ያን ያህል የመጠቀው አስቀድሞ አንጎሉን በሃይማኖታዊ ፍልስፍና ያሰፋው ስለሆነ ነው ይባላል።

የሃይማኖት እውቀት ሳይንስን በፍልስፍና መልክ እየመራው፥ ብዙ ሳይንቲስቶች በእግዚአብሔር የሚያምኑ እንዳደረጋቸው ሁሉ፥ ሳይንስ ለብቻው የሚያድግበት ዘመን እያከተመ ነው ያለው።

አዎ! የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት፥ አይቶም ለማድነቅ፤ አድንቆም የበለጠ ለማወቅና ለመመራመር፥ በምድር ላይ ያለ ሳይንስ ሁሉ ሃይማኖት የግድ ያስፈልገዋል። እንደገናም የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት፥ አይቶም ለማድነቅና ለማምለክ፥ በምድር ላይ ያለ ሃይማኖት ሁሉ ሳይንስ ያስፈልገዋል።

የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያውቅ የለም። እውቀት የእግዚአብሔር ነው፤ ሳይንቲስቶች በእግዚአብሔር ፊት መሃይማን ናቸው።

በነጻነት ማሰብ እውቀትን ያስጨብጣል። አንዱ ያወቀውን ማንም ሰው ሊያውቅ ይችላል። ፍልስፍና ወሰን ድንበር የለውም። ሳይንስ ካለ ፍልስፍና ይጠባል፤ በሃይማኖታዊ ፍልስፍና ሳይንስ ሰብአዊ መልክ ያወጣል፤ ለሃይማኖት (ለእምነት) ማጠናከሪያም ሊውል ይችላል። እና፥ የዚህ መጽሐፍ መነሻውና ተስፋው፥ የሰው ልጅ በፍጥረቱ የተሰጠውን ወሰን ድንበር የሌለበትን አይምሮውን፥ ለሳይንስም ለሃይማኖትም ክፍተት እየሰጠ ቢሆን፥ ለወደፊቱ ሕዝቦችን ሁሉ በማቀራረብ፥ አለም አቀፋዊ አንድነትን የሚሰርጽ አስተሳሰብ (ርዕዮት) ይገኝ ይሆናል የሚል ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ጠፈር

“ምስክሮችህ[1] ድንቆች ናቸው፤

ስለዚህ ነፍሴ ፈለገቻቸው።” መዝ. 118፥ 129

በሳይንስም ቢሆን በሃይማኖት የሰው ችሎታው የተገታ ስለሆነ፥ እንደ ውሱን ተፈጥሮአችን - እንደየንቃተ ሕሊናችን የምንፈልገውን እያደረግን እንኖር ዘንድ በነጻነት ተለቀናልና፤ ሰማይንና ምድርን - የሚታየውንና የማይታየውንም በፈጠረ፥ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምነን፥ ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጹምና ኃያል መሆኑን ለመግለጽ በሚያስችለን መንገድ ሁሉ (በሳይንስም፥ በሃይማኖትም፥ በፍልስፍናም..) ስለ ጠፈር የሰበሰብነውን አጠቃላይ ግንዛቤ አብረን ለመግለጽ እንነሳ።

ባለ አይምሮ ሆነን ስለተፈጠርን፥ እራሳችንን እና በዙሪያችን ያለውን ሁሉ እየመረመርን፥ እኛ ማን ነን (ሰው ማለት ምንድነው?)፥ ከየት መጣን (ፈጣሪያችን ማነው?)፥ ምድሪቱ፥ ጨረቃ፥ ጸሐይና ከዋክብት ከየት መጡ? መጨረሻችን ምንድነው (ከየት ተነስተን ወዴት?) እያልን እራሳችንን ስንጠይቅ ቆይተናል።

በዙሪያችን ስለሚገኝ አካል ሁሉ፥ ስለ መኖሪያ ምድራችን፥ ስለኛም አፈጣጠር በከፍተኛ ደረጃ የምናደርገው ምርምር፥ ጠፈር እንዴት ተጀመረ (ተፈጠረ) ወደሚለው ጥያቄ ያመራናል። በዚህም ስለማያበቃ፦ ለመሆኑ ከጠፈር በፊትስ ምን ነበረ? ማለታችንም አይቀርም።

አንዱ ያገኘውን መረጃ ሌላው ስለማያገኘው፥ እና በሌሎችም ጥቃቅን ምክንያቶች፥ በሳይንቲስቶች መካከል ምንጊዜም በሃሳብ መከፋፈል አይቀርም። ሆኖም ስለጠፈር ምርምር ይህ ነው ልክ፤ ይህ ልክ አይደለም እያሉ ጸጉር ስንጠቃ ውስጥ ከመግባት ይልቅ፥ እስካሁን የተደረሰበትን በፍልስፍናዊ አመለካከት መገምገም ይበልጣል። ያልተማርነውና የማናውቀው ሁሉ ምሥጢራዊ ሆኖ እንዳይቆይብን፥

---

[1] የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ የሚያንጸባርቁ (የሚያበስሩ)፥ ሕይወት ያላቸው፥ የሌላቸውም፥ በሚታየውም፥ በማይታየውም አለም ያሉት ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ምስክሮች ናቸው።

አንዳንድ ለሁላችንም በጋራ ግንዛቤአችን ክልል ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን ሳይንሳዊ ሃሳቦች በትእግስት እየተማርንና እየተመራመርን አብረን እናዝግም።

ስለ ጠፈር ከልዩ ልዩ ጽሑፎች (ድረ ገጾችም) የምናጠናቅረው መረጃ ሁሉ በቂ እውቀት ቢጎድለውም፥ በቀጥተኛ ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰብ የሚመራ ከሆነ፥ አዝማሚያው ወደ እውነት የሚጠጋ መሆኑ ይታወቃል፤ ካልታወቀም ወደጎን ይቀመጣል (ወይም ይጣላል)።

እንደ ታዋቂ ሳይንቲስቶች መረጃዎችን አቅርበን ለማሳመን ባለመቻላችን ሳናፍር፥ ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድናደንቅለት የምናደርገው ጥረት፥ መንፈሳዊ እርካታ ስለሚሰጠን እንደፍራለን።

## ብርሃን

ጨለማን ጨለማ የሚያደርገው እኛ ሰዎች የምናየው (የምናውቀው) ብርሃን አለመኖር ከሆነ፥ ይህ አለም ከመፈጠሩ በፊት በሰማይ የሚኖሩ መላእክት ሁሉ በጨለማ ይኖሩ ነበር ማለት ነው። ግን፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን ብርሃን ይሁን ከማለቱ በፊት፥ እግዚአብሔርና መላእክት ሁሉ የሚኖሩት ምንጊዜም "በብርሃን" ውስጥ ቢሆን የዚህን ብርሃን ጠባይ ልናውቅ አንችልም ማለት ነው። ብርሃን ሲባል ከአካል (ከከዋክብት) የሚመጣ ብቻ ላይሆን ይችላል። ከተለያዩ ከዋክብት ወደመሬት የሚደርሱትም የብርሃን ሞገዶች፥ ሁሉም በሳይንሳዊ መሳሪያዎች ካልሆነ በስተቀር በአይን ብቻ ተለይተው አይታወቁም።

ከማንኛውም ነዳጅ ነገር የሚፈነጠቅ ጨረር ሁሉ ብርሃን ይባላል። ብርሃን ሁሉ የሞገድ ጠባይ አለው (የቁስ አካልነትም ጠባይ አለው)። የብርሃን ሞገድ ከትንሹ የጋማ ጨረር ይነሳና፥ ወደ ኤክስ ጨረር፥ ቀጥሎም ወደ አልትራ ቫዮሌት ጨረር፥ ብሎም ለአይናችን ወደ ተለመደው ወደ ጸሐይ ጨረር (visible light) ይደርሳል። የብርሃን ሞገድ ትልቅነት እየጨመረ ሲሄድ፥ ወደ ኢንፍራ ሬድ ጨረር፥ ብሎም ወደ ሬዲዎ ጨረር ይገባል። ይህንን በአልትራ ቫዮሌትና በኢንፍራ ሬድ መካከል ያለውን የብርሃን ክፍል ነው አይናችን የለመደው። ከማንኛውም ሙቀት የሚፈልቀውን የኢንፍራ ሬድ ሞገድ እንኳን በደረቅ አይናችን አናየውም።

ይህ እኛ የምናየው ብርሃን መኖሩን የምናውቀው ጸሓይና የመሳሰሉት በአካል ላይ የሚያንጸባርቁትን ጨረሮች በአንጎላችን በመተርጎም ነው። ጨረር በአካል ላይ ካላረፈ በስተቀር የምናየው ነገር አይኖርም። ታዲያ ያ እኛ የለመድነው የብርሃን ጨረር ከሌለ፥ አካልም ከሌለ፥ ሁሉ ነገር ጨለማ ሆነ ማለት ነው (ለኛ)። ይህም ማለት፥ በአካላዊው አለም ውስጥ የሚገኝ የብርሃን ዓይነት (ከጋማ ጨረር እስከ ሬዲዎ ጨረር

ድረስ) ብዛት ቢኖረውም፥ ከውስጡ የጸሐይ ብርሃን ቢቀነስለት፥ ብርሃን እያለ ጨለማ ሆነ ማለት ነው (ለኛ)።

ጠፈር ተዘርግቶ፥ ፍጥረተ አካላት በአንድ ወቅት ውስጥ ተፈጠሩ ብለን ይህንን እንደ ፍጥረት የመጀመሪያው ቀን አድርገን መውሰድ እኛን ከምናውቀው ብርሃን ጋር ያዛምደናል። ታዲያ፥ ከዋክብት የተፈጠሩበት ወቅት ከብርሃን መፈጠር ጋር የሚዛመድ ከሆነ፥ እኛም የሚገባን ከብርሃን ጋር የተያያዘውን ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እኛ በሚገባን ቋንቋ ያስተምረናል።

የጠፈር ብርሃን የሚገኘው የሂሊየም ከሃይድሮጂን መገንባት ከሆነ፥ ከዛ በፊት እኛ የምናውቀው ብርሃን አልነበረም ማለት ነው። "እግዚአብሔርም ብርሃንና ጨለማን ለየ። እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው። ማታም ሆነ፤ ጧትም ሆነ፤ አንድ ቀን።" ዘፍ. ፲" 4-5 ሲል፥ ከዋክብት የተፈጠሩበት ወቅትና ብርሃን በጠፈር የታየበት ወቅት ስለማይነጣጠል ያንን አንድ ቀን፥ የመጀመሪያው ቀን በማለት "ማታም ሆነ ጧትም ሆነ፥ አንድ ቀን።" በማለት ይህ እንዲገባን፤ እንድናወቅም ተነገረን።

እኛ በአይናችን የምናየው ብርሃን የአይኖቻችን ብሌኖች ከሚችሉት በላይ ቢሆንባቸው፥ (ለምሳሌ፡- ጸሐይ በድንገት የብርሃኗ መጠን አንድ ሚሊዮን ጊዜ ከፍ ቢል) ይበላሻሉ (ይጠፋሉ)[2]።

የሰው የአይኑ የማየት ችሎታ አንድ ሺህ ጊዜ ከፍ ቢል፥ የጸሐይና ከሌሎች ከዋክብትም የሚነሱ ብርሃኖች ብርሃንነታቸው የዛኑ ያህል ቢጨምር፥ የአይምሮአችን ሰሌዳም እንዲሁ ብርሃንን የመቀበል ችሎታው አንድ ሺህ ጊዜ ከፍ ቢል፥ የአይምሮአችንም ሴሎች (ሕዋሶች) የተቀበሉትን ብርሃኖች ሁሉ የመተርጎም ችሎታቸው በዛው መጠን ቢጨምር፥ የምናያቸውም ነገሮችም ብዛታቸው የዛኑ ያህል ይጨምሩ ይሆናል።

ከብርሃኖች ሁሉ መካከል በኛ የአይን ብሌን ውስጥ ገብቶ በአምሮአችን ሰሌዳ ሊተረጎም የሚችለውን ብቻ ስላወቅነው፥ ለኛ የብርሃን ትርጉም ይኸው ከሆነ፥ ከዚህ ብርሃን ውጪ የተቀረው ጨለማ ነው ለኛ። እና፥ አሁንም የኛ አስተሳሰባችን ከአካላዊነት አንጻር ስለሆነ ሊገባን የሚችለው ነው ቶሎ የሚገባን።

---

[2] "ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ፥ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ፤ ...ሳዖልም ከምድር ተነሳ፤ ዓይኖቹም በተከፈቱ ጊዜ ምንም አላየም፤ እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አስገቡት።" የሐዋ. ሥራ 9:3-9

ለመሆኑ አካላዊ ላልሆነ ሰማያዊ ሕያው ጨለማና ብርሃን ምን ትርጉም ይኖረዋል? እኛ ጨለማ በምንለው ጨለማ የማይበገር የመላእክት ሕልውና ምን አይነት ነው? ይልቅስ አካላዊ ያልሆኑ የመላእክትን ሕልውና እኛ በምናገናዝበው ሁሉ እየገመትን እንዳናስቀምጠው - የሰማያዊው አለም እንደኛ የምድር ብርሃን አይነት እንዳይመስለን - የሰውና የመላእክት አመለካከት የተለያየ ሊሆን ይችላልና[3]።

የብርሃንን ብርሃንነት ብቻ ሳይሆን የኛንም የማየት ችሎታ (በአይን ብርሃን በማየት ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብም ጭምር) መጠኑን እና ይዘቱን ከሰማይ ያለው አባታችን ስለሚያውቅ፥ ሁሉን ነገር ለራሳችን ግንዛቤ አመቻችቶ ሰጥቶናል።

## ፍጥረተ አካል - ከ"ታላቁ ፍንዳታ" በመነሳት

አንዳንድ ሳይንቲስቶች ጠፈር መጀመሪያና መጨረሻ እንደሌለው፥ ጊዜም መጀመሪያ እንደሌለው አድርገው ይወስዱታል። በተቃራኒ፥ የታላቁ ፍንዳታ (the Big Bang) ንድፈ ሃሳብ፥ ጠፈር ከአንድ ሥፍራ በአንድ የተወሰነ ጊዜ ተነስቶ ነው ከዚህ የደረሰው የሚል ነው።

በዘመኑ የሳይንስ ምርምር ዘይቤ መሠረት፥ የተፈጥሮን ሕግጋት የሰው ልጅ ሊገባው በሚችል የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ የግድ ማስገባት (ተፈጥሮን ማቃለል) የተለመደ ነው። ዘመኑ በፈጠረው የኮምፑተር መሳሪያ በመጠቀምና ተፈጥሮን በማቃለል - እጅግ በማሳነስ እና በተለያዩ የማገናዘቢያ ምስሎች (simulation) ውስጥ በማካተት፥ የተለያዩ ጥናቶች ይካሄዳሉ። ለምሳሌ ስለ ጠፈር መዘርጋት ተመራምሮ አንድ ውጤት ላይ ለመድረስ፡- ይህ ዛሬ በጠፈር የሚታየው አካል ሁሉ በታላቁ ፍንዳታ ከአንድ ነጥብ ተነስቶ (ፈንድቶ፥ ተበትኖ - ተዘርግቶ፥ በየጊዜው እየሰፋ) ከዚህ ደረሰ ቢባል፥ ይህንን ጽንሰ ሃሳብ በማገናዘቢያ ምስል (በሂሳብ ስልቶች) ለማብራራት ይቀላል።

በሳይንቲስቱ አልበርት አይነስታይን መላ ምት መሠረት፥ ኃይል ወደ አካል፥ አካልም ወደ ኃይል ይለወጣል። ይህንን የአይነስታይን መላ ምት መነሻ በማድረግ፥ አካላዊው ጠፈር ከ12 እስከ 15 ቢሊዎን ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ፥ በታላቁ ፍንዳታ (the Big Bang) ተጀመረ በማለትና ከዚህም በመነሳት፥ አያሌ ሳይንሳዊ ምርምሮች ተካሂደዋል።

---

[3] "ጨለማ ባንተ ዘንድ አይጨልምም፥ ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለች፤... መዝ. 139፡12 ... "ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይኖርም፤ የመብራት ብርሃን፥ ወይም የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤እግዚአብሔር ያበራላቸዋልና.." ዮሐ. ራዕ. 22:5

በታላቁ ፍንዳታ ንድፈ ሃሳብ መሠረት፥ እፍጋታው (density) ወደ ዘለአለማዊነት የሚጠጋ "ነገር - ኃይል..." ነበረ። ይህ "ነገር - ኃይል.." በ"ባዶነት" (vacuum) የተከበበ፤ ዙሪያውም እጅግ ቀዝቃዛ ነበር። ከታላቁ ፍንዳታ በፊት በዚህ "ነገር - ኃይል.." ውስጥ የታመቀው ሙቀት ዘለአለማዊ (ከግምት በላይ) ነበር። በውስጡም፥ በተቃራኒ የሚካሄዱ የግፊትና የጉተታ ክስተቶች (ጠባዮች) ነበሩ። ይህ "ነገር - ኃይል.." እነዚህን ቅራኔዎች ይዞ ለዘለአለም መቆየት ስላልቻለ በአንድ የተወሰነ ጊዜ ፈነዳ።

በአካል (matter) ትይዩ የጸረ አካል[4] (anti matter) መኖር ይታወቃል። ወደ ዘለአለማዊነት በሚጠጋው "ነገር - ኃይል.." ውስጥ አካልና ጸረ አካልም ከተቃራኒ ጠባዮቻቸው ጋር ባንድነት ታምቀው ቆይተዋልና፤ ይህ "ነገር - ኃይል.." እነዚህን ቅራኔዎች ይዞ ለዘለአለም መቆየት ስላልቻለም፥ በአንድ የተወሰነ ጊዜ ፈነዳ፤ የዛን ጊዜ ታላቅ ቦግታ ሆነ። ይህ ነው የታላቁ ፍንዳታ ንድፈ ሃሳብ ባጭሩ።

ከፍንዳታው በኋላ ወዲያውኑ፥ ዙሪያውን በከበበው ቅዝቃዜ[5] ምክንያት፥ ሙቀት ቀነስ ሲል፥ አካል - ቁስ አካል (matter) ተፈጠረ። ምናልባት በዚህ ቀነስ ባለ ሙቀት ሊኖሩ የሚችሉ፥ እንደ ኢሌክትሮን እና እንደ ኒውትሪኖ ያሉ፥ እጅግ ጥቃቅን ቁስ አካሎች ብቻ ይሆናሉ። የዚያን ጊዜ ገና ጠፈር አልተዘረጋም (ከዋክብት አልተፈጠሩም)፤ ሁሉም እጅግ ጥቃቅን ቁስ አካሎች ብቻ ያሉበት እንደ ጥምል ጋስ - ጢስ (nebulae) ያለ ነበር።

የታላቁ ፍንዳታ ውጤት፥ ኃይል ወደ ቁስ አካል (matter) እንዲለወጥ አደረገ ስንል፥ ይህ መለወጥ ምን ያህል ጊዜ ፈጀ? ማለትም፥ ከፍንዳታው በኋላ ምን ያህል ቆይቶ ነው አካል የተፈጠረው? የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል።

አካል የተፈጠረው ፍንዳታው ከተፈጸመ ከአንድ ሰኮንድ ባልሞላ ጊዜ ውስጥም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የዛን ጊዜ አካላት የሚባሉት እንደ ጋስ ጢስ የሚቆጠሩ በከፍተኛ ሙቀት ሊቆዩ የሚችሉ ረቂቃን አካላት - ኩአርክ፥ ፎቶን፥ ኢሌክትሮን እና ኒውትሪኖ ይሆናሉ። ከዚህ የምንረዳው አንድ ነገር ከመፈጠሩ በፊት በዛ ነገር ውስጥ የሚገኙ አካላት ሁሉ በቅድሚያ መፈጠር እንዳለባቸው ነው።

---

4 ስለ ጸረ አካላት ተጨማሪ ማብራሪያ ከቃላት ትርጉም ይመለከቷል።

5 ቅዝቃዜ ያጠጋጋል፤ ሙቀት ያራርቃል።

ለምሳሌ፥ በአንድ አተም ውስጥ የሚገኙ ፕሮቶን እና ኒውትሮን እንኳን ገንቢዎቻቸው ኩአርኮች ከተፈጠሩ በኋላ ነው የተፈጠሩት[6]።

ጠፈር የተዘረጋው (ከዋክብት የተፈጠሩት)፥ ከታላቁ ፍንዳታ በኋላ፥ እንደ ጢስ ከነበረው ውስጥ ነው። በጢሱ ውስጥ የነበረ ሙቀት ከአስር ሺህ ሚሊዮን ዲግሪ ሴንቲግሬድ ወደ ሦስት ሺህ ዲግሪ ሴንቲግሬድ አካባቢ ዝቅ ሲል ፕሮቶንና ኒውትሮንም እርስ በርስ ተጠጋግተው አተሞችን መሠረቱ። የዛን ጊዜ ነው ከዋክብት የተፈጠሩት። እስከዛ ድረስ ብዙ ጊዜ ፈጅቶ ሊሆን ይችላል (እስቲፈን ሃውኪንግ 1988)።

## ብርቅነት እና ታላቁ ፍንዳታ

የጠፈር መነሻው ምን ይሆን? መጨረሻውስ ምን ይሆን? እያሉ ብዙ ሳይንቲስቶች እጅግ ተመራምረዋል። በብዙ ሳይንቲስቶች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ንድፈ ሃሳብ፥ የጠፈር መጀመሪያ ከብርቅነት (singularity) ተጀመረ የሚለው ነው። በዚህም ንድፈ ሃሳብ መሠረት፥ ጠፈር እጅግ እየሰፋ ቢሄድም፥ በታላቁ መኮማተር (the big crunch) ተሸማቆ፥ እንደገና ወደ ብርቅነት (ምንምነት - ኢምንትነት - ዜሮነት ወይም ወደ ዜሮ የተጠጋ) ይመለሳል።

አንድ እጅግ ዝቅተኛ ቁጥር በእጅግ ከፍተኛ ቁጥር ቢካፈል ውጤቱ ወደ ዜሮ የሚጠጋ ዝቅተኛ ቁጥር ነው የሚሆነው። ከዝቅተኛም ዝቅተኛ ሆኖ፥ ለዝቅተኛነቱ ገደብ የሌለው ቁጥር ዜሮ (ዜሮነት) ነው። አንድ ቁጥር (ማንኛውም ቁጥር) በዜሮ ቢካፈል፥ ውጤቱ የዜሮ ተቃራኒ - ለትልቅነቱ ወሰን የሌለው (ዘለአለማዊ ቁጥር) ይሆናል። የሂሳብ ስልትም ሆነ ማንኛውም ሳይንሳዊ ምርምር ፍቺ የሚኖረው ከዚህ ዘለአለማዊ ቁጥር ውጪ ሲሆን ብቻ ነው። ይህንን ዘለአለማዊ ቁጥር ከብርቅነት ጋር ብናዛምደው ሳይንቲስቶች ተመራምረው የማይደርሱበት ሆነ ማለት ነው።

የጠፈርን መጀመሪያ ከብርቅነት ንድፈ ሃሳብ ጋር የማዛመድ ጽንሰ ሃሳብ እንዴት ተጠነሰሰ?

እስቲፈን ሃውኪንግ[7]፥ "ጠፈር መጀመሪያ ባይኖረው ኖሮ፥ ጠፈር መጀመሪያ የሌለው ዘለአለማዊ ይባል ነበር። ግን ነው ወይ?" በማለት ሲመራመር እንዲህ ብሏል፤

[6] እኛም በውስጣችን ያሉት ንጥረ ነገሮች ከተፈጠሩ በኋላ ነው የተፈጠርነው።

[7] Stephen Hawking (1988): A Brief History of Time.

"ጠፈር ዘለአለማዊ ሆኖ እዚህ የደረሰን ብንሆን ኖሮ፥ በጠፈር ውስጥ ለዘለአለም የበራ ብርሃን፥ ባሁኑ ወቅት ጠፈርን ሁሉ ብርሃን በብርሃን አድርጎት፥ በቀንም በማታም ብርሃን ብቻ ይሆን ነበር። ጠፈር ዝግ ከሆነ (ብርሃን ሾልኮ ለዘለአለም የሚጠፋበት ሁኔታ ከሌለ)፥ ይህ ለዘለአለም የበራው ብርሃን ከጠፈር ስለማይጠፋ፥ ባሁኑ ጊዜ ጨለማ የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም ነበረ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ጠፈር ሁሉ ብርሃን በብርሃን አይደለም ያለው። ስለዚህ ከዛሬው ብርሃን በፊት ጠፈር "ጨለማ"[8] የነበረበት ጊዜ መኖር አለበት ይልና፥ ጠፈር የግድ መጀመሪያ ይኖረዋል" በማለት ይደመድማል።

የእስቲፈን ሃውኪንግ የብርቅነት አስተሳሰብ የተጠነሰሰው ከኤድዊን ኸብል በኋላና የርሱን አዲስ ግኝት (discovery) በመከተል ነበር። ኤድዊን ኸብል ጠፈር እየሰፋ መሄዱን ያሳወቀ ሳይንቲስት ነው። እስቲፈንም ኤድዊን ኸብልን በመከተል፥ ጠፈር እየሰፋ የሚሄድ ከሆነ ከሚል ስነ አመክንዮ (logic) በመነሳት ነበር የራሱን ፍልስፍና የቀጠለበት።

"ጠፈር የማያድግና የማይለወጥ ቢሆን ኖሮ፥ እዛው ረግቶ ለዘለአለም ይቆያል ማለቱ ይቀል ነበር። ግን ጠፈር ይሰፋል ከተባለ፥ ከመስፋቱ በፊትስ እንዴት ነበር? ብሎ ማሰብን ማን ያግደዋል?" በማለት እስቲፈን ይጠይቅና፥ "እንግዲያውስ ጠፈር እንዲህ ሰፊ (ግዙፍ) ከመሆኑ በፊት፥ እጅግ ጠባብ (ትንሽ) የነበረበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፤ ያ ትንሽነት እንዴት ነበረ? ቢባል፤ ይህ ጥያቄ የትንሽነትን ትንሽነት ወደሚያመለክተው ወደ ብርቅነት (ወደ ዜሮነት የሚጠጋ) ንድፈ ሃሳብ ያመራል" በማለት ይደመድማል።

ፍጥረት የጀመረው ከታላቁ ፍንዳታ በመነሳት ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር "የመጀመሪያ ትእዛዝ" በፊት (ጠፈርን ሂድና ተዘርጋ ሳይለው በፊት) ያ ለፍንዳታው ምክንያት የሆነ - በመጀመሪያ የተፈጠረ "ነገር" - (አካላዊ ያልሆነ?..) የትና በእንዴት አይነት ሁኔታ ይገኝ ነበር? የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል።

ከብርቅነት ንድፈ ሃሳብ በመነሳትና የታላቁ ፍንዳታን ንድፈ ሃሳብ በማስከተል ነው ይህንን ከባድ ጥያቄ ለመመለስ የተቃጣው። ከዚህም ጥያቄ በመነሳት ነው ቀደም ሲል፥ "በታላቁ ፍንዳታ" ንድፈ ሃሳብ መሠረት፥ እፍጋታው (density) ወደ ዘለአለማዊነት የሚጠጋ "ነገር - ኃይል.." ነበረ የተባለው። ይህ "ነገር - ኃይል.." በ"ባዶነት" (vacuum) የተከበበ፤ ዙሪያውም እጅግ ጨለማና እጅግ ቀዝቃዛ ነበር"፥ እያልን ነው የተፈላሰፍነው። ይህንኑ፥ በአንድ ነጥብነት ስብስብ ያለ "ነገር - ኃይል.."፥

[8] ለሰው የሚታወቀውን ጨለማ ለማመልከት።

በጠፈር ውስጥ የሚገኘውን የቁስ አካልን ቅድመ ፍጥረታዊ (ቅድመ መዘርጋት) በሁኔታ ለመግለጽ ሲባል ብርቅነት (singularity) የሚል መጠሪያ ስም ተሰጠው።

በብርቅነት ንድፈ ሃሳብ መሠረት፡- እንዲህ ሰፍቶ የምናየው ጠፈር ሳይዘረጋ በፊት፥ በጉተታ ኃይል ጥብቅብቅ (ጭብጥብጥ) ብሎ፥ በአንድ የተወሰነ ሁኔታ የተገኘበት "ጊዜ" ነበር ከሚለው ሃሳብ ብቻ እንነሳለን።

ይህ ሁኔታ እንዴት ነበር? የጠፈር መነሻው (መጀመሪያው) ከአንድ "የኃይል ክምችት" ከሆነ፥ ምናልባት ይህ "የኃይል ክምችት" ከመፈንዳቱ በፊት በአንድ ላይ ጥብቅብቅ በማለትና በመታመቅ፥ በቅዝቃዜም በመከበብ ላልተወሰነ ጊዜ ቆይቷል፤ በከፍተኛ ቅዝቃዜ የተከበበ ነገር ዝግ[9] ስለሚሆን።

በዙሪያው ያለ ቅዝቃዜ ለምን ሙቀቱን አልሰረቀም ቢባል፥ ራሱን አሳንሶ ወደ ዜሮ ከተጠጋ "ነገር" የሚሰረቅ ሙቀት ላይኖር ይችላል፤ ወይንም እጅጉን ትንሽ ይሆናል። ያ የታመቀው ኃይል ጥብቅብቅ ብሎ፥ በቅዝቃዜም ተከቦ፥ አንድ አይነት "ቅርጽ" ይዞ ቆየ ቢባል፥ ያንን "ነገር - ኃይል" ቦታ የሚይዝ ያስመስለዋል። ሆኖም፥ በብርቅነት (singularity) ንድፈ ሃሳብ መሠረት ያ የመጀመሪያው የታመቀ "ነገር - ኃይል" (ይህ ጠቅላላ የጠፈር አካል ሁሉ) አስቀድሞ ምንም ቦታ ሳይዝ በብርቅነት (ትንሽ ሆኖ) በዘላለማዊ ሙቀት ብቻ ቆይቷል።

እንግዲህስ፥ ከአንድ ነጥብ ብንነሳ፥ በዚህ እንደ ነጥብ ዝቅተኛ (ብርቅነት) ሆኖ በሚታሰብ "ነገር - ኃይል.." ውስጥም ኢሌክተሮ ማግኔቲክ እና የኑክሊያር ኃይሎች በኋላ የሚፈጠሩ አካሎችን "ወክለው" መገኘት ነበረባቸው (እኛ ከምናውቀው የአካል ጠባይ ከተነሳን ማለት ነው)። ቀደም ሲል በገለጽነው፥ በአይንስታይን ንድፈ ሃሳብ መሠረት፥ "ወክለው" ስንል፥ እነርሱ ቁስ አካል አይደሉም፥ እነርሱው በኋላ ወደ ቁስ አካልነት ተለወጡ ማለታችን ነው እንጂ ።

ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

በተጠቀሰው አካልዊ ያልሆነ "ነገር - ኃይል" ውስጥ ሁለት አቢይት ኃይላት ቢገኙ፡- አንደኛው ኃይል ወደፊት የሚፈጠሩትን ደቂቀ አካላት (ኢሌክትሮን፥ ፕሮቶን፥ ኒውትሮን..ወዘተ.) ውጡ ውጡ እያለ የሚገፋ የግፊት ኃይል ሲሆን፥ ሁለተኛውም ኃይል ደግሞ፥ የግፊት ኃይልን በመቃረን፥ እነኚህኑ ወደፊት የሚፈጠሩትን ደቂቀ አካላትን፥ ወደ ውጪ እንዳይፈተለኩ (ተሽቀንጥረው እንዳይወጡ)፥ በአንድነት አስተሳስሮ የሚይዝ ጎታች ኃይል ይሆናል።

[9] ዝግ ነገር ማንኛውንም ነገር (ሙቀትንም) የማያስወጣ፥ ከውጪም የማያስገባ ነው።

የግፊት ኃይል ከሙቀት ይመነጫል። ይህም ሙቀት (እሳት)፥ የመጋፋት ጠባይ ያላቸውን (በኋላ ጋስ ጢስ የሚሆኑትን - የሚተኑትን[10] ንጥረ ነገሮች) በዚሁ የግፊት ኃይል ተሽቀንጥረው እንዲወጡ የሚገፋፋ ነው።

ጎታች ኃይል ከኢሊክተሮ ማግኔት፥ ከኑክሊያር እና ከስበት (gravity) ይመነጫል። የጉተታ ኃይል፥ የሚጋፉትን በመቃረን፥ "በኋላ" ሌሎች ከበድ ከበድ ያሉ ንጥረ ነገሮች የሚሆኑትን (ጋስ - ጢስ ያልሆኑትን[11] - የማይተኑትን) አምቆ ስለሚይዝ፥ እርስ በርስ ጥብቅብቅ ብለው እንዲቆዩ የሚታገል ነው።

በመጀመሪያ ተቃራኒ ኃይላት "ይሁን እና አይሁን" የሚለውን ሃሳብ በማፈራረቅ ይዘው እርስ በርስ ሲፋተጉ፥ አካልም ሳይፈጠር ቆየ። ኃይል በእንዲህ አይነት ሁኔታ በነበረበት ወቅት፥ ውስጠ ጎታች ኃይል፥ ቅዝቃዜ፥ ጨለማም "ያመዘነበት ጊዜ" ስለነበር፥ ያ ኃይል የታመቀ ነበር፤ ዙሪያውን ከከበቡት ከቅዝቃዜና ከጨለማ ውስጥ ራሱን አሳንሶ ቆየ። ያ ኃይል (አካልዊ ያልሆነ?..) የታመቀ ነበር ከማለት በስተቀር፥ እንዲህ አይነት ነበር ማለት አይቻልም፤ እኛ የምናውቀው የአካልን ጠባይ ብቻ ነውና።

ጠፈር ከ"ትንሽ ነገር" በታላቁ ፍንዳታ ተጀመረ ስንል የብርቅነትን ንድፈ ሃሳብ በመከተል ነው። በዚሁ መሠረት ጠፈር ቢሰበሰብም፥ በመጨረሻው መሰብሰብ የሚመጣው የጥብቅብቆሽ ክስተት እንደገና ወደ ብርቅነት (singularity) የሚመልስ ይሆናል ማለት ነው።

በደንብ ካልተገነዘብናቸው ጉዳዮችና ከጥያቄዎቻችን ጋር፥ ስለ ብርቅነት እና ስለ ታላቁ ፍንዳታ ንድፈ ሃሳብ ባጭሩ ካወሳን ዘንድ፥ በተጨባጭ የማይታወቀውን ሁሉ ልክ ነው፤ ሳይንስ ነው ከማለት አስቀድሞ፥ ለሁሉ ነገር ፍልስፍናዊ መሠረት እንደሚኖረው መገንዘብ ያስፈልጋል። ሳይንስ ያን ያህል ርቅቅ ብሎ ተጨባጭ መልስ ለማስገኘት መብቃቱን መጠራጠርም ተገቢ ነው። የብርቅነት እና የታላቁ ፍንዳታ ንድፈ ሃሳብ እውነተኛነት - ሳይንሳዊነት ምን ያህል ነው ብሎ መጠየቅም ያስፈልጋል።

አንድ ሳይንሳዊ መላምት ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት የሚያገኘው፥ በመላምቱ ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ሲያገኙ ነው። የታላቁ ፍንዳታ መላምት በብዙ ሳይንቲስቶች ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝም፥ ጠፈር እንዲህ ሰፊ ሆኖ፥ በውስጡ ያለው አካል ሁሉ በደንብ ሳይታወቅ፥ ወሰኑም ከዚህ እስከዚህ ነው ሳይባል፥ ብዙ

[10] እንደ ሃይድሮጂን ያሉትን።

[11] እንደ ብረትና መዳብ ያሉትን።

የማናውቃቸው ነገሮች እያሉ፥ የጠፈርን መዘርጋት በዚህ በአንድ እጅግ የተቃለለ መላምት ብቻ መወሰን ትክክል አይደለም የሚሉ ሳይንቲስቶች አሉ።

በጠፈር ምርምር የተገኙ ሳይንሳዊ ግንዛቤዎች እጅግ ብዙ ቢሆኑም፥ የጠፈር አጀማመር እንዲህ ነበር ብሎ ለመደምደም የሚያበቃ መረጃ ለመሰብሰብ ብቃትና ጊዜ ያላቸው ሰዎች ከዚህች ምድር ይገኛሉ ብሎ ማሰብ፥ አጉል መመጻደቅ ነው የሚሉም ሳይንቲስቶች አሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ዘገባዎችና ጥያቄዎች ሁሉ እንዳሉ ሆነው፥ የብርቅነትን (singularity) መላምት ሙሉ በሙሉ የሚያከሽፍ ሌላ መላምት አልተገኘም።

ሳይንቲስቶች "ለመሆኑ በባዶ ውስጥ የነበረ "ነገር- ኃይል" ከየት መጣ? ሙቀቱስ እንዴት ተፈጠረ?" ብለው ይጠይቃሉ። ነገር ግን ይህንንስ ጥያቄ ፈጣሪ አምላካችንን ሳያመለክት፥ መልሱን በሌላ መንገድ ማወቅ አልተቻለም።

ያ ጊዜና ከብርቅነት በፊት የነበረው ሁኔታ ዘለአለማዊ ስለሆነ፥ ለሳይንስ ባዳ (ከአቅም በላይ) ነው፤ ቀደም ሲል እንደጠቀስን፥ ዘለአለማዊ በሆነ ቁጥር የሚሰላ የሂሳብ ስልት ሊኖር አይችልምና።

ታዲያ፥ ይህንን በብርቅነት የገለጽነውን "ነገር - ኃይል" እንደ እግዚአብሔር ቃል ቆጥረን ከዛ ብንነሳ ልዩነቱ ምንድነው? በእግዚአብሔር ማመናችን የበለጠ ወደ እውነት ያስጠጋናል እንጂ አያርቀንም።

እንዲሁም፥ ይህንን ጠፈር ወደ ዜሮ ከመመለስ፥ ለምን እጅግ በማሳነስ መሬትን የሚያህል ወይንም ኳስ የሚያህል ተብሎ አልታሰበም?

ምንምነት (ብርቅነት) ቢባል በሃይማኖት ከተማርነው ጋር ይመሳሰላል (እግዚአብሔር ሲፈጥር ከምንም - ይሁን በማለት ብቻ ነውና)። ይህም የሰው ልጅ በሳይንስ ምርምር ወደ እውነት እየተጠጋ - ለወደፊት ሳይንስና ሃይማኖት እየተቀራረቡ እንደሚሄዱም ይጠቁማል (ይሆን?)።

ወደዚሁ ወደኛ ጠፈር ብንመለስ፥ እግዚአብሔር ይህንን እኛ የምናውቀውን ጠፈር ከመዘርጋቱም አስቀድሞ ለዚህ ጠፈር መዘርጋት አመቺ የሆነውን የኃይል ክምችት ፈጥሯል፥ ያም እስኪፈጠር ድረስ በውስጡ የመፈጠር ክስተት እንደሚኖር በሚከተሉት ምዕራፋት ተብራርቷል።

## ጠፈር ከመዘርጋቱ በፊት

ይህ "መጀመሪያ" የተባለ ቃል የዚህን የዛሬውን (ከዛሬ 12 ወይም 15 ቢሊዎን ዓመታት በፊት የተፈጠረውን) ጠፈር የሚያመለክት መሆን አለበት እንጂ፥ ከዚያም በፊት

እግዚአብሔር ብዙ ጠፈሮችን እየፈጠረ (እየዘረጋና እየሰበሰበ)፥ ይህም - እንዲህ ያለው ክስተት ዘለአለማዊ ቢሆን፥ አሁንም እኛ ይህንን ልናውቅ አንችልም። የጥንት አይሁዳውያን ሊቃውንት ግን፥ ሁሉን አወቅን ብለው፥ ክርስቶስን፥ “አንተ በዛች ቅዳሜ እለት ሥራ ሠርተሃል - ሰውን ከሕመሙ አድነሃል” ብለው ከሰሱት (ይህ የሚያስገርም ስለሆነ ከዚህ ተጠቀሰ)።

የዛሬው ጠፈር በሰማይ ላይ ከዋክብት እንደማሽላ ቆሎ የተበተኑበት (መስሎ የሚታይ) ነው። ድሮ (ከብዙ ቢሊዎን ዓመታት በፊት) እንዲህ አልነበረም። ለመሆኑ የቀድሞው (primordial) ጠፈር እንዴት ያለ ነበር? በሚል አርእስት ብዙ የተለያዩ መላምቶች ተሰንዝረዋል።

ካሁኑ ጠፈር በፊት - የቀድሞው ጠፈር እንዲሁ ከጥምል የጋስ - ጢስ የተገነባ ጠፈር (nebulae - constant primordial universe) ተጀመረ የሚል መላ ምት ነበረ (እስካሁንም ድረስ አለ)። በታላቁ ፍንዳታ መላ ምት መሠረትም ጥቅል የጋስ - ጢስ  እንደነበረ አይካድም፤ ከፍንዳታው በኋላ የተፈጠረ መሆኑ ይታመናል እንጂ።

አሁንም ቢሆን ጥምል የጋስ - ጢስ የመሰለ በጠፈር ውስጥ መኖሩ ይታወቃል። ታዲያ፤ ጠፈር የተዘረጋው በታላቁ ፍንዳታ ነው የሚለውን መላመት ከሞላ ጎደል ብንቀበለውም፥ ሌሎች ታላላቅ ፍንዳታዎች ካልተካሄዱ በስተቀር በጠፈር ውስጥ ያሉትን ከዋክብት (ጠቅላላ ቁስ አካላት) ሁሉ በአንድ ታላቅ ፍንዳታ ብቻ ማካተት ነገሮችን ከመጠን በላይ አቅልሎ መመልከት ሊሆን ይችላል በማለትም የተለያዩ ሳይንሳዊ ዘገባዎች ይሰነዘራሉ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ጠፈር ከመዘርጋቱ በፊት ከነበረ፥ በርሱ ፈቃድ አካላዊው አለም (አካላዊ ብርሃን) እንደተፈጠረ ሁሉ፥ ይህ እኛ የምናውቀው ጠፈር ከመዘርጋቱ በፊትም የእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጸመባቸው አያሌ ዘመናት ቢኖሩ እና እግዚአብሔር በፈቃዱ ጠፈራትን እየዘረጋና እየሰበሰበ  ቆይቶ  ቢሆን እኛ አናውቅም። አዎ! እንግዲህ እንዲህ ያለውን አይነት ፍልስፍና ስንቀሰቅስ፥ በተዘዋዋሪ የሳይንስን ደካማ ጎን መግለጽ ሊሆንብን ነው።

የመጀመሪያው (የጥንቱ) ጠፈር በአንድ ፍንዳታ ብቻ አይካተትም፤ ጠፈር አንዴ ብቻ አይደለም የተፈጠረው የምንል ከሆነ፥ ብዙ ጠፈሮች ነበሩ ማለታችን ነው። ይህም በብዙ ሳይንቲስቶች ይደገፋል። ብዙ ጠፈሮች ነበሩ፤ ይኖራሉም የሚሉ ሳይንቲስቶች እየበዙ መጥተዋል። ከታላቁ ፍንዳታ በፊትም ቢሆን፥ ሌሎች እንደ ሰፌድ ያሉ ጠፈሮች ነበሩ፤ ሌላ የማናየው ጠፈር ሊኖርም ይችላል በማለት፤ ሳይንሳዊ መላምቶችና ፍልስፍናዊ አመለካከቶች በየቀኑ ከየአቅጣጫው ይፈልቃሉ።

ዘመናዊ ትምህርት ያልተማሩ - ኤ ቢ ሲ ዲን ያልቆጠሩ - በራሳቸው ፊደል፥ አባቶቻቸው ካቆዩላቸው መጻሕፍት እያነበቡና እየተመራመሩ በመንፈሳዊ ሥልጣኔ የረቀቁ፥ የኢትዮጵያ መነኮሳትና ባህታውያን "ከሁሉ አስቀድሞ አንድ ነገር ነበር ይባላል፤ ይህ ነገር ምን ነበር?" ተብለው ቢጠየቁ፥ "ከሁሉ አስቀድሞ የነበረ፥ ከሁሉ መጀመሪያ፥ ከሁሉ መጨረሻም የሚኖር እግዚአብሔር ብቻ ነው። መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው እግዚአብሔር ነው። አልፋና ኦሜጋ የተባለም እርሱ ነው፤" ይላሉ። "ታዲያ እግዚአብሔር ከኖረ፥ እና ሲኖር፥ በውስጡ ምን ነበረው?" ተብለው ቢጠየቁ" እነርሱም መልሰው፡- "በእግዚአብሔር በውስጡ "ቃል" ነበረ (አለ)፥ መንፈስ ቅዱስም ከርሱ ጋር ነበረ (አለ)" ይሉናል።

ወይ ጉድ! እኛ በሳይንስ እየተንጠራራን የደረስንበት ወደ እውነት የቀረበ እውቀት፥ በግልባጩ ወደ ሌላ ልዩ እውቀት - ወደ እምነትና ሃይማኖት መልሰው ሲነግሩን፥ እነርሱ በውስጣቸው ምንም አይነት ጥርጣሬን ሳያሳዩ እኮ ነው።

አስተሳሰባችን እንደ ሳይንቲስቶችም ሆነ እንደ ሃይማኖተኞች፥ ከአንድ መነሻ መነሳቱ ምንም አይደል። ይህ ከአንድ መነሻ መነሳት፥ በሳይንስም ሆነ በሃይማኖት ለውጥ አያመጣም።

ሁለቱንም ሳንለቅ ለምንጓዝ ሰዎች፥ ዛሬና ለወደፊት ከሚከሰቱ የሳይንስ ግኝቶችና አንጻራዊ እውነቶች ጋር ስንቆይ፥ ከሰፊው እውቀታችን ጋር በውስጣችን ጎዶሎነት (ባዶነት) ከተሰማን፡- "አዎን እርሱ ነው አምላክ - የጠፈር ንጉሥ፥ ካለርሱ ፈቃድ ምንም - ማንም የትም አይደርስ" ብንል፥ ይህ እምነታችን ከሳይንሳችን አያፈናቅለንም። "ማንኛውም ነገር መጀመሪያና መጨረሻ ከሌለው ከእግዚአብሔር ይመነጫል" ብንልም፥ ይህንን እምነታችንን ሳይንስ ችሎ አይጥለውም።

እውነትም ሆነ ውሸት የብርቅነት ንድፈ ሃሳብ ወደሌሎች ጥልቅ ሳይንሳዊ ሃተታዎች ውስጥ ያስገባናል፤ ለእምነታችንም ሳይንሳዊ ድጋፍ የሚሰጥ እንጂ የሚያፈናቅል አይደለም። ያ በውጥረት ላይ የነበረው ነገር (ኃይል?) ፈነዳ ብንል፥ በሃይማኖትም፡- እግዚአብሔር በወሰነው ወቅት፥ የርሱ ፈቃድ ሲሆን - በእግዚአብሔር ቃል ጠፈር ተዘረጋ ቢባል ሁለቱም ያው ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ (ትእዛዝ) እና ፍጥረት አንድ ነው፤ ፍጡር ይታዘዛል፤ ስለተፈጠረም ትእዛዙን ተከትሎ ሥራውን ይቀጥላል። ታዲያ፥ እስካሁን ባየነው መሠረት፡-

- "ሳይንስ የሃይማኖት ጠላት ነው" የሚባለው እምኑ ላይ ነው?
- የኛ ጊዜና "የሌላው አለም" ጊዜ አንድ መቁጠሪያ ከሌለው በቢሊዮን ዓመታት መቁጠሩ ምን ትርጉም ይሰጣል?

- እግዚአብሔር መጀመሪያም መጨረሻም የሌለው ከሆነ፥ ስለምናውቀው ጠፈር ስናወራ፥ የዚህ ጠፈር እድሜው ለእግዚአብሔር ምኑ ነው?
- የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ጊዜም የነበረና ያለ ከሆነ፥ በአንድ በተወሰነ "ወቅት" ጠፈርን ቢዘረጋ፥ ያ "ወቅት ምንድነው"?
- የእግዚአብሔር ፈቃድ የዛን ጊዜ ተጀመረ ማለትስ ምን ትርጉም ይሰጣል?
- "የዛን ጊዜ ተጀመረ" የሚለው አባባል ያስፈልጋል?
- ቢያስፈልግስ፥ እኛ (በምድራዊ ቋንቋችን) ችለን እንገነዘበዋለን? ይህስ ሳይንቲስቶች አይችሉትም ወዳልነው ዘለአለማዊ ቁጥር አይመልሰንም?

ከጥያቄዎቻችን ሁሉ ባሻገር፥ አንድ ጠፈር ከመዘርጋቱ በፊት፥ ወይንም አያሌ ጠፈራት ከመዘርጋታቸው - ከሁሉ በፊት - ሰማይና ምድርን (አካላውያንን ሁሉ) ከመፍጠሩ በፊት - እግዚአብሔር በመንግሥቱ ይኖር ነበረ፤ አለ፤ ይኖራልም፤ እስከዘለአለም በማለት እናምናለን[12]።

አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችም ከዚህ አካላዊ ጠፈር ሌላ የማይታይ ጠፈር እንደነበረ (እንዳለ) ያረጋግጣሉ።

> "እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ፤ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ። ከጥንቱ ከዘለአለም ጀምሮ ተሾምሁ፤ ምድር ከመፈጠሯ አስቀድሞ። ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወለድሁ፤ .. ሰማዮችን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ፤ ...።" ምሳሌ 8፡ 22 - 30
>
> "..ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።" ኤፌ. 1፡4

ጥቅሶቹ፥ ባንድ በኩል ለኛ የሚታየን ካልሆነ በስተቀር፥ ሌላ የለም እንዳንል፤ እንዲሁም፥ ጊዜን ከአካል ጋር እያዛመድን በአይምሮአችን የምንቆጥረው ቀን፥ ወር፥ ዓመት፥ ሁሉም ግልጋሎቱ ለእኛና ለምድራችን ብቻ መሆኑን ይጠቁማሉ።

በጠፈር ውስጥ ከማይነጣጠሉት አካልና ኃይል ሌላ የተለየ ነገር ስለመኖሩ አንዳችም ሳይንሳዊ መረጃ አልተገኘም። አለመገኘቱ የሚያመለክተው አለመኖሩን አይደለም። የማይታይ አለም ስለመኖሩ በሳይንሳዊ መንገድ ባይታወቅም፥ ውስጠ ልቦናችን በልዩና ባልታወቀ መንገድ ይገነዘባል። ባይገነዘብም፥ አለመገኘቱን አያመለክትም።

---

[12] "ከጠፈር በላይ ባለ በመንግሥተ ሰማያት የቅዱሳንን ሥራ ሁሉ ይመረምራል።" ሄኖ. 17፡13

ሰው በአንድ ጎኑ አካላዊ ስለሆነ፥ አብዛኛው እውቀቱ ከአካል የሚመነጭ ቢሆንም፥ ሁለተኛ ጎኑ መንፈሳዊ ስለሆነ፥ የእውቀቱ መነሻና መድረሻው ከመንፈስ ጋር የተያያዘ ይሆናል። በአካል ከአካላዊ ጠፈር የተፈጠርን መሆናችን በደንብ ሲገባን፥ መንፈሳዊ መነሻችንን እና መድረሻችንን በደንብ አላወቅነውም። እንዳው በደፈናው በአካላዊው ጠፈር ትይዩ ሌላ መንፈሳዊ ጠፈር መኖር አለበት ለማለት እየቃጣን፥ ግን በሙሉ አፋችን ይህንን ለመናገር እንፈራለን። አንዳንዶቻችንም ከሳይንስ ተነጥለን፥ ለየት ባለ መንገድ መፈላሰፍ አንደፍርም።

አንድ ጠፈርም ቢሆን - ወይንም ሁለት፥

ሦስትም ቢሆን - እልቆ መሳፍርት፥

ትላንትናም ቢሆን - በቀደሙ ጊዜያት፥

እግዚአብሔር በመንግሥቱ ይኖር ነበር፥

ከዚያም - ከዚያም በፊት።

እግዚአብሔር ጠፈርን ከመዘርጋቱ በፊት አካላዊ ባልሆነ መንግሥቱ ውስጥ ሲኖር፥ ይህንን የርሱን ሥራ እንዲያዩለት፥ በርሱም እንዲያመልኩ መላእክትን (“ፍጽምተ አካላዊ - ሰማያዊ አካላዊ” ሕያዋንን) ፈጠራቸው።

“ከብዙ ቢሊዎን ዓመታት” በኋላ ደግሞ፥ ይህንኑ የእግዚአብሔር ሥራ በምድራዊ አካላዊነት እንድንመለከት፥ ተመልክተንም እንድናደንቅለት፥ አድንቀንም እንድናመልከው፥ እኛን (በአካላዊ ሚችነት እና ሰማያዊ ሕያውነት የተቀናጀን ሰዎችን) እግዚአብሔር ፈጠረን። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናገረ፡-

“ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፤ ..።” ዘጸ. 20፡3 - 6

## ስለ መጀመሪያዎቹ የጠፈር አካላትና ስለ ከዋከብት መፈጠር

ማንኛውም ኃይል ወደ አካል ሊለወጥ ሲል፥ ያ አካል እንዳይፈጠር የሚከላከል ተጻራሪ - አጥፊው - ጻረ አካል (anti matter) ካጠገቡ ነበረበት[13]። የታላቁ ፍንዳታን ንድፈ ሃሳብ የምንከተል ከሆነ፥ የጠፈር አካላት ሁሉ ከታላቁ ፍንዳታ በኋላ ተገኙ ማለታችን ነው። የጠፈር አካላት ሊፈጠሩ ሲሉ እንዳይፈጠሩ የሚከላሉ ጠላቶች ነበረባቸው።

---

[13] ሁለት አንድ አይነት፥ ግን ተቃራኒ የሆኑ ደቂቀ አካላትን ብናጋጫቸው፥ እነርሱ ይጠፋፉና በምትካቸው ፎቶን ይፈጠራል።

ፖዚትሮን (የኢሌክትሮን ጸር)፥ ጸረ ፕሮቶን እና ጸረ ኒውትሮን፥ አካላት ካለ መሆን ወደ መሆን እንዳይገቡ የታገሉ ጸረ አካላት የሆኑ አካላት ናቸው እነርሱም። ከአካል የሚለዩት ተቃራኒ በሆነው ጠባያቸው ብቻ ነው።

የመጀመሪያዎቹ ደቂቀ አካላት ከመጀመሪያው ኃይል ወደ አካልነት ሊለወጡ ሲሉ፥ ከፍተኛ የርስ በርስ መጠፋፋት ተካሂዷል። ዳሩ ግን ከመጠፋፋት ቀጥሎ ጠፈር ተዘረጋ ስንል፥ የተጠቀሱት ረቂቃን ንኡስ አካሎች (ኢሌክትሮን፥ ፕሮቶን እና ኒውትሮን) ካለመኖር ወደ መኖር የሚያዘነብሉበት ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነው።

ከጸረ አካል ይልቅ፥ አካል አሸነፈ አይባልም። ምክንያቱም፥ የአካል መገኘት የትግሉን መኖር እንጂ መሸነፍን እና ማሸነፍን አይገልጽም፤ ይህ አንጻራዊ ነውና። ግን፥ ይህ አንጻራዊ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ለመሆኑ የጸረ አካላት ጠፈር ቢኖርስ - ማን ያውቃል?

ካለ ጸረ አካላውያን ተጻራሪነት፥ አካላውያን የገዛ ሕልውናቸውን አስከብረው የሚኖሩበት ጠፈር ከተዘረጋላቸው፥ አሸነፉ ቢባልም ፥ ያ የነርሱ አለም ለነርሱው ነው። በተቃራኒው፥ ካለ አካላውያን ተጻራሪነት ጸረ አካላዊያን የገዛ ሕልውናቸውን አስከብረው የሚኖሩበት ጠፈር ከተዘረጋላቸው፥ እነርሱ አሸነፉ ቢባልም፥ ያ የነርሱ አለም ለነርሱው ነው።

እኛ የምናውቀውን ጠፈርን የመሠረቱት ጸረ አካላት ቢሆኑ ኖሮ፥ እነርሱ ጸር መባላቸው ይቀርና አካላት የሚለውን ስም ይወስዱ ነበር። እኛም በጸረ አካላት የተገነባን እንሆን ነበር። እንግዲህ ሁለት - የአካላትና የፀረ አካላት አለማት ስለመኖራቸውም ልብ ይሏል። ሆኖም፥ ትግል ምንጊዜም እንደሚኖር እና እነኚህም እኛ ዛሬ የምናውቃቸው አካላውያን በትግል እዚህ እንደደረሱ ከተገነዘብን ይበቃል።

የእርስ በርስ መጠፋፋቱ ውጤት ሌሎች እጅግ ንኡሳን አካሎችን (ኒውትሪኖ፥ ሜዞን...ወዘተ.) ያስከተለ ስለሆነ፥ እስካሁን ድረስ እነኚህ እጅግ ንኡሳን እና እጅግ የደቀቁ አካላት በየጊዜው ከጠፈር ወደ መሬት የሚገቡ መሆናቸውን በኮስሞስ ጨረር (cosmic rays) መለኪያዎች ለማወቅ ተችሏል።

ኒውትሪኖ እና ጸረ ኒውትሪኖ ግን እርስ በርስ ስለማይጠፋፉ፥ ጠፈር ሲዘረጋ የነበሩ ኒውትሪኖዎች አሁን በጠፈራችን (በመሬትም) ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል።

ባሁኑ ወቅት፥ በአለም ዙሪያ ስለ ኒውትሪኖ ምርምር ይደረጋል። በጣም የታወቀውም በፈረንሳይና በስዊስ መካከል ጀኔቫ አጠገብ CERN (Conseil Européen pour la Recherche Nucléaire) የተባለው በአውሮፓውያን አገሮች

የሚመራ የደቂቀ አካላት (particles) መመርመሪያ ጣቢያ ነው።[14] ከዚህ ሥፍራ፥ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ኃይል፥ ደቂቀ አካላትን በማጋጨት ውጠቱን ለማየት ይሞከራል።

ዛሬ የምናያቸው ከዋክብት ከታላቁ ፍንዳታ በኋላ የተፈጠሩ ናቸው ስንል፥ እነርሱን የገነቡ ንጥረ ነገሮች ሁሉ ባንድ ጊዜ ተፈጠሩ ማለታችን አይደለም፤ ሁሉም ጊዜውን ጠብቆ የሚመጣ ነውና። ታዲያ የመጀመሪያው (የጥንቱ) ጠፈር (primordial universe) ዛሬ እንደምናየው ከዋክብት ፈንጠር ፈንጠር ብለው የሚታዩበት እንዳልነበረ መገመት አያቅተንም። ምክንያቱም የጥንቱ ጠፈር እጅግ ሞቃት ስለሚሆን፥ ከጋስ-ጢስ በስተቀር ከበድ ከበድ ያሉ ንጥረ ነገሮች ሊኖሩበት አይችልም።

እኛ ከምናውቀው የከዋክብት ሕልውና በፊት (ከዋክብት ብቅ ብቅ ከማለታቸው በፊት) በመጀመሪያው ጠፈር በነበረ ሙቀት ሊኖር የሚችል ሃይድሮጂን የተባለ ንጥረ ነገር (element) ብቻ ነበር። ስለዚህ፥ በጋስ ጢስ ውስጥ ከሚገኙ ኢሌክትሮኖችና ፕሮቶኖች - ሁለቱ ብቻ በጣምራነት እየሆኑ የመጀመሪያውን ንጥረ ነገር - ሃይድሮጂንን ብቻ ገነቡ።

ከዚያ ቀጥሎ፥ በመለስተኛ ሙቀት ሊኖር የሚችል ሂሊየም የተባለ ንጥረ ነገር ስለሆነ፥ ይህም ከሁለት ጣምራ ሃይድሮጂኖች ተፈጠረ። የሂሊየም ከሃይድሮጂን በየጊዜው መገንባት (ሲገነባ) ነው፥ አሁን እኛ የምናየውን የሙቀትና የብርሃን ኃይል እንዲኖር ያደረገ (በማድረግ ላይ ያለ)።

ከሁለት የሃይድሮጂን አተሞች ቅንጅት ሂሊየም ሲፈጠር፥ ቀሪው የብርሃንና የሙቀት ኃይል (የፎቶኖች መረጨት) ብርሃንን አስገኘ። እኛ የምናውቀው ብርሃን እኛ ከምናውቀው ጨለማ ተለየ። "እግዚአብሔር "ብርሃን ይሁን" አለ፤ ብርሃንም ሆነ" ዘፍ. ፩፡3

በመጀመሪያው የሂሊየም ግንባታ የከዋክብት ሕልውና ተረጋገጠ ማለት ይቻላል፤ መኖራቸውን እኛ የምናገናዝበው በብርሃናቸው ስለሆነ። ከጊዜ በኋላ፥ የጠፈር ሙቀት እጅግ መቀነሱ የማይቀር ነውና፤ ፕሮቶን እና ኒውትሮን እርስ በርስ እየተያያዙ ኢሌክትሮኖችን በዙሪያቸው በመሳብ የአንድ ንጥረ ነገር (element) መሠረት የሆነውን አቶም ደረጃ በደረጃ ይፈጥሩ ጀመር።

ቀደም ብለን እንደገለጽነው፥ የአንድ ንጥረ ነገር (element) ትንሹ ገንቢ የሆነው አቶም የተባለው አካል ከመፈጠሩ አስቀድሞ፥ የዛ የአቶሙ ንኡስ አካሎች (ኢሌክትሮን፥ ኩአርክ...) ከፍንዳታው በኋላ፡- በአንድ ሴኮንድ ፥ ወይም ከዛ በላይ

[14] https://home.cern/about

በፊጀ ጊዜ ተፈጥረው ይሆናል። ከጊዜ በኋላ፥ ሙቀት እየቀነሰ ሲሄድ፥ ደቂቃን አካላት (ኢሌክትሮኖች፥ ፕሮቶኖችና ኒውትሮኖች) የበለጠ መጠጋጋት ጀመሩ።

ከሃይድሮጂን አተሞች ቀጥሎ፥ የኮከብ እድገትና ሙሉ ሰውነት (በአካላዊነት መገኘት) በሌሎች ንጥረ ነገሮች መፈጠር ተካተተ። ከጸረ አካል ተርፈው የቀሩት ኢሌክትሮን፥ ፕሮቶን እና ኒውትሮን በተለያየ የሙቀት ደረጃ ሌሎች ንጥረ ነገሮችን ገነቡ ማለት ነው። አዲስ የተወለደ ኮከብ ግን ከሃይድሮጂን እና ከሂሊየም በስተቀር ሌላ አይኖረውም። ታዲያ ሌሎች ንጥረ ነገሮች ያልናቸው እነማን ናቸው?

የአንድ ኮከብ ማእከላዊ ሥፍራ ከበድ ከበድ ያሉ ንጥረ ነገሮችን (ለምሳሌ፥ ካርቦን፥ ኦክሲጂን እና ሰልፈርን) ያካትታል። እነኚህ ንጥረ ነገሮችና ሌሎችም ከበድ ከበድ ያሉ ንጥረ ነገሮች እንደየጠባያቸው፥ በተለያየ የሙቀት ደረጃ ተፈጠሩ። እንደ ብረት ከበድ ከበድ ያሉ ንጥረ ነገሮች የሚፈጠሩት ግን ምናልባት የአንድ ኮከብ መሞቻው ቀን ሊቃረብ ሲል ይሆናል።

የጋስ - ጢስ ጠባይ ያላቸው ምንጊዜም ወደ ውጪ በመፈትለክ ከማእከላዊው የኮከብ ሥፍራ ይርቃሉ። ስለዚህ፥ ከዋክብት የሚኖራቸው ዋነኞቹ ንጥረ ነገሮች በቅደም ተከተል (ከኮከቡ ዳርቻ ጀምሮ) እንደሚከተለው ነው፡-

ሃይድሮጂን፥ ሂሊየም፥ ካርቦን፥ ኦክሲጂን፥ ሲሊኮን እና ብረት።

ከዋክብት፥ ፕላኔቶች፥ ጨረቃዎች፥ ሌሎችም የጠፈር አካላት (የከዋክብት ሽርፍራፊዎችና ስብርባሪዎች፥ የጠፈር ድንጊያዎችና የጠፈር አቧራዎች ..ወዘተ..) በከፊልም ሆነ በሙሉ በተጠቀሱት ንጥረ ነገሮች ተመሠረቱ።

ሆኖም፥ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት የፈጠረ የሙቀት አንጻራዊ ልዩነት ንጥረ ነገሮችም ሲፈጠሩ የዛኑ ያህል ለየት እንዲሉ በማድረግ ነው። ለምሳሌ፡- በምድራችን (ከቆዳ መሬቷ እስከ ማዕከለ ከረሷ ያለው)፥ ዋነኛው ንጥረ ነገር ብረት (32%)፥ ኦክሲጂን (30%)፥ ሲሊኮን (15%)፥ ማግኔዚየም (13%)፥ ሰልፈር (3%)..ወዘተ..። እንዲሁም በምድራችን የንጥረ ነገሮች አይነትና ብዛት፥ በውቂያኖስ፥ በአየር፥ በሰው እና በእጽዋት ዘንድ የተለያየ ነው የሚሆን።

## የከዋክብት አለም

ጨለምለም ሲል፥ ሰማይ በነጠብጣብ ብርሃኖች የተመላ ሆኖ ይታየናል። ከዋክብት በጠፈር እዛና እዛ ተበትነው፥ ብርሃናቸው የሚደርሰንን ብቻ እናውቃቸዋለን። በነጠብጣቦቹም መካከል አጉልቶ የሚያሳይ መሳሪያ ካልተጠቀሙ የማይታዩ አያሌ ከዋክብት መኖራቸውን እንገነዘባለን።

ጸሐይ ለመሬት ስለቀረበችና ከሌሎች ከዋክብት ግዙፍ መስላ ስለታየችን ጸሐይ ብለን ጠራናት እንጂ፥ በአፈጣጠሯም ሆነ በተግባሯ፥ ከሌሎች ከዋክብት የማትለይ፥ ብርሃኗ ወደ ቢጫነት የሚጠጋ አንዲት መጠነኛ ኮከብ ናት እርሷም።

የጥንት ተመራማሪዎች በግልጽ የሚታዩትን ከዋክብት አቀማመጥ ለማጥናት እንዲያመች ብለው፥ ለሰማዩ የጂኦአግራፊ ካርታ አበፈተውለታል። በሃሳብ የተለያዩ የእንስሳት ቅርጽ በመስጠት፥ የሰሜኑን እና የደቡቡን ሰማይ በሰማንያ ስምንት አምሳለ ከዋክብት (constellation) ከፋፍለውታል። በዚህም መሠረት፥ ጎላ ጎላ ብለው የሚታዩትን ከዋክብት በመስመር በማያያዝ፡- አንበሳው ሌዎ፥ አዳኙ ኦሪዎን፥ በጉ አሪየስ፥ ፍየሉ ካፕሪኮም፥ መንታው ጄሚኒ፥ ፒሰስ አሳው፥ ታውሩስ በሬው፥ ኡርሳ ማጆር ትልቁ ድብ፥ ፖላሪስ ትንሹ ድብ..ወዘተ.... በማለት፥ ስለ ከዋክብት ለሚመራመሩ፥ ለጀማሪዎችም ከዋክብትን ሲያዩ በቀላሉ እንዲለዩአቸው አድርገዋል።

አንዳንድ አምሳለ ከዋክብት (constellation) በሁለቱም (በሰሜንና በደቡብ) ንፍቀ ክበባት (hemispheres) ይታያሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ (ለምሳሌ የሰሜኑ መስቀል) የሚታዩት በሰሜን ንፍቀ ክበብ (northern hemisphere) በሚገኘው ሰማይ ብቻ ነው። ሌሎቹም (ለምሳሌ የደቡቡ ደማቅ መስቀል) በደቡብ ንፍቀ ክበብ (southern hemispheres) በሚገኘው ሰማይ ብቻ ነው የሚታዩት።

ቀደም ሲል የጠቀስናቸው አምሳለ ከዋክብት በአይናችን የሚታዩት ናቸው። እንዲሁም በጨለማ፥ ካለ ምንም ማጉሊያ መሳሪያ፥ ሰማዩን ከአድማስ አድማስ ስንቃኝ፥ በርካታ ከዋክብት ቀረብረብ ባሉበት አካባቢ ሁሉ የብርሃናቸው ውጋጋን ልክ እንደ ተነደፈ ጥጥ ሆኖ ይታያል። ይህም በርዝመቱ ሲታይ ወተት ስለሚመስል፥ መልከ ወተት ጎዳና (milky way) ተብሎ ይጠራል። አጠቃላይ ቅርጹ እንደ ክባዊ ጥምዝ (spiral) ያለ ነው። እኛ ግን በውስጡ ስላለን ይህንን አጠቃላይ ቅርጽ በደንብ ማየት አንችልም።

ኸብል ተብሎ የሚጠራው የጠፈር ቴሌስኮፕ ከተፈለሰፈ በኋላ፥ ጠፈር ምንኛ ሰፊ መሆኑ ታወቀ። በዚህ ቴሌስኮፕ በመጠቀም፥ ኤድዊን ፖወል ኸብል የተባለው የከዋክብት ተመራማሪ፥ ደብዘዝ - ፈንጠር - ፈንጠር ብለው፥ በሩቁ እንደ ነጠላ ከዋክብት በሚመስሉን ውስጥ አያሌ ከዋክብት መኖራቸውን፥ ከከዋክብቱም ጋር ጥምል የጋስ - ጢስ (nabulae) መኖሩን ለመመልከት ቻለ።

ኤድዊን ኸብል (እ.አ.አ. ከ1889 እስከ 1953) የሕግ ጠበቃ ሆኖ ለአንድ ዓመት እንደሠራ፥ ስለ ከዋክብት ከማጥናት የበለጠ ምንም የለም በማለት፥ ሥራውን ጥሎ የከዋክብት ተመራማሪ የሆነ ሳይንቲስት ነው።

ከኤድዊን ኸብል በኋላ ጠፈር ብዙ ቢሊዖን ከዋክብት የሚገኙበት ቅልጥ ያለ የከዋክብት አገር መሆኑ ተረጋገጠ። ቀና ብለን ከምናየው ሰማይ ርቆ እንዲሁ ከዋክብት ባንድ በኩል ሰብጥርጥር (ዘርዘር) ብለው፥ በሌላ በኩል ደግሞ አጅብ ብለው የሚታዩበት የጠፈር ክፍል በጉልህ በቴሌስኮፕ ይታይ ጀመር። በደረቅ አይናችን ደብዘዝ - ፈንጠር ብሎ በሩቁ የሚታይ አንድ ኮከብ ቢኖር፥ ያ አንድ የሚመስለን ኮከብ በቴሌስኮፕ ሲታይ፥ ብዙ ከዋክብትን ያካተተ ስለሆነ፥ እንደ አንድ የከዋክብት አገር ይቆጠራል። ስለዚህ፥ ከዋክብት የተለያዩ ቅርጾችን በመያዝ የምናያቸውን የከዋክብት ክምችት አገረ ከዋክብት (galaxy) ብለን እንጠራቸዋለን።

በጠፈር ውስጥ ወደ መቶ ሺህ ቢሊዖን አካባቢ(?) አገረ ከዋክብት እንዳሉ ይገመታል። እያንዳንዱም አገረ ከዋክብት የዛኑ ያህል(?) ከዋክብት ይኖሩታል። ከአገረ ከዋክብት ውስጥ፥ ፈንጠር - ፈንጠር ብለው የሚያበሩ ታላላቅ ብቸኛ ከዋክብትም አሉ።

አገረ ከዋክብት፥ በውስጣቸው ከሚገኙ ከዋክብት፥ ጥምል የጋስ - ጢስ (nebulae) እና ሌሎችም አካሎቻቸው (ፕላኔቶች፥ ጨረቃዎች፥ ..ወዘተ..) ጋር የተለያየ ቅርጽ (መልክ) ያሳያሉ። በአገረ ከዋክብት ማእከላዊ ሥፍራዎቻቸው ሁሉ የስበት (gravity) ማእከል መኖሩ ተረጋግጧል። ይህ የስበት ማእከል በጠፈሮች ውስጥ ሁሉ ስለሚኖር የአገረ ከዋክብት አጠቃላይ ቅርጻቸው፡- እንደ ክባዊ ጥምዝዝ (spiral)፥ እንደ ነጠላ ጥምዝዝ (barred spiral)፥ እንደ ዘርጋ ያለ ሉል (elliptical) እና እንደ ቅርጸ ቢስ (irregular) ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የኛ ጸሐይና በስበቷ ክልል ውስጥ ያሉ ዘዋሪ የጸሐይ ጭፍሮች (planets) ሁሉ የመልከ ወተት ጎዳና ተብሎ ከሚጠራው ክባዊ ጥምዝዝ ከሆነው - ከኛ አገረ ከዋክብት ከወደ ዳርቻ - ጨለምለም ካለው በኩል ይገኛሉ። በደረቅ አይናችን ወደ ሰማይ በመመልከት በብዛት የምናያቸው ከዋክብት በኛ አገረ ከዋክብት ያሉትን ነው።

ከኛ አገረ ከዋክብት ቀጥሎ (ጎረቤታችን) የሚገኝ፥ አንድሮሜዳ የተባለ ክባዊ ጥምዝዝ (spiral) የሆነ ታላቅ አገረ ከዋክብት አለ። ምንም እንኳን ከኛ አገረ ከዋክብት እጅግ የራቀ ቢሆንም፥ ከትልቅነቱ የተነሳ፥ እንዲሁም ማእከላዊው ሥፍራ በጣም ስለሚያበራ፥ ካለ ቴሌስኮፕ እንኳን፥ ፈንጠር ደመቅ ብሎ ይታያል።

ጠፈር የተለያየ ቅርጽ ባላቸው አገረ ከዋክብት የተመላ ሲሆን፥ አንዱ አገረ ከዋክብት ከሌላው ሲርቅ፥ ሌላውም ወደ ሌላው ሲቀርብ፥ ይህ እንዲህ አይነቱ መራራቅና መቀራረብ የሰማዩን ካርታ አሳመረው።

በጠፈር ውስጥ እጅግ እሩቅ ከሆነ ሥፍራ እጅግ በጣም የሚያበሩ “እንደ ኮከብ” ያሉም አሉ። እነኚህ ኩአዛር (quazar) ይባላሉ። ከነርሱ የሬዲዎ ሞገድ

ስለሚመነጭ የሬዲዎ ከዋከብትም ይባላሉ። ጭራሽ ኮከብ ባለመሆናቸው ነው "እንደ ኮከብ ያሉ" የተባሉት። እስከ ዛሬ ድረስ የጠፈር ተመራማሪዎች፥ ከነኚህ ኮከብ መሳይ ነገሮች የሚመነጭ ኃይል እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ እንጂ፥ በእርግጥ ምን እንደሆኑም አላወቁም።

እንደ ነጠብጣብ ከሚታዩት ከዋከብት ሌላ፥ ወቅቱን እየጠበቀ (ከሁለት መቶ ዓመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ) እጅግ ረጅም ሆኖ በሰማይ የሚታይ፥ ጅራታም ኮከብ ተብሎ የሚጠራው ኮሜት (comet) ነው። ጅራታም ኮከብ ተባለ እንጂ፥ ኮከብ አይደለም - ከአንድ ማዕከላዊ ነጥብ ተነስቶ፥ እንደ ጅራት ከበስተኋላው የከበበው የጠፈር አቧራ፥ በረዶ እና ጋስ - ጢስ ነው። ለኛ የሚታየን ለጸሐይ ሲቀርብ ብቻ ነው።

በቴሌስኮፕ በመመልከትና ፎቶግራፍ በማንሳት ከሚገኙ መረጃዎች ሌላ፥ ስለ ብርሃን አይነት፥ ስለ ሞገዶች.. ወዘተ.. አያሌ የጥናት ምርምሮች ይካሄዳሉ። በከዋከብት መካከል ካሁን በፊት ምንም - ምንም እንደ ሌለበት ባዶ ሥፍራ ተቆጥሮ የነበረው ጠፈር ውስጥ ኤተር የተባለ የጠፈር ጋስ - ጢስ (የብርሃን መተላለፊያ የሆነ - "የጠፈር አየር") እንዳለበት ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ በጠፈር ውስጥ ባዶ የሚመስለው ሥፍራ ሁሉ ፈጽሞ ባዶ አለመሆኑን እና በዚሁ በኤተርና ሌላ እኛ በማናውቃቸው ነገሮች የተመላ መሆኑን እንገነዘባለን።

እንዲሁም በጠፈር አካሎች ከሚገኙት የጨረር ሞገዶች መካከል በተለይ ማይክሮ ዌቭ የተባለው የብርሃን ሞገድ እኛ ካለንበት ሳይሆን፥ ከሌላ ከሩቅ አገረ ከዋከብት የሚመጣ መሆኑን ሞገዱን በሚቀበሉና በሚለኩ ሳይንሳዊ መሳሪያዎች ለማወቅ ተችሏል።

በደማቁ ጠፈር ስለሚታዩት ከዋከብት ተነግሮ አያልቅም (ለተጨማሪ ማብራሪያ በየጊዜው በድረ ገጾች የሚጨመረውን የከዋከብት ዜና ይከታተሏል)።

## ***ዙረት***

ከዋከብትን እርስ በርስ እያሳሳበ ባሉበት ሥፍራ ለማቆየት፥ አነስተኛም ቢሆን የግድ የተወሰነ ስበት ያስፈልጋል። ምንም የሚያግድ ፍትጊያ (friction)[15] በሌለበት ጠፈር ውስጥ፥ ትንሿ ስበት ግዙፉን ኮከብ ታሽከረክረዋለች። ምንም የሚያግድ ነገር ስለሌለ፥ አንዴ መሽከርከር የጀመረ ኮከብ መቆሚያ የለውም። ይህ ነው በጠፈር ውስጥ ሁሉ

---

[15] የእንቅስቃሴ ማነቆ።

ለሚታየው እንመስቃሴ (ዙረት) ምክንያቱ። (ለዚህም ይሆናል የኛም ሕይወት ለውጥ የበዛበት፤ በጠፈር ውስጥ ምንም እንቅስቃሴ ባይኖር ኖሮ፥ ማርጀትና መሞትም አይኖርምና (?)።

አገረ ከዋክብት (በውስጣቸው ካሉት ከዋክብት ጋር) በከፍተኛ ደረጃ ይዞራሉ። ምን አይነት ዙረት ነው? ለመሆኑ ካለ ምንም ንቃተ ሕሊና የሚንቀሳቀስ ነገር ይኖራል?

የጸሐይ ጭፍሮች ሁሉ ጸሐይን ከመሃል አድርገው እንደሚዞሩ ሁሉ፥ ጸሐይም ከነጭፍሮቿ በኛ አገረ ከዋክብት ማእከላዊ ሥፍራ ዙሪያ[16]፥ ርቀቷን ጠብቃ፥ ትዞራለች። በሴኮንድ 240 ኪሎ ሜትር እየተጓዘች፥ አንዱን ክብ ለመጨረስ 220 ሚሊዮን ዓመታት ይፈፈጅባታል። ሌሎችም ከዋክብት እንዲሁ ይዞራሉ (ብዙ አይነት ዙረት አለ!)።

አንድሮሜዳ በሴኮንድ 300 ኪሎሜትር እየተጓዘ፥ የኛን አገረ ከዋክብት በታላቅ ፍጥነት እየተጠጋ ነው ይባላል። በዚሁ ከቀጠለ፥ አንድሮሜዳ እና የኛ አገረ ከዋክብት ከሦስት ቢሊዎን ዓመታት በኋላ ይገናኙና አንድ ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል። አሁን የምናያቸው አገረ ከዋክብትም ከሌሎች አገረ ከዋክብት ጋር እየተጋጩና እየተላተሙ ይሆናል እዚህ የደረሱት።

የዚህ የርስ በርስ መላተም መጨረሻው ምንድነው? በአጠቃላይ የሁሉንም አገረ ከዋክብት ቅርጽ በአንድ አይነት ቅርጽ እንወስነው ቢባል፥ ይህ ቅርጽ እንደ ሰፍነግ (sponge) አይነት ይመስላል (ይሆን?) በዚህ ቅርጽ ውስጥ አንዱ አገረ ከዋክብት ሌላውን ሲዞር፥ ይህ ዙረት ምንኛ ውስብስብ ነው።

## ርቀት እና ስፋት

ምን አይነት መራራቅ - ምን አይነትስ መቀራረብ ነው ያለው በከዋክብት አለም? ይህንን ጉዳይ በሂሳብ አስልቶ በመጠኑ ለማስተዋል፥ በብርሃን ጨረር ፍጥነት - የብርሃን ዓመት (speed of light – light year) መጠቀም ግድ ይላል።

ማንኛውም የብርሃን ጨረር የሚጓዘው በሰኮንድ 300 000 ኪሎ ሜትር ሲሆን፥ በዚሁ ፍጥነት እየተጓዘ፥ የብርሃን ጨረር ከጸሐይ ተነስቶ መሬት ለመድረስ 8 ደቂቃዎች ይፈጅበታል። ይህ የብርሃን ጨረር ፍጥነት ስለ ከዋክብት ለሚመራመሩ ሁሉ የርቀት መለኪያ ሆኗል። በዚሁ የርቀት መለኪያ መሠረት፥ ስለጠፈር ሥፋት እንመራመራለን።

---

[16] ይህ እጅግ ብሩህ የሆነ፥ የአገረ ከዋክብቱ ታላቅ ክባዊ ማእከል ነው።

ለምሳሌ፡- የብርሃን ጨረር ለመሬት በጣም ቅርብ ከተባለችው ኮከብ (አልፋ ሴንቱአሪ) ተነስቶ መሬት ለመድረስ አራት ዓመታት ይፈጅበታል። በአራት ዓመታት ውስጥ ያሉትን ሴኮንዶች፥ በ 300,000 በማባዛት፥ የዚህች ርቀቷ 4 የብርሃን ዓመታት ብቻ የሆነች ኮከብ ከመሬት 37,843,200,000,000 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች ማለት ነው።

ከሌሎች ከዋክብትም፥ እንደየርቀታቸው መጠን፥ የብርሃን ጨረር መሬት ለመድረስ 5፥ 6፥ 7፥ 20፥ 100፥ 1,000፥ 10,000፥ 10,000,000..ወዘተ..የብርሃን ዓመታት ቢፈጅ እነኚህን የብርሃን ዓመታት ከላይ በጠቀስነው የሂሳብ ስልት ወደ ኪሎሜትር ስንቀይራቸው ውጤታቸው በአፍ የማይነገሩ ቁጥሮች ይሆናሉ።

የከዋክብትን ርቀት በብርሃን ዓመት እየለካን፥ ስለ ጠፈር ስፋት ለመገመት የቃጣን እንደሆነ፥ የኛ አገረ ከዋክብት ብቻ፥ ከአንድ ጎን ወደ ሌላው ጎን ብርሃን ለመጓዝ የሚፈጅበት ጊዜ ወደ መቶ ሺህ ዓመታት አካባቢ ይሆናል። ጎረቤታችን ከሆነው አንድሮሜዳ ከተባለው አገረ ከዋክብት የሚመጣው ብርሃን መሬት እስኪደርስ ድረስ አንድ ሚሊዮን ተኩል ዓመታት ይፈጅበታል።

የሌሎች አገረ ከዋክብት ስፋታቸው ተገምቶ፥ በመካከላቸው ያለውም ርቀት ተመኑ ታውቆ፤ ባጠቃላይ የጠፈር ሥፋት ይህ ነው ብሎ የሚናገር፥ ከሰው የተፈጠረ አይኖርም። እንኳን የጠፈርን ውስጣዊ ጠባይ መረዳት ይቅርና ግዙፍነቱን እንኳን መገመት ካቅማችን በላይ እንደሚሆንብን ከተረዳን ይበቃናል። ይህ ሁሉ ከምናየው አካላዊ ጠፈር ነው። ሌላ የማናየው አካላዊ ጠፈርም ሊኖር ይችላል።

## እኛ የምናያቸው ከዋክብትና ከነሱ የምናገኛቸው መረጃዎች

በሌሊት ከቤታችን ወጥተን ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ የምንመለከታቸው ከዋክብት ሁሉ፥ እንዲሁ ብርሃናቸውን ከብዙ ዓመታት በፊት የፈነጠቁ ስለሆነ፥ በአንድ ወቅት ለአይናችን የሚደርሰው ብርሃን ያለፈውን ታሪክ እንጂ የአሁኑን አይገልጽም።

ለምሳሌ፡- ከአንድሮሜዳ የሚመጣው ብርሃን መሬት እስኪደርስ ድረስ አንድ ሚሊዮን ተኩል ዓመታት ቢፈጅበት፥ እኛ ዛሬ የምናየው የዛን ጊዜ (የዛሬ አንድ ሚሊዮን ተኩል ዓመታት) የነበረውን ሁኔታ እንጂ፥ በዛሬው እለት አንድሮ ሜዳ በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ አናውቅም።

ከጥንት (ከዛሬ ብዙ ሺህ ዓመታት ጀምሮ) የጠፈር ተመራማሪዎች ስለ ከዋክብት አቀማመጥ (ስለነ አንበሳው ሌዎ፥ አዳኙ ኦሪዎን፥ በጉ አሪየስ፥ ፍየሉ ካፕሪኮም፥ መንታው ጄሚኦ፥..ወዘተ.) በስዕል ያስቀመጡልን አሁንም እንዳለ ከሆነ፥

ቢያንስ በሺህ ዓመታት ውስጥ ከዋክብት እንዳሉ ናቸው ማለት ነው ብንልም፥ በሺህ ዓመታት ውስጥ ለውጥ አለማየታችን የዛሬውን አያሳውቀንም፤ በቅርበት ከሚገኙት ከዋክብት በስተቀር።

የሚሰበሰቡት መረጃዎች ባንድ በኩል ስለ ጠፈር አንዳንድ እውቀቶችን ይከስታሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ- ብዙ አዳዲስ ሃሳቦችን እና ጥያቀዎችን ያስከትላሉ። ባጠቃላይ ስለጠፈር ጉዳይ ካገኘናቸው መረጃዎች ይልቅ ጥያቄዎቹ አመዝነዋል። በእርግጥ በጊዜ ውስጥ የሚከሰተው አንጻራዊ እውነት ብዛት ያደናግረናል። የትላንት፥ የዛሬና የነገ እውነቶች አንድ ስለማይሆኑ፥ በአንድ እውነት ውስጥ ሌላ እውነት እየተከሰተ፥ የቀድሞው እውነት ተራ ሲሆን የዛሬው "ሲበልጥ" አስተውለናል።

ብዙ የማናውቃቸው ነገሮች መኖራቸውን ማሰላሰሉ አይከፋም። በምናየው ነገር ላይ ብቻ (በብርሃን ሞገድ) እያተኮርን ልናውቅ የምንችለው ይህን ያህል ትንሽ ከሆነ፥ ስለማናየው እንዴት ማወቅ ይቻለናል።

ተፈጥሮ ጭራሽ የማይታወቅና ሊታወቅም የማይችል መሆኑን በአንክሮ ያመለከቱ የጥንት ተፈላሳፊዎች ናቸው። የዛሬዎቹ ደግሞ ተፈጥሮን በትንሹም ቢሆን ማወቅ ይቻላል በሚል አዎንታዊ ጠባያቸው፥ ማወቅ የሚቻለውን ያህል ለማወቅ ይፍጨረጨራሉ።

አዎን! ስለ ከዋክብት ማጥናት ልብን ደስ ያሰኛል፤ በጥልቀት ሲያስቡት አይምሮን ያሰፋል፤ ለዚህ እንጂ እኮ ነው ሰው የተፈጠረው፤ ሰውም ንቃተ ሕሊና እንዲኖረው፤ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲያይ፥ አይቶም እንዲያደንቅ።

## የማያቋርጥ እንቅስቃሴ

በፍጥረት ውስጥ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ አለ፤ ፍጥረት ቀጥ አይልም (አይረጋም)። ከፍጥረት ቀጥሎ (ከፍጥረት ጋር) የማያቋርጡ ተፈጥሮአዊ ክስተት አለ። እያንዳንዱ ፍጡር በራሱ ሕልውና ጸንቶ ሲቆይ - እስኪቆይ ድረስ፥ ሲለወጥ -ጨርሶ እስኪለወጥ ወይንም ከተለወጠ በኋላም ቢሆን በውስጡ የማያቋርጥ ክስተት ይኖራል። ለምሳሌ፡ - ሰው፥ ሸረሪት፥ እንጨት፥ ጠጠር፥ አፈር፥ ወዘተ... ተፈጥሮአዊ ሕግጋትን ተከትሎ የሚሄድ፥ በውስጡ የማያቋርጥ ክስተት አለው። ይህም ክስተት በእግዚአብሔር ሕግና ስነስርአት የሚስተዳደር ሲሆን፥ ይህ ሕግ በጥቂቱ በሰዎች ይታወቃል፤ (ለምሳሌ በፊሲክ፥ በባዮሎጂ፥ በኬሚስትሪ...)። በሰዎች የማይታወቅ ሕግም ይኖራል። ለኛ የማይታወቅ የተፈጥሮ ሕግ የለም ማለት ግን ታላቅ ድፍረት ነው።

ሳይንቲስቶች ከዚህ ከእግዚአብሔር  ሕግና ስነስርአት ጥቂቱን - እጅግ ጥቂቱን እርሱ እግዚአብሔር በሚፈቅደው መጠን እየተረዱ ለኛም እውቀቱን ስላካፈሉን፥ ይኸው ሁላችንም በመጠኑ የሳይንስ እውቀት ተካፋዮች ለመሆን በቅተናል። ተመስገን።

ተፈጥሮ ምንጊዜም ለሰው በሚገባ፥ በአንድ በተወሰነ ሕግ ብቻ አይደለም የሚስተዳደር። ከዚህ ቀጥሎ ይህ ይመጣል ለማለት አለመቻል (unpredictability) እና፥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፥ ለሰው የማይገባ ዝብርቅርቅ ያለ ተፈጥሮአዊ ክስተት (randomness) በተፈጥሮ ውስጥ ይኖራል Stephen Hawking (1988)። እንዲህ ባይሆን ኖሮ እስካሁን ድረስ ይህ ጠፈር ከየት ተጀምሮ ወደየት እንደሚሄድ በሳይንቲስቶች ዘንድ ሙሉ በሙሉ ታዋቂ ይሆን ነበር።

ምንም እንኳን የሳይንስ እድገት እዚህ ደረጃ መድረስ፥ የሁሉ ነገር አቅጣጫና ሂደት ይታወቃል ከሚል እምነት በመነሳት ቢሆንም፥ ስለ አጠቃላይ ጠፈር እና ሕግ እኛ ለማወቅ የምንችለው ሁሉ ውሱን መሆኑን፥ ታላቁ ሳይንቲስት እስቲፈን ሃውኪንግ እንደሚከተለው ጽፏል።

“..We could still emagine that there is a set of laws that determine events completely for some super natural being, who could observe the present state of the universe without disturbing it. However, such models of the universe are not of much interest to us ordinary mortals..” Stephen Hawking (1988), pp.55.

ሲተረጎም፡- “ሁኔታዎችን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠሪያ ሕግጋቶች ይኖራሉ ብለን ብናስብም፤ ይህ የሚጠቅመው አዘጋጅቶ ያስቀመጠውን የጠፈር ሕግ እና የጠፈር  እንቅስቃሴ ሳያዛባ እንዲሁ ለሚመለከት፤ ከተፈጥሮ በላይ ለሆነ ኃይል (እግዚአብሔር) ብቻ ነው እንጂ፥ ለእኛ ለሟቾች አይደለም።”

በአካለ ስንኩልነቱ ምንም መንቀሳቀስ የተሳነው እስቲፈን ሃውኪንግ፡- እኔ ሊገባኝ በማይችለው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት ምን ያደርግልኛል ቢል፥ አቅሙና መጠኑን ስላወቀ ነው። ግን ከመፈላሰፍ የማያቋርጥ በመሆኑ፥ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ እየተገፋ፥ በአይምሮው የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እያደነቀ፤ ስለ ብርቅነት እና የመሳሰሉ ጥልቅ ንድፈ ሃሳቦች እያስተማረ ይኖራል። አንዳንድ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር መኖር ለማወቅ የርሱን ቃል ይጠባበቃሉ። እርሱ ግን ሳይንስ እንጂ ሃይማኖት ትምህርቱ ስላልሆነ፥ እምነት የግል ነው በማለት፥ ስለማያውቀው ነገር ከመናገር ይቆጠባል።

ብዙውን ጊዜ ሳይንሳዊ አመለካከት ያለቸው ሰዎች በደንብ በማስረጃ የማያረጋግጡትን ነገር አይናገሩም፤ ሲጽፉም የራሳቸውን እምነት ደብቀው፥ "በፈጣሪ የሚያምኑ (creationists) እንዲህ ይላሉ" በማለት ነው። ሆኖም እስቲፈን ሃውኪንግ ከልቡ የተሰማውን በድፍረት እንደሚከተለው ጽፏል፡-

"..It would be very difficult to explain why the universe should have begun in just this way, except as the act of God who intended to create beings like us" Stephen Hawking (2005), pp.55.

ሲተረጎም፡- "ከብዙ ሌሎች አማራጮች መካከል ለምንድነው በዚህ አይነት መንገድ ብቻ ጠፈር የተጀመረ፤ እንዳው ከጥንቱም እኛን ለመፍጠር እግዚአብሔር አስቦት ካልሆነ በስተቀር።"

ለአንድ ነገር መፈጠር ምክንያት አስቀድሞ መፈጠር ያለበትን እያስታወስን፥ እኛ ከመፈጠራችን በፊት፥ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ልክ እንደዚህ አስተካክሎ ያስቀመጠው፥ እኛን ለመፍጠር አስቀድሞ ያሰበው መሆን አለበት ያሰኛል። ከዚህ ትንሽ ለየት ቢል እኮ! እኛም ሰዎች ያሁኖቹ ሰዎች አንሆንም ነበር።. እንጃ ምን አይነት ፍጡሮች እንደምንሆን....። እግዚአብሔር አስቀድሞ ያስባል። አስቀድሞ የሚያስብ ጠቢብ ነው። ነገር ካለፈም በኋላም የማይገባው ሞኝ ይባላል።

ወደ ቀድሞ ነገራችን እንመለስና፥ የጠፈር መዘርጋት ማለት የተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መስማትና መከተል ማለት ከሆነ፥ እዚህ ላይ ነው ወደ ትሁት ሳይንስ የምንገባው። እዚህ ላይ ነው ስለማያቋርጠው ተፈጥሮአዊ ክስተት መረዳት የምንጀምረው። ሳይንስ የሚያወሳው ስለ ተፈጥሮአዊ ክስተት እንጂ ስለ ፍጥረት አይደለም (ከሚከተለው ምዕራፍ በኋላ (በምዕራፍ 4 እና 5) የምንመለከተው ስለ ተፈጥሮአዊ ክስተት ይሆናል)።

አንድ ፍጡር በአንድ ወቅት ሲፈጠር፥ ፍጥረት መጀመሩን ለማመልከት ሲባል ፍጥረት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ተብሎ ይነገራል። ይህም እግዚአብሔር ሲፈጥር ባንድ ጊዜ እንጂ፥ ብዙ ጊዜ እንደማይፈጅበት ለማመልከት ሊሆን ይችላል። ጊዜ የሚፈጀው የፍጥረት የማያቋርጥ ሂደት ነው። የእግዚአብሔር ትአዛዝ ጊዜ አይወስድም። የመጀመሪያው መጀመሪያ ሲጀመር፥ ይህ የማይገታ ፍጥረት ሲንደረደር፥ ይህ ነው የእግዚአብሔር ትእዛዝ - ከዳር እስከ ዳር፥ መጨረሻው እስኪጨረስ ድረስ የማይቀየር።

ሰው እንዲሁም ሌሎች እንስሳት ሲፈጠሩ አንዴ ይሆናል ስንልም የተፈጥሮን ሕግ ተከትለው ከሚካሄዱ ጠፈራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ጋር መሆኑን ልብ ይሏል።

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ብቻ ፈጥሮ አላበቃምና፤ በየጊዜው ይፈጥራል[17] ብንልም እኛ የማናውቀውን ሁሉ የሚያካትት ፍጥረት እስከሆነ ድረስ ይህ አባባል ከስህተት ውስጥ ላይጥለን ይችላል።

ክርስቶስ፡- "አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ..።" ማቴ. 5፡ 17 ሲል፥ እግዚአብሔር አንዴ ፈጥሮ አብቅቷልና፥ ካለ "ሌላ" ሥራ እንዲሁ የተቀመጠ እንዳይመስለን ይሆናል።

ሕይወት ያላቸው እንስሳት እራሳቸውን በሚያባዙበት ወቅት እና ካባዙም በኋላ፥ በአካባቢያቸው ከሚያጋጥማቸው ሁኔታ ሁሉ ጋር ስምም ሆነው ለመኖር ሲታገሉ፥ ከትውልድ ትውልድ አንዱ ከሌላው ለየት ያለ ይሆናል። ይህ ከተፈጥሮ ጋር የሚያዛምድ ውስጣዊ ክስተት (mutation) ሌላ የተፈጥሮ ሕግ ይባላል እንጂ፥ ፍጥረት አይባልም። ይህ ከተፈጥሮ ጋር የመዛመድ ክስተት በተፈጥሮ ሕግጋት ውስጥ የሚካተት፤ ከእግዚአብሔር መፍጠር ጋር የተያያዘ የእርሱ ትእዛዝ (ፈቃድ) እንጂ ሌላ አይደለም።

እስካሁን የተነጋገርንበትን ጉዳይ ሁሉ ንጉሡ ዳዊት በሚከተለው (እጅግ ደስ በሚያሰኝ ጥቅስ) አጠቃሎታል።

"አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥

ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው።

እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ትኖራለህ፤

ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤

እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል፤

አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥

ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።

የባሪያዎችህም ልጆች ይኖራሉ፥

ዘራቸውም ለዘለአለም ትጸናለች።" መዝ. 102፡ 25 - መጨረሻ።

ጊዜ የማይለውጠውን ሁሉ፥ የሳይንስ እውቀት እንዲህ እንደዛሬው ባልተስፋፋበት ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት፥ ይህንን ቃል ንጉሥ ዳዊት ሲናገር፥ በእውነትም እርሱ ከሳይንቲስትም በላይ - ነቢይ መሆኑን ያሳያል።

---

[17] ይፈጠራል ስንል፥ ካሁን በፊት ያልተፈጠሩትን እና በማያቋርጥ የተፈጥሮ መለዋወጦች ውስጥ የማይካተቱን በማሰብ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## የጠፈር መሰብሰብ

ሳይንሳዊ ምርምር ከአቢይ አካላዊ ክስተቶች እስከ ረቂቅ አካላዊ ክስተቶች ይደርሳል። የመጀመሪያውን ለማወቅ የመጨረሻውን ከመመርምር አይላቀቅም።

በምዕራፍ ሁለት አካል ሁሉ የተሳሰረ መሆኑ ተጠቁሟል። ይህንን መተሳሰር ከአንድ ንጥረ ነገር ወይንም ከአንድ አካላዊ ሕያው ጀምረን እስከ ጠፈር ድረስ ብናዘልቀው፥ ሁለት አይነት መሰብሰብን እናገናዝባለን፡-

- ታላቅ መሸማቀቅ (መኮማተር)፡- በአቢይ መሰብሰብ ታላቅ መሸማቀቅ (the big crunch) ሲፈጠር እና የጠፈር አካላት ሁሉ ወደ አንድ ሥፍራ ሲሰጋሹ።
- ንዑስ መሰብሰብ፡- እጅግ ግዙፍ ያልሆኑ፥ በይዘታቸው መጠነኛ ወይንም አነስተኛ የሆኑ ከዋክብት ሁሉ በያሉበት ብርሃናቸው ሲጠፋና ሲከስሙ (ሲሞቱ)።

በታላቁ ፍንዳታ ጊዜ የተፈጸመው መበተን አስቀድሞ የነበረውን የጉተታ ኃይል ለጊዜው አሸነፈው እንጂ ፈጽሞ አላጠፋውም። ስለዚህ፥ መበተኑ ባስከተለው ውጤት ሳቢያ የተበተነው ኃይል ከአንድ የተወሰነ ሥፍራ ተነስቶ ርቆ ቢሄድም፥ በመጀመሪያ በተፈጠረው ጠፈር ውስጥ - እዛው በሚገኝ የስበት ኃይል - እርስ በርስ እየተሳሳበ በተወሰነ ክልል ውስጥ ይገታል። አንዴ መገታት ከጀመረ፥ በተቀረው የስበት ኃይል መሰብሰብ ይጀምራል። በትንሿ የስበት ኃይል ትንሽ መቀራረብ ከተጀመረበት ወቅት ጀምሮ፥ መሳሳብና መቀራረቡ እየጨመረ ይሄዳል።

የጠቅላላ የጠፈር እፍጋታ (density) ከተወሰነ ወሳኝ ቁጥር (critical value) በታች ድክም ያለ ቢሆን ኖሮ፥ ስበት እንደገና ጠፈርን ለመሰብሰብ ስለሚያቅተው፥ ጠፈር ለዘለአለም እየሰፋ ይሄዳል ማለት ይቻል ነበር። ነገር ግን፥ ለዘለአለሙ እጅግ እየራቀ (እየሰፋ ብቻ) አይሄድም የሚለው ሃሳብ በብዙ ሳይንቲስቶች እየተደገፈ የመጣው የአሁኑን የተዳከመ የጠፈር እፍጋታ ከፍ የሚያደርጉ፥ እኛ የማናያቸው አያሌ አካላት ሊኖሩ ይችላሉ በማለት ነው (ይህ ሃሳብ በኋላ ይፍታታል)።

ጠፈር መጨረሻ ሳይኖረው እንዲሁ እየሰፋ ይሄዳል ስንል፥ ጠፈር ክፍት ነው ወይንስ ዝግ? የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል። ለምሳሌ፡- አስር ሰዎች እጅ ለእጅ ቢያያዙ (የሁሉም እጅ ሌላ እጅ የያዘ ቢሆን)፥ አስሩ ሰዎች ቢቆሙም፥ ቢቀመጡም ቢሮጡም፥ በአንድ የተወሰነ ክልል ውስጥ ከመሆን አያመልጡም። ሁሉም ባንድ ላይ ካላሰቡ በስተቀር አብረው ሮጠው የትም አይደርሱም። እንዲህ ያለው ሁኔታ ብዙ የማያፈናፍን ስለሆነ ዝግ እንለዋለን።

ከአስሩ ሰዎች መካከል እጅ ያልያዙ እጆች ቢኖሩ፥ እየራቁ መሄድና መለያየት፥ መስፋትና መራራቅም ይኖራል፤ ይህም ዘላለማዊ ሊሆን ስለሚችል፥ ይህንን ሁኔታ ክፍት እንለዋለን።

ጠፈር ክፍት ከሆነ፥ ጠፈር ለዘለአለም ይሰፋል የሚለውን ሃሳብ ከዚሁ ጋር አዛምደን እንየው።

ዝግ ነገር ከውስጡ ኃይል ወደ ውጪ እየሄደ አይባክንም፤ ክፍት የሆነ ነገር ግን ከውስጡ ኃይል ወደ ውጪ እየሄደ ይባክናል። ይህ ነው የሁለቱ ልዩነት። በጠፈር ውስጥ ለማንኛውም ቁስ አካል ማስተሳሰሪያ የዝምድና ሃረግ የሆነው ስበት (gravity) ነው። በዝግ ጠፈር ውስጥ የስበት ጠባይ ያለው ሁሉ እርስ በርሱ ከመተሳሰር (ከመዛመድ - አብሮ ከመሆን - አብሮ ከመዝለቅ) አያመልጥም፤ ማንኛውም በጠፈር ውስጥ ያለ ነገር ከጠፈር ውጪ ሊሄድ አይችልምና።

ስለዚህ፥ጠፈር ዝግ ነው ካልን፥ እናም በጠፈር ውስጥ ያለ የአካል እፍጋታ (density) ጠፈርን ለመሰብሰብ በቂ ስበት ቢኖረው፥ ጠፈር ይሰበሰባል ማለት ነው።

በተቃራኒ፥ ጠፈር ክፍት ነው ስንል፥ በጠፈር ውስጥ ያለ የአካል እፍጋታ ጠፈርን ለመሰብሰብ በቂ ስበት አይኖረውም፤ ማንኛውም በጠፈር ውስጥ ያለ ነገር ከጠፈር ውጪ እያመለጠ በዘለአለማዊ ጉዞ ወዳልታወቀ ሥፍራ ይሄዳል ማለት ነው።

የስበት (gravity) ኃይል ከኢሊክተሮ ማግኔትና ከኑክሊየር ኃይል ጋር ሲወዳደር ደካማ ቢሆንም፥ ወደ ውጪ የሚገፋ ኃይል ከሌለ፥ ከአካል አጠገብ ሌላ ትንሽ እንኳን የስበት ኃይል ቢኖር፥ የስበት ኃይሉ ወደ መጣበት አካል የመጠጋት ዝንባሌ ይኖራል። በዚህ አይነት ብዙ መጠጋጋቶች ቢኖሩ፥ ጠፈር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ ብቻ አይሄድም ማለት ይቻላል። ታዲያ፥ ጠፈር ዝግ ከሆነ፥ ከታላቁ ፍንዳታ በኋላ የመበተን ክስተት (የጠፈር መስፋት) አሁንም እየቀጠለ ቢሄድም፥ ግፊት የበተናቸው አካሎች ሁሉ እንደገና በስበት ሊሰበሰቡ ይችላል።

ጠፈር ለዘለአለም እየሰፋ አይሄድም ስንል፥ ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ከሳይንሳዊ ፍልስፍ ጋር የሚኖረውን ዝምድናም ልብ ይሏል።

ጠፈር ዝግ ከሆነ፥ በውስጡ ያለ የስበት ኃይል ከዋክብትን ሁሉ አንድ ቀን ይሰበስባቸዋል። የብርቅነት (singularity) ሃሳብም ሊጠነሰስ የቻለው ጠፈር ዝግ ነው ከሚል ሃሳብ በመነሳትና ከአይንስታይን ሃሳብ ጋር በማስማማት ነው። እንዴት?

ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አይንስታይን ጠፈር ዝግ ስለመሆኑ የሚከተሉትን ሦስት ነጥቦች አቅርቧል፡-

- ጠፈር ክፍት ነው ብሎ ከመነሳት ይልቅ፥ ጠፈር ዝግ ነው ብሎ መነሳት በሂሳብ ስልት[18] እጅግ ይቀላል።
- እውቀት ማለት የሚታመንና እውነት ሲሆን፥ (ከሆነ)[19]፥ ጠፈር በአካል ጠባይ ውስጥ ሆኖ ዝግ ነው ብለን ስንመራመር የምናገኘው እውቀት ያረካናል። ጠፈር ክፍት ነው ብለን የምናገኘው እውቀት አያረካንም። ጠፈር ክፍት ነው ከማለት ይልቅ፥ ጠፈር ዝግ ነው ማለቱ ለአስተሳሰብ ይቀላል።
- ባናውቀውም፥ የጠፈር ማእከላዊ እፍጋታ (average density) ወደር ያለው ነው (ዜሮ አይሆንም) ብሎ ማሰቡ ይቀላል።

የመጨረሻውን ነጥብ በተመለከተ፥ ወሰን የሌለው ክፍት ጠፈር ሊኖር የሚችል የጠፈር ማእከላዊ እፍጋታ (density) ወደ ዜሮ ሲጠጋ ነው። ከዋክብት በየጊዜው እየተራራቁ፥ በአገረ ከዋክብት መካከል ያለውም ርቀት በየጊዜው እየጨመረ ሲሄድ በመመልከት ነው የጠፈር እፍጋታ ወደ ዜሮ ይጠጋል የሚባል። በዚህ አይነት፥ ጠፈር እጅግ ሰፊ ሆኖ በውስጡ ያሉትን ቁስ አካሎች እፍጋታ የማያካትት (እፍጋታው የተዳከመ) ሲሆን፥ ጠፈር መረን የተለቀቀ ሆነ ማለት ነው። ለዘለአለም እየሰፋ ይሄዳል ማለት ነው[20]።

ጠፈር ለዘለአለም እየሰፋ እንዳይሄድ የሚያደርግ (የሚከላከል) አንድ የተወሰነ የጠፈር እፍጋታ ልክ መኖር አለበት። ስለዚህ፥ ጠፈር አንድ ቀን ይሰበሰባል ከተባለ፥ ጠፈር ለዘለአለም እየሰፋ እንዳይሄድ የሚያደርገው የመጨረሻውና ትንሹ እፍጋታ (critical value) በጠፈር ውስጥ አለ ወይንስ የለም የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል።

---

[18] ከዚህ እስከዚህ ድረስ (boundary condition)

[19] Epistemology

[20] ነፃ አስተያየት፡- ጠፈር እንደ ሰፌድ የሰፋ ሆኖ፥ ከከፈፉ ታላቅ እፍጋታ ወደሚኖርበት ወደ ማእከላዊው ሥፍራ ትንሽ እንኳን መለስ የሚል ቢሆን፥ ሲሰፋ ወደ ማእከላዊው ሥፍራ መቅረቡ ስለሚሆን ጠፈር እንዲሰበሰብ አንዱ ምክንያት ሆነ ማለት ነው።

በጠፈር የሚታዩትን አካላት ይዘት ብንደምር እና ለጠፈር (በውስጡ ያሉትን አካላት ሁሉ ባንድነት) እፍጋታውን ብናወጣ፥ የምናገኘው ቁጥር ጠፈርን ሊሰበስብ የማይችል አነስተኛ ቁጥር ነው የሚሆን።

ጠፈርን ለመሰብሰብ ከሚያበቃ ከመጨረሻውና ትንሹ እፍጋታ አንድ መቶኛው እንኳን በጠፈር ውስጥ ከሚታዩት አካላት የማይገኝ መሆኑ ተረጋግጧል። ታዲያ፥ ጠፈር ለዘለአለም እየሰፋ ነው የሚሄደው? አይደለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ አንዳንድ በውስጣቸው ምን እንዳለ በማይታወቅ ጨለምለም ባሉ አካባቢዎችም፥ ሌሎች ብሩህ ከዋክብት ጨለማውን ሥፍራ ሲዞሩ ታየ። ከዚህም በመነሳት፥ ከዋክብትን በዙሪያው የሚያሽከረክር፥ እጅግ ኃይለኛ የሆነ ስበት መኖር እንዳለበት ታወቀ።

ስለዚህ፡- በጠፈር ውስጥ የጨለማ ሥፍራ ፍለጋ ቀጠለ። በፍለጋውም መሠረት፥ በጠፈር ውስጥ ብዙ ጨለምለም ያሉ ሥፍራዎች ይገኙ ጀመር። ጠፈርን እንደ ወንዝ እየከፋፈለ፥ ስበት የሚፈስበት፥ በውስጡ ጠቆርቆር ያለ ሥፍራ (ጽልመተ ጥልቀት) እየታየ መሆኑን በየጊዜው በኢንተርኔት የሚቀርበው የሳይንስ ዜና ያመለክታል። በዚሁ አዲስ ግኝት ሳቢያ፥ የጠፈር እፍጋታ ወደ ዜሮ ይጠጋል፤ ጠፈር ክፍት ነው፤ የሚለውን ሃሳብ ውድቅ የሚያደርገው አስተሳሰብ ጠንካራ መሠረት አገኘ።

በዚህም ምክንያት፥ በአይን የማይታዩ፥ በጠፈር ውስጥ ሌሎችም ከፍተኛ ስበት ያለባቸው ሥፍራዎች  የጠፈርን አጠቃላይ ስበት ከፍ እንደሚያደርጉት ግልጽ ከመሆኑም በላይ፥ ጠፈርን ለመሰብሰብ የሚያበቃ እፍጋታ መኖሩ ታወቀ።

ከተጠቀሱት መረጃዎች ሌላ፥ በማንኛውም ጊዜና ሥፍራ (በማንኛውም አቅጣጫ) ጠፈርን ሲመለከቱት አንድ አይነት መምሰሉ ጠፈር ክብ እና ዝግ መሆኑን ይጠቁማል።

የሰው እምነቱ ሳይንሳዊ አመለካከቱን ሊቆጣጠረው ይችላል። በእግዚአብሔር የሚያምኑም ሆኑ የማያምኑ፥ የጠፈርን ዝግ መሆን እና አለመሆን ሲመራመሩ፥ ሳይንሳዊ አመለካከታቸውን ውስጣዊ ዝንባሌቸው (በእግዚአብሔር ማመን/አለማመናቸው) ሊቆጣጠረው እንደሚችል ልብ ይሏል። ለዚህም እኮ ነው ሁለቱንም መመልከቱ ይጠቅማል የምንለው።

ሳይንስን ከሃይማኖት ጋር የምናዛምድ ከሆነ፥ ጠፈር ለዘለአለሙ እየሰፋ ይሄዳል በማለት መረጃዎች ቢቀርቡልን፥ ከአስተሳሰባችንና ከሃይማኖታችን ጋር ሳይዋሃድ  ቶሎ ብለን አንቀበልም።

አንዳንድ በእግዚአብሔር የማያምኑ ግለሰቦች ጠፈር ክፍት ነው ሲሉ፥ ቀደም ሲል የጠቀስነውን ሃታታ ካለማገናዘባቸውም በላይ፥ እየሰፋ የሚሄደውን ጠፈር የሚገታው - በተፈጥሮ ውስጥ ጣልቃ የሚገባ መለኮታዊ ኃይል - አለመኖሩን ለማሳመን ከመፈለግ ጋር ሊያያዝም እንደሚችል ልብ ይሏል።

## አስቀድሞ የተደነገገ እና የማያቋርጥ ክስተት

በመሰብሰብ ውስጥ የመዘርጋት ሕግጋት፥ በመዘርጋት ውስጥም የመሰብሰብ ሕግጋት ስለሚኖሩ፥ ለወደፊት የሚፈጸመውን ሁሉ የሚወስን፥ አስቀድሞ የተደነገገ ሕግ ይኖራል። ለኛ የሚገባን እንደ ስበት ያለ የተፈጥሮ ሕግ ቢሆን፥  ወይንም ሌላ ለኛ የማይገባንም "ሕግ"[21]  ቢኖር፥ ተፈጥሮ በሕግና በስነስርዓት የሚስተዳደር ከሆነ፥ በጠፈር ውስጥ ያለ አካል ሁሉ የተፈጥሮን ሕግ እንዲከተል፥ ተከትሎም እንዲጓዝ የ"መጀመሪያው" ትእዛዝ (የእግዚአብሔር ቃል) ተሰጥቶታል (እምነት)።

ስለ ጠፈር መዘርጋትም ጉዳይ ቢሆን፥ እግዚአብሔር ጠፈርን ሂድና ተዘርጋ ሲለው ይዘረጋል። ታዲያ ይህ እርሱ አንዴ የሚያስተላልፈው ትእዛዝ (ቃል) ነው የማያቋርጥ ተፈጥሮአዊ ክስተት የተባለ። ምክንያቱም የጠፈር መዘርጋት (በውስጡ ከሚያካትተው ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ጋር) ሌላ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ከመምጣቱ በፊት ሊቋረጥ (ሊገታ) አይችልም፤ ቃል ቃል ነውና (የእግዚአብሔር)። ስለዚህ፥ ሳይንቲስቶች ጠፈር እየሰፋ ይሄዳል ቢሉ ልክ ናቸው። ስለ ጠፈር መሰብሰብም ጉዳይ ቢሆን፥ የጠፈር መሰብሰብ (በውስጡ ከሚያካትተው ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ጋር) ሌላ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ከመምጣቱ በፊት ሊቋረጥ (ሊገታ) አይችልም፤ ቃል ቃል ነውና (የእግዚአብሔር)። ታዲያ፥ እንዲህ የሰፋ ጠፈር መሰብሰብ ቢጀምር፥ እና እግዚአብሔር በቃ ሳይል ቢቆይ፥ መጨረሻው ምን ሊሆን ይችላል (ይመስላል)  ከብርቅነት (singularity) በስተቀር።

የመሰብሰብን እና የመዘርጋትን ጽንሰ ሃሳቦች ከመለኮታዊ ኃይል ገንጥሎ መመልከት እንደማይቻል አንዳንድ ሳይንቲስቶች እየገባቸው መጥቷል። ይህ ተዘርጋ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ምንኛ  ታላቅ ነው። እንዲሁም ይህ ተሰብሰብ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ምንኛ  ታላቅ ነው። እነኚህ ሁለት ቃላት አንዱ ከሌላው አይተናነስም። የማያቋርጥ ክስተት ያልነውም ሕግን ተከትሎ የሚጓዝ፥ በሁለቱም (በተዘርጋና በተሰብሰብ) መካከል ያለ መሆኑንም በመገንዘብ ነው።

[21] "ሕግ" ስንል፥ ለሰው የሚገባው፥ የማይገባውንም ጨምሮ ነው።

አሁንም ጠፈር እየሰፋ እንደሚሄድ ሳይንሳዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ግን እንደገና መሰብሰብ ሳይኖርበት፥ ለዘለአለም እየሰፋ ይሄዳል ማለት፥ ሌላ ትእዛዝ አይኖርም እንደማለት ይቆጠራልና፤ ይህ ሃሳብ በሳይንሱም በሃይማኖትም የማይደገፍ ይሆናል።

መጨረሻውን ሳያሳውቅ የሚጓዝ - ምንድር ነው ይህ ጠፈር ለዘለአለሙ እየሰፋ ይሄዳል ማለት? በዚህች በጠባቧ ምድራችን ውስጥ እንኳን ቢሆን መጨረሻው ሳይታወቅ (መጨረሻ ሳይኖረው) እንዲሁ ለዘለአለም የሚካሄድ ክስተት ምንም የለም።

ጠፈር አሁንም እየሰፋ ቢሆንም/ባይሆንም፥ የጠፈር መስፋት ዘለአለማዊ እንዳይሆን (እንዲገታ) "ግታ - ሰብስብ" የሚል የእግዚአብሔር ቃል (ሂድ ፥ ስፋ - ተዘርጋ) ከሚለው ጋር አብሮ ይኖራል (እኛስ ከመኖራችን ጋር እየሞትን አይደለም ያለነው?)። ከመዘርጋቱ በፊት የተሰበሰበ፥ ከመሰብሰቡ በፊት የተዘረጋ - ይህ ጠፈር - የዛሬው፥ የጥንቱና የወደፊቶቹ ጠፈሮች ለኛ አይታወቁም፤ አልፋና ኦሜጋ ከሆነው ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም ሊቆጣጠራቸው (ሊያስተዳድራቸው) የሚችል የለምና።

እግዚአብሔር ጠፈርን ተዘርጋ ብሎ (እንዳለ) እስከ ዘለአለሙ ዝም ቢል፤ ወይንም እግዚአብሔር ጠፈርን ተሰብሰብ ብሎ (እንዳለ) እስከ ዘለአለሙ ዝም ቢል፤ በሁለቱም አቅጣጫ ምን ይፈጠር ይሆን ብሎ ማሰብ ካቅም በላይ ነው የሚሆን። ግን፥ እግዚአብሔር ካለ፥ እርሱም የሚያደርግና የሚፈጽም ከሆነ፥ መዘርጋት እንደሚኖር መሰብሰብም ይኖራል። መሆን ያለበትን ሁሉ አስቀድሞ እርሱ ያውቃልና፤ ሁሉንም በወቅቱ ያደርጋል።

ጠፈር ለዘለአለም የማይሰፋ ከሆነ፥ ባለበት ቀጥ ይላል ወይም እንደገና ይሰበሰባል። ባለበት ቀጥ ይላል ከማለት ይልቅ፥ ይሰበሰባል ብንል ለዚህ ድጋፍ የሚሆኑን ሳይንሳዊ ፍልስፍናዎች አናጣም። ስለዚህ የጠፈር መሰብሰብ እንዴት ሊሆን እንደሚችል እናስተውል።

## የጠፈር መሰብሰብ እንዴት?

በሳይንስ አንድ ነገር ይሆናል ሲባል፥ እንዴት እንደሚሆንም ማስረዳት ያስፈልጋል። ስለዚህ እኛም ጠፈር ይሰበሰባል የምንለውን፥ ለስነአይምሮአችን ሳይንሳዊ እርካታ ብለን፥ እንዴት እንደሆነ መግለጽ ይኖርብናል (የማናውቀው ቢበዛም)።

ከዋክብት በየጊዜው ይወለዳሉ፥ እነርሱም እንደሰው አርጅተው ይሞታሉ። የአንድ ኮከብ መክሰም (ሞት)፥ ስለ ታላቁ ፍንዳታና የቀድሞው ጠፈር የቀረበውን መላምት ለየት ባለ መልኩ ሊያመሳክር ይችላል። ይኸውም፡- በአንድ ኮከብ ውስጥም፥ ግፊትና ጉተታ በተቃራኒ ይኖራሉ። ግፊቱ የሚያመዝነው በኮከቡ ክበብ ነው።

በአንድ ግዙፍ ኮከበ ውስጥ ያለ እሳት (የሃይድሮጂን ወደ ሂሊየም መለወጥ) ወደ ማለቁ ሲቃረብ፥ ግፊቱ ከሚበዛበት አካባቢ - ኦክሲጂን፥ ካርቦን እና ሂሊየም ያለው የኮከብ ክፍል - እጅግ ይሰፋል። በዚህን ጊዜ፥ ያ ኮከብ ቦግ ብሎ ከፍተኛ ብርሃን ይረጫል፤ ይህ ታላቅ ቦግታ ሱፐርኖቫ (supernova) ይባላል። እንዲህ ያለው ቦግታ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በቀን እንኳን ሊታይ ይችላል። በዚህ አይነት፥ አንድ ታላቅ ቦግታ (supernova) ሲፈጠር አንድ ኮከብ ከሰመ “ሞተ” አንላለን።

ነገር ግን፥ አካል በጠባዩ ከአንዱ ወደ ሌላ አካል ይለወጣል እንጂ ፈጽሞ አይጠፋም። ስለዚህ፥ የአንድ ኮከብ ሞት እንደ አንድ እሳት መጥፋት ይቆጠራል እንጂ፥ የአካልነት መጨረሻው አይደለም። እሳት ነዶ ነዶ ቢጠፋ፥ ያ እሳት ወደ ሙቀት፥ ብርሃን፥ ጢስና አመድ ይቀየራል። እንዲሁም አንድ ኮከብ ተቀጣጥሎ ሲጠፋ የሚቀረው ብረት እና ሌሎችም ከበድ - ከበድ ያሉ ንጥረ ነገሮች ይሆናሉ።

በየጊዜው ከጠፈር ወደ መሬት እየበረሩ የሚቀርቡ፥ አልፎ አልፎም መሬትን የሚመቱ፥ የጠፈር ደንጋዮች የምንላቸው (meteorites) በዚሁ አይነት የከሰሙ - እጅግ ጥቃቅን የከዋክብት ሽርፍራፊዎች ናቸው። ምድራችንም ካሁን በፊት (ከዛሬ 5 ቢሊዎን ዓመታት በፊት) የአንድ ትልቅ ኮከብ አካል ነበረች። እርሷና ሌሎችም ፕላኔቶች (የጸሐይ ጭፍሮች) ከታላቅ ቦግታ ((supernova) በኋላ የከሰሙ - እጅግ ጥቃቅን የከዋክብት ሽርፍራፊዎች ናቸው።

ጠፈር አሁንም እየሰፋ ነው ያለ ብንልም፥ የከዋክብት መክሰም ከጠፈር መሰብሰብ ጋር ይያያዛል። ስለዚህ የኮከብ መክሰም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፥ መጠነኛም ቢሆን፥ የጠፈር መሰብሰብ ነበር ማለት ነው። የከዋክብት መክሰም ከዛሬ 5 ቢሊዎን ዓመታት በፊት (መሬት የተገኘችበት አካባቢ) እንደነበረ እርግጠኞች ከሆንን፥ ቢያንስ ቢያንስ ከዛን ጊዜ ጀምሮ የከዋክብት መክሰም እንደቀጠለ እናውቃለን

ማለት ነው። ታዲያ በአምስት ቢሊዮን ዓመታት ውስጥ ስንት ከዋክብት ይከስማሉ (ከስመዋል)።

እስከ ዛሬ ድረስ የከሰሙ ከዋክብት ስንት ናቸው? እስከ ዛሬ ድረስ ከከሰሙትና አሁን (ዛሬ ማለት ነው) ካሉት ከዋክብት ቁጥር የትኛው ይበልጣል? እስከ ዛሬ ድረስ የከሰሙት ከዋክብት ቁጥር አሁን ካሉት ከዋክብት ቁጥር ቢበልጥም፥ የጠፈር መሰብሰብ መጀመሩን አያበስርም። የጠፈር መሰብሰብን የሚወስነው የጠፈር አጠቃላይ እፍጋታ ጠፈርን ለመሰብሰብ ከሚያበቃው ከትንሹ ወሳኝ እፍጋታ (critical density) መብለጥ ወይንም አለመብለጥ ነው።

አንድ ኮከብ ሊሞት ሲል በኮከቡ የውጪ ግፊት (እሳት ወደ ውጪ እንደሚፈነጣር ማለት ነው) ተይዞ የነበረ ኃይል፥ ሥፍራውን ለከፍተኛ ጉተታ (የኢሌክትሮ ማግኔት እና የኑክሊየር ኃይል) ይለቃል። ቀሪውም ከፍተኛ ጉተታ፥ ሌላ ተቀናቃኝ (እሳትና አየር ወይም ጋስ-ጢስ) ኃይል ስለሌለበት፥ በራሱ የጉተታው ኃይል የተነሳ እራሱን በራሱ ያሽማቅቀዋል። ያ ኮከብ በከፍተኛ የጉተታ ጠባዩ ይሽማቀቅና ግዙፉ ኮከብ ድውይ ኮከብ ይሆናል ማለት ነው።

ቀደም ሲል፥ በከዋክብት ውስጥ ስለተፈጠሩ (ስለተገነቡ) ንጥረ ነገሮች ገልጸናል። እነኚህ ንጥረ ነገሮች መሽማቀቅ ሲመጣባቸው ምን እንደሚሆኑ እንመልከት፡-

በአንድ አቶም ውስጥ ኢሌክትሮን፥ ፕሮቶንና ኒውትሮን ይገኛሉ። ታዲያ ምን ጊዜም ማእከላዊውን ሥፍራ የሚይዙት ፕሮቶንና ኒውትሮን ናቸው። የተቀረው ሥፍራ በኢሌክትሮኖች የተያዘ ነው።

አንድን አቶም በአንድ ቤት ብንመስለው፥ ፕሮቶን እና ኒውትሮን የሚይዙት ማእከላዊው ሥፍራ ከአንድ የምራቅ ጠብታ የማይበልጥ ሲሆን፥ በተቀረው ሥፍራ ሁሉ፥ የቁስ አካል እና የሞገድ ጠባይ ያለው፡- የኢሌክትሮኖች መፈንጫ ባዶ ሥፍራ ይሆናል ማለት ነው።

እንግዲህ በዚህ አይነት፥ አንድ ዝሆን ቢሽማቀቅ (በውስጡ ያለ ባዶ ሥፍራ ሁሉ ቢጠፋ)፤ ክብደቱ ሳይቀንስ (እንዳለ ሆኖ)፤ ያ ግዙፍ ዝሆን ከአንድ የቡና ፍሬ ያነሰ ይሆናል ማለት ነው። እንዲሁም፥ በአንድ ታላቅ ኮከብ ውስጥ በሚገኙ ንጥረ ነገሮች ያለ ባዶ ቦታ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ቢሽማቀቅ የኮከብን ድውይነት እንደሚያስከትል መገመት አያስቸግርም።

የኛይቱ ኮከብ (ጸሓይ) ለመሞት በምትቃረብበት ወቅትም፥ ልክ እንደሌሎቹ ከዋክብት ቦግ ማለቷ አይቀርም። በዚያን ጊዜ የሚፈጠር የመጨረሻ ቦግታ (ከፍተኛ ብርሃን) መሬትንና ሌሎችን ፕላኔቶች ሁሉ ይሸፍናቸዋል ይባላል። በመጨረሻ -

ከቦግታው በኋላ - የሚቀረው የጸሓይ የማእከላዊው ክፍል ብቻ ይሆናል። ይህም በከፍተኛ የጉተታ ጠባዩ ስለሚሽማቀቅ በመጨረሻ ነጭ ድውይ ኮከብ ይቀራል ይባላል።

የኛይቱን ኮከብ (ጸሐይ) በይዘት ሦስት ጊዜ የሚበልጥ ኮከብ በሚከስምበት ወቅት የሚቀረው በብረት የተያዘ የማእከላዊው ክፍል ብቻ ይሆናል። የዚህ ኮከብ የጉተታ ኃይል ከአጀማመሩ (ከኮከቡ ትልቅነት የተነሳ) እጅግ ከፍተኛ ስለሚሆን፥ ከጸሐይ መሽማቀቅ እጅግ የበለጠ፥ ከፍተኛ መሽማቀቅ ይደርስበታል። ይህ እንዴት እንደሚሆን እንመልከት፡-

ቀደም ሲል፥ ከአንድ ኮከብ ዳርቻ ወደ ማእከላዊው ሥፍራ የንጥረነገሮች ክብደት እየጨመረ እንደሚሄድ ጠቅሰናል። በኮከቡ ውስጥ መሽማቀቅ ሲመጣ፥ በኮከቡ ማእከላዊ ስፍራ በሚቀረው የብረት አተሞች ውስጥ ያሉ ኢሌክትሮኖች ሁሉ ከፕሮቶኖቻቸው ጋር ይላተሙና ፕሮቶኑ ሁሉ ወደ ኒውትሮን ይለወጣል።

ፕሮቶን እና ኢሌክሮን ሲዋሃድ - የኢሌክትሮኖች የተሳቢነት ጠባይ ከፕሮቶኖች የሳቢነት ጠባይ ጋር ሲዋሃድ - ተሳቢም ሳቢም ያልሆነ ጠባይ ያለውን ኒውትሮንን ይፈጥራል ማለት ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፥ በኮከቡ የሚቀረው ኒውትሮን ብቻ ስለሚሆን፥ ከመሽማቀቅ የተረፈው ኮከብ የኒውትሮን ኮከብ ተብሎ ይጠራል።

ከአንድ ኒውትሮን ኮከብ አንድ የሻይ ማንኪያ ያህል አካል ቢቆረስ፥ የዚህ አካል ክብደቱ ምን ያህል ይሆን? ቢባል፥ እንደ እስቲፈን ሃውኪንግ (1988) ግምት፥ ይህ በአንድ የሻይ ማንኪያ የተቆረሰ የኒውትሮን አካል እስከ አንድ ሺህ ቢሊዮን ኪሎግራም ሊመዝን ይችላል።

ከዚሁ በመቀጠልና ስለ ጠፈር መሰብሰብ የጀመርነውን ለማጠናከር፥ እንዲሁም ቀደም ሲል፥ በጠፈር ውስጥ ጠቆርቆር ያሉ ሥፍራዎች ስለመገኘታቸው ያነሳነውን ጉዳይ በጥልቀቱ መመልከትን እንጀምር።

## ጽልመተ ጥልቀት

በጠፈር ውስጥ የከዋክብት ብርሃን የሚጠፋበትና ጠቆርቆር ያለ ሥፍራ በብዛት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ በጠቆረ ሥፍራ ከጨለማ በስተቀር የሚታይ ምንም ብርሃን ባለመኖሩ፥ ይህ ሥፍራ ጥቁር (ጸሊም) ተባለ። በጨለማው ሥፍራ ዙሪያ

የጠፈር አቧራና ሌሎች አካሎች ለጨለመው ሥፍራ መጠነኛ ብርሃን ቢሰጡትም፥ ከወደመሃሉ እጅግ ጨለማ ስለሆነ ጽልመተ ጥልቀት (black hole)[22] ተባለ።

ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሁሉ፦ በአንዳንድ የጠቆሩ ክልሎች በዙሪያቸው በከፍተኛ ደረጃ የሚሽከረከሩ ከዋክብት ታይተዋል። ካለ ምንም ማእከላዊ ኃይል እንዲህ መሽከርከር ስለማይችሉ፥ የእነርሱ መሽከርከር ከጽልመተ ጥልቀት ማእከላዊ ሥፍራ በሚመጣ የጉተታ ኃይል መሆኑን ያመላክታል።

የኛይቱን ኮከብ (ጸሐይ) በይዘት ሦስት ጊዜ የሚበልጥ ኮከብ በሚከስምበት ወቅት በብረቱ ውስጥ ያሉትም ፕሮቶኖች ሁሉ ወደ ኒውትሮንነት ይለወጣሉ ብለናል።

ነገር ግን በኒውትሮኖች ውስጥም ሌሎች የተለያየ ጠባይ የሚያሳዩ (ኩአርክ፥ ሌፕቶን፥ ሜዞን፥ ሃርዶን) የሚባሉ እጅግ የረቀቁ አካሎች አሉ። እንግዲህ መሽማቀቁ እንዲቀጥል የሚያደርገው ሁኔታ ካለ (የኮከቡ የኢሌክትሮ ማግኔት እና የኑክሊየር ኃይል እጅግ ከፍተኛ ከሆነ)፥ እነርሱም እርስ በርስ ይጨፈላለቁና የመጀመሪያው ኮከብ የስበት ኃይሉ እንዳለ ሆኖ፥ የሚይዘው ሥፍራ ግን አይኖርም - ብርቅነት (singularity) ይሆናል ማለት ነው።

የጽልመተ ጥልቀት አነሳሱ እጅግ እጅግ ከፍተኛ የስበት ኃይል ከሚኖራቸው ከዋክብት ነው። የነኚህ ከዋክብት ትልቅነት፥ ከአጀማመሩ እጅግ ከፍተኛ (ጸሐይን አስር ጊዜ ወይም ከዛ በላይ ያህል የሚበልጥ) ከሆነ፥ የመሽማቀቁ ኃይል ወሰን እጅግ ከፍተኛ ስለሚሆን፥ የመኮማተሩም መጨረሻው ግዙፉን ኮከብ በአካል ወደ ምንምነት (ብርቅነት) ይቀይረዋል ማለት ነው።

በማንኛውም አካል ዙሪያ የስበት አድማስ አለ። ለምሳሌ ጸሐይና በዙሪያዋ ያሉ ፕላኔቶች ባንድነት የስበት ክልል አላቸው። በተመሳሳይ መንገድ፦ ግዙፉ ኮከብ ከመሞቱ በፊት የስበት አድማስ ይኖረዋል። ኮከቡ ሲሽማቀቅ፥ በኮከቡ ዙሪያው ያለ የስበት አድማስም አብሮት ነጥቡ ወዳለበት አቅጣጫ ይሽማቀቃል። ይህ ሲሆን፦ በቅርጹ የጠጅ ማጥለያ (የዘይት መቅጃ) የመሰለ አድማስ ይፈጠራል። በዚህ “ሥፍራ” የወደቀ ማንኛውም ነገር መመለሻ የለውም።

ብርሃን የሞገድና የቁስ አካል ጠባይ ስላለው በስበት ሊገታ ይችላል። ስለዚህ፥ በብርቅነት ዙሪያ ያለ የስበት ክልል ማንኛውንም ብርሃን ከተወሰነ ክልል ውጪ ርቆ እንዳይሄድ ስበቱ ይገታዋል።

[22] ጥቁር ቀዳዳ ወይንም ጥቁር ጉርጓድ ከማለት ይልቅ፥ ጽልመተ ጥልቀት ቢባል፥ የጥልቀቱን ጨለማነት እና ጥልቀቱን በጣምራነት የሚገልጽ ይሆናል።

ይገርማል፤ ስለ ታላቁ ፍንዳታ (big bang) እና ስለ ጠፈር መዘርጋት፥ እንዲሁም ስለ ታላቁ መሸማቀቅ (big crunch) እና የጠፈር መሰብሰብ ስናወሳ ነበር የብርቅነትን (singularity) ባሕረ ሃሳብ የቀሰቀስነው። አሁን ደግሞ፥ ያንድን ግዙፍ ኮከብ ሊሞት ሲል በታላቅ ቦግታ (supernova) የሚረጨውን ኃይል እና ከዛ ቀጥሎ ስለመሸማቀቁ ጉዳይ፥ ስለ ጽልመተ ጥልቀትም ጉዳይ አንስተን፥ በዚሁ ስንቀጥል፥ ወደ ቀድሞው የብርቅነትን (singularity) ባሕረ ሃሳብ ተመለስን። ሁሉንም እያገናዘብን እንቆይ።

## ታላቁ መሰብሰብ (ሳይንሳዊ ፍልስፍና)

ከዋክብት በተናጠል ሲሸማቀቁ ላጠቃላይ የጠፈር መሰብሰብ ምክንያት ይሆናሉ። እንዲሁም በየአገረ ከዋክብት (galaxie) ማዕከላዊ ሥፍራ ስበቶች ይኖራሉ፤ በአንድ አገረ ከዋክብት ክልል ያሉ ጠቅላላ ከዋክብት ሁሉ በዚህ ማዕከላዊ ሥፍራ ዙሪያ ይሽከረከራሉ። ይህም ማዕከላዊ ስበቶች በጠፈር ሁሉ መኖራቸውን ይጠቁማል።

በተጠቀሰው አጠቃላይ የከዋክብት መሽከርከር (ዙረት) ውስጥ፥ የእፍጋታ በአንድ አቅጣጫ ማመዘን ሲፈጠር፥ አገረ ከዋክብት እርስ በርስ ይሳሳቡና ይጠላለፋሉ። አገረ ከዋክብት እርስ በርሳቸው እየተጠላለፉ፥ ሁለት፥ ሦስት፥ አራት፥ አስር፥ ሃያ..ወዘተ...አገረ ከዋክብት በጣምራነት ግዙፍ አገረ ከዋክብት ይመሠርታሉ። ይህ የመልከ ወተት ጎዳና የተባለውም የኛ አገረ ከዋክብት ከሠላሳ ያላነሱ አገረ ከዋክብት ባንድ ላይ የተገናኙበት መሆኑ ይገመታል።

አንድሮሜዳ እና የኛ የመልከ ወተት ጎዳና እየተቀራረቡ መሆናቸውን ካንዳንድ ሳይንሳዊ ጽሑፎች ተመልክተናል። ታዲያ ይህ እውነት ከሆነ፥ እነኚህም ታላላቅ አገረ ከዋክብት ተጠላልፈው (ተገናኝተው) አንድ ሲሆኑ፥ ማእከላዊ ሥፍራቸውም አንድ ይሆናል ማለት ነው።

ከዚሁ በመነሳት፥ በጠፈር ውስጥ ያሉትም ሌሎች አገረ ከዋክብት በተመሳሳይ መንገድ እየተቀራረቡ ቢመጡ፥ በጠፈር ውስጥ የሚኖረው ማዕከላዊ ሥፍራ ግዙፍነትና የሚኖረው የስበት ችሎታ እጅግ ታላቅ መሆኑን እንገነዘባለን። እንግዲያውስ ይህ ሁሉ እውነት ከሆነ፡-

- ታላላቅ ከዋክብት ይከስሙና እያንዳንዳቸው የስበት ማእከል፥ እንዲሁም የስበት አድማስ (event horizon) ይፈጥራሉ።
- አገረ ከዋክብትም ይጠጋጉና የስበት ማእከል ይፈጥራሉ።
- በተወሰነ ወቅት እጅግ ብዙ ከዋክብት ይከስሙና፥ የጠፈር የስበት ኃይል ይናጋል (የሰማይ ኃይላት ይናወጣሉ)።

- የጠፈር የስበት ኃይል ሲናጋ፥ ከዋክብት ከምን ጊዜውም ይልቅ በብዛት ወደየአቅራቢያቸው የጠፈር አካላት የሚረግገፉት ሁኔታ ይፈጠራል።
- ብዙ ከዋክብት ሲረግፉ፥ የጠፈር የስበት ኃይል ወደ ተወሰነ ስፍራ ይሽጋሽጋል (ያመዝናል)።
- የጠፈር የስበት ኃይል ወደ ተወሰነ ስፍራ ሲያመዝን፥ አገረ ከዋክብት ሳይቀሩ በአንድ አቅጣጫ ይሳባሉ።
- አገረ ከዋክብት ወደ አንድ አቅጣጫ ሲያመሩ፥ እርስ በርስ ይጠላለፉና ግዙፉን አገረ ከዋክብትን ይፈጥራሉ።
- በግዙፉን አገረ ከዋክብትም ማዕከላዊ ሥፍራ ያ የጠቀስነው ጽልመተ ጥልቀት ስለሚኖር፥ ጠፈር ዝግ ከሆነ፥ የጠፈር መሰባሰብ በጽልመተ ጥልቀት ከፍተኛ የስበት ኃይል ይባባሳል።
- በተጠቀሱት በብዙሃን አገረ ከዋክብት ጣምራነት ከጠፈር ከአንዱ ወገን የሚገኙ አገረ ከዋክብት ሲሸማቀቁ ለአጠቃላይ የጠፈር መሰባሰብ (መሸማቀቅ) ምክንያት ይሆናሉ።
- ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አያሌ መሸማቀቆች ተጠቃለው፥ ወደ አንድ መሸማቀቅ ያመሩና፥ የጠፈር የመጨረሻው መሰብሰብ ይሆናል።
- ከዚህ በኋላ፥ አካላዊነት በቅቶታል ማለት ስለሆነ፥ መቀጠል ያለበት ሕይወት ሁሉ ሌላ አካላዊ ወዳልሆነ አለም ይተላለፋል (ይሆን?)።

"The day we roll up the heavens like a scroll rolled up for books (completed) – even as We produced the first creation, so shall We produce a new one, a promise we have undertaken. Truly We shall fulfill it." Sura[23] 21:104

ትርጉም፡- "ብራና ተጠቅልሎ መጻሕፍት እንደሚሆኑ፥ ሰማያትን በጠቀለልን ጊዜ፥ የመጀመሪያውንም ፍጥረት እንዳከናወን፥ እንዲሁም አዲስ ፍጥረትን የምንፈጥር መሆናችንን ተስፋ እንደሰጠን፥ በእውነት ይህንን እንፈጽማለን።" ሱራ 21፡14

"The whole cosmic order is under Me. Under My will it is automatically manifested again and again, and under My will it is annihilated at the end." B.G[24]. 9:8 (see also 8:19)

[23] The Qur'an: Translation by Abdullah Yusuf Ali

[24] Bhagaavad Gita As It Is: by His Devine Grace A. C. Bhaktivedanta Swami Prabhupada

ትርጉም፡- "ሰማያት በእኔ ትእዛዝ ሥር ናቸው። በእኔ ፈቃድ በተደጋጋሚ ይፈጠራሉ፤ በመጨረሻም በእኔው ፈቃድ ይጠፋሉ።" ብ.ጊ. 9፡8 (ብ.ጊ. 8፡19 ንም ይመልከቱ።)

## ማጠቃለያ

አልበርት አይነስታይን የሚከተለውን ተናግሮ ነበር።

"ከግንዛቤአችን ውጪ በሆነ ጠፈር ውስጥ የሚከሰት አንድ ታላቅ ኃይል መኖር አለበት እንድል የሚያደርገኝ ውስጣዊ ስሜቴ፥ ስለ እግዚአብሔር ያለኝን አመለካከት ይወስናል።"[25] ይህ አባባል የሳይንስ እውቀት፥ ስለ እግዚአብሔር ማወቅን፥ አድናቆትን እና እምነትን የሚያጠናክር መሆኑን ያሳያል።

እኛ አማኞች፥ ስለታላቁ ጠፈርና ስለማይታወቀው ሁሉ ስናስብ፥ የፈጣሪአችን የእግዚአብሔርን ኃያልነት ማድነቃችን አይቀርም። እስካሁን ያወሳነውም ተጨማሪ አድናቆትን በአድናቆታችን ላይ የሚያክልበት ቢሆን መልካም ነው።

ለሰው ልጅ አንጎል እውነታ የሚሆኑለት ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳቦች ከጠቅላላ የሕዝቦች ቁጥር ቢበልጥ አይገርመንም። የሚገርመው የፍጹማዊ እውነት አለመገኘት ነው። የሰው ልጅ እግዚአብሔር ጠፈርን እንዴት አድርጎ እንደዘረጋውና እንዴት አድርጎም እንደሚሰበስበው ለማወቅ የሚያስችል እውቀትና ብቃት የለውም (ሊኖረው አይችልም)፤ ግን የሚያውቀውንና የማያውቀውን ለመቀባጠር ያህል ብቻ ችሎታ ተሰጥቶታል።

በእግዚአብሔር ከሚያምኑ ሳይነቲስቶች ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ጋር በጽንአት የቆየነው፥ እነርሱም ከልባቸው ወደ እግዚአብሔር የማያመለክተውን ንድፈ ሃሳብ እየተው፥ ወደ እግዚአብሔር የሚያመለክተውን ንድፈ ሃሳብ የተከተሉ መስሎን ይሆናል። ነገር ግን በዚህች ተለዋዋጭ አለማችን ውስጥ፥ ሰው ሁሉ ለሥጋው ሲሳሳ እና ለገንዘብም ሲል፥ እውነትን ሊሸሻት ይችላልና፤ በተቻለ መጠን እምነታችን በውስጣችን ከሚኖር እውነት ጋር ቢቆይ ነው የሚሻለው።

እስቲፈን ሃውኪንግ "ጠፈር ወሰን የሌለው፥ የማይዘረጋ፥ የማይሰበሰብ፥ አስቀድሞ የነበረና የማይጠፋ፥ ራሱን በራሱ የሚያቆይ ነው ብሎ ማሰብ፥ ለፈጣሪ መኖር ምንም ክፍተት አለመስጠት ነው።" (እስቲፈን ሃውኪንግ፤ 2005) በማለት አስተሳሰቡን ከእግዚአብሔር መኖር ያልገነጠለ ሳይንቲስት ነበር።

---

25 http:/www.spaceandmotion.com/albert-einstein-god-religion-theory.htm

እንዲሁም “The Theory of Everything” በተባለ መጽሐፉ፥ “ዛሬ የሰው ልጅ ደረስኩበት የሚለው እውቀቱ የመጨረሻው ባይሆንም፥ የአካላዊ ክስተቶችን ሂደት ሊያውቅ የሚችለው እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ብቻ መሆኑን ጠቁሞ ነበር።

ነገር ግን፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ ጠቅላላ ጠፈራዊ አካላትን የሚገዛ ሕግ መኖር አለበት፤ ይህም ሕግ በሰዎች ሊታወቅ ይችላል የሚል አስተሳሰብ አመንጭቷል። ይህንንም አስተሳሰብ በጉልህ የሚያንጸባርቅ “The Grand Desighn” የተባለ መጽሐፍ በቅርቡ ታትሞ ተሰራጭቷል።

የሚገርመው፥ ይህንን መጽሐፍ የጻፈው፥ እስካሁን ስለ እግዚአብሔር መኖር ብዙ የተናገረ፥ ይኸው እስቲፈን ሃውኪንግ ነው፤ ከግብረ አበሩ ከሊኦናርድ ምሎዲኖው ጋር።

በዚህ መጽሐፉ፥ “አካል ከምንም ሊፈጠር ይችላል። አካል ከምንም ተገኝቶ የራሱን ሕግ ተከትሎ የሚሄድ ከሆነ፥ የበላይ ተቆጣጣሪ አያስፈልገውም፤ ስለዚህ የፈጣሪም መኖር አያስፈልግም” ይላል።

መጽሐፉ ለተራ ሰው እንዲገባ በቀላሉ ነው የተጻፈው። መሠረተ ሃሳቡም፥ በቁስ አካላት መካከል የሚገኙትን አራቱን ኃይላት በአንድ አጠቃላይ ንድፈ ሃሳብ ለመግለጽ፤ ቀጥሎም የማንኛውም ጠፈራዊ እንቅስቃሴ ጠፈራዊ አካላትን በሚገዛ ሕግ የተወሰነ እንደሚሆን፤ መጀመሪያና መጨረሻው፥ ሂደቱም የሚታወቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። እንደ መጽሐፉ አባባል፥ ማንኛውም አካላዊ ክስተት ከተጠቀሰው አጠቃላይ ሕግ ስለማይወጣ፥ ይህንን ውሱን የእንቅስቃሴዎች ሂደት የሚለውጥ - ከበላይ ሆኖ ተአምር የሚሠራ፥ የውጪ ኃይል መኖር አያስፈልግም ይላል (የለም አይልም - ትንሽ የፍርኃትና የጥርጣሬ ክፍተት ትቷል)።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን አባባል ብቻ በተናጠል ይዘው በእግዚአብሔር ላለማመን ሳይንሳዊ መረጃ ያገኙ መስሏቸዋል። የድሮ ሰዎች ከአንድ ክርስቲያን አስተማሪ ከሚሰሙት መንፈሳዊ ትምህርት ጋር አንድ ተአምራት በሚያዩበት ወቅት፥ ”እኛ ከዛሬ ጀምሮ በአንተ አምላክ እናምናለን” ይሉ ነበር።

የዘመናችንም ጥራዝ ነጠቆች ደግሞ የሳይንቲስቶችን እምነት መከተል ያምራቸዋል። እንግዲያውስ የእስቲፈንን እምነት እከተላለሁ የሚል ተአምራዊ የሂሳብ ስልቱንም የሚረዳ መሆን አለበት። ማወቅን ለእያንዳንዱ ሰው በተለያየ መንገድ የሚሰጥ እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ለማመን ወይም ላለማመን የሳይንቲስቶቸን አፍ መጠበቅ ሞኝነት ነው።

እስቲፈን የወንበር ቁራኛ ሆኖም ከሳይንሳዊ ምርምር አለመላቀቁ በጣም የሚደነቅ ፍጡር ነው። ከመቀመጫው ብድግ ማለት የማይችል መሆኑ፥ በአስተሳሰቡ ላይ ያስከተለውን ተጽንኦ ማወቅ አይቻልም። ከተጠቀሰው "The Grand Desighn" የተባለ መጽሐፉ በኋላ፥ "እስቲፈን በዚህ መጽሐፉ ከስህተት ላይ ወደቀ፤ " ብለው ያዘኑ ሳይንቲስቶች ብዙዎች ናቸው።

ከውጪ ሆነን ተፈጥሮን የመመልከትን እድል ሳናገኝ፥ ከዚህ ተነስተን እዚህ እንደርሳለን ብለን በትክክሉ መተንበይ ካቅም በላይ አይሆንም?

ሳይንቲስቶች እስካሁን ድረስ ምናልባት የአየር ጠባይን አውቀው በትክክሉ መተንበይ ችለዋል ቢባል ነው እንጂ፥ የእሳተ ገሞራ መፈንዳትን፥ የመሬት መንቀጥቀጥን፥ .. እየተነበዩ የሰውን ልጅ ከጥፋት አላዳኑትም። ለወደፊትም የጥፋት ዘመን ቢመጣ ተንብየው ሊያድኑት አይችሉም።

በጥልቀትና በከፍታ የሚያስቡ ሳይንቲስቶች ካቅማቸው በላይ ሲንጠራሩ፥ ማንኛውም አካላዊ ክስተት ከአጠቃላይ ሕግ አይወጣም ካሉ፥ የሰዎችም እንቅስቃሴና ሂደት የተደነገገ ስለሚሆን፤ ነፃ የሆነ ፈቃዳዊነትም አይኖርም ማለታቸው ነው። በእንደዚህ አይነት ሃሳብ መቆየቱ ስለማይጠቅመን፥ ይህንን በዚሁ እንግታው።

ከሁሉም እምነት የሚበልጥ መሆኑን የሚያስረዳ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ እጅግ ጥልቅ ምሥጢር ያለው ጥቅስ በመጥቀስ ስለ ጠፈር ያወራነውን እልባት እናበጅለት። ይህም ጥቅስ የሚከተለው ነው:-

"እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፤ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው። ለሽማግሌዎች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና፤ <u>ዓለሞች</u> በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፥ ስለዚህም <u>የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ</u> በእምነት እናስተውላለን።" ወደ እብራውያን ፲፩:1 - 3

የተሰረዘበትን እናስተውል። በእርግጥ ይህ ጥቅስ የተጻፈው የዘመኑ ሳይንቲስቶችን ሳይንሳዊ እርምጃ በተመለከተ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ግን፥ ሳይንቲስቶች የአካል ትንሽነት መጨረሻው እስከምን ድረስ ነው እያሉ ሲመራመሩ በመቆየታቸው፥ የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ ገብቷቸዋል።

ምናልባት ይህ አባባል ለአንዳንድ ሳይንቲስቶች ኢሳይንሳዊ እና የአላዋቂዎች የድፍረት አነጋገር ሊመስል ይችል ይሆናል። ግን የሰው ልጅ በፍጥረቱ ውሱን ከሆነ፥ ፍጹማዊ እውነትም ፍጹም ከሆነ፥ እውነት በሰው የማይደረስበት ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ፍጹም የሆነ ነገር ወሰን የለውም። ባለ ወሰን የሆነ ሰው ወሰን የሌለውን (እንደ ብርቅነት፥ እንደ ጽልመተ ጥልቀት ያለውን..) ሊደርስበት አይችልም።

ነገር ግን ከአካላዊው ሰው በስተጀርባ ያለ ሰው ከሥጋዊ አይምሮው ውጪ ከዘለአለማዊው ጠፈር ግንኙነት ሊያደርግ፤ በሥጋዊነቱ የማያውቀውን በ"መንፈሳዊነቱ.." ሊያውቅና ሊመራመር ይችላልና፤ ለዚህም ነው ነገሮችን በጥልቀቱ ለመመልከት የምንሻ።

የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን ሲል፡- ሰው ስለ ጠፈር አፈጣጠር የፈለገውን ቢያስብ (እስካሁን የተዘረዘረው ሁሉ ውሸት ቢሆንም) ምንም ለውጥ እንደማያመጣ፤ ከሁሉም እምነት የሚበልጥ መሆኑን ያመለክታል።

"አይናችሁን ወደ ላይ አንስታችሁ ተመልከቱ፤ እነዚህን የፈጠረ ማነው?" ኢሳ. 40፡26

## <u>በረከተ ጸሎት</u>

- ❖ የእውነት እውነትነቱን ለማየት የሚያስችል መንፈሳዊ ጥበብ ይለግሰን።
- ❖ በምድራዊ እውቀት ከመመካት ያድነን።
- ❖ የምናውቀውን አውቀን፥ የማናውቀውን አናውቅም ለማለት የሚያበቃ የልብ ቅንነት ይስጠን።
- ❖ የምናውቀውንና የማናውቀውን መለየት ቢያቅተን፥ እውቀት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ፥ ከሰው ዘንድ የማይገኝ ስለሆነ፤ አለማወቃችን እንዳያስጨንቀን የሚያረጋጋ መንፈስ ይለግሰን።
- ❖ እምነታችን እና ሃይማኖታችን ለራሳችን እውነት እንዲሆንልን እንጂ፥ እንዳያስጨንቀን ያድርገን።
- ❖ የእግዚአብሔር ፈቃደ ብርሃን በልባችን ይብራ፤ እግዚአብሔርን ብቻ በማየት ሕይወታችንን እንድንመራ።

# ምዕራፍ አራት

## ምድራችን - መሬታችን፥ ባህራችን፥ አየራችን

በቀደሙት ምዕራፋት የጠቀስናቸው ሳይንሳዊ መላምቶች በፊዚክስና በሂሳብ ስልት ለሚራቀቁ ሳይንቲስቶች እንኳን እጅግ ጠለቅ ያሉ ናቸው። እኛም ላይ ላዩን የነካካነው፥ አንድም በቅርብ ስለምናውቃት ስለምድራችን፥ እንዲሁም ስለ ሰብአዊነት ጉዳይ መንደርደሪያ (መነሻ) እንዲሆንልን ብለን ነበር።

በጠፈር እና በስነ ምድር ምርምር በገሃድ የታወቁ ፍሬ ሃሳቦችን እያስታከኩ በመመራመር፥ ስለ ምድራችን ያወቅነውን በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናውቀው ጋር ለማመሳከር ጊዜው አሁን ነው። ይህች ምድራችን ከኛ ሰውነት ጋር ተመጣጣኝ አካል ያላት ትንሽ የጠፈር ጠብታ ስለሆነች፥ በመጠኑም ቢሆን አውቀናታል በማለት፥ ስለርሷ አንዳንድ ገለጻዎች ለማድረግ በእምነት እንነሳ።

የምድራችንን አካላዊ ተፈጥሮ፥ በውስጧም የሚገኘውን ሕያውና ሕይወት አልባ ሁሉ በተመስጦ ብንመለከት፥ ወደ አይምሮ ብዙ- ብዙ ሃሳቦች ይሰርጉና ተፈጥሮን ከማድነቅም በላይ መውደድ፤ መጨረሻዋንም ለመተንበይ እስከ መቃጣት የሚያደርስ ሁኔታ ውስጥ ይከተን ይሆናል። ይህም አካላዊ ክስተቶችን በሳይንሳዊ ምርምር፥ መንፈሳዊ ክስሰቶችንም በመንፈስ አርቅቆ መመልከት ነው።

የሚበላ ምግብ ከመሬቷ፥ የሚጠጣ ውሃ ከባህሯ፥ የምንተነፍሰውም አየር ከዙሪያዋ፤ ከጸሐይ በምታገኘውም ሙቀቷ ምድራችን ሁሉን አስተካክላ ስለታቀፈችን፥ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ በሥጋ የምንኖርበት ዓለማችን ሆናለች። መጨረሻዋ እስኪሆን ድረስ አካላዊ ሕያዋን ሁሉ ይፈጠሩባታል፤ ይሞቱባታልም።

የምድር መጨረሻ የሚሆነው ጸሐይ ስትሞት ይሆናል። የምድራዊ ሕያዋን መጨረሻ ግን ከዛም በፊት ሊመጣ ይችላል።

የጸሐይ መጨረሻ የሚሆነው በውስጧ የሚከናወን፥ የብርሃን ፍንጠቃ (የሃድሮጂን ወደ ሂሊየም መለወጥ ክስተት) ሲገባደድ ይሆናል። ሆኖም፥ ባጠቃላይ የኛን፥ የምድርን እና የጸሐይን ሕልውና የሚወስነው በጠፈር ውስጥ የሚከናወነው ሁሉ ነው።

ሕጻን ልጅ በመጀመሪያ እናትና አባቱን፥ ቀጥሎም የቅርብ ዘመዶቹንና አካባቢውን ሁሉ ያጠናል። የአገሌ ልጅ አገሌ እየተባለ፥ በዝምድና መቀራረብና መራረቅ እንደሚታወቅ ሁሉ፥ እኛም ከምድራችን ጀምሮ እስከ ጠፈር ድረስ በአካል ዝምድናችን ከማን ከማን ጋር እንደሆነ ለመለየት እንሞክር።

ግላዊ አስተሳሰባችን ሁሉ  በሌሎች (በሳይንቲስቶቹ) የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ በማስገባት፥ ድንበር ወሰን የሌለውን እውቀት ማጥበብና የግለኝነት መልክ መስጠት - ሰው በነፃ እንዳያስብ ማድረግ የተለመደ ሆኗል። እኛ ግን፥  ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከሌሎች መጻሕፍት፥ ከራሳችንም ግላዊ አመለካከት ርቀን ሳንሄድ፥ ስለጠፈር፥ ስለምድራችንም በምንፈላሰፍበት ወቅት፥ የሳይንስ እውቀትና ግልጋሎት ለመንፈሳዊነትም የሚያገለግል መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ስለ ምድራችን ማሰቡን ከመጀመራችን በፊት ስለ ታላቁ ጠፈር፥ ስለፈጣሪዋም ለአንድ ደቂቃ ያህል እንኳን ቢሆን እናስብ።

ከጠፈር ስፋት አንጻር ምድራችን እንደ አንድ የባህር አሸዋ የምትቆጠር ናት። በአንድ ትንሽ የውሃ ጠብታ የምታክል ህዋስ (cell) የሚገኙ አተሞች ብዛትም የዛኑ ያህል ነው። ታዲያ መብዛትና ማነስ፥ መስፋትና መጥበብ፥ ትልቅነትና ትንሽነት ምንድነው ልዩነቱ?

የትልቅነትና የትንሽነትን ወሰን ስንመረምር፥ ይህንን ሁሉ የፈጠረ ፈጣሪያችንን ከማድነቅና ከማመስገን አልፈን፥ ኃያልነቱን ለመገንዘብ የሚያበቃ አይምሮ እንደማይኖረን ይገባናል። ሆኖም፥ ለእምነታችን ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ፥ የምድርን ውስጧንና ዙሪያዋን እንይላትና፤ በመንፈሳዊ መንገድ እንመልከታት።

“ምድርን እዩአት፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ በርሷ ላይ ከሚሠራው ሥራ የተነሳ፥ የሚታይ የአምላክ ሥራው ሁሉ እንዳይለወጥ ልብ አድርጉ።” ሄኖክ 1፡11

በባሕሮች፥ በደረቅ መሬቶች፥ በተራሮች፥ በሸለቆዎች፥ በሜዳዎችና በጫካዎች አምራና አሸብርቃ፥ ዙሪያዋን እጅግ የምታቃጥል ወይም እጅግ የምትበርድ እንዳትሆን፥ በሰሜን እና በደቡብ ዋልታዎቿ በረዶ ተሸከማ፥ ከበላይዋም ነፋስ እያነፈሰች፥ ሙቀት ካንዱ ወዳንዱ እያስተላለፈች፥ እያዘነበች፥ ውሃ በጉያዊ እየታቀፈች በውስጧ አካላዊ ሕያዋንን ስታርመሰምስ፥ በእውነትም ምድር ነፍሳማ ሆና እኛን እስከዛሬ ድረስ አቆየችን።

ምድራችን ለእኛ ይህንን ሁሉ ስታደርግ፥ እኛ ደግሞ እርሷ ከእግዚአብሔር የተሰጣትን መደበኛ ሥራዋን በትክክሉ እንዳትሠራበት እናውካታለን። እንዴት ነው ይህቺን ነፍሳማ ምድር የምንመለከታት?

ከአንድ ሥፍራ - አንድ አይነት ብቻ አይደለም እውቀት፥
በጠፈር ሁሉ ይኖራል እውነት፤
ግን ሃይማኖታዊ እውነታዎች ሲደበቁ፥ በምድራዊ እውቀት ብዛት፤
ሳይንሳዊ እውነቶችም ሲናቁ፥ ሃይማኖትን ከሳይንሱ ማገናዘብ ሲያቅት፤
እኛ እናጥና በትጋት፤ እናስተውል ተፈጥሮን፥
ከዙሪያችን እስከ ጠፈራችን፥
ሁሉም የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን።
ክረምትና በጋ ሲፈራረቅ፥
ሁሉም ነገር በጊዜ ውስጥ ሲቀያየር፥
መሬትና ባሕር ሲገለባበጥ፥
አንዱ ሕይወት ጠፍቶ ሌላ ሕይወት ሲፈጠር፤
ወንዝ ከተራራ እስከ ባሕር ድረስ ሲፈስ፤
ነፋስም በሩጫ አለምን ሲያዳርስ፥
ቀለል ያለው የባህር ውሃ ከላይ ሲንሳፈፍ፥
በጨው የወፈረውም ሙቀትን ሲያስተላልፍ፤
አየርና ውሃ ሲነጋገሩ፥
ከአፈሩ፥ ከሳርና ከቅጠሉ ጋር ሲዘምሩ፥
ሁሉም ለኛ ሲያስቡ፥ ሁሉም ለኛ ምቾት ሲመክሩ፤
ከተራራ ጫፍ ከከፍታው፥
ከሸለቆው ሥር ከዝቅታው፥
ምንድነው የምናየው?
ምንድነው የምንሰማው?
ከሜዳውና ከጫካው፥
ከቀዩ፥ ከቢጫውና አረንጓዴው።
መንፈሳዊነትን ለመማር ከነፍሳማ ሕያው ምድራችን፥
እናስተውል፥ እንስማቸው ሲያናግሩን፤
የባህር ሞገድ ድንፋታውን፥ የነፋስ ፉጨቱን፥
የጎርፍ ፉከራውን፥ የዛፍ ሽውሽውታውን፥

የቅጠል መርገፍገፉን፥ የመብረቅ ጩኸቱን
የነጎድፍድ መጉረምረሙን፥ የዝናብ መንኮሻኮሹን፥
ምድሪቱ ነፍስ አልባ መስላ ሕያውነቷን ስታረጋግጥ፥
ምንድነው የምናየው መገለባበጥ፥
ምንድነው ያ ሁሉ ድምፅ - የምንሰማው፥
በትዝታ ቅኝት፥
ዶ፥ ሬ፥ ሚ፥ (ፋ)፥ ሶል፥ ላ፥ (ቲ)፥ ዶ፥
ልዩ ዜማ - ደስ የሚለው።
ሲደጋገም - ሲደጋገም ጭልጥ አርጎ በትዝታ የሚወስደው፤
በአይናችን ከምናየው፥ ምንድነው በአይምሮአችን የሚመዘገበው?
ምንድነው ለሕሊናችን የሚጥመው?
ሁሉንም ነገር ባለ ነፍሳማ ሕይወት የሚያስመስለው?
ምንድነው የተፈጥሮ ምሥጢር፥
አብሮ ለመዝለቅ የሚያስችለው?
ሁሉን በፍቅር አይን ለተመለከተው፥
አካል ሁሉ አካላችን - ሕይወታችን ነው።
አብሮ ለመዝለቅ፥
እርስ በርስ መተሳሰብ፥
ተፈጥሮን ከማድነቅ አለፎ፥ መውደድ፥
ይህ ነው ለሁላችን የሚበጀው።

## <u>ከምድር እሳታዊነት ጀምሮ</u>

ስለ ከዋክብት ባወሳንበት ወቅት፥ ስለተጠቀሱት ንጥረ ነገሮች እናስታውሳለን። በምድር የሚገኙ ዋነኛ ንጥረ ነገሮች (ከሂሊየም በስተቀር) ከሞላ ጎደል እነርሱው ናቸው። ነገር ግን በምድራችን ውስጥ ከመቶ በላይ ንጥረ ነገሮች እንደሚኖሩ እናውቃለን። በሌሎችም የከሰሙ ከዋክብትና ሌሎች የጠፈር አካላት ውስጥም ብዙ ንጥረ ነገሮች ይኖራሉ።

በስነ ምድር (geology) እና በሌሎችም ምርምሮች እንደምናውቀው፥ ሁኔታው አስቀድሞ ሳይስተካከልለት የሚፈጠር ምንም ነገር የለም። ስለዚህ፥ በጠፈር ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮችን ብዛትና አይነት የሚወስነው የሁኔታው መስተካከል ነው እንጂ፥ የሁሉም መነሻ አንድ ነው።

ምድራችን በአፈጣጠሯ (በአጀማመሯ)፥ የኮከብ ሽራፊ ናት እንጂ፥ ከማንኛውም የጠፈር አካል አትለይም፤ ግን ሌሎች ከዋክብት አሁንም ሲቃጠሉ፥ እርሷ ግን ትንሽ ስለሆነች በትንሽነቷ ቶሎ ከሰመች። ቶሎ ብትከስምም፥ ቶሎ ስላልቀዘቀዘች ይሆናል ባለ ብዙ ንጥረ ነገር የሆነችው።

ከሁሉም በላይ የሚገርመው፥ እርሷን ባለ “ብዙ” ንጥረ ነገሮች እንድትሆን ያደረገ አካላዊ ሁኔታ ሁሉ ተስተካክሎ መገኘቱ ነው። ባለ ብዙ ንጥረ ነገር ባትሆን ኖሮ የምድራችን - የኛም መልክ የተለየ ይሆን ነበር። ለምሳሌ፥ ከምድራችን ካልሲዩም እንኳን ቢጎድል ኖሮ፥ የምድራችን የኛም የሰውነታችን ቅርጽ እንዲህ እንዳሁኑ አይሆንም ነበር።

ምድራችን እንደ ሌሎች ከዋክብት ባለ ንዳድ (እሳታማ) ነበረች፤ ሁለመናዋ እንደ ቀለጠ ፈሳሽ ሆና ብዙ ቆይታለች። በኩባያ የተቀዳ የፈላ ሙቅ (አጥሚት) ሲቀዘቅዝ መጀመሪያ ከከፈፉ እንደሚሆን ሁሉ፤ ይህ ውስጣዊ ግለቷ (ሙቀቷ) ዙሪያዋን በከበባት ቅዝቃዜ ሲበርድላት - የመሬት ሙቀት ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሲሄድ - ቅዝቃዜው ከከፈፏ ጀምሮ ወደ ከርሷ ተሸጋገረ። በተወሰነ ወቅት እንደ ፈሳሽ የሆነው የሚረጋው እስከተወሰነ ጥልቀት ድረስ ስለሆነ፥ ከከፈፏ ጀምሮ እስከ 10 ኪሎሜትር ያለው አካሏ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ረጋ፤ ሲረጋ ጠጣር መሬት ሆነ።

ምድር በቀዘቀዙ አለቶቿ ቅርጽ ብታወጣም፥ አሁንም በከርሰ ማዕከላዊው ሥፍራ በቀለጡና በከባድ ንጥረ ነገሮች (በተለይ በብረትና በመዳብ) የተያዘ መሆኑ ይታወቃል።

በኮከብነቷ ከጥንት ካገኘችው ሙቀት በተጨማሪ፥ አንዳንድ በመበስበስ እራሳቸውን የሚለዋውጡ ንጥረ ነገሮች (radio active elements)፥ ሲበሰብሱ ብዙ ኃይል ስለሚረጩ፥ የመሬትን ከርሰ ማእከላዊ ሥፍራ እስከ ከፈፏ ድረስ በእሳተ ገሞራ አገናኝተውታል።

ከከፈፍ ጀምሮ ወደ ምድር ከርስ አቅጣጫ ድረስ፥ ቀስ በቀስ ማእድናት በተለያየ ቅንጅት የተለያዩ አለቶችን ፈጠሩ፤ ደረቁ መሬት ራሱን የቻለ (ፈሳሽን መሸከም የሚችል) ጠጣር ሥፍራ እየሆነ በመምጣት ላይ ሳለ፥ ሙቀት (heat)፥ ግፊት (pressure) እና ጊዜ (time) በተባሉ ሦስት ታላላቅና ወሳኝ የተፈጥሮ

ሁኔታዎች ምክንያት፥ የተለያዩ ማዕድናትን ያካተቱ አለቶች በተለያየ ቅርጽና ቀለማት አሽብርቀው ቀስ በቀስ ብቅ - ብቅ ማለት ጀመሩ።

ከንጥረ ነገሮች ጀምሮ እስከ ማዕድናት፥ ቀጥሎም እስከ አለቶች ድረስ ግዑዛን የተባሉት ሁሉ እንደ ነፍሳት አስተዳደጋቸውና ሥራቸው ሁሉ ተወስኖ የተሰጣቸው መሆኑን እንመለከታለን።

በመሬት ውስጥ በሚመነጭ ሙቀት አለቶች በየጊዜው ከመሬት ውስጥ እየቀለጡ፥ በእሳተ ገሞራ አማካኝነት ወደ ውጪ እየተገፉና በመሬት ላይ እየፈሰሱ፥ እሳት ወለድ አለቶችን (volcanic rocks) ያስገኛሉ።

በመጀመሪያው የነበሩት እሳት ወለዶች ግን ተፈጠሩ (ተወለዱ) እንጂ፥ ሕልውናቸውን ጠብቀው (በውስጣቸው ያሉትን ማእድናት ሁሉ እንደያዙ ሆነው) ለመቆየት ገና ብዙ- በዙ ፍዳ - መከራ ይጠብቃቸው ነበር።

በድሮ ጊዜ ምድር ብዙ መከራ ነበረባት። ፍጥረት (መወለድ) ከብዙ አለመረጋጋት በኋላ ነውና፤ በውስጧ የነበረ ሙቀት በረድ (ቀነስ) እስኪል ድረስ፥ በከርሷ የነበረ የሚጎረባብጥ የሆድ ህመም ብዙ ዘመን ቆይቶባታል። ህጻን ከእናቱ ማህጸን ሲወጣና ወደ ቀዝቃዛው አለም ሲሸጋገር በብዙ በሽታ እንደሚጠቃ ሁሉ፥ ከመጀመሪያው የነበሩት (አስቀድመው የተፈጠሩት) እሳት ወለዶች በሙቀትና በግፊት ብዙ ተንገላተዋል።

ይህ አለመረጋጋት በተለያየ የሙቀትና የግፊት ኃይላት የመጀመሪያዎቹን ያልተረጋጉ የእሳት ወለዶችን (ገና ፈጽሞ ጠጣር አለት ሳይሆኑ የቀሩትን) እያጎበጡ፥ እያጣጠፉ፤ ጠጣር የሆኑትንም እየሰባበሩ፥ ዛሬ በደቡብና በሰሜን፥ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ የምናያቸውን አይነት ልውጠ አለቶችን (metamorphic rocks) አስገኙ።

የምድር ከፈፍ እየቀዘቀዘ በመጣበት ወቅት፥ ንጥረ ነገሮች (elements) በተወሰነ የሙቀትና የግፊት ኃይል እርስ በርሰ በመያያዝና በመሰካካት የተለያዩ ማእድናትን (ለምሳሌ፡- አዛሂት (quartz)፥ ጋርኔት፥ ቶፓዝ .. ወዘተ..) ፈጠሩ። በመጀመሪያው ገጸ ምድር የነበሩ አለቶች (እሳት ወለድ አለቶችም) ሲለወጡ (ልውጠ አለት[26] ሲሆኑ)፥ በውስጣቸው ያሉ ንጥረ ነገሮችም ልዩ ማእድናትን ሲገነቡ፥ መሬትም ልክ ጠጉሯን አበጥራ - ተኳኩላ ከቤቷ ብቅ እንደምትል ቆንጆ ልጅ አገረድ መሰለች፤ አደገች፤ መልክ አወጣች፤ የብስ የሚል ስም ተሰጣት።

---

[26] ልውጠ አለቶችን ከሌሎች አለቶች የሚለያቸው፥ በውስጣቸው የሚገኙ ጎላ ጎላ ብለው የሚታዩ የማእድናት አይነትና አጠቃላይ ቅርጻቸው ነው።

የአለቶች መፈጠር የነበረና አሁንም ያለ ነው። አለቶችም እንደ ውስጠ ፍጥረታቸው (በውስጣቸው እንደሚገኙ ማእድኖቻቸው ጠባይ)፥ በሙቀት ውስጥ መኖር የሚችሉት፥ ድቅቅ ብለውም ቢሆን፥ ቶሎ ይፈጠራሉ። ለምሳሌ፥ ጥቁር አለት (basalt) ካለ ማይክሮስኮፕ በደረቅ አይን የማይታዩ ማዕድናት ነው በውስጡ ያለው። ዘግይተው የሚፈጠሩትም፥ ለምሳሌ፥ ግራናይት (granite) የተባለ ዥንጉርጉር አለት፥ ቀስ በቀስ ያደጉ፥ ጎላ ጎላ ያሉ ማዕድናት ነው በውስጡ ያለው። በተጠቀሱት ሁለት የአለት አይነቶች መካከል ብዙ አይነት አለቶች አሉ። ሁሉም በተለያየ ሙቀት፥ ግፊት እና ጊዜ የተፈጠሩ ናቸው።

ለሰዎች ሥልጣኔ፥ ብልጽግና እና እድገት ምክንያት የሆነው የዛሬው የማዕድን ክምችት በረጅም ጊዜ ውስጥ በሙቀትና በግፊት ኃይል እንጂ፥ ባንድ ጊዜ የተፈጠረ አይደለም። በመጀመሪያው ገጸ ምድር የነበሩ አለቶች እንዲሁ ሲለዋወጡ መቆየታቸው ለምን አስፈለገ? እንዲህ ባይሆን ኖሮ - በተጠቀሰው መንገድ ማእድናት (ብረት፥ መዳብ፥ ወርቅ፥ ብር፥ ...ወዘተ) በአንድ የተወሰነ አካባቢ እየተከማቹ ባይቀመጡ ኖሮ፥ የዘመኑ ሰው ሥልጣኔ እዚህ አይደርስም ነበር።

ከፈሳሽነት ወደ ጠጣርነት የተሸጋገረች ይህች ምድር የብስ ሆነች እንጂ ገና ውሃ አልቋጠረችም፤ ከሞቃትነት ወጥታ፥ ወደ ቅዝቃዜ ስትመጣ የተወለደች በመሆኗ፥ እርሷም እንደ ህጻን ልጅ በውሃ መተጣጠብ ያስፈልጋት ነበር።

የመሬት ቅዝቃዜ እየቀጠለ ሲሄድ፥ በዙሪያዋ ከነበረ ጋስ - ጢስ መካከል ሃይድሮጂን እና ኦክሲጂን በመዋሐድ ገና ፈሳሽ ያልሆነ ውሃ (የውሃ ትነት) ፈጥረው ቆይተው ነበር። ይህ ፈሳሽ ያልሆነ ውሃ (ትነት) ፈሳሽ ሆኖ ወደ መሬት የወረደው የረጋው የየብሱ ሙቀት ከብዙሺህ ዲግሪ ሴንቲግሬድ እየቀነሰ መጥቶ ወደ መቶ ዲግሪ ሴንቲግሬድ ($100^0$ C) አካባቢ ሲጠጋና ከዛም የበለጠ ሲቀዘቅዝ ነበር።

“እግዚአብሔር ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ሥፍራ ይሰብሰብ፥ የብሱም ይገለጥ አለ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔር የብሱን ምድር ብሎ ጠራው። የውሃ መከማቻውንም ባህር አለው።” ዘፍ. 1፡9 - 10

ይህ ጥቅስ አሁን በምድር ላይ ያለ ውሃ ሁሉ አስቀድሞ በሰማይ ላይ ተንጠልጥሎ እንደነበረ ያመለክታል።

የመጀመሪያው የምድር አየር ሲቀዘቀዝ፥ ውሃ ወደ ማረፊያው - ወደ ረባዳ ሥፍራ (ውቅያኖስ፥ ባህር ፥ ሐይቅ) ሲወርድ፥ አየር ሲጠራ፥ የውሃ ዑደት ቀጠለ። ውሃ ከባህር እየተነነ በደመና መልክ ተከማችቶ ሲቀዘቅዝ፥ ዝናብ ሆኖ መሬትን አራሰ።

ዝናብ አለቶችን በመሰርሰር፥ በጊዜ ብዛት አፈር እንዲፈጠር አደረገ። ከጊዜ በኋላም አፈር በአንድ ሥፍራ ተከማችቶ ሲጠጥር፥ ድንጋይ የሚል መጠሪያ ስም

ተሰጠው። አፈሩም እንደ ሰፍነግ (spong) የዝናቡን ውሃ በመጠጣት (በመሸከም) ውሃ መቋጠሪያ ሆነ። የተሰነጠቁና የተሰባበሩ አለቶችና ድንጋዮችም በውስጣቸው ውሃ መቋጠሪያዎች ሆኑ።

ዝናብ በማይኖርበት ጊዜ ሁሉ መሬት ከያለበት ውሃ የምታፍለቀልቅ ባለ ብዙ ምንጮች ሆነች። ከተራሮችና ከከፍተኛ ሥፍራዎች የሚፈልቁ ምንጮች ሁሉ ቁልቁል ሲወርዱ፥ ከመሰሎቻቸውም ጋር ሲገናኙ መሬት ባለ ብዙ ወንዞችና ሐይቆች ለመሆን በቃች።

የዝናብ ውሃ በቶሎ ካልፈሰሰ፥ ምንጭም በመሆን ከመሬቱ ውስጥ ብቅ ካላለ፥ ወደታች መስረጉ አይቀርም። በውሃ ጉድጓድ የሚገለገሉ ሰዎች ይህንን የከርሰ ምድር ውሃ አመጣጥ አውቀውታል። ስለዚህም፥ ወንዝና ምንጭ በሌለበት ሥፍራ ሁሉ - ለምሳሌ በጅጅጋ አካባቢ - እስከ ሃምሳ ሜትር የሚደርሱ የውሃ ጉርጓዶችን እየማሱ ይጠቀማሉ።

ውሃም ወደታች መውረድ ልማዱ ነውና፤ ባጠገቡ ያገኘውን እየጠራረገ አንዳንድ ልፍስፍስ ማእድናትን፥ ለምሳሌ ካልሳይት፥ ጂብሰም.... በውስጡ እያሟሟ ጠንካሮቹንም፥ ለምሳሌ አዛሂት (quartz)፥ ማይካ.... እየገፋ ወደ ረባዳ ሥፍራ (ውቅያኖስ፥ ባህር፥ ሐይቅ) ይጨምራቸው ጀመር። ይህ ክስተት እስከዛሬ ስለቀጠለ፥ በአፈጣጠሩ ቀጭን የነበረውን የባህር ውሃ፥ ልፍስፍስ በሆኑ ማእድናት መሟሟት ምክንያት ከጊዜ ብዛት አወፈረው። የባህር ውሃ ሲቀምሱት ላፍ የሚከብድና የሚጎመዝዝ - ጨዋማ የሆነው ለዚህ ነው።

የባህር ኬሚስትሪ ወደፊት ለሚፈጠሩ ሕያዋን አመቺ ሁኔታን ፈጠረ። ንጥረ ነገሮች፡- ካልሲዩም፥ ሶዲዩም፥ እና ፖታሲዩም የተባሉት ዋነኛ የአካላዊ ሕይወት ገንቢዎች ናቸው። የነኚህ ንጥረ ነገሮች የወደፊት እድል ለጊዜው በነበረው የባህር ኬሚስትሪ ተወስኖ ቆይቷል።

በካርቦኖች እና በኦክሲጂኖች ጣምራነት የተፈጠሩ የካርቦንዳይኦክሳይድ ጋሶች ከብደት ስላላቸው ከባህር ጋር ይላተሙ ጀመር። ካርቦንዳይኦክሳይድ አየር (ጋስ-ጢስ) ስለሆነ፥ በአየርነቱ ጠባዩን ጠብቆ ከውሃ ጋር መኖር ስለማይችል፥ በውሃ ውስጥ መሟሟት ነበረበት።

ካርቦንዳይኦክሳይድ በውሃ ውስጥ ሲሟሟ፥ አስቀድመው በወንዞችና በጅረት ውሃዎች የሟሙትን እነ ካልሲዩምን[27] አገኛቸው። እነርሱም ገና ሌጣዎች

[27] እነ ካልሲዩም እና ማግነዚዩም አስቀድሞ - ዝቅጠ አለቶች ሳይፈጠሩ በፊት - በሌሎች እሳት ወለድና ዝቅጠ አለቶች ውስጥ ነበሩ።

(ያላገቡ) ስለነበሩ፥ ከካርቦንዳይኦክሳይድ ጋር እየተጣመሩና እየተጋቡ፥ ካልሲዩም ካርቦኔት (calcium carbonate) የተባለውን ማዕድን (የንጥረ ነገሮች ማህበራዊ አንድነት) መሠረቱ።

እንደገና ወደ አየሩ ሁኔታ መለስ ስንል፥ የዛን ጊዜ (ጥንት ገና ሕያዋን ሳይፈጠሩ) ኦክሲጂኖች ከሃይድሮጂኖች እና ከካርቦኖች ጋር እየተጋቡ ስለቆዩ፥ በአየሩ ውስጥ የሚኖር የነበረው የኦክሲጂን መጠን እጅግ ተቀንሶ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሁሉ፥ በአየር የተያዘው ሰማይ የኦዞን መጋረጃ ስላልነበረው ከጸሐይ የሚመጣ የአልትራ ቫዮሌት ጨረር አየሩን እየጣሰ ምድራችንን ይቀጠቅጣት ነበር።

ተወርዋሪ ኮከብ የምንላቸውም (የጠፈር ደንጋዮች - meteorites) በብዛት ከጠፈር እየተወረወሩ ከምድራችን አየር ውስጥ ሲገቡ፥ አየሩ ኦክሲጂን የጎደለው ስለሆነና በቶሎ ስለማይቀጣጠሉ፥ መሬትን በብዛት ይደበድቧት ነበር።

አየር አልባ የሆነችዋን የኛንም ጨረቃ፥ የጠፈር ደንጋዮች (meteorites) በብዛት ከጠፈር እየተወረወሩ፥ በየጊዜው ይቀጠቅጧታል። ለዚህ ነው ባለ ጠቃጠቆ መስላ የምትታየው።

መሬት ይህንን በየጊዜው የሚመጣባትን ሁሉ ችላ በትእግስት ቆየች። ደግነቱ የዛን ጊዜ ሕይወት ስላልነበረ፥ ጉዳት የደረሰበት ሕያው አልነበረም።

የውቅያኖስ ውሃ ከመሬት እየተሸረሸሩ በሚመጡ ማእድናት ውፍር ሲል፥ ባህርም ወደፊት ለሚፈጠሩ ሕያዋን ምግብ ይሆን ዘንድ ተዘጋጅቶ ተቀመጠ። ለሕያዋን ሁሉ ኦክሲጂን ያስፈልጋቸዋል። ይህም ኦክሲጂን ከአየር ውስጥ እየጎደለ ቢመጣ (ወይንም አነስተኛ ቢሆን) ወደ ባሕር እየገባ ቆይቷል።

በአየሩ ውስጥ የነበረ ኦክሲጂን አነስተኛ በነበረበት ወቅት፥ ጠጣሩ የምድር ከፈፍ ለሕያዋን መፈጠር ምንም አመቺ አልነበረም። በባህር ግን ምግብ ሁሉ ተዘጋጅቶ ቆይቷልና፤ የመጀመሪያዎቹ ሕያዋን በባህር ውስጥ ተፈጠሩ ብንል በቂ ምክንያቶች ይዘን ነው።

ሆኖም፥ ለሕይወት መፈጠር ግዑዛን ንጥረ ነገሮች ተሰናድተው ቆዩ እንጂ፥ በባህርም ሆነ በመሬት ላይ ሕይወት ሊኖር የሚችልበት ጊዜው እጅግ - እጅግ በጣም ረጅም - ብዙ ሚሊዮን ዓመታት የፈጀ ነበር።

የመጀመሪያዎቹ ሕያዋን የተፈጠሩት በባህር ውስጥ እንደሆነ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቁሟል።

“ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ።” ዘፍ. ፩፡20

## **ጠጣሩ የምድር ከፊፍ**

የከርሰ ምድር ንቅናቄ አንዱን የመሬት ክፍል ከፍ፥ ሌላውንም ዝቅ ሲያደርግ፥ የባህር ውሃ ረባዳ በሆነው መሬት ላይ ይወጣና ሰፊውን ደረቅ መሬት በውሃ ይሸፍነዋል። በዚህን ጊዜ፥ የባህር ውሃ ከዋናው ባህር ተገንጥሎ ስለሚቆይ፥ በውሃው ውስጥ ሟምተው የነበሩ ማእድናት ቀስ በቀስ ከውሃው እየዘቀጡ ይከማቻሉ።

የዝቅጠ አለቶች (sedimentary rocks) አፈጣጠር ከባህር መንገላታት ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ የኖራ ድንጋዮች[28] (limestones) እና የመሳሰሉት፥ ከባህሩ ተለይተው ወደታች ይዘቅጣሉ።

የባህር ማዕበል እንደ አዛሂት (quartz) እና የመሳሰሉትን በውሃ የማይሟሙ ማእድናትን እያንገላታና እያንገዋለለ፥ ወደ መሃል አገር እየገፋ ይተፋቸዋል። በዚህን ጊዜ የአሸዋ ደንጋዮች (sandstones) ከባህሩ ተለይተው በምድር ላይ ይከማቻሉ።

እንግዲህ ምድርን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፥ ከሰሜን እስከ ደቡብ፥ ዙሪያዋን ዞረን ብንቃኝ፥ ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው፡- ከእሳት ወለድና ልውጠ አለቶች ጋር ዝቅጠ አለቶችም ተጨምረው፥ እነኚህን ሦስት አይነት መሠረታዊ አለቶችና ዝርያዎቻቸውን ብቻ ነው የምናገኘው።

ዝቅጠ አለቶችም እየዘቀጡ፥ የቀለጡ አለቶችም በአንድ በተወሰነ ሥፍራ እየተጋገሩ፥ ወይንም ወቅት እየጠበቁና በመሬት ስንጥቆች እየተተፉ፥ ተራራዎችን ሲገነቡ፤ ወንዞችም በበኩላቸው መሬቱን ካለ ማቋረጥ እየሰረሰሩ ሸለቆዎችን (ሸንጥሮዎችን) ሲያበጁ፤ ሁሉም በበኩላቸው ለመሬት ወጣ ገብ ቅርጽ አተረፉላት።

ለምሳሌ፥ የኢትዮጵያን ምድር ስንቃኝ፥ የኖራ (የበሃ) ድንጋዮች በመቀሌ፥ በሙገርና በአባይ ሸለቆ፥ በደብረ ሊባኖስና ሌሎችም ሥፍራዎች በግልጽ የሚታዩ ናቸው። ከነርሱ ሥር ያሉት ሌሎች አለቶችም (ዝቅጠ አለቶች - የአሸዋ ደንጋዮች) በተከዜና በአባይ ወንዞች ግራና ቀኝ ይታያሉ።

ከዝቅጠ አለቶቹ ሁሉ ሥር ያሉት፥ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ልውጠ አለቶች በኤርትራና በትግራይ በብዛት ይገኛሉ፤ በወለጋ፥ በሲዳሞና በሐረርጌም በየሸለቆዎቹ በግላጭ ይታያሉ። በነዚህ ሥፍራዎች ብዙ የማዕድን ጥናት ይካሄዳል።

በመሬት ውስጥ በሚመነጭ ሙቀት፥ አለቶች ከከርሰ ምድር እየቀለጡ፥ በእሳተ ገሞራ አማካኝነት ወደ ውጪ ስለሚተፉ፥ ከማእከላዊው ኢትዮጵያ (ሸዋና

---

[28] የኖራ ድንጋዮች የበሃ ድንጋዮችም ተብለው ይጠራሉ።

ጎጃም) ጀምሮ እስከ ሰሜን ተራራዎች (ዳሽን ተራራ) ድረስ፥ በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያም (በሐረርጌ) ታላላቅ ተራራዎች ተገንብተዋል።

ከእሳተ ገሞራዎች እየቀለጡ ከሚፈሱትም የባሳልት (ጥቁር አለቶች) ሌላ፥ እንደ አቧራ ወደ ሰማይ ተበትነው ከውሃ ጋር እየተዋሃዱ፥ እንደገናም መሬት የረገፉት እሳት ወለዶች፥ እንደ ጭቃ መሬቱ ላይ እየተጠፈጠፉ፥ ነጣ ነጣ ያሉ - ኢግኒምብራይት የተባሉት፥ ቀደም ሲል በጠቀስናቸው የኢትዮጵያ ዝቅጠ አለቶች ላይ ተደረቡባቸው። ኢትዮጵያም ከሌሎች የአፍሪካ አህጉራት ሁሉ ከፍ ብላ የምትታይ ባለ ተራራማ እና ሜዳማ አገር ሆነች። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ተራሮች (the Ethiopian Plateau - Amhar Mountains) ባካባቢዋ ካሉት የአፍሪካ ምድሮች ሁሉ ቀዝቀዝ ያሉ ሆኑ። ቀጥሎም ተራራዎቿና ሸለቆዎቿ ባለ ሜካዎች ሆኑ።

የአባይ ወንዝ መሬቱን እየሰረሰረ ታላቅ ሸለቆ በመፍጠር ከእሳት ወለድ አለቶች በታች የሚገኙትንም ዝቅጠ አለቶች ገለጣቸው። እንዳውም ከዛ አልፎ ከዝቅጠ አለቶቹ በታች የሚገኘውንም ልውጠ አለት አልፎ አልፎ በገሃድ እንዲታይ አድርጎታል። ተከዜና ራማ፥ ሌሎች ወንዞችም በወለጋና በሐረር እንዲሁ መሬቱን እየለረለሩ፥ እስከ ልውጠ አለቱ ድረስ ያሉትን አለቶች ገላልጠዋቸዋል።

የተጠቀሰው ነፍሳማ የተፈጥሮ እንቅስቃሴ እንዳለ ሆኖ፥ አህጉራትን በመከፋፈል የታወቀው የከርሰ ምድር እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ምድር ሰነጠቃት - ለሁለት ከፈላትና፥ በፊት ያልነበራትን ስምጥ ሸለቆ የተባለ ረባዳ መሬት ከፈተላት።

በባህረ ኤርትራና በኤደን በኩል ወደ አፋር ውስጥ የገባው የመሬት ክፍተት (ስንጥቅ) ወደ ደቡብ እስከ ሲዳሞ - ከዛም አልፎ - አገር አቋርጦ፥ ወደ ኬንያና ሞዛምቢክ ተሻገረ። ባህረ ኤርትራን እንደ ግርግዳ መከቶ የያዘ የደንከል ተራራ ባይኖር ኖሮ የባህር ውሃ ወደ ረባዳው (ከባህር ከፍታ በታች ወደሆነው) ወደ ዳሎል ይገባ ነበር።

ወጣት እሳተ ገሞራዎች ከሰሜን ምሥራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በረድፍ በረድፍ ተሰልፈው እነ አሰቦት፥ አየሉ፥ ዝቋላ፥...ወዘተ...የተባሉ በስምጥ ሸለቆ የታወቁ ተራራዎችን ገነቡ።

ከከርሰ ምድር የእሳተ ገሞራው ሲያንቀላፋ፥ አልፎ አልፎም ሲገነፍልበትና ሲገላበጥ፤ መሬትን ሲያንቀጠቅጥ፥ ሲሰነጥቅ፥ የስምጥ ሸለቆ ነፍሳማ መሬት ሆኗል። አሁንም በዳሎል አካባቢ - በኤርታሌ እሳተ ገሞራዎች እሳት ወለድ አለቶችን፥ ማእድናትን፥ ፍል ውሃዎችንም እየተፉ ናቸው። ከጨውና ከድኝ (sulphur) ጋር በመዋሃድ፥ የፍል ውሃ እየተፍለቀለቀ ይፈሳል፤ እየተነነም ይጨሳል።

## የክፍለ አህጉራት እንቅስቃሴ

ክፍለ አህጉራትን ከገነቡ ከደረቅ ቆዳ መሬቶች ሥር፥ ባህርንም ከተሸከሙ ደረቅ ቆዳ መሬቶች በታች - ምድር አሁንም ዙሪያዋን በከፊል ፈሳሽ ናት - ከጉያዋ - ከከርሷ። ስለዚህ፥ ዛሬ የምናያቸው ክፍላተ አህጉራት ሁሉ እንዲሁም ከባህር በታች ያለው ጠጣር ቆዳ መሬት፥ በከፊል ፈሳሽ በሆነው አለት (mantle) ላይ እንደ መርከብ የተንሳፈፉ ስለሆነ፥ የሚገፉቸው ኃይል ሲመጣባቸው ይገፋሉ።

ክፍላተ አህጉራት ከሥራቸው አዲስ የውቂያኖስ መደብን በሚከፍቱ (ocean floor spreading) ውስጣዊ ኃይላት ካለማቋረጥ ሲገፉ - ሲገፉ፥ ከጊዜ ብዛት ቀደም ሲል የነበሩበትን ቦታ እየለቀቁ ይሄዳሉ። እነኚህ ውስጣዊ ኃይላት ያልናቸው፥ ከመሬት መንቀጥቀጥና መሰንጠቅ፥ ከከርሰ ምድር ከሚነሱ ከእሳተ ገሞራዎችም ጋርም ጋር የተያያዙ ናቸው።

ከታች አዲስ መሬት በእሳተ ገሞራ እየተገፋ ወደ ምድር ቆዳ መሬት ከፈፍ ሲመጣ፥ ከባህር በታች ያለውን ቆዳ መሬትም ሰንጥቆ ሲወጣ፥ አስቀድሞ የነበረው ቆዳ መሬት የግድ ላዲሱ መሬት ቦታ መልቀቅ አለበት። ስለዚህ በተጠቀሱት የውስጥ ኃይላት ምክንያት ግፊት ከመሬት ከርስ ወደላይና ወደጎን ሲመጣ ክፍላተ አህጉራት የግድ መገፋት ነበረባቸው። እነርሱ እንደመርከብ ከፊል ፈሳሽ በሆነው ላይ የተንሳፈፉ በመሆናቸው፥ እየተገፉ - እየሄዱ - እየተንሸራሸሩ ቆይተዋል።

የስምጥ ሸለቆ (rift valley) አመሰራረት በግላጭ በኢትዮጵያ ምድር ቢታይም፥ ኢያሌ የስምጥ ሸለቆዎች ከባህር በታችም አሉ። ይህ የአትላንቲክ ውቂያኖስ ብለን የምንጠራው፥ አፍሪካን እና አሜሪካንን ያለያየ፥ ልክ እንደ ኢትዮጵያ የስምጥ ሸለቆ ከጊዜ በኋላ የተፈጠረ ነው። በስምጥ ሸለቆ መከፈት ሐረርጌና ሸዋ እንደተለያዩ ሁሉ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ መከፈት ምክንያት አሜሪካና አፍሪካ ተለያዩ።

በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ፥ ወጣት እሳተ ገሞራዎች ታላላቅ ተራራዎችን እንደ ገነቡ ሁሉ፥ በአትላንቲክ ውቂያኖስም እንዲሁ ከሰሜን እስከ ደቡብ፥ መሃል መሃሉን፥ በረድፍ በረድፍ ተሰልፈው፥ የባህር ውስጥ የተራራ ሰንሰለትን (the Mid Oceanic Ridges) መሥርተዋል። አይስላንድ የተባለችዋ አገር በዚሁ አይነት ከባህር በታች ተፈጥራ በቁመት ከሌሎቹ በልጣ ከባህር ብቅ ብላ ስለተገኘች ነው ታላቅ ደሴት ሆና፥ አገር ለመሆን የበቃችው። እንዲሁም በተመሳሳይ ከባህር ውስጥ ብቅ ብለው ስለታዩ ደሴት ለመባል የበቁ ኢያሌ ናቸው።

አንድ የመሬት አካል በከፍታ (vertically) ወደ ላይ ልደግ ቢል፥ ወሰን ድንበር የለበትም፥ ግን አግድሞሽ (horizontaly) ልደግ ቢል ከጎኑ ያለ ሌላ የመሬት

አካል (ክፍለ ሃገር) በቀላሉ አይገፋለትም። አዲስ የባህር መደብ ሲከፈት ነባር የባህር መደብ የግድ መጥፋት (መጨፍለቅ ወይም እራሱን ማሳነስ) አለበት።

ግማሽ ፈሳሽ በሆነው ላይ የተንሳፈፈ ቆዳ መሬት ሲገፋ፥ በተገፋበት አቅጣጫ ጠጣሩ መሬት ሲያጋጥመውና አልገፋ ሲለው፥ ያለው አማራጭ፥ ለስለስ ወደሚለው ወደታች መደፋት (መስረግ) ስለሆነ፥ ከክፍለ አህጉራት ሥር ሰቅስቆ ይገባል - ራሱን ይደፋል (subduction)።

በዚህን ጊዜ፥ ከጠጣሩ መሬት ሥር ተሽካሚ ሰቅስቆ ሲገባ፥ ከላይ ያለው መሬት ሁሉ፥ ልክ እንኮኮ እንዳስቀመጡት ልጅ፥ ወደላይ ከፍ ይላል። ወይንም (እንዲሁም) የመሬት መዛባት ይፈጠርና ለእሳተ ገሞራ መፈንዳት እድል ይሰጣል። በዚህን ጊዜ፥ የመሬት መንቀጥቀጥና የባህር ውሃም መሬትን ማጥለቅለቅ (ሱናሜ) ሊከተል ይችላል።

አለቶች እንደ ፈሳሽ በስንጥቆች እየወጡ ሲከመሩ፥ ወደላይ ብቻ ለማደግ የተፈቀደለት መሬት ቀስ በቀስ ከፍ ከፍ ሲል፥ በዚህ አይነት መንገድ ነው፥ በአለም ዙሪያ ዛሬ የምናያቸው ታላላቅ የተራራ ሰንሰለቶች (ሂማላያ፥ አልፕስ፥ ሮኪ፥ አንደስ ...ወዘተ..) ሰማይ ጠቀስ መስለው የሚታዩት።

በጣም ይገርማል፤ ከሂማላያ የሚበላልጡ ተራራዎችም በውቂያኖስ ውስጥ ከውሃ በታች ይገኛሉ። ደግሞም፥ ከአባይ ሸለቆና ከግራንድ ካንዮን የሚበላልጡ ሸለቆዎቸም በውቂያኖስ ውስጥ ከውሃ በታች አሉ።

በስነ ምድር ምርምር ስለ ክፍላተ አህጉራት የማያቋርጥ እንቅስቃሴና ሂደት ያቀረብነው የብዙ ጂኦሎጂ ጥናቶች ውጤት ነው። ትክክል ስለመሆኑም በጠቀስናቸው ሁለት አበይት እንቅስቃሴዎች (የመሬት መከፈትና መጨፍለቅ) የተነሳ የእሳተ ገሞራዎችና የመሬት መንቀጥቀጥ በየጊዜው የሚካሄድ መሆኑ እንደ አንድ ማረጋገጫ መቁጠር ይቻላል።

እነኚህ እንቅስቃሴዎች ሲፈጸሙ በሚታዩበት ሥፍራዎች ሁሉ (ኢትዮጵያ፥ አይስላንድ፥ ጃፓን፥ ኢንዶኖዢያ፥ ኢራን፥ ፓኪስታን፥ ጣሊያን፥ ምዕራባዊ ደቡብ አሜሪካ ወዘተ..) እሳተ ገሞራዎችና የመሬት መንቀጥቀጥ የሚበዛ መሆኑ ሌላ ማረጋገጫ ነው። እስከዛሬ ድረስ እንደነበረው፥ ለወደፊትም በነኚህ ሥፍራዎች አያሌ የምድር እንቅስቃሴ ይካሄዳል፤ በሰዎች ላይም ከባድ ጥቃት ይደርሳል።

የምድር ሙቀት ከምድር ከፈፍ ጀምሮ ወደታች - ወደ ከርሷ እየጨመረ እንደሚሄድ ይታወቃል። ይህ የምድር ሙቀት ለሰው ልጅ የተለያዩ ጥቅሞችን እየሰጠ ነው ያለው። በዚህ የምድር ሙቀት ምክንያት የከርሰ ምድር ውሃ ሞቅ ስለሚል፥ አያሌ የበራድ አገር ሕዝቦች (ለምሳሌ ካናዳ)፥ የቤቶቻቸውን ቅዝቃዜ ለመቀነስ፥

እንዲሁም ተክሎችን ለማሳደግ፥ ሞቅ የሚለውን ውሃ፥ ጥልቅ የውሃ ጉርጓድ ቆፍሮ በማውጣት፥ ሞቃቱን ውሃ በቧንቧ እያመላለሱ ይጠቀሙበታል።

**የምድር ሙቀት ኃይል** (Geothermal energy) እንደ ስምጥ ሸለቆ የመሬት መናወጥ ባለበት ሥፍራ ሁሉ፥ ቆዳ መሬት ሲሰነጠቅና ሲከፈት፥ የስንጥቁ ጥልቀት ከፍተኛ ከሆነ፥ ፈሳሽ የዝናብ ውሃም ሰተት ብሎ፥ እስከ ብዙ ሺህ ሜትር ድረስ ወደታች ይዘልቃል። በዚህን ጊዜ ኃይለኛው የምድር ሙቀት  የከርሰ ምድሩን ውሃ በከፍተኛ ግለት (እስከ 200 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እና ከዛም በላይ) ያፈላዋል። ይኽም ሊሆን የሚችል የፈላው ውሃ ወደላይ ተኖ እንዳይወጣ ከበላዩ አምቆ የሚይዝ የአለቶች ርብርብ እንደ ጥብቅ ክዳን ሆኖ ስለሚያፍነው ነው እንጂ፥ በመሬት ላይ ውሃ ወደ እንፋሎት የሚቀየረው እስከ 100 ዲግሪ ሰንቲግሬድ ባለው ሙቀት ብቻ ነው።

እጅግ ጥልቅ (ሁለት ሺህ ሜትር እና ከዛም በላይ) የውሃ ጉርጓድን በመቆፈር፥ የከርሰ ምድር ፍል ውሃ በአለቶች ርብርብ መታመቅ  ሲቀርለትና ወደ ምድር አየር ሲፈተለክ፥ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ግፊት ነው። ከዚህ ግፊት የሚገኘው ኃይል ነው ተርባይን የሚያዞርና ሞተር የሚቀሰቅስ። ከዚህም ቀጥሎ ነው ከታላላቅ ግድቦች ባላነሰ ከፍተኛ የሙብራት (ኢሌክትሪክ) ኃይል የሚገኘ።

ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው አገሮች ውስጥ (አይስላንድ፥ ጃፓን፥ ኢንዶኖዢያ፥ ኢራን፥ ፓኪስታን፥ ጣሊያን፥ ምዕራባዊ ደቡብ አሜሪካ ወዘተ..)፥ ጥልቅ ጉርጓዶችን በመቆፈርና በከፍተኛ ግለት ታምቆ የቆየውን ፍል ውሃ እያወጡ፥ ለኢሌክትሪክ ማመንጫነት ይጠቀሙበታል።

በኢትዮጵያችንም ይህ የተፈጥሮ ሃብት በስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች ሁሉ ሊኖር እንደሚችል፥ አያሌ ጥናቶች ተገባደዋል። በጥናቱም መሠረት፥ በተለይ የተንዳሆ እና የላንጋኖ አካባቢዎች በእጩነት ከተቀመጡ ቆይተዋል። እኛ ግን፥ ፍል ውሃ መሬት ድረስ መጥቶ ሲፈስልን ነው እንጂ፥ የተደበቀውን የተፈጥሮ ሃብት በተለያዩ ምክንያቶች ሳንጠቀምበት ቆይተናል (ምናልባት ወደፊት)።

## <u>**የምድር አየር**</u>

ከጥንት ጀምሮ የምድር አየር እየተለዋወጠ፥ በዚህም ምክንያት ፍጥረታት እየጠፉ፥ ከቦታ ቦታም እየተሰደዱ ቆይተዋል። ስለ ምድራችን የምንነጋገረው ሁሉ (ሕይወት ያለውም የሌለውም) ከምድር የአየር ለውጥ ጋር የተያያዘ ነው።

ባሁኑ ጊዜ የምድር አየር ተለወጠ ብለው መንግሥታት ይንጫጫሉ፤ እኛ በበኩላችን ምን እናድርግ ብለው ተጨንቀዋል፤ ነገር ግን ይህች ነፍሳማ ምድር ምን አስባ ይሆን? ብለው አይጠይቁም።

እኛ ምን ማድረግ እንደምንችል ምድሪቷ ታውቃለች፤ እርሷ ያሰበችው ካለ፥ የሰው ልጅ ምንም ቢፍጨረጨር ምንም ማድረግ አይችልም። ለዚህ ነው ድርቅ ያለ ሳይንስ ላይ ሙጭጭ ከማለት፥ ወደ መንፈስ ጉዳይ በመግባት ጠለቅ ብሎ መፈላሰፍ የሚያስፈልግ።

ምድር ምን አሰበች በእውነት በኛ ላይ ጨከነች?

እስካሁን ያቆየችን፥ እኛ ለሷ ሳናስብ፥ እሷ ለኛ እያሰበች፤

አሁን ምን ነካትና ነው ትእግስቷንና እንክብካቤዋን የቀነሰች፤

ሰዎች በጢስ አጠኗት? ከመጣችበት ሊመልሷት!

አፈኗት? መተንፈስ እስኪያቅታት!

ፈሳሽ ውሃዋና አየሯ እስኪሞቅባት፥

በረዶው ከዋልታዋ እስኪቀልጠባት።

የባህር ከፍታ ሲጨምር፥ የብዙሐን ሕይወት እንዳያጥር፥

ይህንን እያሰበ የአለም ሕዝብ እንዳይቸገር፥

ጥሩውን በመንፈሳዊነት አብረን እናስብ ከምድር ጋር፤

ጥሩውን በመንፈሳዊነት አብረን እናስብ ከምድር ጋር።

## ድንቅ ሥራ - ከሕይወት አልባ እስከ ባለ ሕይወት

ሁኔታው አስቀድሞ ሳይስተካከልለት የሚፈጠር ምንም ነገር የለም ማለታችን ሕይወት ላላቸው ብቻ አይደለም፤ ለሌላቸውም ነው እንጂ። ለምሳሌ፡- እንደ ጃስፐር፥ ክሪሶሊት፥ አጋት፥ ኦፓልና የመሳሰሉ ለቀለበት ፈርጥ በመሆን የሚያገለግሉ በከፊል የከበሩ (semi-precious) ማዕድናት በተለያዩ ሥፍራዎች እንደ ተራ ድንጋይ ወዳድቀው ይገኛሉ። እንዲህ ነው አፈጣጠራቸው፡-

ውሃ ስንጥቅ አግኝቶ እጅግ ሙቅ ወደ ሆነው ወደ ምድር ከርስ ሲጓዝ፥ ወደ እንፋሎትነት ይለወጥና እንደገና ስንጥቅ ሲያገኝ፥ ተመልሶ ወደ መሬት ከፊፍ በትነት መልክ ይወጣል። ነገር ግን፥ እንፋሎቱ ቶሎ ወደመሬት ተመልሶ የሚወጣበት ሁኔታ ካላጋጠመው፥ እዛው በዙሪያው ያለውን አለት በሙቀትና በግፊት እያሻሸው ይቆያል።

ከጊዜ ብዛት፥ ማዕድናቱ (minerals) በእንፋሎቱ መተሻሸቱ ሲበዛባቸው፥ ከውሃው ጋር ውህደትን ይፈጥራሉ (ይሟሟሉ)። በማዕድኑ ውስጥ የሚገኙ ንጥረ ነገሮችም (elements) ከውሃው ጋር በመዋሃድ ወዲያ ወዲህ ሲነሸራሸሩ፥ የተለያዩ ቀለሞቻቸው በረድፍ በረድፍ ይነጠፋሉ።

ከጊዜ ብዛት እንደ ፈሳሽ የሆነው ይረጋል፤ ከመሬት ውስጥ የነበረውም እየተሸራረፈ ይወድቃል። እነኚህም እንደ ተራ ድንጋይ በያለበት ወዳድቀው የምናያቸው በመዶሻ ሲሰበሩና ውስጣቸው ሲታይ፥ የተለያዩ ህብረ ቀለማት ያላቸው፥ የብዙ ጊዜ የተፈጥሮ ሥራ የሆኑና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ናቸው። ሕይወት በሌላቸው ዘንድ እንዲህ እና የመሳሰሉ ብዙ ድንቅ - ድንቅ ሥራዎች ይሠራሉ።

በሕያዋን ዘንድም፥ ድንቅ ሥራ ይሠራል። ለምሳሌ፥ በባህር ውስጥ የተለያዩ ጥቃቅን እንስሳት ለኛ ጌጥ የሚሆን ቤታቸውን ሲሠሩ እጅግ ርቅቅ ባለ መንገድ - በማዕድናት ደረጃ ነው።

በመሬት ላይም፥ ለምሳሌ ተርቦች[29] ቤታቸውን ሲሠሩ፥ ሴቶቹ በሚፈለፍሉት እንቁላል ነው። የእኛ ቤት አሰራር ግን ድንጋይ በመጥረብ ስለሆነ፥ ምንም ቢሆን የእንስሳቱን ያህል ረቂቅና ቆንጆ አይሆንም።

እግዚአብሔር ፍጥረትን በቅደም ተከተል እያስተካከለ ፈጠረ እንጂ፥ እንዲሁ ካለ ቅደም ተከተል - በዘፈቀደ አይደለም። የእግዚአብሔር ሥራ ከሰው ሥራ የሚለየው እንዲህ ነው፡-

በእግዚአብሔር ሥራ የተገኙ ሁሉ፥ በውስጣቸው ማርጀትና መሞት ቢኖርባቸውም፥ መጨረሻ ግባቸው ለአዲስ ፍጥረትና መወለድ ያዘጋጃቸዋል (ትውልድ በትውልድ ይተካል)። ሰው ግን አንዴ የሠራው ሥራ ሲሞት ይሞታል። ለምሳሌ፡- አንድ አናጺ እንጨት ጠርቦ፥ የሚሠራቸው ወንበሮች፥ ሳጥኖች፥ ወዘተ.. ሁሉም አርጅተው ሲሞቱ፥ ያ የመጨረሻቸው ይሆናል እንጂ፥ ከውስጣቸው የሚወጣ ሌላ ምንም ነገር አይኖርም።

የጥቃቅን ነፍሳትን (ጉንዳኖችን፥ ሸረሪቶችን፥ ንቦችን.. ወዘተ..) ኑሮ እየተመለከትን እናደንቃለን፤ ሕይወት አልባ የሆኑትም እንዲሁ የሚደነቁ ናቸው። ሁሉም የእግዚአብሔር ሥራ ዕጹብ ድንቅ እንደሆነ ነው የሚያሳየው።

"ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፤ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ .." ዮሐ. ራዕ. 15፡3

[29] ተርብ - wasp

## ምድራችን እና ሕይወታችን

ምድራችንን ዞረን እንመልከታት። አረጀች እንዴ? መጨረሻዋ ተጀመረባት ወይ? የመጨረሻዋስ መጨረሻ የሚሆነው መቼ ነው? ይህንን ጥያቄ ሳይንስ ብቻውን፥ የሃይማኖት ትምህርትም ብቻውን ችሎ የሚመልሰው አይደለም።

አካላዊ ሁሉ መጀመሪያ እንደሚኖረው መጨረሻም ይኖረዋል። ሕፃን ሲወለድ ባንዴ ነው፤ አድጎ ተመንድጎ፥ አርጅቶም ሲሞትም አንዴ ነው። ግን በድንገት ካልተቀጨ በስተቀር ሰው ሲያድግ ሲመነደግ፥ በውስጡ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን አካሂዶ ነው፣ ወደ ሞትም ሲሸጋገር እንዲሁ ነው፤ (መኖርን ከሞት ጋር ይዘን ነው የምንኖረው)።

እንዲህ ሰፊ ሆኖ የሚታይ ጠፈራችን በውስጡ የተለያዩ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን አካሂዶ ነው ከዚህ የደረሰው። ጠፈር ሊሞት ሲልም/ጉዞውን ወደሞት ሲያመራ ፥ እንዲሁ በውስጡ የተለያዩ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን ማካሄዱ አይቀርም፤ ጠፈርም መኖርን ከሞት ጋር ይዞ ነው የሚጓዘው። ታዲያ፥ ሰው ሲያረጅ ወደሞት እንደተቃረበ (ከእርጅና ምልክቶቹ) ካወቅን ዘንዳ፥ ምድራችንም ወደሞት እንደተቃረበች የሚነግሩን ምልክቶች ይኖራሉ።

ምድራችንም በእግዚአብሔር የተጀመረላት መጀመሪያዋ እርሱ በቃ እስከሚል ድረስ ይቀጥላል። መቼ ነው በቃ የሚለው -- የምድር መጨረሻዋ የሚጀመረው? ሰው ቢያረጅ (ቢሸብት፥ ቆዳውም ቢኮማተር)፥ ወደ መጨረሻው መቃረቡ እስኪገባው ድረስ ብዙ ይኖራል። ታዲያ በዚሁ ረገድ፥ በስነ ምድር ምርምር፥ "ልውጠ አለቶች ተለዋውጠው፥ ዝቅጠ አለቶችም ዘቅጠው፥ የሚቀልጡ አለቶችም ቀልጠው፤......... በምድራችን ላይ መሠራት ያለበት ሁሉ ተሠርቶ አልቋል ወይ?" ብሎ በመጠየቅ ብዙ የምንገነዘበው ነገር ይኖር ይሆናል።

ለምሳሌ፥ በምድር ላይ በተለያየ ሥፍራ በእሳተ ገሞራ የተተፉትንና በባህር የዘቀጡትን አለቶች በቅደም ተከተል ከነእድሜአቸው ተመልክተን፥ እነኚህ የጂኦሎጂ ክንውኖች መዳከማቸውን ወይንም ማብቃታቸውን በመመርመር፥ ይህች ምድር የህጻንነት እና የጉርምስና ጊዜዋን አገባድዳ ወደ ሽምግልና ዕድሜዋ መግባት አለመግባቷን መገመት እንችል ይሆናል። ይህን ካደረግን በኋላ፥ የምድር ሕልውና የሚካተተው በምድር በራሷ ሥራ መሆኑን/አለመሆኑን ከግምታችን ውስጥ እናስገባዋለን።

ሰው ሲያረጅ እንቅስቃሴው እንደሚቀንስ ሁሉ፥ የተጠቀሱትን የጆኦሎጂ ክንውኖች በመመልከት፥ ይህች ምድር ወደ እርጅናዋ የተቃረበች ይመስል ይሆናል። ግን ምድር ብታረጅም፥ የእርጅናዋ ክስተት ቀስተኛ ይሆናል (አርጅታም ብዙ ልትቆይ

ትችላለች)። መጨረሻዋ ተጀምሮ ሲቀጥል (ወደ መጨረሻዋ ስትገሰግስ)፥ ምድር አንድ ቀን መጨረሻዋ ሲሆን፥ ምናልባት የዛን ጊዜ የአካላዊነትም መጨረሻ ይሆናል ማለትም ይቻላል።

ግን ያን ያህል ራቅ ብለን ከመሄዳችን በፊት፥ “ምድርን በራሷ ብቻ (ካለ ጸሐይና ሌሎች የጠፈር አካሎች) መመልከት ይበቃል ወይ?” ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ምድር አንድ የሰማይ አካል እንደመሆኗ መጠን፥ መጨረሻዋ የሚካተተው፥ ከሌሎች የሰማይ አካላት ጋር ስለሚሆን፥ አብዛኛዎቹ ከዋክብት ሲከስሙ፥ የጸሐይም ብርሃንና ሙቀት ሲጠፉ፤ የዛን ጊዜ የምድራችን መጨረሻ ይሆናል።

ምድር እንዴ ተፈጥራለችና፤ እንዴ ትጠፋለች። በላይዋ የነበሩና አሁንም ያሉ ሕያዋን ሁሉ ደግመው ደጋግመው ሲፈጠሩና ሲጠፉ - በመፈጠርና በመጥፋት መካከልም በመለዋወጥ አዲስ ፍጥረት እየተተካ ከዚህ ደረሰናል። ካሁን በኋላም፥ በጠፈር ውስጥ የሚከናወኑት፥ በኛ ምድር - በከርሷ ውስጥና በላይዋ ከሚከናወኑት ታላላቅ ሁኔታዎች ሁሉ ጋር በአንድ አቅጣጫ ሲነጽሩ፥ የአካላዊነታችን መጨረሻ የሚሆንበት ወቅት መቃረቡን ይረጋገጣል።

የምድርን እድሜና የጂኦሎጂ ክንውን (ከጸሐይና ከሌሎች ጠፈራዊ አካላት ጋር) በጂኦሎጂ ጊዜ አቆጣጠር (በሚሊዮንና በቢሊዎን ዓመታት) እንደምንቆጥር፤ የአካላዊነትም መጨረሻ ቅርብ አለመሆኑን እንገነዘባለን። ግን እግዚአብሔር ከፈለገ፥ የተፈጥሮን ሕግ ሊለውጥ ይችላል፤ እርሱ ከፈለገም፥ ይህ መጽሐፍ ተነቦ ሳያልቅ የአካላዊነት መጥፊያውን ሊያቀርበው ይችላል።

በተፈጥሮ ምክንያት የሚመጣውን አደጋ ለመከላከል የሚያስችለው የሰው አቅም ትንሽ ነው። ተፈጥሮ አስቦ በራሱ ሁሉንም ያስተካከላል። እኛ ግን ከሶዶምና ገሞራ፥ ከመተሃራ እና ሌሎችም ተፈጥሮአዊ አደጋ ከተፈጠረባቸው ሥፍራዎች ታሪክ ተምረን የበኩላችንን ማድረግ ይጠበቅብናል።

ምድራችን ለኛ የሚያስፈልገውን ሥርታ አብቅታለች ማለት ይቻላል። የወርቅ፥ የብረትና የመዳብ ክምችት፥ ካርቦንም ባንድ በኩል ተንሸራሽሮ ጋዝና ዘይት አስገኝቷል።

# ምዕራፍ አምስት

## ምድራዊ አካላዊ ሕያዋን

እግዚአብሔር ሁሉ ሥፍራ ይገኛል ስንል፥ የርሱ ፍቃድ ሁሉም ሥፍራ አለ ማለታችን ነውና፤ የተፈጥሮና የፍጥረታት ሁሉ እንቅስቃሴ (ወይንም ክስተት) በተደነገገላቸው የተፈጥሮ ሕግ ክልል ውስጥ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ካለማቋረጥ ይካሄዳል ማለት ነው። ይህንን ክስተት በማጤን ነው የእግዚአብሔርን ኃያልነት በደንብ የምንረዳው።

በእግዚብሔር ፈቃድ የተጀመረው ፍጥረት እርሱ በቃ እስኪል ድረስ መቋረጥ ስለማይችል፥ ቀስ በቀስ፥ በየብስና በባህር ብዙ ምግብ ተዘጋጀ። ያንን ምግብ እየተመገቡ የባህርና የየብስ ፍጡራን ተበራከቱ። ሕይወት እየተራባ መጣ። የውሃ እንስሳት ተፈጠሩ፤ የተለያዩ ተክልና እንስሳት ተፈጠሩ። በአየር ላይ የሚበሩ ትንኞች ተፈጠሩ። እንስሳትም በብዛትና፥ በአይነት ብቻ ሳይሆን "በጥራትም" ጭምር የኋለኞቹ ከበፊተኞቹ "እየተሻሻሉ" መጡ፤ ሕይወት እየተበራከተ ምድራችንን ነፍሳማ አደረጋት።

ፍጥረታት አካላዊ ሕያው ለመሆንና ለመኖር ብዙ ምግብ ከማያስፈልጋቸው ተጀመረና ወደ ሆዳሞቹ ቀጠለ። ሕያው ከዝቅተኛ የሕይወት ሕዋሳት (ሴሎች) እንዲጀመር ሆነና፥ በየብስም በባህርም ይህንን ተዘጋጅቶ የቀረበ ምግብ እየተመገቡና እየተለቁ፤ መኖርን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ በሚያስችል የመራባት የተፈጥሮ ጠባይ እየተባዙ ተበራከቱ።

የተለያዩ እጽዋት እና እንስሳት ተባዙ ። ፍጥረታት በግምት ከዛሬ አምስት መቶ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ ሲበዙና ሲባዙ እንደነበር፤ እስከዚህ ድረስ በሳይንሳዊ እውቀታችን በመጠኑ እርግጠኞች ሆነናል።

"እግዚአብሔርም አለ፡- ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደወገኑ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ።" ዘፍ. 1፡24

እስካሁን የተነጋገርንበትን በተመለከተ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በእጃቸው ጨብጠው ጂኦሎጂ ከሚያስተምሩ ፕሮፌሰሮች፡- "እርሱ ብሎአልና ሆኑም፤ እርሱ አዝዞአልና ተፈጠሩም፤..." መዝ.148፡5 የሚለውን ጥቅስ ለተማሪዎቻቸው

“እያመሳሰሉ” ቢያስተምሩ፥ ሳይንሱን አላወገዱትም፤ ወይንም የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ካለቦታው አልተጠቀሙበትም። ሳይንሳዊ እውቀት ከሃይማኖት (እምነት) ጋር ሳይጣላ መዝለቅ የተቻለበት ዘመን ውስጥ መሆናችንን የተገነዘቡ ብዙዎች ናቸው።

ስለ አካላዊ ሕያዋን በምድር መባዛት ጉዳይ በሳይንስ አያሌ መላ ምቶች ቢቀርቡም፥ እስከዛሬ ድረስ ትክክለኛውን ያወቀ የለም። እኛ ግን ሳይንስ ያስገኛቸውን እውነቶች በመመርኮዝ፥ “እግዚአብሔር የተከለው የሕይወት ዛፍ ባለ ብዙ ቅርንጫፍ ሆነና ከዚህ ደረሰ፤” ከሚል ጽንሰ ሃሳብና እምነት እንነሳለን። ምንጊዜም በሳይንስ ያልተደረሰበትንም ለማወቅ የሚያስችል መነሻችን እምነታችን እንዲሆን ፈቅደን፥ ያወቅነውን ያህል በስነአመክንዮ እያገናኘን እንቀጥላለን።

## <u>ከቅሪተ አካላት የሚገኙ መረጃዎች</u>

አካላዊ ሕያዋን እንዴት በምድር (በየብስና በባህር) እንደተፈጠሩና እንደተባዙ በጊዜ ውስጥ ወደ ኋላ ተጉዘን መመርመር ይኖርብናል። እኛ ያለነው አሁን ነው፤ መረጃዎቻችንም አርጅተዋል (ተለዋውጠዋል)። ሆኖም፥ ወደኋላ ለመመለስና እውነቱን ለማየት የምንጠቀምበት የእውቀት መሳሪያችን በሳይንስ ብዙ እና ጥልቅ ናቸውና፤ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ከተገኙት መረጃዎች እንነሳለን።

ዛሬ እንደምናየው ሁሉ፥ ሕዋሳት በሚሞቱበት ወቅት፥ ባካባቢያቸው በሚገኘው አፈር ይሸፈናሉ። አፈሩም ከጊዜ በኋላ ወደ ዝቅጠ አለት ይለወጣል። በዚህን ጊዜ፥ የተለያዩ የሕዋሳት አካል በዝቅጠ አለት ውስጥ ተከማችተው ይገኛሉ። ይህ ክምችት ቅሪተ አካል ይባላል፤ ከአካላዊ ሕያው ነፍሱ ሲወጣለት፥ በመሬት የሚቀረው አካል ካካባቢው አፈር ጋር ተዋህዶ በጠጣርነት የቀድሞ መልኩን ይዞ ቀርቷልና።

በአይናችን ከምናየው ቅሪተ አካል፥ የፍጥረታትን የአፈጣጠር ቅደም ተከተል በዝቅጠ አለቶቹ ንብብሮሽ በመመልከት (sedimentology)፥ ከታች ሆኖ የተገኘውን እላይ ካለው ያረጃል እያልን፥ ሌሎችም የስነምድር ምርምር እውቀቶችን (paleontology and structural geology) በመጠቀም ለቅሪተ አካላት የአፈጣጠር ቅደም ተከተል አወጣንላቸው። እድሜአቸውንም ጊዜው ባፈራው መሳሪያ በመጠቀም፥ በድንጋዮች ውስጥ ከሚገኝ የካርቦን ርዝራዥ ($^{14}C$) መጠን ለመገመት ያህል በቅተናል። በዚሁም መሠረት፥ ከጥቃቅን ሕዋሳት ጀምሮ እስከ ትላልቅ እንስሳት

እስከተገኙበት ድረስ ያለው ጊዜ በብዙ ሺህ ብቻ ሳይሆን፥ በብዙ መቶ ሚሊዮን ዓመታት የሚገመት መሆኑን አረጋገጥን።

በዘቀጡ አለቶች ውስጥ የሚገኙ አካለ ቅሪታት አንድ የጋራ ጠባይ ይታይባቸዋል። ይኸውም፦ ባጠቃላይ፥ ዝቅተኛ ዕድሜ ባላቸው ዝቅጠ አለቶች ውስጥ የተገኙት ቅሪተ አካላት፥ ከፍተኛ ዕድሜ ካላቸው ዝቅጠ አለቶች ውስጥ ከተገኙት ቅሪተ አካላት በአካል መጠን ይበላልጣሉ። አንዳንድ ጊዜም በብዛት ይበልጣሉ። ባጠቃላይ የሰውነት ቅርጽ፥ ቁመና፥ እና ሌሎችም አካላዊ መግለጫዎች መሠረት፥ ጥንት ከተፈጠሩት ይልቅ በኋላ የተፈጠሩት "የረቀቁ ናቸው - ይሻላሉ" ማለት ተለምዷል። ግን ይህ በተቃራኒውም የሆነበትም ጊዜ ይኖራል፤ ምድሪቱ ሲመቻትና ምግብ በብዛት ስታመርት፥ ወይንም በተለያዩ ምክንያቶች ምግብ ሲጎልባት፥ በዛው መጠን የምድራዊ ሕያዋንም የይዘት መጠንና ብዛት ይለዋወጣልና።

"እንስሳት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በዝግመተ ለውጥ እራሳቸውን በመጠንና በጥራት "እያሻሻሉ" ስለመጡ፥ በኋላ የተገኙት እንስሳት ሁሉ አስቀድሞ ከነበሩት "የወጡ" (የተፈጠሩ ሳይሆን የተገኙ) ናቸው የሚል አመለካከት ከተዛባ ስነአመክንዮ የመነጨ መሆኑን በሚከተሉት ምዕራፋት እንመለከታለን።

በመሠረቱ፥ የተጠቀሰው የተዛባ ስነአመክንዮ ከሚከተለው የጂኦሎጂ የንብብሮሽ ሕግ (law of superposition) በመነሳት የተገኘ ይመሳሰላል፦ አንድ ዝቅጠ አለት በሌላው ላይ ተደርቦ ከታየ፥ እና ያም ዝቅጠ አለት ከቦታው ካልተገለበጠ፥ በዛ ሥፍራ ተደርቦ የሚታየው ዝቅጠ አለት ከሥሩ ካለው ዝቅጠ አለት በእድሜ አነስተኛ መሆን አለበት። ስለዚህ፥ በምድራዊ ኃይል ሳይገለበጥ፥ ከላይ በተቀመጠ ዝቅጠ አለት ውስጥ የሚገኙ ቅሪተ አካላትም እድሜ ከበታች ካለው ዝቅጠ አለት ውስጥ ከሚገኙ አካለ ቅሪታት እድሜ ያንሳል። (ይህም፥ እጄን ከጠረበዛው ላይ ባውለው፥ እጄ በጠረቤዛው ላይ ከማረፉ በፊት ጠረቤዛው ነበር እንደማለት ይቆጠራል)።

ከዚህ የንብብሮሽ ሕግ በመነሳት (ሌላ ሳይንሳዊ መረጃ ሳይታከልበት)፥ "ከላይ ያሉት አካለ ቅሪታት አመጣጣቸውም በአዲስ ተፈጥሮ ሳይሆን፥ በሥራቸው ካሉት በጊዜ ውስጥ ቀስ በቀስ በመለወጥ ነው።" ብሎ መደምደም ፍጹም ሳይንሳዊ ስላልሆነ፥ ይህንን በሚከተሉት ምዕራፋት እንመለከታለን።

## የእልቂት ዘመናት

የእልቂት ዘመናት መኖራቸውን በዝቅጠ አለቶች ከተገኙ አካለ ቅሪቶች መብዛት እና ማነስ (ወይንም ጥፍት ማለት) መገመት ይቻላል። በአንድ የተወሰነ የዘመን ክልል ውስጥ፥ በዘቀጡ አለቶች ውስጥ በብዛት ተከማችተው የሚገኙ ቅሪተ አካላት በሌላ ዘመን ውስጥ በዘቀጡ አለቶች ውስጥ ጥፍት ሲሉ፥ ይህ የእልቂት (extinction) ዘመናት ስለ መኖራቸው አንዱ የምንገነዘብበት ምልክት ነው። የአካላዊ ሕያዋንን መበራከት፥ ከሚፈጥሩ ሁኔታዎች አኳያ፥ መጥፊያቸውም እንደነበረላቸው የእልቂት ዘመናት ይመሰክራሉ። ታዋቂ በሆኑት የእልቂት ዘመናት ውስጥ አያሌ የመሬትና የባህር እንስሳት አልቀዋል። ይህም የሆነው፡-

- የዛሬ አምስት መቶ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥
- የዛሬ አራት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥
- የዛሬ ሦስት መቶ ስልሳ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥
- የዛሬ ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥
- የዛሬ ሁለት መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥
- የዛሬ መቶ አርባ አራት ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥
- የዛሬ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ እና
- የዛሬ ሰላሳ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ ነበር።

የባህርና የመሬት እንስሳት እንዲያልቁ የሚያደርግ አቢይ ተፈጥሮአዊ አደጋ መፈጸም ነበረበት። ይህም አደጋ፥ በአየር ለውጥ (ቅዝቃዜ ወይም እጅግ ከፍተኛ ሙቀት)፥ በውሃ ሙላትና ጎርፍ፥ በነፋስ፥ በእሳተ ገሞራዎች ሊከናወን ይችላል። ትላልቅ የጠፈር ደንጋዮች (meteorites) በሚወድቁበት አካባቢ አያሌ ፍጥረታት ይወድማሉ - ለዛ አካባቢ የእልቂት ዘመን ይሆናል ማለት ነው።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፥ በተደጋጋሚ ለሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነ አንዱ የበራድ ዘመን ነበር። በተለያዩ ወቅቶችና በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ፡- ምድር ለጸሐይ ቀረብ ወይም ራቅ የምትልበት ሁኔታ ሲፈጠር)፥ የሙቀት መጠን ከፍና ዝቅ ሲል ቆይቷል። በዚህም ምክንያት፥ ምድራችን ስትቀዘቅዝ በበረዶ እየተሸፈነች፥ ሲሞቃትም በረዶው እየቀለጠና ከፍተኛ የጎርፍ መጥለቅለቅ እየሆነ፥ አያሌ ፍጥረታት ጠፍተዋል። የበራድ ዘመን ከ800 - 600 ሚሊዮን ዓመት፥ ከ350 - 250 ሚሊዮን ዓመት፥ እና የዛሬ 4 ሚሊዮን ዓመት አካባቢ መፈጸሙን ከጂኦሎጂ ጥናት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል።

ግግር በረዶ፥ ከትልቅ አለት እስከ ትንሽ ጠጠር፥ ደቃቅ አፈርና አሸዋ ድረስ ያሉትን፥ ሁሉንም ባንድነት አቅፎ ከቆየ በኋላ፥ ሙቀት ሲያቀልጠው የተሸከመውን ሁሉ ባንድ ላይና አንድ ጊዜ ሲዘረግፈው የሚታየው የዝቅጠ አለት አይነት፥ የተጠቀሱት በራድ ዘመናት በምድር ላይ ስለመከናወናቸው ማመሳከሪያ የጆኦሎጂ መረጃ ነው።[30]

በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ ሌሎች አያሌ ጥቃቅን ወይም መጠነኛ የሙቀትና የቅዝቃዜ ዘመናት ቢኖሩ፥ ባሁኑ ጊዜ መረጃዎቹን ሁሉ አጠናቅሮ ሁሉንም ማወቅ አይቻልም። ሆኖም፥ በቅርብ ጊዜ - ከዛሬ 2 ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ምድሪቱ ለሃያ ጊዜ የሙቀትና የበራድ ዘመናት ማሳለፏን ከተለያዩ አገሮች የተገኙ የጂኦሎጂ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

የመጨረሻው የበራድ ዘመን እስከ የዛሬ አስር ሺህ ዓመታት ድረስ የቆየ እንደነበር ይታወቃል። ከዛ በኋላ ቀለጠ ማለት ነው፤ ግን ከዛን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ያልቀለጠበት ሥፍራ፥ በሰሜን አሜሪካ፥ በግሪንላንድ፥ በሰሜን እና በደቡብ የምድር ዋልታ ይገኛል።

እንስሳት ምን አጠፉ? እንዲህስ ያለው የተፈጥሮ አደጋ ለምን መጣባቸው? የሚለውን ጥያቄ ሳይንስ አይመልሰውም። እኛም ይህንን ጥያቄ ለመመለስ አንቃጣም። ስለ እልቂት ዘመናት ይህንን ያህል ከተነጋገርን፥ ስለ ሕይወት ዘመናት እና ስለ ሕይወት መባዛት ባጭር ባጭሩ እንመለከታለን።

## <u>የሕይወት ዘመናት</u>

ብዙ ቅሪተ አካል የተገኘበት ዘመን፥ ከዛሬ አምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ዓመት ጀምሮ ያለው ነው። ሕይወት በጣም እየተበራከተ የመጣው በዚህ ዘመን ውስጥ ስለሆነ፥ ይህንን ዘመን በሚከተሉት በሦስት ታላላቅ የዘመናት እርከኖች በመከፈል፥ በየዘመናቱ የታዩትን የእንስሳቱን አይነት በሚገባ ማጥናት ተችሏል፡-

- ቀዳማይ ሕይወት (Paleozoic) - ከአምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ዓመት እስከ ሁለት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመት፤

[30] በወንዝና በነፋስ ከሚገፉ የመሬት ላይ ክምችቶች ለየት ብለው የሚታዩ፥ በግግር በረዶ (glaciers) እየተገፉ የተከማቹ ዝቅጠቶች - በረዶ መጥ ድንጋዮች (tillites) ይባላሉ።

- መሐል ሕይወት (Mesozoic) ከሁለት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመት እስከ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዓመት፤
- ደኃራይ ሕይወት (Cenozoic) ከስልሳ ሚሊዮን ዓመት እስከ ዛሬ ድረስ።

ከቀዳማይ ሕይወት በፊት የነበረው ዘመን ፕሪካምብሪያን (Precambrian) ይባላል። ይህ ዘመን መሬት ከተፈጠረች ከ4500 ሚሊዮን ዓመት ጀምሮ እስከ 570 ሚሊዮን ዓመት ድረስ ያለውን ያጠቃልላል። በዚህ ዘመን ውስጥ ከ4500 እስከ 2500 ዓመት ድረስ ያለው ዘመነ አረኪያን (Archean) የተባለው ነው። በዚህ በአርኪያን ዘመን ውስጥ ምንም ሕይወት አልተገኘበትም።

ሕይወት የተጀመረው በሁለተኛው የፕሪካምብሪያን ኢጋማሽ ላይ፥ በዘመነ ፋነሮዞይክ (Phanerozoic)፥ ከዛሬ 2500 ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ እንደነበር ይገመታል።

ከ2500 ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ እስከ አምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ዓመት - እስከ ቀዳማይ ሕይወት (Paleozoic) ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ፥ አካላዊ ሕያዋን እራሳቸውን ቁልጭ ባለ መልክ አላሳዩም ነበር። የዛን ጊዜ አካላዊ ሕያዋን እጅግ ትናንሾች እንደነበሩ ነበሩ ማለት ነው። በእርግጥ ስለመኖራቸውም የተገኘ መረጃ የዛኑ ያህል የፈዘዘ ነው የሚሆን። አካለ ቅሪቶቹ ጥቃቅን እና በቁጥር እጅግ አነስተኛ በመሆናቸው፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረው የስነ ምድር እንቅስቃሴም መረጃዎችን ስለሚለዋውጥ፥ ስለነኚህ ጥቃቅን ቅሪተ አካላት የምናውቀው በጣም የተወሰነ ነው። ሆኖም፥ የቅሪተ አካላቱ በአካል ጥቃቅን መሆን፥ የዛን ጊዜ በባህር ውስጥ የነበረው ምግብ በመጠኑ እንደነበረና ለምግብነት የሚያገለግለውም ለተወሰኑ ሕያዋን ብቻ መሆኑን ያመለክታል።

የዝግመተ ለውጥ (evolution) ተከታዮች የሕይወት ዛፍ (Tree of Life) ብለው የሚጠሩት፥ የዛፉ ሥር፥ ከዚሁ ፕሪካምብሪያን በተባለው ዘመን ኢጋማሽ ላይ በዘመነ ፋነሮዞይክ (Phanerozoic) ነው። ሆኖም፥ ከዛ በፊትም ቢሆን፥ በዘመነ አርኪያን (Archean) ሕይወት ሙሉ ሕይወት ሳይሆን - በግዑዛን አካላትና በሕያው ህዋሶች መካከል እርስ በርስ “እየተዳቀሉ?” የሚባዙ ሞኔራ (monera) የተባሉ እንደ ልጋግ (gel) በየቦታው የሚከመሩ ነበሩ ይላሉ (ይህ ሃሳባዊ እንጂ፥ ተጨባጭ መረጃዎች የለውም)።

ከዚያ ቀጥሎ ሙሉ ሕይወት ያላቸው አሜባዎች ተባዙ የሚሉም አሉ። ስለዚህ የሕይወት ዛፍ ጉዳይ በኋላ (በምዕራፍ ስድስት) በስፋት የምንመለከተው ጉዳይ ስለሆነ፤ ካሁኑ የእንስሳቱን አይነት ልብ እያልን እንለፍ።

ከአካለ ቅሪቶች አይነትና ብዛት፥ ከዝቅጠ አለቶች አይነትና እድሜ፥ የአየር ለውጥን ከሚያመለክቱ ምርምሮች፥ በመሬት ላይ ከወደቁ ታላላቅ የጠፈር ደንጋዮች እና ሌሎችም የጆኦሎጂ ክንውኖች በመነሳት፥ በተጠቀሱት ሦስት አቢይ የሕይወት ዘመናት ስለተፈጸሙ ዋና ዋና ሁኔታዎች እንደሚከተለው መረዳት ተችሏል።

## ቀዳማይ  ሕይወት (Paleozoic)

አካላዊ ሕያዋን ግዙፍ ሆነው በአካልነት ቁልጭ ብለው የተገኙት በቀዳማይ  ሕይወት ዘመን (Paleozoic) ነበር። ከጊዜ በኋላ በባህር ውስጥ ምግብ እየተበራከተ ሲሄድ አካላዊ ሕያዋንም ያንኑ እየበሉ ተለቅ ተለቅ ማለት ጀመሩ።

በመጀመሪያ በባህር በብዛት የተራቡ ብራኪዎፖድ የተባሉት ነበሩ። እነኚህም በጊዜው እጅግ ግዙፋን፥ ግን የወፍ እንቁላል የሚያካክሉ ፍጡራን ናቸው። ቀጥሎም እንደ ቀንድ አውጣ ያሉ፥ ሞሉስካና አሳ የመሳሰሉ ባለ ለስላሳ ሰውነቶች፥ ቀጥሎም ከፍ - ከፍ ያሉ ትሪሎባይት የተባሉ ተፈጥረዋል። ሁሉም ሲበዙና ሲባዙ፥ እየተዳቀሉም ሌሎች በአይነት የሚመሳሏቸውን ፈለፈሉ። እነርሱም ሲበዙና ሲባዙ፥ በባህር ውስጥ ሕይወት ተበራከተ።

ከዛሬ አምስት መቶ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ እስከ ሁለት መቶ ሚሊዮን ዓመታት ድረስ የባህሩን አለም የገዙት የተለያዩ አሳዎች (የአሳ አይነቶች) ነበሩ።

በዚህን ጊዜ ሁሉ የመሬቱ አለም ለመሬት ሕያዋን እየተዘጋጀ ነበር እንጂ፥ በደረቁ መሬት ላይ ምንም ሕይወት አልነበረም። ግን ቀስ በቀስ (ከብዙ የዝናብ ዑደቶች በኋላ)፥ በምድር ላይ የመሬት አፈር ወፈረ። በማዕድናትና በውሃ የተዋሃደና የተቀላቀለ፥ ለስለስ ያለ ምግብ ከመሬት ላይ ተዘጋጅቶ ቀረበ። ነገር ግን ለጊዜው ይህ ምግብ የተዘጋጀው በመጠኑ ስለነበር፥ ምግብነቱ ከቦታ ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ለሚያድጉ ጥቃቅን እጽዋት ብቻ ነበር።

እጽዋት ሁሉ ከአየሩ ውስጥ የሚያገኙትን ካርቦንዳይኦክሳይድ በመጠቀም ኦክሲጂንን ወደ አየር በፎቶሲንተሲስ (photosynthesis) ሲመልሱት አየሩ ውስጥ ቀስ በቀስ ኦክሲጂን ተበራከተ። እጽዋትም ተበራከቱ።

ትንሽ ቆይቶ፥ እነኚህን እጽዋት የሚመገቡ ጥቃቅን እንስሳት በመሬትም ላይ ተፈጠሩ። የመጀመሪያዎቹ የመሬት እንስሳት ከትንሽነታቸው የተነሳ እራሳቸውን ቁልጭ ባለ መልክ አላሳዩም ነበር፤ ነገር ግን እጽዋትን እየተመገቡ ስለቆዩ በአካል ትልቅ ሆኑና ለመታየት በቁ።

ከአራት መቶ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ በመሬት ላይ የተጀመረ ሕይወት በአየር ላይ ከሚንሳፈፉ ባክቴሪያዎች ጀምሮ እስከ በራሪ ትንኞች፥ የተለያዩ ተባዮች፥ በረሮች፥ ከዛም አልፎ እስከ ኤሊዎች ደረሰ።

ከባህር እንስሳዎችም መካከል አንዳንዶቹ እየገዘፉ ሲመጡ፥ ሌላውን ማጥቃት፥ እያሳደዱም መብላት ጠባያቸው እየሆነ ስለመጣ፥ የባህሩ አለም ለደካማዎች አስጨናቂ ሆነባቸው። በዚህን ጊዜ አንዳንዶቹ የባህር እንስሳት ወደ ባህር ዳርቻ በመሄድ የመሬቱን አለም መመርመር ጀመሩ። በሰውነት ከነርሱ ያናነሱ፥ ለምግብነት የሚሆኑ ሲያገኙና ቀስ በቀስ ወደነርሱው ሲጠጉ፥ የባህሩን አለም ትተው ወደ መሬቱ አለም ተሸጋገሩ። እነኚህም እንቁራሪት፥ አዞ፥ አርጃኖ እና የመሳሰሉት ናቸው።

የዝግመተ ለውጥ (evolution) ተከታዮች የሕይወት ዛፍ (Tree of Life) ብለው የሚጠሩት የዛፉ ዋናው ግንድ በቀዳማይ ሕይወት (Paleozoic) ዘመን ከነበሩ፥ ባጠቃላይ ጋስትሪአዳ (Gastreada) ብለው ከሚጠሯቸው ትላትሎች ጀምሮ፥ አምፊቢያ (Amphibea) የተባሉትን (እንቁራሪት፥ እባብ፥ ወዘተ..) ያጠቃልላል።

## <u>መሐል ሕይወት (Mesozoic)</u>

በአካላዊ ሕያዋን ታሪካዊ እድገት ውስጥ፥ እንስሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዙና እየተባዙ በአካላቸውም እየገዘፉ ሲመጡ፥ ሥጋ በሊታ የሆኑትም፥ ታናናሾችን ሲበሉና፥ እርስ በርስ ሲጨራረሱ እንደነበረ፥ አያሌ የእልቂት (extinction) ዘመናት እንደመጣባቸውም እንገነዘባለን። ከነኚህ እልቂቶች መካከል ከዛሬ ሁለት መቶ ሳምሳ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ የመሬትና የባህር እንስሳት ያለቁበት ዘመን አንዱ ታሪካዊ ጊዜ ነበር። ምን ጊዜም ከእልቂት በኋላ ፍጥረት፥ ስለሚከተል፥ ከፍጥረትም ፍጥረት ልዩ አይነት፤ ጡት የማያጠቡ እንስሳት ያለቁበት፥ ጡት የሚያጠቡ እንስሳት የተተኩበት ነው የመሐል ሕይወት ዘመን (Mesozoic) ።

መሐል ሕይወት የዳይናዞር አይነት የበዛበት ዘመን እንደመሆኑ ሁሉ፥ ሌሎችም እንደ አይጠ መጎጥ ያሉ ትናንሽ ጡት አጥቢዎች፥ የባህርና የመሬት እንስሳትም የተባዙበት ዘመን ነበር።

መሐል ሕይወት (Mesozoic) በመሬትም በባህርም ሕይወት የተበራከተበት ዘመን ነበር። በዘቀጡ አለቶች ውስጥ በታየው መረጃ መሠረት፥ በመሐል ሕይወት መጀመሪያ አካባቢ ጥድ፥ ዝግባና የመሳሰሉ የተለያዩ ታላላቅ ዛፎች በብዛት ታይተዋል።

የዛን ጊዜ፥ ዛሬ የምናውቃቸው ክፍላተ አህጉራት ሁሉ ባንድነት ነበሩ (Pangea)። ክፍለ አህጉራት ሲንሸራሩ መቆየታቸው የአትላንቲክ እና የፓሲፊክ ውቂያኖሶችን በመካከላቸው እንዳስገባ ሁሉ፥ አሁንም ይኸው እንቅስቃሴ እየቀጠለ ሲሄድ፥ ክፍለ አህጉራትን እንደገና አጠጋግቶ እንደበፊቱ አንድ ያደርጋቸዋል ተብሎ ይገመታል (Pangea Ultima)።

ድሮ ክፍላተ አህጉራት በአንድነት በነበሩ ጊዜ አብረው በመቆየታቸው፥ የዛፍ አይነት (ጥድ፥ ወይራ፥ ብሳና፥ ዋርካ፥ ሾላ፥ ክትክታ፥ ዋንዛ፥ እንባጮ፥ ግራር፥ ወዘተ..) በአንድ አካባቢ ሲባዛ፥ በጠቅላላ ለምድር ሁሉ እንዲዳረስ ረድቷል።

እጽዋት የተመጣጠነ ምግብ (ማእድናትን) በብዛት እየተመገቡ፥ ሲያድጉና ሲወፍሩ፥ እንሳሳቱም እንዲሁ እነርሱን እየተመገቡ በቁመትና በርዝመት ከፍ - ከፍ እያሉ መጡ። የባህር እንስሳት ከሚመገቧቸው ትናንሽና ደካማ ፍጥረታት  የበለጡ ግዙፎች እንደሆኑ ሁሉ፥ የምድር ላይ እንስሳትም እጽዋትን እየተመገቡ መወፈርና ትልቅ መሆን ጀመሩ።

የዛሬ መቶ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዓመት አካባቢ፥ ዳይናዞር የተባለ የመሬት ግዙፍ እንስሳ ተፈጠረ። በዝቅጠ አለቶች ውስጥ ከተገኙት ቅሬተ አካላት ውስጥ ማንም የመሬት እንስሳ እንደ ዳይናዞር በትልቅነት፥ በአይነትና በብዛት ተበራክቶ ለረጅም ጊዜ (መቶ ሚሊዮን ዓመታት ያህል) የኖረ አልተገኘም።

በዚህ ጊዜ ውስጥ (ከዛሬ መቶ ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ) ነበር፥ አትላንቲክ ውቂያኖስ በመከፈት፥ የአፍሪካና የአሜሪካ መለያየት የተፋጠነው።

በማእከላዊው ሕይወት ባህር በተለይ የምሥራቅ አፍሪካን መሬት ሲያጥለቀልቅና ሲሸፍናት፥ እንደገናም መሬትን ትቶ ሲሸሽና ሲገልጣት የቆየበት ዘመን ነበር። ለምሳሌ፥ በኢትዮጵያ ያሉ ዝቅጠ አለቶች ሁሉ (የኖራ ድንጋዮችና፥ የአሸዋ ድንጋዮች) እድሜአቸው በማእከላዊ ሕይወት ውስጥ የሚካተት ነው።

በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ መከፈት የጀመረው በዚሁ ዘመን ውስጥ ከዛሬ ሃያ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ ነበር። ነገር ግን በአለም ላይ የስምጥ ሸለቆ መክፈት የጀመረው ቀደም ብሎ እንደነበር ልብ ይሏል። የስምጥ ሸለቆ አሁንም መከፈቱን አልተወም፤ በዓመት ሁለት ሴንቲሜትር እየተከፈተ መሆኑ ተለክቶ ታይቷል።

በቀዳማይ ሕይወት፥ የመሬት እጽዋት በብዛትና በአይነት ተበራክተው እንደነበረ ሁሉ፥ በማእከላዊው ሕይወትም ከጫካዎች ይልቅ ሜዳዎች በዙ። በማእከላዊው ሕይወት ብዙ የባህር ሽርሽር ስለተከናወነና ዝመጠ አለቶች በመሬቱ ላይ ስለዘቀጡ ነው ሜዳዎች የበዙት።

የእግዚአብሔርን እቅድ (ድንቅ ሥራ) ለአንዳፍታ እናስተውል። በአለም ላይ ያሉ ዝቅጠ አለቶች ሁሉ የዘቀጡት በማእከላዊው ሕይወት ውስጥ ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ምናልባት መሬት በጠቅላላ ሜዳ ብቻ ሆና ትቀር ነበር፤ እና የዛፍ ዘር ይጠፋ ነበር (ሁሉም በባህር ስለሚሸፈኑና ስለሚሞቱ)። ዳሩ ግን፥ በአንዳንድ ሥፍራ (ለምሳሌ በአሜሪካ) የመሬት ዝቅጠ አለቶች የዘቀጡት አስቀድሞ በቀዳማይ ሕይወት ዘመን ነበር። ስለዚህ፥ የዛን ጊዜና እስከ ማእከላዊው ሕይወት ዘመን ድረስ ዛፎች እየተባዙ ቆይተዋል። ታዲያ ከአንድ ሥፍራ የባህር መጥለቅለቅ ቢሆን እና መሬቱ ሁሉ ሜዳ ሆኖ ዛፍ ቢጠፋም፥ በኋላ መሬቱ ለዛፍ መብቀል አመቺ ሲሆን፥ የዛፍ ዘር ከሌላ፥ መሬቱ በባህር ካልተሸፈነበት ሥፍራ፥ በነፋስ ይዛመታል።

## ***<u>ደኃራይ ሕይወት (Cenozoic)</u>***

የመሐል ሕይወት በታላቁ የእልቂት ዘመን ተካተተ። የዛሬ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ የመሬትና የባህር እንስሳት አለቁ። የዛን ጊዜ ዳይናዞሮች ከምድር ገጽ እልቅ ብለው ጠፉ። አሞናይት የተባሉ የባህር እንስሳትም የዛን ጊዜ ነበር ከባህሩ አለም እልቅ ብለው የጠፉት።

ምን ጊዜም ከእልቂት በኋላ ፍጥረት ስለሚከተል፥ ከፍጥረትም ፍጥረት ልዩ አይነት፤ ከባህር አሞናይት ያለቁበት፥ ከገጸ ምድር ዳይናዞር የጠፉበት፥ በመሬት ላይ ሰዎች የታዩበት ነው የደኃራይ (ድኅረ) ሕይወት ዘመን።

እንደገና የዝግመተ ለውጥ (evolution) ተከታዮች የሕይወት ዛፍ (Tree of Life) ብለው ወደሚጠሩት ዛፍ ተመልሰን የእንስሳቱን አይነት ስንመለከት፥

ከእልቂት በኋላ የሚፈጠሩት የእንስሳት የዘር መደብ አይነት ከቀድሞዎቹ የተለዩ ሆነው ነው የሚገኙት።

ዛሬ ከምናያቸው የመሬት እንስሳት መካከል ዝሆን፥ ጎሽ፥ አንበሳና ነብር፥ ዝንጀሮና ጦጣ፥ በባህር ውስጥም ሻርክ የተባለው አሳ በሊታ የተፈጠሩት በደኃራይ የሕይወት ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል። በዚሁ በደኃራይ ሕይወት ውስጥ፥ የዛሬ ሰላሳ ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ ሌላ የእልቂት ዘመን መጥቶ ብዙ የባህር ፍጥረታት ጠፍተዋል።

ምን ጊዜም ከእልቂት በኋላ ፍጥረት ስለሚከተል፥ ከዚህ እልቂት በኋላም የባህር ውስጥ እንስሳት በአይነትና በብዛት ተበራከቱ።

በድኅረ ሕይወት ውስጥ (በሰላሳና ሃያ ሚሊዮን ዓመታት መካከል) አነስ - አነስ ያሉ፥ ብዙ አይነት የመሬት እንስሳት ተፈጠሩ። ከነኚህም መካከል ሰላማዊ የሆኑ እንስሳት (አህያና ፈረስ) ይገኙበታል።

ከያንዳንዱ የእልቂት ዘመን በኋላ የተፈጠሩት ከቀደሙት ለየት ያሉ መሆናቸውን ተመልክተናል። ታዲያ፥ ተፈጥሮ የአስጨናቂና ጨካኝ እንስሳት ጠባይ ካንገፈገፋት በኋላ ነበር (?) በጠባያቸውም "ሻል ሻል" ያሉትን የምትቀበል ብለን ለመደምደም ይቃጣናል።

ነዳጅ ዘይት - የፍጥረታት እልቂት ውጤት መሆኑ ነው። በተለያዩ ዘመናት አካላዊ ሕያዋን (እንስሳትም እጽዋትም) በመሬትና በባህር እየተባዙ እንደሚያልቁ፥ ይህንንም ሁኔታ በዝቅጠ አለቶች ውስጥ ከሚከማቹ አካለ ቅሪቶቻቸው መረዳት እንደምንችል ተመልክተናል። ከዚሁ ጋር በማገናዘብ፥ ለዘመናችን ሥልጣኔ ምክንያት የሆነው፥ የንኡስ ከበርቴዎችን ኪስ ያራቆተ፥ ነዳጅ ዘይት ከተገኘባቸው ሥፍራዎችም ቱጃሮችን ያንደላቀቀ፥ የዚህ የነዳጅ ዘይት አፈጣጠር እንዴት እንደሆነ እንመልከት።

የእንስሳትና የእጽዋት ክምችት፥ በየጊዜው ከበላዩ ጭቃና አፈር ሲደረብበት፥ ካካባቢው አየር ተለይቶ፥ ኦክሲጂን አልባ ሥፍራ ውስጥ ሲገባና ሲቀበር፥ ካለ ኦክሲጂን የሚኖሩ ባክቴሪያዎች ይህንን የዘአካላት ክምችት እየተመገቡ ይራባሉ። የሙቀቱና የግፊቱም ኃይል ሲጨምር፥ ይህ የዘአካላት ክምችት ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት ካለ ኦክሲጂን ተከድኖ ይበስላል። አስቀድሞ የተገኘው ኃይል ሳይባክን ለብዙ ዘመን ስለሚቆይ፥ በመጀመሪያ ፈሳሽ ዘይት፥ ቀጥሎም በግፊትና በሙቀት ብዛት የሚተን ጋዝ (ጋስ) በዝቅጠ አለቶቹ ውስጥ "አመቺውን ሥፍራ" ፈልጎ ይከማቻል።

ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት ሲኖሩና ሲሞቱ የቆዩ የባህርና የመሬት እንስሳትና እጽዋት፥ የነርሱም ክምችት  እንደ ማንኛውም ዝቅጠት ወደ ጠጣርና ፈሳሽነት ሲለወጥ፥ ፈሳሹ በማንኛውም የዝቅጠ አለቶች ስንጥቆች፥ ሽንቁሮችና ቀዳዳዎች በመሹለክለክ በረባዳ ሥፍራዎች ይከማቻል።

ነዳጅ ዘይት ከመሬት በታች ተቆፍሮ ሲወጣ፥ ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት በሙቀትና በግፊት ተከድኖ ሲንተከተክ የቆየ ወጥ ተጨልፎ እንደሚወጣ መቁጠር ይቻላል። ይህንን ድፍድፍ (ያልተጣራ) ዘይት ለጊዜው እድለኞቹ - ሳውዲያ አራቢያ፥ ሩሲያ፥ ዩናይትድ እስቴትስ፥ ኢራን፥ ቻይና እና ሌሎችም እያወጡ ይጠቀሙበታል።

ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደማይኬድ ሁሉ፥ አስቀድሞ አካለ ቅሬታት የሚገኙበት ዝቅጠ አለት መኖር አለመኖሩ በጂኢሎጂ ይጠናል። ለምሳሌ፥ በባሌ እና በኦጋዴን አካባቢም የጂኦሎጂ ሁኔታዎች ለነዳጅ ዘይት አመቺ ሆነው መቆየታቸውና፤ ከአስር ሺህ ሜትር ጥልቀት በላይ ያላቸው ዝቅጠ አለቶች መኖራቸው ይታወቃል። በዝቅጠ አለቶቹ ውስጥ የሚገኙ አካለ ቅሪታት አይነትና ብዛት፥ በጂኦፊዚክ ምርመራዎችና ሌሎችም መረጃዎች መሠረት፥ ለነዳጅ ዘይት መገኘት አመቺ ሁኔታዎች ተዘጋጅተው እንደቆዩ ከታወቀ ቆይቷል።

በኢትዮጵያ ጥልቅ ጉድጓዶች ተቆፍረው ጋዝ በከፍተኛ ግፊት እያፏተለከ ሲወጣ እንደታየ የጋሱም መኖር ከሥሩ ፈሳሽ መኖሩን ይጠቁማል።

ይህ በኦጋዴን ኢትዮጵያ ተቆፍሮ ሊወጣ የሚችል የዘይት ሃብት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚዳረስ መሆኑ፥ የኦጋዴን ሶማሌዎችም በእርግጥ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እንደመሆናቸው፥ የዘይት ሃብት ተካፋዮች መሆናቸው ሲረጋገጥ፥ የጎረቤት አገር ከሆነችው ከሶማሊያ ጋርም ለምንጊዜም በሰላምና በመልካም ጉርብትና ለመኖር የሚያስችል ሁኔታ ሲፈጠር - በድህነትም ሆነ በብልጽግና የኢትዮጵያና የሶማሊያ ብሔረሰቦች በሰላምና በጸጥታ አብሮ እንዲኖሩ የሚያደርግ የሶሻል፥ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መዋቅሮች ሲዘረጉ፥  የዛን ጊዜ ዘይቱን ቆፍሮ ማውጣት ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ይህ ቶሎ የማይተካ የነዳጅ ኃይል እያለቀ ሲሄድ፥ ኑሮ ለሚቀጥሉት ትውልዶች እንዲህ እንዳሁኑ የሚያንቀባርር እንደማይሆን ግልጽ ነውና፤ በመልካም አስተዳደር ጥቂቱ ብዙ እንደሚሆን (በረከት እንደሚኖረው) ሁሉ፥ ለሰላምና ለጸጥታ ቅድሚያ የሚሰጥ፥ ለጋራ ብልጽግናም የሚታሰብ ከሆነ፥ ለወደፊቱ አገራችን ባለ በረከት በሆነ በልዩ ሃብት ትበለጽጋለች፤ ሃብታም አገር ተብላም ትጠራለች።

ፍጥረታትን ሁሉ እግዚአብሔር በቅደም ተከተል መፍጠሩ ብቻ ሳይሆን፥ ጊዜ መፍጀቱንም ጭምር ላንድ አፍታ እናስተውል። እኛ የተፈጠርነው በምድር ላይ ሰልጥነን በሰማይ ለመብረር የሚያስችሉ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ሁሉ ከተስተካከሉ በኋላ - ብረት፥ መዳብ፥ ወርቅ፥ ነዳጅ ዘይት - ሁሉ ነገር ተቀነባብሮ ከተቀመጠልን በኋላ ነው።

ግን የእግዚአብሔር ፈቃዳዊ ትኩረት "ሠለጠኑ" በሚባሉ ሰዎች ላይ ብቻ አይደለም። የዛሬዎቹ ሃብታም አገሮች ወደ ድህነት ሲያመሩ፥ ዛሬ ድሆች የተባሉት አገሮች ደግሞ በተራቸው እንደሚበለጽጉ ግልጽ ነው። የጂኦሎጂ ክንውኖችም ለወደፊቱ ትውልድ ያስቀምጡት አለ። መጪው ለኢትዮጵያ እና ሌሎችም ባሁኑ ወቅት በድህነት ለታወቁ አገሮች ሁሉ ጥሩ ይመስላል።

አባት ለልጆቹ ገንዘብ እንደሚያስቀምጥላቸው፥ አድገውም እራሳቸውን ሲችሉ እንደሚሰጣቸው፥ እኛም ይህንን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም የምንችልበትን እድገት ስናሳይ፤ በሆነ ባልሆነው መጣላቱን ትተን፥ ጠባያችንን አሳምረን፤ አንዲቷን ኢትዮጵያን በእኩልነት፥ በፍቅርና በአንድነት ካቆየናት፥ ለጋራ ብልጽግና፥ ሰላምና ጸጥታ፥ ለመንፈሳዊ አንድነትም በሕብረት ስንንቀሳቀስ፥ የዛን ጊዜ የሚያስፈልገን ሁሉ ይሰጠናል።

## ስለ ሕይወት ዘመናት ማጠቃለያ

እስካሁን ከቅሪተ አካላት በተገነዘብነው መሠረት፥ እንስሳት ሁሉ ባንድ ጊዜ አልተፈጠሩም። የአካላዊ ሕያዋንን ታሪክ ስንመረምር፥ ካለ ቅድመ ዝግጅትና ካለ ምክንያት የተፈጠረ እንስሳ አለመኖሩንም እንገነዘባለን።

በኋላ የተፈጠረ እንስሳ ቀደም ብሎ ከተፈጠረ እንስሳ ተለውጦ አዲስ ፍጥረት እንዳላመጣ በሚከተለው ምዕራፍ እናያለን። ሆኖም፥ ቀደም ብሎ የተፈጠረ እንስሳ፥ በኋላ ከሚፈጠረው እንስሳ ጋር አንድ የሚያገናኝ ምክንያት ቢኖር፥ ያንን ምክንያት ማወቅ ከባድ ነው።

ጫካዎች አስቀድመው ስለተፈጠሩ አንዳንድ ደካማ እንስሳት መደበቂያ ጫካ አግኝተው ነበር። ዳሩ ግን፥ የእንስሳት እርስ በርስ መጠቃቃት አሁንም ቀጥሏል። ቅጠል በሊታዎችንና ሰላማዊ የሆኑ እንስሳትን የሚመገቧቸው (እንደ ሰው፥ ጅብና አንበሳ ያሉ ሥጋ በሊታዎች) አሁንም አሉ፤ በእንስሳዊነት እድገት ውስጥ የእርስ በርስ መተላለቅ አልቀረም። በዚህ አንጻር ሲታይ፥ የምድራችን ምድራዊነት እጅግ የከፋ

ይመስላል። ይህ በዚህ እንዳለ፥ በመተላለቅ ፋንታ ተስማምቶ በሰላም አብሮ መኖርም የተፈጥሮ ሂደት መሆኑ በግልጽ ይታያል።

እግዚአብሔር ለፍጠራት ሁሉ፥ በውስጠ ጠባያቸው በበራሂያቸው (gene) ውስጥ እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያሻሽሉ የሚያደርግ ቅመም (በኬሚካሎች የተመዘገበ መልከ ጠባይ) አስቀምጦላቸዋልና፤ አንዳንድ እንስሳትም ከአጥቂዎቻቸው ጋር ለመኖር ችለዋል። ታዲያ፥ ምንም እንኳን የምድራችን ምድራዊነት እጅግ የከፋ ቢሆንም፥ ማለሳለሺያ ዘዴውንም ፍጡራን ሁሉ እንዲያውቁበት ልዩ ባህሬ ተሰጥቷቸዋል። የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጥልቅ ሃሳቦችን በመንፈሳዊነት እንድንፈላሰፍባቸው የሚረዱ ስለሆነ፥ እስካሁን የተጠቀሱትን ሳይንሳዊ ዘገባዎች በማመሳሰል ደረጃ እንመልከታቸው (በትርጉም ሳንጣላ)።

- “ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ፤ ነፍሳቸውን ታወጣለህ፥ ይሞታሉም፤ ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ። <u>መንፈስህን ትልካለህ፥ ይፈጠራሉም፥</u>[31] የምድርንም ፊት ታድስለህ።” መዝ. 103፡29 - 30
- “የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች። በእግዚአብሔር ኃይል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ ባፉ እስትንፋስ።” መዝ. 32፡5
- “የእግዚአብሔር ክብር ለዘለአለም ይሁን፤ እግዚአብሔር በሥራው ደስ ይለዋል።” መዝ. 103፡31

በዳዊት መዝሙር ውስጥ ብዙ - ብዙ ምሥጢር እንደተጠቀሰ ሁሉ፥ በዚህ ምዕራፍ የተነጋገርንበትም በዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 103 በጥቅሉ ተቀምጧል (ለሚመስለን)።

አቤቱ እናመሰግንሃለን፤

ክብርህን ለመናገር ስላበቃኸን፥

የእጅህንም ሥራ ለማወጅ ስላነቃኸን።

[31] ከእልቂት ዘመን እና አዲስ ፍጥረት ጋር ይመሳሰላል (እንደ አንባቢው)።

# ምዕራፍ ስድስት

## ዝግመተ ለውጥ እና ፍጥረት

የዝግመተ ለውጥ (evolution) ፍልስፍና “ይህ ዛሬ የምናየው ሕያው የሆነ ሁሉ ከባለ አንድ ህዋስ (ሴል) ተጀመረ” ከሚል መላ ምት በመነሳት፥ ሕያዋን እንዴት በአይነት እንደተባዙ፥ የሕይወትን አካላዊነት ብቻ ይዞ ሰፊ ማብራሪያ ይሰጣል።

በጊዜ ውስጥ ለውጥ ሊኖር አይችልም ብለን መነሳት ስለማንችል፥ ለውጥ የሚለውን ቃል ከሚገባው በላይ ሳናሳድግ ወይም ሳናሳንስ፤ “ዝግመተ ለውጥ” የሚለውን ቃል በሚከተሉት በሁለት አይነት መንገድ እንጠቀምበታለን።

1. በዚህ መጽሐፍ የማይደገፍ የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ፡- ምድራዊ ሕያዋን ሁሉ ከአንድ የዘር መደብ ወደ ሌላው የዘር መደብ በዝግመት የሚለወጡበት።
2. በዚህ መጽሐፍ የሚደገፍ ዝግመተ ለውጥ፡- ምድራዊ ሕያዋን - ፍጡራን ሁሉ በምድራዊነታቸው የሚያጋጥማቸውን እክል ሁሉ ለመቋቋም የሚያስችል፥ ከአካባቢያቸውም ስምም ሆነው እንዲኖሩ የሚረዳቸው መለወጥ ነው። ይህ ለውጥ ከአንድ የዘር መደብ ወደሌላው መለወጥን አያስከትልም።

ዳርዊን መቶ በመቶ ልክ ሊሆን ይችላል፤ ላይሆንም ይችላል ብሎ ማሰብም አይከፋም። ፍጹም እውቀትንና ፍጹም እውነትን አመንጪ የሆነ እግዚአብሔር እውነቱን ይግለጽልን።

ፍጥረትና ዝግመተ ለውጥ ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው እንጂ፥ ሕያዋን ሁሉ በዝግመተ ለውጥ ብቻ ከዚህ እንዳልደረሱ የሚያመለክት፥ የዳርዊን ዝግመተ ለውጥን የተቃውሞ ጽሑፍ በዚህና በሚከተለው ምዕራፍ አቅርበናል።

የሰውን ምድራዊነቱን የሚያሰምርለት - ጠባዩን ከሚወስነው አካላዊ ጠባዩ ሌላ - የመንፈሱ ጠባይ - የእሱነቱ አንደኛው ወሳኝ ባህሬው መሆኑን ለመግለጽም እንሞክራለን። በውሱን (መጠነኛ) የባዮሎጂ እውቀታችን ሳንገታ፥ በበራሂ (gene - ጂን) ውስጥ የሚመዘገብ የጠባይ ለውጥ ቢኖርም፥ ይህ ለውጥ ሊመጣ የሚችል ከምድራዊነት ጋር በተያያዘ መንገድ ብቻ መሆኑን፥ ይህም አካላዊ ለውጥ እንጂ

መንፈሳዊ ለውጥ አለመሆኑን፥ በዚህና በሚከተለው ምዕራፍ ለመግለጽ እንሞክራለን። መንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) የሆነውን አባባል ሳይንሳዊ ከሆነው እየለዩ፥ የግል እምነትን ለራስ እያደረጉ ማስተዋልን ለአንባቢያን እንተዋለን። ለምሳሌ፡-

፤ኛ) ከጥንት ጀምሮ ሕይወት ከዝቅተኛው ህዋስ (ሴል) ጀምሮ በአካላዊ መልክና በትልቅነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለዋወጠ (እየተሻሻለ ማለት ላይሆን ይችላል) መምጣቱን ከአካለ ቅሪት ማስረጃዎች መመልከት ይቻላልና፤ ይህንን እንደ እውነት መቁጠር ይቻላል።

2ኛ) የዳርዊን[32] የሕይወት ዛፍና ቅርንጫፎቹ በሚያሳዩት መሠረት፥ በእንስሳት ውስጥ የሚገኙ የበራሂዎቻቸው ጠባይ የተራራቀ ሲሆን፥ እነኚህ እንስሳት በዝግመተ ለውጥ ታሪካቸውም የተራራቁ ናቸው በማለት፥ የበራሂዎቻቸው (genes) ጠባይ የተቀራረበ ሲሆን ደግሞ፥ በዝግመተ ለውጥ ታሪካቸውም የተቀራረቡ ናቸው በማለት፥ የእንስሳት አይነት በተለያዩ የዘር መደቦች (species) ተከፋፍለዋል። ለፍጥረታት የሕይወት ዛፍና ቅርንጭፍ አበጅቶ በዘር መደብ ከፋፍሎ ማስቀመጡ፥ ይህንንም እንደ እውነት እና መልካም ሥራ መቁጠር ይቻላል።

ስህተቱ ድምዳሜው ላይ መሆኑን በኋላ እናያለን። በቅድሚያ በምድራችን ይህንኑ የአካላዊ ሕያዋን በዘር መከፋፈል በተመለከተ፥ የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እናስተውል፡-

“እግዚአብሔርም አለ፡- ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደወገኑ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔር የምድርን አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፤ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ፤ እግዚአብሔር ያ መልካም እንደሆነ አየ።” ዘፍ. ፤፡24 - 25

ይህንን አንድ መጠነኛ ገለጻ፥ ከሰፊው የዳርዊን ማብራሪያ ጋር ማወዳደር ሞኝነት ነው ይሚሉ ይኖራሉ። በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተካተተውን መንፈሳዊ ግንዛቤ ለማብራራት፥ ከሳይንሱ ጋር ያለውንም ዝምድና ለመግለጽም ሆነ ለማመሳሰል አቅም ሊያጥረን ይችላል። ግን በዚህ እና በሚከተለው ምዕራፍ በጥቅሉ፡- እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ እንደየወገኑ - የዘር መደቡ (species) ይባዛ ዘንድ ፈቅዶ፥ ዝግመተ ለውጥን እንደ አንድ ተቀጽላ የተፈጥሮ ሕግ ሊያደርገው እንደሚችል - ዝግመተ ለውጥና ፍጥረት (ሁለቱም) ከእግዚአብሔር የፈለቁ (የሚፈልቁ) መሆናቸውን፤ ከፍጥረት ቀጥሎ (ከፍጥረትም ጋር) የማያቋርጥ ተፈጥሮአዊ የእድገት

---

[32] ዳርዊን የዝግመተ ለውጥን ጽንሰ ሃሳብ ያመነጨ ተፈላሳፊ ሳይንቲስት ነው።

ክስተት እንደሚኖር፥ ይህ ክስተት ሕይወት በሌላቸው እና ሕይወት ባላቸው ውስጥ ሁሉ እንደሚካሄድ ለማመልከት ነው ጥረታችን።

ዳርዊን (1809 - 1882)፡- ገሃድ የሆነውን ሁሉ የበለጠ ገሃድ ለማድረግ ብዙ ጽፏል፤ አረፍተ ነገር እያስረዘመ እና በድግግሞሽም ለማሳመን ብዙ እየጣረ። በወቅቱ ታላቅ ክብር አግኝቶ፥ እስካሁን ድረስ እንደርሱ የሚያስቡ ብዙ ተከታዮች አፍርቷል። የርሱ መጽሐፍ ታዋቂ የሆነው፡- ዛሬ በምድር ላይ የሚታዩ ሕያዋን ሁሉ በተናጠል ለየብቻ የተፈጠሩ አለመሆናቸውን የሚያስረዳ ሰፋ ያለ ትንተና በማቅረቡ ነው። ግን፥ ሥራው ሁሉ ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ የመደምደሚያው ስነ አመክንዮ ነው በኢሳይንሳዊነቱ የተወቀሰው። ለምሳሌ የሚከተለውን እንመልከት፡-

"If different species of groundfinches or armadillos could be produced by evolution from a common ancestor, then, given enough time, the same must hold for different families, orders and classes and for diversity of life as a whole" Charles Darwin 1958, p.11

ወደ አማርኛ ሲተረጎም፡- "ከግራውንድፊንች (የወፍ አይነት) ወይንም ከአርማዲሎ (ኤሊ እና ጃርት የመሰለ አውሬ) የተለያዩ ዝርያዎች፥ የጋራ ከሆኑ የዘር ግንዶች በዝግመተ ለውጥ ከተገኙ፥ ሌሎች ሕያዋንም፥ በረጅም ዘመን ውስጥ፥ በዝግመተ ለውጥ ለመለወጥ ስለቻሉ መሆን አለበት በአለም ላይ ሕይወት እንዲህ የተበራከተው።"

በመጀመሪያ፥ "በዝግመተለውጥ ከተገኙ" ሲል ዝግመተለውጥን እውነተኛ ክስተት ያስመስለዋል። ቀጥሎም፥ መሆን አለበት ብሎ - ነው ቢባል፥ ይህ መቶ በመቶ እውነት ሊሆን ስለማይችል፥ ቀጥተኛ ስነ አመክኖአዊ ሂደት አይደለም - ሳይንሳዊ አይደለም። ከተፈጠረ ጀምሮ ለየብቻው ያልኖረ ሕያው እርስ በርሱ (ማለት - በዘር የሚቀራረበው) እየተዳቀለ በመሃል በመሃሉ ብዙ አይነት ፍጡር በየጊዜው ሊከሰት እንደሚችል ይህንን ገሃድ የበለጠ ገሃድ ማድረጉ ጥሩ ነበር። ግን የሚከተለውን ለማስረገጥ ሲል ሰፊውን ተፈጥሮ ድምስስ አድርጎታል፡-

"..All living organisms must be related through their common descent from some simple original stock.."

ወደ አማርኛ ሲተረጎም፡- "ማንኛውም ነዋሪ ዘአካል እርስ በርሱ በመዛመድ ወደ ተቃለለ የጋራ የዘር ግንድ የሚያመራ መሆን አለበት።"

ለዳርዊን የሚከተለው መደምደሚያ ቢሆን ነበር የተሻለው፡- "በአለም ላይ ሕይወት እንዲህ የተበራከተው፥ እርስ በርስ በመባዛትና ተፈጥሮ በሚያስከትለው

ምርጫ፡- ጭራሽ ከመጥፋት ይልቅ፥ መለወጥን በመከተል ነው።" ይህ አባባል እግዚአብሔር መደበኛ የዘር መደቦችን ሁሉ መፍጠሩን፥ እኛም ትክክለኛው ዝግመተ ለውጥ የምንለውን ያካትታል።

የዳርዊንን ሥራዎች ሁሉ ለመንቀፍ አልተነሳንም፤ እኛ የምንነቅፈው አንዳንድ ከሚገባው በላይ እየደፈረ የሚያቀርበውን መደምደሚያውን ነው እንጂ። እግዚአብሔር በሰጠው ችሎታ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ አብራርቶ ከገለጸ በኋላ፥ መደምደሚያውን ኢስነአመክንዮአዊ (ኢሳይንሳዊ) ያደረገው እሱ ነው። የሳይንቲስቶች ሥራ ተፈጥሮን ለመግለጽ መሞከር ነው እንጂ፥ መቶ በመቶ እርግጠኛ ሳይሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት የሚያስክድ ደምሳሳ - ኢሳይንሳዊ መደምደሚያ አበጅቶ ሰውን ሁሉ ጥርጣሬ ውስጥ መክተት መሆን አልነበረበትም። ዳርዊን፥ አንድ ጋዜጠኛ ወሬውን አውርቶ ሲደመድም፥ የዳኝነትን ሥፍራ ከዳኛው ቀምቶ የራሱን ፍርድ እንደሚሰጥ ነው የሆነው።

በዲ ኤን ኤ (DNA)[33] ውስጥ በሚፈጠሩ መለዋወጦች ምክንያት የእንስሳት ሁሉ ውስጣዊና ውጫዊ አካላዊ ጠባዮቻቸው እየተለዋወጡ (እየተሻሻሉ ማለት ላይሆን ይችላል)፥ በጊዜ ብዛት የአንዱ እንስሳ ከሌላው መለየት ግዴታ ስለሆነ፥ ይህ የምናየው የእንስሳትም ሆነ የእጽዋት አይነት በአይነት ተበራከተ። ይህም የእንስሳቱን አለም አበራከተው፤ የእንስሳቱ ዘር ገና ከፍጥረቱ በተናጠል የተጠበቀ ሆኖ።

እንስሳት ሁሉ "የራሱ ዘር" ከሆነው እየወጣ ከሌላው ዘር ጋር መዳቀል አይችልም። ግን እርስ በርሱ ስለሚባዛ፥ በጊዜ ውስጥ ከጥቃቅን ለውጦች (ዝግመተ ለውጥ) ጋር መበራከቱም ይሆናል የእንስሳቱን አለም ቆንጆ ያደረገው። እዚህ ላይ ክርክር እንዳይነሳ፥ ዘር የምንለው፥ በአህያና በፈረስ እንዳለው ሳይሆን (ሁለቱ በአንድ የዘር መደብ ውስጥ ስለሚካተቱ)፥ በፍየልና በዶሮ መካከል እንዳለው አይነት ነው (ሁለቱ በተለያየ የዘር መደብ ውስጥ ስለሚካተቱ)።

በዲ ኤን ኤ መለዋወጥ ከመደበኛ ዘር የማያስወጣ ከሆነ - ከዘር ውጪ መዳቀል ካልተቻለ፥ "ይህ በአካለ ቅሪቶች የምናየው የአካላዊ መለዋወጥና እድገት፥ ከዛው ከመደበኛ ዘሮች ውስጥ እየሰፋ የሄደ ነው" ቢባል ግን፥ ይህ በዚህ መጽሐፍ የሚደገፍ ዝግመተ ለውጥ ይሆናል። ስለዚህ፥ ከዝግመተ ለውጥ የተገኘ አካላዊ ለውጥ ቢኖር እንደሚከተለው አይነት ይሆናል፡- ከወፍ መደበኛ ዘር የወፍ አይነቶች (አሞራ፥ ቆቅ፥ ዶሮ..ወዘተ.)፥ ከውሻ መደበኛ ዘር የውሻ አይነቶች (ቀበሮ፥ ተኩላ፥..ወዘተ.)፥ ከሰው መደበኛ ዘር የሰው አይነቶች (ነጭ፥ ጥቁር፥ ቢጫ)። ይህንን መደምደሚያ

[33] DNA – deoxyribonucleic acid (በቃላት ትርጉም የቀረበውንም ማብራሪያ ይመለከቷል)።

ኃይለ ቃል (የሰው ዘር አንድ ብቻ መሆኑን) ለማስረገጥ በቂ መረጃዎችን አንሻም (ግልጽ ስለሆነ)።

የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ በአካላዊ ቁመና፥ በመልክ (በቁንጅና) ላይ ያተኮረ በመሆኑ፥ ምድራዊነቱን ስለሚያንጸባርቀው ስለ አካላዊ ጠባዩ ብቻ ነው የሚያወራው (መልካም ነው)። ግን፥ የማንኛቸውም ባለ ሕይወት አካላት - ዘአካላት (organism) ጠባይ የሚወሰነው በበራሂአቸው ውስጥ በሚገኝ ዲ ኤን ኤ (DNA ) የተባለ ኬሚካል ብቻ ነው ወይ?

ይህ መጽሐፍ ከዚህ አልፎ ለመሄድ ችሎታ ስለሌለው፥ አዎ! ምድራዊ ጠባይን በተመለከተ፥ የማንኛቸውም ባለ ሕይወት አካላት - ዘአካላት (organism) ጠባይ የሚወሰነው በበራሂአቸው ውስጥ በሚገኝ ዲ ኤን ኤ (DNA) ብቻ ነው እንበል።

ይህ ኬሚካል አንድ ባለ ሕይወት አካል፥ ህዋሳቶቹ ሁሉ ለመኖር የሚያስፈልገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ትክክለኛ መረጃ የሚያስተላልፍ ስለሆነ፥ በኬሚካሎቹ መለዋወጥ የእንስሳትም አይነት፥ የዘር መደቡ የተጠበቀ ሆኖ፥ ሊበራከት ቻለ ቢባል ምንም ቅራኔ አያመጣም። ይህንን የዲ ኤን ኤ ሥራ አብዝቶ የሚናገር የሳይንስ እውቀት - ያ በዚህ መጽሐፍ የማይገለጽ ታላቅ ጥበብ የዳርዊንን የዝግመተ ለውጥ እንዴት አድርጎ እንደሚደግፈው/እንዴት አድርጎ እንደማይደግፈውም አላወቅንም፤ ግን እርግጠኞች የሆንበትን በዲ ኤን ኤ አማካኝነት ከጊዜ ብዛት ጥቃቅን ለውጦች ይኖራሉ ማለትን እንደ አንድ የተፈጥሮ ሕግ መውሰድ ይቻላል፤ በጂኦሎጂ ምርምርም ቢሆን ግዑዛን ማእድናትም፥ የተወሰኑ የተፈጥሮ ሕግጋትን ተከትለው ስለሚጓዙ፥ በውስጣቸው ዝግመተ ለውጦች ይታይባቸዋልና።

ባጭሩ፡- ማንኛውም አካላዊ ሕያው ካለ ፈጣሪ ወይም መላእክት እርዳታ የአካባቢ ሁኔታዎችን ተከትሎ ሲንቀሳቀስ፥ ራሱን በራሱ መለዋወጥ እንዲችል - ምድራዊነትን በደንብ አድርጎ እንዲያውቅበትና በራሱ እንዲኖር፥ ዝግመተ ለውጥ ውስጣዊ የተፈጥሮ ጠባዩ እንዲሆን አስፈልጓል፤ ይህ መልካም እንደሆነ እግዚአብሔር አይቶ ፈቅዷል ማለታችን ነው። እግዚአብሔር አንዴ ፈጠርኩ ብሎ አይተውምና፤ ፍጡራን በምድር ላይ እየተራቡ እንዲበዙለት ስለፈለገ፥ ፍጡራኑ የአካባቢያቸውን ሁኔታ እያቸነፉ የሚዘልቁበትንም መንገድ በውስጠ ባህሪያቸው (በ ዲ.ኤን.ኤ.) ውስጥ ፈጥሮላቸዋል። ዝግመተ ለውጥን የራሳቸውን ውስጣዊና ውጫዊ ጠባይ መለወጫ መሳሪያ አደረገላቸው ማለት ነው (ውስጣዊና ውጫዊ ጠባይ ስንል መንፈሳዊ ያይደለ፥ ሁሉም ሥጋዊ የሆነ ማለታችን ነው)።

ይህች ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ የነበረውን ያካባቢ ለውጥ ተመልክተናል። በነኚህ ለውጦች መካከል ሁሉ፥ ባህር መሬትን ሲከድንና ሲገልጥ፥ በበራድ ዘመን መሬቱ በበረዶ ሲሸፈን፥ የጎርፍ መጥለቅለቅም ሲከተል፥ ነፋስ፥ ውርጭና ሙቀት ሲለዋወጥ፥ የሞተው ሞቶ፥ የተረፈውም ሲባዛ፤ ይኸው እስካሁን አካላዊ ሕይወት ከባህርም ከየብስም አልጠፋም፤ እግዚአብሔር በፍጡራኑ ውስጥ ሁሉ - ሕያዋን እንደ አካባቢው ሁኔታ እራሳቸውን እንዲለውጡ የሚያስችል ዲ ኤን ኤ የተባለ የኮምፐዩተር ኮድ ፈጥሮላቸዋልና።

ማንኛውም ዘአካል ምድራዊነቱ ካልሰመረለት ቶሎ ሊጠፋ ስለሚችል፤ በውስጣዊ አካላዊ ጠባዩ (መንፈሳዊ ያይደለ) እየተመራ በየጊዜው የሚመጣበትን ያካባቢ ሁኔታ ይቋቋማል። ይህንን ስላደረገ "መጠነኛ" ለውጥ ቢታይበት አያስደንቅም። እንዲህ አይነቱን "መጠነኛ" ለውጥ በተጨባጭ ዛሬም (በዚህ ትውልድ እንኳን) ቢሆን የምናየው ነውና።

እራስን በራስ መለወጥ (mutation) እና ጠቃሚውን መርጦ መውሰድ (natural selection)፥ ሁለቱም ዳርዊን የተጠቀመባቸው የርሱ የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና መሠረቶች ቢሆኑም፥ እኛም ባግባቡ እንጠቀምባቸዋለን።

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፡- የዲ ኤን ኤ መለዋወጥ እንዴት አድርጎ እራስን በራስ መለወጥ እና ጠቃሚውን መርጦ መውሰድን እንደሚያመጣ በግልጽ አላወቅንም (የሚያውቁ ወይንም አውቀናል የሚሉ ይኖራሉ)። ሆኖም፥ እንስሳት ለጠባያቸው ተስማሚ የሆነው ኬሚካል በአካላቸው እየተመረጠ እንደሚገነባ መገመት ይቻላል። ስለዚህ፥ እራስን በራስ ለመለወጥ እና ጠቃሚውን መርጦ ለመውሰድ እንዲችሉ ሆነው ተፈጥረዋል ማለት እንችላለን። በዚህ በውስጣቸው በሚካሄደው የአዲስ ኬሚካል ምርት (ግንባታ) እጅግ ብዙ ዓመታት ቆይቶም ቢሆን፥ በግልጽ የሚታየውን "ለውጥ" ነው ከፍጥረት ለይተን ዝግመተ ለውጥ ያልነው (የዳርዊን አይነት ያልሆነ - ከመደበኛ ዘር የማያስወጣ ዝግመተ ለውጥ)። እንዲህ አይነቱን የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ በአጽንኦት እያሰላሰልን፥ በዳርዊን የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ ውስጥ ምን ጉድለት እንደሚኖር እንመልከት።

## ስለ መጀመሪያው ሕይወት መሠረታዊ ጥያቄ

የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ተከታዮች እግዚአብሔር አልፈጠረም፤ መንፈስ የለም፤ መንፈስ በአካል ውስጥ ጣልቃ አልገባም፤ ባለ ሕይወት አካል የተገኘው ከአካል በአጋጣሚ ነው ይላሉ። ከአካል በስተቀር ምንም ነገር የለም ማለት ደግሞ፥ ሕያዋን እንደ መኪና ካልተቀሰቀሱ በስተቀር ሙት ናቸው፤ መንፈስ የለም ማለት ነው።

ከሕያዋን አካልን ከነፍስ እየለዩ መመለከት የአማኞች ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ነው። ከሕያዋን አካልና ነፍስን ባንድነት በመመልከት፥ አካል በድን በሚሆንበት ጊዜ ቀሪ ነፍስ እንደማይኖር አድርጎ መቁጠር ደግሞ የአላማኞች ፍልስፍና ነው።

ለመሆኑ፥ ሕይወት ሁሉ አካላዊ ብቻ ስለመሆኑ ማን ምን ማረጋገጫ አለው? አካላዊ ያልሆነ ሕይወት አይኖርም?

በሃይማኖታዊ ፍልስፍና መሠረት፥ አካላዊ ሕያዋን ይንቀሳቀሳሉ ስንል፥ ለሕያውነት ምክንያት የሆነውን "ዘለአለማዊ ነፍስ" በማስደገፍ ነው።

ሳይንቲስቶች በፊዚክስ እውቀታቸው እየተጠቀሙ፥ ንጥረ ነገርን እየሰባበሩ፥ የመጨረሻውንና ደቂቁን አካል ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ይደረጋሉ። (ለምሳሌ CERN የተባለው በአውሮፓውያን አገሮች የሚመራ የደቂቀ አካላት (particles) መመርመሪያ ጣቢያ ውስጥ በሚደረገው ምርምር፥ ካሁን በፊት ያልታወቁ፥ እንደ ሃርዶን[34] ያሉ ደቂቀ አካላት መኖራቸው ታውቋል።

እንዲሁም፥ የመጨረሻው ረቂቅ አካላዊ ሕያው ባለ አንድ ሴል ብቻ ነው ከማለት ይልቅ፥ ከዛም አልፎ እስከ ማይታይ የረቀቀ "ሴላ" ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰብም አይከፋም።

ዳርዊን "ሕያው የሆነ ሁሉ መሠረቱ ከአንድ ከዝቅተኛ የሕያው ህዋስ፥ ካለ ፈጣሪ በገዛ ራሱ ሕይወትን መሥርቶ፥ በገዛ ራሱ ቀስ በቀስ እየተለዋወጠ ዛሬ የሚታየውን የእንስሳትና የእጽዋት ብዛትና አይነት አስገኘ" በማለቱ፥ በብዙ ቅን ሳይንቲስቶች ፊት እስከዛሬ ድረስ ይተቻል። በሚከተለው አረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን የስነ አመክንዮ ጉድለት (የጥራት ማነስ) እንመልከት።

"ሕይወት ከመጨረሻውና ከዝቅተኛው ህዋስ (ሴል) በመልክም "በጥራትም" ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ስለመጣ፥ የምድር ሕያዋን ሁሉ መነሻቸው የመጀመሪያውና ዝቅተኛው ህዋስ መሆን አለበት።"

ይህ አረፍተ ነገር ዛሬ የምድር ሕያዋን ሁሉ (ሰውም ጭምር) ከዚህ የደረሱት በዝግመተ ለውጥ እንጂ በመፈጠር አይደለም ለማለት ተስተካክሎ የተቀመጠ ይመስላል። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ እውነት አለ፤ እውነት ያልሆነም አለ።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው፥ "አካላዊ ሕይወት ከመጨረሻውና ከዝቅተኛው ህዋስ (ሴል) በመልክም በጥራትም (በብዛትና፥ በትልቅነት..) ከጊዜ ወደ ጊዜ

[34] ሃርዶን - Hardon - a composite particle made of quarks held together by the strong force in a similar way as molecules are held together by the electromagnetic force.

እየጨመረ መጣ” ሲል እውነት ነው። በእውነት መሆን ያለበት ነው የሆነው፤ የፍጥረታትም በብዛትና፥ በትልቅነት.. መገኘት ግዴታ ነበር (ነው)።

ነገር ግን፥ ሕያዋን **ሁሉ** መነሻቸው ከመጀመሪያውና ከዝቅተኛው ህዋስ መሆን አለበት (ካለ ፍጥረት) ስንል - ዛሬ የሚታዩትን የእንስሳትም ሆነ የእጽዋት አይነት በዚህ እጅግ ቅልል ባለ መንገድ ብቻ መግለጥ ስለሆነ፥ ይህ ሳይንሳዊ አይደለም። ሳይንሳዊ ቢሆን ኖሮ ሚዛናዊ አስተሳሰብ ላለው ሰው ሁሉ እንዲህ አጨቃጫቂ አይሆንም ነበር።

ሁለንተናዊ የሕያውነት ጠባይ በእንስሳትም በእጽዋትም ውስጥ ቢኖር አያስደንቅም። ሕያዋንን እና ግዑዛንን እንኳን አንድ የሚያደርጋቸው - የሚያዛምዳቸው የጋራ ጠባይ አለላቸው (ሁሉም በአተሞቻቸው - ኢሌክትሮኖቻቸው፥ ኒውትሮኖቻቸውና ፕሮቶኖቻቸው የተገነቡ ናቸው፤ ሁላችንም ከዚችው ምድር የበቀልን ስለሆነ)። የመጀመሪያው ባለ አንድ ህዋስ (ሴል) በራሱ ተገኘ ስንል ግን፥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያስከትላል (Southwood, Richard 2002)፡

1. እንዴት ነጠላ የሕይወት መስራች ሞሌኩሎች (ካርቦን፥ ኦክሲጂን፥ ሃይድሮጂን፥ ናይትሮጂን፥ ሰልፈርና ፎስፎረስ) ባንድ ላይ ተከማችተው ተገኙ?
2. እነኚህ ሞሌኩሎች እንዴት ነው ባንድነት ተቀናጅተው (ማንም ሳይነካቸው በራሳቸው) ለህዋሱ ሰውነት የሚሆኑትን ኬሚካሎች (starch, cellulose) የመሠረቱት?
3. እንዴት ነው ህዋሱ እነኚህን ኬሚካሎች (starch, cellulose) በአንድ አካሉ የታቀፉቸውና የራሱ ያደረጋቸው - እንዴት ነው ኬሚካሉቹ እንዳይረግፉ (እንዳይፈሱ - እንዳይፈርጡ) ዙሪያውን መታቀፊያ ቆዳ (membrane) ለራሱና በራሱ ያበጀ?
4. ህዋሱ ለመንቀሳቀስ ኃይል ያስፈልገዋል፤ የመጀመሪያው ኃይል እንዴት ከኬሚካሎቹ ሊመነጭ ቻለ? ወይንም እንዴት ነው ኬሚካሉን የሚቀሰቅስ ውጫዊ ኃይል (የጸሐይ ብርሃንና መቀት) ነፍስ ዘሪ የሆነ?
5. የአካላዊ ሕያዋን ሁሉ የተፈጥሮ ሕግ የሆነው - እራስን የማባዛት ጠባይ እንዴት ነው በመጀመሪያው ህዋስ ውስጥ የተከሰተ?

ቅሪተ አካላት የፍጡራንን አይነትና መበራከት ስለሚያመለክቱ፥ ከዝቅጠ አለቶች የተገኙ አጥንቶችን በመገጣጠምና በሃሳብ ሥጋና ቆዳ በማልበስ፥ ይኸውና እንዲህ ነበረ የእንስሳት እድገት ማለት አይከፋም። ግን የሁሉም አመጣጥ ከአንድ ዝቅተኛ

ዘአካል ነው ብሎ፥ በቂ መረጃዎችን ሳይደረድሩ እንዲህ ደፍሮ በደምሳሳው መደምደም ልክ አይሆንም።

የተጠቀሱትን መሠረታዊ የሳይንስ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ሳይመለሱ፥ ወደ ክህደት የሚስበውን የዳርዊንን የዝግመተ ለውጥን ፍልስፍና ሙሉ በሙሉ መቀበል ኢሳይንሳዊነት ይሆናል። ግን፥ ሳይንስ ዛሬ የተጠቀሱትን ሁሉ በሚገባ ባይመልስም፥ ለወደፊት ይመልሳቸው ይሆናል ብሎ የዳርዊንን ያልተሟላ የዝግመተ ለውጥን ፍልስፍና ለጊዜው ወደጎን ራቅ አድርጎ ማቆየት ይቻላል።

ከዛም በላይ፥ ከሕያዋን ነፍስ መዝራት በስተቀር፥ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ በራሳቸው ሊተገበሩ ይችሉ ይሆናል። ግን፥ “ዛሬ በዚህ ምድር ላይ የምናያቸው እንስሳትና እጽዋት፥ በዝተውና ተባዝተው እዚህ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት፥ ገና ከጥንስሱ ነፍሳቸውን ያመጡት ከየት ነው”? ለሚለው ጥያቄ የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ትምህርት በቂ መልስ እንዳልሰጠ እንመልከት።

ከተጠቀሱት አምስት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራቱ ጥያቄዎች በሚከተለው አንድ ጥያቄ ይጠቃለላሉ፡- እንዴት ነው ሕይወት ከግዑዛን የሚመነጭ?

ነጠላ የሕይወት መስራች ሞሌኩሎች (ካርቦን፥ ኦክሲጂን፥ ሃይድሮጂን፥ ናይትሮጂን፥ ሰልፈርና ፎስፎረስ) ባንድ ላይ ተከማችተው ሊገኙ፤ እነኚህም ሞሌኩሎች ባንድነት ተቀናጅተው (ማንም ሳይነካቸው በራሳቸው) ለሰውነት ገንቢ የሚሆኑ ኬሚካሎች (starch, cellulose) ሊመሠርቱ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን፥ እነኚህ ግዑዛን ወደፊት ለሚፈጠሩ ሕያዋን ለምግብነት የቀረቡ ይሆናሉ እንጂ፥ እነርሱ ከምግብነት አልፈው እንዴት በራሳቸው ሕያው ሆኑ የሚለውን ጥያቄ የዝግመተ ለውጥ መላ ምት ሊመልስ አልቻለም።

ስለዚህ፡- ከዚህ ሁሉ የምግብ ዝግጅት ባሻገር፥ በላተኛ ባለ ሕይወት ከየት መጣ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ካለ ሕያውነት እንዴት ሙብላት ተቻለ?

ግዑዛን ነገሮችን እየበላ ያደገ፥ አድጎም አካላዊ ባለ ሕይወት ለመሆን የበቃ፥ ቀጥሎም እራሱን እያባዛ የገዛ ዘሩን ያበራከተ፥ ገና ከመጀመሪያው ከግዑዛን ተለይቶ፥ በራሱ ሕልውና ጸንቶ የቆየ መሆን አለበት። እንዲህ አይነቱን ሥራ ለማከናወን የተመደበ፥ እኛ የማናውቀውና የማናየው ሕያው ምንኛ ረቂቅ ይሆን።

አካል በገዛ ፈቃዱ እራሱን በጊዜ ውስጥ የመለዋወጥ ችሎታ ቢኖረውም፥ ያን ያህል ረቂቅ ሆኖ ዛሬ በምድር የሚታየውን የፍጥረታት ሁሉ ድንቅ ተፈጥሮ በገዛ ራሱ ሊያመጣ ቢችል ኖሮ፥ እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ እያደገ የመጣው የሰዎች ሥልጣኔ ይህንን ጉዳይ በግልጽ መመልከት አያቅተውም ነበር - ሳይንስና ሳይንሳዊ መረጃዎች ሁሉ በግልጽ ለሁላችንም በጉልህ ይቀርቡልን ነበር። ግን ይህ አልሆነም።

“በመጀመሪያ በምድር ላይ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ምግብ ለመብላት የመጣው የመጀመሪያው ሕያው ከየት ነው”? የሚለው ጥያቄ ዳርዊንን እጅግ ስላስጨነቀው፥ የሚከተለውን ደብዳቤ ለጓደኛው ጽፏል፡-

"....but if (and oh! what a big if!) we could conceive in some warm pond, with all sorts of ammonia and phosphoric salts, light, heat electricity, etc. present, that a protein compound was chemically formed ready to undergo still more complex changes, at the present day such matter would be instantly devoured or absorbed, which would not have been the same case before living organisms evolved.” Southwood Richard, 2003

ባጭሩ ወደ አማርኛ ሲተረጎም” “ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ኬሚካሎች ሁሉ በአንድ ኩሬ ተዘጋጅተው ቢቀርቡ፤ በአሁኑ ጊዜ ይህንን ምግብ ለመብላት ሲሉ ስንት ዘአካላት[35] በተረባረቡበት ነበር። ነገር ግን የጥንቱ ዘመን በአሁኑ ጊዜ እንዳለው አይደለም።”

አዎ! ዳርዊን በቅንነት እውነት ተናግሯል። የጥንቱን አናውቀውም። ዛሬማ፥ አየሩን ቫይረስና ባክቴሪያ ሞልተውታል። ከመሬት ላይ ስኳርና ዘይት ብናፈስ፥ ያንን ለመብላት የሚሽቀዳደሙ፥ በልተውም ባንድ ሌሊት አድገውና ወፍረው በአይናችን የምናያቸው ብዙዎች ናቸው።

በጥልቅ ባህር ውስጥ - የእሳተ ገሞራ ባለበት አካባቢ እንኳን ሳይቀር፥ ምግብ አግኝተው፥ ከዚያ እየተመገቡ የሚኖሩ ብዙ ሕያዋን መኖራቸው ታውቋል። ስለዚህ ተንጠልጥሎ ለቀረው፡- “የመጀመሪያው ዘአካል ነፍሱን ከየት አመጣት?” ለሚለው ጥያቄ እስከ ዛሬ ድረስ የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ቀጥተኛ መልስ ሊያገኝለት አልቻለም።

የመጀመሪያው ሕይወት የመጣው፥ በመሬት ላይ ለፍጡራን ምግብ ተዘጋጅቶ ቆይቶ፥ ሕይወትን በምድር ያስጀመረ ሕያው፥ በምድራችን ዙሪያ ከሌለ፥ ምናልባት ከሌላ ጠፈር፥ በጠፈር ድንጋይ ላይ ተጣብቆ የመጣ ሊሆን ይችላል ብለው በበኩላቸውን የሚሰማቸውን ያስታወቁም አሉ።

አንዳንድ የባዮሎጂ አስተማሪዎች “የመጀመሪያው ሕይወት የመጣው፥ በምድር ላይ ለፍጡራን ምግብ  ተዘጋጅቶ ቆይቶ፥ ሕይወትን የሚያቀጣጥል የጸሐይ

[35] የማይታዩ ጥቃቅን ነፍሳት - ከመሬት፥ ከአፈርና ከውሃ።

ብርሃንና ሙቀት ነፍስን ፈጠረ” ይላሉ። “ሁኔታዎች ሲስተካከሉ አካልም በድን ከመሆን ድንገት ብድግ ብሎ ቅጽበታዊ ሕይወትን ዘርቷል” በማለት ያስተምራሉ። “ለምሳሌ፡- በባህር ውስጥ የሚገኝ ኬሚካል (በተለይም ፖታሲየም ክሎራይድ) እና ተስማሚ ሙቀት እንደ ቀስቃሽ ሞተር ሆኖ ሕይወትን ያንቀሳቅሳል” በማለት፥ “በምድር ላይ ሕይወት የተፈጠረው በዚህ አይነት (ወይንም ተመሳሳይ) አጋጣሚ መሆን አለበት” በማለት ይደመድማሉ።

አዎ! ከጉድለቶቹና ከድክመቶቹ ባሻገር፥ አንድ ትንሽ ቀስቃሽ እውነት ላይ የሙጥኝ ብሎ ይዞ የሚፍጨረጨር ወደ እውነት መጠጋቱ አይቀርም። ከዚህ የዘመኑ ሥልጣኔ ደረጃ የተደረሰውም፥ ባንድ ጊዜ ከውሸት ወደ እውነት በመዝለል አይደለም፤ ከቀላል እውነት ተነስቶ በእውነቱ ላይ ብቻ የሙጥኝ በማለት ነው እንጂ። እውነቱን እውነት ውሸቱን ውሸት፤ የማይመስለውን አይመስልም፤ የሚመስለውንም ይመስላል ለማለት አንፍራ።

ለምንድነው ዳርዊን “ከአንድ ህዋስ ተነስተን በጊዜ ብዛት እዚህ ደረስን፤” ሲል ተቃዋሚው የበዛ? የሚሉ ቢኖሩ የሚከተለውን ያስተውሉ።

የተለያዩ አለቶችን በላቦራቷር መፍጠር ይቻላል። ማዕድናትም በሙቀት፥ በግፊትና በጊዜ፥ ልክ ነፍስ እንዳለው፥ እርስ በርስ እየተሰካኩ አለቶችን ሲፈጥሩ መመልከት ይቻላል (ተችሏል)። ልክ በዚህ አይነት፥ የአንድ አካላዊ ሕያው የዘር መደብ ወደ ሌላ አካላዊ ሕያው የዘር መደብ ሲለወጥ ማየት ግን አልተቻለም። እና፥ በላቦራቷር ወይንም በዱር ያልታየውን ሁሉ፥ እንዲሁ በስነ ልቦና ብቻ በማውጠንጠን፥ የዛሬውን የባዮሎጂና የኬሚስትሪ እውቀት ወደኋላ መልሶ፥ ስለአለፈው የሕያዋን እድገት ታሪክ ማገናዘቢያ ማድረግ አይቻልም።

“የተለያዩ ጠፈሮች በተለያዩ ጊዜያት ተዘረጉ - ብዙ ፍንዳታዎች ተካሂደዋል” የሚል መላምት እንደመኖሩ፥ እንዲሁም “የተለያዩ መሠረታዊ የሕያው ሴሎች ነበሩ” ከሚል መላምት ብንነሳም፥ ከግዑዝ አካል ብዙሐን ሕያው ሴሎች ብቅ ይላሉ[36] ለማለት የሚያስችለንን - ዝግመተ ለውጥ ከዘር መደቦች ወደኋላ ሲሄድ የሚያርፍበትን - ሥፍራ ማግኘት ነው ያስቸገረው። ይህንን እጅግ ርቅቅ ያለ ተፈጥሮ ካለ አንዳች መለኮታዊ ኃይል እንዲሁ ባጋጣሚ (እድል) ይቻላል ማለት አስቸጋሪ ሆኗል።

መቼም በሃሳብ ተረዳድቶ መዝለቅ የሰው ጠባዩ ነውና፥ እዚህ ላይ፡- ከዳርዊን ቀጥሎ እስከ ዘመናችን ድረስ ሳይንቲስቶች ያደረጉትን ጥናት፥ ሁለት

[36] abiogenesis

ክርስቲያን ሳይንቲስቶች (Fazale Rona and Huge Ross, 2004) እንደሚከተለው አቅርበውታል።

"እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከ1850 ዓ.ም. ከዳርዊን ቀጥሎ ለመቶ ሃምሳ ዓመታት ያህል የዝግመተ ለውጥ ትምህርት የተለያዩ አቅጣዎችና ቅርንጫፎችን ይዞ ከዘመናችን ደረሰ። በ1871 ዓ.ም. ዳርዊን በግዑዛን አካላት ቅንጅት ሕያው ህዋስ ብቅ ብሏል በማለት ደምድሟል፤ ግን የዛን የሱን ሕያው ህዋስ ግንባታ አብራርቶ አላስቀመጠውም ነበር።

በዳርዊን ጊዜ የነበሩ ሌሎች ተመራማሪዎች፥ በግዑዛን አካላትና በሕያው ህዋሶች መካከል፥ እርስ በርስ እየተዳቀሉ የሚባዙ ሞኔራ (monera) የተባሉ እንደ ልጋግ (gel) በየቦታው የሚከመሩ ነበሩ የሚል መላምት አቀረቡ።

የአንድ ሕያው ህዋስ ግንባታ በደንብ ታውቆ ሳይለይ ብዙ ከቆየ በኋላ፥ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን፥ የአንድ ሕያው ሴል ኬሚካሎች በበለጠ ተለይተው ታውቀዋል።

በዘመናችን፥ በአንድ ሕያው ህዋስ ሰውነት ውስጥ፥ ኢያሌ ፕሮቲኖች (የተለያዩ የንጥረ ነገሮች ሞሌኩሎች) ውስብብ ባለ ቅንጅት፥ የህዋሱን ሕልውና እንደሚወስኑ ታውቋል። ግን ከኬሚካሎቹ ጋር ነፍስ እንዴት እንደሚጣመር - መሠረታዊው የዝግመተ ለውጥ አንቀሳቃሽ ሞተር - የመጀመሪያው ሕይወት አመጣጥ ጥያቄ መልስ አላገኘም።

በቀደሙ ተመራማሪዎች፥ ሕይወትም (ነፍስ ያለው ነገር) እንደ ግዑዝ አካል ዘለአለማዊ መሆን አለበት፤ እና፥ ሕይወትም (ነፍስ ያለው ነገር) እንደ ግዑዝ አካል ሁሉ ቦታ መኖር (መገኘት) አለበት የሚል የፓናስፐርሚያ (panaspermia) ጽንሰ ሃሳብ ተሰነዝሮ ነበር። ከዚህ በመነሳት፥ የሕይወት በምድራችን መገኘት ምን ያስደንቃል፤ እንደ ግዑዝ አካል ሕይወት (ነፍስ ያለው ነገር) በጠፈር ሁሉ ነበረ፤ አለ፤ እድል ሲያጋጥመው ወደምድራችን ይገባል ተባለ።

በሌሎችም የጠፈር አካላትም ሕይወት (ነፍስ ያለው ነገር) ተዘርቶ ሊሆን ይችላል በማለትም፥ ሕይወት በጠፈር ደንጋዮች ተጣብቆ ከጠፈር ወደመሬት ተወርውሮ ገባ የሚሉ ነበሩ (ይኖራሉም)።

ሕይወት (ነፍስ ያለው ነገር) በሌሎች የጠፈር ሰዎች አማካኝነት ከምድራችንም ተዘራ..ወዘተ ሲባልም ቆይቷል። ሆኖም በጠፈር ሁሉ ሕያዋንን የሚያቆይ ሁኔታ - ነፍስ ስለ መኖሩ ባለመታወቁ፥ የpanaspermia ጽንሰ ሃሳብ በሃያኛው ክፍለ ዘመን በጠፈር ተመራማሪዎች ዘንድ ድጋፍን አላገኘም።

ከጥንት የአየር ሁኔታ ጋር በማዛመድና ጽንሰ ሃሳቦችን በዘመናዊ ላቦራቷር በመፈተን፥ የዘመኑ ሳይንቲስቶች ስለ ጥንቱ ሕያው አመጣጥ ለማወቅ ብዙ ደክመዋል። ውጤት፡- ንዴትና ብስጭት።"

ይህ ንዴትና ብስጭት ብቻ ሆኖ የቀረው የድካም ውጤት ለሕዝብ የማይገለጸው ለምን እንደሆነ፥ ፋዛል ሮና እና ሁጅ ሮስ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

"First they believe it opens the door to religious fundamentalism, second, they worry that a frank admission of ignorance will undermine funding.." Fazale Rona and Hugh Ross, 2004, pp.26

ሲተረጎም፡- "በመጀመሪያ ለሃይማኖት አጥባቂዎች በር መክፈት (እጅ መስጠት) ይሆናል፤ ቀጥሎም፥ የራስን ድንቁርናን በገሃድ ማሳየት፥ ለምርምር ገንዘብ አለማግኘትን ያስከትላል...።"

ከላይ የተጠቀሰውን በመጽሐፋቸው ያሰፈሩ ሁለት ግለሰቦች፥ እነርሱም ስለ ሕይወት አመጣጥ በአለም አቀፍ የሳይንቲስቶች ጉባኤ የሚሳተፉ ታላላቅ ሳይንቲስቶች ናቸው። እነርሱ ለሳይንቲስቶች ንባብ የሚሆኑ፥ ሰፋፊ ሳይንሳዊ ሃተታዎችን ጽፈዋል። ግን ከዛ መለስ፥ በተለይ ፋዛል ሮና በክርስቲያናዊ እውቀቱ፥ ከልቡ የተሰማውን ሲጽፍ፥ "እኔ በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት የሃሳብ ጥርቅሞች ሁሉ በእግዚአብሔር የበለጠ እንዳምን ነው ያደረጉኝ" ብሏል።

ይህንን ኃይለ ቃል የተናገረበት ምክንያት፥ ሌሎች ሃቀኛ ሳይንቲስቶች ከዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ራቅ ራቅ እያሉ እንዲሄዱ የሚያደርጋቸውም ዋና ምክንያት፡- የአካላዊ ሕያዋን ተፈጥሮ እጅግ ርቅቅ ያለ መሆኑን ሲያስተውሉ ነው። የመጨረሻዋ የባክቴሪያ ህዋስ እንኳን ወደ ሁለት ሺህ የፕሮቲን አይነቶችን ታካትታለች። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

ተፈጥሮአዊ ክስተቶች በዘፈቀደ የሚከናወኑ ቢሆን ኖሮ፥ በግዑዝ አካልና በሕያው ህዋስ መካከል አያሌ ሞኔራዎች ይከሰቱ ነበር። እንዲሁም በአንድ የዘር መደብና በሌላው የዘር መደብ መካከል ልክ እንደ ሞኔራ ተሠርቶ ያልተጨረሰ፥ መሃል ሰፋሪ ፍጥረት መኖር ነበረበት። ከየት ይምጣ፥ ያ ያልተጨረሰ - ንድፍ ሥራ።

ቀደም ሲል፥ ሕይወት ሙሉ ሕይወት ከመሆኑ በፊት፥ በግዑዛን አካላትና በሕያዋን ህዋሳት መካከል ሞኔራ (monera) የተባሉ መኖር ነበረባቸው ብለው የተፈላሰፉ እንደነበሩ ጠቅሰናል። ይኸውም ካለመኖር ወደመኖር ሲገባ፥ በሁለቱ (በመኖርና ባለመኖር) መካከል ቀሰስተኛ ሕይወት መኖር አለበት ከሚል ጽንሰ ሃሳብ በመነሳት ነው። ታዲያ፥ በቀድሞው ሃሳባዊ ሞኔራ መሠረት አንድ ልዩ ፍጡር

ከመምጣቱ በፊት ከመሃል የበፊቱንም የኋላኛውንም የሚመስል መገኘት የለበትም? (አንባቢ ይፍረደው። ለምንድነው አዲስ እና ፈጽሞ ልዩ የሆነ ፍጥረት በድንገት ብቅ የሚለው?)።

አንድ የዘር መደብ በዝግመተ ለውጥ ወደ ሌላው የዘር መደብ የሚለወጥ ከሆነ፥ ተፈጥሮ ቀርፋፋ ነው (ጊዜ ይፈጃል)፤ ስለዚህ እንደ ሞኔራ፥ በእንስሳትም የዘር መደቦች መካከል ቅርፍርፍ ያለ፡- የዚህ የዘር መደብ የማይሉት፥ የዛኛውም የዘር መደብ የማይባል - መሐል ሰፋሪ (ተሠርቶ ያልተጨረሰ - የተፈጥሮ ንድፍ ሥራ) መገኘት ነበረበት። የታለ? (አንባቢ ይፍረደው። ለምንድነው መሃል ሰፋሪ የጠፋው?)።

አሜባ ያልተጨረሰች እንስሳ አይደለችም፤ ቁልጭ ያለች - ምንም እንከን የማይወጣላት ናት እንጂ። እንቁራሪት፥ እባብ፥ ዳይናዞር፥ አይጠ መጎጥ..ወዘተ.. ሁሉም አንዴ እንደተፈጠሩ ሙሉ ሆነው የተገኙ፥ ምንም እንከን የማይወጣላቸው ናቸው። የቀድሞው ሃሳባዊ ሞኔራ - መሐል ሰፋሪ (ተሠርቶ ያልተጨረሰ - የተፈጥሮ ንድፍ ሥራ) የት ጠፋ? እንዴት ነው ከአንድ መደብ ወደሌላ የሚዘለል - መሃል ሰፋሪ ሳይኖር?

ከንቱ ልፋት። አንዲት ቁንጫ የምትዘለውን ያህል ሰው መዝለል ቢችል ኖሮ፥ መኪና፥ ባቡርና አይሮፕላን ባላስፈለገን ነበር። አንዲት ቁንጫ በፍጥረቷ ምን ይጎድልባታል? እስቲ በፍጥረታቸው ጎዶሎ የሆኑትን (ያልተሟሉትን) ሕያዋን ለይተን እናውጣ። የትኞቹ ናቸው ጎዶሎዎቹ? ለራሱ ለሚኖርበት አካባቢ ብቁ ሆኖ ያልተፈጠረ የትኛው ፍጥረት ነው? የትኛው ነው ሞኔራ - ወልጋዳ ፍጥረት - ያልተጨረሰ - ንድፍ ሥራ? እንዴት ነው፥ ዛሬ የምናየው የዘር መደብ ሁሉ፥ እንዲህ ቁልጭ ብሎ፥ ራሱን ችሎ፥ ራሱን መስሎ የሚገኘ።

ብዙውን ጊዜ ሳይንቲስቶች ልክ እንዲህ ባይሆን ኖሮ እያሉ ይመራመራሉ። ፍጥረት (ነፍስ ያለውም የሌለውም) ልክ እንዲህ ርቅቅ ባይል ኖሮ በሚለው አስተሳሰብ ብዙ ሲቆዩበት፥ ያው የነሱ አስተሳሰብ ወደ እግዚአብሔር ይመራቸዋል።

ፋዛል ሮናም እንዲህ አለ፡- "..The scientific harmony between the Bible and nature's record reinforces my conviction." ሲተረጎም፡- "የተፈጥሮን እንዲህ መቀነባበር፥ በመጽሐፍ ቅዱስና በሳይንስ መካከል ያለውንም ስምምነት ስመለከት አመለካከቴን ያጠናክርልኛል።"

ፋዛል ሮና በለሰለሰ አንደበትና በትህትና በአንድ አባሪ ገጽ ብቻ ለርሱ ሳይንሳዊ አመለካከቱን የሚያስምሩለትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዘርዝሯቸዋል። እነኚህ ጥቅሶች የሰውን ሁሉ ሳይንሳዊ አመለካከት የሚያስምሩ ናቸው ብሎ፥ እነርሱን

በይፋ ማውጣት፥ ትርፉ ጭቅጭቅ ሊሆን ይችላል። እስከዚህ ድረስ ለጠቃቀስናቸው ጥቅሶች እንኳን፥ እስካሁን ብዙ ትችት አይቀርልን ይሆናል።

በዚህ መጽሐፍ ግን አልፎ አልፎ ነስነስ የተደረጉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አንድም በድፍረት፥ እንዲሁም ከመንፈሳዊ ቅንአት የተነሳ ነው እንጂ፥ ሳይንስና ሃይማኖትን በማዛመድ፥ ትክክሉ ይህ ነው በማለት አይደለም። እግዚአብሔር እውነቱን ይግለጽልን እንጂ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከሳይንስ መጻሕፍት እውነቱን ፈልቅቆ የሚያወጣ አልተገኘም (ከእምነት በስተቀር)።

በሳይንስ ተራቀን የምንደርስበት እውቀት ውሱን ቢሆንም፥ የሚመስለውን ከማይመስለው የመለየት ችሎታ አናጣም። በውስጠ ልቦናችን አገናዝበን፥ በራሳችን አውቀን የምናምነውን ለማመን (የምንቀበለውን ለመቀበል) እንዲረዳን ከብዙ ሳይንሳዊ ጥያቄዎች መካከል ጥቂቶቹን አቅርበናልና፤ በጥሞና እናስተውላቸው።

## <u>ፈጣን ዝግመተ ለውጥ እንዴት?</u>

በትርጉም የምንስማማ ከሆነ፥ ዝግመተ ለውጥ ሲባል ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ነው። ታዲያ፥ ቀደም ሲል፥ ከእልቂት በኋላ የፍጥረታትን መበራከት በቂ ሳይንሳዊ ማስረጃ ከሚገኝላቸው ሳይንሳዊ መጻሕፍት (ጂኦሎጂ - ፓሌዎንቶሎጂ.. ወዘተ..) የተመለከትነውን ላንድ አፍታ እየከለስን እናሰላስል።

ባለፈው ምዕራፍ ባጭር ባጭሩ የጠቀስናቸው፥ በተለያዩ የእድሜ ክልሎች የዘቀጡ አለቶች ውስጥ ተከማችተው የተገኙ የአካለ ቅሪቶች ብዛትና አይነት፥ በአይናችን አይተን፥ በሌሎችም በቂ ሳይንሳዊ መረጃዎች የተደገፉ መሆናቸውን አረጋግጠናል።

ከአንድ የእልቂት ዘመን በኋላ፥ በዝቅጠ አለቶች ውስጥ በብዛትና በአይነት የሚታዩት አካለ ቅሪቶች፥ በአንጻራዊ አነጋገር፥ “በአጭር ዘመናት” የተከማቹ መሆናቸውን ከዝቅጠ አለቶች ምርምር ተረድተናል። ይህም ሆኖ ሳለ፥ በሁለት የተለያዩ ዘመናት በዘቀጡ መደቦች ውስጥ የሚካተቱት በርከት - በርከት ያሉ አካለ ቅሪቶች ምንጊዜም አንዱ ከሌላው የተለየ ነው። ፍጥረት ከሌለ፥ ለምንድነው በአንድ የዝቅጠ አለት መደብ በብዛት የሚታዩት ቅሪተ አካላት በሌላው መደብ ከሚታዩት እጅግ የተለዩ የሚሆኑት? ለምንድነው በመካከላቸው ሁለቱን አካለ ቅሬታት የሚያመሳስሉ ሌሎች አካለ ቅሪቶች ጥፍት የሚሉት?

ይህ መጽሐፍ የባዮሎጂ ምርምር ቢያንሰው እንጂ፥ የጂኦሎጂ ምርምር ጎዶሎነት ስለሌለበት፥ አሁንም “ከእልቂት በኋላ ድንገተኛ - “በአጭር ዘመናት” ውስጥ

- የፍጥረታት መበራከት እንዴት ሊሆን ቻለ? እንዴት ነው ይህ መበራከት ካለፍጥረት በዝግመተ ለውጥ ብቻ (ባንድ ጊዜ) የተከናወነው? ዝግመተ ለውጥ ፍጥን ፍጥን የሚለው መቼና መቼ ነው? ፈጣን ዝግመተ ለውጥ አለ እንዴ? ካለስ እንዴት? ፈጣን ከሆነ ለምን ዝግመት ተባለ? ወይንስ ይህንን እጅግ የሚፈጥነውን ዝግመተ ለውጥ ይሆን እኛ በስህተት ፍጥረት እያልን የጠራነው" በማለት ይጠይቃል። ።

የማይጣጣሙ ሳይንሳዊ አመለካከቶች ያሉ ይመስላል፤ እናም፥ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ሕጋዊ ናቸው። ለጠየቅነው ጥያቄ ያው የጂኦሎጂ ምርምር ጎዶሎነት ያለበት ዳርዊን፥ አሁንም ጭንቀት ሲገባው የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል፡-

"I can answer those questions and objections only on the <u>supposition</u> that the geological rercord is far more imperfect than most geologists believe." Charles Darwin 1958, pp. 439

ሲተረጎም፥ "የተጠቀሱትን ጥያቄዎችና ተቃውሞዎች የምመልሰው፥ በጂኦሎጂ የተገኙ መረጃዎች፥ ጂኦሎጂስቶች ከሚያስቡት በላይ የተዳከሙ ናቸው በሚል ግምት ነው።"

ግድየለም፤ የዳርዊንን አባባል ልክ ነው ብለን እንቀበለው። ታዲያ ለወደፊት በጂኦሎጂ የሚገኙ መረጃዎች ይጠበቃሉ እንጂ፥ መረጃዎቹ ሳይገኙ ለዳርዊን ብለን የማይመስለውን ሁሉ እንቀበል? ዳርዊን አንኳን ምናልባት በቅንነት <u>supposition</u> (ግምት) የሚለውን፥ ለዛሬ ተማሪዎች እንደ እውነት ባይቆጥሩት ይሻላል። ሆኖም፥ ከዳርዊን በኋላ (ከ1850 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2018 ዓ.ም. ድረስ፥ ለመቶ ስልሳ ስምንት ዓመት) በጂኦሎጂስቶች የተሰባበሩ ድንጋዮች ይመስክሩ። ከጥፋት ዘመናት ሁሉ ቀጥሎ፥ አዳዲስ ፍጥረታት በዝቅጠ አለቶች ከመታየታቸው ሌላ፥ የዳርዊንን ዝግመተ ለውጥ የሚያጠናክር ሁለት የተለያዩ የዘር መደቦችን የሚያገናኝ ቅሪተ አካል በዝቅጠ አለቶች ውስጥ አልተገኙም።

በእርግጥ፥ የአንድ መልእክት ይዘት ደረጃ በደረጃ መታየት ይኖርበታል። ለተጠቀሱት ጥያቄዎች የዳርዊን መልስ ግምታዊ መሆኑን እርሱ ራሱ ተናግሯል። ሆኖም፥ ብዙውን ጊዜ ሰዎች በደምሳሳው የተነገረውን ሁሉ (በግምት የተነገረውን ሁሉ) እንደ ሳይንሳዊ አድርገው ይወስዱታል። ስለዚህ፥ "እንዴት ነው በአንድ ዝቅጠ አለት ውስጥ፥ ባንድ ጊዜ አያሌ የተለያዩ አካለ ቅሪታት በብዛት የሚታዩት?" ለሚለው ጥያቄ በቂ ሳይንሳዊ መልስ ሳይሰጡ፥ እንዳው በደፈናው ከዝግመተ ለውጥ በስተቀር ፍጥረት የለም ማለት ሞኝነትና ድፍረት መሆኑ ይነገራቸው ዘንድ ግድ ይላል። ሃቀኛ ሳይንቲስቶች "ቢሆን ኖሮ" ብለው አይደመድሙም።

የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ለመካድ የሚያስችል ሳይንሳዊ ድጋፍ የለም። በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሳይንቲስቶች እግዚአብሔር የፈጠረና የሚፈጥር - እንዴ ፈጥሮ ያላበቃ - ዝግመተ ለውጥና ቅጽበተ ፍጥረት - ሁሉም የርሱ የአምላካችን ሥራ መሆናቸውን ያስረዳሉ። እነርሱም ቢሆኑ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደፈጠረ ሳይንሳዊ መግለጫ መስጠት ስለማይችሉ፥ በመንፈሳዊነታችን እንድንመራመርበት ነው የሚተውት።

እንግዲህ አንባቢ ያስተውል። እኛ ምድራውያን ስለሆንን፥ እናም፥ በምድራዊነታችን ምክንያት ሊገባን የሚችለው ምድራዊ የሆነውን ብቻ ነው። ከዛ አልፈን መሄድ - እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደፈጠረ ማወቅ አንችልም። እዚህ ላይ ነው ሃይማኖታዊ ሃተታዎች እምነት የሚሆኑት (እንደ ሰው)።

ታዲያ፥ ባንድ በኩል የሃይማኖትና የእምነት በሌላም በኩል የሳይንስን ድንበርና ወሰን ያላወቁ አንዳንድ ግለሰቦች፥ ሳይንስን ከበላይ ያደርጉና፥ የእግዚአብሔር ፈጣሪነቱን ለማረጋገጥ የሳይንስን ድጋፍ ይሻሉ። አይደለም። የእግዚአብሔር ፈጣሪነት በሳይንስ አይረጋገጥም። ይህንን የሚያረጋግጥ ግላዊ እምነት ብቻ ነው።

እነኚህ የሳይንስን ድንበርና ወሰን ያላወቁ አማኞች ይቀባጥራሉ፤ እንዲህም ይላሉ፥ "ፍጥረታት ሁሉ በቀዳማይ ሕይወት ባለ ጊዜ (በዴቮንያን) ውስጥ ተፈጥረዋል፤ ባንድ ጊዜ።" ይህንን የሚሉት አብዛኛው አካለ ቅሪት የሚገኘው በዚያን ዘመን በዘቀጡ ዝቅጠ አለቶች ውስጥ ስለነበር እና ፍጥረት ባንድ ጊዜ ተከናወነ ለማለት ፈልገው ነው።

አዬ! ከንቱ ልፋት። ተሳስተዋል፤ ምክንያቱም፡- ዝሆን፥ ጎሽ፥ አንበሳና ነብር፥ ዝንጀሮና ጦጣ፥ በዴቮንያን ዘመን ከዘቀጡ ዝቅጠ አለቶች ውስጥ ስለመገኘታቸው የሚያመሳክር አንድም በዝቅጠ አለት የተገኘ ቅሪተ አካል አልተገኘም። ስለዚህ፥ ፍጥረታት ሁሉ በቀዳማይ ሕይወት ውስጥ ባለ ጊዜ (በዴቮንያን) ተፈጥረዋል የሚሉ በፈጣሪ የሚያምኑ (ክሪኤሺኒስቶች)፥ እግዚአብሔር ፈጠረ ለማለት የጂኦሎጂ መረጃዎችን በትክክሉ ካላስቀመጡ አይሆንላቸውም።

የዳርዊን ተከታዮች የጂኦሎጂ መረጃዎችን ቢጠባበቁ፥ አንድ ትንሽ መረጃ ቢቀርብ እንደገና ሌላ አዲስ የጽንሰ ሃሳብ ጥንስስ ይፈላል። የዚያን ጊዜ ለእምነት የሳይንስን ድጋፍ የሚከታተሉ ተጠራጣሪዎች የበለጠ ይወናበዳሉ። ሳይንሱንና ሃይማኖቱን ማጣጣም አስቸግሮአቸው፥ እግዚአብሔር በአንድ ቀን ፈጠረ ለማለት እየፈለጉ፥ በጎንም የጂኦሎጂ መረጃዎችን በትክክል ባለመተርጎም፥ እንዲሁ በዝምታ የተቀመጡም አሉ። ግን አይፈረድባቸውም፤ ፍጥረት በተለያዩ ጊዜያት ነበር እንዳይሉ

በሃይማኖት የተማሩት ይዟቸው ይሆናል። "አንድ ቀን" የተባለውን በሌጣው ስለተመለከቱት ይሆናል፥ በሳይንስና በሃይማኖት መካከል የሚማልሉ ተጠራጣሪዎች የሆኑት። እግዚአብሔር ሲፈጥር ለኛ በተለያዩ ጊዜያት ቢሆን (ቢመስለንም) ለርሱ ግን "ባንድ ጊዜ" መሆኑን ካለመገንዘብ የተነሳ - ለዚህ ነው ከሃይማኖትም ከሳይንስም ሳይሆኑ፤ ከሁለት የተራራቁ ሃሳቦች መሃል የሚንገላቱት።

አላማኝ ሳይንቲስቶች አማኝ ሳይንቲስቶችን፥ "በእውነት እናንተ እግዚአብሔር ፈጠረ የምትሉ ከሆነ፥ አካላዊ ማስረጃዎቻችሁን አቅርቡልንና እኛም እንደናንተ እንመን" ይሏቸዋል። አማኞቹም የተጠየቁትን ማቅረብ ያቅታቸዋል።

እንደገናም፥ "ከአንድ የእልቂት ዘመን በኋላ አዲስ ዘር ቢታይ፥ ያንን አዲስ ዘር፥ የዛን ጊዜ ነው፥ የናንተ እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረትን ፈጠረ የምትሉት?" ብለው ያፋጥጧቸዋል።

ፍጥረት የዛን ጊዜ እንዳልተከናወነ፤ እግዚአብሔር ሲፈጥር የጂኦሎጂ የጊዜ ሚዛኖችን (geologic time scales) እየተከተለ እንዳልነበረ ቢነገራቸው፤

"ታዲያ እግዚአብሔር ባንድ ጊዜ ከፈጠረ ለምንድነው ፍጥረቱ ሁሉ ባንድ ላይ በአንድ የጂኦሎጂ መደብ ያልታየ?" ይላሉ።

እዚህ ላይ ነው ይህ መጽሐፍ ወገቤን ከማለቱ በፊት፥ በዚህና በሚቀጥሉት ምዕራፋት በአጽንኦት "ለየት ያለ ሃሳብ" በትህትና የሚያቀርብ። የዚህ መጽሐፍ ዋና አላማ አንድ ወጥ በሆነ ፍልስፍና ጥያቄዎቻችንን ለመመለስና አላስፈላጊ ጥርጣሬዎችን በማስወገድ፥ ለተሻለ ሚዛናዊ አመለካከት በር መክፈት ነው።

መቼም ብዙ ነገር ከአካላዊው አለም ብቻ - በሳይንስ እውቀት ብቻ - መረዳት ስለማይቻል፥ ወደ መንፈሳዊ ምርምር መግባት አስፈላጊ ይሆናል። ቀድሞም፥ የዚህን የዳርዊንን ጉዳይ ከዳር እናድርስ ብለን ነው እንጂ፥ ከአንባብያን ጋር ብዙ አዳዲስ ሃሳቦች ይኖሩናል። (ፍጥረት ከሰማይ ስለመሆኑ እና ስለ "ጊዜ ጽንሰ ሃሳብ" በሚቀጥለው ምዕራፍ እናያለን)። ግን፥ እስቲ ከዛ በፊት፥ ለተማራማሪ ሳይንቲስት፥ ለተማሪዎችም ብለን፥ የዳርዊንን ጉዳይ እልባት እናበጅለት።

## **"ፈጥኖ ደራሽ" ዝግመተ ለውጥ እንዴት?**

የሚከተለው "ሳይንሳዊ ነው፤ ወይም ሃይማኖታዊ ነው፤" ሳንል፥ ለእንስሳትም የሚያስብላቸው መኖሩን በቀላሉና ቶሎ ለማገናዘብ ይረዳ ዘንድ ብቻ፥ ስለ ዝሆኖች ያለ ጥርስ መወለድ በምሳሌነቱ ብቻ፥ ዘና ብለን እንመልከት።

ዝሆኖች፥ በዱር ሳርና ቅጠል እየበሉ፥ ሌሎች እንስሳትን የማይተናኮሉ፥ በሰላምና በፍቅር የሚኖሩ የዋሃን እንስሳት ናቸው። ዝሆኖችም እንደ ሰው የተጠናከረ ማህበራዊ ኑሮና የራሳቸውም ቋንቋ አላቸው። ጩኸታቸው በረጅም የድምጽ ሞገድ ስለሚጓዝ ለነርሱ ከሩቅ ይሰማቸዋል። አብሮ መዝፈን እና አብሮ መጨፈር በዝሆኖች የተለመደ ነው። ማዘን - መተከዝ፥ ማልቀስም በዝሆኖች ያለ ነው። የኛ የሰዎች ሕብረተሰብአዊ አብሮ የመኖር ሁናቴ ከዝሆኖች ሕብረተሰብእዊ አብሮ የመኖር ሁናቴ በምን ይበልጣል (ይሻላል)?

ተፈጥሮም ሲያቆነጃቸው፥ ሁለት ነጫጮችና ትላልቅ ጥርሶች አደላቸው። ሰዎችም እነኚህን ጥርሶች ከዝሆኖቹ እየነጠቁ ለራሳቸው ለማድረግ ፈለጉ። ግን፥ የዝሆን ነፍሱ ካልጠፋ ጥርሶቹን አውልቆ መውሰድ ስላልተቻለ፥ ለሁለት ጥርስ ሲባል የዝሆኖች ሕይወት በከንቱ ይጠፋ (ይረግፍ) ጀመር በሰዎች።

አይይይይይ! ግዙፉ ዝሆን ሕይወቱ ከምታልፍ ሲል፥ በቀን ከአስራ ሁለት ሰዓት በላይ ሳርና ቅጠል እየበላ ያዳበራቸውን ጥርሶቹን፥ ለሰዎች በውዴታና በነጻ ቢለግስ ይመርጥ ነበር፥ ሕይወቱን ከሚያጣ።

አፍሪካውያን፥ ከሌሎችም አውሮፓውያን ጋር በመተባበር፥ ለሁለት ጥርሶች ሲሉ፥ ዝሆኖችን እየገደሉ በየጫካው እንዲበሰብሱ አደረጉ። ካሁን በፊት ምድር የነርሱ እንዳልነበረች ሁሉ፥ አሁን በሰዎች ስለተሰቃዩ ዝሆኖች እጅጉን አለቀሱ፤ አዘኑ፤ ተከዙ፤ ጮሁ። ልጆቻቸውም በአባቶቻቸው መገደል ምክንያት፥ በዚህም በዚያም ምድራዊ ኑሮ ያልሆነላቸው፥ በኑሮአቸው ሃዘንተኞች፥ የተበደሉ እና የተጎዱ ሆኑ። እናቶችም፥ የልጆቻቸው ጥርስ ባደገ ቁጥር፥ በፍርኃትና በሰቀቀን እየተሸማቀቁ የሚኖሩት ኑሮ ካለመኖር ምንም አልተሻለም።

አይይይይይ! ለእንዲህ አይነቱ የሰው ልጅ ግፍ በእግዚአብሔር ፍጡር ላይ፥ ምን ምላሽ ይኖረዋል? እግዚእብሔር እንኳን ባይኖር (ወንም ባይሰማ)፥ ምን ይላል ይህ ተፈጥሮ፥ ይህ የሕያዋን በዚች ምድር ላይ የመገኘት እጣ ፈንታ?

አንባቢያን ሆይ! ይህ መጽሐፍ ለማስረገጥ የሚሞክር፥ እኛ ሰዎች ብንሆንም፥ ሰዎች ብቻ አለመሆናችንን ነው። እኛ ሰዎች ብንሆንም፥ የከዋክብት ሽራፊዎች እንደመሆናችን መጠን፥ ዝሆኖችም ነን። እኛ ስንተነፍስ የሚተነፍስ ሕያው ሁሉ፥ በዛች ባንድ እስትንፋስ በምትባል ነገር (ሕያውነት) እንዛመዳለን። ሁላችንም ምድራውያን ነን። ለመኖር ስንል የምናደርገው ሁሉ አኗኗራችንን ይወስናል። የሁሉም ሕይወት ለሁላችንም ያው ሕይወት ነው፤ ያንዱ ከሌላው አያንስም ወይንም አይበልጥም። እኛ በዘፈን ራሳችንን እንደምናስደስት፥ ዝሆኖች ኩንቢያቸውን ወደላይ ከፍ አድርገው በሚያሰሙት ልዩ ዜማ (የነርሱ ዘፈን)፥ እራሳቸውን ያስደስታሉ። እኛ

ስንደንስ እነርሱም እንደሚደንሱ ሁሉ፥ እኛ እንደምናዝን ዝሆኖችም ያዝናሉ። በኛ ቤት ያለው ሁሉም ዘንድ አለ። ሁላችንንም የሚለያየንን ትተን የሚያዛምደንን ብንመለከት፥ የሁላችንም አንድነት ነው ጎልቶ የሚታይ።

ይህንን ከላይ የጠቀስነውን ሁሉ እንደነ አባ ሳሙኤል ዘ ዋልድባ ያሉ መንፈሳውያን ይገነዘቡታል፥ ያውቁታልም። አብዱል መሲህ (ገብረ ክርስቶስ) የተባሉ ኢትዮጵያዊ ባህታዊ በግብፅ በረሃ በዋሻ ውስጥ ብቻቸውን ሲኖሩ፥ ጎረቤቶቻቸውና ጠያቂዎቻቸው የዱር አራዊት ነበሩ። ከእንስሳቱም ጋር (እባብ ሳይቀር) ምግብ እና ውሃ እየተካፈሉ ነበር የሚኖሩት።

ባህታዊውን - አብዱል መሲህን (ገብረ ክርስቶስን) "እንዴ! ምን ይሠራሉ ከዚህ ከበረሃው? ተኩላ ቢበላዎትስ?" ሲሏቸው፥ "እንዴ! እኔም እኮ ተኩላ ነኝ፤" ነበር መልሳቸው[37]።

ከሳይንስ ውጪ - "በቅጽበት ሊያጠፉን የሚችል ኃይል ድንገት ሲመጣብን፥ እራሳችንን በራሳችን ለማዳን በማንችልበት ወቅት፥ ለኛ ረዳት እየሆኑ የሚያገለግሉ መናፍስት ቢኖሩስ!" ብለን እንድንመራመርበት ያህል ብቻ፥ የሚከተለውን እንመልከት።

ወሬ የሚያጣፍጠው BBC News/Africa: -"Elephants 'ditch tusks' to survive" ወደ አማርኛ ሲተረጎም፥ "ዝሆኖች ከመገደል ለመዳን ሲሉ፥ ጥርሶቻቸውን ይጥሉ ጀመር" ብሎታል። እንዲሁም "Our research indicates that more than 38% of Luangwa elephants carry no tusks" ወደ አማርኛ ሲተረጎም፥ "ባገኘነው ምርምር መሠረት ከ38% በላይ የሚሆኑ የሉአንግዋ ዝሆኖች ጥርስ የላቸውም" በማለት፥ ካለ ጥርስ የሚወለዱ ዝሆኖች መበራከታቸውን ይጠቁማል።[38]

ሰዎች ዱርና ጫካውን ሲመነጥሩ አፈሩ ተሸረሸረ። በዚህን ጊዜ በአፈሩ ውስጥ የሚገኙ፡- ካልሲየም፥ ፎስፎረስ፥ ፖታሲየም እና ሌሎችም ለጥርስ መገንባት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ከአፈሩ ተለይተው፥ በውሃ እየሟሙ፥ ወደ ወንዝ ገቡ፤ ስለዚህም የሚወለዱ ዝሆኖች ለትላልቅ ጥርሶች የሚሆን በቂ ንጥረ ነገሮችን ባለማግኘታቸው፥ ጥርስ ሊያበቅሉ አልቻሉም ማለት ይቀል ነበር። ግን ይህም ቢሆን ካለ በቂ ማስረጃ አይታለፍም። ካለ ጥርስ የሚወለዱ ዝሆኖች ያሉበት አካባቢ፥

---

[37] ግጥም - ስለ ገብረ ክርስቶስ - ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሁለተኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ዘጠኝ።

[38] http//news.bbc.co.uk

ከአፈሩ ውስጥ የተጠቀሱት ንጥረ ነገሮች መጉደላቸውን የሚያመለክት ምንም መረጃ ስለሌለ፥ ይህ ሃሳብ ውድቅ ነው።

የተፈጥሮ ሁኔታ ሁሉ እንዳለ ሆኖ፥ ዝሆኖች ከሚገደሉበት አካባቢ የሚኖሩ ዝሆኖች ናቸው ካለ ጥርስ የሚወለዱት፥ ግድያ ከሌለበት አካባቢ የሚኖሩት እስካሁን ደህና ናቸው። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ግን እኛም በቸኮላ መቶ በመቶ ያልተረጋገጠ ወሬ ይዘን በመነሳት ወደማይፈለግ አቅጣጫ እንዳናመራ እንጠንቀቅ። ይህንን በዚህ እንተወውና፥ ለመሆኑ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ስምም ሆኖ ለመኖር የሚያበቃ ለፍጡራን ሁሉ የተሰጠ ጸጋ ከሁላችንም ዘንድ የሚኖር ከሆነ፥ የዚህን የተፈጥሮ ጸጋ ሥራውን ከዚህ እስከዚህ ድረስ ብቻ ነው ብሎ መወሰን እንዴት ይቻላል።

የአካባቢ ሁኔታ ሲለዋወጥ እራስን በራስ ለመለወጥ በሚያስችል ውስጠ ተፈጥሮአችን መጠነኛ ለውጥ (mutation) ስናደርግ ቆይተናል፤ መስሎ ማደር የእንስሳት ሁሉ ጠባይ ነውና።

በቅጽበት ሊያጠፋን የሚችል ኃይል ድንገት ሲመጣብን፥ እራሳችንን በራሳችን ለማዳን በማንችልበት ወቅት፥ ለኛ ረዳት እየሆኑ የሚያገለግሉ መናፍስት መኖር አለባቸው በማለት የሚያምኑ ሰዎችን ለማሰናከል (?)፥ ከሳይንቲስቶችም ሆነ ከሌሎች አወቅን ባዮች(?) የሚከተለው ሃሳብ ቀርቧል።

"effective evolutionary response to escape slaughter by poachers”[39] ሲተረጎም፡- “ግድያን ለማምለጥ “ፈጥኖ ደራሽ” ዝግመተ ለውጥ ከተፍ ብሎ ዝሆኖችን ከችግር አወጣቸው።”

ይህንን “ፈጥኖ ደራሽ” የተባለ ዝግመተ ለውጥ ከእልቂቶች በኋላ ከተፈጠሩ አዳዲስ እንስሳት ጋር ለማዛመድ እንሞክር። በእውነት እንደ እልቂት አይነት ከፍተኛ አደጋ ሲከሰት ዝግመተ ለውጥ የሚፈጥን ከሆነ፥ ከእልቂቶች በኋላ የተፈጠሩ እንስሳትም አዳዲስ ሰውነታቸውን ያገኙት በዚህ “ፈጥኖ ደራሽ” ዝግመተ ለውጥ ይሆናል ማለት ነው? ከዚህስ ግሩም ማመሳሰል አልፈን ፈጣኑን እና ቀሰስተኛውን ዝግመተ ለውጥ መለየት የሚያስችል ሳይንሳዊ ጥበብ ብንፈልግ ይመረጣል። ይህ ጥበብ ከወዴት ይገኛል?

እስከመቼ ድረስ የተጻፈውን ሁሉ አሜን እያልን እንቀበል? እስከ መቼ ድረስ ነው ከዳርዊን ፍልስፍና ላለመላቀቅ ስንል “effective evolutionbary response” - “ፈጥኖ ደራሽ ዝግመተ ለውጥ” እያልን የምንቀባጥረው?

ከጋዜጠኛው ይልቅ፥ ሳይንቲስቶች የሚስማሙበት የሚከተለው ይሆናል።

---

[39] http//news.bbc.co.uk

ግድያን ለማምለጥ "ፈጥኖ ደራሽ" ዝግመተ ለውጥ ከተፍ ብሎ ዝሆኖችን ከችግር አላወጣቸውም። ከቀድሞውኑ በተወሰኑ ዝሆኖች ውስጣዊ የዘር ጥንስስ (ጂን - በራሂ) ውስጥ ካለ ጥርስ የመወለድ ጠባይ ይኖራል። በአካባቢ የሚመጣው ለውጥ ዘገምተኛ ነው የሚሆን። ሲወለዱ ጥርስ የማይኖራቸው ዝሆኖች ከጥንቱም ከእናትና አባቶቻቸው የዘር ጥንስስ (ጂን - በራሂ) ውስጥ በሚመነጭ ባህሬ መሆን አለበት። ግን፥ እንስሳት ሁሉ በዝግመተ ለውጥ እዚህ ደረሱ እንጂ አልተፈጠሩም ከተባለ፥ በተዘዋዋሪ እግዚአብሔር አልፈጠረም ማለት ነው። እግዚአብሔር አልፈጠረም ማለት ደግሞ እግዚአብሔር የለም ማለት ነው። እግዚአብሔር የለም ማለት ደግሞ መንፈስ የለም ማለት ነው። መንፈስ የለም ማለት ደግሞ ከአካላዊው አለም በስተቀር ሌላ አለም፤ መላእክት የሚባሉት ሁሉ የሉም፤ ሰውም በአካሉ ሲሞት ነፍሱም ለዘለአለም ጠፍታ ትቀራለች ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነ ሁሉ የአካባቢ ሁኔታዎችን ተከትሎ በራሱ ላይ መጠነኛ ለውጥ እንዲያመጣ ከሚያደርገው ውስጣዊ ባህሬ ጋር የተፈጠረ በመሆኑ፥ ይህ የዝሆኖች ካለ ሁለት ጥርስ መወለድ እራስን በራስ ለመለወጥ የሚያስችል ውስጣዊ ባህሬ (mutation) ነው ብንልም፥ እንዲህ አይነቱ ለውጥ በድንገት በአንድ ሰው እድሜ ውስጥ መፈጸሙ ከአካላዊ (ሳይንሳዊ) ገለጻ በላይ ነውና፤ ይህ ጉዳይ አንድ የማናውቀውና ያልገባን ነገር ነው ብለን፥ በትህትና የሚከተለውን እንጠይቅ።

ሕያው በምድር እንዴት ይኖራል የሚያስብለት ሳይኖር? ለዝሆንስ ከሰው በስተቀር ሌላ የሚያስብለት አይኖርም ወይ? ሰው ቢጨክን - ለእንስሳውም ለእጽዋቱም ሳይራራ - ሁሉንም ለማጥፋት ዘመቻ ቢጀምር፥ ለአንድ ለአካላዊ ሕያው (እንስሳም ሆነ እጽዋት) የወደፊት ሕልውናውን የሚያስከብርለት (ተፈጥሮ እንዲቀጥል የሚያደርግ)፥ ከሰው በላይ የሆነ፥ ሌላ ኃይል ሊኖር አይችልም ወይ?

ማንኛውም ፍጥረት (ወይንም ቁስ አካል) ለምክንያት - በምክንያት ተፈጥሯልና፤ በበቂ ምክንያት ይኖር ዘንድ፥ ካለ በቂ ምክንያትም እንዳይጠፋ ሕያው መንፈሱ አካላዊ ባልሆነ መንገድ አስቀድሞ ይኖር እንደነበር፤ አሁንና ለወደፊትም አብሮት ይኖራል ብሎ ማሰብም ይቻላልና፤ እስቲ ከዚሁ ጋር በማያያዝ፥ ካሁን በፊት በተለያዩ ምክንያቶች ስለ ጠፉ (extinct) እንስሳት እናስብ። ጠፍተዋል የተባሉ እንስሳት ከየት ነው እንደገና ብቅ የሚሉት? ለምን እና እንዴት?

ለፍጡራን (ለዝሆኖችም ሆነ ሌሎች እንስሳት) በስተጀርባቸው ሆኖ ሕልውናቸውን የሚጠብቅላቸው ኃይል ቢኖር (እነርሱንም ዘራቸው እንዳይጠፋ የሚጠብቃቸው፤ ከጠፉም እንደገና ሁኔታዎች ሲስተካከሉ ብቅ እንዲሉ የሚያደርግ ኃይል ቢኖር)፥ ይህ በሳይንቲስቶች ባለመገለጹ ብቻ ውሸት ነው አይባልም።

ከቀድሞውኑ በተወሰኑ ዝሆኖች ውስጣዊ የዘር ጥንስስ (በራሂ) ውስጥ ካለ ጥርስ የመወለድ ጠባይ ሊኖር እንደሚችል ገልጸን ነበር። ታዲያ፥ ይህንንም ቢሆን፥ እግዚአብሔር አውቆ ያደረገው ሊሆን ይችላል፤ የወደፊቶቹን ጨካኝ ሰዎች አስቀድሞ በመመልከት።

አሁንም "ዝሆኖቹ እንዴት ካለ ጥርስ ተወለዱ?" ጥያቄያችን አልተመለሰም። ይኸው እንግዲህ፥ በሳይንሱም በእምነቱም በኩል ብንመጣ፥ እውነት እውነትነቱ የሚረጋገጥ ከውሸት ሲርቅ መሆኑ ነው። ታዲያ፡-

- ለጥያቄዎቻችን ሁሉ መሠረታዊው ጥያቄ የሚሆን፡- "የፍጥረታት (እንስሳትም) አካላዊነታቸውና መንፈሳቸው እንዴት ይነጣጠላሉ?
- "የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ፥ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?" መክብብ 3፡21
- የሰው ልጅ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ያዳበረው እውቀቱ የምድር ሕያዋንን ሁሉ ጠራርጎ ለማጥፋት የሚያበቃ ሊሆን ይችላል። ግን ሰው በገዛ ተንኮሉ እራሱን ቢያጠፋ፥ ሌሎች ምስኪን እንስሳትን እንዲተርፉ የሚያደርጋቸው ተከላካይ መንፈስ የላቸውም?
- በፍጡራን ላይ አንዳንድ አካላዊ ለውጦች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝና፥ ይህ ለውጥ "በሰማያዊ ኃይል" የሚደነገግ ቢሆን ማን ያውቃል?

እውቀት ቢኖርም ባይኖርም፥ ለአንድ ግለሰብ የሚቀለው እስከ እምነት የሚያደርሰውን ክስተት፥ በስነ አመክንዮ መመራመርና መቆየት ሳይሆን አይቀርም። በምድር ላይ የሰው ዘር ለብዙ ዘመናት ይቆይ ዘንድ የሚያስብላቸው አምላክ ካለ፥ እንስሳትም አብረው እንዲዘልቁ ማድረግ  አያቅተውም።

እስቲ በተጨማሪ በዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍናዎች ውስጥ፥ እንደ ድጋፍ ሆነው የተቀመጡትን፥ የሚከተሉትንም፥ በውስጣቸው ምን ምን ጉድለቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ እንመልከትና፥ የየግላችንን አስተያየት እናጠናክር።

## <u>ከአራት ክንፎች አራት እግሮች?</u>

ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ይኖር የነበረ፥ ለየት ያለ አሳ በዝቅጠ አለቶች ውስጥ ተገኝቷል። ይህም አሳ እንደ ሌሎች አሳዎች  "ባለ አራት ክንፎች" ሲሆን፥ በተለይ የዚህ አሳ ክንፎች እግር ይመሳሰላሉ (እንደ ተመልካቹ)። ይህ አሳ በባህር የሚያገኘው ምግብ ስላልጠቀመው (ወይም ስላልጣመው)፥ በምድር ምግብ ይቀምስ ዘንድ ለመዋኛ ሲገለገልባቸው የነበሩ አራት ክንፎቹ ቀስ በቀስ ወደ አራት እግሮች ተለወጡለት። እንዲህም ያለው አሳ ነው በኋላ በዝግመተ ለውጥ ቀስ በቀስ ወደ

አርጃኖ እና ወደ አዞ የመሳሰሉ በውሃና በመሬት የሚኖሩ  እንስሳት የተለወጠው (በፍጥረት ሳይሆን፥ በዝግመተ ለውጥ) ተብሏል።

ይህ እውነት ነው? እውነትነቱን ለማረጋገጥ ከቅሪተ አካላት ሌላ የተሰጠ (ማመሳሰል ብቻ ያይደለ) ሳይንሳዊ መረጃ አለ?  "ይህ እውነት ነው፤" ብሎ መቀበሉ ብቻ አይደለም ያስቸገረው። "ይህ እውነት አይደለም፤" ብሎ፥ ካለ በቂ ማስረጃ መከራከርም ነው ያስቸገረው። ሆኖም፥ ለእውነተኛ ሳይንቲስት ከቅሪተ አካላት የተገኘ መረጃ ብቻውን በቂ አለመሆኑን እንመልከት።

በመጀመሪያ፥ ሕዋሳት ወደ ቅሪተ አካልነት ሲለወጡ ግዑዝ የሆነው ኬሚካል ባለ ሕያው የሆነውን አካል (ዘአካል - organism) ይተካዋል።[40] ብዙውን ጊዜ፥ ግዑዝ አካለ ቅሬት ከአምሳያው ባለ ሕያው ይገዝፋል፤ በተለያዩ ተፈጥሮአዊ የግንባታ ክስተቶችም (physical and chemical processes) በየጊዜው እያደገ ሲመጣ፥ መጠነኛ መወላገድ ሊደርስበትና ከእውነተኛ መልኩ ሊለይ ይችላል።

ስለዚህ፥ ሌላ ተጨማሪ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ሳያቀርቡ፥ አሁን የሚታየውን ቅሪተ አካል ልክ እንደ ጥንቱ ዘአካል አድርጎ መቁጠር፤ "ይህንን ይመስል ነበረ፤" ብሎ በሃሳብ የተገኘ ምስል ከግምታዊነት አሳልፎ፥ እውን ማድረግ፥ ከትዕይንታዊ የማስመሰል ደረጃ አልፎ ፍጹም ሳይንስ አይሆንም።

በእርግጥ ቅሪተ አካላት ከድንጋይ ውስጥ በጥንቃቄ ተፈልቅቀው ሲወጡ፥ ስለአለፈው ሕይወት ጥሩ መረጃዎች መሆናቸው አይካድም። ሆኖም፥ መረጃ አሰባሰቡ አጠያያቂ ከሆነ መደምደሚያውም አጠራጣሪ ሊሆን ይችላልና፤ በተለይ "ይህ አሳ ለመዋኛ ሲገለገልባቸው የነበሩ አራት ክንፎቹ ቀስ በቀስ ወደ አራት እግሮች ተለወጡለት" ወደማለት የሚያደርስ የምርምር ውጤትና መደምደሚያው፥ ከስሜታዊ ማመሳሰል አልፎ የሚሄድ - የረቀቀ መሆን ይኖርበታል።

## ወፎችም ከዳይናዞር?

በተለያዩ ሥፍራዎች አካለ ቅሪቶችን በመመልከትና የይመስላል ባህረ ሃሳቦችን በመጋበዝ፥ በአየር ላይ የሚበሩ ወፎችም ቴሮሳውርስ (Pterosaurs) ከተባለ የዳይናዞር ዝርያ (በፍጥረት ሳይሆን፥ በዝግመተ ለውጥ) ተገኙ ተብሏል። ይህ እውነት ነው? እውነትነቱን ለማረጋገጥ ከቅሪተ አካላት ሌላ የተሰጠ ሳይንሳዊ መረጃ አለ? "ይህ እውነት አይደለም፤" ብሎ፥ ካለ በቂ ማስረጃ መከራከርም ነው ያስቸገረው። ሆኖም፥

[40] በአዛሂነት (silicification) ወይንም በካልሳይትነት (calcification)

ለእውነተኛ ሳይንቲስት ከቅሪተ አካላት የተገኘ መረጃ ብቻውን በቂ አለመሆኑን እንመልከት።

በዳይናዞርና በወፍ መካከል አካላዊ መረጃ ተገኝቷል ተብሎ የሚቀርብ አርኪዎፕቴሪክስ (Archaeopteryx) የተባለው ቅሪተ አካል ነው። የዚህ አውሬ ዲ ኤን ኤ. (DNA) ጠባይ በዳይናዞርና በወፍ መካከል መሆኑ ስላልተረጋገጠ በቂ ማስረጃ የለም። ለእውነተኛ ሳይንቲስት ከቅሪተ አካላት የተገኘ መረጃ ብቻውን በቂ አይደለም።

የዛሬው ምርምር ስለ ጥንት ዘመናት ሁኔታ (ስለ ጥንቱ አየር ጠባይ፥ የንጥረ ነገሮችና በራሂዎች መለዋወጥ) በቂ መረጃ አያስገኝም። በዝቅጠ አለት ስለምናየው ሁሉ ብዙ አወቅን፤ ግን ከዛሬ አንድ ሚሊዮን ዓመታት በፊት፥ በማንኛቸውም ዘአካላት በራሂ (gene) ውስጥ ስለሚገኘው የኬሚካል ጠባይ ማወቅ የሚችል ማንም የለም።

የጥንቱን ያካባቢ ሁኔታ አናውቀውም፤ ብናውቀውም እንኳን፥ ነዋሪዎቹ በየጊዜው ያጋጠማቸው ሁኔታ ምን ነበር? እንዴትስ ነው በውስጣቸው የሚገኘውን የበራሂ ኬሚካል ሊለውጥ የቻለ? እንዴትስ ነው (በምን አይነት መንገድ ነው) አንዱ ዘአካል ወደ ሌላው ዘአካል የተለወጠ (የተፈጠረ ያይደለ)? ይህ እና ብዙ የማይታወቁ ጉዳዮችን መጠየቅ ተገቢ (ሕጋዊ) ነው።

በእውነት ሲሆን ያየ በማይኖርበት ወቅት፥ ሊሆን የሚችለውን ከየአቅጣጫው መገመት፥ የሚመስለውንም መቀበል የኛ ፈንታ ነው። የተዳከመ ማስረጃ ይዞ ግምቶችን እውነት ማስመሰል ግን ሃቀኝነት አይደለም። እኛ በእግዚአብሔር ሥራ ጣልቃ አንገባም። ፍጥረታቱን ሁሉ ሲፈጥር የተጠቀመው ዝግመተ ለውጥን ብቻ ከሆነ፥ መልካም። ግን ነወይ?

ጋዜጠኞች ያዩትን በማውራት ፋንታ ፈራጅ - ዳኛ ሆነው ወሬ ሲያሰራጩ ውጤቱ አያምርም። እኛም ያየነውን ከመናገር አልፈን የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ብንከድ፥ እራሱን ዳኛ እንዳደረገው ጋዜጠኛ መሆናችን ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ መማር የሚፈልጉ ይህንን ጥቅስ ያስተውሉ፡- "ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ" ዘፍ. ፲፡ 24

በጣም ግልጽ ባይሆንም፥ ይህ ጥቅስ ወፎች የተፈጠሩት መሬት እጽዋትን እንጂ እንስሳትን "በብዛት" ልትይዝ በማትችልበት ወቅት መሆኑን፥ ትላልቅ የምድር አራዊትና እንስሳት የተፈጠሩትም በኋላ እንደሆነ ይጠቁማል። እንግዲህ፥ "ማን ከማን ተገኘ?" ከማለት ይልቅ፥ "ከወፎችና ከዳይናዞሮች ማነው በቅድሚያ የተፈጠረ?" ብሎ መጠየቅ ይሻላል።

## ከአንትሮፓይዳ ፕሪሜትስ?

በመሐል ሕይወት፥ ከዛም በደኃራይ ሕይወት፥ ፕሪሜትስ (ባለ አከርካሪ አጥንቶችና ባለ ትላልቅ ጭንቅላቶች) ተባዝተዋል። እንግዲህ የዳርዊንን የሕይወት ዛፍ እውን ለማድረግ፥ ከአንትሮፕይዳ (አሳ፥ ኤሊ፥ እንቁራሪት፥ አዞ እና አርጃኖ..) ፕሪሜትስ ተገኙ ማለት አስፈልጓል። እነቺምፓንዚ ፕሪሜትስ ናቸው። ሰውም ከቺምፓንዚ በሆሚኒድ ይዛመዳል ተብሏል። የዚህን ጉዳይ ዝርዝሩን ለተመራማሪዎች ትተን፥ ቁልፍ የሆኑ ጥያቄዎችን ብቻ በማቅረብ ስነአመክኖአዊ አመለካከታችንን እንፈትን።

## ሰው ከዝንጀሮ ይዛመዳል?

በዳርዊን የሕይወት ዛፍና በቅርንጫፎቹ የሰፈሩትን የዘር መደቦች፥ ከነ እድሜአቸው ስናስተውል፤ የሰው እና የዝንጀሮ ዘር ወደኋላ ሲመለስ የሚገናኙበት ዘመን የዛሬ 6 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ ይሆናል።

ቀደም ሲል (በምዕራፍ አምስት)፡- ቀዳማይ ሕይወት (paleozoic) ከምንለው በፊት፡- በግምት ለ2500 ሚሊዮን ዓመታት ያህል፥ አካላዊ ሕያዋን እራሳቸውን ቁልጭ ባለ መልክ እንዳላሳዩ፤ የዛን ጊዜ አካላዊ ሕያዋን እጅግ ትናንሾች ስለነበሩ፥ አካለ ቅሪቶቹ ጥቃቅን እና በቁጥር እጅግ አነስተኛ መሆናቸውን ገልጸን ነበር። እንግዲህ፥ የዳርዊን የሕይወት ዛፍ የሰውን ዘር ወደ አንድ ሕያው ህዋስ የሚመልሰው ከሆነ፥ መረጃዎች ከፈዘዙበት ከጥንቱ ዘመን ከመነሳት ይልቅ፥ ከዛሬ ጀምሮ ወደኋላ መመለሱ ነው የሚቀለው።

ስለዚህ የሰው እና የዝንጀሮ ዘር ወደኋላ ሲመለስ የሚገናኙበት ዘመን የዛሬ 6 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ ከሆነ፥ ይህ ዘመን ከቀድሞው የሕይወት ዘመን ጋር ሲወዳደር (6 ሚሊዮን ለ2500 ሚሊዮን ሲካፈል) .0024 ብቻ መሆኑ ነው። እንግዲያውስ ወደ ኋላ ብዙ ሳንርቅ ይህቺን ትንሿን ዘመን (.0024) በደንብ እንወቃት፤ ከቻልን። አካልን ከጊዜ፥ ጊዜንም ከአካል ነጣጥለን ማየት ስለማንችል፥ ወደ ኋላ መለስ ብለን የዳርዊንን የዘር ግንድ ከዛፉ ጫፍ እንጀምርና ወደ ዛሬ እንምጣ፤ ከቻልን።

የዛሬ 6 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ የቺምፓንዚና የሰዎች ዝምድና ከአንድ ሆሚኖይዲያ (hominoidea) ከተባለ የዘር ግንድ (አንደኛው የዛፉ ቅርንጫፍ መሆኑ ነው) ተጀመረ ተብሏል። ይህም የዘር ግንድ የሰውና የዝንጀሮን ጠባያት በአንድነት ያካተተ ነበር ተብሏል። ከጊዜ በኋላ የወንድማማች ልጆች ብቅ አሉ (ወደ ሰው የሚጠጋውና፥ ወደ ዝንጀሮ የሚጠጋው ማለት ነው)።

የሰው ዘር ሆሚኒድ (hominid) የተባለውን የዘር ዘርፍ ተከትሎ ሄደና፥ ከዛሬው የሰው ዘር - የዘመኑ ሰው (homo sapien) ተደረሰ ማለት ነው።

በተጨባጭ የሚታዩ ተከታታይ ሳይንሳዊ መረጃዎች ተገኝተዋልና እንመርምራቸው ከተባለ፥ እነኚህኑ ሆሚኖይዲያ (hominoidea) የተባሉትን “የጥንቱ ሰው መሳይ ፍጡራንን” እንመርምር።

በጠፈር ሁሉ የእውነት ምንጩ አንድ ነው፤ ሁለት ወይም ሦስት ሊሆን አይችልም። ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ እዛ ወደ አንድ የእውነት ምንጭ (ወደ እግዚአብሔር) መጠጋቱ ነው ያስቸገረን። ትኩረታችን የዳርዊንን የሕይወት ዛፍ እውን ለማድረግ (ወይም አለማድረግ) ሳይሆን፥ እውነቱን ለማግኘት መሆን አለበት።

አያሌ የሰውን መልክ የሚመሳሰሉ፥ “የጥንቱ ሰው መሳይ ፍጡሮች” አካለ ቅሪቶች ከተለያዩ ሥፍራዎች ተገኝተዋል። በእውነት የእነኚህን ፍጥረታት መልክ፥ ትኩር ብለን ስንመለከተው፥ ከዘመኑ ሰው ጋር የሚመሳሰል ብዙ አካላዊ ጠባዮችን እናይባቸዋለን። እነኚህ አካለ ቅሪቶች፥ አንድ ሕያው ፍጥረት ከአንድ ትውልድ ወደሌላ ትውልድ ሲሸጋገር፥ በውስጠ አካሉ ለውጦች ሲካሄድበት መቆየቱን ያንጸባርቃሉ።

እነኚህ የእድገት ደረጃዎች ያስከተሉት አካላዊ እድገት (መለዋወጥ)፥ የሰውን ዘር ከሆሚኒድ ጋር የሚያገናኝ ከሆነ፥ ይህንን ለማረጋገጥ የዘመኑን ዲ ኤን ኤ ምርመራ ይበቃል (ከተቻለ)።

የጥንት ሰው መሳይ ፍጡር፥ አንዱ ከሌላው በአካል በመለየቱ (የኋለኛው ከቀደመው “ይሻላል” በማለትም)፥ እንደየእድሜአቸው ሦስት የተለያዩ ስሞች ተሰጥቷቸዋል። እነኚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

1) አውስትራሎፒቴኩስ (ከሦስት ሚሊዮን ዓመት አካባቢ ጀምሮ የኖረ)፥
2) ሆሞ ሃቢሊስ (ከሁለት ሚሊዮን ዓመት አካባቢ ጀምሮ የኖረ)፥
3) ሆሞ ኢሬክቱስ (ከአንድ ሚሊዮን ተኩል ዓመታት አካባቢ ጀምሮ የኖረ)።

የሆሚኒድ አይነቱ ከሃያ ይበልጣል፤ ከተጠቀሱትም ከሦስቱ ዋና ዋና ክፍፍሎች አንደኛው - ሆሞ ኢሬክቱስ[41] የተባለው - በአጥንቶቹ፥ በፊቱና በጭንቅላቱ ቅርጽ ሰውን (የዘመኑን ሰው) የበለጠ ይመስለዋል ተብሏል። የተቀሩት ግን ምንም እንኳን ሰውን የመምሰል ዝንባሌ ቢኖራቸው፥ ምድባቸው ወደ ዝንጀሮዎቹ መሆኑን የሰውን ዘር በሚያጠኑ (paleoanthropologists) ተረጋግጧል።

---

41 በአውሮፓ (ጂኦርጂያ) የተገኘው የሆሞ ጆርጂክስ አጥንት አይነት ሆሞ ሃቢሊስን እና ሆሞ ኢሬክተስን ያዛምዳል ተብሏል።

እንግዲህ ሰውና ዝንጀሮን በደንብ ለማዛመድ ወደ ኋላ የምንመለሰው እስከ አንድ ሚሊዮን ዓመት ድረስ ብቻ ከሆነልን፥ ይህቺን ጥቂት ዘመን (.0006)፥ አፈር ደርምሰን፥ ድንጋይ ፈንቅለን፥ አጽሞችን ሰባስበንና ገጣጥመን፥ አምሳያ ስዕሎችንም ፈጣጥረን፥ በዘመኑ ሰውና በዝንጀሮ መካከል የዘር መሰላል የሚሆንልንን ማበጃጀት አያቅተንም ካልን እንሞክር። ከሆሞ ኢሬክቱስ እንጀምርና ባጭር ባጭሩ እንገምግም።

- የሆሞ ኢሬክቱስ አጥንት (ጭንቅላትና የተቀረው) በአፍሪካ፥ በእስያና በአውሮፓ ተገኝቷል። እራሱ በጣም ትንሽ ነው፤ አገጭ የለውም።
- የሆሞ ኤርጋስተር አጥንት ከሆሞ ኢሬክቱስ አጥንት የሚለየው በጥቂቱ ነው (የአፍሪካው - የኬንያው ቱርካና ምድቡ ከሆሞ ኤርጋስተር ነው)። ይህም ከእስያው ትንሽ ለየት በማለቱ ነው የተለየ ስም የተሰጠው።
- የሄይደልበርገነሲስ አጥንት አይነት (ጭንቅላትና የተቀረው) በሆሞ ኢሬክቱስ እና በሰው አጥንት መካከል ነው። ለሁለቱም የቀረበ ቢመስልም በብዛት የሚቀርበው ከሰው ይልቅ ለሆሞ ኢሬክቱስ መሆኑ ተረጋግጧል።

የጥንት ሰው መሰል ፍጡር ዝንጀሮ (ቺምፓንዚ) ይመስላል የተባለበት ዋነኛ ነጥብ በዲ ኤን ኤ መቀራረብ (ተመሳሳይነት) ነው። ነገር ግን፥ በአፍሪካ የሚገኙ ቺምፓንዚዎች ዲ ኤን ኤ ከዘመኑ ሰው ዲ ኤን ኤ የሚመሳሰሉበት፥ የሚለያዩበትም ብዙ ጠባዮች ይኖሯቸዋል።

ቀደም ሲል፥ ሁሉ ነገር ከሁሉ ነገር ጋር በተለያዩ መንገዶች ይነካካል (ይያያዛል) ብለን ነበር። ሰውም ከቺምፓንዚ ጋር ብቻ አይደለም፥ ከእንቁራሪት ጋርም ተፈጥሮ ያገናኘዋል። በጠፈር ውስጥ ብዙ መመሳሰል ይኖራል፤ መመሳሰልም፥ በጊዜና በቦታ ከመቀራረብ ጋር አብሮ ይሄዳልና። ለዚህ ይሆናል ሰዎች የሚመስላቸውን ሁሉ እንደ እውነት እያደረጉ ብዙ የሚያወሩት። ቋንቋንም ስክትክት አድርጎና አጣፍጦ በመናገር የቺምፓንዚን ዘር ከእነ እንቁራሪት፥ አዞ እና አርጃኖ ጋር ማዛመድ ተችሏል። ሳይንሱ ግን ይህንን - "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ይሏታል" እንደሚሉት አይነት ማመሳሰል - ማዛመድ፥ ከዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ጋር ሊያዋህደው አልቻለም።

"ይኸውና ዘራችን! ተደብቆ የተቀመጠውን ዛሬ ከመሬት ፈንቅለን አወጣነው.." ብሎ ከመጮህ በፊት - "እስቲ ተመልከቱት እርሱ እኮ ነው ወገናችን.." ብሎ በልፍለፋ ብዛት ሰውን ከማደናገር በፊት፤ "ለመሆኑ እኔ ማነኝ?" ብሎ በመጠየቅ፥ ወደ ኋላ እስከ ጥቂት ሺህ ዓመታት ድረስ ብቻ የነበረውን እውነተኛ ሰው - እውነተኛ ዘራችንን ማጥናትና ማወቅ ይሻላል (ይህ ይበቃናል)።

የዘመኑ ሰው ምድቡ ሆሞ ሳፒያን ከተባለው ነው። ይህም ከመቶ ሺህ ዓመታት አካባቢ ጀምሮ እንደነበረ በካርቦን ርዝራዥ የጊዜ መቁጠሪያ (carbon dating) የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህ የዘመኑ ሰው የተባለ - በምሥራቅ አፍሪካ (ኢትዮጵያ) የተፈጠረ ሆሞ ሳፒያን - ከአፍሪካ ወጥቶ አለምን ያጥለቀለቃት መሆኑ ተረጋግጧል። ሆሞ ኢሬክቱስ ግን ሆሞ ሳፒያን በኖረበት ዘመን አልነበረም ጠፍቷል።

ቀደም ሲል የተጠቀምንበትን የስነ አመክንዮ የአመለካከት ዘይቤ (የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ተከታዮችም የሚቀበሉትን) ከዚህም እናምጣው። ከአንድ የዘር መደብ ውስጥ ያሉ አካላዊ ጠባዮች፥ በዝግመተ ለውጥ ቀስ በቀስ (በጊዜ ውስጥ) ተለውጠው፥ ሌላ ቁልጭ ያለ - አዲስና ልዩ መደብ ከማምጣታቸው በፊት፥ ሁለቱን መደቦች የሚያዛምድ (የሁለቱንም መደቦች አካላዊ ጠባይ የያዘ) ማእከላዊ መደብ (የዚህ ዘር ወይም የዚያ ዘር የማይባል) መኖር አለበት።

በተጠቀሰው የስነ አመክንዮ የአመለካከት ዘይቤ መሠረት፥ ሰውን ከዝንጀሮ ማዛመድ ከተፈለገ፥ ከዝንጀሮ የዘር መደብ ውስጥ ያሉ አካላዊ ጠባዮች፥ በዝግመተ ለውጥ ቀስ በቀስ (በጊዜ ውስጥ) ተለውጠው፥ ሌላ ቁልጭ ያለ - አዲስና ልዩ ሰው የሚባል የዘር መደብ ከማምጣታቸው በፊት፥ ሁለቱን መደቦች የሚያዛምድ (የሁለቱንም መደቦች አካላዊ ጠባይ የያዘ) ማእከላዊ መደብ (የዝንጀሮ ዘር ወይም የሰው ዘር የማይባል) መኖር አለበት።

ወደ ቀድሞ ነገራችን እንመለስና፥ የዝንጀሮን ዘር ከሰው በትክክል የሚያዛምድ ጠፍቶ ቆይቶ ሳለ፥ ኒአንደርታል የተሰኘ ሰው መሳይ አጽም ከጀርመን አገር ተገኘ። ይህ አጥንት (ጭንቅላትና የተቀረው) ከሆሞ ኢሬክቱስ ይልቅ የሰውን በመምሰሉ፥ የሰውን ዘር ቀጥታ ከኒአንደርታል ጋር ለማዛመድ ተሞከረ (ኒአንደርታል ሆሞ ኢሬክቱስ ነው በማለት)።

ሌላም እንዲሁ፥ ከጭንቅላቱ ሾጠጥ ያለ፥ በቁመቱም ረዘም ያለ፥ ሰውንም ዝንጀሮንም የመሰለ አጽም ከፈረንሳይ ተገኘ። በተገኘበት ሥፍራ ስም፥ ክሮ ማኞን ብለው ስም አወጡለት። ይህ አጥንት (ጭንቅላትና የተቀረው) ከሆሞ ኢሬክቱስ ይልቅ የሰውን በመምሰሉ፥ የሰውን ዘር ቀጥታ ከክሮ ማኞን ጋር ለማዛመድና ተሞከረ (ክሮ ማኞን ሆሞ ኢሬክቱስ ነው በማለት)።

ኒአንደርታልም የሰው ዘር ብቻ ሆኖ ተገኘ፤ የሰው ዘር አይደለም የሚሉ አሉ። ምናልባትም አውሮፓውያንና እስያውያን ከአፍሪካኖች ትንሽ ለየት የሚሉት ከኒአንደርታል ጋር ስለተዳቀሉ ሳይሆን አይቀርም የሚሉም አሉ፤ ግን የቀድሞውን አጽም ተከትሎ ወደ ትክክለኛ ድምዳሜ መድረስ አልተቻለም።

ክሮ ማኞን የተባለውም፥ በደንብ ሲታይና ሲመረመር፥ የሰው ዘር ስለመሆኑ አጠራጣሪ አልሆነም (ሰውዬው ሰው ብቻ ሆኖ ቀረ)። እንግዲህ አንድም፥ በሰው ዘርና በዝንጀሮዎች መካከል፥ እንደ ማስረጃ የሚቀርብ መሃል ሠፋሪ መጥፋቱም ነው የዳርዊን ተከታዮችን የዝግመተ ለውጥ አጠያያቂ ያደረገው።

በዚች በምድራችን ላይ ካለ ምክንያት የተፈጠረ አንድም ባለ ሕይወት እንደሌለ ልብ ይሏል። በቁመታቸው አጠር አጠር ያሉ ሰው መሳይ ፍጡራንም (humanoid) በምድራችን ላይ የቆዩበት ዘመን ቢኖር፥ ካለ ምክንያት አልተፈጠሩም። "እነኚህ ፍጡራን ለምን ተፈጠሩ?" ብሎ መጠየቅም ወደ እውነት ሊመራን ይችላልና እናስተውል።

ተፈጥሮን ስንመለከት (ነፍስ ያለውም የሌለውም)፥ ምን ጊዜም ቀደም ብለው የተፈጠሩት በኋላ ለተፈጠሩት አንዳንድ ሁኔታዎች እንዲዘጋጁላቸው ምክንያት ይሆናሉ (ኃጢአት በመሥራትም ቢሆን)። ይህንን ጉዳይ፥ እግዚአብሔር ካለ ምክንያት አይፈጥርም በማለት፥ በመንፈሳዊ አይን ብንመለከተው፡- ሰው መሳይ ፍጡራን፥ ሌሎችም በነርሱ ዘመን የነበሩ እንስሳት እና እጽዋት ሁሉ ለዘመኑ ሰዎች አንዳንድ ሁኔታዎች እንዲዘጋጁላቸው ምክንያት ሳይሆኑ አልቀረም።

እግዚአብሔር ለምን ይህንን ሰው መሳይ ፍጡር (humanoid) ፈጠረ? ከኛ መፈጠር በፊት፥ የዚህ ሰው መሳይ ፍጡር መፈጠር ለኛ ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻችቶልናል ወይ? ይህ ሰው መሳይ ፍጡር ባካባቢው ካሉት እንስሳት (አንበሳ፥ ነብር፥ ጅብ..) ጋር እንዴት ነበር ተስማምቶ የኖረው? ይህንን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለባህረ ሕሊናችን እንተወው።

ብዙ የማናውቃቸው ጉዳዮች ቢኖሩም፥ እኛ የዘመኑ ሰዎች የሰብአዊነታችን ምልክት ተክለ ሰውነታችን (አካላችን) ብቻ አለመሆኑን፥ በውስጣችን ከተጠቀሱት ፍጡራን ሁሉ የሚለየን ልዩ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን መኖሩን ካወቅን፥ "አዎ! እኔ ሰው ነኝ፤ ሰው ሆኜ የተፈጠርኩ - እኔ ነኝ ሰው ማለት" ስንል፥ አላስፈላጊው ሃተታ ወደኋላ ይቀርና፥ ሰብአዊነታችን (ሰውና መንፈስ መሆናችን) ይቀድማል።

እግዚአብሔር ሰውን ጭቃ ጠፍጥፎ ነው የሠራው ማለት፥ ወይንም እግዚአብሔር ሰውን እንዴት እንደፈጠረው እኔ አውቃለሁ ብሎ አላስፈላጊ ትንተና ውስጥ መግባትም የድፍረት ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ፍጥረቱን በፈለገው አይነት መንገድ ይፈጥራል። እግዚአብሔር በቅድሚያ ቺምፓንዚን ፈጥሮ፥ ከዚያ በኋላ የራሱን መንፈስ ቺምፓንዚ ውስጥ ሲያስገባ ከሆነ እኛ ሰው የሆነው፥ ይሁና። ምናለበት?

ግን፥ አሁንም ቢሆን፥ ቺምፓንዚ ቺምፓንዚ ነው፤ ሰውም ሰው ነው። እኛ ሰዎች ሰው የሚያሰኘን አካላዊ ጠባያችን ብቻ ቢሆን ኖሮ እና፥ ሰውን ከዝንጀሮ የሚያገናኝ ሳይንስ ቁልጭ ብሎ ቢቀርብልን ኖሮ፥ ይህ ሁሉ ሃተታ ባላስፈለገ ነበር።

እኛ ሰዎች ባለ አንደበት፥ ባለ ቋንቋ፥ ባለ አይምሮ ነን። ከዚህም በላይ፥ ባለ መንፈስ ነን እንጂ፥ *ሥጋ* ብቻ ስላልሆንን፥ ግንዛቤአችን ከሕይወቱ ዛፍ ዘልቆ ይሄዳል። ለሚታያቸው፥ የሰው ረቂቅነት ወሰን የለውም (በመንፈሱ)። እና፥ ሰው በ*ሥጋ*ው ዝንጀሮ ቢመስል ምንም አይደል፤ ማመሳሰል የአካላዊ አይምሮ ዝንባሌያዊ ጠባይ ነውና። የቀድሞው ሰው በፊቱ ገጽታ ዝንጀሮ ቢመስል አይገርምም፤ እንኳን የጥንቱ፥ የዛሬውም ሰው (ነጩም፥ ቢጫውም፥ ጥቁሩም) ቢሆን፥ ትክ ብለው ካዩት ሁሉም ዝንጀሮ ይመስላል።

አዳምና ሔዋን በአካል ዝንጀሮ ይመስላሉ ከተባለም አንፈር፤ በመንፈሳቸው እግዚአብሔርን ስለሚመስሉ ደስ ይበለን። እነርሱ በእግዚአብሔር አምሳያ በመንፈስ ከተፈጠሩ ቆይቷል..... ቆይቷል።[42] *ሥጋ*ዊ ሰው ቢቀላም ቢጠቁርም እግዚአብሔርን በአካላዊ መልኩ ሊመስለው አይችልም። የሰው ልጅ ሚዛናዊነቱ በአካላዊነቱ ምክንያት የተዛባ (መንፈሳዊነቱ የተሸፈነ) እየሆነ ነው፥ ስለ መንፈሳዊ እድገት ጉዳይ ብዙ ሲወራ የማንሰማ። ምድራዊነታችን ብቻውን ፈር እየለቀቀ ሲሄድ ያጨቃጭቀናል፤ ሰብአዊ አንድነታችንንም የሚያሳጣን እርሱ ነው። ግን፥ የኛ ሰብእነት እግዚአብሔርን በመንፈስ በመምሰላችን ስለሆነ፥ በውስጣችን የሚኖረው ሰላማችን አንድ ያደርገናል።

ሰዓሊዎች የመላእክትን *ሥ*ዕል የሚስሉት አንዳንድ መንፈሳዊ ትምህርት ለማስተጋባት ነው እንጂ፥ መላእክት አካላውያን ናቸው ለማለት አይደለም። እግዚአብሔርን ቀይ አስመስለው ቢስሉት፥ ጥቁር አስመስለውም ቢስሉት ለራሳቸው ደስ እንዲላቸው - *ሥጋ*ዊነታቸውን ለማርካት ነው እንጂ፥ እግዚአብሔር አካላዊ ስላልሆነ፥ የቆዳ ቀለም የለውም።

እግዚአብሔር በአካል ሰው የሆነው በእመቤታችን የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ነው። የዛን ጊዜ፥ የክርስቶስ የቆዳው ቀለም ነጭ አልነበረም፤ ጥቁርም አልነበረም (በሁለቱ መካከል ይሆናል፥ እንደ አዳም)። ከክርስቶስ በፊት እግዚአብሔርን በአካል ሆኖ ያየው የለም። ሙሴ የእግዚአብሔርን ጀርባ ቢመለከት፥ ያ ጀርባ የተባለው የሚያመለክተው ምን እንደሆነ አይታወቅም።

---

42 "ሰው በመንፈስ የተፈጠረው ምድራችን ከመፈጠሯ በፊት ይሆናል፤" ብሎ በመፈላሰፍ ወደሌላ ሰፊ የፍልስፍና ጎዳና መሸጋገር ይቻላል።

የምድራዊነት ጠባይ "መሻሻል" መንፈሳዊ እድገትን አያመለክትም። የሰው ቁንጅናው ጠባየ ሸጋ አያሰኘውም። ምድራዊነት ሰውን ጦረኛ ቢያደርገው፥ በዚህም ምክንያት ጨካኝ ቢሆን፤ ግን መንፈሳዊ እድገት ካለው፥ ጦረኛም ሆኖ ጥሩ ሰው ሊሆን ይችላል።

ሰው ከዝንጀሮ ተዛምዷል ብሎ መደምደም እጅግ ከባድ ጉዳይ መሆኑን የተገነዘቡ ሳይንቲስቶች፥ ይህ መላ ምት ትክክል አለመሆኑን ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ። ግን እስካሁን በቂ ሳይንሳዊ ማስረጃ ባለማግኘታቸው ዝም ስላሉና መድረኩን የያዙት አሁንም የዳርዊን ተከታዮች ስለሆኑ፥ እነርሱ ናቸው ትክክል ብለን ቁጭ ማለት አይገባም።

ሳይንሳዊ ያልሆነ ሃሳብ ሳይንሳዊ ባለመሆኑ ብቻ ውሸት ነው ለማለት የማንደፍር ከሆነ፥ የሰው ፍጥረቱ የተጀመረው ከቀደሙ እንስሳት ሳይሆን ከሰው ነውና፤ ያንን የመጀመሪያ የሰው ፍጥረት (አዳምና ሔዋን) ከሌላ ከማንም እንስሳት ጋር ሳናዛምድ በጥልቀቱ እናጥናው ካልን፥ በሚከተለው ምዕራፍ የፍጥረትን አመጣጥ ለየት ባለ መልኩ እንመራመራለን (ፍጥረት ከሰማይ መሆኑን እናስተውላለን)። ከዛ በፊት ግን መለኮታዊ ኃይል ስለመኖሩ ጥቂት እናወሳለን።

## <u>ሁሉም በራሱ ነው ወይንስ መለኮታዊ ኃይል አለ?</u>

ለዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ መሠረት የሆኑት፥ እራስን በራስ መለወጥ (mutation) እና ጠቃሚውን መርጦ መውሰድ (natural selection)፥ ሁለቱም ትክክል ቢሆኑም፥ ከዚህ በመነሳት፥ ማንኛውም አካላዊ ሕያው፥ ራሱን በራሱ እየለወጠና፥ ጠቃሚውን እየመረጠ በመውሰድ፥ ለራሱ ሕልውና የሚያስፈልገውን ሁሉ በራሱ ያደርጋል - "ሁሉም በራሱ" ነው፤ ሌላ የውጪ ኃይል የለም ብሎ መደምደም ትክክል ነው ወይ? አንድ አካላዊ ሕያው በራሱ ብቻ - "ሁሉም በራሱ" ተጠቃሎ እየተለዋወጠ ቢቆይ..ቢቆይ፥.. እራሱን በገዛ ፈቃዳዊ ፍላጎቱም ይለውጠው ነበረ። ግን፥

"ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚቻለው ማነው?" ማቴ. 6፡27 ይላል።

ይህንን የክርስቶስን ቃል የጠቀስነው ለማስረጃነት ሳይሆን ለመንፈሳዊ ግንዛቤአዊ ማመሳሰል ነው። "በእውነት ሁሉም በራሱ ነው" የሚል የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍናን በመንፈሳዊ አይን ስንመለከተው ደስ አይልም። "ጠፈር ክፍት ነው፤ በራሱ ተጀመረ፤ እንቅስቃሴው ሁሉ ካለ የበላይ ተቆጣጣሪ በራሱ ፈቃድ ለዘለአለም ይካሄዳል፤" ከሚለው ደስ የማይል አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰላል።

ደስ አለማለታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት የሚከተሉትን እናስባቸው፡-

1. “ሁሉም በራሱ” ነው፤ እያልን ፍጥረት እራሱን በራሱ እየፈጠረ፥ ለዘለአለሙ እንዲቀጥል እንልቀቀውና፥ ውጤቱን እናስበው።
2. “ጠፈር ክፍት ነው”፤ እያልን ጠፈር ካለ ምንም መገታት ለዘለአለሙ እየሰፋ እንዲቀጥል እንልቀቀውና ውጤቱን እናስበው።

በእነኚህ በተጠቀሱት ሃሳቦች ላይ ብዙ ብንቆይ ምን ያህል ቅፍፍ - ክፍት እንደሚለን እናስበው። ተፈጥሮ የበላይ ተቆጣጣሪ ከሌለበት፥ ወደ ክፉ ሊያመራ እጅግም ሊያስከፋ እንደሚችል እናስበው። ግን ይቅር አንከፋ፤ ደስ ይበለን፤ ተፈጥሮ ያን ያህል አስከፊ አይደለም። የተፈጥሮ ሂደት፥ እንኳን እንዲያ እጅግ ከፍ ባለ ደረጃ ይቅርና፥ በትንሹም ቢሆን አቅጣጫው ወደ ጥሩ እንጂ ወደ መጥፎ አይጓዝም።

በቅርብ ጊዜ አንድ ሳይንቲስት፥ በገዳማት የሚኖሩ መነኮሳትን በራሂ (gene) በመመርመርና በማጥናት እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- “መንፈሳውያን የሚሆኑ ሰዎች በበራሂአቸው ውስጥ አንድ የተለየ የኬሚካል ጠባይ ይታይባቸዋል።

በተመሳሳይ ሌቦችና ነፍሰ ገዳዮች የሚሆኑ ሰዎችም በበራሂአቸው ውስጥ አንድ የተለየ የኬሚካል ጠባይ ይታይባቸዋል ቢባል አያስደንቅም፤ መቼም “ከሞላ ጎደል”፥ የሰውን እድል ወሳኙ ራሱ ነውና፤ “የእድልህ መሃንዲስ አንተው ነህ” እንደሚባል ሁሉ። ግን መቶ በመቶ ሰው የራሱን እድል በራሱ - በጂኑ ውስጥ ባለው ኬሚካል ብቻ ይወሰናል ማለት፥ አሁንም የሰው ልጅ የወደፊት እድል ፈር እየለቀቀ፥ እጅግ ዘግናኝ ወደ ሆነ አቅጣጫ ቢያመራ፥ የሚመልሰው ሌላ ሁለንተናዊ ኃይል (መንፈስ) የለም እንደማለት ይቆጠራል። ይህ ልክ ነወይ?

በማንኛቸውም ዘአካላት ውስጥ ከአካልና በውስጣቸውም ከሚገኘው ወሳኝ ጠባያቸው በስተቀር ሌላ ምንም ነገር (መንፈስ) አልነበረም የሚያሰኝ የአካባቢ ማስረጃዎችን ለማቅረብ የሚችል ማነው?

ወደኋላ መለስ ብለን፥ ጠፈር እንዴት እንደተገነባና እኛም እንዴት እዚህ እንደደረስን ብንመለከት፥ ከዛ ውስብስብ ተፈጥሮአዊ ሂደት ውስጥ የእኛ ብቅ ማለታችን፥ ተፈጥሮ የበላይ ተቆጣጣሪ እንዳለው እንጂ፥ በራሱ ብቻ እንደማይጓዝ ቀደም ሲል ከሳይንቲስቱ እስቲፈን የጠቀስነውን ያስታውሰናል።

“..It would be very difficult to explain why the universe should have begun in just this way, except as the act of God who intended to create beings like us” Stephen Hawking (2005), pp.55. ሲተረጎም፡- “ከብዙ ሌሎች አማራጮች መካከል ለምንድነው

በዚህ አይነት መንገድ ብቻ ጠፈር የተጀመረ፤ እንዳው ከጥንቱም እኛን ለመፍጠር እግዚአብሔር አስቦት ካልሆነ በስተቀር።”

ምናልባት እስቲፈን ይህንን የተናገረው፥ ለከባዱ ጥያቄ ቶሎ መልስ የሚያስገኝና ለማሰብም የሚቀል ስለሆነ ነው የሚሉ ይኖራሉ። ያም ሆነ ይህ፥ “ከሁሉም በራሱ ነው” ዘልቆ ለሚሄደውም መንፈሳዊ አስተሳሰብ ክፍተት መስጠትና መመራመር አይከፋም።

## ነፃ አስተያየት

የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ብዙ እውነቶችን ያዘለ መሆኑ አያጠራጥርም። ግን የእውነተኛነት ወሰኑ ከልክ በላይ ስለ ሰፋ፥ አንዳንድ ኢሳይንሳዊ የሆኑ ስንኩል ጽንሰ ሃሳቦች ገብተውበታል በማለት ስንነጋገር ቆየን። እስካሁን የተነጋገርንበትንም በስነአመክንዮ እንፈትነው።

1) “በተሟላ ሳይንሳዊ መረጃዎች የተጠናከረ - የተቃና ሳይንሳዊ አስተሳሰብ መጨረሻው ወደ እምነት ያመራል - በፈጣሪ አምላካችን ላይ ያለንን እምነት ያጠናክረዋል” ብንል፥ ይህንን ኃይለ ቃል በቀላሉ እውነት ነው ብሎ መቀበል ያስቸግር ይሆናል። ግን ይህ አባባል ልክ መሆኑን ወይንም አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተቃራኒውን እንመልከት፡-
2) “በጎዶሎ ሳይንሳዊ መረጃዎች ተሸፋፍኖ የተቀመጠ - ያልተቃና ሳይንሳዊ አስተሳሰብ (የአስተሳሰብ ጉድለት) መጨረሻው ወደ ክህደት ያደርሳል - በፈጣሪ አምላካችን ላይ ያለንን እምነት ያዳክመዋል” ብንል፥ የመጀመሪያው እውነት ከሆነ ሁለተኛውም እውነት ይሆናል።

ነገር ግን፥ “ከሆነ” ከሚል የተንጠለጠለ (ያልተጨረሰ) ስነ አመክንዮ ነው የተነሳነው፤ ስለዚህ መጨረሻውም እንዲሁ የተንጠለጠለ (ያልተጨረሰ) ስለሚሆን ማጠናከሪያ ሃሳቦችን እንሻ። ለምሳሌ፡- የተለያዩ መላምቶች የሚከተሉትን አይነት ስሜት ይሰርጻሉ፡-

1) ገና ሲጀምሩት የሚያደናግር፥ ጥርጥር ውስጥ የሚከት፥ ጭንቀትን የሚያመጣ መላምት።
2) ገና ሲጀምሩት የማያደናግር፥ ጥርጥር ውስጥ የማይከት፥ ሲያስቡትም ደስ የሚል መላምት።
3) በጊዜ ውስጥ የማይለወጥ፥ ለሰው ልጅም ዘላቂና የሚጠቅም እውቀት የሚያስገኝ መላምት።

"ፍጥረት የለም፤ በዝግመተ ለውጥ ብቻ ነው ከአንድ ህዋስ ጀምሮ ቀስ በቀስ እየተለዋወጥን በራሳችን ከዚህ የደረስን" ቢባል፥ ይህ ሃሳብ የሚጠጋው ወደ ተራ ቁጥር አንድ ነው።

የዳርዊን አይነት ያልሆነ ዝግመተ ለውጥ ለፍጥረት ድጋፍ ነው ቢባል፥ ይህ ሃሳብ የሚጠጋው ወደ ተራ ቁጥር ሁለት እና ሦስት ነው። ለዚህ ነው ይህንኑ የሚያጠናክሩ ሃሳቦች ላይ የቆየነው።

እውቀት በቀላሉ ሊመጣ ይችላል፤ አስተሳሰብ ግን አንዴ ከተዛባ ማቃናቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ፥ በቅድሚያ ዝግመተ ለውጥ (የዳርዊን አይነት ያልሆነውን) እና ፍጥረት ሁለቱም የማይለያዩ መሆናቸውን ለመግለጽ ስንል እውቀታችንን ሳይሆን አስተሳሰባችንን እንከልስ።

ሳይንቲስቶች በቀን ተቀን ሳይንሳዊ ምድብ ሥራቸው ላይ ሳሉ፥ አይምሮአዊ ቅንነት ከጎደላቸው - አድሎአዊም ከሆኑ፥ በመጨረሻ የሚያቀርቡት የሥራ ውጤት አያምርም፤ ዘላቂነት አይኖረውም። ሳይንስ የሰውን ልጅ ሕሊናዊ ሚዛናዊነቱንም የሚፈትንና እውነትን ለእውነተኛ ሰው የሚያስረግጥ ነው። እውነተኛ ሳይንስ እውነት ስለሆነ፥ ሁለንተናዊነት ቢጎድለውም ዘላቂነት ይኖረዋል።

ካለ ምንም ተጨባጭ ሳይንሳዊ መረጃ፥ ከገዛ ራሱ ሕሊናዊ ሚዛናዊነት ተነስቶ ሳይንስን ለማራመድ ቆርጦ የተነሳ፥ ሁለንተናዊነትና ዘላቂነት አይኖረውም፤ እንደ እሳት ቦግ ቢልም ቶሎ ጥፍት ማለቱ አይቀርም።

ባለ ሙያዎችም የቀን ተቀን ምድብ ሥራቸው ሳይንሳዊ ምርምር ከሆነ፥ በግብታዊነት ሳይንሳዊ ሪፖርት ከማቅረባቸው በፊት፥ እራሳቸውን በሚከተሉት ሁለት ተጻራሪ አመለካከቶች በመፈተን የትኛውን እንደሚከተሉ ማወቅ ግዴታቸው ነው።

1) በአይምሮህ ዘልቆ የገባ እውነት የሚመስል መላምት ቢኖር፥ ያን መላምት ለማጠናከር ስትል መረጃዎችን ሰብስብ። በአይምሮህ የተቀረጸ አስተሳሰብህ እንዳይለወጥብህ፥ ማስረጃ ሊሆኑ የማይችሉትን ሁሉ ወደጎን እየተውክ፥ ላንተ እውነት የሚመስለውን ብቻ እያጎላህ፥ የደረስክበትን የምርምር ውጤት በችኮላ አቅርብ።
2) ማስረጃዎችን እየሰበሰብክ የሚታሰቡ ጉዳዮችን አጣራ እንጂ፥ ማንኛውንም መላምት እንደ እውነት አትቀበል። በአይምሮህ የተቀረጹ ጥያቄዎችን ሁሉ ለመመለስ ከማሰብ፥ ከመፈላሰፍ፥ ከመመራመርና ማስረጃዎችን ከመሰብሰብ አታቋረጥ። በሙሉ ማስረጃ ያልተደገፈ ምንም ነገር በችኮላ አታቅረብ። በቅንነት የደረስክበትን የምርምር ውጤት ላቅርብ

ካልከም፥ በቅድሚያ ጉድለቶቼንንና ድክመቶቼን ሁሉ ከዘረዘርኩ በኋላ ይሁን።

በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሰውን መመሪያ በመከተል፥ በአይምሮአቸው የተቀረጸ አስተሳሰብ እንዳይለወጥ ለማድረግና ቶሎ ለመታወቅ የሚሮጡ አሉ። እንዲህ ያሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ሕይወታቸው በግል ክብራቸው ዙሪያ ያተኮረ ስለሆነ፥ እውነቱ ከሚነገር ይልቅ ስለራሳቸው ገናናነት ቢወራ ደስ ይላቸዋል። ለራሳቸው ክብር ብቻ ሲሉ እውነትን እያጣመሙ ይኖራሉ፤ እነርሱ ገንዘብና ሥልጣን የሚወዱ ናቸው።

በአንጻሩ ደግሞ፥ በተራ ቁጥር ሁለት የተገለጸውን መመሪያ በመከተል፥ ሳይንሳዊ መግለጫ የሚያስተላልፉ አያሌ ረጋ ያሉ እውነተኛ ሳይንቲስቶች አሉ። ከነኚህም መካከል አብዛኛዎቹ (ወይንም ጥቂቶቹ)፥ ከሳይንስ መጻሕፍት አልፈው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ገጾች በመሽጋገር ልቦናችውን ክፍት አድርገው በደንብ እስኪገባቸው ድረስ የሚማሩ ናቸው። ለወደፊት እንደነዚህ ካሉት እውነተኛ ሳይንቲስቶች ብዙ እውነቶች ይገለጻሉ።

እንግዲህ የዳርዊን ሳይንቲስትነት መደቡ ከተራ ቁጥር አንድ ወይንም ከተራ ቁጥር ሁለት መሆኑን አንባቢ ይፍረደው።

የዳርዊንን ቅንነት እና አድሎአዊ መሆን/አለመሆን እርሱ ራሱ ከጻፋቸው ጽሑፎች ሲመረመር፥ ዳርዊን እጅግ ሲበዛ ዘረኛ እንደነበረ የሚጠቁሙ ጽሑፎች አሉ። ለምሳሌ፡- "I could not have believed how wide the difference between savage and civilized man was. It is greater than between a wild and domesticated animal…" (From the Voyage of Beagle – Darwin 1839 a: 228)[43]

ወደ አማርኛ ሲተረጎም፡- “በሰለጠነው እና ኋላ ቀር በሆነው ሰው መካከል ያን ያህል ልዩነት ይኖራል ብዬ አላምንም ነበር። በለማዳ እንስሳ እና በጫካ አውሬ መካከል ከሚኖር ልዩነት የበለጠ ነው።”

ቺምፓንዚና ሰው ሲቀራረቡለት፥ ሰውና ሰው ተራራቁበት። ይሁን፤ ይህ የርሱ ነፃ አመለካከት ነው። ግን፥ ከእንዲህ አይነት “ነቢይ ሰው” የሚከተለው ትንቢት ቢፈልቅ አያስደንቅም።

---

43 See also http:// www.infidels.org/library/historical/charles_darwin

“At some future period not very distant as measured by centuries, the civilized races of man will almost certainly exterminate and replace the savage races throughout the world..” (From the Races of Man” 1874. p.178)[44]

ሲተረጎም፡- “በቅርቡ ወደፊት - በመቶ ዓመታት በማይቆጠረው ወደፊት - ይህ የሰለጠነው የሰው ዘር ኋላ ቀሩን ከምድር ገጽ አጥፍቶ በራሱ ዘር እንደሚተካው አያጠራጥርም።”

ዳርዊን ከሞተ በኋላ፥ ብዙ ሳይቆይ የተቀሰቀሱትን ሁለት የአለም ጦርነቶች ልብ ይሏል። ዳርዊን የዘራው ሳይንሳዊ የዘረኛነት ጥንስስ፥ በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት (1914 -1917 ዓ.ም. እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር) እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት (1939 -1945 ዓ.ም. እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር)፥ በሁለቱም ውስጥ፥ ዘረኛነት የጦርነቱ ተካፋይ በሆኑ ተዋጊዎች ስነ አይምሮ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሳያደርግ አልቀረም። በተለይም በሁለተኛው የአለም ጦርነት ብዙ የሰው እልቂት የተከሰተው፥ ከዘረኛነት ጋር በተያያዘ ጥፋት እንደ ነበር ሁሉ፥ የዳርዊን ሳይንሳዊ ዘረኛነት ለፋሺስቶችም ድጋፍ ሳይሆንላቸው አልቀረም።

ዳርዊን ግን፥ “ይህ የሰለጠነው የሰው ዘር ኋላ ቀሩን ከምድር ገጽ አጥፍቶ በራሱ ዘር እንደሚተካው..” ሲል፥ በእውነት ይህ የራሱ አስተሳሰብ ነው? ወይንስ የሰይጣንም ተቀላቅሎበታል? ወይንስ ሰዎች ይህንን ያስባሉ ማለቱ ነው? አይታወቅም፤ ግን ልክ እርሱ እንደተነበየው የተሞከረ መሆኑ፥ አንዳንድ ዘረኞች እኛ ብቻ እንኑር፤ ሌላው ይጥፋ እያሉ እንደሚያስቡ ያመለክታል።

ከ2005 እስከ 2012 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ፥ በየሳምንቱ በማእከላዊው ግምት፥ ሁለት አፍሪካዊ አሜሪካዊያን በነጭ ፖሊሶች እንደተገደሉ የሚያመለክቱ የስታቲስቲክ መረጃዎች እንደሚኖሩ ልብ ይሏል። ይህም የሚጠቁመው፥ ዛሬም ቢሆን፥ ጸረ ጥቁር የሆኑ ዘረኞች፥ ለዘረኛነታቸው ሳይንሳዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ሊመስላቸው ይችላል።

በመሠረቱ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የዳርዊን ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፥ ሁለት ጊዜ አንገራግሯል። ግን በመጨረሻ እውነት የሚሆነው የትንቢት አይነት ከትንቢቱ አመንጪም ጋር የተያያዘ እንደመሆኑም መጠን፥ ከክፋቶች ሁሉ ባሻገር፥ ፍቅር

44 See also http:// www.infidels.org/library/historical/charles_darwin

የሰዎችን ሕልውና ጠብቆ አቆይቶልናል። ፍቅር እውነት ነው፤ መገዳደል ግን ውሸት ነው፤ እውነት ያልሆነ ሁሉ በመጨረሻ ይከሽፋል።

ዳርዊን ተሳስቷል። አንዱ የሰው ዘር ሌላውን የማጥፋት ችሎታ አይኖረውም። ሰው እርስ በርስ ተጨራርሶ የሚጠፋ አውሬ አይደለም። በአሁኑ ዘመን ሰው ሁሉ በሰውእነቱ እንጂ በዘሩ አይደለም የሚታወቀው። ለወደፊትማ የሰው ዘር[45] እየተዳቀለ አንድ መሆኑ አይቀርም፤ አሁንና ወደፊት የሰው ዘር አንድ ነው።

ከዳርዊን ትንቢት ይልቅ የሚከተለው የዚህ መጽሐፍ (የብዙዎቻችንም) ትንቢት ይፈጸም ዘንድ እውን ሊሆን ይችላል፡-

“በቅርቡ ወደፊት - በሙቶ ዓመታት በማይቆጠረው ወደፊት፥ የሰው ዘር ሁሉ በጋራ በመኖር የጋራ ሰላሙን እና አንድነቱን የበለጠ ያጠናክራል።”

አዎ! ለመኖር ትግል ይኖራል፤ ግን ትግል ሲባል የግድ መገዳደል መሆን የለበትም። እንደ ዳርዊን፥ የሰው ዘር ሥጋዊ ብቻ እንጂ፥ ባለ መንፈስ መሆኑን ያላወቀ፥ በምድር ለመቆየት ከጉልበት ሌላ ፍቅር መኖሩን አያስተውልም። የወደፊቱ ሰው ግን በጉልበቱ የሚመካ አይሆንም። በምድር ለመቆየት፥ በመንፈሳዊ አንድነት፥ በሰላምና በፍቅር ተስማምቶ ከመኖር የተሻለ አማራጭ አይኖርም።

ከተጠቀሱት ዘገባዎች ብቻ የዳርዊንን ዘረኛ መሆን/አለመሆን ለማረጋገጥ አይቻልም። እንዳውም የዳርዊን ደጋፊዎች፥ ዳርዊን በተወሰነ ወቅት እንዲህ ያለ ጽሑፍ በመጻፉ ብቻ ዘረኛ አያሰኘውም። ይልቅስ፥ በጊዜው ከነበሩ ሰዎች እርሱ በጣም ተራማጅ ነበር በማለት፥ ስለ ባርያ ገዢዎች ጭካኔና ግፍ በመዘርዘር፥ የርሱንም ርህራሄና ሃዘኔታ በመጥቀስ፥ ዳርዊን የጻፋቸውን ጽሑፎች እንደመረጃ ያቀርባሉ። ስለ እምነቱም ጉዳይ፥ በልጅነቱ በእግዚአብሔር ያምን እንደነበረ፥ በኋላ ቢክድም፥ መሞቻው ሲቃረብ በእግዚአብሔር አምኗል የሚሉ አሉ። አላመነም[46] የሚሉም አሉ።

እንዲህ ያለ ሃተታ ያቀረብነው፥ የዳርዊን ዘረኛ መሆን/አለመሆን ባቀረባቸው መረጃዎቹ ሁሉ ላይ ተጽንኦ ሊኖረው ስለሚችል፥ በችኮላ እርሱን እንደ ነቢይ ከመከተላችን በፊት፥ ስለ ማንነቱ (እምነቱና አመለካከቱ) ማወቅ ይጠቅማል በማለት ነው እንጂ፥ ዳርዊን ዘረኛ ስለሆነ ውሸት ተናግሯል ብሎ ግለሰቡን ለመወንጀል አይደለም።

---

45 በዚህ መጽሐፍ የሰው ዘር ስንል፡- ነጭ፥ ጥቁር፥ ቢጫ ሁሉንም በማጠቃለል ነው እንጂ፥ በአንድ ጥቁር ዘር ውስጥ በቋንቋ የሚለያዩትን ቤተሰቦች፥ ጎሳ፥ ነገድ፥ እያሉ እንደሚለያዩት አይነት አይደለም።

46 ስለ ዳርዊን ሕይወት ዳርዊን በሚል ርዕስ ከድረ ገጾች ይመለከቷል።

ዳርዊን ዘረኛ ቢሆንም፥ እውነትን ሊናገራት፤ ወደ እውነት ተጠግቶም ሊሆን ይችላል፤ ግን ጥያቄው፥ "በእውነት እውነትን ነኪቷታል ወይ?" ነው። ዳርዊን ለሳይንስ ያደረገው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ፥ እናደንቀዋለን። ሆኖም፥ ከትሁትና ከቀላል ሳይንስ ወደ ከባድ ሳይንስ ስንሸጋገር፥ እናም የማናውቀው ነገር ሲኖር፥ ድንቁርናችንን በትእቢት ለመሸፈን ከምንጣደፍ ይልቅ፥ ማንኛውም ሳይንሳዊ መላምት ትክክል መሆኑን/አለመሆኑን በተጨባጭ ማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ በትእግስት እንጠብቅ። በቅንነት ስንታገስ፥ ሃቁን የሚከድንብን ይህ ተፈጥሮአዊ ተመጻዳቂነታችን ይቀራል። የዛን ጊዜ ጠቅላላ ሰብአዊነትን ከሁለት የሚከፍል አወዛጋቢ (አጨቃጫቂ) ሃሳብ ይቀርና እውነቱ ይገለጣል።

በንጹህ ሳይንሳዊ ምርምር ውስጥ፥ አስቀድሞ መቅረብ ያለበት የምርምሩን ውጤት ሊያዛባ የሚችል የጥራት መመዘኛ (uncertainity factor) ነው። ይህ የዝግመተ ለውጥ ምርምር በውስጡ የታቀፈው የጥራቱ መመዘኛ (uncertainity factor) ምን ያህል ነው? ብሎ መጠየቅ ይገባል።

የዘአካል መባዛት ጉዳይ በዝግመተ ለውጥ ትምህርት ውስጥ በጥሩ አይነት ተቀምጧል። ነገር ግን ፍጥረታት በጥራትና በአይነት እንዲህ የተበራከቱት በውስጣቸው በሚገኘው አካላዊ ጠባያቸው ብቻ ላይሆን ይችላል ብሎ ማሰብም አይከፋም። ለፍጥረትም ከፍተት የሚሰጥ ሳይንስ ሚዛናዊነቱ ይጎላ ሊሆን ይችላል።

ሳይንቲስት ነን የሚሉ ሁሉ ከፈጣሪ በታች እራሳቸውን ዝቅ አድርገው ያስተውሉ። ውሸት አልባ (ሳይንሳዊ) የሆነ መረጃ ይዞ ብዙ መዝለቅ ይቻላል፤ ጭቅጭቅና ክርክር የሚበዛው ግን ውሸት ሲኖር ነው። ከውሸት እንራቅና፥ ለሌላው ብለን ሳይሆን፥ ለራሳችን ብለን፥ እራሳችንን እያስጨነቅንም ቢሆን፥ ወደ እውነቱ እንጠጋ። ለአንድ የሳይንስ ተማሪና ለአንድ የሃይማኖት ተማሪ፥ በቅድሚያ በዝግመተ ለውጥ ትምህርት ውስጥ ሳይንሳዊ የሆነውና ያልሆነውን ለያይቶ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

በዝግመተ ለውጥ ትምህርት ውስጥ ከብዙ ቦታ እውነት ሞልቶ ሳለ፥ ይህንን እውነት ሰዎች ሲያሰተላልፉ፥ ሰዎችም መቀበል ሲቸግራቸው፥ እነርሱን ለማሳመን ሲባል ብቻ እውነት ከሚገባው በላይ ይጋነናል። እውነት ከመጠን በላይ ሲጋነን ወደ ውሸትነት ያመራልና፤ ለዚህ ነው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው።

የዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ወደ እውነት ለመጠጋት የሚሮጥ፥ ግን እውነትን የማይነካ በመሆኑ፥ ከይመስላል ይነሳና፥ መሆን አለበት የሚለውን ሃሳብ ያስረግጥና፥ ነው ለማለት ይቃጣዋል። ከይመስላል መነሳቱ ጥሩ ነው፤ መሆን አለበት

በማለት ፋንታ ግን፥ ሊሆንም ላይሆንም ይችላልና፥ እውነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ምርምራችንን እንቀጥላለን ቢል የተሻለ ነበር።

የዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና መነሻው ቅን ነው፤ ብዙ እውነትም ያለበት በመሆኑ ስለፍጥረታት ሁሉ ለመማርና ለመመራመር ይጠቅማል። ነገር ግን፥ ለፍጥረት ምንም ክፍተት የማይሰጥ ከሆነ፥ ስግብግብና ምድራዊ ነው፤ ትሁት አይደለም። ሰዎችን ከእግዚአብሔር ለማራቅ ሰይጣን የሚጠቀምበት ሊሆንም ይችላል። ሰይጣን ምን ጊዜም ይሞክራል፤ ግን ዘልቆ አያቸንፍም፤ ይህም መጽሐፍ አጋልጦታል።

አንዳንድ ሃይማኖተኞች በፍጥረታት የሚገኙ "ንዑስ ልዩነቶች" በዝግመተ ለውጥ ሊመጡ እንደሚችሉ በመካድ፥ የእግዚአብሔርን ሥራ የማያቋርጥ መፍጠር ብቻ ቢያስመስሉት፥ ይህም የማይጥም ነው። አንዳንድ ሌሎች ዘመናዊና ተጠራጣሪ ሃይማኖተኞች ደግሞ፥ ዝግመተ ለውጥ ብቻውን ሳይንሳዊ እውነት ሆኖ መዝለቅ እንዳቃተው ከሃቀኛ ሳይንቲስቶች ስለሰሙ፥ ዘላቂ በሆነው እምነታቸው ላይ በመጽናት ፋንታ፥ ወደ ሳይንቲስቶቹ ያልተሟላ አስተሳሰብ በማዘንበል፥ ዝግመተ ለውጥን እንደ አቢይ የተፈጥሮ ሕግ፤ እግዚአብሔርን እንደ ጣልቃ ገብ (እንደ አንድ ታላቅ ሳይንቲስት - ጠቢብ ሰው) በማድረግ - ታላቁና ኃያል አምላካችንን በማሳነስ - የዝግመተ ለውጥ መረጃ ማሟያ አስመስለውታል።

በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሳይንቲስቶች፥ ይህ መቶ በመቶ እርግጠኞች ያልሆንበት ጉዳይ ስለሆነ፥ ይህ ከዚህ መለስ ሳይንስ ነው፥ ከዚህ መለስ ደግሞ እምነት ነው ብለው፥ የሰብአዊነትን ስነአይምሮአዊ ሕልውና በመንከባከብ፥ እድገቱንና አቅጣጫውን በራሱ እንዲወስን ይተውታል እንጂ አያደናግሩትም። እነኛ ጥራዝ ነጠቅ የሃይማኖት ሰባኪዎች ግን፥ የዝግመተ ለውጥን ፍልስፍና እውነተኛ መጠኑን፥ ይዘቱን እና ሳይንሳዊ ችሎታውን አላወቁም።

ለእውነት የሚቻኮል የወጣቶች አይምሮ፥ እውነት የሚመስሉትን ሁሉ እየፈተነ፤ ሃቀኛውን እውነት እስኪያገኝ ድረስ እርጅና ይመጣል። ወጣቶች ይህንን የእምነት ደንቃራ - የጥርጣሬ መድረክን የሚከፍት ትምህርት ካለ ምንም መንፈሳዊ ትምህርት ወይንም ሳይንሳዊ ትችት (ክሪቲክስ) ጣልቃ ገብነት ከአስራ ሁለተኛ ክፍል ጀምረው ይማሩታል። ወጣቱ ተጠራጣሪ ሆነ።

በዚሁ እድሜአችን ውስጥ ብዙ ስንኩል ሳይንሳዊ ጽንሰ ሃሳቦች ስናስተናግድ እንደቆየን ሁሉ፥ የዛሬ ወጣቶችም በየዋህነት የሚቀበሉትን የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሃሳብ፥ የወደፊት ወጣቶች ጊዜ እንዳለፈበት ስንኩልነት የሚቆጥሩበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል።

እነሆ! በዘመናችን፥ የዝግመተ ለውጥ ትምህርትነቱ ከእውነት ጋር ብቻ አብሮ ካልሄደ፥ ቢቀርም አይጎዳም የሚሉ ብዙ ሰዎች ተነስተዋል። በሌሎች ሳይንሶች የሚቀርቡ መላምቶች ሳይንሳዊነታቸው ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ካላገኙ ቶሎ ውድቅ ይሆናሉ፤ ይኸኛውም ለሚያቀርበው መላምት ከግምታዊነት አልፎ ይህንን ያህል እየደፈረ እራሱን ከሌሎች ሳይንሶች ጋር ማዛመዱ ትክክል አይደለምና፤ የተለየ ይሁን ብለው የሚሟገቱ ሳይንቲስቶች እየበዙ መጥተዋል።

የዝግመተ ለውጥ ደጋፊዎች ደግሞ፥ ይህ ትምህርት ሌሎቹንም የሳይንስ ትምህርቶች እንደ ሰም በማያያዝ፥ ሳይንስ ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ላይ እንዲውል የሚያደርግ በመሆኑ ሊቀር አይችልም እያሉ ይሟገታሉ። እኛም፥ “በምድር ያሉ እንስሳት ሁሉ በዝግመተ ለውጥ ተገኙ፤ እንስሳት ሁሉ መነሻቸው አንድ ነው” ብሎ መደምደም ከአስተሳሰባችን ውጪ ስለሆነ፥ ከማወቃችን ጋር ብዙ የማናውቃቸው ጉዳዮች መኖራቸውን በመገንዘብ፥ ተገንዝበንም በመቆጠብ (ትሁት በመሆን፥ እራስን በማሳነስ) የሚከተለውን በአንክሮ እንመክራለን፡-

- በሳይንሳዊ ማስረጃ ሙሉ በሙሉ ያልተረጋገጡ ጽንሰ ሃሳቦች እንደ ሳይንስ ትምህርት ሆነው አይቅረቡ (ይለዩ)።
- እራሳችንን ሳይንቲስት ብናደርግ፥ የሳይንስ ተማሪዎችም ብንሆን፥ ኢሳይንሳዊ የሆነውን በቀጥተኛ ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰብ እየፈተንን እንለይ።
- በዝግመተ ለውጥ ትምህርት ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ለማስካድ ተስተካክሎ የተቀመጠ አለ። ትምህርትነቱ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድናደንቅለትና ስለ መለኮታዊ ኃይሉም መፈላሰፊያ እየሆነ መንፈሳዊ እመርታን የምናገኝበት ቢሆን ኖሮ፥ ይህ ትምህርት የተባረከ ነው ይባል ነበር። ግን አይደለም፤ ስለዚህ ይህ ትምህርት ይሰውን ልጅ ነፃ አስተሳሰብ (እምነቱንም ጭምር) ስለሚጨቁን የተለየ ይሁን።
- በእውነትና ማረጋገጫ በሌለው መላምት ላይ እየተመርኮዘ፥ መጨረሻው የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያስክድ ከሆነ፥ ይህ ትምህርት ሰይጣናዊ ነው ከመባል አያመልጥም። ቅንነት ከጎደለው፥ አመኔታም ከጎደለው፥ በራሱ ተንገዳግዶ ይወድቃል፤ እስከዛው ግን ከሌሎች ሃቀኛ ሳይንሶች ተለይቶ ይታይ።

አንዳንድ የዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ትምህርት ተከታታዮች አካላዊ ሕያዋን ሁሉ ተገኙ (ተለወጡ) እንጂ አልተፈጠሩም በማለት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ኃይል ስለተቋቋሙበት፥ ጠቢባን ነቀፉት፤ ሃይማኖተኞች አወገዙት፤ እውነተኞች የሆኑ

ተራ ሰዎች ሁሉ ጠሉት፤ ፈላስፎች አኮረፉት፤ አንዳንዶቹም አመረሩበት፤ ብዙሁኑ ተከፉበት። ከእግዚአብሔር የሚያስርቅ ሁሉ መጨረሻው እንዲህ ነው።

መጨራረስ አንዱ የዳርዊን ስብከት፥
ልባዊነት ቀርቶ በጉልበት መመካት፥
መንፈስን አውጥቶ፥ ለሥጋ መገዛት፥
ልዩ የሚያደርገንን ከሁሉም ፍጥረት - ሰውን ከእንስሳ አለመለየት፥
እንዲህ ያለው ሃሳብ ደስ አይልም በእውነት።

ዳርዊን ተፈጥሮን አብራርቶ ጽፎ - መዝግቦ ስናየው፥
በሥራው ተደስተን ስንዘጋጅ ልንመርቀው፥
ሥራውን ሁሉ በገዛ እጁ ደመሰሰው።

ዳርዊን የከጀለው፥ ሰውን ከዝንጀሮ በሆሚኒድ ሊያዛምደው፥
ዝንጀሮን በፕሪሜትስ ከአንትሮፓይዳ ሊያገናኘው፥
እንዲህ እያለ ወደ አንዲት ህዋስ ሰውን ሊመልሰው።

ተከታዮቹ የሕይወቱን ዛፍ ማሟላት ሲያቅታቸው፥
ይቅርታ መጠየቅ ተሳናቸው።

ሰው ከሰው ይለያል፥ ደግሞም ይመሳሰላል፥
ሰው መሳይ ፍጡር ነበር፥ አሁን ጠፍቷል፤
የሰውን ዝምድና ሳይለዩ ከኒያንደርታል፥
እስከ ሕያው ህዋስ መድረስ ያስቸግራል፤
የተሳለው የሕይወት ዛፍ እጅግ ቀሏል፤
በሃቀኛ ሳይንቲስቶች ተነቅፏል።

ዝንጀሮ የመሰሉ፥ ሰውም የመሰሉ ፍጡራን፥
ባለ ትላልቅ መንጋጋ፥ ባለ ሰፋፊ አጥንት፥
ባለ ጡንቻ፥ ተስማሚ የነበረ ሰውነታቸው፥
ምግብ ፈልጎ ለመብላት የሚጠቅማቸው፤
ነበሩ፥ ተመላልሰዋል ቢባልም በምድራችን፥
እልም ብለው ጠፍተዋል፥ ሲጨርሱ ጊዜያቸውን፤
ይህስ ካልሆነ ማን አወቀው? ቀጣይ ሕይወታቸውን።

# ምዕራፍ ሰባት

## ፍጥረት ከምናየው ሁሉ ባሻገር

የዳርዊንን የዝግመተ ለውጥ የሚተካ ሌላ እውነት እስኪገኝ ድረስ ሳይንሳዊ ምርምር አይቋረጥም። እኛም እስካሁን በትችቱ ላይ መቆየታችን እንዳያሳፍረን፥ ሳይንቲስቶች እና ሃይማኖተኞች የሚቀራረቡበትን መንገድ ከማሰብ አናቋርጥም። በሁለቱም አቅጣጫ ቀጥተኛ መልስ ያልተገኘላቸውን ጥያቄዎች ለየት ባለ መልክ መመልከትን የሚጋብዝ፥ የተጠራጣሪዎችን ጥርጣሬ ቀነስ የሚያደርግ፥ ለእምነትም ድጋፍ የሚሆን ጽንሰ ሃሳብ አቅርበናል። በተለይ አስተሳሰባቸውን በሳይንስ እውቀት ላይ የመሠረቱ ሃይማኖተኞች ይህንን ምዕራፍ እና የአጠቃላይ የመጽሐፉን ይዘት እንዲያስቡበት ተጋብዘዋል።

በዚች ምድርም ሆነ በሌሎች ምድሮች በአካላዊ ሕያዋን ትይዩ፥ ለሰው የማይታዩ (የማይገለጹ) ሕያዋን ሊኖሩ እንደሚችሉ ማሰብ አይከፋም። ግን፥ በሳይንሳዊ አስተሳሰብ የተጠመደ አይምሮአችን ካለ እምነት ይህንን ለማገናዘብ ቢነሳ፥ በሰዎች ሃሳብ ሊካተት የሚችለውን የጽንሰ ሃሳብ ማስረገጫ ፍልስፍና ካልተጠቀመ አይሆንለትም። ስለዚህ ወደዚሁ እናምራ። ከአካል በስተቀር ምንም የለም ብለው ለሚከራከሩን ሰዎች አንዳንድ መነሻ ፍሬ ሃሳቦችን እንሰንዝር።

- እግዚአብሔር አሁን የምናየውን አካላዊ ፍጥረት እና ለወደፊት የሚከሰቱትን አካላዊ ፍጥረታት ሁሉ “ቀደም ሲል” ፈጥሯቸዋል።
- እነኚህ አስቀድመው የተፈጠሩ ሕያዋን፥ ምድራዊ ሁኔታው ሲስተካከል በየጊዜው ሕልውናቸውን በአካላዊነት ይከስታሉ (ከምድር የሚገኘውን ምግብ እየበሉ)። ምድራዊ ምግብ (ኬሚካል) እየበሉ ምድራዊ አካላዊ ሕያዋን የሚሆኑት፥ ምናልባት ለሰው የማይታዩ (የማይገለጹ) ሰማያዊ ሕያዋን ሳይሆኑ አይቀሩም።
- እግዚአብሔር ሰማያዊ ሕያዋንን የፈጠራቸው በራሱ ጊዜ ሲሆን፥ ያ ጊዜ፥ አንድ ሴኮንድ፥ ቀንም፥ ሚሊዮን ዓመትም ቢሆን፥ ይህንን ማወቅ ለሰው ልጅ አይረባውም።

- ከላይ የተጠቀሱትን ሰማያዊ ሕያዋን እግዚአብሔር የፈጠራቸው እርሱ ከሚኖርበት ሥፍራ - ከአርያም ቢሆን፥ ይህንንም ማወቅ ለሰው ልጅ አይረባውም።

እንግዲህ ሰማያዊ ሕያዋን በአካላዊነት ከመታየታቸው በፊት የነበሩ፥ ለምድራዊ አካላውያን ሕያውነት መነሻ፥ ማንቀሳቀሻ፥ ሆነው እዚህ እንደደረስን ብንነጋገር፥ አላማችን ሳይንቲስቶችም ሆኑ ሌሎች፥ እነርሱ ከሚያስቡት ሌላ የአመላከከት አማራጭ ሊኖር እንደሚችል ለማሳሰብ ነው እንጂ፥ ይህ ነው እውነቱ ለማለት አይደለም።

አሁን የምናየውን አካላዊ ፍጥረት እና ለወደፊት የሚከሰቱትን አካላዊ ፍጥረታት ሁሉ “ቀደም ሲል” በሰማያዊ ሕያዋንነት ተፈጥረዋል ብንል፥ ይህ ከግንዛቤአችን ውጪ ሊሆን የሚችለው፥ ስለ ሰማያዊው አለም ነገር ማወቅ ባለመቻላችን እና፥ በእኛም አንጎል በተጨባጭ የሚቀረጸው አካላዊ የሆነው ብቻ ሊሆን ስለሚችል ነው። ሆኖም፥ ይህንን ጽንሰ ሃሳብ፥ በእውቀት ደረጃ ሳይሆን፥ እንዲሁ በሃሳብ ደረጃ ልንፈትሸው እንችላለን።

በጠፈር ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ የተገነባው ከአራት ነገሮች (ከአየር፥ ከእሳት፥ ከውሃ እና ከመሬት) ነው በማለት አሪስቶትል እና የቀደሙ አባቶች በማጠቃለል አስቀምጠውታል። ነገር ግን፥ ከተጠቀሱት አራት ጠባያት ጋር የሚዛመዱ እኛ የማናያቸው ሞገዶች መኖራቸውም ስለታወቀ፥ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ለመገልገል በቅተናል።

በጠፈር ያለ አካል ሁሉ እርስ በርሱ የሚያያዝ ከሆነ፥ በጠፈር አካላት መካከል አንድ ነገር ይኖራል እንጂ፥ እንዲሁ ባዶ ሆኖ አይቀርም። ይህም ማለት፡- በከዋክብት መካከል የሚኖረው ኃይል በጠፈር ውስጥ ባዶ ሥፍራ የሚባለውን ሁሉ “ፍጹም ባዶ - (vacuum)” እንዳይሆን ያደርገዋል ማለት ነው።

ይህ በጠፈር ያለውን አካል ሁሉ የሚያያይዘው ነገር ምን እንደሆነ ለመግለጽ የሞከሩ ብዙዎች ናቸው። በሂንዱ ፈላስፋዎች ዘንድ “አካሻ” በመባል የታወቀው ከተጠቀሱት አራት ጠባያት ሌላ አምስተኛው ሲሆን፥ ይህም አራቱን ጠባያት እርስ በርስ የሚያዛምድና የሚያገናኛቸው ነው።

በጠፈር ውስጥ በረቂቃን አካላት ሁሉ በመካከላቸው የሚያገናኝ ነገር (ኃይል) ይኖራል። ለምሳሌ፡- ኩአርክ፥ ሌፕቶን፥ ሜዞን፥ ሃርዶን የተባሉ እጅግ ረቂቃን አካላትን የሚያገናኛቸው “ግሉኦን” የተባለ ኃይል ይኖራል ተብሎ ይታሰባል።

ከዚህ ከአካላዊው አለም ተለይቶ የት ሊቀመጥ ነው የሰማይ መንግሥት? በውስጡ የሚኖሩትስ ሕያዋን ሰማያዊ ሕልውናቸውን የሚገልጡት በምን አይነት መንገድ ነው? ለምሳሌ፥ አንድ ብርጭቆ ውስጥ የሚገኝ አካል በአዛሂት (ሲሊካ) አተሞች የተገነባ በመሆኑ የብርጭቆው ሕልውና በአዛሂት አካላዊነት ይከሰታል። የሰማይ ሕይወትስ በምን ተከስቶ ነው ሰማያዊ ሕልውናው የሚረጋገጠው? ሰማያዊ ሕያውነት ካለ አካል በሌላ መንገድ ይከሰታል? ሰማያዊ ሕያውነት ካለ አካል በሌላ መንገድ የሚከሰት ከሆነ፥ ይህንን "ሌላ - ከአካል የተለየ" የተባለውን ምን ብለን እንጥራው?

ማንኛውም ቁስ አካል በአካላዊነቱ ይዘት (mass) ስላለው በውስጡ ስበት አለበት። ስበት ያለበት ሁሉ ክብነት መሠረታዊ ጠባዩ ነው። በምድራችን "አካል" ስንል እንደ ድንጋይ የሚጠጥር፥ እንደ ውሃ የሚፈስ፥ እንደ አየር የሚተን የሆነውን ሁሉ ሲሆን፥ ከዚህ የተለየውና ለኛ የማይታየው፥ ልክ እንደ አካል ሕልውና ያለው "ነገር" ለኛ ግልጽ አይደለም። አካላዊ ሕያው የመኖሩ ሕልውና በአካሉ ይከሰታል። አካል ሳይኖረው የሚኖር ህያው፥ መኖሩ እንዴት ይከሰታል?

በቋንቋ ለመግባባት እንችል ዘንድ፥ በተለያዩ ቃላት መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ፡- ፍጽምተ አካል፥ ረቂቀ አካል፥ ንጽረ አካል፥ ሰማያዊ ትስብእት፥ የመንፈስ አካሉ፥ ሰማያዊ አካል፥ ብርቅ አካል፥ አጸደ ነፍስ..ወዘተ...ብንል፥ ስለማናውቀውም ሁሉ መሸፈኛ፤ የማይገባንንም ወደሚገባን ማሸጋሸጊያ ይሆንልናል። የተጠቀሱትን ድርብ ቃላት ልንጠቀምባቸው ካልፈልግን እና፥ እንዳው በደፈናው፡- "ሚሻክል" የሚል ቃል ፈጥረን ብንገላገልም፥ ከእንግዲህ በመካከላችን መግባባትን ሳንፈጥር አንቀርም (በዚህ መጽሐፍ)።

እኛ ስናይ - ስንቆጥር፥ ስንዳስስ፥ ስናሽት፥ ስንሰማ፥ የአካልነት ጽንሰ ሃሳብ ቁልጭ ይላል። በሰማይ ቤት እንዴት እንደሆነ ስናስብም፥ ቶሎ ከሃሳባችን ድቅን የሚለው በህልም እንደምናየው አይነት ይሆንብናል። ይህም በሃሳብ የሚቀረጽ የህልም አካል ወይም የቅዠት አካል፥ ሕልውናውን በእውን ሊያረጋግጥ የሚችል ስላልሆነ፥ ከቁም ነገር የሚገባ አይደለም። ነገር ግን በሰማይ ቤት አንድ ነገር ከሌላው መለየቱን የሚያመለክተን ሃሳባችን ብቻ እንዳልሆነ እናምናለን። የሰማይ ቤት ሕያዋንም ሰማያዊ ሕልውናቸውን (መኖራቸውን) የሚገልጹበት መንገድ በኛ ምድራዊ አስተሳሰብ የማይለካ፥ የማይመዘን (የማይታወቅ) እንደሆነም ይገባናል።

ስለ መንፈሳዊ ጉዳይ በተነጋገርን ቁጥር፥ በምድር አካል የተባለ በሰማይም አካል ቢባል (እኛም የሰማይ ወይንም የመንፈስ አካል እያልንም ብናወራ)፥ ሁለቱን አለም አንድ የሚያስመስለው አይምሮአችን በአስተሳሰብ ተሳታፊ ስለሚሆን እውነቱን

ሳያውቅ ይቀራል። በተለይ በነጠላው “አካል” የሚለውን ቃል ለሰማይ ቤት መጠቀማችን ምድራዊ የአስተሳሰብ ተጽንአ ሳያስከትል አይቀርም።

ለምሳሌ፡- ስለ ሥላሴዎች ሦስትነት ስናስብ ልክ እንደ ምድራዊ አካላዊ ሦስትነት ሊመስለን ይችላል። በእርግጥ ስለ ሥላሴዎች ምሥጢር ሰው ሊያውቅ አይችልም። በአንክሮ መታወቅ ያለበት ግን በባህሪ አንድ መሆናቸው ሆኖ ሳለ፥ በአካል ሦስት ናቸው ሲባል በምድራዊ አመለካከት እንደምናስበው እየመሰለንም በዚህ ጉዳይ ላይ ስንጨቃጨቅ ቆይተናል። ነፍስ፥ ሕያው ነፍስ፥ መንፈስ፥ የተባሉትም ቃላት ለሁሉም ሰው አንድ አይነት የጋራ ፍቺ ላይኖራቸው ይችላል።

መንፈስ ቅርጽ ቢኖረውም ባይኖረውም፥ በአካላውያን የሚቆጠርና የሚሠፈር አይደለም። የመንፈስ ሰውነቱ “የሚቆጠር የሚሠፈርም” ቢሆን፥ ይህ ሊሆን የሚችለው በምድራዊ ሰው ሳይሆን በሰማይ በሚኖሩ ሕያዋን ይሆናል።

በሂንዱ ፍልስፍና መሠረት አምስቱን ጠባያተ ጠፈር ጠቅሰናል። በኛም ፍልስፍና ጠባያተ ጠፈር አምስት ናቸው። አምስተኛውም መንፈስ ነው። በእርግጥ ይህ ሥጋችን የመሬት (ውሃ፥ አፈር፥ እሳትና ነፋስ) ሲሆን፥ በውስጣችን የመሬት ያልሆነ ጠባይ ያለውና አምስተኛው መንፈስ ነው። መንፈስ የተባለው ቃል ሰማያዊውን አለም ሲያመለክት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአምስት መቶ በላይ ተጠቅሷል።

መንፈስ “ቅርጽ” ይዞ (መስሎን) በሰው ፊት እንደ ዛፍ ወይም እንደ ደመና ሆኖ ቢታይ፥ የሚታየንን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ምድራዊ ቃላት አይበቁንም። አካል ስንል በውስጡ ያለ ነገር ሁሉ ስብስብ የሚልበት ማለታችን ነው። መሰብሰብ ከሌለ አካልነትም አይኖርም። በዚሁ አንጻር፥ የአካላዊነት ጠባይ የሌለው (ንጽረ አካል/ፍጽምተ አካል) የመሰብሰብ ግዴታ የለበትም። ስለዚህ ተገንጥሎ በመሄድና፥ ተመልሶም በመምጣት ቢሆን፥ እጅግ ግዙፍ መሆንን ወይንም እጅግ ረቂቅ መሆንን - ሁለቱንም ጠባያት ይዞ ይኖራል ማለት ነው (ይሆን?)።

አካላዊነትን ክብነት እና ስበት (gravity) ይገዙታል። ምድር፥ ጸሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ ሁሉ ባለ ቅርጽ (ክብ)፥ ባለ ጥላ እና ባለ ስበት ናቸው። መንፈስ (የመንፈስ አካሉ - ንጽረ አካል - ሚሻክል) ግን በክብነት የማይወሰን፥ የማይቆጠር፥ የማይወሰን፥ የማይመዘን ነው። አካላዊነት ባለ ጥላ ነው፤ መንፈስ ግን አካል ስላልሆነ ጥላ ሊኖረው አይችልም።

መንፈስ በስበት የማይወሰን፤ ከሚፈልገው ሥፍራ ከመቅጽበት የሚደርስ፤ የሚያግደውም ምንም አካላዊ የሆነ ነገር (ግርግዳ፥ ተራራም ሆነ ባህር) የሌለበት ነው። መንፈስ ከስበት ውጪ በመሆኑ ይፈጥናል። በአንጻሩ፡- ኑሮው ሁሉ ከስበት ጋር

ፍትጊያ ያለበት፥ ክብነት ቅርጹ የሆነ አካል (ቁስ አካል) ነው። አካላዊ ሕያው ሁሉ ፈዛዛ፥ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚከብደው ነው።

አካል ወይም ቁስ አካል ስንል ማንኛውንም ይዘት ያለውንና ቦታ የሚይዘውን ሁሉ ያጠቃልላል። በዚህ የአካል ትርጉም መሠረት እሳትን ከፋፍለን ብናየው፡- በእሳት ነበልባል ውስጥ የተለያዩ ጋሶች (ኦክሲጂን፥ ካርቦንዳይኦክሳይድ፥ ካርቦን ሞኖክሳይድ…ወዘተ) ስለሚኖረው አካላዊ ይዘት አለው። ነገር ግን፥ የነበልባሉ ሙቀትና ብርሃን ይዘት የሌለውና ቦታም የማይዝ በመሆኑ ራሱን የቻለ አካል አይደለም። እንደ አካል በቁጥር አይቆጠርም። ለምሳሌ፡- በአካላዊነት ከሚቆጠር እንጨት እሳት ሲወጣ፡- አንድ፥ ሁለት፥ ሦስት.. እሳት ወጣ ተብሎ አይቆጠርም።

እኛ የምናውቀው እሳት አካል ሲቃጠል፥ በአካል ውስጥ ያሉት ኢሌክትሮኖች ማእከላዊውን የአቶም ክፍል (ፕሮቶን እና ኒውትሮን ያሉበትን) እየለቀቁ ሲወጡ የሚረጭ ኃይል ነው። ኢሌክትሮኖች ተረጭተው ሲያልቁ የፕሮቶኖች ሕልውና ይናወጻል፤ ያም በአካልነቱ የሚታወቅ ነገር እንደ እንጨት ወይም እንደ ወረቀት ሰነፍ ከሆነ፥ ቶሎ ወደ አመድነት ይቀየራል። እንደ ድንጋይ ጎበዝ ከሆነም፥ ሕልውናውን ሳይለቅ ይቆያል።

ከምድራዊ አካል ውስጥ የአካላዊ ጠባያትን የማያሟላ እሳት ብቅ ካለ፥ በጠፈር ውስጥም የአካላዊ ጠባያትን የማያሟላ "ነገር" እንደማይጠፋ እናስበው። ከጠፈር ሌላ፥ ለኛ የማይታይ ሰማይ ቢኖርም፥ በመንፈሳዊው አለም፡- የሰማይ ሰዎች መላእክትም ከሚኖሩበት ሥፍራ (አርያም)፥ ፍጽምተ አካላቸውን (ንጽረ አካላቸውን) በራሳቸው ቋንቋ "አካሌ - አካላችን" በማለት ይገልጹ ይሆናል።

የሰማይ ሰዎች (ወይም መላእክት) እንደ አካላዊ ሰው አካላዊ መግለጫ ካልተሰጣቸው በስተቀር መኖራቸው አይታወቅም ማለት አይደለም። እና፥ በዚሁ በምድራችን ቢኖሩስ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

አካላዊ ያልሆነ - የማይታይ - የዘመኑ የሞገድ መለኪያ መሳሪያ የማይለካው "ነገር" ቢኖርና፥ ይህም በሕያዋን ፍጥረት ውስጥ የሚጫወተው ሚና ቢኖረው ማን ያውቃል?

ቀደም ሲል ስለ አካላዊው ጠፈር ብዙ ተነጋገርን፥ አሁን ደግሞ ስለ ሰማይ ስናወራ፥ መጠነኛ መደናገርን ሳንጋብዝ አልቀረንም። ሰማይ ከምድር ተለይቶ ጠፈር ውስጥ አንድ የተደበቀ ቦታ ቢሆን፥ ይህንን ችለን መመለስ ስለማንችል፥ ለኛ ለግንዛቢያችንም የሚገባን፥ ሰማይ ስንል በምድራዊ ገለጻ፥ አካል ከምንለው ውጪ ያለውን ሁሉ ይሆናል። ስለዚህ ሰማይ (ለኛ የማይታይ የመላእክት መመላለሺያ) ሲሆን፥ ይህም ሰማይ በዚሁ በምድራችንም ክልል ውስጥ ሊካተትም ይችላል።

በአካል ትይዩ “ሌላም” ሊኖር እንደሚችል ዳንኤል ይጠቁማል። “ዓይኖቼንም አነሳሁ፥ እነሆም በፍታ የለበሰውን ጥሩም የአፌዝን ወርቅ በወገቡ ላይ የታጠቀውን ሰው አየሁ። አካሉም እንደ ቢሪሌ ይመስል ነበር፤ ፊቱም እንደ መብረቅ ምስያ ነበር፤ አይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና፥ ክንዶቹና እግሮቹ እንደ ጋለ ናስ፥ የቃሉም ድምጽ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምጽ ነበረ።” ዳን. 10፡5 - 7

በአካላዊ አለም ያ<u>ለ</u> ማንኛውም ነገር አካላዊ ባልሆነውም አለም ውስጥ በልዩ መልኩ እንደሚገኝ በሃይማኖት (በእምነት) እናውቃለን። ለምሳሌ፥ የመሬት ቤት አካላዊ በሆነ ደንጊያ ይሠራል፤ የሰማይ ቤት ደግሞ ምድራዊ - አካላዊ ባልሆነ (ሰማያዊ አካል- ደንጊያ የመሰለ ነገር) ይሠራል።

“ልቦናዬ ትራቀቅ ጀመር፤ ከሰማዮች በላይ ወዳለች ወደ ጽርሐ አርአይም ትወጣ ጀመር። ከቅዱሳን መላእክት በክብር የተወለዱ ጻድቃንንም በእሳት ዋእይ ላይ ቁመው አየኋቸው። ቀሚሳቸው መጎናጸጋያቸውም ነጭ ነው፤ የፊታቸውም ብርሃን እንደ በረዶ ነው።...

መንፈስ ቅዱስም ሄኖክን በሰማዮች በላይ ባለ ሰማይ ሰወረው። በዚያም ብርሃን መካከል በእንቁ የተሠራ ቤትን አየሁ። በነዚያም ድንጋዮች መካከል ደህነኛ የሚሆን የእሳት አንደበቶች አሉ።....” ሄኖክ 20፡29 - 36

ሄኖክ በጠፈር ሲመላለስ እንደተመለከተው፥ በመንግሥተ ሰማያት ያሉ ቤቶች ግርግዳና ጣሪያቸው ሁሉ እንደ ምድራዊ ቁስ አካል ሆነው ነው የተገለጹት።

የሰው ልጅ በተሰጠው የተፈጥሮ የአስተሳሰብ ጸጋ፥ ከሁሉ ነገር ውስጥ ዘላቂ የሚሆነውን እውነት መርምሮ ካልደረሰበት፥ ያ እውነት የተባለ ነገር እንደሌለ ነው የሚቆጠረው። ስለዚህ፥ ግልጽ ካልሆነ ሃሳብ ተነስቶ ከመፈላሰፍ ይልቅ፥ ግልጽ ከሆነ ሃሳብ ተነስቶ ወደ ሃቅ የሚመራውን ሃሳብ ማጠናከር ይሻላል።

ይህ ሁሉ ሃተታ ያስፈለገው እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሲፈጥር ምድራዊ ጭቃ አብኩቶ፥ በጁ ጠፍጥፎ ላይሆን ይችላል በማለት፥ ባጠቃላይ ፈጣሪ በጥበቡ ያከናወነውን፥ ከኛ ግንዛቤ ውጪ የሆነውን ሁሉ በሃሳባችን እንድንፈላሰፍበትም ያህል ነው። ስለዚህ የሚከተሉትን ጽንሰ ሃሳቦችም እናስተውል፡-

- እግዚአብሔር ሲፈጥር ለኛ በማይታወቅ መንገድ መሆኑን፤
- እግዚአብሔር ከዛው በሚኖርበት በመንግሥቱ (በጽርሐ አርያም) አስቀድሞ አካላዊ ያልሆኑ ሕያዋንን ሊፈጥር እንደሚችል፤
- አካላዊ ያልሆኑ ሕያዋንን አስቀድሞ ፈጥሮ፥ ከዚሁ ከምድራችን ገብተው አካላዊ እንዲሆኑ ሲያደርግ፥ ምናልባት እኛ ያንን፥ በአካላዊነት የሚገባንን ስናይ ብቻ እንደሆነ ፍጥረት የምንለው።

## ፍጥረት ከኛ ክልል ውጪ

ጠፈር ከመዘርጋቱ በፊት በሚል አርእስት ተነጋግረናል፤ ስለጠፈር አካላት ግንባታም አውስተናል፤ ስለ ምድራችን ግንባታና ስለ አለቶቿ ሁሉ ተነጋግረናል። ስለ አካላዊ ሕያዋን በምድር መባዛት ጉዳይ፥ በዝቅጠ አለቶች ውስጥ በቅሪተ አካላት ከሚታዩት ተነስተን በግልጽ የሚታወቀውን ጠቀስን። ወደፊት ለሚፈጠሩ ሕያዋን እንዴት ምድር ምግብ ሆና እንደተዘጋጀችም አውስተናል። ከዚህም በመቀጠል፥ ስለ ዳርዊን ዝግመተ ለውጥ አጠቃላይ ግምገማ በማድረግ፥ ይህ ፍልስፍና የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ሰዎች እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ ትምህርት ሊሆን ስለሚችል፥ ወደ እግዚአብሔር የሚያመለክተውን ትምህርት እንድንሻ መክረናል። ሆኖም፥ ምድራዊ ሕያዋን ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ መሬት ላይ ስለመገኘታቸው ያወቅነውን ያህል፥ ስለመፈጠራቸው ምንም ያወቅነው ነገር የለም፤ ከእምነት በስተቀር።

የመጀመሪያው ምድራዊ ሕያው ተገኘም ተፈጠረም፥ ሳይንቲስቶችን ሊያሳምን የሚችል - ሕያውነት እንዴት በምድር ላይ እንደተቀጣጠለ የሚያስረዳ ሃይማኖታዊ ገለጻ ቢገኝ ኖሮ፥ በተፈጠረ እና በተገኘ መካከል ያለው ልዩነት ጠፍቶ ለጋራ እምነት መሠረት የሚሰጥ ትንተና ሰውን ሁሉ ባረካው ነበር። ሆኖም፥ ቀኑን ጠብቆ ሁሉ ነገር እንደሚገለጽ ሁሉ፥ በጊዜው ማወቅ የሚገባንን የሚያሳውቅ እግዚአብሔር፥ እርሱ በፈቀደ ጊዜ እናውቃለን።

አብዛኛው የአለም ሕዝብ በየወቅቱ የሚነገረውን ሳይንሳዊ ዜና እንዳለ ይቀበላል እንጂ፥ እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ ጊዜውም ችሎታውም አይኖረውም። እስቲ ሁላችንም (ሳይንቲስት የሆነውም ያልሆነውም) ከቅንነትና ከእውነት እንነሳ፤ ችሎታው ባይኖረንም፥ ከዝግመተ ለውጥ ባሻገር አንዳንድ ያላደጉ ሃሳቦችን በጥራዝ ነጠቅነትም ቢሆን ለመመልከት እንሞክር።

እውቀት ለሰው እንዲገባ ተደርጎ በመጽሐፍ እስኪጻፍ ድረስ፥ ወይንም አዋቂ በተባሉ ሰዎች እስኪነገር ድረስ አንጠብቅ። እውቀት ምንጊዜም በዙሪያችን አለ።

“ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።” መዝ. 19፡1

ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ሲናገሩ እንስማቸው፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ሲያወራ እናዳምጥ፤ ሕይወት ያላቸው ሁሉ ሲለፈልፉ ጆሮአችንን እንክፈት።

ምድራዊ አካላዊ ሕያዋን ሁሉ ከባለ አንድ ህዋስ ጀምሮ፥ በዝግመተ ለውጥ (ቀስ በቀስ በራሳቸው እየተለዋወጡ) ከዚህ ደረሱ ብንል፥ በመንፈሳዊነት አርቆ

ማሰቡን ይገታብናል፤ ሁሉን ነገር በምድርና ለምድር ወስኖ ያስቀርብናል፤ ከምድራዊነታችንም ባሻገር እንዳንመለከት ያውከናል።

በሃይማኖት እግዚአብሔር ጠፈርን በቃሉ ብቻ (ከምንም) ዘረጋ ብለን የምናምነው እና በዘመናችን የሳይንስ ምርምር ጠፈር ከብርቅነት ተጀመረ ያልነው በሃሳብ ደረጃ እንደሚመሳሰል ቀደም ሲል ጠቁመናል። ግን፥ አንድ ነገር እንዴት ከምንም ይፈጠራል? የሚለው ጥያቄ ነው ከሳይንሳዊ አመለካከት ወደ እምነት የሚከተን። እንዲሁም በተመሳሳይ፥ ከዳርዊን የዝግመተ ለውጥ በስተጀርባ፡- አካላዊ ሕያዋን እንዴት ነፍስ ዘሩ? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ መልስ ያልተገኘለት፥ ይህንኑ ጉዳይ በስነ አመክኖአዊ ምርምር ትንሽ እንቆይበታለን።

እንስሳት በተለያዩ የጂኦሎጂ መደቦች ውስጥ በግልጽ መታየታቸውን አስመልክቶ፥ በአንድ ወገን በራሳቸው ተገኙ ሲባል፥ በሌላ በኩልም እንዲህ ባንድ ጊዜ አይነታቸው የሚበራከተው ካለ ፍጥረት ሊሆን አይችልም ስንል፥ የተለያዩ የሃሳብ ግጭቶች ውስጥ ሳንጋባ አልቀረንም። በዚህም ሆነ በዚያ ስንመለከት፥ ቁልጭ ያለ እውነትን ማየት የሚያቅተን፥ እኛ አካላውያን ስለሆን እና የሚገባንም አካላዊ (ሥጋዊ - ምድራዊ) የሆነው ብቻ ሊሆን ስለሚችል፥ አሁን ወደ ሌላ አለም ለመግባት እንሞክር።

"ሰማያዊ ሕያዋን" አካላዊውን (ኬሚካል) ሲበሉ ምድራዊ አካላዊ ሕያዋን ሆኑ ቢባል፥ ለጥያቄዎቻቻችን ሁሉ መልስ ማቅረብ የሚቻልበትን መድረክ እንከፍታለን። ይህ ጽንሰ ሃሳብ እውነትነት ሊኖረው መቻሉን በሳይንሳዊ መንገድ ማረጋገጥ አይቻልም።

ሕይወትም እንደ ግዑዝ አካል ሁሉ ቦታ መኖር (መገኘት) አለበት የሚል የፓናስፐርሚያ (panaspermia) ጽንሰ ሃሳብ ያቀረቡ ሰዎች እንደነበሩ ቀደም ሲል ጠቅሰን ነበር። ነገር ግን ለዚህ በቂ ማስረጃ የሚሆን ስላላቀረቡ፥ በጠፈር ውስጥም የሕያዋንን ሁሉ ቦታ መገኘት የሚያረጋግጥ ፍንጭ ባለመታየቱ፥ ይህ ጽንሰ ሃሳብ፥ ሁሉን ነገር እኛ ካላየን አናምንም በሚሉ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

ሕይወትም እንደ ግዑዝ አካል ሁሉ ቦታ መኖር (መገኘት) አለበት በማለት ፋንታ፥ ሕይወት እኛ በማናየው ሰማያዊ አለም ይፈጠራል ቢሉ ኖሮ፥ የዚህን ጽንሰ ሃሳብ እውነትነት በሳይንሳዊ መንገድ ለማፍረስ አይቻልም ነበር።

ሳይንሳዊ አመለካከታችንን በሃይማኖት (በእምነት) እና በስነ አመክንዮ በማጠናከር፡- እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፤ እግዚአብሔር በሰማይ በመንግሥቱ ከሚኖርበት ሥፍራ ሆኖ ይፈጥራል፤ ከፈጠረም በኋላ፥ እነርሱ ሰማያዊ ሕያዋን

ይሆናሉ፤ ወደ አካላዊው አለም ሲገቡና ምግብ መቅመስ ሲጀምሩ በአካላዊነት ይከሰታሉ (ይገለጻሉ - ይታያሉ) በማለት እንጀምራለን።

እግዚአብሔር አሁን የምናየውን አካላዊ ፍጥረት እና ለወደፊት የሚከሰቱትን አካላዊ ፍጥረታት ሁሉ "ቀደም ሲል" ፈጥሯቸዋል ስንል፡- እግዚአብሔር በንጽረ አካላዊነት (ፍጽምተ አካላዊነት) "አንዴ" ከፈጠረ በኋላ፥ ፍጥረታቱ በምድር የሚገኘውን ምግብ በልተው ምድራዊ አካላዊ እንዲሆኑ አደረገ፤ አካላዊ ከሆኑም በኋላ፥ እርስ በርሳቸው እንዲበዙና እንዲባዙ ፈቀደላቸው (አንዴ የፈጠረውን መልሶና መላልሶ ስለማይፈጥር) የሚለውንም ሃሳብ በማቀፍ ነው።

እግዚአብሔር አስቀድሞ በማይታይ አለም (በሰማይ) የፈጠራቸውን ንጽረ አካላዊ (ሚሻከላዊ) ሕያዋንን በምድር ላይ ወደ ምድራዊ አካላዊነት ለወጣቸው ወይንም ምድራዊ ሕይወት ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው፤ ሂዱ ወደ አካላዊው አለም ግቡ፤ ከዛም እየበላችሁ እደጉ፤ ተባዙም ብሎ፥ ወደ ዘአካልነት ለወጣቸው ስንል፥ እስካሁን ስንነጋገርበት የቆየነውን - ፍጥረት ወደ ምድራችን መግባቱንና በአካላዊነት መከሰቱን (ተገኘ የተባለውን) በማስመልከት ነው። ታዲያ፥ ምንም እንኳን ሕይወትም እንደ ግዑዝ አካል ሁሉ ቦታ መኖር (መገኘት) አለበት የሚለውን የፓናስፐርሚያ (panaspermia) ጽንሰ ሃሳብ የሚደግፉ መረጃዎች ባናገኝም፥ ሕይወት የተዘራው በዚች እንደ አንድ የጠፈር ጠብታ የምትቆጠር ምድራችን ውስጥ ብቻ አለመሆኑን ያስተውሏል።

ጠፈር ከተዘረጋ ጀምሮ ምግብ ተዘጋጅቶ የተቀመጠው (የሚቀመጠውም) በዚች እኛ በምናውቃት ምድር ብቻ አለመሆኑንም ልብ ይሏል። ታዲያ የፓናስፐርሚያን ጽንሰ ሃሳብ ለየት ባለ መልኩ ብንመለከተው፥ ሕይወት ከሌላ የጠፈር አካል መጣ ከማለት ይልቅ፥ እግዚአብሔር ከሰማይ (ከመንግሥቱ) የፈጠራቸውን ሕያዋን፥ ለአካላውያን የሚሆኑ ምግቦች ከተዘጋጁበት ከጠፈራዊ ምድሮች ሁሉ ሲያከፋፍል፥ ጊዜው በደረሰ ጊዜ፥ ይህ ዕድል ለዚህች እኛ ለምናውቃት ምድር ደረሰ ማለቱ ሳይሻል አይይቀርም።

በምድር ላይ የተለያዩ ምግቦች የተገኙት በተለያዩ ጊዜያቶች ስለሆነ፥ እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያት ቢፈጥርም፥ ባንድ ጊዜ ቢፈጥርም፥ የተለያዩ ምግቦች ካዘጋጀ በኋላ ይሆናል ፍጡራኑን አካላዊ (ምድራዊ) ሕያዋን እንዲሆኑ የሚለቃቸው (ለኛ ምድር እንዲሁም ለሌሎቹ)። እርሱ ባይለቃቸው (ባይፈቅድላቸው) እና እነርሱ በገዛ ፈቃዳቸው ወደ አካላዊ ምድር ጥልቅ ቢሉ፥ ለነርሱ የሚስማማ ምግብ ስለሚያጡ ሕያውነታቸውን በአካላዊነት መከሰት ይሳናቸዋል፤ ስለዚህ ወደ ቀድሞ ሥፍራቸው ይመለሳሉ። እንደገናም በራሳቸው ይሞክራሉ፤ ከተሳካላቸው ይቀራሉ፤

ካልተሳካላቸው ይመለሳሉ። ወይንም ለገቡበት ምድር ተስማሚ የማይሆን አካል ይይዙና አስጨናቂዎች ይሆናሉ። ለምሳሌ በምድራችንም፥ እጅጉን ግዙፋን ሆነው በማደግ፥ ቁመታቸው እስከ ሦስት ሺህ ክንድ የደረሰ ግዙፋን እንደነበሩ በመጽሐፈ ሄኖክ ተጠቅሷል።[47] እነኚህ ኃጥአን መላእክት ከፈጣሪያቸው ፈቃድ ወጥተው፥ የራሳቸውን ስሜት በመከተላቸው፥ መሬት ልትሸከማቸው ያቃታት ግዙፋን ሆኑ።

"አሁንም ከመንፈሥና ከሥጋ የተወለዱ ረዓይት በምድር ላይ ክፉዎች መናፍስት ይባላሉ።" ሄኖክ 4፡40 (በተጨማሪ እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት የተሰኘውን ግጥም ከምድራዊነታችን ባሻገር ሁለተኛ መጽሐፍ ይመልከቱ)።

የመጀመሪያው ባለአንድ የሕያው ሴል ሕይወቱን በገዛ ራሱ ሊያገኛት እንደማይችል ብንገነዘብም፥ አንዳንድ መሠረታዊ ጥያቄዎች ካልተመለሱ በስተቀር ማወቃችን ወደ እውነት አያስጠጋንም። ስለዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ደግመን በመጠየቅ፥ መልሱን እኛው ራሳችን ለመስጠት እንሞክር።

- አካላዊ ሕይወት እንዴት ሊኖር ቻለ ካለ ምግብ?
- ምግብ ሳይበላ ሕያው የሚሆን ማነው?
- ተፈጥሮ ያዘጋጃቸውን ምግቦች በልቶ አካላዊ ሰውነትን የተቀናጀ፥ ግን አስቀድሞ አካላዊ ያልሆነ ባለ ሕይወት ነበር ወይ?
- ቢኖርስ ማነው እሱ?

የመጀመሪያዎቹ የምድር ሕያዋን ባለ አንድ ሴሎች ነበሩ፤ የመጀመሪያው ባክቴሪያ እንዲሁም አረንጓዴ የውሃ ተክል (አልጌ) ከዛሬ ሦስት ሺህ ሚሊዮን ዓመት ጀምሮ የነበሩ የመጀመሪያዎቹ አካላዊ ሕያዋን ናቸው ቢባል፥ ይህ ውሸት ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ የረቀቀ አነጋገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሕያዋን ከዛም በፊት ይኖሩ ስለነበር ነው። እንዴት? ለሚለው መልስ የሚከተለውን መላ ምት እናስተውል።

ያ የመጀመሪያው አካላዊ ህዋስ (ሴል) ትንሽ ነበር ማለት አይቻልም፤ ትንሽነት አንጻራዊ ነውና። ባሁኑ ጊዜ ፊዚስቶች በየጊዜው እጅግ ትናንሽ ነገሮችን ሲያገኙ የትንሽነት ጽንሰ ሃሳብ ቅጥ ያጣ ሆኖባቸዋል። እስቲ ያቺን ባለ አንድ ሴል እንደ ዝሆን አተልቀን እንመልከታት። ለምን? እርሷስ በሕያውነቷ ከዝሆን በምን ታንሳለች። ያቺን ባለ አንድ ሴል ትንሽ ያደረጋት አይምሮአችን ነው። እስቲ "ትልቅ

---

[47] ሄኖክ 2፡ 12

ነች! ትልቅ ነች!" ብለን እናስብ።......አሃ! ከዚህ ግዙፍ ባለ አንድ ሴል በፊት ሌላ አነስ ያለ ሌላ ባለ ሕይወት ነበር፤....ሌላም ነበር....ሌላም ነበር...።

ያ ግዙፍ ባለ አንድ ሴል ከየት መጣ? በውስጡ ያለውን ሕያውነት ከየት አገኘው? እንዴት ያን ያህል ግዙፍ ሆነ ሳይበላ? እንዴትስ ሊበላ ቻለ ሕያውነት ሳይኖረው? ይህ ጥያቄ የዳርዊን ተከታዮች ባለ አንድ ህዋስ (ሴል) ካለ ምንም መለኮታዊ ኃይል በራሱ ተገኘ ሲሉ፥ ቀደም ሲል ያቀረብናቸውን አምስት ጥያቄዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ይጋብዛል።

ሕያዋን ራሳቸውን በአካላዊነት የከሰቱት ባለ አንድ ሴሎች በምድር ላይ "መታየት" ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ነው ቢባል፥ ይህ የረቀቀ አነጋገር ይሆናል። ነገር ግን በአኳያው ሌሎች የማይታዩ ሕያዋን ቢኖሩስ? ፍጥረት ሁሉ፥ ሰውም ጭምር ከዛ ከመጀመሪያው ህዋስ በፊት በረቀቀ መልኩ ተፈጥሮ እንደሆነስ? ማን ያውቃል።

በምድራችን የሚገኙ ንጥረነገሮች (elements) በሌሎች በጠፈራዊ አካላት ሁሉ እንደሚገኙ፥ አይነትና ብዛታቸውም ተቀራራቢ እንደሚሆኑ ጠቅሰን ነበር። ታዲያ፥ እንደዚሁም በተመሳሳይ፥ የምድራዊ ሕያዋን አይነታቸው ከባክቴሪያ ጀምሮ እስከ ሰው ድረስ እጅግ ብዙ እንደሆነ ሁሉ፥ በሰማያውያን መካከልም ያለው ብዛትና አይነት ያን ያህል ወይንም ከዛ በላይ ቢሆን፥ ከነርሱም ዘንድ፥ በአካላዊ ሕያዋንነት የተከሰቱትም ያን ያህል ቢሆኑስ? ይህንን ማን ያውቃል።

ሕይወት አካላዊ ሆኖ በምድራችን መራባት የጀመረው እንዴት ነው? ባዮሎጂስቶች ስለ ሕይወት መባዛት ያስተምሩናል። የምናውቀውንና በግልጽ የምንረዳውን አብራርተው ይገልጹልናል። ስለመፈጠርስ ማን ነው የሚያስረዳን?

ከባለ አንድ ሴል (ህዋስ) የረቀቀ "ነገር" ሊኖር አይችልም ወይ? ብለን ስንጠይቅ፥ ከአካላዊነት ውጪ ሊኖር ስለሚችል "ነገር" - ስለ ሰማያዊነት ማሰባችን አይቀርም። ያ የመጀመሪያ በላተኛ ባለ ሕይወት መሆን አለበት። ሕይወትማ ከሌለው እንዴት አድርጎ ይበላል? ነገር ግን እንዴት ሕይወት ኖረው ሳይበላ? አካላዊ ሕያዋን ካልበሉ ይሞታሉ። በአንጻሩ፥ ሰማያዊ ሕያዋን "ሲበሉ" እና በሰማያዊነት "ሟች" ሲሆኑ በአካላዊነት ይፈጠራሉ ብንል ወደ ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ይስበናልና፤ በድፍረት እንቀጥል።

ምድር ወደፊት ለሚፈጠሩ ሕያዋን ምግብ ሆና እንደመቆየቷ ሁሉ፥ ከምድራዊ ወይንም ጠፈራዊ አካላዊያን ትይዩ ንጽረ አካላውያን (ሚሻከላዊያን) በመኖራቸው (እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው) ይህንን ምግብ ተመግበው ወደ ምድራዊ አካላዊ ሕያዋንነት እንደተለወጡ፤ ይህንን የምድራዊ ሕያዋን አመጣጥ - ከሰማያዊ ሕያዋን የጀመረ መሆን አለበት የሚል ፍሬ ሃሳብ፥ በበለጠ ለመፈላሰፍ ይረዳ ዘንድ፥ ተመራማሪዎች፥ የሚከተሉትን እንዲጠይቁ እንተዋቸዋለን።

1) ካሁን በፊት የነበሩ የአንድ የዘር መደብ አካላዊ ሕያዋን በዚህ አለም ላይ የነበሩበት ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር ወይ?
2) በአንድ የተወሰነ ወቅት ዘራቸው የጠፉ እንስሳትና እጽዋት ሁኔታዎች ሲስተካከሉ ተመልሰው አልመጡም ወይ? ለምሳሌ፡- ለወደፊት የምድሪቷ ሁኔታ ለዳይናዞውሮች የሚስማማ ቢሆን ተመልሰው እንዳይፈጠሩ ምን ይከለክላቸዋል?
3) በእርግጥ እኛ የመሬትን ገጽታ ስለለዋወጥን፥ ለግዙፋን እንስሳት የሚስማማ መሬት ጠፍቷል፤ ሆኖም የጥንት ጥቃቅን እንስሳት አሁንም ቢሆን ብቅ እያሉ ነው። ታዲያ ጥቃቅን ሕዋሳት እራሳቸውን በአካላዊነት ቢከስቱ፥ ምግብ ስላገኙና በልተው ስላደጉ ነው እንጂ፥ ሕያውነታቸው ተጠብቆ አካላዊ ያልነበሩበት (በነፍሳቸው ብቻ ወይንም ሰማያዊ ሚሻከላዊ ሆነው የኖሩበት - የሚኖሩበት) ጊዜ አልነበረም (የለም) ወይ?
4) ከመጀመሪያው ምድራዊ አካላዊ ሕያው ቀጥሎ፥ ከሕይወት ሕይወት እንደሚወጣ ሁላችንም በጋራ ተስማምተናል። ምድራዊ አካላዊ ባልሆነ መልካቸው (በሰማያዊነት - ንጽረ አካላዊነት - ሚሻከላዊነት) አሁን ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ቢኖሩ ማን ያውቃል?
5) የእግዚአብሔር ጥበብ በሰው የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ የማይካተት መሆኑን እንመልከት። በአንድ ጠብታ የሕይወት ዘር ውስጥ የተመዘገበው ዝርዝር የአካላዊ ሕያው ጠባይ (genetic code) ሙሉ በሙሉ ቢታወቅና በጽሑፍ ቢሰፍር፤ ይህንንም ጽሑፍ እንደ አንድ ትልቅ የሕንጻ ሥራ እቅድ አድርገን ብንቆጥረው፥ እቅዱ ስላለ ብቻ ሕንጻው ብድግ ብሎ ራሱን ችሎ አይቆምም (እንጨቶች፥ ምስማሮች፥ ሲሚንቶዎች፥ ድንጋዮች... ወዘተ. ከያለበት መጥተው በራሳቸው ሥፍራቸውን ይዘው ሕንጻውን አይገነቡትም)። ታዲያ በአንድ ህዋስ ውስጥ የሚገኙ ሞሌኩሎች እንዴት ነው የተገነቡት?

6) የተለያዩ የውሻ ዘሮችን እያዳቀሉ ከአራት መቶ በላይ የውሻ አይነቶችን መፍጠር ተችሏል። ነገር ግን ንጥረ ነገሮችን አገናኝቶ (ሞሌኩሎችንም አያይዞ) ሕይወትን መመሥረት የሚችል ማነው?
7) የፍጥረታት መባዛት በፍጥረት ሳይሆን በዝግመተ ለውጥ ብቻ ነው ካልን፥ በሕያው ዘር ውስጥ የሚገኙ ንጥረ ነገሮች እንዴት ነው ሕዋሳትን ለመገንባት የበቁት? እንዴት በራሳቸው ቦታ ቦታቸውን ይዘው - ራሳቸውን ችለው ሕዋሳት ለመሆን ቻሉ? ይህ ሁሉ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መገለጽ አለበት እንጂ፡- ይህንን ችግኝ ተክዬ፥ ውሃ አጠጥቼ አሳደግሁት ቢባል - ለመሆኑ ችግኙን ማን ሰጠህ? መባሉ አይቀርም።
8) በባዮሎጂ እና በኬሚስትሪ መራቀቅ የተደረሰበት ከፍተኛው ደረጃ የተፈጥሮን ምሥጢር - የአካላዊ ሕያው ጠባይ (genetic code) ገላልጦታል ቢባል፤ እነኛ የዲ ኤን ኤ ኬሚካሎች (DNA – deoxyribonucleic acid) እንዴት ተገኙ? ተገኝተውስ በእውነት እነርሱ የሚሠሩት ሥራ የነርሱ ብቻ ነው ወይ? ማነው ይህንን በደንብ እንኳን ያልተረዳነውን የተፈጥሮ ምስጢር መጻፍ የሚችል።
9) ተፈጥሮን በስነ ስርአትና በሕግ የሚያስተዳድር እግዚአብሔር አምላካችን ሰማያዊ ሕያዋንን የሚፈጥርበት - ለጠፈር ሁሉ የሚያገለግል አንድ ማእከላዊ ሥፍራ ቢኖር ማን ያውቃል?
10) እግዚአብሔር አምላካችን ሰማያዊ ሕያዋንን ምድራዊ አካላዊ ባልሆነ መልካቸው (በሰማያዊነት - ንጽረ አካላዊነት - ሚሻክላዊነት) ፈጥሮ (እየፈጠረ)፥ በጠፈር ሁሉ - በሌሎች ምድሮችም በአካላዊ ሕያውነት እንዲኖሩ ያደረገ (የሚያደርግ) ቢሆን፥ ይህንን ማን ያውቃል?

ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎችም ጥያቄዎች፥ በወቅቱ የደረስንበት ሳይንስ አይመልስም። ይልቁንም ሳይንስና እምነትን (ሃይማኖትን) ያደናገረና ያከራከረ የጊዜ ተመን ጉዳይ ስለሆነ፥ ይህንን ጉዳይ በጽንኦት እንመልከታለን።

## **<u>ፍጥረት በሰማያዊ ጊዜ</u>**

በሃይማኖትና በሳይንስ አደናጋሪ የሆነው የጊዜ ተመን ጉዳይ ነው። ከእሁድ እስከ አርብ ያሉትን ስድስት ቀናት "አንዴ" ብንል፤ ወይንም አስራ አምስት ቢሊዮን ዓመታትን "አንዴ" ብንል ሁለቱም ወደ ምድራዊ አመለካከታችን ይመልሱናል። በሂሳብ ስልት

ያሰላነው እንደሆነ ግን፥ እነኛ ስድስት ቀናት “አንዴ” መሆናቸው ነው ከአስራ አምስት ቢሊዮን ዓመታት ትይዩ ሲቀመጡ።

ፍጥረት “አንዴ” ቢሆን፥ ዝግመተ ለውጥም የማያቋርጥ ክስተት ቢሆን፥ ይህ አጨቃጫቂ ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም፥ እንዲህ ከታሰበ፥ ጠፈር ከተዘረጋ አስራ አምስት ቢሊዮን ዓመታት ሆኖታል ብለው የሚያምኑ ካሉ፥ እነኚህም ሰዎች በእግዚአብሔር ፈጣሪነት የሚያምኑ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ለብዙ ቢሊዮን ዓመታት ሲፈጥር ቆይቷል ማለትን ውድቅ ያደርገዋልና ነው።

ፍጥረት ከውጪ (ከማይታየው አለም - ከሰማይ) መሆኑን ለመግለጽ ስንል፥ ከምድራዊ አካላውያን የረቀቀ ሰማያዊ አካል - ንጽረ አካል፥ ሚሻክል መኖር አለበት አልን። ፍጥረት “በሰማያዊ ጊዜ” መሆኑን ለመግለጽ፡- “ሰማያዊ ጊዜ”ን እንዴት እንግለጸው?

ሰው በአንድ ወቅት ተወልዶ በአንድ ወቅት ስለሚሞት፥ ያለፈውን እንጂ የወደፊቱን “አያስታውስም”። በአካላዊው አለም ለሚኖር ሰው ጊዜ ወደፊት ብቻ ነው የሚነጉደው፤ የጊዜ ወደፊት ብቻ መሆን ነው ሰውን የሚያስረጀው። ለሰው ጊዜ ባንድ አቅጣጫ ወደፊት ብቻ ስለሚያመራ፥ በአንድ ወቅት አንድ ድርጊት ተፈጸመ ሲባል፥ ምንጊዜም ሰው ከራሱ የጊዜ አቆጣጠር ጋር ነው የሚያዛምደው።

ለእግዚአብሔር ፍጥረት “አንዴ” ነው ስንል ግን፥ ለየት ባለ መልኩ ነው። ይኸውም፥ እግዚአብሔር ያለፈውንም የወደፊቱንም ባንዴ ማወቅ ስለሚችል፥ ለርሱ ያለፈውም የወደፊቱም “አንዴ” ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት፥ የወደፊቱን ልክ እንዳለፈ አድርጎ “አይቶታል - ያያል” ማለት ነው።

ጠፈር በሚሰበሰብበት ወቅትም ቢሆን፥ ጊዜ ወደፊት ብቻ ይጓዛል። ጠፈር ሲሰበሰብ ወደኋላ ይመለሳል ብንል፥ ካሁን በፊት የተሠራው ሁሉ እንዳልተሠራ ይሆናል ማለታችን ነው። ጠፈር በሚሰበሰብበት ጊዜም ቢሆን አካል ከቀላሉ ወደ ዝብርቅርቁ (entropy) እያመራ ይቀጥላል እንጂ፥ የተሰበረ ብርጭቆ ተመልሶ እንደሚገጣጠም አይነት አይሆንም (እስቲፈን ሃውኪንግ 2005 ገጽ 116)።

ወደፊት ብቻ ለሚጓዝ አካላዊ ሰው ስለ ጊዜ የሚኖረው ትርጉም ውሱን ቢሆንም፥ ሌላ ትርጉም የለውም ማለት አይደለም። ጊዜ ወደፊት ብቻ እንጂ ወደኋላ አይሄድም ስንል፥ ይህንን ማገናዘቢያችን አካላዊ አለማችን ነው። በአካላዊው አለም መገኘትና መጥፋት ስላለ ነው የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ እንዲህ እኛ እንደምናስበው የሆነው። ለምሳሌ ወጣት ደበበ በዚህ አለም ተገኝቶ መጥፋቱን ለመግለጽ የግድ የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ ያስፈልጋል። ታዲያ፥ ልክ በሰው አይምሮ በሚቀረጸው የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ

መሠረት ከተመራን፥ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በተለያዩ ጊዜያት ፈጠረ ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ አናገኝም።

ነገር ግን፥ መገኘትና መጥፋት በሌለበት ዘላለማዊ - የፈጣሪ - የእግዚአብሔር እና የዘለአለማዊ ሕያዋን - የመላእክት - ሰማያዊ አለም ውስጥ፥ የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ እኛ እንደምናውቀው ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔርም አልፋና ኦሜጋ ስለሆነ፥ ለኛ ወደፊትና ወደኋላ የምንለው ለርሱ እና እርሱ ለሚኖርበት አለም እንደዛ አይሆንም።

ለኛ ጊዜ በጫፉ ላይ የጦር ምልክት እንዳለው ቀጥ ያለ መስመር ቢሆን፥ ለእግዚአብሔር ግን፥ ጊዜ እንደ አንድ ነጥብ ይቆጠራል፤ በዛ ነጥብ ውስጥ ያለ ሁሉም ነገር ባንድ ጊዜ (ወዲያውኑ) ታዋቂ ይሆናልና።

ታዲያ፥ የወደፊቱን የሚያይ አምላካችን የነገውን ትላንት መፍጠር ያቅተዋል? ከዛሬ አምስት መቶ ሚሊዮን ዓመታት በኋላ ያለውንም ባንድ ጊዜ መፍጠር ወይንም ፈጥሮ ለእኛ እስኪታይ ድረስ ማቆየት ያቅተዋል?

ስለጊዜ በተሰጠው የሁለት አለም ትርጉም መሠረት፥ ይህ የዛሬውና ለኛ የሚታየው አለም (ጠፈር - ሰማይ) የተፈጠረው የዛሬ አምስት ሺህ ዓመት ወይንም የዛሬ አስራ አምስት ቢሊዎን ዓመት ቢሆንም፥ ይህ የሚያጣላና የሚያጨቃጭቅ ሊሆን አይገባም።

"እግዚአብሔርም አለ፡- ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ ታውጣ..." ሲል፥ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ያመለክታል። "እንዲሁም ሆነ፤" ሲል ደግሞ የድርጊቱን መፈጸም ያመለክታል። ከርሱ ትእዛዝ ቀጥሎ፥ ትእዛዙ እስኪፈጸም ድረስ አንድ ቀን ነው የፈጀው፥ ወይንስ አንድ ሴኮንድ? ጊዜ የማይመከተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ - ዛሬ ተፈጽሞ የምናየውን፥ ወደፊት የሚፈጸመውንም ሁሉ እናስበው። "በዛን ጊዜ" ሆነ ቢባል፥ ለእግዚአብሔር "ያን ጊዜ" (በዛች ቀንና ሰዓት??) የተፈጸመ ቢሆን፥ ለኛ ግን በእርግጥ የምናየውና የምናውቀው (ሊገባንም የሚችለው) በሚሊዮን ዓመታት ውስጥ የተፈጸመውን ብቻ ነው የሚሆን። የጊዜ ትርጉሙ ያለፈውን የዛሬውንና የወደፊቱን ሲያመለክት ብቻ ነው ለኛ የሚገባን። ለምሳሌ፡- "ታውጣ" የሚለው ቃል ከአንድ ከተወሰነ ወቅት ጀምሮ የወደፊቱን የሚያመለክት ሲሆን ነው ሊገባን የሚችለው።

"....ያ መልካም እንደሆነ "**አየ**"..." ሲል፥ ያየውን የፈቃዱን መፈጸም በጊዜ ውስጥ ሁሉ (በብዙሚሊዮን ዓመታት ውስጥ) መሆኑን ይሆናል የሚያመለክተው። እግዚአብሔር ከዛሬ አስር ቢሊዎን ዓመታት በኋላ የሚፈጥረውን ሁሉ ባንድ ጊዜ ማየት ይችላል ብለን የምናምን ብንሆን፥ "**አየ**" ሲል በኛ ሰዓት አቆጣጠር አለመሆኑ ይገባናል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ - "እንዲሁም ሆነ፤" ሲል፥ የሰውን

ትላንትና፥ የሰውን ዛሬ እና የሰውን የወደፊቱን ሁሉ እንደሚያጠቃልል አድርገን ልንወስደው እንችላለን። የሚከተለውን ምሳሌ በአጽንኦት እንመልከት፡-

ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባቷ ከኢያቄምና ከእናቷ ከሐና መወለዷን ሰው ሊያውቅ የሚችለው ስትወለድና ከተወለደች በኋላ ነው። ከዛ በፊት ተወልዳለች ቢባል ግን፥ ይህ ለሰው አይገባም። ማርያም መወለዷን ከዛሬ ብዙ ቢሊዮን ዓመታት በፊት እግዚአብሔር የፈቀደውና የሚያውቀው ከሆነ፥ ለምንድነው እኛ ለኛ የሚገባንን፡- የማርያምን የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት መወለድ ብቻ የምናስተውል? የሃይማኖት ሊቃውንት ግን፥ ተራ ከሆኑ ንግግሮች አልፈው ስለሚሄዱ፥ ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በፊት - ምድሪቷም ሳትፈጠር፥ በእግዚአብሔር ታስባ "ቆይታለች" ይላሉ።

ግን "ቆይታ" ለእግዚአብሔር ምኑ ነው? እኛ ማርያምን ፈጠራት ስንል አካላዊ ሆና ስትወለድ ነው? ገና አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከመሥራታቸው በፊት የሚሆነውን ሁሉ አውቆ እግዚአብሔር ማርያምን "አስቧታል" ስንል፥ በዚያን ጊዜ (ከጊዜ በፊት) እግዚአብሔር ማርያምን "ካሰባት" እንዳይፈጥራት ምን አገደው?

በእርግጥ እኛ የቋንቋ ችግር አለብን። እኛ ፍጥረት የምንለው በአካል መገለጥን (መከሰትን) ብቻ ነው። ፍጥረት የምንለው ይህንን ብቻ ሲሆን ይገባናል፤ ከዛ ውጪ አይገባንም። ትንቢት ተናጋሪዎች ስለወደፊቱ ቁልጭ አድርገው የሚተነብዩት፥ ለነርሱ የወደፊቱን እንዳለፈ አድርገው ስለሚያዩት ከሆነ፥ ለእኛ ትንቢት ለነርሱ ያለፈውን አስታውሶ መናገር ይሆናል ማለት ነው።

ለምሳሌ፡- ንጉሥ ዳዊት ማርያም ከመወለዷ ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት ለማወቅ እንደቻለ[48] አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይጠቁማሉ (መዝ. 87፡5፥ መዝ. 131፡13-14)።

እግዚአብሔር "እኛ"ንም[49] እንደ ማርያም አስቀድሞ "አስቦን" ይሆናል፤ ካሰበንም በርሱ ጊዜ (የዛሬ አስር፥ መቶ ወይንም ሺህ ቢሊዮን ዓመት..) ፈጥሮናል፤ ብለን ብንፈላሰፍ፥ እግዚአብሔር "እኛ"ን የቀድሞ ዘመን ሰዎች፥ "እኛ"ን የዛሬ ዘመን ሰዎች፥ "እኛ"ን የወደፊት ዘመን ሰዎች አስቀድሞ ፈጥሯል ብንል፥ እስካሁን ከተነጋገርንበት ሃሳብ አይወጣም።

---

48 ዳዊት ስለ ጽዮን ሲናገር ማርያምን ኢያመለከትም ብሎ ከመደምደም አስቀድሞ፥ ስለዚህ ጉዳይ ተብራርቶ የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ ይጠቅማል (ለምሳሌ፡- አንዱአለም ዳግማዊ (መምህር)፡ 1988" ወ.ዘ.ተ.።

49 የማርያም ድምሯ "ከእኛ" ከሰዎች ጋር ቢሆንም፥ እርሷን ምንጊዜም ልዩ የሚያደርጋት ባሕሪ አላት።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ ይላል። እግዚአብሔር ሰውን በመንፈሱ እንጂ በአካሉ አይመስለውም። ስለዚህ ሰውም ሲፈጠር አምላኩን መስሎ ከሆነ፥ ያ በመጀመሪያ የተፈጠረ ሰው አካላዊ ሊሆን አይችልም።

ታዲያ ምግብ በልቶ አካላዊ ያልሆነ፥ ያ እግዚአብሔርን የመሰለ ሰው ከተፈጠረ ቆይቷል ማለት ነው። ምን ያህል ጊዜ ቆየ? አንድ ቀንም ሊሆን ይችላል። ሚሊዮን ወይም ቢሊዎን ዓመትም ሊሆን ይችላል...።

ብዙውን ጊዜ የእውቀት ጎዳናን የሚከፍት፥ ብሩህና ደስ የሚል ሃሳብ እውነት ሆኖ ይገኛልና፤ ይህንን ጉዳይ - እግዚአብሔር ሰውን አስቀድሞ በመንፈስ እንደፈጠረው የሚያመላክቱ፥ ጥልቅ ሃሳቦችን እንድንፈላሰፍባቸው የሚረዱንን የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመልከታቸው፤ የምድሪቱንና የሰማዩን በማመሳሰልም ቢሆን፥ በማቀራረብም ቢሆን - በሥጋዊ አንጎላችንም ቢሆን - በልባችን ወይም ከአይምሮአችን ውጪ - ዘለአለማዊ ከሆነው ኃይል ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በመፈለግ ደረጃ እናስበው (በትርጉም ሳንጣላ)።

- "እኔ **<u>በስውር</u>** በተሠራሁ ጊዜ፥ **<u>አካሌም በምድር ታች</u>** በተሠራሁ ጊዜ፥ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሠወሩም። **<u>ያልተሠራ</u>** አካሌን አይኖችህ አዩኝ፤ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ እንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።" መዝ. 139፡15-16
- "**<u>ዓለም ሳይፈጠር</u>** በፊት ቅዱሳን፥ ንጹሓንና ያለ ነውር በፍቅር ያደርገን ዘንድ ለእርሱ መረጠን። በኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ፈቃዱ ለእርሱ ልጆች ልንሆን **<u>አስቀድሞ</u>** ወሰነን።" ኤፌ. 1፡ 4-5
- "አቤቱ፥ አንተ ለትውልድ ሁሉ መጠጊያ ሆንህልን። ተራሮች ሳይወለዱ፥ ምድርም አለምም ሳይሠሩ፥ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ድረስ አንተ ነህ። ሰውን ወደ ኃሳር አትመልስም፤ የሰው ልጅ ሆይ፥ ተመለሱ ትላለህ፤ ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፥ እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና። ዘመኖች በፊትህ የተናቁ ይሆናሉ፤ በማለዳም እንደ ሣር ያልፋል። " መዝ. 90 (89)፡1 - 6
- "የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው፤ የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘለአለም ነው።" መዝ. 118፡160

## ማጠቃለያ

ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ የነበረውን ሁኔታ በግምት እንጂ፥ በተጨባጭ ሳይንሳዊ ማስረጃ እንዲህ ነበር ብሎ መቶ በመቶ ማረጋገጥ አይቻልም። ሆኖም፥ ለችሎታችን ወሰን እና መጠን እንደአለው በማመን፥ እስካሁን የተነጋገርንባቸውን ሁሉ በሚከተለው እናገባድዳለን።

- ከሁሉ አስቀድሞ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ተስተካክሎ የተቀመጠ፥ የጊዜ ቆጠራን የማይመለከተውን የፍጥረት ቅደም ተከተል፡- ከመጀመሪያው ብርሃን፥ እስከ ባህር አካላዊ ሕያዋን፥ እስከ የየብስ አካላዊ ሕያዋንና እስከ ሰው መፈጠር ድረስ ያለውን  እናስበው። በእውነት ይህ፥ በሳይንሳዊ እውቀት ተመራምረን ከደረስንባቸው የፍጥረት ቅደም ተከተል ጋር ምንም ተቃርኖ እንደሌለው ይመለከቷል።
- በመቀጠልም፥ በስነ ምድር (ጂኦሎጂ) የምናገናዝብበት የስነ ምድራዊ ዘመናት አቆጣጠር (Geologic Time Scale) ሳይንሳዊ ማስረጃ የሚገኝለት ስለሆነ፥ ከሞላ ጎደል ትክክል ነው። በዚህ የስነ ምድር ዘመናት አኳያ የተዘረዘሩት መሪ የእንስሳት ቅሬተ አካሎችም በአይን የሚታይና የሚጨበጠውን ያህል ትክክል ነው።
- በስነ ምድር ዘመናት ውስጥ የተጠቀሱት እጽዋትና እንስሳት ሁሉ በቅደም ተከተል በአይነትና በብዛት መበራከታቸው ከመዋለድ ጋር ፍጥረት መኖሩንም ያረጋግጣል። ሆኖም ይህ ጊዜ (የስነ ምድራዊ ዘመናት አቆጣጠር) የሚያመለክተው ፍጥረታት በአካል የተገኙበትን (የተከሰቱበትን) ጊዜ ነው እንጂ፥ የተፈጠሩበትን ጊዜ አይደለም።
- በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱትን መሪ ሃሳቦች ብናጠቃልላቸውና እንደገና ብንከልሳቸው፥ እግዚአብሔር ፍጥረታትን “በስድስት ቀናት” ፈጥሮ አገባደደ ከሚለው እምነታችን ጋር ምንም ቅራኔ አያመጣም።
- ከአካላዊው ፍጥረት አስቀድሞ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረው በስድስት “ቀናት” ቢሆን፥ በሳይንስና በሃይማኖት የተፈጠረ ቅራኔ በዚህ “ቀናት” በተባለ አንድ ቃል ብቻ አጨቃጫቂ መሆን የለበትም። ምክንያቱም፥ እግዚአብሔር ሁሉንም - እጽዋትና እንስሳትን፥ ሰውንም በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠራቸው (በአንድ ሰኮንድ ውስጥ ፈጠራቸው፥ ወይንም በብዙ ቢሊዮን ዓመታት ውስጥ ፈጠራቸው) ስንል፥ ለሟች ሰው ይህ የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ፡- ቀንና ሌሊት፥ ክረምትና በጋ ሲፈራረቁበት፥ የግድ ጊዜ መቁጠሪያ ስላስፈለገው ነው እንጂ፥ ዘለአለማዊ ለሆነ እግዚአብሔር ቀን መቁጠር ፍቺ የለውም።

- ምን ጊዜም አካልና ጊዜ አይነጣጠሉም። ስለዚህ የጊዜ ነገር ሳይጨመርበት ሰው አይገባውም። የጊዜ ነገር ሳይጨመርበት የሚገባው አካላዊ ያልሆነ ብቻ ነው።
- “በመጀመሪያ” እግዚአብሔር ለማንኛውም በምድር ላይ ላለ ሕይወት በተለያየ ጊዜ (ወይም አንድ ጊዜ ብቻ) በሰማይ ነፍስ እየፈጠረ (ወይንም ፈጥሮ) ዘለአለማዊ ሕያው እያደረገ (ወይም አድርጎ) ወደ ምድር ላካቸው ቢባል ይህ ከሃይማኖታችን (ከግል እምነታችን) ጋርም፥ ምንም የማይቃረን ቢመስለንም/ባይመስለንም፥ ይህ ነው ትክክል ሳንል፥ ሊሆን ይችል ይሆናል ብለን፥ በጎን እያሰብን መቆየቱ አይጎዳም። ይህ እምነታችን አይደለም፤ እምነታችን የግላችን ነውና።
- ስለ ሰማያዊ አለም ማሰብ ደስ ይላል። ደስ ስለሚልና ብዙ ሲታሰብበት አንዳንድ ጽንሰ ሃሳቦች ይገለጣሉ፤ እምነትም በቀጥተኛ ሃሳቦች ብዛትና ጥራት ይጠናከራል። እንዲሁም፥ የሰብአዊነት የእውቀቱ እድገት ወደ ፍጹማዊነት እንደማያደርሰው በመገንዘብ፥ ትሁታን ሆነን እርስ በርሳችን ብንማማር፥ መንፈሳዊነታችንን ብናሳድግ እና፥ ለሰው በጎ የሆነውን ሁሉ እያሰብን ብንቆይ ደስ ይላል።
- ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ምንም - ምንም ነገር ሊኖር ስለማይችል፥ ሁሉም ነገር - የረከሰውም መንፈስ ቢሆን የመኖሩ ሕልውና ካለ እግዚአብሔር ፈቃድ አልተገኘምና፤ ሁላችንም በመንፈስ እየተመራን እዚህ ደረስን።
- አሁንም መገናኛ ቋንቋችን መንፈስ እየመራን ነው ከምድራዊነታችን ባሻገር የማይታየውን ለማየት የሞከርን። ሁለቱ አለማት የሚገናኙበት (የሚተዋወቁበት) ጊዜው ሲቃረብ ይሆናል፥ እውቀትና እምነት (ሳይንስና ሃይማኖት) አንድ የሚሆኑት።
- ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬና ለወደፊትም፥ የዳርዊን አይነት ያልሆነ ዝግመተ ለውጥ በዘአካላት ላይ እየተካሄደ ነው ያለው። ይህም ለውጥ የማያቋርጥ በመሆኑ፥ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ፥ ዘአካላት ከተፈጠሩ ጀምሮ፥ እየተባዙ፥ በጥራትም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል። ሆኖም፥ ዘአካላት በአካላዊ መልካቸው (ቁመናቸው) እና ጠባያቸው ያን ያህል መሻሻል ያገኙት በዝግመታዊ ለውጥ ቢሆንም፥ ይህ ከፍጥረት ቀጥሎ የሚመጣ፥ በምድር ለመቆየትና ለመበራከት አስፈላጊ የሆነ የፍጥረት ሌላ ተቀጥላ ሕግ ነው (የእግዚአብሔር ፈቃድ)። እናትና አባት ልጆች ወልደው ልጆቻቸውን ያሳድጓቸዋል እንጂ፥ አንዴ ወልደናል ብለው

አይተውአቸውም። እግዚአብሔርም ይፈጥርና በዝግመተ ለውጥ ያሳድጋል፥ እንጂ እንዲሁ አይተውም።

- አንዳንድ እንስሳት በሰውነታቸው ጥንካሬ የደፋርነት ጠባይ ቢኖራቸው፤ ይህ በውስጣቸው በበራሂአቸው (gene) ውስጥ የምድራዊነታቸው "ወሳኝ" ጠባይ ሆኖ ለዚህ በቅተዋል።
- ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ የሰው ልጅም የሚሠራው ሥራ ሁሉ በአንድ በተወሰነ መንገድ በበራሂው ውስጥ እየተመዘገበና ለልጅ ልጅ እየተላለፈ ነው በምድራዊነቱ ሕልውናው የተጠበቀለት፤ እጅግም እየተሻሻለ፥ ሳይንቲስት - ፈላስፋ ለመባል የበቃ።
- መንፈስ የጎደላቸው[50] የአካላውያን የመኖር ሕልውና፡- በምድር ላይ እኔና የእኔ ዘር ብቻ ይኑርበት በሚል ጠባይ የተመሠረተ የምድራዊነት ፈሊጥ ስለሆነ፥ እርስ በርስ ሲጠቃቁ ቆይተዋል። ግን እኛ ሰዎች በመንፈሳችን ሰማያዊ ጠባይ ወርሰናልና፥ ብንጠቃቃም እስካሁን አልጠፋንም፤ ተመስገን።
- ለወደፊት፥ የሰው ዘር በአይምሮው ነቅቶ፥ ብዙ ነገር ሲያውቅ፥ ባለ አንድ መልክ ይሆናል (በአካል በመንፈስም)። የዚያን ጊዜ፥ ሳይንሳዊ እውቀቱም፥ መንፈሳዊ እውቀቱም አንድ ወጥ - አንድ አይነት (የፈጠረውን እግዚአብሔርን የሚያመለክት) ይሆናል።
- ለወደፊት፥ አንዱ ሰው ሌላው እንደሚፈልገው ይሆንለታል። የዛን ጊዜ ሉላዊ ሰብአዊ አንድነት ይፈጠራል።

---

[50] መንፈስ የጎደላቸው ስንል፥ እንስሳትን እና የእንስሳ ጠባይ ያላቸውን ሰዎችንም ጭምር ነው። ሰማያዊ - መንፈሳዊ ጠባዩን ትቶ፥ በምድራዊነቱ ብቻ የሚኖር፥ ስግብግብ፥ ክፉ፥ ጸበኛ፥ ዘረኛ የሆነ ሰው ቢኖር፥ እርሱን መንፈስ እንደጎደለው መቁጠር ይቻላል።

# ምዕራፍ ስምንት

## ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና

ሰዎች ብዙ ይሰማሉ፥ ብዙ ያነባሉ፥ ብዙ ይማራሉ፥ ብዙም ያውቃሉ፤ ግን አንዳንድ ጊዜ ረጋ ብሎ፥ በአይምሮ የሚገቡትን ሃሳቦች (የሚታወቁትን የማይታወቁትንም) ሁሉ፥ መከለስና፥ እያሰላሰሉ መፈላሰፍ ለአንዳንድ እውነቶች ፍንጭ የሰጥ ይሆናል። ለምሳሌ፡- ሁሉም ነገር ከሁሉም ነገር ጋር ቢያንስ በአንድ፥ አለዚያም በሁለትና ከዚያም በላይ መያያዙ አይቀርምና፤ በአካላውያንና አካላዊ ባልሆኑትም መካከል መያያዝ ሊኖር ይችላል ብለን ብናስብ፥ ይህ ከሚያውቁት ተነስቶ ወደማያውቁት አለም መግባት ይሆናል።

እኛ ሰዎች በአካል ብቻ ሳይሆን፥ በባህርይ፥ በሥራችንና በታሪካችን እንመሳሰላለን፤ ሁላችንም በዝምድና የተሳሰርን፥ በሥጋም በመንፈስም "አንድ" ነን። ዝምድናችን እርስ በርስ ብቻ ሳይሆን፥ ከምድራችን ጋርም ነው። ምድራችንም ከሌሎች እርሷን ከሚመስሏት የጸሐይ ጭፍሮች (planets) ጋር ትዛመዳለች፤ ጸሐይም ከከዋክብት ጋር ዝምድና አላት፤ ከዋክብትም እርስ በርስ በዝምድና የተሳሰሩ ናቸው። የባህር አውሎ ነፋስ (hurricane) ቅርጽ እንኳን ከአገረ ከዋክብት (galaxie) ቅርጽ ጋር መመሳሰሉ፥ በምድር የሚፈጸም እንቅስቃሴ በጠፈር ሁሉ ሊኖር እንደሚችል፤ ይህም የጠፈር አካላት ሁሉ በባህሪያቸው እንደሚመሳሰሉ ነው የሚጠቁመው።

ሰውና ኮከብ፥ እንዲሁም ሰውና ጨረቃ ይያያዛሉ። ጨረቃ በመሬት ዙሪያ ስትዞር የስበቷ ኃይል በመሬት ላይ በሚንሳፈፍ ውሃ (ሃይቅ፥ ባህር ወይም ወንዝ) ላይ ሞገዶችን እንደሚፈጥርና እንደሚያንቀሳቅስ (እንደሚያናውጥ) ይታወቃል። ታዲያ፥ ከጨረቃ ወደ መሬት የሚደርስ ኃይል የመሬትን ውሃ የሚያናውጥ ከሆነ፥ በሰው ውስጥ ያለ ውሃ ከጨረቃ የስበት ኃይል ትንሽም ቢሆን ሊደርሰውና ሊናወጥ ይችላል። በርቀት የሚዳከም ቢሆንም፥ የጠፈር አካላትን ሁሉ የሚያያይዝ ኃይል መኖር አለበት። ይህም ኃይል (ትንሽም ቢሆን) ለግለሰቦች ይደርሳቸዋል።

ሁላችንም ከአፈርና ከድንጋዩ፥ ከውሃው፥ ከአየሩ፥ ከሳርና ቅጠሉ፥ ከእንስሳት (ነፍስ ካላቸውም ከሌላቸውም) ጋር የምንዛመድ መሆናችን ነው። በአካል የሚቀራረቡ

ሁሉ በመንፈሳቸውም የዛን ያህል ተቀራራቢዎች ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ የአንድ አባትና እናት ልጆች በአካል የመመሳሰላቸውን ያህል በመንፈስም ይቀራረባሉ። በተለይ መንታዎች በተለያየ አገር ቢኖሩ እንኳን አንድ አይነት ጠባይና ስሜት እንደሚኖራቸው፣ የሚሠሩት ሥራ እና የሚያጋጥማቸው ዕድል ሁሉ ተመሳሳይ እንደሚሆን በተለያዩ ጥናቶች ታዋቂ ሆኗል። እንዲሁም፣ በአንድ የዘር መደብ የሚገኝ የሰው ዘር (ነጭ፣ ቢጫና ጥቁር)፣ በሥጋም በመንፈስም የሚቀራረቡት ተገናኝተው አብረው ስለኖሩ፣ የሚሠሩት ሥራ እና የሚያጋጥማቸው ዕድል ሁሉ ተመሳሳይ ይሆናል። ለዚህም ነው የሰው ዘር (ነጭ፣ ቢጫና ጥቁር) የተባለ እንጂ፣ በሰው ዘር (ነጭ፣ ቢጫና ጥቁር) ውስጥ ልዩነቶች ቢኖሩ፣ ያንን እንደ ዘር መቁጠር፣ ኢሳይንሳዊ ከመሆኑም በላይ፣ ጠባብነት ነው።

የሰው ንቃተ ሕሊና ከጠፈር ሁሉ ጋር የታያያዘ ከሆነ፣ የአንድ ሰው አንጎልም ከሌላው አንጎል ጋር በቅርብ እንደሚገናኝ ነው የሚጠቁመው። ከአንድ ግለሰብ አይምሮ የሚመነጭ የኃይል ሞገድ ወደሌላው ይሄዳል። ሰዎች አብረው ሲኖሩ፣ የማይዛመዱም ቢሆኑ፣ አንዱ ሌላውን የሚመስለው በአስተሳሰቡ፣ በንግግሩና በስሜቱ ብቻ ሳይሆን፣ በቁመናውና በመልኩም ጭምር እንደሆነ በህብረት ከሚኖሩ ሰዎች በቀላሉ መመልከት ይቻላል።

ከዚህና ከዚያ ብንበተን፣ የሚያዛምደን ሃረጋችን - ምድራዊነታችን አይለቀንም። አዎ! ሁላችንም ከዚችው ምድር በአካል ተገኘን፤ ሁላችን ይህቺን ምድር ተመገብናት፤ በንጥረ ነገሮቿ ተገነባን፤ ባንድ ላይ እንርመሰመሳለን፤ ሰውና ውሻ አብሮ ይኖራል፤ ድመቶች፣ ግመሎች፣ ፈረሶች፣ አህዮች፣ ዝሆኖችም ከሰው ጋር አብረው ይኖራሉ። ምድራዊነት ያጠጋጋቸው በጎች፣ ፍየሎች፣ በሬዎች፣ ዶሮዎች..ወዘተ. እየተራቡና ሰውን እየቀለቡ አንድ ላይ ይኖራሉ።

የሰው አይምሮ ከራሱና ለራሱ ብቻ አይኖርም፤ ለዘመዶችና ለወገኖች ሁሉ ያስባል፤ ይጨነቃል። በዚህ ምክንያት፣ ራሱን ችሎና በራሱ ተጠናቆ ለብቻው እንደማይኖር ይታወቃል።

የሰው አይምሮ ዝግ አይደለም፤ ለጠፈር ሁሉ ክፍት ነው። አይምሮ በጠፈር ውስጥ ከሚገኙ ኃይላት ጋር (እንደየቅርበታቸውና እንደየርቀታቸው) የተወሰኑ ግንኙነት የሚያደርግ ከሆነ፣ አይምሮን ለጋራ ጥቅም እንዲያስብ የሚገፋፋ ኃይልም ይኖራል። ለዚህም ይሆናል የሰው ልጅ በደረቅ አይኑ ሊያይ ከሚችለው አልፎ የጠፈርን ጥልቀቱን ለመመርመር የበቃው። ይህ የሰው ልጅ ችሎታ ለወደፊት ጠፈርን እና የሰውን አይምሮ የበለጠ ያቀራርበዋል፤ በአካላዊነትም ሆነ በመንፈሳዊነት

እየተጠቀመ፥ ከዘመኑ የጠፈር መንኮራኩር በሚፈጥን “ሁኔታ” ጠፈርን ይመላለስበታል (አገሩ ያደርገዋል?)።

ከአንድ ግለሰብ አይምሮ የሚመነጭ ሃሳብ ወደ “ኃይል” ተለውጦ ወደሌላ ተቀባይና መላሽ ሥፍራ የሚሄድ ከሆነ፥ የሰው አይምሮ በድምጽ ሞገድ በጆሮ ከሚገባው፥ በአይን ብሌንም ከሚገባው ጨረር አስቀድሞ ሊያውቅ ይችላል ማለት ነው (ይሆን?)። በጠፈራዊ አካላት መካከል ያ<u>ሉ</u> ሥፍራ ሁሉ ጭራሽ ባዶ ካልሆነ፥ በአካላት ላይ ምን አይነት ተጽእኖ ይኖረዋል?

ለጥያቄዎቻችን ሁሉ መልስ ስንሻ ወደ የግል ንቃተ ሕሊና (conciousness) መለስ ማለታችን አይቀርም። በአይምሮ ውስጥ ያሉ ህዋሶች ባለ ሕይወት የሆኑ አካላውያን ናቸውና፤ የሰውም ንቃተ ሕሊና ከነኚህ ህዋሶች (gray matter) መኖር ጋር የተያያዘ ነው የሚሆን። እነኚህን የአንጎል ህዋሶች ከሌሎች ህዋሶች እጅግ የተለዩ የሚያደርጋቸው የኬሚካልና የሌሎችም፥ ባዮሎጂካልና ፊዚካል ጠባዮች እንዳሏቸው እናውቃለን።

ነገር ግን፥ ከአይምሮ የሚመነጭ ሃሳብ - ንቃተ ሕሊና (conciousness) ራሱ አካላዊ አይደለም (ወይም አካላዊ ያልሆነ ብቻ አይደለም)። ታዲያ እንዴት ነው አካላዊ ያልሆነው (ወይም አካላዊ ብቻ ያልሆነው) ንቃተ ሕሊና አካላዊ ከሆነው (የአንጎል ህዋስ) የሚፈልቀው? በማለት ፈላስፋዎችም ይጠይቃሉ።

ፒተር ረስል የተባለ ፊዚስት ፈላስፋ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፡-

“We do not need to explain how unconceous matter generates immaterial conceousness, because conceousness may not be entirely immaterial, and matter may not be entirely unconceous” Ervin Lazio 2006 p. 53

ሲተረጎም፡- “ቁስ አካላዊ ያልሆነው ንቃተ ሕሊና፥ ንቃተ ሕሊና ከሌለው ቁስ አካላዊ ነገር እንዴት እንደሚመነጭ ማወቅ አይኖርብንም፤ ምክንያቱም፥ ንቃተ ሕሊና ፍጹም ቁስ አካላዊ ያልሆነ፤ ቁስ አካላውያንም ፈጽሞ ንቃተ ሕሊና የሌላቸው ስለመሆናቸው አናውቅምና።”

ፊዚስቱ ፒተር ረስል ቁስ አካላውያን ፈጽሞ ንቃተ ሕሊና የሌላቸው ስለመሆናቸው አናውቅም እንዲል ያደረገው፥ በቁስ አካላት ውስጥ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የተወሰኑ ሕግጋትን ተከትለው፤ ሁኔታዎች ሲለወጡም ልክ

አይምሮ እንዳለው ሁሉ፥ እንቅስቃሴያቸውን እያስተካከሉም እንደሆነ በመመልከት ነው።[51]

በእውነቶቻቸው መካከል ሌላም እውነት ቢኖር እያልን፥ በትምህርት ቤት ከሚሰጠው ትምህርት ወጣ እያልን እርስ በርስ ብንማማርም መልካም ስለሆነ፥ በዚሁ እንቀጥል።

## አንዳችነት (ሃሳባዊ ፍልስፍና)

ጠፈር በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘረጋ በእግዚአብሔር ቃል ይሰበሰብ ይሆናል። ግን የወደፊቱን የጠፈር ቁስ አካላት ሁሉ በሃሳባችን ወደ "ብርቅነት" ስንመልሳቸው፥ ያ ሁሉ ቁስ አካል የት ይሄዳል? የሚለው ጥያቄ ለማንኛችንም እንዳልተመለሰ ግልጽ ነበር። ስለወደፊቱ ጠፈር ማሰቡ ደስ ካለን እንዲሁ እየተፈላሰፍን ትንሽ እንቆይ።

ከመጨረሻው የጠፈር መሰብሰብ በፊት፥ የጠፈር አካላት ሲናወጡ፥ አንዱ ባንዱ ላይ እየተደራረበ፥ የአንዳንድ ከዋክብት ፕላኔቶች እና ጨረቃዎች ይዘት ይጨምራል። ይህ ክስተት ካሁን በፊት የነበረ፥ አሁንም ያለ ነው፤ በየጊዜው በምድራችን ላይ የሚወድቁ የጠፈር ደንጋዮች (meteorites) የምድራችንን ይዘት እንደሚጨምሩ ሁሉ።

ሆኖም፥ ከመጨረሻው የጠፈር መሰብሰብ በፊት፥ የጠፈር አካላት በከፍተኛ ደረጃ የሚናወጡበት ጊዜ ሲመጣ፥ ከፍተኛ የጠፈር መተረማመስ ስለሚኖር፥ አንዱ ባንዱ ላይ መደራረብና መጨፈላለቅም ይባባሳል፤ በዚህ ምክንያት የአንዳንድ ጠፈር አካላት (አስቀድመው የከሰሙ ከዋክብት) ይዘት ይጨምራል። ስለዚህ፥ የታላቁን መሰብሰብ የመጨረሻ ውጤት በሚከተሉት ሦስት መልኮች ማየት ይቻላል፡-

- ታናናሽ ከዋክብት የሚከስሙበትና በአካላዊነታቸው ሳይለወጡ የሚቆዩበት፤ እንዲሁም እርስ በርስ ተገጣጥመው የሚገዝፉበት።
- ታላላቅ ከዋክብት የሚከስሙበትና ከግዙፍ አካላዊነት ወደ ረቂቅ አካላዊነት (ኒውትሮንነት) የሚለወጡበት።
- ታላላቅ ከዋክብት የሚከስሙበትና ከግዙፍ አካላዊነት ወደ ረቂቅ አካላዊነት (ኒውትሮንነት) ከተለወጡ በኋላ፥ ወደ ኃይል ብቻ የሚለወጡበት።

ሁሉ ነገር ወደ ኃይል የማይለወጥ ከሆነ፥ ወደ ኃይል የማይለወጡ አካላት ሁሉ እርስ በርስ ሲጠጋጉ (ሲጋጩ ወይንም ሲደራረቡ) ታላቅ የአካል ክምችት

[51] በተለይ፥ ማዕድናት ልክ ነፍስ እንዳለው እርስ በርስ ግጥምጥም ብለው (በሙቀት፥ በግፊትና በጊዜ) የተለያዩ አለቶችን ይፈጥራሉ።

መፈጠሩ አይቀርም። ይህ ታላቅ የአካል ክምችት የብርቅነት ተቃራኒ ስለሆነና፤ በየጊዜው እያደገ እጅግ ትልቅ ሊሆን እንደሚችል ለመግለጽ “አንዳችነት” በሚል መጠሪያ እንጠቀማለን።

የ”አንዳችነት” ወደ ኃይል ብቻ መለወጥ ምንም ዋስትና የለውምና፤ ግዙፋን አካላት ወደ ኃይል ካልተለወጡ፥ በ”አንዳችነት” ረግተው ይቀራሉ ማለት ነው (ለጊዜውም ቢሆን)።

ጠፈር እየሰፋ እንደሚሄድ አንዳንድ መረጃዎች ቢጠቁሙም፥ አንዳንድ አገረ ከዋክብት እየተቀራረቡ መምጣታቸውንም የሚጠቁም ምልክት ታይቷል። ለምሳሌ፥ አንድሮሜዳ የተባለው አገረ ከዋክብት የኛን አገረ ከዋክብት በታላቅ ፍጥነት እየተጠጋ ነው። ሁለቱ አገረ ከዋክብት አንድ ላይ ሲሆኑ፥ ምን አይነት መተረማመስ እንደሚፈጠር - ምን አይነት አንዳችነት እንደሚከተል መገመቱም ካቅም በላይ ይሆናል። የጠፈር መተረማመስ ምን ጊዜም ያለ ቢሆንም፥ በጊዜ ውስጥ (ለወደፊት) ካሁን በፊት ከነበረው መተረማመስ የሚበልጥ እንደሚሆን ነው የምንገምተው።

በአጠቃላይ፥ በጠፈር ውስጥ በሚካሄድ ክስተት አንጻር፥ ከትንሽ አካል እስከ ትልቁ ድረስ፥ ሁሉም ደረጃ በደረጃ፥ በውስጡ አበይት ለውጦችን የማስተናገድ ግዴታ ውስጥ ይገባል። ለምሳሌ፥ ሁለት ታላላቅ አገረ ከዋክብት ሲጠጋጉ፥ የከዋክብት፥ የፕላኔቶችና የጨረቃዎች የዙረት ፍጥነት ከፍ ይላል። ቀናት፥ ወራትና ዓመታት ያጥራሉ፤ ሕያዋን ሁሉ ቶሎ ቶሎ እያረጁ ቶሎ ቶሎ ይሞታሉ..ወዘተ..።

በአንዳችነት የተገነቡ ከዋክብት ከጊዜ ብዛት ታላላቅ መሬቶችን ቢፈጥሩ፥ ከነኚያም መሬቶች ግዙፋን አካላዊ ሕያዋን ቢፈጠሩ ማን ያውቃል።

በማንኛውም አቅጣጫ ሲታሰብ፥ ፍጹማዊ እውነትን የሚያስረግጥ መደምደሚያ ማግኘት ያቅታል። ለምሳሌ፥ ስበትና መጠጋጋት ቢቀጥል በመጨረሻ አንድ አንዳችነት እና ከዛም ቀጥሎ አንድ ብርቅነት ነው የሚቀሩው? ወይንስ ብዙ አንዳችነቶችና ብዙ ብርቅነቶች ይኖራሉ? አካል የተባለ ፈጽሞ ይጠፋል?

## የጠፈር ብሌኖች (ሃሳባዊ ፍልስፍና)

የአይኖቻችን ሥራ ድንቅ ነው። የብርሃን ጨረሮች በሁለት ትናንሽ ብሌኖች ሰርገው ይገቡና፥ ከአይን ጀርባ ከሚገኝ ስሜት ሰጪ ሰሌዳ ያርፋሉ። በጠባቡ መንገድ አልፈው የአንጎል ህዋሶችን ይቀሰቅሳሉ። የሰው አይን ሊያይ ከሚችለው ሁሉ፥ ለአካላዊ አለም (ጠፈር) ትርጉም በመስጠት እኛን ወደሰፊው ባህረ ሃሳብ ይከቱናል።

ወደ አይኖቻችን የሚገቡ ብርሃኖች ሁሉ አቅጣጫቸው አንድ ነው፤ አንዴ ከገቡ አይመለሱም። ጽልመተ ጥልቀቶችንም እንደ ጠፈር አይኖች ብንመስላቸው፥ በጠፈር ውስጥ ወደ ጠፈራዊው ጥልቀት የሚገቡ ብርሃኖችም አቅጣጫቸው አንድ ነው፤ አንዴ ከገቡ አይመለሱም።

ታዲያ፥ በጽልመተ ጥልቀት አማካኝነት ብርሃን ከአንድ ጠፈር ወደ ሌላ ጠፈር ከሄደ፥ በጽልመተ ጥልቀት የተሰበሰቡ የብርሃን ጨረሮችም የሚሄዱበት ልዩ አለም ካለ፥ ጽልመተ ጥልቀቶችም እንደ ጠፈር የአይን ብሌኖች መሆናቸው ነው።

በጽልመተ ጥልቀት የተሰበሰቡ የብርሃን ጨረሮች ሄደው የሚያርፉበትም ሥፍራ ቢኖር፥ ያንንም ሥፍራ፥ ከሰው አይን ጀርባ እንደሚገኝ ስሜት ሰጪ ሰሌዳ መቁጠር ቢቻል፥ ብርሃኖች በዓይኖቻችን ብሌኖች ሰርገው በአንጎል ሰሌዳ ላይ አርፈው፥ የአንጎል ህዋሶችን ቀስቅሰው፥ ስለሚታየው አካላዊው ዓለም ትርጉም እንደሚሰጡ ሁሉ፥ ብርሃኖች በጠፈር አይኖች (ጽልመተ ጥልቀቶች) ሰርገው ሲገቡ፥ እነርሱም የሚቀሰቅሱት የስሜት ህዋስ በጠፈር ውስጥ ሁሉ ይኖር ይሆናል (ማን ያውቃል?)።

ወደ አይን የሚገቡ ብርሃኖች ሁሉ የሚያርፉበት የአይምሮ ሰሌዳ እንደሚኖር ሁሉ፥ በጽልመተ ጥልቀት ለሚሰርግ ብርሃንም ትርጉም የሚሰጥ የጠፈር ሰሌዳ ቢኖር፥ ይህ የጠፈር ሰሌዳ፥ ለጠፈር ግንዛቤን - ንቃተ ሕሊናን የሚሰጥ ሆነ ማለት ነው (ይሆን?)።

ጽልመተ ጥልቀቶችን እንደ ጠፈር ብሌኖች (ወይም አይኖች) ብንመስላቸውና፥ ከዚህ በምድር የተሠራው ሁሉ በጠፈር ሰሌዳ በዝርዝር ይጻፍ ይሆናል ብንል፥ ይህ በሃይማኖት ከምናምነው ጋር "መዛመዱ" ነው።

ጠፈር ዝግ ከሆነ፥ በአለም ላይ የተንጸባረቀ የብርሃን ጨረር ሁሉ የትም እንደማያመልጥ፤ እንዲሁም ሥራችን ሁሉ በአንድ እኛ በማናውቀው ሥፍራ እንደሚመዘገብ ማመሳሰላችን ነው።

ጠፈራዊ ቁስ አካላትን የሚያንቀሳቅሱ የጠፈር ኃይላት፥ ካለ ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና በአካላዊ ትርምስ ብቻ ከዚህ እንዳልደረሱ፥ ካለ ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና የትም አይደርሱ። በሰው የአይን ብሌን የሚገባ ብርሃን፥ በትንሹም ቢሆን ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊናን ይሰርጻልና፤ ውሱን ከሆኑ አስተሳሰቦች ከፍ ከፍ እያሉ፥ በመንፈስ አርቅቆ መሄድንም ሰው ሁሉ መለማመድ ይቻላል።

## ***ብቸኝነት የለም***

ሁሉን በቁጥጥሩ ማድረግ ስለሚችል ስለ እግዚአብሔር ነቃ ብለን ብናስብ፥ የኛ ንቃተ ሕሊና፥ መጀመሪያ በምድራችን ቀጥሎም ወደ ሌሎች ጠፈራዊ ምድሮች ይዛመታል። ካሰብንበት፥ የማንደርስበት ሥፍራ አይኖርም።

በዚህ ሰፊና ግዙፍ ጠፈር ውስጥ ፍጥረት የተጀመረው እኛ ከምናውቀው ምድር ብቻ መሆን አለመሆኑን አናውቅም። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ፈጠረ ስንል፥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በዚህ ምድር ላይ ብቻ መፍጠሩን አናወቅም።

ከዚህ ምድር በስተቀር ስንት የሰው ልጅ (ወይንም የሰው ልጅን የመሰለ ፍጡር) ሊኖርበት የሚችልበት ምድር መኖር አለመኖሩን አናውቅም። በቁጥር አንድ ሚሊዮን ወይም ከዛም በላይ የሚሆኑ አለማት ውስጥ፥ የሰው ልጅ (ወይንም የሰው ልጅን የመሰለ ፍጡር) የሚኖርበት አለም ቢኖር፥ እኛ ምንም የምናውቀው ነገር የለም።

እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው ብለን ካመንን፥ የጠፈርን ግዙፍነት እየተመለከትን፥ እግዚአብሔር ኃያልነቱን በዚህች በኛ ታናሽ ምድር ላይ ብቻ ወስኗል ብሎ ከማመን ይልቅ፥ ኢያሌ አካላዊ ሕያዋንን በጠፈር ሁሉ ፈጥሯል ብሎ ማመን ይቀላል።

በምድራችን ንጥረ ነገር የበዛው ምድሪቱ ቀስ በቀስ ስለቀዘቀዘችና ለተለያዩ ንጥረ ነገሮች መፈጠር አመቺ ሁኔታዎች ስላጋጠሟት ከሆነ፥ በጠፈር ውስጥም ይህን እድል የሚያገኙ ሌሎች ፕላኔቶች እንዳይኖሩ ምንም የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም። ታዲያ፥ ከነዚህም ሥፍራዎች ከመሬት የተሻለ ለሰው ልጅ መኖሪያ የተስማማ፥ እንደ ገነት እጅግ ጥሩ ሥፍራ ሊኖር ይችላል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሳይንቲስቶች አንዳንድ ፍንጭ ለማግኘት ሲሉ ብዙ ምርምር አካሂደዋል።

በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ማስረጃ ባይገኝም፥ በጠፈር ውስጥ ኢያሌ የኛን ምድር የመሳሰሉ የሕያዋን መኖሪያ ሥፍራዎች (መሬቶች - ምድሮች) ስለመኖራቸው እንደሚከተሉት መላምቶች ያሉ ከያለበት እየተሰነዘሩ ናቸው (Laszlo Ervin, 1986, p.46)።

- ከአንድ ሺህ ከዋክብት መካከል፥ አንዲት ኮከብ እንኳን በዙሪያዋ የምትዞር ቢያንስ አንድ ፕላኔት አታጣም። ይህቺን ኮከብና ፕላኔት የሚመሳስሉ አንድ ሺህ ቢኖሩ፥ ከነኚህ ከሺዎቹ በአንዷ ዙሪያ እንኳን ቢሆን አየር አይታጣም።

- ከነኚህ ባለ አየር ፕላኔቶች መካከል፥ ከሺዎቹ በአንዷ ዙሪያ፥ እንደ ምድራችን ለሕይወት ተስማሚ የሚሆን ሙቀት፥ ኬሚካል፥ ውሃ....ወዘተ. አይታጣም።
- በዚህ አይነት ሲታሰብ፥ በጠፈር ውስጥ ከመቶ ሚሊዮን በላይ ምድራችንን የመሳሰሉ የሕያዋን መኖሪያ ሥፍራዎች (መሬቶች) ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል።
- በጠፈር ውስጥ፥ ፕላኔት ካሏቸው ከዋክብት መካከል ከመቶ እጅ በአምስቱ (5%) ምድራችንን የመሳሰሉ የሕያዋን መኖሪያ ሥፍራዎች እንደሚኖሩ ይገመታል። በዚሁ ግምት መሠረት፥ በጠፈር ውስጥ መቶ ሚሊዮን ብቻ ሳይሆን፥ መቶ ቢሊዎን መሬትን የመሳሰሉ የሕያዋን መኖሪያ ሥፍራዎች እንደሚኖሩ ይገመታል።
- የተጠቀሱት ቁጥሮች በአዎንታዊ አስተሳሰብ ተጽንኦ (ነገር በማጋነን) ምክንያት ከፍ ቢሉም፥ በአንጻሩ በአሉታዊ አስተሳሰብ ተጽንኦ ምክንያት ዝቅ ይላሉ እንጂ፥ በጠፈር ውስጥ አያሌ ምድራችንን የመሳሰሉ የሕያዋን መኖሪያ ሥፍራዎች መኖራቸው ከጥርጣሬ ውጪ ነው።

የፍጥረት ሁሉ እርስ በርስ መተሳሰር በአካል ብቻ ቢሆን ኖሮ ሕሊናዊነት አይኖርም ነበረ፤ ማስታወስና መርሳት፥ መውደድና መጥላት፥ መደሰትና ማዘን..አይኖርም ነበረ።

በአካላዊነት ብቻ ሲታይ ነው ብቸኝነት የሚኖረው፤ ብቸኛን አካል ከሌላ ብቸኛ አካል ጋር ሌላ አካላዊ የሆነ ነገር ሊያስተሳስረው አይችልም። የፍጥረት ሁሉ እርስ በርስ መተሳሰር በአካል ብቻ ቢሆን ኖሮ ከብቸኝነት መላቀቅ አይቻልም ነበር። ነገር ግን በውስጡ መንፈስ ያለው አካላዊ ሕያው ብቸኝነት የለበትም። ብቸኝነት ከሌለ፥ መረዳዳትና መተሳሰብም ይኖራል።

ታዲያ፥ በዚህ አንጻር ስናየው፡- በምድራዊነታችን ስቃይ ሲበዛብን - ለኛ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላ ፍጡራን ተንከባካቢ መንፈስ (ሰማያዊ ኃይላት - መላእክት..) እንዲኖር እግዚአብሔር ፈቀደ ብንል፥ ይህንን ጉዳይ ካጠቃላይ የጠፈር አካላዊ ሕያዋን ሁሉ ሕልውና አንጻር መመልከት ይቻላል። በኛ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን፥ መኖር ካለብን፥ እንኖር ዘንድ ብቸኝነት የለብንም።

በጠፈር ያለ አካል ሁሉ ሕሊናዊ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፥ እንደ ምንም (ዜሮ) ይቆጠራል። በጠፈር ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ፥ ሕሊናዊ ትርጉም እየሰጠን እና በአይምሮአችን እያነላን ነው መኖሩንም ለማወቅ የበቃን። መኖራችን በሕሊናዊነት ለጠፈር መኖር ሕሊናዊ ትርጉም እንድንሰጥ ስለሆነ፥ በሕሊናዊነታችን

ጠፈርን የዘረጋ አምላካችን መኖሩን እናረጋግጣለን፤ የኛም በዚህች ሶላር ሲስተምና በኛ አገረ ኮከብ ውስጥ መገኘት ለዚሁ ይሆናል።

ታዲያ፥ እግዚአብሔር በቢሊዎኖች የሚቆጠሩ አገረ ከዋክብትን የፈጠረ፥ ለኛ ብቻ ብሎ ላይሆን ይችላል። ሌሎች በቢሊዎኖች (በሚሊዎኖች ወይም በሺዎች) የሚቆጠሩ መሬቶችና እንደ ሰው የመሳሰሉ ፍጥረቶች፥ እንዲሁም ሰብአዊ መሰል ንቃተ ሕሊናዎች ይኖሩ ይሆናል።

በጠፈር ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር፥ ከራሱ ውጪ በጠፈር ውስጥ በተፈጸሙ ሌሎች ሁኔታዎች ይገለጻል። ስለዚህ፥ በጠፈር ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ አንዱ የሌላውን መኖር ያሳውቃልና፤ ሁላችንም አብረን አለን።

አንዱ ሌላውን ይገልጸዋል። ስለዚህ፥ በጠፈር ውስጥ ሌሎች "ብዙ ነገሮች ቢገቡ"፥ የእኛም መኖራችን የበለጠ ታዋቂ ይሆናል፤ እንዲሁም ከጠፈር ውስጥ ሌሎች "ብዙ ነገሮች ቢቀነሱ" የኛም የመኖራችን መታወቅ ይቀንሳል ማለት ነው። ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና በብቸኝነት ስለማያድግ፥ የእያንዳንዱ ሰው ጠፈራዊ ሕብረተሰብአዊ ግንዛቤ አስፈልጓል።

በሃይማኖት ከሰማያዊ መላእክት ጋር አንድ ሕብረተሰብ መመሥረት እና አብሮ መኖር ከዚህ የተለየ አይደለም። በተለይ እኛ ኦርቶዶክሶች (ካቶሊኮችም)፥ በአካላዊ ሕያውነት ብንታይም፥ እራሳችንን በአካላዊ ሕያውነት ከማይታዩት - ከመላእክት ጋር አብረን እንደምንኖር አድርገን ነው የምንቆጥረው። መላእክት ከጎናችን አሉ ብለን እናምናለን። በተለይም፥ የምንወዳት እናታችን ማርያም በአካል ባናያትም፥ ከኛ አትለይም እያልን፥ ሙጭጭ ብለናል (ይህ መጽሐፍ ይመስክር)። ይህንን ጠፈራዊ ሁለንተናዊ የአብሮነት መንፈስ የሚነጥቀን ማነው?

እስከካሁን በተነጋገርነውም መሠረት፥ በጠፈር የሚኖሩ ሰማያዊ ምድራዊ ሕያዋን ሁሉ በአንድ ጠፈራዊ ሕሊና መገናኘታቸው አይቀርም። ስለዚህ በጠፈር ሁሉ ብቸኝነት የለም ካልን፥ የሰው ሁሉ አይምሮ "መገናኘቱ" አይቀርም። አንድ ግለሰብ (በአይምሮው - በአስተሳሰቡ ሁሉ) የአለም ሕብረተሰብ ወይንም የሰብአዊነት አንድ አካሉ ነው። ግለሰብ ሙሉ ሰው የሚሆነው ከተጠቀሰው ሕብረተሰብ (ወይም ሰብአዊነት) ጋር በአንድነት ሲሆን (ሲኖር፥ ሲያስብ፥ ሲሠራ..ወዘተ) ነው። አለበለዚያ ለብቻው ከሆነ ጎዶሎ ነው።

በዘረኛነት ወይንም በሌሎች ጥላቻዎች በመቀስቀስ፥ ግለሰብን (በትንሹ)፥ ሕብረተሰብንም (በትልቁ) ገለል ማድረግ፥ ጎዶሎነትን ማባባስ ነው።

በአስተሳሰባችን አንዱን ሕዝብ ከሌላው እንለያለን፤ እርስ በርስ ለመጣላት፥ ለመገዳደል እንዲያመችን ብለን የሚያቀራርበንን (የሚያመሳስለንን፥ የሚያፋቅረንን)

ሃሳብ እየጣልን፥ የሚያራርቀንን (የሚለያየንን፥ የሚያጣላንን) ሃሳብ እናነግሳለን። ግን ይህንን ማድረጋችን፥ ለጠፈራዊ የሕሊና እድገት እንቅፋት መሆኑን አልተገነዘብነውም።

## የመንፈስ ሕያውነት

መንፈሳዊነት መረጋጋትን ያመጣል፤ ሆኖም፥ አካላዊው ሰው ሲሞት እና በሰማያዊነት ፍጹም መንፈሳዊ ሕልውናው ሲጸና - የሰው እውነተኛው ማንነቱ ሲረጋገጥ፤ የዛን ጊዜ ይሆናል፥ የበለጠ ረጋ ብሎ በፍጹም ነፃነት እና በፍጹም ሰላም መኖር የሚቻል።

"እስከ ዘለአለሙ መጥፋት" የሚለው ሃሳብ ደስ አይልም። ብዙውን ጊዜ ደስ የማይል ሃሳብ ውሸት ነው። በጠፈር ብሌኖች (ጽልመተ ጥልቀቶች) የሚገቡት የብርሃን ጨረሮች እስከዘለአለሙ እንደማይጠፉ ሁሉ፥ እኛም አንጠፋም፤ እኛ ከመንፈስ የተፈጠርን ስለሆንን፥ መንፈስም ዘላለማዊ ሕያው ነውና።

ከጽልመተ ጥልቀት ክልል ጀምሮ ወደ ማእከላዊው ነጥብ (ብርቅነት) የሚገባ ሁሉ ወደ "ሌላኛው አለም" ቢሸጋገር እንጂ፥ መጥፋት እንደሌለበት ሁሉ፥ ከመጣንበት ከወደ "ሌላኛው አለም" እንመለሳለን የሚለው ሃሳብ ታላቅ ተስፋን ያዘለ በመሆኑ፥ በሃሳባችን ብናጸድቀው፥ ፍጹማዊ እውነት ከመሆን እንዳያመልጥ ማድረጋችን ስለሆነ፥ የኛም ይህንን ማሰብ ጥሩ ነው፤ ደስታንም ይሰጠናል።

ጠፈርን በሚከተሉት በሁለት አይነት መልኩ መመልከት ይቻላል።

- በአካላዊነቱ፡- ካለ ምንም የራሱ ንቃተ ሕሊና የሚኖር ግዑዝ ነገር - በውስጡና ከውጪ የሚመጡ አካላዊ ትእዛዛትን ብቻ ተከትሎ የሚንቀሳቀስ፤
- በመንፈሳዊነቱ፡- ንቃተ ሕሊና ያለው፥ አካባቢውን የሚገነዘብ፥ የመጣበትንና የሚሄድበትንም አውቆ ለፈጣሪው የሚታዘዝ እና የሚሰግድ።

ጠፈርን በአካላዊነቱ ስንመለከተው፥ በሥፍራዎች ሁሉ የሚተረማመስ ነው። ቀና ብለን በደረቅ አይናችን እንኳን ቢሆን ጨረቃን ብንመለከት፥ ምን ያህል በጠፈር ደንጋዮች እንደተደበደበች መገመት አያቅተንም።

በጠፈር ውስጥ ብዙ የከዋክብት ሽርፍራፊዎችና የጠፈር አቧራዎች ይተረማመሳሉ፤ ሆኖም ሕይወት በጠፈር ውስጥ ሁሉ ቢኖር፥ ይህ ሕይወት በቁስ አካላት መደብደብ የሚያስከትለውን ጉዳትና፥ ከተለያዩ ጥቃቶች ማምለጫ መንገዱንም ስለሚያውቅ፥ የግድ የነቃ መሆን አለበት።

አካላዊ ሕያው ሁሉ በዘለአለማዊነት ሕያው ሆኖ መኖር እንዴት እንደሚቻል የሚያሳውቅ የተፈጥሮ ጠባይ አለው። የሚታወቅ ነገር ካለ ምክንያት አይታወቅም። የሚታወቅ ነገር ያለ ነው፤ ባይኖር ኖሮ እንዴት ሊታወቅ ቻለ? አንዴ ታውቆ በመታወቁ ሕያው ሆኖ የሚኖር ነገር በተለያየ መንገድ ይገለጣል። ስለዚህ፥ የጠፈር ሕያዋንም በሚከተሉት በሁለት መልኮች ይታወቃሉ፡-

- በአካላዊነት ሲገለጡ (እንደ ሰው)፤
- በፍጽምተ አካላዊነት እንደ መላእክት ሲገለጡ።

የጠፈር ሕያዋን በንጽረ አካላዊነት ህልውናቸው በመንፈስ ሕያው ሆነው ሲኖሩ፥ በአካላዊነት የሚገለጡትም በጠፈር ውስጥ ሕያዋን ሆነው ሲኖሩ፥ ሁሉም በአንድ የተወሰነ ስርዓት መሆን አለበት። በጠፈር ያለ ሁሉ በአንድ የተወሰነ መንገድ ይዛመዳል። ስለዚህ የጠፈርም ሕያዋን (እኛን ጨምሮ) ሁሉም በሚከተሉት በሁለት መንገድ (ሕግጋት) ይኖራሉ፡-

- እንደ አጠቃላይ የጠፈር ሁኔታ (ሕግጋት)፤
- እንደሚኖሩበት አካባቢ ሁኔታ (ሕግጋት)።

ጠፈርን ስናስተውል፥ ሕይወት ሊኖር በሚችልበት ሥፍራ ሁሉ የተጠቀሱት ሁለት አይነት ሕግጋት ይኖራሉ። ስለዚህ የሁሉም የሕይወታቸው ስርዓት ተመሳሳይ (በተወሰኑ ሕግጋት የሚዛመድ) መሆን አለበት።

በአካላዊው ጠፈር ያለነውን ሁላችንንም የሚያያይዘን (የሚያዛምደን) የጠፈር ኃይል አንድ ነው። ስለዚህ በጠፈር የሚኖሩ ሁሉ ሕይወታቸው ከኛ ምድር (አለም) ጋር የሚመሳሰል መሆን አለበት። እሩቅ ለሩቅ ስለሆነ፥ የዛኑ ያህል በመካከላችን ልዩነት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ርቀት የማይወስነው የመንፈስ ኃይል ያገናኘናል። ስለሆነም፥ እኛ ከነሱ እንማራለን፤ እነርሱም ከኛ ይማራሉ። አለማዊነታቸውንና መንፈሳዊነታቸውን፥ ሃዘንና ደስታቸውን፥ ጸሎታቸውንና ቅዳሴያቸውን፥ ዘፈንና መዝሙራቸውን፥ ሁሉንም - ሁሉንም በስሜቶቻችን እንሰማለን (ሰምተናል)።

አንድ እጅግ ትልቅ የሆነ ኮከብ ሲሞት፥ የራሱ የሆነ የስበት አድማስ መሥርቶ፥ ባጠገቡ የሚያልፈውን ሁሉ በስበቱ (በውስጣዊ ኃይሉ) እንደሚውጥ፤ ይህም የስበት አድማስ ከመጀመሪያው ኮከብ ስፋት ብዙ ጊዜ እንደሚበልጥ፥ የሰዎችም አካል ቢሞትና ብስብስ ቢል፥ አፈር ቢበላውና ጭራሽ ጥፍት ቢልም፥ ሥጋው ቢጠፋ፥ የመንፈሱ ኃይል አይጠፋም። ሰው ቢሞትም፥ ሳይሞት አብሮት የነበረው ኃይል ፈጽሞ ጥፍት አይልም። ስለዚህ፥ ከሚሞቱ (ከሚከስሙ) ከዋክብት ውስጥ ያለ ኃይል የሚያካልለው፥ የነርሱው ከነርሱ የመነጨ ኃይል፥ አድማስ እጅግ ሰፊ እንደሚሆን

ሁሉ፥ አንድ ሰውም በሚሞትበት ወቅት፥ የመንፈሱ ኃይል የመሬትን ዙሪያ ቢያካልል አያስደንቅም።

የሞቱ ሰዎች ሁሉ ሙተዋልና የሉም የሚሉ አሉ። በእውነት ጥፍት ቢሉ ለምን ከአይምሮአችን አይጠፉም? የመኖራቸውስ ሁኔታ በየጊዜው በሚደርሰን መንፈሳዊ ስሜት የሚከሰት አይደለምን? በጨነቀን ጊዜ፡- እናንት የማናያችሁ ሰዎች እባካችሁ ተመልከቱን፤ ከተቻላችሁ እርዱን ብለን ከልባችን ከጠየቅናቸው፥ ከነኛ ከምንወዳቸው ሰዎች የመንፈስ እርዳታ እናገኛለን (አግኝተናልም)። አንዳንድ ጊዜም ሳንጠይቃቸው ይደርሱልናል።

የኛ የምድራዊ አካላውያን መኖር በሰማያዊ አለም ለሚኖሩቱ፥ የእነርሱን በመንፈሳዊው (ሰማያዊው) አለም የመኖራቸውን እውነታ በአካላዊ መንገድ ማመሳከሪያ እንደምንሆንላቸው ሁሉ፥  የኛም በአካላዊው አለም የመገኘታችንን እውነታ በመንፈሳዊ መንገድ የሚያጠናክሩልን እነርሱ (በሰማያዊ አለም የሚኖሩቱ) ናቸው። አሉልን (ይኖራሉ)፥ አለንላቸው (እንኖራለን)።

ሰማያዊ ሕያዋን በጊዜ ውስጥ ወደፊትና ወደኋላ የሚመላለሱ ከሆነ፥ አንድ መነሻ ነጥብ (reference point) መኖር አለበት። ለሰማያዊ አለም መነሻቸው ዘላለማዊ (አልፋና ኦሜጋ) የሆነ ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ከሆነ፥ የኛም እራሳችንን ከሰማያዊ ሕያዋን (ከመላእክት) ጋር ማዛመድ ወደ ፈጣሪያችን ያቀርበናል። እንዲሁም፥ ማርያም ማርያም ስንል (ማለታችን) ወደ እናቱ ያስጠጋናል።

በጠፈር ውስጥ ንቃተ ሕሊና ካለ፥ ይህንን እኛ የተገነዘብነውን ሁሉ የሚገነዘቡ ሕያዋን በጠፈር ሁሉ ይኖሩ ይሆናል። ሁላችንም የአንድ ጠፈር አካሎች ነን። አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳል እንደሚባለው፥ በማንኛውም ሥፍራ የሚከናወን ማንኛውም ነገር ሁላችንንም ይመለከታል። ይህንን እኛ የተገነዘብነውን ሁሉ የሚገነዘቡ ኃይላት በጠፈር ሁሉ ካሉ፥ እኛ ለእግዚአብሔር እንደምንሰግድ እነርሱም እንዲሁ ይሰግዳሉ።

“..ይህም በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት[52]  ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።” ፊሊ. 2፡10

በዚህች ምድር እና በጠፈር ውስጥ በጠቅላላ ስነአይምሮአዊ ሕሊና ያለው ሁሉ ይሰግዳል፤ የማይሰግዱ ቢኖሩ እነርሱ “ንቃተ ሕሊና” የሌላቸው ናቸው።

[52] በጠፈር ውስጥ ያሉት ሁሉ ማለትም ሊሆን ይችላል።

"..እነዚህ ዝም ቢሉ ደንጋዮች ይጮሃሉ።" ሉቃ. 19" 40 እንዲል፥ በጠፈር ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ተከትለው ሁሉም ማድረግ ያለባቸውን ያደርጋሉ፤ (የሚዞሩትም፥ የሚወድቁትም...ወዘተ.)።

ለኛ ግን የተለየ ጸጋ ተሰጥቶናልና፤ እግዚአብሔር አብሮን እንደሚሆን ተስፋ ሰጥቶናልና፤ በአምልኮት መሰብሰቢያ ሥፍራዎች ተሰባስበን ስንቀድስ፥ ስንዘምር፥ ስንጸልይ፥ ከምድራዊ ችግሮች ስለምንላቀቅ፥ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል።

"ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ። " ማቴ.18፡20።

እግዚአብሔርን ስናመልከው የእርሱን ዘለአለማዊ ሕልውና መግለጻችን ስለሆነ ደስ ይለዋል፤ እርሱ ደስ ሲለው እኛም ደስ ይለናል። አንድ ላይ መሆን እና በአንድነት መጸለይ መንፈሳዊ እውነታን ያጠናክራል።

በጠፈር ኃይላት እንቅስቃሴ ትርምሱ ሲቀጥል፥
ዘላቂና ቀሪው - አቸነፊውም ንቅት ሲል፥
ሁሉም ለፈጣሪው ሲሰግድ፥ በአምልኮት ሲተባበር፥
የእግዚአብሔርን ኃያልነት ሲመሰክር፥
ይህ ነው ከዘለአለማዊነት ጋር የተጣመረ የሕያውነት ምሥጢር።

ይህ የጠፈር ሕያውነት ምንኛ ረቂቅ ነው፤ ምንኛ ታላቅ ነው፤
የሰበት ክልል - አድማስ - በከዋክብት እና በሰው ዙሪያ ያለው፤
እስቲ ረጋ ብለን እናስተውለው፤
ከኛ ጋር ያለውን ዝምድና እናጥናው።

ከአብራኮቹ አንዱ - የአይን ብሌኑ፥ ጠፈር አይናማ፥
አስተዋይ - ተመልካች፥ የሚያነብ፥ የሚተረጉም፥ ነፍሳማ።
እኛ ስንጠይቅ ጠፈርም ይሰማል፤
ፍላጎት ሲመጣ ከሰው፤
ሁሉም በረድፍ በረድገ ይነጠፋል - ይደረደራል፤
ምን እናድርግ? ምን እንርዳ? ይላል።
በጠፈር ውስጥ ትእዛዝ አክባሪ ሞልቷል፤
ሽር ጉድ ይላል፥ ይተባበራል፤
ባለሟል፥ አስተናጋጅ ሞልቷል፤

እግዚአብሔር የሰውን ክብር ከፍ አድርጎታል፤
ከጠፈር አካላት፥ ከብዛታቸውም ትንሽ ትንሽ ይደርሰናል፤
አለ ሁሉም ሞልቷል፤
የእግዚአብሔር ችሮታ ተትረፍርፏል፤
እድል ፈንታችን ካለንበት ይጠብቀናል፤
ከልብ ሲያለቅሱ እንባ ይፈሳል፤
ለለመነ ይሰጣል፤ በር ላንኳኳ ይከፈታል። (ማቴ. 7፡7)

ስለዚህ፥ እናንት የጠፈር ኃይላት
መላእክትም ብትሆኑ በሰማይ ያላችሁ፥
ሰዎችም ብትሆኑ በሰማያዊነት የነቃችሁ፥
ለጌታ ክርስቶስ የቀረባችሁ፥
እኛም ስለናንተ የተሰማንን እንዳወራንላችሁ፥
እግዚአብሔርን ስትለምኑ ለራሳችሁ፥
ለኛም ጸልዩልን እባካችሁ፥
የጎደለንን  እያያችሁ።
በግልም ሆነ፥ በሕብረተሰብ ደረጃ፥
ሲናጋ ሕልውናችን፥
ሰብእናችን ሲገፈፍ፥
በደል ጭቆና ሲበዛብን፥
እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲሰማልን፥
የማያቋርጠውን እርዳታ እርሱ እንዲያፋጥንልን፤
እኛ ለራሳችን ስንጸልይ፥
እናንተም በጸሎታችሁ ተራዱን።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ፍጥረታችን እና ስደቶቻችን

እስካሁን ከጠፈር ምርምር ወደ ምድራችን ገብተን ስለ አካልና መንፈስ ጉዳይ ስናወሳ እንደቆየን፤ ይህንኑ እጅግ ሰፊ ምርምር ወደኛው ሕብረተሰብ እንመልሰውና መቋጫ እናበጅለት።

ሰብአዊነት በአካላዊነቱም በመንፈሳዊነቱም መድረስ የሚፈልግበት ቦታ ለመድረስ ሲል እንደ ጎርፍ ውሃ ካለማቋረጥ ወደፊት ይገሰግሳል። ይህ ወደፊት መገስገስ በፍጥረታት ሁሉ ያለ ቢሆንም፤ እኛን የሚመለከተው ለየት ይላል። የሰው ድካሙ ሁሉ ወደ ፍጹማዊነቱ ለመጠጋት የሚያደርገው ጥረት ስለሆነ፥ የጉዞአችን አላማ አስቀድመን ወደመጣንበት ለመድረስ ነው። ድሮ በመንፈስ የምንኖር ሰዎች ነበርን፤ በኋላ ሥጋ ለበስን፤ በመጨረሻም ወደ ጥንቱ የመንፈስ ሰው እስክንመለስ ድረስ እንደክማለን።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው። እኛም እርሱን የምንመስለው በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም። አብርሃም ግን ልጁን ለመሰዋት ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ፥ በመንፈሱ አምላኩን እንደሚመስል አረጋግጧል። ማንም ሰው ጥሩው መንፈሱ አምላኩን መምሰሉ፥ የኋላ ኋላ ሰው ሁሉ በጥሩው መንፈሱ እንደሚገናኝ ያሳውቃል።

እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ሲፈጥረው፥ የሰውን መንፈስ ከራሱ መንፈስ ጋር አመሳስሎ ስለሆነ፥ ያ አስቀድሞ በእግዚአብሔር መንፈስ የተፈጠረ የመንፈስ ሰው ፍጹማዊ መሆን አለበት። ሰው ግን ፍጹማዊ እንዳይሆን ምድራዊነት (የሥጋ ነገር) አንቆ ይዞታል። ታዲያ ሰው ሥጋ ከለበሰ በኋላ ያንን እሱኑ ፍጹማዊውን የመንፈስ ሰው እስኪሆን ድረስ፥ ብዙ ውጣ ውረድ ይጠብቀዋል።

እራሳችንን ከዘለአለማዊ ክስተት ገንጥለን መመልከት አንችልም። የአካል መጨረሻ እስኪሆን ድረስ፥ ብቅ ጥልቅ (መፈጠርና መሞት፥ መገኘትና መጥፋት) ምንጊዜም ያለና የሚኖር ነውና፤ የግለሰቦች መሞትና አለመሞት (የብቅ ጥልቅ ምልክት) የማያቋርጥ ክስተት ሆኖ፥ የሰብአዊነትን ታሪክ (በአካልና በመንፈስ) ቁልጭ አደረገው።

በዚችው በምድራችን፥ እንዲሁም በጠፈር ውስጥ፥ ተፈጥሮ በጊዜ ውስጥ አንዴ ሲገኝ አንዴ ጥፍት ሲል እዚህ ደረሰ። ሰብአዊነትም እንደ አይን መርገብገብ ጥፍት ግኝት እያለ ነው ከዚህ የደረሰ።

አንድ በጦርነት ውስጥ ከቤተሰቡ ተለይቶ በጥይት የቆሰለ ሕጻን፥ ከመቁሰሉ የበለጠ ከቤተሰቡ መለየቱ ያስፈራዋል። ለምን በአለም ያሉ ሕጻናትን ሁሉ ጥፍት - ግኝት ማለትን የሚመስል የድብብቆሽ ጨዋታ (hide and seek) ያዘወትራሉ? ግኝት ማለት መገለጥን (ከአካል ጋር መዛመድን)፥ ጥፍት ማለትም በመንፈስ ሆኖ ከአካል መሰወርን ሁለቱም (መገኘትና መጥፋት) ምንጊዜም ባንድነት በተፈጥሮ ውስጥ የተቆራኙ በመሆናቸውና፥ እኛም ሁለቱንም ስለሆንን ይሆናል፥ አንዱ ከሌላው ሲለይ የሚያስፈራን።

በመንፈስ አንዴ የተፈጠረ ሰው ሕያው ሕይወቱ በሥጋ በመወለዱ ምክንያት አይቆራረጥም። በሥጋ ስንወለድ ቀድሞ የነበርን ወደፊትም የምንኖር መሆናችንን፥ ይኸው ቀድሞ የነበረ መንፈሳችን በተለያየ መንገድ ያሳውቀናል።

ብቅ ጥልቅ ከማለታችን ጋር ርቅቅ እያልን ወደፊት መጓዛችን፥ የመጀመሪያ ፍጥረታችንን እስከናገኘው ድረስ ይሆን? ታዲያ፥ ይህንን ቀዳማዊ ፍጥረታችንን ሳናገኝ እንዳንቀር የሚረዳን ማነው? የምድራዊነትስ ሚና የት ድረስ ነው? ወደ ፍጹማዊነት ለመጠጋት በምናደርገው እርምጃ ምድራዊነታችን ወደፊት ያራምደናል ወይ?።

እስቲ የሰውን ልጅ እድገት በተለያየ አቅጣጫ እንመልከት። የፍጥረታት ሁሉ እንቅስቃሴ በተደነገገላቸው የተፈጥሮ ሕግ ከልል ውስጥ (ለሰው የተገለጠውና ያልተገለጠው ሕግ ሁሉ) በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ካለማቋረጥ እንደሚካሄድ ሁሉ፥ የእኛም እስካሁን መቆየት ለአንድ እኛ የማናውቀው፥ እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀው ምክንያት ይሆናል።

ከልጅነት እስከ አካለ መጠን ድረስ ስንጫወት አደግን፤ ትዳር ይዘን ስንኖር ለወሬና ለጨዋታ መድረክ ከፍተን ብዙ ጊዜ እናጠፋለን። ግን ምን ጊዜም ቢሆን አውርተን አውርተን ሲበቃን፥ ሌላ የዛኑ ያህል ያላወራነው - የተደበቀ ወሬ አለ። የትኛው ወሬ ነው ያላወራነው - የተደበቀው፤ እሱንስ የምናወራው መቼ ነው? አንዳንድ ጊዜ ወሬ አውርቶ ከማስረዳት ይልቅ ማልቀስ ይቀላል። ይህች አለም እራሳችንን ለመግለጽ በቂ አይደለችም። ተደብቀናል፤ ተገኝተናል (ሁለቱም ነን)።

አዎ! እህ! አካላዊ ባልነበርንበት ወቅት “ሌላ” ያልገባን ነገር ስለነበረ፥ ያ “ሌላ” የተባለው በደንብ ይገባን ዘንድ (እውቀት?) አካላውያን ሆንን፤ እና ሁሉንም ቁልጭ - ቁልጭ ብሎ ተመለከትን።

“ገና ድሮ - ድሮ” ብለን ወደማይገባን ነገር መለስ ስንል፥
መንፈሳችንም ሲያሳውቀን ማስታወሱን፥
ነበርኩ፤ አሁን አለሁ፤ እያለ ሲያካፍለን ምሥጢሩን፥
ጥንት ያልገባን ነገር ሁሉ አሁን ገብቶን፡-
“እንዲህ እኮ ነበረ..” እንድንል፥
ሁሉ ነገር ፈካ፥ ፈካ ብሎ - ቁልጭ፥ ቁልጭ ብሎ ሲገለጥ በአካል፥
የመንፈስን ነገር ስናመሳስል፥ በጉልህ ከሚታይ - ከአካል።
ሁሉም ከባዶነት ተነስቶ ሲያድግ ሲመነደግ፥
ቆንጆዋ ልጃገረድ አርጅታ ስትሞት፥ ጽጌረዳ ሲጠወልግ፥
በሽታና ጦርነት ሕዝቦችን ሲጠራርግ፥
ያለው ሲጠፋ፥ የሌለው ሲተካ፥
ይህ ጥፍት ግኝት - ይህ ብቅ ጥልቅ፥
ከነፍስ አልባ እስከ ባለ ነፍስ - ከግዙፍ እስከ ረቂቅ።
እንደ ቁጫጭና ዘመሚት ሕይወት ሲፍለቀለቅ፥
ለጊዜው አንድ አለም፥ ግን የማያቋርጥ - የማያልቅ።

## <u>የሰው ፍጥረቱ</u>

የእግዚአብሔር ሥራው በተወሰኑ ሰዎች (ሃይማኖተኞች ወይንም ሳይንቲስቶች) ብቻ ተገልጦ የማይበቃ ስለሆነ፥ ሁላችንም እናስተውልና በበኩላችን የሚሰማንን ካለአንዳች ፍርኃት እንግለጽ።

የሰው እምነት በጥራዝ ነጠቃዊ - ኢስነአመክኖአዊ አስተሳሰቦች በከንቱ እንዳይላላ ለመከላከል ስለ ሰው ፍጥረት በግልጽ ከሚታወቁ ጉዳዮች ተነስተን፥ እጅግ ቅልል ባለ (በተጠቃለለ) መንገድ ለመከታተል፤ ሁሉን ሊያውቅ በሚችል በፈጣሪ አምላካችን አምነን እንነሳ።[53]

[53] “አቤቱ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ ሃሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።” መዝ. ፲፱፡፲፬

ይህ ተመራማሪ አይምሮ አሁንም ቢሆን አዳምና ሔዋን የተባሉት ከየትኛው ወገን ናቸው? ከአውስትራሎፒቴኩስ፥ ከሆሞ ሃቢሊስ፥ ከሆሞ ኢሬክቱስ ወይንስ ከሆሞ ሳፒያን? ብሎ ይጠይቃል። ብዙ እውቀቶችን ታቅፎ ከመቀመጥ፥ ጥቂት እውነቶችን ይዞ መፈላሰፍ ይበልጣልና፤ አንዳንድ የምናውቃቸውን ይዘን ጠለቅ ወዳለ ሃሳብ ለመስመጥ እንድፈር።

በሳይንስ ስለ ሰው አመጣጥ አወቅን የምንለው ሥጋዊነቱን (መልክና ቁመናውን) በተመለከተ ነው። ከአዳምና ሔዋን የተጀመረው የሰው ዘር አመጣጥ በሥጋ ከመሬት አፈር፥ በመንፈስም "አስቀድሞ" ከሌላ ሥፍራ ነው ብንል፥ የሃይማኖት ሊቃውንት፡- ይህ እኮ እኛ የምናውቀው ጉዳይ ነው፤ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? ይላሉ። አዲስ ነገር መፍጠር ሳይሆን፥ አዳምና ሔዋን በመንፈስና በሥጋ መፈጠራቸውን ስናምን፥ ሁለቱ የተለያዩ - የሁለት አለም ጠባያት ባንድ ላይ (ባንድ ጊዜ - ባንዳፍታ) እንደተፈጠሩ አድርገን የምንቆጥር ስለምንኖር፥ "አስቀድሞ" የሚለውን ቃል በማብራራት አንዳንድ ጉዳዮችን ግልጽ ለማድረግ ነው የተነሳነው።

የሰው ዘር (homo sapien - የዘመኑ ሰው) ከቃኤን፥ አቤልና ሴት ጀምሮ፥ በአካላዊነቱ ለተፈጥሮ ሕግ (ምድራዊ) እየተገዛ፥ በመንፈሳዊነቱም ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ የሆኑ (ሰማያዊ) ሁኔታዎችም እየተፈጸሙበት፥ በነኚህ በሁለት ኃይላት መካከል እየተንገዳገደ ሲኖር ቆይቶ (ሲጠፋ - ሲባዛ) ከዚህ ደርሷል።

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ ....።" ዘፍ. 2፡7 በማለት ተነግሮናል። ይህ ጥቅስ በመሬት ያለ አካላዊ ሕያው ሁሉ በእርግጥ በአካሉ አፈር መሆኑን ያመለክታል እንጂ፥ በሕያው ፍጥረቱ አመጣጡን አይገልጽም።

ከብዙ ሺህ ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ፥ ክፍለ አህጉራት ግማሽ ፈሳሽ በሆነ የከርሰ ምድር ክበብ ላይ መንቀሳቀስ ሲጀምሩና ውቂያኖስ ሲከፈት፥ ተራሮች ሲገነቡ፥ ሜዳዎችም ሲሰነጠቁ፥ በኃርፍ ሲሸረሸሩና ሸለቆዎች ሲሆኑ፥ በተለያዩ ጊዜያት አካላዊ ሕያዋን ሲበራከቱና ሲያልቁ፥ ምድር በበረዶ ስትሸፈን፥ ስትቀዘቅዝና ስትሞቅ፥ አዳምና ሔዋን በመንፈስ አለመኖራቸውን የሚያውቅ ማነው?

አዳምና ሔዋን በገነት (ኃጢአት ሳይሠሩ በፊት) ምን ያህል ዘመን እንደኖሩ የሚያውቅ ሰው ማነው? እግዚአብሔር አስቀድሞ በአምሳሉ የፈጠራቸውን አዳምና ሔዋንን በገነት ያኖራቸው እንደነበር አወቅን፤ ግን በገነት (ገነት ሰማይ ከሆነ) ምን ያህል ጊዜ እንደኖሩ አይታወቅም። ሥጋዊ ደማዊ ከሆኑ በኋላ ግን፥ የኖሩት ዘመን ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት መሆኑ ተጠቅሷል። ዘፍ. 5፡5

አዳም ከምድር ተፈጠረ ማለት፡- እግዚአብሔር አዳምን ሥጋዊ (አካላዊ) ይሆን ዘንድ ከምድር አፈር ፈጠረው ለማለት ነው። ስለዚህ፥ አዳም ከምድር ተፈጠረ

ሲል፥ እግዚአብሔር አዳምን ሥጋዊ ደማዊ (ምድራዊ) ማድረጉን እንጂ፥ እንዴት አድርጎ እንደፈጠረው አያመለክትም ፡፡

ይህንን ጉዳይ፥ “የሰው ልጅ የጠፋውን በግ ለማዳን መጥቷልና..” ማቴ. 18፡ 11 የሚለው ጥቅስ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘጠና ዘጠኝ የተመሰሉ መላእክትን በሰማይ ትቶ፥ የጠፋውን በግ (አዳምን - የሰውን ዘር) ለማዳን ወደ ምድር ወረደ ሲል፥ የአዳም ምድቡ ከመላእክት ጋር እንደነበረ፥ በመንፈስ የተፈጠረበትም ዘመን በመሬት በሥጋ ከተፈጠረበት ዘመን “አስቀድሞ” እንደነበረ ይጠቁማል፡፡ በምድር ላይ ሕይወት የተጀመረው ከዛሬ ሁለት ሺህ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ቢሆንም አዳምና ሔዋን ከዛ በፊት ተፈጥረዋል ማለት ነው፡፡ ይህንን አባባል በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ጋር እያወዳደርን ጠለቅ ብለን ብንመረምረው ምንም አይነት ቅራኔ አያመጣም፡፡

ከጥንት ጀምሮ የነበረ፥ አሁንም ተወዳዳሪ የማይገኝለት፥ ስለ ሰው ልጅ ታሪክ የሚያወሳ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ እስካሁን አልተገኘም፡፡ በዚህ ቅዱስ መጽሐፍ መሠረት፥ የሰው ልጅ እህል ዘርቶና ከብት አርብቶ መኖር የጀመረው፤ ከአዳምና ሔዋን ልጆች (ከቃየንና አቤል) ጀምሮ መሆኑን እንረዳለን፡፡ “አቤልም በግ ጠባቂ ነበረ፤ ቃየንም ምድርን የሚያርስ ነበረ፡፡” ዘፍ. 4፡2

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የሰው ልጅ ታሪክ ከሆሞ ሳፒያን በፊት ወደነበሩት ሰው መሳይ ፍጡራን አያመለክትም፤ እነርሱ ገበሬዎች አልነበሩምና፡፡ ስለዚህ፥ ቃየንና አቤልን ሆሞ ሳፒያን እንደሆኑ፤ የሰው ዘርም ከአዳምና ሔዋን የቀጠለው በቅርብ ጊዜ - የእርሻና የከብት ርቢ በተጀመረበት ጊዜ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ቃየን ወንድሙን ከገደለ በኋላ፡- “በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ፤ የሚያገኙኝም ሁሉ ይገድሉኛል” ዘፍ.4፡14 ሲል፥ በዘመኑ ብዙ ሕዝቦች እንደነበሩ ስለሚያመለክት፥ ይህ ለብዙ ሰዎች የሚያደናግር ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ የሚገርመው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ይህንን እና የመሳሰሉትን አደናጋሪ ጥቅሶች ይዟል፡፡ ይህም የሚያሳየው፥ እንደ ዘመኑ ደራሲያን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እውነት እንጂ፥ አንባቢ ምን ያስባል የሚል ስጋት እንደሌለበት ነው (ሊገባው የሚችል ሁሉ ይገባዋልና)፡፡

አንዳንድ የሃይማኖት ሰባክያን ግን ከራሳቸው ስነአመክኖአዊ አመለካከት ጋር የሚጋጩውን ሁሉ እየዘለሉ ነው የሚሰብኩት፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፥ የጠቃቀስናቸው አበይት ጉዳዮችን ሁሉ በአጽንኦት ቢከልሷቸው ግን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ካለ ምንም ስነአመክኖአዊ መዛባት ቁልጭ ብለው ይታዩአቸዋል፡፡

አዳምና ሔዋን አስቀድመው በመንፈስ ተፈጥረዋል ስንል፥ እነርሱን በአካል ከተወለዱት ለይተን መመልከታችን ስለሚሆን፥ ስነአመክኖአዊ አመለካከታችን አይዛባም፤ በመንፈስ የሰብእነታችንን አመጣጥ (የትውልዳችንን ሐረግ) ያረጋግጥልናል እንጂ።

የእርሻና የከብት ርቢን የጀመረው ሆሞ ሳፒያን እንጂ ሆሞ ኢሬክቱስ አለመሆኑ ይታወቃል። ስለዚህ፥ የዘመኑ ሰው ከቃየንና አቤል ተጀመረ ብንል፤ ይህ ዘመን የዛሬ ሰላሳ ሺህ ዓመትም ቢሆን፥ የዛሬ አስር ሺህ፥ ወይም ሰባት ሺህ ዓመትም ቢሆን፥ ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊ አመለካከታችንን አይለውጠውም።

ዳሩ ግን፥ "የሰው ልጅ የኑሮ እድገቱ የተጀመረው በከብት ርቢና በእርሻ ሥራ ከተሰማራበት ጀምሮ አለመሆኑ እየታወቀ፥ ለምንድነው ቃየንና አቤልን የመጀመሪያዎቹ የሥጋ ተወላጆች የምናደርጋቸው? ለመሆኑ የአዳምና ሔዋን ልጆች ቃኤንና አቤል ብቻ ናቸው ወይ? የሰው ልጅ ሕብረተሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ለምን በነርሱ ላይ ብቻ ያተኩራል?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

በእርግጥ የሰው ዘር እሳት ማንደድን ተምሮ፥ ቀስ በቀስ ከጊዜ ብዛት አካባቢውን እያጠና ለብዙ ዘመን ቆይቶ እንጂ፥ ባንድ ጊዜ የእርሻ ሥራና የከብት ርቢ አልጀመረም። የአዳምና ሔዋን ልጆችም ቃየንና አቤል ብቻ አለመሆናቸውን ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አምስት ከተጠቀሰው ለመረዳት ይቻላል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በመነሳት፥ የሰው ዘር በምድር ላይ እንዴት እንደተባዛ ሙሉ በሙሉ መረዳት እንችላለን ማለት መመጻደቅ ይሆናል። ሌሎችም ታሪካዊ መረጃዎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል። ታሪካቸው ያልተመዘገበላቸው፥ የአዳምና የሔዋን ልጆች የተበተኑበት በአለም ዙሪያ እንጂ፥ በአንድ አካባቢ ብቻ እንደማይሆን ይገመታል። ሆኖም፥ የአዳምና የሔዋን (የሰው ዘር) መነሻ ሥፍራው አንድ ብቻ እንደሚሆን እናያለን።

## <u>የሰው ሁለትነት</u>

ሁለትነታችንን እናውቀዋለን፤ ግን ስናውቅ አናውቀውም። በንግግራችን ዘይቤ ውስጥ እንኳን፥ "እንዲህ ይለኛል፤ እንዲህ ያደርገኛል.." ስንል፥ ፈቃዳዊ ምርጫችን ከአንድ ራሳችን ብቻ አለመሆኑን ነው የሚያመለክት።

የዚህ መጽሐፍ ምርጫ ግን፥ ከብዙ እንግልት ባሻገር፥ አንድና አንድ ነው። ይኸውም፡- ከእውቀቶች ሁሉ ባሻገር በአምልኮተ እግዚአብሔር ታላቅ እምነትና ጽናት ነው። የተንጠለጠሉ ጥያቄዎቻችንን ሳንረሳ፥ ስለ አዳምና ሔዋን ፍጥረት (ስለኛም

ከየት ወደየት ጥያቄ) በበለጠ ለመረዳት ይረዳን ዘንድ፥ አስቀድመን ስለ ሰው ሁለትነት እንመራመር። ሁላችንም አብረን እናስተውል ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን።

ማንም ሰው ሲያስብ፥ ባንድ በኩል አጥፊውን፥ በሌላ በኩል ደግሞ አልሚውን ሃሳብ ባንድነት፥ ወይንም ተራ በተራ ነው። እንዲህ ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦችን የሚያስብ ስለሆነ፥ ሰው ሁሉ የሁለትነት ጠባይ ይኖረዋል እንጂ፥ በዚህ ምክንያት ሁለት ነው አይባልም። ግን፥ ሰውን ሁለት የሚያደርገው እንዲህ ነው፡-

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።" ዘፍ. 2፡7

ይህ ጥቅስ፡- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ሥጋውያን ነፍሳማ እና ባለ መንፈስ ሕያው አድርጎ ፈጠራቸው ማለት ይሆናል። በቋንቋና በቃላት ትርጉም ጊዜ ሳናጠፋ "ሕያው ነፍስ" በሚል የተጠቀሰውን በነጠላው "ነፍስ" ከተባለው ለይተን እንመልከትና እንቀጥል። ነፍስ (አንዳንድ ጊዜ መንፈስ እየተባለ ቢጠራም) እኛ ሰዎች ከእንስሳት የምንለየው ክቡርና ቅዱስ በሆነው የእግዚአብሔር እስትንፋስ - ልዩ ቅዱስ መንፈስ ምክንያት መሆኑን አውቀናል።

ሰው በአካሉ ውስጥ በሚገኝ አንቀሳቃሽ ኃይል (ነፍስ) በሰውነት ደረጃ የተመደበ፥ አንድ እንደ እንስሳ ያለ ፍጡር ስለሆነ፥ በዚሁ በሥጋውና በነፍሱ አንድ ሰው ይባላል። በተጨማሪ፥ ከአካላዊው ሰው (ከነጠላ ነፍሱ ወይም አንቀሳቃሽ ኃይሉ ጋር) የእግዚአብሔር መንፈስ ሲታከልበት ሁለተኛ ሰውን የያዘ ድርብ ሰው ይባላል። ሰው ሁሉ በሥጋና በመንፈሱ ሁለት ስለሆነ፥ በአንድ ጎኑ ሞቶ የመበስበስን ጠባዮች ይዞ ሲኖር፥ እንስሳነቱንም በምድራዊነቱ ሲያንጸባርቅ እናያለን። ግን የሚያስብ እንስሳ በመሆኑ፥ በምድር ብቻ እንዳልተወሰነ፥ ነፍሱ ስትወጣ መንፈሱ የሚሄደው ወደ ሰማይ መሆኑን እያወቀ (እያመነ) ይኖራል። ያ፥ ወደ ላይ፥ ወደ ላይ የሚያስመለክተው ውስጣዊ ስሜቱ ብዙ ብዙ እያሳወቀው፥ በሳይንስም በሃይማኖትም እጅጉን ይራቀቃል።

በሰው ልጅ አካላዊነት ውስጥ ሁለት ቅራኔዎች አሉ ቢባል፤ ለምሳሌ፡- እሳትና ነፋስ ባንድ በኩል (ወደ ላይ)፤ መሬትና ውሃ በሌላ በኩል (ወደ ታች) - ይህ ሃሳብ ሰው ተቃራኒዎችን በመያዝ መፈጠሩን ለማመልከት እንጂ፥ በአካል የሁለትነቱን ጠባይ ለመግለጽ አይደለም።

ማንኛውም ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ ነፍስ አለው፤ ነፍስ አካልን ከግዑዝነት የሚለየው ጠባዩ ነውና። ግን በቁንጽሉ ነፍስ ሲባል ዘላለማዊነትን ቢያመለክትም፥ ሕያው ነፍስ (ባለ መንፈስ) ሲባል ግን፥ የሚያመለክተው የሕያው የእግዚአብሔርን መንፈስ ስለሆነ፥ ዘላለማዊ ነው።

የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የሰውን ሁለትነት፥ የነፍስና መንፈስም አንድ አለመሆን የሚጠቁሙ ይሆናሉ፡-

- **<u>“…የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች</u>** መልካሞች እንደሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶች ለራሳቸው ወሰዱ። እግዚአብሔርም መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም" እርሱ ሥጋ ነውና፤ ዘመኖቹም መቶ ሃያ ዓመት ይሆናሉ አለ።” ዘፍ.6፡1 -3
- “ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች። መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች..” ሉቃ.1፡47
- “የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፤ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ።” ኢዮብ 33፡4
- “እርሱ ልቡን ወደ ራሱ ቢመልስ፥ መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደ ራሱ ቢሰበስብ፥ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል፤ ሰውም ወደ አፈር ይመለሳል።” ኢዮብ 34፡ 15
- “አሁንም ከሥጋቸው የተለዩ ነፍሳት እነሆ ይጮሃሉ፤ እስከ ሰማይ እስኪደርስ ድረስ ይከሳሉ።” ሄኖክ 2፡39

“የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች” ሲል፥ ሁለቱ የተለያዩ መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው። ቀጠል አድርጎ እርሱ ሥጋ ነውና ይላል። እንግዲህ መንፈስ የሌለው ሰው ሥጋ ብቻ ነው ማለት ነው (ከነፍሱ ጋር)። ሰው መንፈስ ከተለየው የሚቀረው ሥጋና የዛ የሥጋው አንቀሳቃሽ ኃይል (ነፍስ) ብቻ ይሆናል ማለት ነው (እንደ እንስሳ)።

“እግዚአብሔርም መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፤ እርሱ ሥጋ ነውና..” ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት ከዚህ ሥጋ ለባሽ እንደሚለይ በግልጽ ያስረዳል። እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ሲል፥ እሱን እራሱን እያስመሰለ መፍጠሩን እንጂ፥ በአካሉ (በመልኩ) እነ ከበቡሽን፥ ወይም እነ ሺፈራውን፥ እነ እስሚዝን ወይንም እነ ካሮልን፥ እነ ቹክዋካን ወይንም እነ ሞኒካን፥ እነ ሊን ወይንም እነ ዛንግን ..ወዘተ. በሥጋ በመምሰል አይደለም፤ እግዚአብሔር ሥጋ ለባሽን አይመስልምና። ይመስላል ከተባለ፥ ከተጠቀሱት ውስጥ እነማንን ይመስላል ሊባል ነው?

እግዚአብሔርን በሥጋ አንመስለውም፤ እርሱም እኛን በሥጋ አይመስለንም። የእግዚአብሔር ሥጋዊ ያልሆነ መልኩ፥ እርሱ ከፈጠራቸው ከመላእክትም ለየት ያለ ቢሆን፥ እኛ ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ነገር ግን፥ በሰው ውስጥ የሚኖር

የእግዚአብሔር መንፈስ ሰውን ሥጋዊ ብቻ ያልሆነ፥ ሕያው ነፍስ ያለው (ሥጋዊ መንፈሳዊ የሆነ) - ባለ አይምሮ፥ ባለ መንፈስ አደረገው። መንፈስ ምን እንደሚመስል፥ እግዚአብሔርም ምን እንደሚመስል የሚያውቅ የለም። እኛ የማናየው - በእግዚእብሔር አምሳል የተፈጠረ ረቂቅ መልአካዊ ፍጡር (መንፈስ) ይዘን (ሆነን) የምንኖር - የከበርን ነን እኛ ሰዎች።

ሰው ባንድ በኩል ባለ ቅርጽ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ ቅርጹ የማይታወቅ (ወይም ቅርጽ የለሽ) ነው። በሰማያዊ ጠባዩ ቅርጽ የለሽ ነው ስንል፥ ባለ ብዙ ቅያስ (dimension) ሊሆንም ይችላል ማለታችን ነው። ይህም ከሆነ፥ ከአምስቱ የሰው ልጅ የግንዛቤ አካሎቹ ሌላ ብዙ ሌሎች የግንዛቤ አካሎች ቢኖሩት፥ ያንን የማናየውንና አካላዊ ያልሆነውን ሰው እጅግ የረቀቀ ያደርገዋል። በሕልም፥ በራእይና በሌሎችም በማይገለጹ ስሜቶች የወደፊቱን ለማየት የሚችል፥ ይህ ሰው ተራ አካላዊ ብቻ አይደለም፤ እጅግ ረቂቅ መንፈስም በውስጡ ይኖረዋል እንጂ።

በሁለትነታችን ስንኖር፥ ሁለትነት ምንጊዜም መሳ ለመሳ ሆነው አይመጡም። ካንዱ ወዳንዱ መመላለስ ይኖራል። በምድራዊነትም ሆነ በመንፈሳዊነት መራቀቅ የሚመጣው አንድ ራስን ሲሆኑ ነው። ምድራዊ ተዋንያን በተመስጦ ሲዘፍኑና ሲደንሱ፥ መንፈሳውያንም በተመስጦ ሲጸልዩ (እንዲሁም በዮጋና በመሳሰሉት በመንፈስ አርቅቀው ሲሄዱ)፥ በሁለቱም አቅጣጫ መራቀቅ ይኖራል።

ከምድራዊነታችን እየለቀቅን በመንፈስ መጓዝን ለመለማመድ ቅድመ ሁኔታዎች መስተካከል ይኖርባቸዋል። እነኚያ ቅድመ ሁኔታዎች የሚያመለክቱት፥ መልካም ምግባርን፥ ፍቅርን፥ ሰላምና አንድነትን ወደሚሰብኩ መንፈሳዊ ፍልስፍናዎች ሲሆን፥ ጾምና ጸሎትም በዘልማድ ወይም በትዕዛዝ ካልሆነ፥ ወደ መንፈሳዊነት መወጣጫ የሚያገለግሉ ድልድዮች ይሆናሉ።

እንግዲህስ የእኛ መልካችን በመንፈሳችን እግዚአብሔርን ስለሚመስል፥ ከሥጋዊ (አካላዊ) ልዩነቶቻችን ሁሉ ባሻገር መንፈሳዊ አንድነት ሊኖረን ይችላል። በዚህ ብቻ ደስ ይበለንና፥ ትኩረታችንን ወደ እግዚአብሔር መንፈስ እያደረግን እንቀጥል።

## ***ገነት***

የዚህ መጽሐፍ ስነ አመክንዮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር፥ ካለ ምንም ቅራኔ፥ ጎን ለጎን እየተጓዘ ስለሆነ፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ጥቅሶችን እየጠቀስንም፥ ሃሳቦቻችንን እያጠናከርን ስለመጣን፥ አሁንም በዚሁ እንቀጥላለን።

"እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔደን ገነትን ተከለ፤ **<u>የፈጠረውንም</u>** ሰው ከዚያ አኖረው።" ዘፍ. 2፡8 ይላል።

ይህ ጥቅስ፥ እግዚአብሔር ሰውን በሰማይ ፈጥሮ በምድራችን ላይ ሲጥለው፥ የወደቀበትን ሥፍራ ከማመልከት አልፎ፥ ሰው የተፈጠረበትን አያመለክትም። **<u>የፈጠረውንም</u>** የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ሌላ ሥፍራ መሆኑን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቋንቋዎች ሲጻፍ የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ስለሚችል፥ በዚህ በአንድ ቃል ላይ በመመርኮዝ ወደ ሠፋፊ ባሕረ ሃሳብ ሰውን መምራት ተገቢ አይደለም ይባል ይሆናል። ሆኖም፥ ሰው የተፈጠረው ከገነት ከሆነ፥ ገነትም ከምድር ላይ ከሆነ፥ ሰው የተፈጠረው ከዚሁ ከምድር ላይ ነው ማለት ነው። ግን ገነት ከምድር ላይ ላይሆን ይችላል ብሎም መመራመር ይቻላል።

አዳምና ሔዋን ሥጋዊ የሆኑበት ዘመን፥ በምድር ላይ ዛፍ፥ ሳርና ቅጠሉ፥ ፍራ ፍሬውና አትክልቱ ሁሉ እጅግ የተበራከተበት፥ የሚበላ የተትረፈረፈበት ዘመን ነበረ። በዛን ዘመን የነበረውን ሥፍራ ከገነት ጋር ማመሳሰላችን ምን ጊዜም ከምናውቀው ጋር ስለሆነ ነው እንጂ፥ በገነት ውስጥ ከምግብ የተለየ፥ ሌላ ጥሩ - ከምድራችን የማይገኝ ነገር እንደነበረ አላወቅንም። ግን ያ ሥፍራ እጅግ ደስ የሚል መሆኑን ሲያመላክት -

"....እግዚእብሔር አምላክ **<u>ደስታ ከሚገኝበት ገነት</u>**[54] አስወጣው።" ዘፍ. 3፡23 ይላል።

ሄኖክ - የያሬድ ልጅ - በጠፈር ለሦስት መቶ ዓመታት ሲመላለስ (ዘፍ. 5፡24) ብዙ ነገሮችን እንደተመለከተ፥ በመሬት አካባቢ ሁለት አይነት አለም እንዳለ በመጽሐፈ ሄኖክ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ከተጻፈው ውስጥ አብዛኛው ስለ መሬት የሚያወራ ይመስለናል፤ ግን ላይሆን ይችላል። ይህም፥ የምናውቅ የሚመስለን የማናውቀውን ሁሉ ጨምሮ መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ፡-

- ".. ያን ጊዜም ይህች <u>የተባረከች</u> ሁለመናዊ እንጨቶችን የተመላች ይቺ ምድር ለምን ተፈጠረች። ይችስ <u>የተረገመች ቈላ</u>[55] በመካከላቸው ለምን ተፈጠረች።.." ሄኖክ 7፡31 - 33
- "ወደ ኤርትራ ባህርም ሄድሁ፤ ከዚያም ቦታ <u>የራቅሁ</u> ሆንሁ። ዘጡኤል በሚባል መልአክ በላይ አልፌ ሄድሁ፤ በቸርነቱም ወደምትደርስ ገነት

[54] ሰማይ ማለት ይሆን?

[55] በ1980 እትም፤ ቈላ የሚለውን ቃል ሸለቆ ይለዋል።

መጣሁ። ከነዚህ እንጨቶች ወዲያ፥ ብዙዎች ታላላቆች እንጨቶችን በዚያ በቅለው አየሁ። ሽታቸውም ያማረ ሲሆን ታላላቆች ናቸው፤ ብርሃናቸውም ብዙ ነው፤ እነሱም ያበራሉ...” ሄኖክ 8፡20 - 22

የተሰረዘባቸውን እናስተውል። ይህች የተባረከች፤ ይህች የተረገመች የሚለው የሁለት አለማትን መኖር ያስረዳል። ሄኖክ ከኤርትራ ባህር ባሻገር ራቅ ያለ ሥፍራ ሄደና ገነት ውስጥ ገባ። ከዚህም ሥፍራ (ከገነት) የሚያበሩ እንጨቶችን አየ። ምድራዊ እንጨቶች አያበሩም፤ ስለዚህ ሄኖክ የሚገልጸው ስለ ሌላ አለም ይሆናል። የሚያበሩ እንጨቶች ለተባሉት የሚሰጠው ትርጉም ሁሉ በገነት ያሉትን (ለምሳሌ፡- መላእክትን) የሚያመለክት ከሆነ መልካም፤ የሚያወራው ስለ ገነት ነውና። የሚያበሩ እንጨቶች የሚያመለክተው በዚሁ በምድር ያሉትን ነቢያትን ነው ማለትም ይቻላል፤ እነርሱ ለዚህ ለጨለማው አለም የሚያበሩ ናቸውና።

በእርግጥ ገነት ሰማይ ሳይሆን፥ እዚሁ መሬት ላይ ሊሆን ይችላል፤ በምድር የሚኖር (መኖር የሚችል) ሥጋዊ (አካላዊ) ብቻ ላይሆን ስለሚችል። በዚችውም ምድር ላይ መላእክት ቢመላለሱበት፥ ሰውም በመንፈሱ ብቻ ሆኖ ቢኖርባትስ፤ ይህንን ማን ያውቃል?

“ድሮ” - ገና ድሮ፥ ድሮ፥ ዛፍና ሳር ቅጠል በመሬት ሳይበቅል በፊት፥ ገና ድሮ ከቅድመ ሕይወት - ከዛሬ አምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ዓመታት በፊት - የሰው ልጅ ከምድር ላይ በመንፈሱ ብቻ ቢኖርስ፤ ይህንን ማን ያውቃል?

በመጽሐፍ ቅዱስ ቀለል ባለ መንገድ የተነገረንን ጠለቅ አድርገን እንመልከት። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፥ ጊዜው ባይታወቅም፥ አዳምና ሔዋን በመንፈስ በእግዚአብሔር አምሳያ ተፈጥረዋል። እግዚአብሔርም መለኮት ስለሆነ፥ እርሱ ካልፈለገ በስተቀር ሥጋዊ መልክ - ቁመና (ቅርጽ) አይኖረውም። ስለዚህ አዳምና ሔዋን በገነት ከእግዚአብሔር ጋር ሲኖሩ ሥጋዊ አልነበሩም፤ ሆኖም፥ ለሥጋዊ ሰው መፈጠር በእጩነት ቆይተው ሳለ፥ እርሱ በፈቀደው ጊዜና ሰዓት በሥጋ ፈጠራቸው ብንል፥ ይህ ለሃይማኖታችንና ለእምነታችን ታላቅ ድጋፍ የሚሆን ርቅቅ ያለ እውነት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ከዚህም ብንነሳ፥ ዋናው የእምነታችን ጽናት ነው።

አዳም በደረሰበት እርግማን መሠረት ሠራተኛ ሆነ። ሥራን ሥራ ሲለው፥ “ከምድር ስበት ጋር እየተፋተግህ ኑር፤” ማለቱ ስለሆነ፥ እግሮቹን እያፈራረቀ ሲያነሳ ብዙ ኃይል ያስፈልገዋል። ይህንን ኃይል ለማግኘት ሲደክም፥ ሲሠራ - ሲበላ፤ እንደገናም ኃይል ሲያልቅበት፥ አሁንም ሲሠራና ሲበላ - ይህ የማያቋርጥ ሂደት እስከ ሞት ድረስ ሆኖበታል። ይገርማል! የሰው ልጅ ይህንን ግዙፍ አካል በሕይወት ለማቆየት ሲዳክር (ሲደክም)፥ ያልተፈነቀለ ድንጋይ የለም።

ድሆች ሠርተው ለመብላት ሲጥሩ፤ መንገዱ ሁሉ ሲታጠርባቸውና ግራ ሲገባቸው፤ ቆዳ አኘኩ ቀቅለው፤ ሳርና ቅጠል በሉ አብስለው፤ አፈር ቃሙ ዘግነው፤ ምንም የለም የቀራቸው፥ የሚሆናቸው ለሆዳቸው። ይህ ሁሉ ድካም ሥጋን እያተለቁ፥ ሥጋን ተሸከሞ ለመንቀሳቀስ ሲሆን፤ እንግዲህ ይህንን ጉልህ ሆኖ መታየት ነው አካላዊነት የምንለው። ግን፥ በአካላዊ ገለጻ ስለማይገለጽ አለም ለመግለጽ ከምንጠቀምባቸው ቃላት መካከል በተለይ "ትልቅነት" እና "ትንሽነት" ብዙ ፍቺ አይሰጡም።

ገነት ለሰው የማይታይ ሰማያዊ አገር (ከተማ) ከሆነ፥ ሄኖክ እንዴት ብሎ ነው ገነትን የሚመለከት? "ወደ ገነት መጣሁ" ሲል ገነት ዛሬም ያለ ያስመስለዋል። የለም ወይ? ቢኖርስ እኛ እንዴት ልናውቅ እንችላለን፥ ሳናይ?

"አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ፥ በእጃቸው የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን የያዙ ኪሩቤል ከገነት ደጃፍ ቆመው ይጠብቃሉ።" (ዘፍ. 3፡24) ታዲያ ገነት ለኛ መታየቱን ያቆመው (ተመልሶ የማይገቡበት የሆነው) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሆነ፥ ገነት ሰማይ ይሁን፥ ወይንም ከዚሁ ከምድር ይሁን፥ ይህንን እንኳን ለይተን አለማወቃችን ስለ አዳምና ሔዋን አፈጣጠር ብዙ እንዳናውቅ አድርጎናልና፤ አለማወቃችንን በትህትና እንቀበል።

አዳምና ሔዋን አትብሉ የተባሉትን ፍሬ በመብላታቸው ኃጢአተኞች ሆኑ። ሕያው መንፈሳቸው በኃጢአት ስለረከሰ፥ እግዚአብሔር ተቆጣ። ኃጢአት ከዘር ዘር የሚተላለፈው በመንፈስ ነው እንጂ በሥጋ አይደለም። በሥጋ የሚተላለፍ በበራሂ ውስጥ የሚገኝ ሥጋዊ ጠባይ ነው። ኃጢአት ከዘር ዘር ይተላለፋል የምንለው፥ ኃጢአት በሕያው መንፈስ ውስጥ ስላደረና፥ ሥጋዊ ሰው ቢሞትም እርሱ (ሕያው መንፈሱ) የማይሞት በመሆኑ ነው።

አዳምና ሔዋን ከምድራችን ጋር ሲነካኩ - የምድራዊነት ግዴታ የሆነውን አንዱን (መብላትን) ሲፈጽሙ - ትእዛዝ ስለጣሱ - ኃጢአት ሠርተው ሥጋዊ ስለሆኑ፥ አካባቢያቸው ተለዋወጠ (ተገለባበጠ)፤ የኖሩባት ገነት መልኳን ቀየረችባቸው - ገነት ምድራዊ ሆነች። የዛን ጊዜ ከዘር ዘር የሚተላለፍ - አካላዊ ያልሆነ - ኃጢአት የሚባል ነገር በውስጣቸው ተመዘገበ። ገነት ተለውጣ፥ እግር የምትዋጋ እሾካማ፥ አድካሚ ባለ ዳገትና ቁልቁለት፥ አሳማሚ ባለ ተናዳፊ ንብ፥ አስፈሪ ባለ ተናካሽ አውሬ ሆነችና፥ ከዛፍ ፍሬ ለቅሞ ኑሮም የከበደባት ይህችው እኛ የምናውቃት ምድር ሆነች። እነኛ የሚያበሩ ዛፎች ቅጠላቸውን የሚያረግፉ የሚጠወልጉም ሆነው ተገኙ። እነኚያ አስቀድሞ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠሩት መናፍስት (የእግዚአብሔር ልጆች) ከገነት ወጡና የአውሬዎች መፈንጫ ከሆነ መሬት ላይ ወደቁ። ግን ይህንን ስንል፥ ያቺ

ሰማያዊዋ ገነት አሁን ጠፍታለች ማለታችን እንዳልሆነ ልብ ይሏል። ኃጢአት እየሠሩ የሚኖሩበት አለም ከገነት (ከሰማይ) ብቻ መሆኑን ከተገነዘብን ይበቃል።

"...በእርሱ ላይ ኃጢአት ሠርተናልና፥ በእግዚአብሔር ባርያ በሙሴ ሕግ የተጻፈው መሃላና እርግማን ፈሰሰብን።" ዳን. 9፥11

አሁንም ሰማያዊ ገነት መኖሩን፡- በመንፈስ የሚንቀሳቀሱ - አካላዊ ያልሆኑ - ሰማያዊ ሕያዋን ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እንዲሁ የተለያየ ጥፋት እያጠፉ ከሰማያዊ ገነት እየተባረሩ፤ ወደ ምድራችን የገቡ (የሚገቡ?) መሆናቸውን የሄኖክ ጽሑፍ ይጠቁማል (መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት)።

ይህንን ጉዳይ ከዚሁ ላይ እንተወውና፥ የዛሬው አለም አቀፍ ሕብረተሰብ፥ ወደሚሄድበት አቅጣጫ፥ ከፍጥረቱ በምድራዊነቱ የሚጠብቀውን በመመልከት፥ ሰላሙን፥ ፍቅሩንና አንድነቱን የሚያረጋግጥበትን ከራሱ አውጥቶ እስኪወስድ ድረስ የሚጠብቀውን ውጣ ውረድ እንመልከት።

## <u>የሰው ዘር</u>

መቼም ከሰማነውና ካነበብነው ሁሉ መካከል ለሰው ልጅ የሚጠቅመውን ብቻ እየለየን የማንወስድ ከሆነ፥ ሃሳባችን ወዳልተፈለገ ሥፍራ ሊያመራ ይችላልና፤ አሁንም ትኩረታችን ወደጥሩው እንዲሆን ተፈላጊ እውቀቶችን እንገንባ። የሰውን አካላዊ ቁመናውን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ጠባዩንም እየተመለከትን እናጥናው።

ታሪክ አንዱ የሰው ዘር እንዴት በሦስት እንደተከፋፈለ (ከአንድ የሰው የዘር መደብ ውስጥ እንዴት ልዩነቶች እንደተከሰቱ) አይገልጽም። ሳይንሱም በዚህ ላይ ደካማ ነው። ሆኖም፥ በየጊዜው ከሚተረከው (ከሚጻፈውም) ባለ ብዙ አቅጣጫ ትንተና ባሻገር፥ አንባቢ ከሁሉም ጨው በጣት እንደሚቆነጠር እያደረገ፥ የራሱ የሆነውን ሚዛናዊ አመለካከት እንደሚያጠናክር በማመን፥ በቀድሞ ዘመን (ሰዎች በአካላዊ ልዩነቶች ሳይከፋፈሉ በፊት) በአንድ ላይ እንደኖሩ፥ ከጊዜ በኋላ ግን ሁሉም ብጤውን ሲፈልግ የራሱን ክልል እንደሚወስን ለመገምገም ከሄኖክ ጽሑፍ እንነሳለን።

"ከሷም (ከሔዋን) ሁለት ጥጆች ተወለዱ፤ ከሁለቱ አንዱ ጥቁር ሆነ፤ አንዱም ቀይ ሆነ፤....ከዚያም በኋላ ሌላ ነጭ ላምን ወለደች፤ ከሱም ቀጥሎ ብዙ ላሞችን፥ ጥቋቁሮች ጊደሮችን ወለደች...።" ሄኖክ 30፥5 - 13

ሔዋንን እንደ መጀመሪያው ሰብአዊነት ብንቆጥራት፥ ይህ ጽሑፍ፡- በምድር ላይ አሁን የምናየው የሰው ዘር[56] (race) ነጭ፥ ቢጫ እና ጥቁር (white race, yellow race, black race) ከሔዋን የቀጠለ እንደሆነ ይጠቁማል። አንዳንድ ሰዎች ግን፥ የሰው ዘር በአይነቱ በሦስት ቀለማት የተከፈለው ከኖህ በኋላ ባንድ ጊዜ - ባንድ ትውልድ - ነው ይሉ ይሆናል። ሄኖክ የጠቆመን ግን ከኖህ በፊትም ቢሆን ያ ሦስት የሰው ዘር በኖህ ውስጥም ተቀብሮ እንደተቀመጠ ነው። ሁሉንም እያወዳደሩ ማየት ያንባቢ ኃላፊነት ነው።

ከኖህ ቤተሰብ ሦስት ቀለማትን ያካተቱ ሰዎች ተወልደዋል ብንል፡- ካለ ቅድመ ተፈጥሮአዊ ጠባይ፥ ከአንድ የነጭ ቤተሰብ፥ ባንድ ጊዜ እንዲህ የተለያየ ሦስት የሰው አይነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ማለታችን አይቀርም።

ከአንድ ሰው የዘር ግንድ ሦስት አይነት የቆዳ ቀለማት ከተገኙ፥ የዚህ ሰው ቀለሙ ነጭ፥ ጥቁርና ቢጫማ (ብርቱካን አይነት) አጣምሮ የሚይዝ ቡናማ አይነት ነው መሆን ያለበት። ኖህ ቀለሙ ነጭ መሆኑ በሄኖክ መጽሐፍ ተገልጿል። ታዲያ ከዚህ ነጭ ሰው እንዴት ሦስት አይነት ሰው ሊፈጠር ይችላል?

ኖህ ራሱ ነጭ ቢሆንም፥ ምናልባት የርሱ እናትና አባቶች፥ የቀድሞ አያቶቹና ቤተሰቡ ሁሉ ሦስቱን ቀለማት ያካተቱ ይሆናሉ። ኖህ ብቻውን ነጭ ስለሆነ፥ የቀድሞው የዘሩ ግንድ እንደማይቋረጥ፥ እርሱም በእርግጥ ነጫጭ ካልሆኑ እናትና አባት የተወለደ ስለመሆኑና፥ በዘሩም ውስጥ ሦስቱን ቀለማት ያካተተ ስለመሆኑ እንደሚከተለው ተገልጿል።

የሄኖክ[57] የልጅ ልጅ የሆነ፡- የማቱሳላ ልጅ (ላሜህ) ሚስት አግብቶ ወንድ ልጅ ወለደ። ይህም ልጅ መልኩ ነጭ፤ ጠጉሩም ብዥት (blond) ሆነና፥ አባትዬው (ላሜህ) እጅግ ተጨነቀ። እርሱ ወይንም ሚስቱ ፍጹም ነጭ ብትሆን ኖሮ፥ ነጭነትን በርሷ ያሳብብ ነበር።

ላሜህ "ከኔ እንዴት እንዲህ አይነት ነጭ ሰው ይፈጠራል? በአባቴ በማቱሳላ በአያቴም በሄኖክ፥ በቤተሰቦቼ ሁሉ የሌለ ነጭ ከየት መጣ?" ብሎ ሃሳብ ገባው። ላሜህ እየገሰገሰ ወደ አባቱ ወደ ማቱሳላ ሄደና፥ የዚህ ልጅ ልዩ ሆኖ መፈጠር ያስፈራው መሆኑን እና ከርሱም ከራሱ (ከአብራኩ) የተፈጠረ ለመሆኑ የሚጠራጠር

---

[56] ሰው የተባለ ፍጥረት ሁሉ ዘሩ አንድ ነው፤ እርሱም የሰው ዘር ወይንም የሰው የዘር መደብ ይባላል። የተቀረው የሰው ልዩነት (የቆዳ ቀለም፥ አካላዊ ቁመና እና ገጽታ) የዘር ልዩነት አይደለም።

[57] ሄኖክ ትውልዱ ከምሥራቅ አፍሪካ (የጥንቷ ኢትዮጵያ) ሊሆን ይችላል።

መሆኑን ነገረው። ማቱሳላም፡- እንዲህ አይነቱን ነገር የሚያውቅ አባቱ ስለሆነ፥ ይህንን ጉዳይ ይዞ ወዳባቱ ወደ ሄኖክ ገሰገሰ፥ እንዲህም ብሎ ነገረው፡-

"..መልኩ ፍጥረቱም እንደ ሰው ፍጥረት ያልሆነ፥ መልኩም ከእንቁ ይልቅ የሚነጣ፥ ከጽጌረዳም የሚቀላ፥ የራሱም ጠጉር ከብኸርት ይልቅ የሚነጣ፤ አይኖቹም እንደ ጸሐይ እግር የሚያበሩ ልጅ፥ ለልጄ ለላሜህ ተወልዷልና፤ አባቴ (ሄኖክ) አሁንም ስማኝ። ዓይኖቹንም በገለጠ ጊዜ ቤቱ ሁሉ አበራ፥ ካዋላጂቱም እጅ ተነስቶ፥ አፉንም ከፍቶ፥ የሰማይ ጌታ እግዚአብሔርን አመሰገነው። አባቱ (ልጄ ላሜህም) ፈርቶ ወደኔ ሸሸ። ከሰማይ መላአከት የተወለደ አስመሰለው (መሰለው) እንጂ እሱ (ሐጻኑ) ከሱ (ከላሜህ) የተወለደ መሆኑን አላመነም። እውነቱን ትነግረኝ ዘንድ እነሆ ወዳንተ መጣሁ።" ሄኖክ 41፡11 - 14

የዛን ጊዜ ወደ ምድር እየወረዱ ከሰው የሚጋቡ መላእከት ስለነበሩ ነው ማቱሳላ የተጠራጠረው። ሄኖክ ግን ማቱሳላ ለአቀረበለት ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥቶታል፡-

"...በዚህ አለም ሁሉ ጽኑ ጥፋት ይደረጋል፤ ጥፋት ያለበት ውሃ ይወርዳል። ታላቁም ጥፋት ባንዱ ዓመት ይደረጋል። ለናንተ የተወለደ ልጅ ይህ ነው። "በዚህ አለም" እሱ ብቻ ይቀራል። ሦስቱም ልጆቹ ከሱ ጋራ ከማየ አይህ (የጥፋት ውሃ) ይድናሉ። በዚህ አለም ያለው ሰው ሁሉ በሞተ ጊዜ እሱ ይድናል። ልጆቹም አርበኞች ሰዎችን ይወልዳሉ። እነዚህም ሥጋውያን ናቸው እንጂ መንፈሳውያን አይደሉም። ጽኑ መቅሰፍትም በዚህ አለም ይደረጋል። ምድርም ከኃጢአት ሁሉ ትነጻለች። አሁንም ይህ የተወለደ ልጅ በእውነት የሱ ልጅ እንደሆነ ለልጅህ ለላሜህ ንገረው፤ እሱ ከጥፋት የቀረ ይሆንላችኋልና፥ ስሙንም ኖህ ብለህ ጥራው።..." ሄኖክ 41፡15 - 20

ይህ የተወለደው ልጅ ከራሱ ከላሜህ አብራክ የተወለደ እንጂ፥ ከሌላ ከመላእከት ያልተወለደ መሆኑን ግልጽ አድርጎ ሄኖክ ለልጁ ለማቱሳላ አስረድቷል። የኖህ አባት ላሜህ ነጭ ቢሆን ኖሮ "ከኔ እንዴት እንዲህ አይነት ነጭ ሰው ይፈጠራል?" በማለት አይደናበርም ነበር። ስለዚህ ከኖህ የጀመረው የዘር ጥንስስ (ጂን - በራሂ) ነጭነት እንዳለበት እንጂ ፍጹም ነጭ አለመሆኑን፤ ኖህ ነጭ ቢሆንም፥ በዘሩ (በአያቱና በቅድመ አያቱ) ሦስቱን ቀለማት የሚያካትት (ምናልባት ቡናማ አይነት) መሆኑን ይጠቁማል። ስለዚህ ከኖህ ቤተሰብ ብቻ ወጣ የተባለው ሦስት ቀለም፥ ባንድ ጊዜ (በጥቂት ዓመታት) የተገኘውን የዘር ልዩነት አይደለም የሚያመለክተው ።

የሰው ዘር ሁሉ ግንዱ አንድ ነው ከተባለ፥ የጥንቱ የሰው ዘር እጅግ ያልጠቆረ፥ እጅግም ያልቀላ (ወይም ያልነጣ) - ጥቁርና ነጭን፥ ቢጫንም ያካተተ ቡናማ አይነት መሆን አለበት። እንዲህ አይነቱ ሰው ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከ

ሄኖክና ኖህ ድረስ ቢደርስ፥ ከዛ በኋላ ሲሰደድና እንደገናም በጂኦግራፊ ክልሎች ምክንያት ሲለዋወጥ፥ በአካላዊነቱ እየተራራቀ መምጣቱን መገመት አያስቸግርም።

ሄኖክ የዘረዘረውን ሁሉ እንርሳውና ወደራሳችን ግምት እንምጣ። የሰው ልጅ አካላዊ ሰውነቱ በአካባቢ ሁኔታዎች መጠነኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ግልጽና ለማንም የሚታይ ነው። ግን የሰው ዘር በመሠረታዊ ፍጥረቱ ዛሬ በግልጽ የሚታዩትን ሦስት አይነት የሰው ዘር (በአንድ የዘር መደብ ውስጥ) ገና ከጅምሩ ያካተታቸው ካልሆነ በስተቀር፥ የአካባቢ ለውጥ ቢኖርም፤ ይህ ብቻ የተጠቀሱትን ሦስት አይነት የሰው ዘር ለማፍራት በቂ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ግለሰቦች፥ "ከአፍሪካ ወጥቶ ወደሰሜን የተጓዘ ጥቁሩ ሰው (ሆሞ ሳፒያን)፥ ከጊዜ ብዛት በአየር ለውጥ (በቅዝቃዜና በብርድ) ምክንያት ወደነጭነት ተለወጠ" ይላሉ። ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም።

አዳምና ሔዋን (ወይንም የመጀመሪያዎቹ ሰዎች) ቀለማቸው ፍጹም ጥቁር ወይም ፍጹም ነጭ ቢሆን ኖሮ፥ የኛ ዝግመተ ለውጥ (የዳርዊን ያልሆነው) ጥቁሩን ነጭ ወይንም ነጩን ጥቁር ሊያደርገው ፈጽሞ አይችልም። ግን ሁላችንም እንደምናውቀው፥ ከጊዜ በኋላ፥ የአዳም ዘር እየበዛ ሲሄድ፥ ከአብራኩ የሚወጡት ሕዝቦች እያንዳንዳቸው ጥሩነትና መጥፎነት ባለመልቀቅ፥ ሦስት አበይት ቀለማት (ነጭ፥ ጥቁር፥ ብርቱካን አይነት ወይም ቢጫማ ቀይ)፥ በነኚህ ቀለማት መካከልም፥ ሌሎች ቀለማት (አስራ ሁለት አይነት ወይም ከዛ በላይ) ሆኑ። ይህ ሊሆን የቻለው፥ ከቀድሞውም (ከኖህ በፊት) የሰው ልጅ የቆዳ ቀለም ሁሉንም ቀለማት ያካተተ (ቡናማ አይነት) ቢሆን ነው።

መጀመሪያና መጨረሻ ያለው ሁሉ (ሕይወት ያለውም/የሌለውም) ወደ መጀመሪያው ፈጠን ፈጠን፤ ወደመጨረሻውም ቀርፈፍ ይላል። የሰብአዊነት ሕይወት በተጠቀሰው አይነት የእድገት ፍጥነት ውስጥ ሲያልፍ፥ በውስጣዊ ተፈጥሮም ሆነ በአካባቢ ሁኔታዎች ምክንያት ይለዋወጣል። ይህም ለውጥ፥ "ቶሎ ቶሎ" ከመለዋወጥ ቀጥሎ እያዘገመ፥ የሰው ዘር አለምን በሦስት አበይት ቀለማት አደመቃት። ይህ "ቶሎ ቶሎ" ያልነው መለዋወጥ በቅድሚያ ከሰው ውስጣዊ የዘር ጥንስስ (ጂን - በራሂ) የሚመነጭ ሲሆን፥ ይህ ገና ከእናቶች ማህጸን የሚጠነሰስ ሽል (embryo) ነው። ይህ ነው ፍጥን የሚለው ለውጥ። ይህንን ከዝግመተ ለውጥ አንቆጥረውም። በአካባቢ የሚመጣው ለውጥ ግን ዘገምተኛ ስለሆነ፥ ከዝግመተ ለውጥ ይቆጠራል።

ከጥንቱ በውስጠ ጠባዩ ሦስቱን ቀለማት ያካተተ ሰው ሲወለድ የተለያየ መልክ ይዞ ወጣ። ከጊዜ ብዛት ሦስቱ ቀለማት አንዱ ከሌላው በግልጽ እየተለየ መጣ። ሁሉም ብጤውን ሲፈልግ፡- ጠቆር ያለው ጠቆር ወዳለው፥ ነጣ ያለውም ነጣ ወዳለው፥ ቢጫማውም ወደ ቢጫማው ሲጠጋ የተጠቀሱት ሦስት የሰው ዘር አይነቶች

ብጤአቸውንና የሚመስሏቸውን እየተከተሉ፥ ከምድር መሀል ከሆነው ከምሥራቅ አፍሪካ (የድሮዋ ኢትዮጵያ ማለት ነው) ሲርቁ - ሲርቁ፥ በጊዜው ወደ ምድር ዳርቻ ወደነበረው (ከአውሮፓ እና ከእስያ ወደ ሰሜን፥ ወደ ምሥራቅና ወደ ሰሜን ምዕራብ፥ ከአፍሪካም ወደ ደቡብና ወደ ምዕራብ) ተሸጋሸጉ። ከጊዜ በኋላ፥ ሰዎች በአውሮፓ፥ በእስያና በአፍሪካ ተባዙ። ሰብአዊ ሕይወት ሲባዛ አካላዊ ልዩነትም መበራከቱ የተፈጥሮ ሕግ ስለሆነ፥ የሰው ልጅ በአካል ቅርጽ የተለያየ ሆነ፤ በቆዳ ቀለምም ደመቅ - ደመቅ ብሎ ታየ። ይህም ድምቀት ባካባቢ ሁኔታ፥ በምግብ አይነት..ወዘተ ሊባባስ ይችላል።

በአካባቢ ሁኔታ ብቻ ጥቁሩ ነጭ፥ ወይንም ነጩ ጥቁር ሊሆን እንደማይችል- ጥቁር ሰው ሰሜን ዋልታ ሄዶ ኑሮውን ከዛ ቢመሠርት ነጭ እንደማይሆን ሁሉ፥ ነጭም ሰው ከሰሜን ዋልታ መጥቶ፥ ኑሮውን ከመሀል አፍሪካ ቢመሠርት ጥቁር ሊሆን አይችልም። በአካባቢ የሚመጣ ለውጥ ደካማ ነው፤ ከውስጣዊው የዘር ጥንስስ (ጂን - በራሂ) ቀጥሎ (ከመወለድ) የሚመጣና ብዙ ጊዜም የሚፈጅ ነው።

ባሁኑ ዘመን እንዲህ ድምቅምቅ ብሎ የሚታይ የቆዳ ቀለም የመጀመሪያዎቹን ሰዎች እንዴት እዚህ ደረጃ እንዳደረሳቸው ለመገመት - ጊዜና የለውጥ ፍጥነቶችን አብሮ ማያያዝ ያስፈልጋል።

ያ የመጀመሪያው ሰው የአካባቢ ሁኔታ በቀላሉ ሊለዋውጠው እንደሚችል ቢገባንም፥ ሦስት አይነት የሰው ዝርያዎች እንዲሁ ከአብራኩ የማፍራት ችሎታም በውስጣዊ ተፈጥሮው (ካለ አካባቢ ሁኔታ) ሊኖረው እንደሚችል እንገነዘባለን። ይህ ዛሬ የምናየው ዘር (የሰውም ሆነ የእንስሳ) በውስጡ ፍጥረትና ዝግመተ ለውጥን (ሁለቱንም) ያቀፈ በመሆኑ፥ በአካባቢ ኃይል ተበግሮ የገዛ ዘሩ እንዳይጠፋ፥ እንደየአካባቢው ሁኔታ መጠነኛ ለውጥ ማሳየቱ አይካድም። ግን ይህ ለውጥ በአካሉ ያስከተለው ለውጥ በሄደበት ሥፍራ ሁሉ፥ እንደየአካባቢው ሁኔታ ለመኖር የሚያበቃውን ያህል ብቻ መሆኑን ልብ ይሏል። ስለዚህ፥ ይህ የአሁኑ የሰው ዘር በአንድ መቶ ሺህ ዓመታት ውስጥ ተለውጦ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷልና - ጥቁሩም ጥቁር ብሎ፥ ነጩም ንጥት ብሎ፥ ቢጫውም ብጭጭ ብሎ አብቅቶታልና፤ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣ ለውጥ ከመዳቀል የሚመጣ ብቻ ነው የሚሆን። ይህ መዳቀል በስደት፥ በንግድ ልውውጥና በጦርነት ሳቢያ ሰዎች አብረው ሲኖሩ ይመጣል።

ይህ መጠነኛ ለውጥ አሁንም ያለና የሚቀጥል ነው። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው እንደሚባለው ሁሉ፥ በተጠቀሱት ሦስት ደማቅ ቀለማት (ጥቁር፥ ቢጫና ነጭ) መካከል ያሉ ሰዎችም ከጊዜ ብዛት በመዋለድና በመባዛት ከጊዜ ብዛትና እንደየአካባቢው የተቀየጡ ሆኑ።

እግዚአብሔር በመጀመሪያው የሰው ውስጣዊ የዘር ጥንስስ (ጂን - በራሂ) ውስጥ ያስቀመጠው ዲ አን ኤ የወደፊቱን እንደሚወስን፥ ዛሬ የምናየው የሰው አይነት ይህንን ከመሰለ፥ አሁንም ያ ዲ አን ኤ የሚጫወተው ሚና ይኖራል። በእግዚአብሔር አይን የወደፊቱን ሰው መመልከት ከቻልን እንመልከት።

በማያቋርጥ ለውጥና የእድገት ክስተት ውስጥ የሰብአዊነት እድገት ወደ አካላዊ ፍጹማዊነት አልተጠጋም። የሰው ዘር ቁልጭ ባለ የቆዳ ቀለም መታየቱ በአካላዊነቱ የደረሰበትን ከፍተኛ የእድገት ደረጃ አያሳይም። አሁንም ሰው በአካሉ ፍጹምነት ከእንስሳት እንኳ በልጦ አይታይም (ከአንድ ሽረሪት የበለጠ ፍጹማዊነት አይኖረውም)። የበሽታው አይነትና ኃይል ከመድኃኒቱ አይነትና የማዳን ችሎታ በበለጠበት አለም ውስጥ ነው የምንኖረው። በገዛ ራሱ በሽታዎችን ሁሉ ተከላክሎ ለረጅም ዘመናት የሚኖር አካላዊ ሰውነት የለንም።

## <u>የሥጋዊ ሰው መነሻ ሥፍራ - ነፃ አስተያየት</u>

የሰማያዊ ገነትን መነሻ ሥፍራ ማወቅ ባንችልም፥ የዚህን የሥጋዊ ሰው መነሻ ሥፍራ ማወቅ ያን ያህል ከባድ መሆን የለበትም።

የሰው ዘር (ኃጢአት ከሠራ በኋላ) ተባዝቶ እዚህ የደረሰው ከአንድ የዘር ግንድ ከሆነ፥ ይህ የዘር ግንድ አንድ መነሻ ሥፍራ ይኖረዋል። የሰው ዘር መነሻ ለሆኑት አዳምና ሔዋን አፍሪካውያን - ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሎ ዜግነት መስጠት ተገቢ ላይሆን ይችላል። ዜግነት የመጣው በኋላ - እጅግ ቆይቶ ቢሆንም፥ የሰው ዘር (ሥጋዊው) አመጣጡ ከአፍሪካ መሆኑን ከዳርዊን ጀምሮ ብዙዎቻችን የምንስማማበት ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም የሰው ዘር (ሥጋዊው) አመጣጡ በተለያየ መንገድ ተጠቁሟል።

“የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል።” ዘፍ.2፡13 በማለት የገነት ወንዝ ከኢትዮጵያ እንደሚነሳ ይጠቁማል። አራተኛው ወንዝ ኤፍራጥስ ነው ሲል (ዘፍ. 2፡15) ደግሞ ወደ ኤስያም ይገባል።

አዳምና ሔዋን ሥጋዊ - ምድራዊ ኑሮአቸውን የጀመሩት ከአንድ ሥፍራ ቢሆንም፥ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች የሰው ዘር መነሻው ከተለያዩ ሥፍራዎች መሆኑን ያመለክታሉ። ነገር ግን፥ ከጥፋት ውሃ በፊት የሄኖክ ቤተሰቦች (ከሳባውያን በፊት የነበሩ - ምሥራቅ አፍሪካውያን - ኢትዮጵያውያን) ቢሆኑ ነው እንጂ፥ የሄኖክ ቤተሰቦች አረቦች ወይንም ኢራቃያውያን ቢሆኑ ኖሮ፥ ሦስቱንም የሰው ዘር የሚያካትት አካላዊ ጠባዮችን አይኖራቸውም ነበር። ስለዚህ ከኖህ በፊት የሰው ዘር መነሻው ከአንድ ሥፍራ ከሆነ፥ ያ ሥፍራ ከወደ ምሥራቅ አፍሪካ ነው መሆን ያለበት።

ከኖህ በኋላም፥ የሰው ዘር መነሻው ከአንድ ሥፍራ ከሆነ፥ የኖህ አያቶችና ቅድመ አያቶች ምሥራቅ አፍሪካውያን (ኢትዮጵያውያን) ነው መሆን ያለባቸው።

ከጂኦግራፊ ክልል አንጻር ብቻ እንኳን ብንነሳና፥ የሄኖክንም መጽሐፍ ብንመረምረው፥ የሰው ልጅ መነሻው ከኢትዮጵያ እንደነበረ መገመት አያስቸግርም። ጥንታውያን ኢትዮጵያውን (ሳባውያን[58] ያልሆኑ) ምን ይመስሉ እንደነበረ ማወቅ አይቻልም፤ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንማ ብዙ ስለተዳቀሉ የጥንቱ መልካቸው (ቡናማ መስሎ ጥቁረትን፥ ቢጫነትንና ንጣትን ያካተተው) ጠፍቷል።

የጥንት ዘራችን አንድ[59] በመሆኑ ከተስማማን፥ እንዴት እንደተለያየን መገመት አያቅተንም። አዳምና ሔዋን ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ብለን፥ እስካሁን ድረስ በአርከኦዎሎጂ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ውጪ የተቀረውን አማራጭ እንመልከተው።

ቀደም ሲል ከጠቀስነው የአካባቢ ለውጥ (ዝግመተ ለውጥ) ጋር ለማያያዝ የሚከተሉት አማራጮች ይኖራሉ።

1) ከኖህ በፊት የሰው ዘር መነሻው ከአንድ ሥፍራ ከሆነ፥ የሰው ዘር ከወደ ምሥራቅ አፍሪካ ከአዳም እስከ ሄኖክ ድረስ ሦስቱን የሰው ዘር በማካተት ቆይተው ሳለ፥ ከዛው ከአፍሪካ ምድር ሳይወጡ ሲዋለዱና ሲባዙ ሦስቱንም አይነት የሰው ዘር፥ ግን ጥቁሩ በጣም ሳይጠቁር፥ ቢጫው በጣም ሳይበጭጭ፥ ነጩም በጣም ሳይነጣ የተለያዩ መልኮች አውጥተው ከቆዩ በኋላ ስደት ተጀመረ።
2) ከስደት በኋላ በተሰደዱበት ሁሉ እንደየአካባቢያቸው ሁኔታ መጠነኛ አካላዊ ለውጥ (ዝግመተ ለውጥ) በውስጣቸው ስለተካሄደ፥ ጥቁሩ ጥቁር አለ፥ ነጩ ንጥት አለ፤ ቢጫውም ብጭጭ አለ።
3) የተጠቀሱት ሦስቱን ቀለማትና በመሃልም ያለውን ጉራማይሌ ቀለማት ከምስራቅ አፍሪካ በመቅረብና በመራቅ የተባባሱ መሆናቸው በግልጽ ይታያል።
4) ከኖህ በፊት የሰው ዘር መነሻው ከአንድ ሥፍራ ከሆነ፥ የሰው ዘር ከወደ ምሥራቅ አፍሪካ (ኢትዮጵያ) ከአዳም እስከ ሄኖክ ድረስ ሦስቱን የሰው ዘር በማካተት ቆይተው ሳለ፥ የጥንት መልካቸውን እንደያዙ ተሰደዱ።

[58] ሳባውያን የሚለው ስም - ሳባውያን ከጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ጋር ከተዳቀሉ በኋላ፥ የየመን እና የኢትዮጵያ ሕዝቦችን - በጠቅላላ ኢትዮጵያውያንን ሊያጠቃልል ይችላል። ዘፍ. 10፡7፤ ኢሳ. 43፡3፤ መዝ. 72፡10

[59] የቆዳቸው ቀለም ቀይ ዳማ ወይንም ቡናማ ከመሳሰሉ አዳምና ሔዋን።

5) ከዚያም በኋላ - ከስደት በኋላ - በተሰደዱበት ሁሉ እንደየአካባቢያቸው ሁኔታ መጠነኛ አካላዊ ለውጥ (ዝግመተ ለውጥ) በውስጣቸው ስለተካሄደ፥ ጥቁሩ ጥቁር አለ፥ ነጩ ንጥት አለ፤ ቢጫውም ብጭጭ አለ።
6) እነኚህን ሦስቱን ቀለማትና በመሃልም ያለውን ጉራማይሌ ቀለም የምናየው፥ ከምስራቅ አፍሪካ በመቅረብና በመራቅ፥ ያካባቢ ለውጥ ያስከተለውን ሲሆን፥ ከዛውም ጋር፥ በመዋለድ (በመዳቀል) የሚመጣውንም ለውጥ ነው።
7) መቼም ሰው ቢሰደድም ከገዛ አገሩ ጥርግ ብሎ ስላልወጣ፥ የተቀረው ሕዝብ፥ ከአዳምና ሔዋን የወረሰው ቡናማ መስሎ፥ ጥቁረትን፥ ቢጫነትንና ንጣትን ያካተተው መልኩ ጭራሽ እስኪጠፋ ድረስ መከፋፈል አልቀረለትም። ይህ መከፋፈል "ዘር" አደለም። በፍጥረታት መካከል ዘር የሚያመለክተው የተለያዩ የፍጥረታት ዝርያዎችን ነው። ለምሳሌ፡- የሰው ዘር፥ የዝንጀሮ ዘር፥ የአሳ ዘር፥ እና ሌሎችም።
8) እስካሁን በተነጋገርነው መሠረትና፥ ሠፋ ባለ አመለካከት፥ ዛሬ በኢትዮጵያችን ያለነው ሕዝቦች የምንዋደድ፥ በተለያዩ ስሞች የምንጠራ ቤተሰቦች ነን፡- የኦሮማይ ቤተሰብ፥ የትግራይ ቤተሰብ፥ የአምሃራይ ቤተሰብ፥ የጉራጌ ቤተሰብ፥ የአፋር ቤተሰብ፥ የወላይታ ቤተሰብ፥ የኩናማ ቤተሰብ..ወዘተ...።
9) በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሕዝቦች፥ በአካል (በበራሂ)፥ በቋንቋ፥ እና በባህል ይቀራረባሉ፤ እንዲሁም ግለሰቦች ከአንድ ቤተሰብ እየወጡ ወደሌላው ይገቡና በቋንቋና በባህል ልዩነቶች ሳይበገሩ፥ ከመዋደድና ከመፋቀር የተነሳ፥ ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ ይሆናሉ። በዚህን ጊዜ ቤተሰብ የሚለውንም መለዮ ለገዛ ቤተሰባቸው ይተውና፥ ቤተሰቦችን በሚያጠቃልል በአንድ መልዮ ይጠቀማሉ (ኢትዮጵያዊነት)።
10) መበተንና መሰብሰብ ጠፈራዊ የተፈጥሮ ሕግ መሆኑን እንደተመለከትን ሁሉ፥ ለወደፊት የኢትዮጵያ ቤተሰቦች እየተቀራረቡ ይመጣሉ፥ ብሎም በአንድ ዜጋ ይጠቃለላሉ - ሁሉም ለአንድነት። ሕዝቡ ለወደፊት አንድ ቅዱስ ሕዝብ ይሆን ዘንድ በጠባዩ፥ በአመለካከቱና በእምነቱ ጠንከር - ቀና ማለትን ካወቀበት፥ እግዚአብሔር ከፍ ያደርገዋል።

ኢትዮጵያ የተባለችው አገር የቷ ናት? ሕዝቦቿስ እነማን ናቸው? በሚል አርእስት ላይ ሰዎች እንደየግል አስተሳሰባቸው (እንደየሃይማኖት እና የፖለቲካ ተቋማቸውም ጭምር) የተለያየ አስተያየት ይሰጣሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰችው ኢትዮጵያ ግን፥ ዛሬ አነስ ብላ ብትታይም፥ አያሌ አፍሪካውያን ብሔረሰቦችን

የምታጠቃልል፥ ያቺው ድሮ አንድ ታላቅ አገር የነበረችዋ፥ ዛሬ ተቆራርሳ ትንሽ የሆነችዋም ናት።

ኢትዮጵያ ስንል አሁን በኢትዮጵያ የጂኦግራፊ ክልል ውስጥ የሚኖሩትን ሕዝቦች ሁሉ የሚያጠቃልል ቢሆንም፥ ከዛ ውጪ የተቀሩትን አፍሪካውያን፥ በተለይ ደቡብና ሰሜን ሱዳንን አያጠቃልልም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ይሁን። ስለ ቀድሞ ታሪክ ስናወራ፥ የቀድሞውን ኢትዮጵያ የጂኦግራፊ ክልል - እስከ ሳሃራና ሜዲተራኒአን የሚደርሰውን፥ የሳባዎች መኖሪያ የነበረውንም ደቡብ አረብንም እናስበው።

በጥንት ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት ታዋቂ ስለነበረ (2ኛ ነገሥት 19፡9፤ ኢሳ.37፡9..ወዘተ..)፥ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት የሆነውን የአይሁድ ሃይማኖት ተቀብለው በመቆየታቸው፥ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጽፎ ይገኛል። ሆኖም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሁኗን ኢትዮጵያ እንደማያጠቃልል አድርገው የሚያወሩ አሉ። በጥንት ጊዜ የነበረው የጂኦግራፊ ክልል በአሁኑ ጊዜ ካለው የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው። በጥንት ጊዜ በምሥራቅና ሰሜን አፍሪካ ታዋቂዎች የሆኑት ግብጽና ኢትዮጵያ (ሱዳንን ጨምሮ) ነበሩ።

ከኖህ ዘመን በፊት ጀምሮ ከፍተኛ ሥልጣኔ የነበራቸው፥ ከኖህ ዘመን በኋላ የአየር ጠባይ ሲለወጥና እጅግ ሞቃት ሲሆንባቸው፥ ወደ ሰሜንና ምሥራቅ አፍሪካ ተሰደው ከዛ የኖሩ ብሔረሰቦች በሙሉ ኢትዮጵያውያን በመባል፥ ከፍተኛ የሥልጣኔ እድገት ያሳዩ መሆናቸውን ከታሪካዊ መረጃዎች ጋር ማመሳከር ይቻላል።

ከተጠቀሰው የአየር መለዋወጥና የሕዝቦች ስደት በመነሳት፥ ሰዎች ከየት ተነስተው ወዴት እንደሄዱ፥ በየትኛው የጂኦግራፊ ክልል ተወስነው እንደቀሩ መገመት ይቻላል። ሳሃራ በረሃ ሲሆንባቸው፥ ተሰደው የሚሄዱት ውሃ ከዓመት ዓመት ወደሚፈስበት፥ እንዲሁም ቀዝቀዝ ወደሚለው ተራራማ ሥፍራ መሆን አለበት። ይህም ሥፍራ ሊሆን የሚችለው የነጭ እና የጥቁር አባይ ወንዞች ከሚመነጩበት ጀምሮ፥ የሚፈሱበትን ምድር ሁሉ ተከትሎ፥ እስከሚጠልቁበት ባህር ድረስ መሆን አለበት።

በተጠቀሱት ሥፍራዎች አካባቢ ኢትዮጵያና ግብጽ በጥንታዊ ባለ ታሪክነት ይታወቃሉ። በጥንታዊት ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሕዝቦች ወንዝ ተከትለው ከትመዋል፤ በአለም የታወቀ መንግሥታዊ አስተዳደር መሥርተዋል፤ ከልዩ ልዩ አህጉራት ጋር የንግድ ልውውጥ አድርገዋል፤ በሥልጣኔም ታዋቂ ሆነዋል።

ይህንን የከፍተኛ የአባይ ወንዝ ክልል የተባለውን አካባቢ በበለጠ የሚገልጠው ኩሽ የተባለው ቃል ሳይሆን ኢትዮጵያ የተባለው ነው። ኩሽ የተባለው

ቃል የኢትዮጵያን አገሩን ሳይሆን ሕዝቡን ነው የሚገልጸው። የሰውን ዘር እና ጂኦግራፊን ለያይቶ ካለማስቀመጥ መደናገር ይፈጠራል።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የጂኦግራፊ አካባቢን ሲያመለክት (ዘፍ. 2፡13፤ 2ኛ ነገሥት 19፡9፡ አስቴር. 8፡9፥ ኢዮ.28፤19...)። ኩሽ የሚለው ቃል ደግሞ ሕዝቡን ሲያመለክት፥ "ኩሽም ናምሩድን ወለደ.." ዘፍ. 10፡8 በማለት ይለየዋል። አንዳንድ ሰባኪያን እንዲህ ለየብቻ የተቀመጡትን ሁለት ስሞች ካላግባቡ ይጠቀሙባቸዋል።

ኢትዮጵያ (ኤርትራንም፥ ሱዳንንም ጨምሮ) ድሮ የነበረች፥ አሁንም ያለች፤ መንፈሳዊ ታሪካችንም ከጥቁር አፍሪካውያን መንፈሳዊ ታሪክ ጋር የሚዛመድ ነው።

ከፍጥረት ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ፥ ከሙሴ ጀምሮ እስከ ዳዊት ድረስ፥ ከዳዊት ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ዘመንና ከዛም በኋላ፥ እንደ እስራኤል የኢትዮጵያም ስም የተጠራ መሆኑ፥ ኢትዮጵያውያን (ጥቁር አፍሪካውያን ሁሉ) - ሁላችንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሆናችንን ያመለክታል። ከጥንት ጀምሮ መንፈሳዊ ታዋቂነት ያገኘች ይህች አገርም ለጥቁር ሕዝቦች መመኪያ መሆኗን፥ ታቦተ ሕጉን በአካል የሚታቀፉ ቤተ ክርስቲያናት ይመሰክራሉ።

## <u>የመጀመሪያው ስደትና ለውጥ</u>

የጥንቱ ኢትዮጵያዊ በሄደበትና በተሰደደበት ሥፍራ ከአዳምና ሔዋን የወረሰው ቡናማ መልኩ ጭራሽ እስኪጠፋ ድረስ ሲከፋፈል ቆይቷል። ከኖህ በኋላ የመጣውም መከፋፈል በእስያ (ምናልባትም በቱርክ አካባቢ) የተካሄደ አንደኛው መከፋፈል ነበር (ይሆናል)።

ኢትዮጵያውያን ከምሥራቅ አፍሪካ ወደ ሰሜን፥ ወደ ደቡብና ወደ ምዕራብ ተሰደዱ። ከዚያም የተለያየ መልክ አውጥተው ተቀመጡ። ከኢትዮጵያ ያልተሰደዱት የጥንት መልካቸውን ይዘው ቆዩ እንዳይባል፥ የሌሎች ዘሮችን ወደ ኢትዮጵያ መምጣትና መዳቀል ማን ያግደዋል?

ወደ ሰሜን፥ ወደ ደቡብና ወደ ምዕራብ አፍሪካ የተሰደዱ ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን በአየር ለውጥ ምክንያት እንደገና መሰደድ ነበረባቸው። (ይህንን ጉዳይ በሚቀጥሉት ምዕራፋት በሠፊው እንመለከታለን)።

አዳምና ሔዋን በመንፈስ የተፈጠሩት በሰማይ ቢሆንም፥ አካላዊው ሰው ከምድራችን የጀመረ እስከሆነ ድረስ፥ የኛ መነሻ ሥፍራ የጥንቱ ምድራዊው ገነት የት ሊሆን እንደሚችል ከተለያዩ መረጃዎች ማወቅ ይቻላል። በቅድሚያ ግን፥ የሰው ዘር

ከዚህ ተነስቶ እዚህ ደረሰ ከማለት በፊት፥ "የሰው ዘር ከአንድ ቤተሰብ - የዘር ግንድ (monogenism)፥ ወይንስ ከተለያዩ ቤተሰቦች - የዘር ግንዶች (polygenism) ተነስቶ ነው ከዚህ የደረሰው?" ብሎ መጠየቅ አግባብ አለው።

እስካሁን ብዙ ድጋፍ ያገኘው ንድፈ ሃሳብ፡- የሰው ዘር ሁሉ ከአንድ የቤተሰብ ግንድ ተጀመረ የሚል ነው። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ጋር ይስማማል። ያ የመጀመሪያው የሰው ዘር ሦስቱን የሰው አይነቶች ያካተተ መሆኑን እና፥ ከጊዜ ብዛት ቁልጭ ቁልጭ ብሎ የዛሬውን መልክ መውሰዱ የማያጨቃጭቅ ከሆነ፥ በመጀመሪያ የሰው ዘር ከየት ተነሳ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፥ መረጃዎችን በሚከተሉት መንገድ መሰብሰብ ያስፈልጋል።

1) በስነ ቋንቋ (linguistics)፡- ጥንታውያን የአለም ቋንቋዎች እርስ በርስ ይዛመዳሉ። ጥንታውያን የአለም ቋንቋዎች ከጥንቱ የግዕዝ ቋንቋ፥ አገው፥ ኮፕት፤ እብራይስጥ እና ሌሎችም ቋንቋዎች ጋር ያላቸውን ዝምድና በማጥናት የቋንቋዎች ሁሉ ግንድ ወደየትኛው አገር (እንዲሁም ወደየትኛው መነሻ የቋንቋዎች ሁሉ ምሰሶ) እንደሚያመራ መመልከት።
2) በስነ ቅርሳቅርስ (archeology)፡- ከአንድ ሥፍራ ተነስቶ በአለም ዙሪያ - በየአቅጣጫው የተበተነውን የዘመኑን ሰው (modern man - homosapien) አጽም፥ እድሜውን በማጥናት፥ የአጽም ዕድሜ እየጨመረ የሚሄድበትን አቅጣጫ ማገናዘብ።
3) በስነ ባህርይ (genetics)፡- በስነ ቅርሳ ቅርስ የተሰበሰበውን በእድሜ ከፍተኛ የሆነውን አጽም (ከመዳቀል በፊት መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ) የዲ ኤን ኤ ጥናት ማድረግ።
4) ስለ ጥንቱ አየር ሁኔታና ስለ ሕዝቦች ስደት በደንብ ማጥናትና መረዳት።
5) ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከሌሎችም የታሪክ መረጃዎች ማጠናቀርና መመርመር።
6) ከላይ የተጠቀሱትን ጥናቶች በማከናወን መረጃዎችን ሁሉ ማጠናቀርና በስነ አመክንዮ ማያያዝ።

የተጠቀሱትን ዝርዝር ጥናቶች በማጠናቀር፥ የሰው ልጅ በአካሉ የተፈጠረበትን ሥፍራ ማወቅ ባይቻልም፥ ሊሆን በሚችለው ላይ የጠቢባን ግምት ወስዶ፥ በይሆን ይሆናል መደምደም ይቻላል።

የአሁኑ ሁኔታ የጥንቱን እንዳይመስል - ሁሉም በጊዜ ውስጥ እንደሚቀያየር - ሳሃራ ለምለም እንደነበር በአሸዋ ሳይሸፈን፤ መተሃራም ለምለም እንደነበር እሳተ ገሞራ ሳይሸፍነው፤ እንዲሁም ጊዜው እሩቅ ስላልሆነ፤ በዚችው በምድራችን ከአንድ

ሥፍራ ተነስቶ የተበተነውን ሕዝብ ወደ ኋላ መልሶ መመልከቱ ይህንን ያህል ከባድ ላይሆን ይችላል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ለመፈጸም በአዎንታዊነት የሚነሱ ሰዎች እውነቱን ያገኙታል። ይህ መጽሐፍ ይህንን በዝርዝር የማቅረብ ችሎታ የለውም። ሆኖም፥ የሰው መነሻው አፍሪካ ነው ከተባለ፥ "የት ነው ይህ ሥፍራ፥ የጥንቱ የአዳምና ሔዋን መኖሪያ የነበረ? ማነው የጥንቱ ኢትዮጵያዊ፥ አዳምና ሔዋንን የመሰለ?" ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ፥ የአሁኑ የምድር ሰው ሁሉ፥ የጥንቱ ከርታታ ኢትዮጵያዊ ዝርያ ነው፤ እኛም ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር የቀረን የስደት ቅሪቶች ነን - የምንዋደድ ቤተሰቦች - ኦሮማይ፥ ትግራይ፥ አምሃራይ፥ ጉራጌ፥ አፋር፥ ወላይታ፥ ኩናማ..ወዘተ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የተረዳነው፡- አስቀድሞ የሰው ዘር አንድ አይነት እንደነበረ፥ በኋላ ግን በሦስት እንደተከፋፈለ የተማርነው ከሥጋዊነታችን አንጻር ነው። በመንፈሳዊነት አንጻር ግን፥ ደግ ሠሪዎችን ከመጥፎዎቹ ለመለየት እነኚህ የተባረኩ፥ እነኚህም የተረገሙ ብሏቸዋል። አንዳንድ ሰዎችም ይህንን ታሪክ ቀበል አድርገው፡- እነኚህ በከፋታቸው የጠቆሩ ብለው በጥቁሮች ላይ ፈርደውባቸዋል።

ጥቁረትና ከፋትን፥ ደግነትና ንጣትን የሚያዛምዱ ምድራውያን ናቸው። ሥጋዊ አካል የሆነ ፍጡር (ጥቁር፥ ነጭም፥ ቢጫም) ሁሉም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ (መንፈስ የተመላበት) በመሆኑ፤ ሙሉ በሙሉ ክፉ (መጥፎ) ሊሆን አይችልም፤ ደግነትንም ያዘለ ፍጡር ነውና። የሰው ልጅ የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለበት፥ በአካላዊ (በሥጋዊ) ጠባዩ (መልኩ፥ ቀለሙ፥ ገጽታውና ቁመናው ..ወዘተ.) ላይ ምንም አይነት ለውጥ አላስከተለም። ክቡር ቅዱስ የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰውን በመንፈሳዊነት ያሳድገዋል እንጂ፥ በአካላዊ መልኩ አይለውጠውም።

ሥጋዊ አካል በጊዜና በቦታ ብዙ መለዋወጦችን (እድገቶችን) ቢያሳይ፡- በቀለም ከቡናማነት ተነስቶ እስከ ጥቁረት፥ ወይንም ነጭነት ቢደርስ፥ በመልክ ገጽታ አፍንጫው ቢሰፋ፥ ጸጉሩ ቢከረድድ፥ አፍንጫው ቢጠብ፥ ጸጉሩም ቢለሰልስ፥ ይህ ለውጥ አካላዊ ካልሆነው መንፈስ ጋር የተዛመደ አይደለም። መንፈሳዊ ክስተት የራሱ የሆነ የተለየ ሕግ ስላለው፥ የመንፈስ ከምድራዊ ፍጡሮች ጋር መቀላቀል በአካል ለውጥን አላስከተለም። ስለዚህ፥ እገሌ ስለቀላ መንፈስ ቅዱስ አለው፤ እገሌ ስለጠቆረ መንፈስ ቅዱስ ርቆታል ማለት ስህተት ነው።

የመጥፎነት ጠባይ በቆዳ ቀለም የሚለይ ቢሆን ኖሮ (ለምሳሌ፡- ነጭ ሰው ጥሩ፥ ጥቁር ሰው መጥፎ ቢሆን፤ ወይም በተቃራኒው፡- ጥቁር ሰው ጥሩ፥ ነጭ ሰው መጥፎ ቢሆን ኖሮ)፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያዳረሰውን ሕዝብ የእግዚአብሔር መንፈስ ካላዳረሰው ሕዝብ በግልጽ ለይቶ ማወቅ ይቻል ነበር - የጂኦግራፊ

ክልሎችንም በመከተል ከዚህ መለስ የእግዚአብሔርን መንፈስ ያገኙ፥ ከዚህ መለስ ያላገኙ ብለን መከፈሉ ይቀለን ነበር። ግን ይህ አይደለም እውነቱ።

ኃጢአት ከዘር ዘር ሲተላለፍ በመንፈስ እንጂ በሥጋ እንዳልሆነ ሁሉ፥ መንፈስ ለመንፈስ ሥጋም ለሥጋ ነው። ስለዚህ፥ መንፈስ በሥጋ ውስጥ ቢያድር የሰውን መንፈሳዊ ጠባይ ለማሻሻል እንጂ ሥጋዊነቱን ለማስተካከል አይደለም።

ሰው ሁሉ በፍጥረቱ የእግዚአብሔር መንፈስ ይኑርበት እንጂ፥ አጠቃላይ አካላዊ ጠባዩን የሚወስነው፥ በበራሂው ውስጥ የተመዘገበ፤ በምድራዊነቱም "የሰለጠነ"፥ የደግነቱ ወይም የክፋቱ ዝንባሌ መሆን አለበት። ታዲያ፥ ከእውቀት ማነስም ጋር ተባብሮም እየሆነ፥ ሰውና ሰው ሲጠቃቃ ይታያል። ግን ብዙውን ጊዜ ድንቁርና ከሰው አይምሮ ሲገፈፍና በመልካም እውቀት ሲተካ፥ ሰላም፥ ፍቅር፥ አብሮ መኖርና አንድነት ይፈጠራል።

አንድ ኃጢአተኛ ኃጢአት የሚሠራው በፍጥረቱ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለጎደለው ሳይሆን፥ ሥጋዊ-ምድራዊ ጠባዩ ስላመዘነበት ነው ማለት ይቻላል። እኛ ሰዎች ለምን የእግዚአብሔርን መፍቀድና ያለመፍቀዱ ሁሉ ባንድነት እናከናውናለን? እርስ በርሳችን የምንጣላው ለምንድነው? ዘረኛነትና ጥላቻስ ከየት መጣ?

የሰብአዊነት እድገት በማያቋርጥ ለውጥና የእድገት ክስተት ውስጥ ወደ መንፈሳዊ ፍጹማዊነት አልተጠጋም። ሰዎች በአስተሳሰብ መጥቀዋል፤ በሙዚቃ፥ በስነጽሑፍ፥ በሳይንስ፥ ..ወዘተ እጅግ ተራቀዋል (ሥልጥን ብለዋል)። ግን የዛኑ ያህል፥ መዋሸት፥ ተንኮለኛነት፥ ምቀኝነት፥ ስርቆሽ፥ ባጠቃላይ ሰውን የሚያረክስ መጥፎ ሥራዎችን ይሠራሉ።

ሰብአዊነት በሥጋውም በመንፈሱም አንድ አይነት ፍጹማዊ ሥራዎችን እየሠራ እንዲኖር የሚያደርግ ፍጹማዊ አስተሳሰብ እና አኗኗር ካላገኘ፥ ፍጥረት ገና አልተሟላም (አልተገባደደም)። እስካሁን በተነጋገርነው መሠረት፡- እግዚአብሔር ገና በፍጥረቱ አልተደሰተም፤ እኛ ወደ ፍጹምነት ተጠግተን እግዚአብሔርን ስናስደስተው፥ "የዛን ጊዜ" የአለም መጨረሻ ይሆናል - ወደ ፍጹማዊ አለም እንሸጋገራለን።

ሰውን ወደ ፍጹማዊነት የሚያስጠጋውን አስተሳሰብ እና አኗኗር ገና አላገኘንም። ሃይማኖቶች ተስፋፍተው ሕዝቦች በብዛት ወደ መንፈሳዊነት እየተጠጉ ናቸው። ግን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ ደስ እንዲለውና፡- በእውነት እናንት የምወዳችሁ ሕዝቦቼ ናችሁ እንዲለን፤ ፍጹም ሰው ለመሆን (ክርስቶስን ለመምሰል) ገና ብዙ ይቀረናል።

እግዚአብሔር የዱሮ ጊዜ ሰውን (ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ) በመንፈሱ እንዲሻሻል ለማድረግ እጅግ ጥሯል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ በኋላ የሚመጣውን ሰው አስቀድሞ በማየት መሆን አለበት፡፡ “ .. እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ **ዓለሙን** እንዲሁ ወዷልና፡፡” ዮሐ. 3፡16 ሲል፥ እግዚአብሔር በሕዝቦች ሁሉ መካከል ልዩነት እንደማይፈጥርና ሁላችንንም እንደሚወደን፤ ሁላችንንም በመንፈሱ (በክርስቶሳዊነት) አንድ ሊያደርገን ማሰቡን ያመለክታል፡፡

በመሬት ላይ የተበተነ የማሽላ ቆሎ ሲያዩት ደስ የሚል፥ ቢበሉትም የሚጣፍጥ መሆኑን አንድ ሕጻን ልጅ ቶሎ ይገባዋል፡፡ ነገር ግን ያልተቆላ ማሽላ ከታረሰ መሬት ላይ ቢበተን ብዙ የማሽላ ቆሎ ሊያስገኝ እንደሚችል በበለጠ የሚረዳ ከሕጻኑ ልጅ ይልቅ ገበሬው ነው፡፡ ገበሬው በእጁ ማሽላ ዘግኖ ከታረሰ መሬት ላይ ሲረጭ፥ በእያንዳንዱ ማሽላ ውስጥ የሌሎች የብዙ ማሽላዎች ጠባይ እንደሚገኝ፤ በኋላም ለብዙ ጊዜ የማሽላ ቆሎ እየዘገነ እንደሚበላ በመገንዘብ ነው፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፥ የወደፊቱ ሰው ከዛሬው ሰው የሚወጣ ከሆነ፥ በድሮ ጊዜ ሰው ውስጥም የወደፊቱ ሰው ነበር ማለት ነው፤ በዛሬ ጊዜ ሰው ውስጥም የወደፊቱ ሰው መኖር አለበት፤ እግዚአብሔር የወደፊቱን ሰው ሳያይ ሰውን ለማሻሻል በከንቱ አልደከመምና፡፡

ሁላችንም በውስጣችን የፍጹም ሰው ጠባያት ያሉብን፤
እኛው እኮ ነን፤ ያለፈው የወደፊቱም አዳምና ሔዋን፡፡
ከነኃጢአታችን እግዚአብሔር ቢወደን፥
አንድያ ልጁን ለኛ ሰጠን፥
የሰብአዊነት እድገት እጅግ እንዲፋጠን፥
የእግዚአብሔር ሥራው - የድካሙ መሳካት፥
ይህ ነው በመንፈስ ክርስቶስን መምሰል ማለት፥
የመጨረሻውን ሰብአዊነት ለፍጹም ሰውነት ማብቃት፥
አዳምና ሔዋንን ወደገነት ማምጣት፥
ይህ ነው የቀኑ መቃረብ ምልክቱ፥
እግዚአብሔር በፍጥረቱ መደሰቱ፡፡

## ***የስደቶቻችን ምክንያቶች***

የአየር ለውጥ የሚያስከትለውን ችግር ለመወጣት፥ ከጥንት ጀምሮ እንደ መፍትሔ ሕዝቦች የሚጠቀሙት ዘዴ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ነበር። ሰው ሲቸገር መሰደዱ አይቀርም፤ ይህቺም ምድር ለስደት ትመቻለች - ባንድ በኩል ተስፋ ስታስቆርጥ፥ በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ እድል (ተስፋ) ትሰጣለች።

እጅግ በተቃለለ መልክ ስንመለከተው፥ ማንኛውም ነገር (ሕይወት ያለውም ሆነ የሌለው) ምቾቱን ይፈልጋል። ሕዝቦችንም ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርጋቸው የምቾት ፍለጋ ስለሆነ፥ ይህንን ሁኔታ በማጥናት፥ ካሁን ቀደም እንቅስቃሴያቸው እንዴት እንደነበረ መገመት ይቻል ይሆናል።

ቆንጆ ቆንጆ አበቦች ሲመቻቸው ከሜዳ ችፍ ብለው ይበቅላሉ፥ ሲከፋቸው ደግሞ ከዛው ከበቀሉበት ድብቅ ይሉና፥ አመቺ ሁኔታ ሲፈጠርላቸው እንደገና ብቅ ይላሉ። የሰው ልጅ እንደ አበባ ጥውልግ ብሎ እንዳይጠፋ፤ የምድራዊነቱም እውነታ ከሕልውናው ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ ስለ አየሩ ሁኔታ ማወቅ ግዴታ ሆነበት።

ምድር ሉል ክብ ሆና ባንድ በኩል 23.5 ዲግሪ ዘንበል ትላለች። ዘንበል በማለቷ ምክንያት፥ ምድራችን ጸሐይን ስትዞር፥ የሰሜንና የደቡብ ዋልታዎች በመፈራረቅ ወደ ጸሐይ ይጠጋሉ። አንዱ ዋልታ ከጸሐይ ሲርቅ - ክረምት ቀዝቃዛና 24 ሰዓት ጨለማ፤ ሌላው ዋልታ ለጸሐይ ሲቀርብ - በጋ ሞቃትና 24 ሰዓት ብርሃናማ ይሆናል። ምድር ምንም የማታዘነብል ብትሆን ኖሮ፥ ክረምትና በጋ አይኖርም ነበር።

ከዋልታዎቹ ጀምሮ ወደ ምድር መቀነት ባለው ሥፍራ በክረምትና በጋ መካከል የሙቀት ልዩነት ይኖረል። በምድር መቀነት (equator) ላይ ግን የክረምትና በጋ መፈራረቅ አይኖርም። የምድር ዝንባሌ ትንሽ (ከ23.5 ዲግሪ ወደ 21.5 ዲግሪ) ቀነስ ቢል፥ ለምድር ዋልታ የቀረቡት አገሮች በሙቀት ይቃጠላሉ፤ ወይንም የምድር ዝንባሌ ትንሽ (ከ23.5 ዲግሪ ወደ 24.5 ዲግሪ) ቢጨምር በብርድ ይኮማተራሉ።

በተፈጥሮ ውስጥ ተቃራኒዎች ስለሚፈራረቁ፥ ለበራድ ዘመን ምክንያት የሚሆነውን የሚያመጣ ክስተት፥ ተቃራኒው ሙቀት በቅድሚያ እንዲመጣ የሚያደርገውንም ክስተት በማስቀደም ነው። ለምሳሌ፡- ከእያንዳንዱ የበራድ ዘመን በፊት የሞቃት ጊዜ መኖር ነበረበት። የዛን ጊዜ ምድር እጅግ ይሞቃታል፤ ውሃ ከወንዞችና ከሃይቆች፥ ከባህሮችና ከውቂያኖሶች እየተነነ ከአየሩ ላይ ይንጠለጠላል። የተነነው አየር የጸሐይን ሙቀት ይጋረዳታል፤ በዚህም ምክንያት የምድር ሙቀት ይቀንሳል። የምድር ሙቀት ሲቀንስ፥ የተነነው ውሃ በጣም ባልቀዘቀዙሥፍራዎች በውሃ መልክ ይዘንባል፤ በጣም በቀዘቀዙሥፍራዎች ደግሞ በበረዶ መልክ ይወርድና ይከመራል።

ለጥቃቅን የምድር ሙቀትና ቅዝቃዜ መለዋወጥ ይህ አንዱ ምክንያት ቢሆንም፥ በየመቶ ሺህ ዓመታት (አንዳንዴም በየ40 ሺህ ዓመታት) የሚመጣው ከፍተኛው የበራድ ዘመን ለምን እንደሆነ የሚገልጹ መላ ምቶች ብዙ ናቸው።

ከነኚህም መላ ምቶች መካከል፥ ምድር በጸሐይ ዙሪያ የምታደርገው ጉዞ ሲጨምር (ወይንም ጠቅላላ ሰውነቷ ከጸሐይ ሲርቅ)፥ ማለትም ምድር ከጠቅላላ የጠፈር አካላት ጋር በሚኖራት የመሳሳብ ግንኙነት ምክንያት (በተለይ ካጠገቧ ያሉ ፕላኔቶች) በተወሰነ አቅጣጫ የመሳሳብ ኃይላቸው ሲደማመርና ምድርን እየሳቡ ከጸሐይ ሲያርቋት ይሆናል የሚለው መላምት በብዙዎች ዘንድ ይደገፋል።

የአለም ማእከላዊ ሙቀት በሦስት ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንኳን ዝቅ ቢል፥ የበራድ ዘመን በቀላሉ ይመጣል። ባጠቃላይ፥ ከፍተኛም ሆነ መጠነኛ የበራድ ዘመን ሲመጣ ቅዝቃዜው በሚያካልለው ሥፍራ ሁሉ የበጋ ወራት ይቀንሳሉ፤ የአንድ ዓመት ክረምት ከሚቀጥለው ዓመት ክረምት ጋር ይጠጋጋል። በዚህን ጊዜ በአንድ ክረምት የሚከመረው በረዶ ቀልጦ ሳያልቅ ሌላ በረዶ በላዩ ላይ ይከመርበታል። እንዲህ እያለ መሬቱ ሁሉ በበረዶ ይሸፈንና የበረዶው ክምር እንደ ዳሸን ተራራ ይሆናል። የበራድ ዘመን እንዲህ ያለውን የአየር ሁኔታ የሚግለጽ ነው።

መሬት ከተፈጠረች ጀምሮ፥ እስከ ዛሬ ድረስ ይህች ምድር በተለያዩ ወቅቶች ብዙ የበራድ ዘመናት አሳልፋለች። ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የነበሩት የበራድ ዘመኖች ሁኔታ እንዴት እንደነበረ የሚያመለክት የጂኦሎጂ መረጃ ፈዛዛ ስለሚሆን፥ ከሰውም ስደት ጋር ስለማይገናኝ፥ ያንን ትተን፥ ከዛሬ 10 ሺህ ዓመታት አካባቢ ጀምሮ ወደኋላ እስከ ዛሬ 110 ሺህ ዓመት ድረስ የነበረውን ብንመለከት፡-ምድር ጥቃቅን የበራድና የሞቃት ዘመናት (በየ10 ሺህ እና 30 ሺህ ዓመታት) ተፈራርቆባታል። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ሰሜን አፍሪካ፥ የኢትዮጵያን ከፍተኛ ሥፍራዎች ጨምሮ በበረዶ ተሸፍኖ እንደነበረ የሚያመለክቱ የጂኦሎጂ መረጃዎችም ተገኝተዋል።

የበራድ ዘመን እንደ ጥፋት ውሃ ባንድ ጊዜ ብቻ ተፈጽሞ ስላላበቃ፥ በምድራችን ላይ ያስከተለውም ለውጥ ከቦታ ቦታ ይለያያል። ከጥንት (መቶ ሺህ ዓመታት አካባቢ) ጀምሮ፥ ንኡሳን የበራድ ዘመናት እና የሙቀት ጊዜ እንደነበረ ሁሉ፥ የሕዝቦችም መሰደድ ይህንኑ የአየር መለዋወጥን ተከትሎ መሆን አለበት በማለት ነው ስለ ሕዝቦች ስደት የምናጠናው።

ከዛሬ 75 ሺህ ዓመታት አካባቢ ጀምሮ ሰሜን አሜሪካ ዊከሶንያን ተብሎ በሚጠራው ግግር በረዶ ተሸፍኗል። ውር የሚባለው ግግር በረዶም አውሮፓን እስከ ሰሜን አፍሪካ፥ ምናልባትም ሳሃራን ጨምሮ ያዳረሰ ነው። በሌሎች ስሞች የሚጠሩ ሌሎች የግግር በረዶ አይነቶችም ብዙዎች ናቸው።

ምድሪቱ መቀዝቀዝ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ፥ በረዶ ለብዙ ሺህ ዓመታት ሲከማችና ሲከመር ቢቆይም፥ አልፎ አልፎ ምድሪቱ ሞቅ ሲላት በረዶው እየቀለጠ፥ በበረዶ የተያዘው መሬትም ከወደቡብ አቅጣጫ ወደ ሰሜን እየሰፋ ሄዷል። በዚህን ጊዜ ሁሉ ሰዎች ሞቅ ሲላቸው፥ ሰፋፊ መሬቶችንም በመፈለግ ስደት ይጀምራሉ (ሙቀቱ ካየለበት ተነስተው ቀዝቀዝ ወደሚለው ይጓዛሉ)።

ብዙውን ጊዜ በባህር ዳርቻ እየከተሙ የሚኖሩ ሰዎች ካጠገባቸው (ከባህር ውስጥ) ብዙ የሚበላ ስለሚያገኙ የምግብ እጥረት አያጋጥማቸውም። በዚህ ምክንያት፥ ሳይሰደዱ ከባህር ዳርቻ ብዙ ይቆያሉ። ከዚያም ለረጅም ዘመናት ሲኖሩ ይሠለጥናሉ። ግን በአየር ለውጥ እና ከመሬት መንቀጥቀጥ ጋር በተያያዘ ማእበል (ሱናሜ) የባህር ውሃ በላያቸው ላይ ሲደፋባቸው ይጠፋሉ፤ ሥልጣኔአቸውም አብሮ ይወድማል።

ምድሪቱ ቅዝቃዜና ሙቀት ሲለዋወጡባት ምን እንደምትመስል ለማገናዘብ ያህል የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት።

1) ሙቀት ቢያይል በባህርና በመሬት ያለ ውሃ ሁሉ ወደ አየር ውስጥ ገብቶ ከዚያ ይንጠለጠላል። ሁሉም ውሃ ዝናብ ቢሆንና ቢዘንብ መሬት በውሃ ትጥለቀለቃለች፤ አለዚያም ውሃ በበረዶ መልክ ቢወርድ፥ መሬት በበረዶ ተራራዎች ትሸፈናለች፤ የባህርም ከፍታ እጅግ ዝቅ ይላል።
2) በዋልታዎች አካባቢ በበረዶ መልክ የተከማቸ ውሃ ቢቀልጥ፥ የባህሩ ከፍታ ይጨምራል፤ ምድሪቱም በውሃ ትጥለቀለቃለች። የዛን ጊዜ፥ ሞቃቱን አየር የሚያቀዘቅዘው በረዶ ስለሚጠፋ፥ ሙቀት ይጨምራል - የምድር አየር ሁኔታ የበለጠ ይናጋል።
3) ይህ ዛሬ ተገላልጦ የምናየው መሬት፥ ካሁን በፊት (በተለያዩ ጊዜያት) ከባህር በታች እንደነበረ ከዝቅጠ አለቶች አይነት ለማወቅ ተችሏል። ስለዚህ፥ በተለያዩ የከርሰ ምድር እንቅስቃሴዎች ምክንያት የቆዳ መሬት መዛባት ሲፈጠር፥ ከፍተኛ የባህር ከፍታ እንደሚፈጥር በጂኦሎጂ ጥናት ይታወቃል።
4) የባህር ከፍታ በሚጨምርበት ወቅት ደሴቶች አይኖሩም፤ የባህር ከፍታ ዝቅ ብሎ በቆየበት ወቅት፥ ዛሬ የምናያቸው ደሴቶች እርስ በርስ የተያያዙ ሰፋፊ መሬቶች ነበሩ።

## ***ስደቶቻችን ከኖህ በፊት***

በጂኦሎጂ ጥናቶች የተረጋገጠውን የበራድ ዘመን እና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን ስለ ኖህ ዘመን የተጻፈውን ገለጻ እንደ መነሻ በማድረግ፥ ስለ ሕዝቦች እንቅስቃሴ በአይነ ሕሊና እንመለከታለን።

የዛሬ አስር ሺህ ዓመት አካባቢ በራድ ዘመን (የበረዶ መከመር) አብቅቶ የበረዶ መቅለጥ የጀመረበት፥ ሞቃትና የዝናብ ዘመን እንደነበረ በሳይንስ ምርምር (isotope hydrology) ታውቋል። በኖህ ዘመን የነበረ የጥፋት ውሃ ምድርን ቢያጥለቀልቅ፥ ከውሃ ዝናብ ሌላ የበረዶውም መቅለጥም አንድ ተጨማሪ ምክንያት እንደነበረ ይገመታል።

የሕዝቦች ስደት በተደጋጋሚ የተፈጸመ መሆን አለበት ስንል፥ በተለይ እንቅስቃሴዎቹ የሚያይሉት በተወሰኑ የጂኦግራፊ ክልሎች እንደሚሆንም በመገመት ነው።

በጥንት ዘመን በውቂያኖሶች ላይ ሰዎችን የሚያጓጉዝ መርከብ ሊኖር አይችልም ነበር። ስለዚህ ሰዎች ከእስያ ተነስተው ወደ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ፥ እንዲሁም ወደ አውስትራሊያና ወደ ኒውዚላንድ የተጓጓዙት በደረቅ መሬት በእግራቸው መሆን አለበት። በደረቅ መሬት ከተጓዙ፥ ክፍላተ አህጉራትን የሚያገናኝ ደረቅ መሬት መኖር ነበረበት። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

በኖህ ዘመን የነበረ የውሃ መጥለቅለቅ ከመጨረሻው (የዛሬ 10 ሺህ ዓመት) የበረዶ መቅለጥ ጋር የተያያዘ ከሆነ፥ ይህንን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደተከሰተ አቢይ የአየር ለውጥ መቁጠር ይቻላል። የሰው ዘር ሁሉ ባንድ ጊዜ ጥፍት ብሎ ከጥፋት ዘመን በኋላ በኖህና ቤተሰቡ ብቻ ተጀመረ ብንል ግን፥ እስካሁን የተነጋገርንበትን ሁሉ ያፈርሰዋል።

በአንድ የተወሰነ ወቅት የምድር አየር ሞቃት ነበር። በዚህን ጊዜ ከባህር ብዙ ውሃ እየተነነ ሰማይን ጋረደ፤ ተመልሶ በውሃ መልክ ወደ ባህር በመፍሰስ ፋንታ ወደ በረዶነት ተለወጠ። የተነነው ውሃ ጠጣር በመሆን ከአንድ ሥፍራ የተከማቸው በበራድ ዘመን ነበር። በዚህ ምክንያት ጠጣሩ በረዶ እስኪቀልጥና ወደ ባህር እስኪገባ ድረስ፥ የባህሩ ከፍታ እስከ 119 ሜትር ዝቅ ብሏል (ይህ በሚከተሉት ገጾች ተብራርቷል)። መቅለጥ ከጀመረበት ከ10 ሺህ ዓመታት ጀምሮ እንደገና የባህሩ ከፍታ እየጨመረ መጥቷል።

የአለምን ካርታ ብንመለከትና፥ እንዲሁ በሃሳባችን የአሁኑን የባህር ከፍታ አሁን ካለበት ትንሽ ዝቅ ብናደርገው፥ በሰሜን ዋልታ በኩል አሜሪካና እስያን፤ በደቡብ ምሥራቅም ዛሬ ብዙ ደሴቶች በሚታዩባቸው ኢንዶኔዢያ በኩል እስያን

ከአውስትራሊያና ከኒውዚላንድ ጋር የሚያገናኝ ደረቅ መሬት አይታጣም። የሰው ልጅ በነኚህ ደረቅ መሬቶች በእግሩ በመጓዝ መኖር ከሚቻልበት ሥፍራ ሁሉ ደርሶ ለብዙ ሺህ ዓመታት ኖሯል።

የባህር ውሃ እንደቀነሰ ስለማይቆይ፥ ከዋልታዎች የተከማቸ ጠጣሩ በረዶ ስለቀለጠና ተመልሶ ከባህር ስለገባ፥ የባህር ከፍታ ጨመረ፥ ስለዚህ አያሌ ረባዳ መሬቶች ከውሃ በታች ሆኑና ከፍ ከፍ ያሉ መሬቶች ብቻ ቀርተው ደሴቶች ሆኑ።

የባህር ከፍታ የሚጨምርበት ሌላም ምክንያት ይኖራል። ይኸውም፥ በጂኦሎጂ ጥናቶች እንደሚታወቀው ሁሉ፥ አህጉራት ሲቀራረቡ፥ የባህር መደብ ቆዳ መሬት ሲቀንስ - የባህር ውሃ መቀመጫው ሲነፈገው - የግድ ከፍ ብሎ ወደ ደረቅ መሬት መሰደድ አለበት። ለምሳሌ፥ አፍሪካ ከአሜሪካ ሲሸሽ ወደ አውሮፓ ተጠግቷል። አንዳንድ ጊዜ ይህንን የመጠጋጋት ክስተት የመሬት መዛባት (fault) ያባብሰዋል። አፍሪካ ወደ አውሮፓ በመጠጋት ክስተት ላይ እንዳለና፥ የመሬት መዛባትም ሲፈጠር፥ በሜዲተራኒያን ባህር በታች ያለ ቆዳ መሬት ቀነሰ። ይህ ቆዳ መሬት ሲቀንስ፥ ባህር መቀመጫ ሥፍራ ተነፈገው። ባህር መቀመጫ ሥፍራ ሲነፈገው ወደ መሬት ይወጣና ረባዳ ቦታዎችን ያጥለቀልቃል። ይህ በጂኦሎጂ የጊዜ አቆጣጠር ከዝቅጠ አለቶች መዝቀጥ ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ የአትላንቲስ ሰዎች (በሜዲተራኒያን ባህር ዙሪያ ይኖሩ የነበሩ) የጠፉት፥ ሥልጣኔአቸውም ውድም ያለው በዚህ መንገድ ሳይሆን አይቀርም።

እንዲሁም በተቃራኒው፥ አህጉራት ሲራራቁ፥ የባህር መደብ ቆዳ መሬት ሲሰሽ፥ የባህር ውሃ መቀመጫው ሲለቀቅለት፥ የግድ ዝቅ ይላል። ነገር ግን ይህ በጂኦሎጂ የተጠቀሰው የባህር ከፍና ዝቅ ማለት በምድር ሥፍራዎች ሁሉ ከቦታ ቦታ የሚሸጋሸግ ስለሆነ አንድ ወጥ ሊሆን አይችልም (አድሎአዊ ነው)።

ጠቅላላ ምድርን የሚመለከት ለውጥ (ሉላዊ ሙቀትና ቅዝቃዜን በተመለከተ የሚመጣ የባህር ከፍና ዝቅ) ሊፈጠር የሚችለው ከምድር ውጪ በሆነ ኃይል ስለሆነ፥ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ሲለዋወጥ የነበረ የአየር ጠባይ የባህርን ከፍታ ሲጨምርና ሲቀንስ ቆይቷል። የሕዝቦችም እንቅስቃሴም ይህንኑ የቅርብ ጊዜውን የአየር ለውጥ ተከትሎ ነበር።

ከጥፋት ውሃ በፊት ወደ አውስትራሊያና አሜሪካ የተሰደዱ ሰዎች አሁን መታየታቸው አለመጥፋታቸውን ነው የሚያመለክተው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሃሳብ አይቃረንም። ነገር ግን በቀድሞ ጊዜ "ምድሪቱ" በማለት የተጠቀሰው የሚያመለክተው አለምን በጠቅላላ አለመሆኑን፤ "የሰው ልጅ ሁሉ በኃጢት ተበከለ" ሲልም በተለይ በአንድ አካባቢ የሚኖሩትን ሕዝቦች (በባህሮችና በውቂያኖሶች ዳርቻ

የሚኖሩትንም) በአንክሮ ለማመልከት እንጂ፥ ጠቅላላ በአለም ዙሪያ (አሜሪካና አውስትራሊያን ጨምሮ) የሚኖሩትን ሕዝቦች ሁሉ ላይሆን ይቻላል።

ከስነ ቅርሳቅርስ (archeology) መረጃ ሌላ፥ የሰው ዘር ከአፍሪካ ተነስቶ አለምን ያዳረሰ መሆኑን የሚያመለክቱ በቂ ድጋፎች ከስነ ባህርይ (genetics) እና የስነ ቋንቋ (linguistics) ምርምሮች በመገኘታቸው የጥንታዊ ስደቶችን አቅጣጫ እንደሚከተለው ለመገመት ተችሏል።

- ከመሃል አፍሪካ ኢትዮጵያን አልፎ በባቤል መንደብ በኩል ባህረ ኤርትራን (ቀይ ባህርን) አቋርጦ፥ አራቢያን በመሻገር ወደ እስያ የገባ፤
- ከመሃል አፍሪካ ኢትዮጵያን፥ ኤርትራን፥ ሱዳንን እና ግብጽን አልፎ፥ ባህረ ኤርትራን (ቀይ ባህርን) አቋርጦ ወደ ፓለስታይን እና እስራኤል በመሻገር ወደ እስያ እና ወደ አውሮፓ የገባ።
- ጥቂት ሕዝቦች ወደ እስያ ገብተው ከዚያ ከተባዙ በኋላ፥ በአራቱም ማዕዘናት የተበተኑ።

እውነተኛውና የተረጋገጠው የሰው ዘር (የዘመኑ ሰው) በአለም ሁሉ የተዳረሰው ከአፍሪካ የዛሬ መቶ ስልሳ ሺህ ዓመታት አካባቢ እንደሆነ ከመሬት ተቆፍሮ ከወጣው የዘመኑ ሰው አጽም እድሜ መገመት ተችሏል[60]።

አጽሞች ከአፍሪካ ሲርቁ እድሜአቸውም ይቀንሳል። ከኢትዮጵያ (ኦሞ ሸለቆ) እና ከሌሎችም የአፍሪካ አገሮች ውጪ የተገኙ ተመሳሳይ የዘመኑ ሰው አጽሞች ሁሉ እድሜአቸው ሲቆጠር፥ ከአፍሪካ አገሮች ከተገኙ አጽሞች እድሜ የሚያናንሱ ናቸው። ለምሳሌ፥ ከእስራኤል የተገኘው አጽም መቶ ሺህ ዓመት፥ ከአውስትራሊያ የተገኘውም ባለ አርባ ሺህ ዓመት ነው። አጽሞች ከአፍሪካ ሲርቁ እድሜአቸውም እየቀነሰ ከመጣ፥ የስደቱን አቅጣጫ ሊያመለክት ይችላል። ሌሎች መረጃዎችን እና ተጨማሪ ገለጻዎችን ከሌሎች ምንጮች ይከታተሏል።

[60] ከተለያዩ ምንጮች የተለያዩ ግምቶችም ይኖራሉ።

## ***ሥልጣኔ ከኖህ በፊት***

ከኖህ በፊት፥ በተለያዩ ጊዜያቶች፥ በረዶ እንደሚከመርና እንደሚቀልጥ ተመልክተናል። በረዶው ሲቀልጥ ከሥሩ የነበረ አፈር ይለሰልሳል። በአሁኑ ጊዜ በበረሃነት የሚታወቁ ሥፍራዎች (ለምሳሌ ሳሃራ እና ጎቢ) በረዶው በቀለጠ ጊዜና ከዛ በኋላ የተለያዩ እጽዋትን የሚያበቅሉ፥ ልዩ ልዩ እንስሳትም የሚኖሩበት አመቺ ሥፍራ እንደነበር የሚጠቁሙ አያሌ ሳይንሳዊ ጥናቶች (isotope studies) ተካሂደዋል። በዚህ አይነት የሳሃራን ለምነትና የቀድሞ አፍሪካ ሥልጣኔ፥ የጎቢን ለምነትና የአካባቢውን ነዋሪዎች ሥልጣኔ፥ የአትላንቲስን መጥፋት፥ በታሪካዊ መረጃነት ለሚቀርቡት ሁሉ የአስተሳሰብ ክፍተት በመስጠት እንመልከተው።

የሰዎችን መሰደድ፥ የሥልጣኔአቸውንም መጥፋት፡- እነ ክሮ ማኞን (የጥንት የዋሻ ሰዎች)፥ እነ ትዋረግን (በሰሜን አፍሪካ የበርበር ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች)፥ እነ ቫስኮችን (በሰሜን እስፓኛ የሚኖሩ)፥ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ የሚኖሩ ነባሮችን እና ሌሎችንም በአንድ ታሪካዊ እንቅስቃሴ ለማገናኘት ብንሞክር፥ የተፈጥሮን አካላዊ ክስተቶች በቅደም ተከተል ከማገናዘብ ጋር መሆን አለበት።

ስለዚህ፥ የሰዎችን እልቂት እና የሥልጣኔ መውደም ከእልቂት ለሚተርፉትም የስደታቸውን ሁኔታ፥ ከባህር ከፍታ ጋር በተያያዘ መንገድ ለማገናዘብ ይረዳን ዘንድ በሚከተሉት በሦስት ደረጃዎች የተከፈለውን የባህር ጥልቀት እንመልከት።

1) የአህጉር እርከን (continental shelf)፥ ከባህር በታች፥ በማእከላዊ ግምት፥ ለሰባ ኪሎሜትር ያህል በመጠኑ ዘቅዘቅ ያለ ሜዳ ነው። ይህም ሥፍራ በአንድ ኪሎሜትር የአግድሞሽ ርቀት ውስጥ 1.7 ሜትር ብቻ ወደ ታች ዝቅ ይላል።
2) የአህጉር ቁልቁለት (continental slope) - የአህጉር እርከን በድንገት ከሚያቆለቁልበት ጀምሮ ያለው ወጣ ገብ ሥፍራ ነው። ይህም ሥፍራ በአንድ ኪሎሜትር ርቀት ውስጥ 70 ሜትር ያህል ዝቅ ይላል።
3) ጥልቅ ሜዳማ ሥፍራ (abysaal plain) - ከባህር ዝቅተኛውና ጥልቁ ሥፍራ ነው።

ከተጠቀሱት ሦስት ከባህር በታች የሚገኙ የመሬት ቅርጾች መካከል፥ አህጉራት እንዲህ ከመለያየታቸው በፊት የሚኖረውን የአህጉር ወሰን (የስንጥቁን የመሬት ቅርጽ) በበለጠ የሚያንጸባርቀው የአህጉር ቁልቁለት (continental slope) ነው። ይህም ማለት፥ ክፍለ አህጉራትን እንደቀድሟቸው መልሰን ብናገጣጥማቸው፥ በትክክሉ ግጥምጥም የሚሉት አሁን በካርታ ላይ እንደሚታየው

ሳይሆን፥ ከአህጉር እርከን ላይ (continental shelf) የባህሩ ውሃ ሲነሳለት የሚቀረው፥ የአህጉር ቁልቁለት (continental slope) ከሚጀምርበት ድንበር ይሆናል ማለት ነው። ይህንን የአህጉር ቁልቁለት የሚጀምርበትን ከፍታ እንደ መነሻ በመቁጠር፥ እስከ ዛሬ በባህር መጥለቅለቅ ስለተፈጸመው ጉዳት ሚዛናዊ ግምት መውሰድ ይቻላል።

ከኖህ በፊት፥ መሬት በበረዶ በተሸፈነችበት ወቅት የባህሩ ከፍታ እጅግ ዝቅ ብሎ መቆየቱን፥ በዚህም ምክንያት ሰዎች ከአንድ ክፍለ አህጉር ወደሌላ እንደተሰደዱ ጠቅሰናል። የባህሩ ከፍታ ለምን ያህል ጊዜ ዝቅ ብሎ እንደቆየ በደንብ አይታወቅም።

በኖህ ጊዜ (የዝናቡ ዘመን - የዛሬ 10 ሺህ ዓመታት አካባቢ) በዘነበ ዝናብ የተከማቸ ውሃ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ የተከማቸ በረዶ ቀስ በቀስ ሲቀልጥ የውቂያኖስና የባህር ከፍታ ይጨምራል። የአህጉር እርከን (continental slope) እስከ 70 ኪሎሜትር ያህል በመጠኑ ዘቅዘቅ ያለ ሜዳ ሥፍራ ስለሆነ፥ ለሕዝቦች መኖሪያ የሚስማማ ሥፍራ እንደነበረና፤ በዚህም ሥፍራ ብዙ ሕዝቦች እንደኖሩ ይገመታል።

የአህጉር እርከን (continental shelf) በአንድ ኪሎሜትር የአግድሞሽ ርቀት ውስጥ 1.7 ሜትር ብቻ ወደ ታች ዝቅ እንደሚል ጠቅሰናል። ከዝናቡ ዘመን በኋላ ባህሩ ለ119 ሜትር ያህል ከፍ ቢል፥ 70.6 ኪሎሜትር የሚሆን ደረቅ መሬት (የአህጉር እርከን በሙሉ) በውሃ ይሸፈናል ማለት ነው። በዚህን ጊዜ ከውቅያኖሶችና ከባህሮች ዙሪያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችና ሥልጣኔአቸውም ውድም ይላል።

በተጠቀሰው የውሃ ከፍታ ሊዋጡ የሚችሉ ረባዳ ሥፍራዎች ብዙዎች መሆናቸውን የመሬትን ከፍታ ከሚያሳይ የአለም ካርታ (bathymetric maps) መመልከት ይቻላል። ከነኚህ ሥፍራዎች መካከል፥ የሳሃራ በረሃ አንዱ ስለሆነ፥ በኖህ ዘመን የተጠቀሰው የጥፋት ውሃ ያጥለቀለቀው በቀጥታ የሚያመለከተው በተለይ ይህንን ሥፍራም ይሆናል ማለት ነው።

ከባህር ጋር በቀጥታ የማይገናኙ መሬቶች የሚጠቁት በቀጥታ በሚዘንበው ዝናብ በሚያስከትለው የውሃ ከፍታ እና በጎርፍ መጥለቅለቅ ስለሆነ፥ ለአርባ ቀናት በተከታታይ ቢዘንብ በከፍተኛ ሥፍራዎች የሚኖሩ ሰዎችም በውሃ የሚዋጡበት ሁኔታ ይኖራል።

በሜዲተራኒያን የባህር ውሃ የተሸፈኑ የሥልጣኔ ደረጃን የሚያበሥሩ ቅሪቶች (ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችና ሃብቶች፥ የሸክላ ሥራዎች..ወዘተ..) መታየታቸው፥ ካሁን በፊት የባህር ከፍታ እጅግ ዝቅ ብሎ ሰዎች ከውቂያኖስና ከባህር ዙሪያ ይኖሩ እንደነበረ፥ በኋላ ግን እንደሰጠሙ ይጠቁማል።

በሳሃራ በረሃ አካባቢ ከሚገኙ አንዳንድ ዋሻዎች ውስጥም፥ ሳሃራ ብዙ ወንዞች የነበሩት፥ የፈረሶች መፈንጫ፥ የከብቶችና ሌሎች ለማዳ እንስሳትም መኖሪያ - ለም ሥፍራ እንደነበረ የሚያመለክቱ ስዕሎች ተገኝተዋል[61]።

ምናልባት ከባህር በታች ሰጥሟል የሚባለው አትላንቲስ ባንድ በኩል የአውሮፓውያንን ሥልጣኔ ቢያመለክት፥ በሰሜን አፍሪካም የበርበር ሥልጣኔ በመባል ከሚታወቀው የአፍሪካውያን ሥልጣኔ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆናል።

ሳሃራና ሰሜን አፍሪካ - ከባህረ ኤርትራ (ከቀይ ባህር) ጀምሮ እስከ አትላንቲክ ድረስ ብዙ ረባዳ ሥፍራዎች ያሉትና የባህር አሸዋም አልፎ አልፎ የተከመረበት ነው። የተፈጥሮን ተለዋዋጭ ጠባይ ከማገናዘብ ጋር፥ የሜዲተራኒአን አካባቢ፥ ጥንታዊት ኢትዮጵያ - ሳሃራ - አራቢያ - ኢራቅ - ኢራን.. በኖህ ጊዜ ሰዎች የከተሙበትና በከፍተኛ ሥልጣኔ ለረጅም ዘመናት የቆዩበት መሆኑን መገመት ይቻላል።

ሳሃራ ለም በነበረ ጊዜ በደቡብ ሳሃራ የሚገኝ የአፍሪካ መሬት ሁሉ የአውሬዎች እንጂ የሰው መኖሪያ አልነበረም። አፍሪካውያን ሁሉ የሚኖሩት በጥንታዊት ኢትዮጵያ (ሳሃራን ጨምሮ) መሆን አለበት። የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ዙሪያ ሰብሰብ ብለው ነበር የሚኖሩት፤ ቀስ በቀስ መሆን አለበት ወደ ደቡብ የተሰደዱት (ነፃ አስተያየት)።

የመጨረሻው የበራድ ዘመን ከማለቁ አስቀድሞ (በረዶው ሳይቀልጥ)፥ ሰሜን አውሮፓና ሰሜን እስያም ነፍሳት ዝር የማይሉበት የበረዶ አገር ብቻ ነበረ (ቀስ በቀስ ነው ወደ ሰሜን የተሰደዱት)። የዛን ጊዜ ሰዎች የሚኖሩት ከአውሮፓ በስተደቡብ፥ ከእስያም ከበስተደቡብ አካባቢ መሆን አለበት። ስደት የተጀመረው የመጨረሻው የበራድ ዘመን ካለቀ በኋላ ብቻ ነው ማለታችን አይደለም።

የበራድ ዘመናት እና የሞቃት ዘመናት በተፈራረቁ ቁጥር ስደቶች እንደሚኖሩ፥ በተቀሩት አለማትም (አሜሪካ፥ አውስትራሊያና ሌሎችም ሥፍራዎች) ሰዎች እንደተሰደዱ ልብ ይሏል።

---

[61] Researchers uncovered the Garamantes' walled towns, villages, and farms after poring over modern satellite images—including high-resolution pictures used by the oil industry—as well as aerial photos taken during the 1950s and 1960s. https://news.nationalgeographic.com/news/2011/11/111111-sahara-libya-lost-civilization-science-satellites/

ዋነኛውና የመጨረሻው የስደት ጉዞ የመጨረሻው የበራድ ዘመን ካበቃበት ከዛሬ አስር ሺህ ዓመት (ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት) ተገባደደ። ከዚህ የበራድ ዘመን በኋላ የባህር ከፍታ እጅግ ስለጨመረ፥ ወደ አሜሪካና አውስትራሊያ የተሰደዱ ሁሉ፥ ከመጡበት ተመልሰው መሄድ አልቻሉም። ስለዚህ ከተቀረው አለም ጋር ግንኙነት ሳይፈጥሩ፥ የራሳቸውን ሥልጣኔ ለራሳቸው ብቻ አድርገው ቆዩ። እንደየአካባቢያቸው ተጽንኦ በአካላዊ ቁመና (በመልክ፥ በቆዳ ቀለም..) በአኗኗር፥ በባህል፥ በልምድ፥ በሃይማኖት እና ባጠቃላይ የሕብረተሰብ አኗኗር የተለያዩ ሆኑ።

በመረጃዎች ተረጋግጦ የተመዘገበ የሰዎች ታሪክ ወደኋላ የሚዘልቀው ከክርስቶስ ልደት በፊት ግፋ ቢል እስከ 4000 ዓመት ድረስ ስለሆነ፥ ከኖህ ዘመን በፊት የሕዝቦች እንቅስቃሴ እንዴት እንደነበር ብዙ አይታወቅም። በዚህ ጉዳይ ላይ አያሌ ጸሐፊዎች የሚመስላቸውን አስፍረዋል። ነገር ግን ወደ እውነት የሚጠጋውንና ከእውነት የራቀውን መለየቱ ለብዙ ሰዎች ቀላል አይደለም።

በእርግጥ ስለሕዝቦች እንቅስቃሴ ብዙ ያልታወቁ ጉዳዮች እንዳሉ እናውቃለን። አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆች የሃቀኛ አርኪዎሎጂና የአንትሮፖሎጂ ተመራማሪዎችን ሥራ እየለቀሙ፥ እነርሱ ወሬ ለማጣፈጥ ሲሉ፥ የራሳቸውን አስተያየት እየጨማመሩና እያጋነኑ፥ ከጥቃቅን ሃቆች ተነስተው፥ ወይንም የተዛቡ መረጃዎችን ይዘው ቀስ በቀስ ወደ ልብ ወለድ ታሪክ ያመራሉ። ለነርሱ ተስማሚ የሆነውን ሃሳብ ሲያሰፉ እንደመረጃ የሚያቀርቡት ብዙዎችን ያሳስታል።

ለምሳሌ፥ እሳተ ገሞራ ከባህር በታች ሲፈነዳ የቀለጠው አለት በቶሎ ስለሚቀዘቅዝ ቶሎ ቶሎ ጠቅለል ጠቅለል እያለ የትራስ መልክ ይወስድና ይደራረባል። እነርሱ ይህንን በትራስ መልክ የረጋ ቅልጥ የእሳተ ገሞራ ድንጋይ (pillow lava) ሲያዩ፥ ይህ በቀድሞ ሥልጣኔ፥ ሰዎች የገነቡት የፈራረሰ ግንብ ነው ይላሉ።

የቦካ መረሬ ጭቃ በጸሐይ ሙቀት ሲሰነጣጠቅ ባለ ስድስት ማእዘን ቅርጽ እንደሚያወጣ ሁሉ፤ በረባዳ ወይም በሜዳ ላይ (ከባህርም በታች) በመፍሰስ በብዛት የተከመረ ቅልጥ የእሳተ ገሞራም ቶሎ ሲቀዘቅዝና ቅዝቃዜው ከላይ ወደታች ሲዛመት፥ በስድስት በስድስት ማእዘን እየሆነ ይሰነጣጠቃል። እነርሱ ይህንን ሲያዩ፡- የጥንት ሰዎች ድንጋዩንም እንዲህ አስተካክሎ ለመሰንጠቅ የሚያስችል ከፍተኛ ሥልጣኔ ነበራቸው በማለት ይደመድማሉ።

በሙቀትና ቅዝቃዜ መለዋወጥ፥ እንዲሁም በነፋስና በውሃ አንዳንድ አለቶች (በተለይም ኦብሲዲያን) በቀላሉ ይሸራረፍና ስለታማ ይሆናሉ። እነርሱ የተጠረበ የሚመስል ትናንሽ ድንጋይ ባገኙ ቁጥር፥ ይህ በድንጋይ ዘመን የነበሩ ሰዎች የተጠቀሙበት የጦር መሳሪያ ነው ይላሉ።

ባለማወቅም ሆነ አውቆ በመዋሸት፥ አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆች፥ አዋቂ መስሎ በመታየት እንጀራቸውን ያበስላሉ (እውነተኛ አርኪዎሎጂስቶችን አይመለከትም)። ወደ ፍጹም እውነት፥ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ያዋቂዎችን፥ የፈላስፎችን እና የሃይማኖት መሪዎችን እርዳታ እንሻለን። ቢረዱን መልካም ነው፤ ትክክለኛ እርዳታን የማናገኝ ከሆነ ግን፥ እውቀቱም ባይኖር፥ ከእግዚአብሔር ጋር የራስን እውነት መርምሮ መጓዝ ይሻላል።

አንባብያን ከዚህ የተጻፈውን የሕዝቦች እንቅስቃሴ (ስደት) ሲያነቡ የሚመስለውን ከማይመስለው እንዲለዩ በማሳሰብ ነው። “ከጥንት ጀምሮ ሕዝቦች በምድራዊነታቸው ያደረጉት አካላዊ እንቅስቃሴ እንዴት ነበረ?” ማለታችን፥ “ከጥንት ጀምሮ ሕዝቦች በመንፈሳዊነታቸው ያደረጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዴት ነበር?” ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፋናል። ብዙ ባናውቅም፥ ሊያያዙ የሚችሉ እውቀቶችን አካብተናልና፤ ብናገናኛቸው፥ ምናልባት ለማወቅ በሚኖረን ከፍተኛ ጉጉትና ሃሳብ በማብዛት፥ አንዳንድ ለእውነት የሚጠጉ መረጃዎችን እናገኝ ይሆናል በማለት፥ ለወደፊትም (በአራተኛ መጽሐፍ) ስለምንነጋገረው የመንፈሳዊነታችን ጉዳይም መሠረት ለመጣል ነው ጥረታችን።

## ሥልጣኔ ከኖህ በኋላ

በተፈጥሮአችን ጥበብን (እውነትን) ካለችበት ለማግኘት እንጥራለን፤ ግን በብዙ ተቃራኒ ሃሳቦች እንዋጥና ከዚህም ከዛም የምንይዘውና የምንጨብጠው ስናጣ አንዳንዶቻችን እንጨነቃለን። ሰው ጥሩ ያስባል፤ ጥሩ ከማሰብ ጥሩ ነገር ይወጣል። ለዚህ ነው ለማወቅ ብለን የምንጨነቀው፤ አውቀንም ለሌላው - ለዚህ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ያወቅነውን ለማስተላለፍ የምንፈልግ።

እንግዲያውስ፥ ከኖህ በፊት የነበሩ ሰዎችም እንደኛ አሳቢዎች ናቸውና፤ እነርሱ ያወቁትን ሁሉ ለኛ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ አስተላልፈውልናል (ይሆን?)። ለዚህ ነው (ይሆን?) ባጭር ጊዜ ውስጥ ከዚህ ደረጃ የደረስነው? እስቲ በቅድሚያ ይህንን እንመልከት።

ዛሬ (ባንድ አፍታ) የአለም ሕዝብ ሁሉ ጠፍቶ በምትኩ ሌላ ሕዝብ ይፈጠራል ቢባል፥ ያ የሚፈጠረው ሕዝብ ሥልጣኔ ከድንጋይ ዘመን ወደ ብረት ዘመን ቀስ በቀስ ቢያዘግም ይሻላል? ወይንስ አሁን እኛ የምናውቀውን በትንሹም ቢሆን አውቆ፥ ሥልጣኔው ቢፋጠንለት ይሻላል።

በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ተንቀሳቃሾችን ሁሉ በየወገናቸው ሁለት ሁለት (ተባትና እንስት) እየሆኑ የሚገቡበት ባለ ሦስት ደርብ (ፎቅ) መርከብ (ዘፍ. 6፡16) ለመሥራት የሚያበቃ መሳሪያውን (መዶሻ፥ መጋዝ፥ ምስማር፥ ወዘተ.)፥ ኖህ ከጥንት ሰዎች የወረሰው መሆኑን መገመት ይቻላል። ምስማርና መዶሻን ለማዘጋጀት የተወሰነ ሥልጣኔ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ሰብአዊነት ከዚህ የሥልጣኔ ደረጃ መድረሱ ከኖህ በፈለቀ ሥልጣኔ ብቻ አለመሆኑን፤ አካላዊና መንፈሳዊ ሃብትን ከኖህ በፊት ከነበሩ ሰዎችም የወረስን መሆኑን እናገናዝባለን። ኖህ ለኛ ያወረሰን ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ የወጣውን የሰው ዘር አይነት (ነጭ፥ ቢጫና ጥቁር) ብቻ ሳይሆን፥ የነርሱንም የቀድሞ ሥልጣኔ ጭምር መሆን አለበት (ነፃ አስተያየት)።

“ነገር ግን፥ ከኖህ በፊት በምድር ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በከፍተኛ ሥልጣኔ ያለፉ ቢሆን ኖሮ፥ የነርሱን የሥልጣኔ ቅርስ መሬት በተቆፈረ ቁጥር በብዛት ተከማችቶ በቀላሉ እናገኘው ነበረ፤ አለማግኘታችን አለመሠልጠናቸውን ይነግረናል” ይባል ይሆናል። ግን እኮ የጥንት ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ ካልሆነ፥ ከመሬት የሚገኘውም መረጃ የዛኑ ያህል አነስተኛ ነው የሚሆን። ከዚህም በላይ፥ ብዙዎቹ ይኖሩበት የነበረ ሥፍራ አሁን በባህር ከተሸፈነ፥ መረጃዎችን ከዛ ቆፍሮ ማግኘት ያስቸግራል።

ሄኖክ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ጠፈርን ሲዞር የቆየው በአካላዊ መንገድ ከሆነ፥ ከኖህ በፊት የነበረው አካላዊ ሥልጣኔ በእርግጥ ከዛሬው አካላዊ ሥልጣኔ ይበልጣል ማለት ነው። ወይንም ሄኖክ ያን ያህል ጊዜ በጠፈር የቆየው በመንፈሳዊ መንገድ ከሆነም፥ ከርሱ በፊት የነበረው መንፈሳዊ ሥልጣኔ በእርግጥ ከዛሬው መንፈሳዊ ሥልጣኔ ይበልጣል ማለት ነው። ምናልባት ስለ ቀድሞ ሰዎች ሥልጣኔ ጥቂት ፍንጭ ይሰጠን እንደሆን የሄኖክን መጽሐፍ በድጋሚ እንመልከት።

“ይህ የዘመኑ እውቀት፥ በውስጡ ሰይጣናዊ ጠባይ ይኖረዋል፤” የሚሉ እንደሚኖሩ ሁሉ፥ ሄኖክም ማንነታቸው ስላልታወቀ (መላእክት ወይም ሰዎች)፥ ከነርሱ ያልተጠበቀውን፥ የነርሱን ሥልጣኔ ለሰዎች አስተላለፉላቸው ብሎ እነርሱን በብዛት ሲወቅሳቸው፥ እንዲህ ይላል፡-

“ከብዙ ዘመናት በኋላ፥” ሁለት መቶ መናፍስት (ደቂቀ ሴት) እና አለቃቸው ስማዝያ ወደ መሬት በመጡ ጊዜም ለሰው ልጅ ብዙ- ብዙ ነገር አስተማሩ። “የተሠወረ ጥበባቸውን ሁሉ አስተማሯቸው፤ ለሰዎችም በጥቁር ቀለም በወረቀት መጻፍን አስተማሯቸው። ሰዎች የተፈጠሩት እንደ መላእክት ንጹሐን ጻድቃን ሆነው ይኖሩ ዘንድ ነው እንጂ፤ ሰዎች ለእንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠሩም። ... ስለዚህ ነገር ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘላለሙ፥ እስከዚያች ቀን ድረስ ብዙ ሰዎች ይስታሉ።” ሄኖክ 19፡23 - 24

ይገርማል! ይህ አወቅን የምንለው እውቀት ሁሉ እንደመሳት ይቆጠር ይሆን? በእርግጥ ሰዎች እንደ መላእክት ጻድቃን ሆነው ሊኖሩ የሚችሉት በሰማይ ነው፤ በመሬት ግን በተለያዩ ሥራዎች ሲሰማሩ የተወሰኑ እውቀቶችን ማወቅ ግዴታ ይሆናል (ምድራዊ እውነታ)። ስለዚህ፥ ሄኖክ፥ “ሰዎች የተፈጠሩት እንደ መላእክት ንጹሃን ጻድቃን ሆነው ይኖሩ ዘንድ ነው” ሲል፥ ምድር ከመፈጠሯ በፊት አስቀድሞ በሰማይ በመንፈስ የተፈጠረውን ሰው ያመለክታል ማለት ነው የሚቀለው።

ያም ሆነ ይህ፤ እኛ የመጽሐፉን ትርጉም (ከአባቶች) ስንመረምር፥ የወሰድነው ሁለት አማራጭ ብቻ ነበረ።

1) አዎ! ሄኖክ የሚያወራው ከደብረ ቅዱስ (ከመንግሥተ ሰማይ) ስለወረዱ መላእክት ነው አልን።
2) አይ! ሄኖክ እኮ የሚያወራው ስለ መላእክት ሳይሆን፥ በዚሁ በምድር ስለሚኖሩ ሰዎች ነው አልን።

ሦስተኛ አማራጭ ቢኖር - ሰማያውያን (መላእክት) በምድራችንም ቢመላለሱ - ይህንን ጉዳይ ድፍን አደረግነው። የሄኖክ መጽሐፍ የማናውቀው ነገር

ሊኖር እንደሚችል ይጠቁማል እንጂ፥ ወደ እውቀት ጎዳና ስተት አድርጎ የሚከት አይደለም (እየተመራመሩ እውነቱን ማግኘት የኛ ፋንታ ነው)።

መቼም ሰው እርግጠኛ ስላልሆነበት ጉዳይ በግልጽ አያወራም እንጂ፥ እንዳው ከማናውቀው ጋርም ቢሆን፥ የሰው ሥጋው በአፈር፥ በድንጋይና በበረዶ ክምር ቢቀበርም፥ የሰው መንፈሱ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ብቻ ሳይሆን፥ ከአንድ የጥፋት ዘመን ወደ ሌላው የሚስተላለፍ መሆኑንም ነው፥ በውስጠ ልቦናችን የምናስበው።

እርሱ (ያ ሕዝብ) የሚያውቀውን (ትንሽም ብትሆን) ለሚቀጥለው ሕዝብ ለማስተላለፍ መንፈሱ (የዛ የድሮው ሰው መንፈስ) ዝም ብሎ እንደማይቀመጥ፥ እውቀትም በተለያየ መንገድ ለሰዎች እንደሚገለጥ፤ መንፈስም እንደ አካል ሥራውን መሥራት እንደሚችልና፤ ከኖህ በኋላ ባንድ ጊዜ ስለተላለፈልን ሥልጣኔም ነው፥ በውስጠ ልቦናችን የምናስበው።

ያም ሆነ ይህ፥ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ የጥንቱ ምድራዊ ሰው በምድራዊነቱ ምክንያት ተጨናቂም ሆነና (ለቤተሰቡ ለወገኑ የሚያስብም ሆነና)፥ ብረት ማቅለጥን፥ የጦር መሳሪያ መሥራትንም ተማረና፤ ሰው መግደልንም በደንብ አድርጎ አወቀበት።

የሕዝቦች ቁጥር ቢቀንስም፥ የሥልጣኔ እድገት ከፍ - ከፍ እያለ መሄዱን አላቋረጠም። ከኖህ የእልቂት ዘመን በኋላ የአየሩ መለዋወጥ እና የመሬቱም በጎርፍ መጥለቅለቅ አፈሩን ለሰብል ተስማሚ ሳያደርገው አልቀረም። መሬት በግብርና ሲለማና ምርት ሲትረፈረፍ፥ የንግድ ሥራም አብሮት ስለተስፋፋ፥ ሰዎች ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሱ ጀመር። እቃዎቻቸውንም ለገበያ ሲያቀርቡ፥ በዚያውም ሙያቸውን በማሳየት እውቀታቸውን ያካፍሉ ነበርና፤ ተሰባስበው በሚከትሙበት ሥፍራ ሁሉ፥ የነዋሪዎቹን እውቀትና ሥልጣኔ ወደ ከተማ በሚገቡና በሚወጡ ሰዎች አማካኝነት ከቦታ ቦታ አዳረሱት።

በአንጻሩ፥ ከከተማ ራቅ ብለው የሚኖሩት የሥልጣኔ ተካፋይ ለመሆን ስላልበቁ፥ እጅግ ወደኋላ ቀርተው ነበርና፥ በሰለጠኑትና ባልሰለጠኑት መካከል የጎላ የእውቀት መራራቅ ተፈጠረ። ብልጦች የሆኑት ኑሮአቸውን ካለማቋረጥ ሲያሻሽሉ፥ በየዱሩና በየጫካው የሚኖሩት ግን እያደገ ከሚሄደው ሥልጣኔ ጋር አብሮ መራመድ አልቻሉም። ብልጦቹ ሞኞቹን እያስገደዱ የራሳቸው ኑሮ ማሟያ አደረጓቸው።

ዘረኛነትና ባሪያ መግዛት ከእንዲህ ያለው "ሥልጣኔ" ጋር የተያያዘ በመሆኑ፥ የባሪያ ስርአትና ሥልጣኔ አብሮ ይጓዝ ጀመር። ይህ በዚህ እንዳለ፥ በአንድአንድ አካባቢ በጦር ስልት የበላይነት ያላቸው፥ በሥልጣኔ ግን ኋላ ቀሮች (barbarians)

የሆኑት፥ በየጊዜው ወደ ከተማ እየመጡና ሕዝቦችን በመውረር፥ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሱ ነበር።

ከጥፋት ውሃ በኋላ፥ ሕዝቦች በየአህጉራቱ ተበታተኑ፤ መንግሥታትም በያለበት ግዛታቸውን አስፋፉ፥ ኃይላቸውንም አጠናከሩ። በአለም ላይ የጦር መሳሪያ መሥራትና ጦርነት በረከተ። ሰዎች እየወገኑ መጣላት ጀመሩ። ያንዱ ወገን ሌላውን እየወጋ፥ አገር መቀማት፥ ሃብት ንብረት መዝረፍ፥ የተገዢውን ወገን ከግር በታች ረግጦ መግዛት የኑሮ ዘይቤ ሆነ። በዚህን ጊዜ (ጭንቅና መከራ ሲበረታ) የሰው ልጅ በሁለትነቱ ሲኖር ሥጋዊ ደማዊ የሆነው አካሉ ለመከራ፥ መንፈሳዊ የሆነው ደግሞ፥ ለዘለአለም ደስታ የተመደበ መሆኑን የሚያሰላስልበት አይምሮው የሰላ ሆነ።

በአንድ የተወሰነ ወቅት፥ ከብዙ ሕዝቦች መካከል፥ የተወሰኑ ሕዝቦች ከምድራዊነትና ከጦርነት ይልቅ መንፈሳዊነትና ሰላማዊነትን የመረጡ ስለነበሩ፥ እነርሱ ያቆዩልን መንፈሳዊ ሥልጣኔ እስከዛሬ ድረስ በየገዳማቱ ይታያል።

መጠነኛ የአየር ለውጥ በአንድ ሰው እድሜ እንኳን ያየነውና የምናውቀው ነው፤ ለምሳሌ፥ በፈርኦን ጊዜና ከዛም በኋላ የተለያዩ የድርቅ ዘመናት እንደነበሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተምረናል። በአሁኑ ጊዜም በበረሃነት የሚታወቁ ሥፍራዎች (ለምሳሌ ሳሃራ እና ጎቢ) "ከተወሰነ ጊዜ" በኋላ፥ ያንን ለም ሥፍራ እንዳልነበረ የሚያጠፉ በተከታታይ የድርቅና የረሃብ ዘመን አጋጥሟቸዋል።

የሳሃራ በረሃ ካሁን ቀደም ለም እንደነበረ፥ በዛ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችም ሥልጡኖች እንደነበሩና፥ የግብጻውያን ሥልጣኔም በሰሜን አፍሪካ ከመስፋፋቱ አስቀድሞ ከዚሁ የሳሃራ አካባቢ ይኖሩ ከነበሩ የአፍሪካ ሰዎች እንደተጀመረ፥ ይህ ቀደም ብሎ በደንብ ያልታወቀ ታሪክ አሁን አሁን ታዋቂ እየሆነ መጥቷል[62]።

ከጊዜው መርዘም የተነሳ፥ በጽሑፍ ያልተመዘገበ ሁሉ ተረስቶ ይቀራል። ለምሳሌ:- ከተወሰኑ ዓመታት በፊት (የግብጾች ሥልጣኔ ተብሎ ከሚታወቀው በፊት) የነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ አይታወቅም። ነገር ግን፥ በጥንታዊ ግሪኮች አፈ-ታሪክ እጅግ ዝነኛ የነበረ አንድ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበረ። የእርሱን እና የቤተሰቡን ስሞች የሰው ልጅ ምንጊዜም እንዳይረሳ በጠፈር ከዋክብት ስሞች ተመዝግቦለታል[63]። ታዲያ፥ የሜሶፖታሚያ (ኢራክ) የቀድሞ ሥልጣኔ እና የሌሎችም የቀድሞ

---

[62] http://www.ablongman.com/stearnspreview/pdf/chapter_9.pdf

[63] https://starchild.gsfc.nasa.gov/docs/StarChild/questions/88constellations.html

ሥልጣኔዎች መነሻ ከሕዝቦች ስደት ጋር የተያያዘ መሆኑን፤ ሰው ሲሰደድ ሥልጣኔውንም ይዞ እንደሚሰደድ የምናስበው ከሆነ፥ ለም በነበረ የሳሃራ ግዛት የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ሲሄድ፥ የአየሩ ጠባይ ሲቀየር፥ ለማዳ እንስሳት (ላም በሬ፥ ፍየልና በግ፥ ፈረስ ..ወዘተ..) የሚመገቡት ሳርና ቅጠል የሚያበቅል የዝናብ መጠን እየቀነሰ ሲመጣ - ድርቅ ሲሆን፥ ነባር አውሬዎችም ወደ ደቡብ፥ ወደ ምስራቅና ወደ ምዕራብ ሲሰጋሸጉ፥ ሰዎችም ተከትለዋቸው ሄደዋል (ተሰደዋል) ማለት ነው።

ለድርቅ ምክንያት የሆነ የአየር ለውጥ (ሙቀት) ቀስ በቀስ ለምለም የነበሩትን የሳሃራ አካባቢዎች አደረቃቸው። የጸሐይ ንዳድ የሰውን ቆዳ ሲያቃጥለው ሳርና ቅጠሉም በአሸዋ ሲሸፈን፥ የሳሃራ በረሃ የአፍሪካን ነዋሪዎች (ኢትዮጵያኖች) ከሁለት ከፈላቸው።

ያ ዝቅተኛ (ረባዳ) የሳሃራ መሬት፥ ከጥንቱም - በኖህ ጊዜና ከዛ በፊት - ባህር ያልራቀው ሥፍራ ስለነበረ፥ የአሸዋ ክምር በዝቶበታል። አየሩ ሲደርቅ - ዝናብ ሲጠፋ፥ ነፋስ በነፈሰ ቁጥር አሸዋው ከመሬት እየተነሳ፥ እጽዋቱን እና ሌሎች ከስደት የተረፉ ነፍሳቶችን ሁሉ እየገረፈ ገደላቸው።

ከሳሃራ በስተደቡብ የሚገኘ የአፍሪካ ምድር በበረዶ ያልተሸፈነ፥ አየሩም በድርቅ ያልተጠቃ ስለሆነ ነው የእንስሳት ሁሉ መፈንጪያ - ነፍሳማ ምድር የሆነው። ከሰሳራ በስተደቡብ የዘመቱት አፍሪካውያን (ኢትዮጵያኖች) ትግል ብዙውን ጊዜ ካውሬዎች ጋር ነበር። በአውሮፓና በእስያ የዘመቱት የጥንት አፍሪካውያን (የዛሬ ሌሎች ሕዝቦች) ትግል ግን ብዙውን ጊዜ ሰው ከሰው ጋር ነበረ። የሁሉም የጦር መሳሪያዎቻቸው አይነት እና ማሕበራዊ ኑሮአቸውም በከፊል የሚያንጸባርቁት ይህንኑ የፍትጊያ ኑሮ ነው።

ወደ ደቡብ የተሰደዱ አፍሪካውያን (ኢትዮጵያኖች) ግን፥ ከእንስሳት ጋር እንጂ፥ እርስ በርሳቸው ሳይጣሉ ለብዙ ሺህ ዓመታት በሰላምና በነፃነት ኖረዋል። ቅኝ ገዢዎች መጥተው እስኪገድሏቸው ድረስ በድሎት ሰንብተዋል፤ በመጠኑ እያረሱ፤ እያደኑ፤ ከብትም እያረቡ። በምቾት ተረጋግተው ተቀምጠዋል፤ የተመጣጠነ ምግብ (ፍራፍሬ፥ ዳቦ፥ ሥጋ) እየበሉ፤ እየሳቁ፤ እየተጫወቱ፤ እየዘፈኑ እና እየደነሱ።

ከደቡብ አፍሪካ ጀምሮ እስከ ሰሜን አፍሪካ ድረስ፥ የጥንት አፍሪካ ሕበረተሰቦች በወቅቱ ከነበረው የአለም ሥልጣኔ በንግድ ልውውጥ ይገናኙ እንደነበረ፥ መንግሥታቱም ታዋቂዎች እንደነበሩ፥ ብዙ ታሪካዊና የቅርሳ ቅርስ ማስረጃዎች ይገኛሉ[64]።

---

[64] https://link.springer.com/article/10.1023%2FA%3A1021659928822

ወደኋላ መለስ ብለን በደቡብ ሳሃራ ዙሪያና የሚያካልለውን መሬት (የዛሬዪቱን ኢትዮጵያን - ኤርትራን እና ሰሜን ሱዳን ጨምሮ) ምን እንደሚመስል ከታሪካዊ ማስረጃዎች ብንመለከት፥ ሁሉም ለምለም እንደነበረ እንረዳለን። ታዲያ፥ በዘመናችን በተደጋጋሚ በድርቅ የተጠቃች አገራችን ኢትዮጵያ፥ በከፍታዋ ምክንያት፥ ከመቶ ዓመት በፊት እስከ ኖህና ከዛም በፊት እጅግ ለም እንደነበረች እንገምታለን።

የሳሃራ ድርቀት እየሰፋና እየጠበበ በየጊዜው የሚለዋወጥ ነበረ። ይህ የሳሃራን አካባቢ የሚለዋውጥ የአየር ሁኔታ ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያን ያላጠቃበት (ሌሎቹን እንዳጠቃቸው ማለት ነው) ዋና ምክንያቱ፥ የኢትዮጵያ መሬት አቀማመጥ በዙሪያዋ ካሉ አገሮች ሁሉ ከፍ ያለ በመሆኑና ቀዝቃዛ አየር የሚነፍስበት ስለሆነ ነው።

አሁንም ቢሆን የአፋርና የኢሳ ረባዳ ሥፍራዎች ብዙ የማይዘንብባቸው በረሃማ ናቸው። ከዚሁ የኢትዮጵያ በረሃማ ሥፍራ ተያይዞ የአረብ፥ የኤደን ግዛቶችም (ሰናይ እና ኔጌቭን ጨምሮ) ዛሬ በረሃማ ቢሆኑም፥ ከኖህ የጥፋት ውሃ ዘመን አስቀድሞ እና ከዛም በኋላ የሳሃራ በረሃ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ለም እንደነበረ መገመት ይቻላል።

የመተሃራ እሳተ ገሞራ መሬቱን ሳያቃጥለው በፊት (ከአንድና ሁለት መቶ ዓመታት በፊት)፥ አካባቢው ሁሉ የጤፍ አገር እንደነበረ፥ ነዋሪዎቹም በድሎት ይኖሩ እንደነበሩ ይነገራል።

በኢትዮጵያና ባካባቢዋ ዛሬ በረሃማ የሆነ ሥፍራ ሁሉ ካሁን በፊት ለም ነበረ ብንል፥ በዛው አንጻር እጅግ ከፍተኛ ከተባሉት ተራራማ ሥፍራዎችና በመለስተኛ ከፍታ የሚገኙ ሥፍራዎችም እጅግ ለም እንደሚሆኑ በመገመት ነው። ታዲያ በጥንት ጊዜ የሰው እና የተለያዩ አውሬዎችን መኖሪያ በዚሁ የተለያየ ከፍታ ብንመድበው፤ የሰዎቹ መኖሪያ ሥፍራ በአፋርና በኢሳ በረሃዎች ዳርቻ ወደ ተራራው ተጠግቶ እንደሚሆን መገመት ይቻላል (ሜዳማና ገላጣ ሆኖ ለም ስለሆነ፥ ትንሽ ሞቅም ስለሚል)።

ሙቀትን የሚመርጡ አውሬዎችም እንዲሁ ወደ ዝቅተኛው ሥፍራ ይኖራሉ፤ ብርድ የማያስጨንቃቸውም በከፍተኛው ሥፍራ ይኖራሉ። ሁሉም በተፈጥሮ ሃብት ተደስቶ ይኖር ነበር። ከጊዜ ብዛት የሰው ብዛት እየጨመረ ሲሄድ፥ ሰዎች ከሜዳማው ሥፍራ እየለቀቁ፥ በጫካ በተዋጡ ከፍተኛ ሥፍራዎች፥ ተራራዎችና ሸለቆዎች መካከል መኖር ጀመሩ።

ከጊዜ በኋላ፥ በተራሮቿ በስተግርጌ - በዝቅተኛ ሥፍራዎቿ ዙሪያ እንደ ገነት ባለ ሥፍራ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ፥ የአየሩ ጠባይ ሲቀየርባቸውና ካለመጠን

ሲሞቃቸው ወደ ከፍተኛ ሥፍራዎች ዘመቱ (ሳባውያንና ሌሎችም)፤ ከዚያም የተለያዩ የእጽዋትና የእንስሳት መኖሪያ የነበረውን ሥፍራ ለራሳቸው መኖሪያ ሥፍራ ሲያዘጋጁት፥ አወደሙት።

ዛፉ ሲመነጠር፥ ነባር አውሬዎችም በአዳኞች ወደ ደቡብ ሲባረሩ፥ የአየሩ ጠባይ እየተቀየረ መጣ። ኢትዮጵያ ምንም ከፍተኛ ሥፍራ ባይኖራት ኖሮ፥ የሱዳን በረሃና አፋርና ኢሳ፥ እንዲሁም የአረብ በረሃ በአየር ጠባይ ይገናኙ ነበር።

ኢትዮጵያ እንደ ሳሃራ ረባዳ ብትሆን ኖሮ፥ እስካሁን አንድም ነፍስ አይተርፍ ነበር። ግን አሁንም እስከ ሜዲተራንያን ባህር ድረስ ነፍስ የሚዘሩ፥ ከተራራዎቿ የሚፈልቁ ውሃዎች አልደረቁም። ስለዚህ፥ የግብጻውያን ሥልጣኔ እየተባለ የሚነገረን (የጥንት ግብጻውያንን የሚያጠቃልል የአፍሪካውያን - የኢትዮጵያኖች ጥንታዊ ሥልጣኔ ) በሳሃራው የበረሃ ቃጥሎ ምክንያት እንዳይቋረጥ፥ ወደ ዛሬዪቷ ኢትዮጵያችን ሄደና ተስፋፋ፤ ከዚያም ቆየ - ከጥንት ዘልቆ ወደ ዘመናችን ደረሰ። ተመስገን።

እንግዳ ተቀባይ አገራችን ከጥንትም ቢሆን ሰውን ብቻ ሳይሆን እንስሳውንም ጭምር ነበር ስታስተናግድ የቆየች። እስካሁን በቅደም ተከተል የተዘረዘሩት የአየር ሁኔታ መለዋወጦች በጊዜና በቦታ ያመሳከርነው እንደሆነ፥ ኢትዮጵያ በተለያዩ ከፍታዎቿ ምክንያት ምንጊዜም ሰው የሚያስኖር የአየር ጠባይ እንደነበራት፤ ሰዎች ከአፍሪካ ወደ እስያ ቢሰደዱም፥ ከኢትዮጵያ ሲደርሱ ከዚያው መኖርን ሳይመርጡ እንዳልቀረ፤ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ የአፍሪካ እና የእስያን ሕዝቦች ከጥንት ጀምሮ ያገናኘች፥ እንግዳ ተቀባይና መተላለፊያ አገር (ኬላ) እንደነበረች፤ ሥልጣኔዋም ከጥንታውያን ሥልጣኔዎች ጋር የተመሳሰለው ለዚህ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

ባጠቃላይ፥ ከፍተኛውን የአጽሞች እድሜ የሚያበስሩት ከኢትዮጵያ የተገኙት ከሆኑ፥ ቀደም ሲል የገለጽናቸውን የተፈጥሮ መለዋወጦችም በማከል፥ ምንጊዜም ከኢትዮጵያ ምድር ሰው እንዳልጠፋ ለመገመት ችለናል።

የሳሃራን አካባቢ ሥልጣኔ በሁለት ከፍለ ዘመናት ከፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. ከኖሕ በፊት (ከዛሬ 10 ሺህ- 7 ሺህ ዓመት በፊት) የነበረ ሥልጣኔ፤ በኋላ በውሃ መጥለቅለቅ የጠፋ፤
2. እና ከኖሕ በኋላ (ከዛሬ 7 ሺህ- 4 ሺህ ዓመት በፊት) የነበረ ሥልጣኔ፤ በኋላ በንዳድ ተቃጥሎ እና በአሸዋ ተሸፍኖ የጠፋ።

በነዚህ በሁለት ጊዜያት ውስጥ፥ ሥልጣኔ (የግብጽ እና የሌሎችም የሰሜን አፍሪካ አገሮች ሥልጣኔ) ከተጠቀሱት የተፈጥሮ አደጋዎች ራሱን ለማዳን ሲል የግድ ወደ ከፍተኛ ሥፍራ መሄድ ነበረበት።

ታዲያ፥ የግብጽ ሥልጣኔ (ከኖሕ በፊትና ከኖሕ በኋላ) ከዜሮ ተጀመረ ከማለት ይልቅ፥ በከፍተኛ የኢትዮጵያ ሥፍራዎች ለረጅም ጊዜ በመኖር፥ ቀደም ብለው በሰለጠኑ፥ በኢትዮጵያውያን ተጀምሮ ተዛመተ ማለት ነው የሚቀለው። ይህንን ለታሪክ ተመራማሪዎች እንተዋለን።

ወደ መጽሐፍ ቅዱሳችን መለስ ብለን፥ ስለሰው መባዛትና ስለ ስደት የሚጠቁም መኖሩን ስንመረምር፥ የሚከተለውን እናገኛለን፡-

"ኩሽም ናምሩድን ወለደ፤ እርሱም በምድር ላይ ኃያል መሆንን ጀመረ። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ ነበረ፤ ስለዚህም፡- በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ። የግዛቱም መጀመሪያ በሰናዖር አገር ባቢሎን፥ ኦሬክ፥ አርካድ፥ ካኔል ናቸው።" ዘፍ.10፡8-10

የጥቁር ዘር (የኩሽ ዘር) ከአፍሪካ ጋር የተያያዘ ከሆነ፥ በቅደም ተከተል የተቀመጠውን የጥቁር ዘር መሰደድና ወደ እስያ መግባት፥ ከዚህም በላይ፥ የኩሽ ልጅ ናምሩድ በምድር ላይ ኃያል መሆኑን፥ በእግዚአብሔር ፊትም ጎላ ብሎ መታየቱን፥ ከዚህ ጥቅስ ማገናዘብ አያቅትም።

ይህ የሆነው መቼ እንደነበረም ተገልጿል። ኢትዮጵያዊው/አፍሪካዊው(?) ሄኖክ ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት ነበረ። የኩሽ ልጅ ናምሩድም ታዋቂ የሆነው ከኖህ የጥፋት ውሃ በኋላ ነበረ። እንግዲያውስ ቀደም ሲል የገለጽናቸውን ጽንሰ ሃሳቦች ሁሉ ከዚሁ ጥቅስ ጋር ብናያይዛቸው፥ የናምሩድ ግዛት ወደ ምሥራቅ የተስፋፋው ከአፍሪካ በመነሳት መሆኑን ገሃድ ያደርገዋል።

ከዚሁ የግዛት መስፋፋት ጋር ተያይዞ፥ የሥልጣኔ (የባህል፥ የሃይማኖት፥ ባጠቃላይ የሥጋዊና መንፈሳዊ ኑሮ) መጀመር፥ መስፋፋትና መዛመት ግዴታ ይሆናል። ለምሳሌ፥ በህንዶች ሃይማኖት እጅግ ዝነኛ የሆነው ሽሪ ክሪሽና[65] የቆዳው ቀለም ጥቁር ሰማያዊ እንደሆነ ይነገራል። የእርሱ ቤተሰቦች ከየት ነበር አመጣጣቸው? መልሱን ለተመራማሪ አንባቢያን እንተዋለን።

የአሁኑ ሉላዊ የአየር ሙቀት እየተባባሰ ሲሄድ፥ የተመነጠሩት ጫካዎችና ደኖች ካልተመለሱ በስተቀር፥ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራዎች እንደ ጥንት ሰውን የማዳንና የማስተናገድ ችሎታ እንደማይኖራቸው አንባቢ ይመልከተው።

[65] Bhaktivedanta Swami Prabhupada A.C (His Devine Grace), 1972, 1983:

እስቲ እንመልከታት ጥንታዊት ኢትዮጵያን፥
ከጂኦግራፊ - ከታሪክ እንመርምር ምክንያቱን፥
እንዲህ ልዩ ያደረጋትን፥
ሰው እና እንስሳትን ከንዳድ ያተረፈችበትን፥
አሳድጋ ያቆየችበትን፥
ስደተኞችን ያስተናገደችበትን።
　　እናጥናው ባለ ታሪክ ሆኖ የቆየውን፥
　　ሕዝቡን ሃይማኖቱን፥ አየሩን፥
　　ወንዙን፥ ሃይቁን ጫካውን፥..
　　ባለ አደይ አበባ መሬታችንን፥
　　ከዓመት ዓመት ያቺን መስከረምን እየጠበቀ የሚበቅልበትን፥
　　ጤፍ ተዘርቶ የሚታጨድበትን፥
　　የጠፋውን፥ የቀረውን - የወጣውን፥ የገባውን፥
　　አንድላይ ሁሉንም እናስበው፥
　　እጽዋቱን፥ እንስሳቱን፥ እንዲሁም ሰውን።
አዎ! አንዳንዴም አንዘንጋ ወደ ኋላ መመልከቱን፥
ምድራዊና መንፈሳዊ ሥልጣኔአችንን፥
ከኖሕ በፊት የነበረውን፥ ከኖሕም በኋላ የቆየውን።
ያልተቀየረውን፥ የተቀየረውን፥
መልሚያችንን - መጥፊያችንን፥
የሕዝቦችን አኗኗር፥ አስተሳሰባቸውን።
ከሁሉም በላይ፥ አንዘንጋ፥
በምድራዊ ሥልጣኔን ብትበለጥ አገራችን፥
መንፈሳዊው ሥልጣኔ ነው የኛ ትልቁ ሃብታችን፥
ከፍ ከፍ የሚያደርገው ልባችንን።

በጠቅላላ በአለም ላይ የሚኖሩ (የተሰደዱትም ያልተሰደዱትም) ባሳለፉት ዘመናት ሁሉ ከትውልድ ትውልድ የተላለፈላቸው የሥልጣኔ እድገት በቁስ አካል ብቻ ሳይሆን በመንፈስም ጭምር መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም፥ የተሰደደው ከምድራዊነት

ጋር ባደረገው ፍትጊያ እና አብሮት ባለው በመንፈሳዊነቱ፤ ያልተሰደደውም ካካባቢው የሸመተውን የኑሮ ዘይቤ እና አብሮት ባለው በመንፈሳዊነቱ - ሁሉም በየበኩሉ የደረሰበትን ምድራዊና ሰማያዊ የእውቀት ደረጃ፥ ለመገመት የሚያስችል ሚዛን የለንም።

ስለ ሕብረተሰቦች ሥልጣኔ እና ኋላ ቀርነት የምንሰጠው አስተያየት ሁሉ ከምድራዊነት አንጻር ብቻ ከሆነ፥ አስተያየታችን የተዛባ ከመሆን አያመልጥም። ግን ብዙውን ጊዜ ለእውነት የምንጠጋው፥ አንድ ወጥ ከሆነ ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰብ በመነሳትና በመንፈሳዊ ምጥቀት፥ በጥቅል በጥቅሉ ስንመለከተው ስለሆነ፥ እስካሁን የተዘረዘሩትን ሃተታዎች በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች እናጠቃልላለን።

- ስለ አየር ሁኔታ ማወቅ ከሥልጣኔ ሁሉ የቀደመ ሥልጣኔ ነውና፥ ከጸሐይ ጋር ሌሎችም የጠፈር አካላት የምድራችንን አየር መለዋወጥ የሚወስኑ መሆናቸውን የጥንት ሰዎች ተገንዝበውታል። ለዚህም እንደማስረጃነት የሚያገለግሉ፥ አንዳንድ የከዋክብትን ጉዞ ለመከታተል የሚረዱ ትላልቅ የድንጋይ ክምሮችና ተቋሞች (አንደ እስቶን ሄንጅ፥ ፒራሚዶች፥ ወዘተ. ያሉ ምልክቶች) እስከ ዛሬ ድረስ አሉ።
- ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት፥ የሰዎች ሥልጣኔ በባህር ዙሪያ በከተሙ አገሮች "ከፍተኛ ደረጃ" ደርሷል፤ ሕዝቦቹም ጥሩ ኑሮ የሚኖሩና ጤነኞች ነበሩ፤ በተሰጣቸው ረጅም እድሜ ብዛት የሚያካብቱት እውቀትም የዛኑ ያህል የላቀ ነበረ።
- የመጨረሻው የበራድ ዘመን ካበቃበት ከዛሬ አስር ሺህ ዓመት (ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት)፥ በምድር የአየር ጠባይ መለዋወጥ ምክንያት የሰው ልጅ ከቦታ ቦታ ሲሰደድ ቆይቷል። በዚህም ምክንያት ቀስ በቀስ በእግሩ ያደረገው ጉዞ ከአፍሪካ አውጥቶ እስከ ኒው ዚላንድ፥ አውስትራሊያ፥ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ አድርሶታል።
- የመጨረሻው ከፍተኛ የስደት ጉዞ የመጨረሻው የበራድ ዘመን ካበቃበት ከዛሬ አስር ሺህ ዓመት (ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት) ተገባደደ (የዘመኑ ስደት የፖለቲካ ስደት ነው)።
- ከኖህ የጥፋት ውሃ በኋላ፥ አየር ሲሞቅ፥ በረዶ ሲቀልጥ የባህር ከፍታ ሲጨምር፥ በደረቅ መሬት ላይ በእግር መጓዝና መሰደድ ቀነሰ። ሆኖም፥ በመሬት (በእግር ጉዞ) ሊገናኙ የሚችሉ ሁሉ እየተገናኙ በደህና ጊዜ የንግድ ልውውጥ ሲያደርጉ፤ መጠነኛ የአየር ለውጥ ሲኖርና ሲቸገሩም ከቦታ ቦታ እየተሰደዱ ቆይተዋል። በዚህን ጊዜ ሁሉ ሕዝቦች ከሕዝቦች

ጋር ጦርነት እየገጠሙ እርስ በርስ መጋጨትና መጨራረስ የተለመደ ነበር።

- ከኖህ የጥፋት ውሃ በኋላ፥ የኩሽ ልጅ (የናምሩድ) ግዛት ከአፍሪካ በመነሳት ወደ ምሥራቅ ተስፋፋ።
- በሳሃራ አካባቢ በረሃማነት ምክንያት ከሳሃራ በስተደቡብ የኖሩ አፍሪካውያን በመሬት (በእግር ጉዞ) በቀጥታ ወደ ሰሜን መጓዝ ስላልቻሉ ኑሮአቸውን በራሳቸውና ለራሳቸው እንደሚስማማ አድርገው - የራሳቸውን ሥልጣኔ ለራሳቸው ብቻ አድርገው ቆይተዋል። ግን ከጊዜ በኋላ፥ ከአውሮፓና ከእስያ ጋር የንግድ ልውውጥ እያደረጉም የመላው አለም የሥልጣኔ ተካፋይ ለመሆን በቅተዋል።
- ይህ የዘመኑ ሰው (homosapien)፥ በተጠቀሱት ተፈጥሮአዊ ልዩነቶችና አካባቢ ምክንያት፥ በአኗኗር ተከፋፍሎ ይኑር እንጂ፥ ምድራዊና መንፈሳዊ ሥልጣኔ እያቀራረበው በመምጣቱ፥ "የሰው ዘር" የሚባል ነገርም እየጠፋ ነው የመጣው።
- በእርግጥ ዘረኞች በአለም ዙሪያ እኩይ ሥራዎቻቸውን እየፈጸሙ ይገኛሉ። እነርሱ፥ ሳይንሳዊም ሆነ መንፈሳዊ አመለካከት የሌላቸው ስለሆነ፥ ለሰው ልጅም ለምድሪቱም የማይረቡ ናቸው። ስለዚህ፥ ይህች ምድር ትተፋቸዋለች።

# ምዕራፍ አስር

## ምድራዊት ምድራችን - ሰማያዊ

የሰው ሃሳቡ ርቅቅ ሲል መግቻ የለውምና፤ ከቅርቡ ወደ ሩቁ፥ ከሩቁ ወደ ቅርቡ፥ ከሚታየው ወደማይታየው፥ ከማይታየው ወደሚታየው፥ ከጉልሁ ወደ ረቂቁ፥ ከረቂቁ ወደ ጉልሁ፥ የሥጋን፥ የመንፈስንም ሥራ እየተመላለሰ (እየደጋገመ) ማውራት ደስ የሚለው ይህ ሰው የተባለ ፍጥረት፥ የገዛ ስነአይምሮውን እየተከተለ ሲጓዝ፥ ሳይንቲስት፥ አዋቂ፥ ፈላስፋም ነኝ እያለ ብዙ አውርቷል በከፍታ።

የሰው ተፈጥሮ ገደብ የት ድረስ መሆኑ ተለይቶ አልታወቀምና፤ ሳይንቲስቶች ለማንኛውም ነገር አለማዊ (አካላዊ/ሥጋዊ) ማስረጃ እንፈልግለት በማለት ሲጣደፉ ብዙ ትውልድ ያልፋል። እነርሱ የሚታወቀውን እናውቅ ይሆናል በማለት ባቅማቸው ይደከማሉ። ግን ማነው በዚህ አለም ላይ ሙሉ በሙሉ እንደሚኖር ሆኖ የሚሰማው? ሰው ምድራዊ ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ምድራዊ መሆኑ ሙሉ በሙሉ ይታወቀው ነበር፤ ኑሮም ግልጥልጥ ያለ፥ የሚታወቅ አይነት ይሆን ነበር።

ሰው ሰማያዊ ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ሰማያዊ መሆኑ ሙሉ በሙሉ ይታወቀው ነበር፤ ኑሮም ግልጥልጥ ያለ፥ የሚታወቅ አይነት ይሆን ነበር። ግን ሰው ሁለቱንም (ምድራዊና ሰማያዊ) በመሆኑ፥ በዚህ አለም ላይ ሙሉ በሙሉ እንደሚኖር ሆኖ ሳይሰማው፥ በምድራችን ሙሉ በሙሉ ሳይኖርባት ይኖራል። በዚህም ምክንያት፥ እርስ በርሱ በደንብ አይግባባም፤ ኑሮውም ግልጥልጥ ያለ፥ የተስተካከለና ከፉም ደግም ቢሆን የሚታወቅ አይነት አልሆነም።

እስካሁን ድረስ ከምድራችን - ከጠፈራችንም እንወቅ እንጂ ብለን በመነሳት፥ የሳይንሱን፥ የመንፈስንም ጉዳይ ስንወያይ ከዚህ ደረስን። ሁሉን ነገር የምናይበት የአይምሮአችን ትኩረት ከምድራዊነት ባሻገር እንዲሆን በማድረግ፥ የምናውቃቸውን ጉዳዮች ከምድራዊ ባህርይ ውጪ እየተረጎምን፥ ከእምነታችንም ጋር ለማዛመድ ጣርን። በጋራ የምናስበውን ሁሉ እያጠቃለልን፤ ከዚያም ትንሽ ዘለቅ ብለን የማይታየውን በሃሳብ ለመቃኘት ሞከርን።

የሰው እድገት በአካላዊነቱ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊነቱም ጭምር ነው (መሆን አለበት) ከሚል ሃሳብ ተነስቶ ሕዝቦችን ሁሉ ወደ መንፈሳዊነት እንዲጨመሩ

የሚመክር፥ ለቆንጆ ምድራዊ ሕይወት ፍለጋ ብቻ ስላልሆነ፥ በራሳችን ላይ ሃሳብ አበዛን። ግን ይህ ሃሳብ ጥሩ ስለሆነ፥ ከብዛቱ የተነሳ በመንፈስ አነቃን፤ ደስተኞችም አደረገን።

ጥረታችን ለጠቅላላ እውቀት ማዳበር ብቻ ሳይሆን፥ ከዚህ ያደረሰን አምላካችን፥ ፈጣሪያችን፥ አባታችን፥ አዳኛችንና ጠባቂያችን ቸሩ እግዚአብሔር መሆኑን እና እርሱን ለማመስገን ነው።

የትልቅነትንም የትንሽነትንም ምሥጢር በእጁ ጨብጦ የያዘ፤ በእርሱ ፍቃድ የነበረ፤ በእርሱ ፍቃድ የኖረ፤ ሁሉ በእርሱ የሆነ፤ ከደቂቅ እስከ ትልቅ፥ ለሁሉም ቦታና ጊዜን አበጅቶ፤ ነፍስ ቢኖረውም ባይኖረውም፥ ለሁሉም መልክና ጠባይ ሰጥቶ፤ ሁሉንም በተወሰነ የተፈጥሮ ሕግጋት ውስጥ አስተዳድሮ፤ ለያንዳንዱ በግዴታ እና በፍላጎት እንደየአካባቢው የራሱን ሕልውና መጠበቂያ ውስጣዊ ስነስርዓት አበጅቶ፤ ለለውጥ፥ ለመሻሻል፥ ለመወለድ፥ ለማደግ፥ ለማርጀትና ለመሞትም እድል ሰጥቶ፤ የሰውን ዘር ከእንስሳት ለይቶ (የራሱን መንፈስ ሰጥቶ)፤ ሕብረተሰባዊ መተዳደሪያ ሕግ አውጥቶ፤ ይህንንም ከሰዎችም በመረጣቸው ሰዎች አማካኝነት አስተላልፎና አስተምሮ፤ ሁሉም እንደየአስተሳሰቡ፥ እንደየስሜቱና መንፈሳዊ ዝንባሌው የፈቀደውን ሃይማኖት እንዲከተል ነፃነቱን ሰጥቶ፤ የሰው ሁሉ የመጨረሻ ጉዞው ወደ ላይ - ወደ ላይ መሆኑን አሳወቀን (እንዲገባን አደረገ)። ስለዚህም፥ ከምናየውም ሁሉ ባሻገር የምንመራመር ባለ አይምሮዎች ሆንን። ተመስገን።

በሳይንሳዊ መረጃ ያልተደገፈ መንፈሳዊ ነገር ሁሉ፥ እርስ በርሳችን እንዳንግባባ ለሚያግደን ሰዎችም፥ ሳይንሳዊ - መንፈሳዊ የአመለካከት ዝንባሌ ለመፍጠር ሞከርን። ራቅ ብሎ ወደ ጠፈር በሃሳብ መጓዝ፥ ቀጥሎም ወደራስ መምጣቱ አንዱ የሰብአዊነት ምልክት ነውና፤ ይህ እንዲህ ያለው የሃሳብ ምልልስ በጣም አስፈልጎናል። በተለይም፡- ሰማያዊ ሕያዋን ወደ ምድራችን ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ፥ መከራን ችለው ይቆዩ ዘንድ፤ ለእድገትና መሻሻልም እንዲረዳቸው፤ በውስጣቸው የመለዋወጥን ጠባይ እንዲያገኙ የዝግመተ ለውጥ ጠባይ እንደተሰጣቸው።

ጫካው ሜዳ ሲሆን፥ ሜዳውም ጫካ ሲሆን፥ ምግብ ከመሬት ሲቀንስ ወይም ሲበራከት፥ አየሩ ሲቀዘቅዝ ወይንም ሲበርድ፥ ወዘተ.. በሚያጋጥሟቸው የአካባቢ ለውጦች ሁሉ፥ ከአካባቢው ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ የሚያደርግ ተፈጥሮአዊ ጠባይ ስለተሰጣቸው፥ ፍጡራኑ ሁሉ የየራሳቸውን ውስጣዊና ውጫዊ ጠባይ እንደ አካባቢው ሁኔታ መለዋወጥ እንደቻሉ - እራሳቸውን ለየአካባቢው ተስማሚ (አሳዳጊ፥ እድሜ ሰጪ) ለማድረግ የሚያበቃ ችሎታ ስለተሰጣቸው፥ በዚህ ምክንያት እንደበዙና እንደተባዙ፤ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑንም

ስንነጋገርበት ከመቆየታችን ጋር አያይዘን፥ በዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ውስጥ፥ አያሌ የስነ አመክንዮ እና ሳይንሳዊ ጉድለቶች እንዳሉበት በመዘርዘር፥ የሳይንስ ተማሪዎች፥ የመንፈሳዊ አባቶችም በማስረጃ የተደገፉትንና ያልተደገፉትን ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳቦችን በጥንቃቄ እንዲመለከቱት አሳስበናል።

በዚህ አለም ላይ ብዙ እውነቶች ቢኖሩም፥ በጣም የታወቁት ጥቂት እውነቶች ብቻ ሳይንሳዊ መልክ ይዘው ስለቀረቡ እንማራቸዋለን። የዘመኑን ትምህርት እንደ እምነት እየወሰድን ሌላም አማራጭ ሊኖር መቻሉን እንረሳለን።

እግዚአብሔርን የሚያውቅ፥ ሁሉን ነገር አስቀድሞ እንዲያውቅ፥ ይህ እውነት በመሆኑ፥ ኖህ ገና ሲወለድ እግዚአብሔርን አመሰገነ። እኛስ? እኛምኮ! ገና ድሮ ድሮ ምድሪቷ ከመፈጠሯ አስቀድሞ፥ ትንሽ ትንሽ ያወቅነውን፥ ይህች ምድር ከተፈጠረች በኋላ - በአካላዊነት ተገለጥንና ነው፥ በፊት ያወቅነውን የረሳን (ይሆን?)

በኋላ የመጣ ሳይንስን ተከትሎ ምድራዊ እውቀት ሲገለጽ - በአካላዊ ማስረጃዎች፥ ሳይንሳዊ መግለጫዎችና ትምህርቶችን በመከታተል፥ ምድሪቷ ከመፈጠሯ አስቀድሞ፥ ትንሽ ትንሽ ያወቅነውን የበለጠ ረሳነው? ወይንስ ሳይንስ ማስታወሱን ጨመረልን? እንጃ። ግን፥ በሳይንስ፥ በሃይማኖትም፥ በእውንም ቢሆን በሃሳባችን፥ በህልምም ቢሆን፥ በራዕይ፥ በጠፈር ያለ ሁሉ በአካልም በመንፈስም የሚያያዝ መሆኑን ከተረዳን፥ ሰውም አካላዊ ሆኖ፥ በመንፈስ ሊራቀቅ - ወደ ሰማይ፥ ወደ ጠፈር ሊገባ ከጠፈር ሕያዋን (ሚሻክላውያን) ጋርም ሊቀላቀል ይችል ይሆናል።

እኛስ "ለትርጉም እንዲያመች" አካላዊ አለም ውስጥ እንደገባንና በመሬት ስበት ከተወሰኑ ሥጋውያን ጋር ተጣብቀን እንደቀረን፤ ይህንንም አለም ከነርሱው ጋር ሆነን፥ ጥርት ባለ መንገድ (በብርሃን ሞገድ አማካኝነት) እንደተመለከትን፤ መኖራችን ከዚህ አደረሰን፤ ተመስገን።

በጊዜ ውስጥ - "የማይገባው ሁሉ ሊገባው" እንደማይችል የሚያሳውቅ ማወቃችን አበይት ስሜቶችን ብቻ አትርፎልን፤ በምድር ያልጨረስነው ሥራም ከሰማይ ቢጠብቀን፤ እነሆ! በዚህም ሆነ በዚያ፥ ፍጹማዊ ሰው ለመሆን የሚያበቃንን ሁሉ እየሠራን እንድንኖር እንገደዳለን።

እስካሁን የተረዳነውን - የሁሉን ነገር ነፍሳማነት - ሕያውነት፥
የጠፈርን እንቅስቃሴ የሚመራ፥ የልብን ትርታ የሚቆጣጠር፥
የፍጥረታትን ሕይወት፥
እስከ ጨረቃዎች፥ ፕላኔቶችና ከዋክብት ዙረት፥
ሁሉን ለሚያውቅ እግዚአብሔር እንተወው በእውነት።

ግን ቀኑ ሲመሽ፥ መጠየቃችን፥
ፈጣሪ እግዚአብሔር መሆኑን ካረጋገጠልን፥
ይቀጥላል ምርምራችን፥
በዚህም ይጠናከራል እምነታችን።

ሕይወትን አራዝሞ በአለም ለመኖር፥
አማራጩን መንገድ አንባቢ ይመርምር።

ወደ ላይ እንኳን ባይወጣ፥ የሰማይ ቤትም ባይኖር፥
ስንት ደስ የሚል ነገር ሞልቷል በዚህቺው በምድር፥
መጥፎው ሲወጣለትና ጥሩው ብቻ ሲቀር።

ከጥንት ጀምሮ የተሰበከውና የተማርነው፥
በልዩ ልዩ የሃይማኖት መጻሕፍት የተጻፈው፥
በአምላካችን አንድነታችንን የሚያረጋግጠው፥
ደስታን የሚሰጠው፥ (ሮሜ 10፡12)
ከተጠቀምንበት በቂያችን ነው፥ በቂያችን ነው።

በየብስና በባህር ሲርመሰመሱ ነፍሳት፥
ሁሉም ባካባቢው፥ በአካላዊነቱ ሲታይበት፥
ማን ነበር የሚያደንቅለት - ይህን የእግዚአብሔር ፍጥረት።
እኛ ወይም የኛ መንፈስ፥ ገና አካላዊ ሳንሆን፥
ማን ያውቃል? ካሁን በፊት አይተን ያደነቅነውን፥
ረስተነውስ ቢሆን።
እንደ ሳሙኤል አምስት መቶ ዘመን እንደቆዬው፥
የትንቢቱን መፈጸም - ሕጻኑን ለመታቀፍ እንደቻለው፤
ያቆየናል እንጂ በሥጋም ባይሆን በመንፈስ፥
በምድር በጠፈርም ቢሆን ለመመላለስ።
ሁሉም ሲፈጸም ለማየት።
አለዚያማ ማን ይሰንብት?
ለእግዚአብሔር ማን ይቅርለት?
ሲነጋ ሲመሽ - ድንቅ ሥራውን ማን ይመስክርለት።

ነገር ግን የኛ ምርጫ ከሆነ ከእምነት ይልቅ ክህደት፥
ከእግዚአብሔር ጋር አለመተያየት፥
መጥፋት - ጭልጥ ብሎ መቅረት፤
ይህ ነው አንዱ የሰማያዊ ድንጋጌ ምልክት፥
መለየት - ከጠላት አምባ መግባት - ገሃነመ እሳት ማለት።

መደማመጥ ቢኖር በግንዛቤአዊነት፥
መስማማትም ቢኖር፥ እግዚአብሔርን በመፍራት፥
ተጠጋግተን በፈቃዳዊ አንድነት፥
ተሰባስበን በአምኃ ቅድሳት፥
አብሮ መሆን - አለመለየት፥ ከእግዚአብሔር ቤት መግባት፥
እንዲህ ነው በቅድስና መመቻቸት፥
ሌላው የሰማያዊ ድንጋጌ ምልክት።

ካመንን፥ በድን ብንሆንም በሥጋችን፥
ነፍሳችን ይኖራል፥ ይቀጥላል ግዴታውን፥
እንድናደንቅለት የእግዚአብሔር ሥራውን፥
ደስ እንዲለው - ደስ እንዲለን፥
እስከ አለም መጨረሻ፥ ከዛም በኋላ ቢሆን።

ሳንጠፋ ከምድር ብዙ ቆይተናል፤
ማድረግ ያለብንን አሁን አስተውለናል።
እስክንገናኝ - እስክንገናኝ፥ ከእግዚአብሔር ቤት፥
ከመሄዳችን በፊት፥ ከመጣንበት፥
አንድነትና ሰላሙን ያብዛልን፤
ፍቅሩን ያድለን ለሁላችን።

በዚህ መጽሐፍ ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳቦችን በቅድሚያ ያቀረብነው ወደ እምነት የሚወስደውን ጎዳና ለማስረገጥ መሆኑን አንባቢ ይረዳዋል። ከሃይማኖት በማይላቀቀው ባህላችን መሠረት፥ አመትባል ሲሆን፡- “እንኳን አደረሰህ፥ እንኳን አደረሰሽ..” ስንባባል፥ በራሳችን ያልተገኘን (በራሳችን ከዚህ ያልደረስን) ፍጡራን

መሆናችንን በደንብ ያወቅን መሆኑን ያመለክታል። ፈጣሪ አምላካችን ለዘለአለም የተመሰገነ ነው።

በሳይንስ የተጣበበ አይምሮ፥ አንድ ቀን፥ በስተእርጅናም ቢሆን፥ “ምድራዊነት የወጣለት እውቀት - መልካም ጥበብ ከወዴት ይገኛል?” ብሎ መጠየቁ አይቀርም። በእርግጥ የሰው ልጅ እድገቱ መታየት ያለበት ከምድራዊነቱ አንጻር ብቻ መሆን የለበትም። ለምሳሌ በብራዚል የአማዞን ጫካ፥ እንዲሁም በሌሎች በአንዳንድ ሞቃት ሥፍራዎች የሚኖሩ ሰዎች፥ “ልብስ ምን ይሠራል፥ ቶሎ ያድፋል፤ ቶሎም ያልቃል፤ እግዚአብሔር የሰጠን ገላችን ይሻለናል..” በማለት እራቁታቸውን ይኖራሉ። የእነኚህ ሰዎች መንፈሳዊ እድገት እና ማህበራዊ ኑሮ አሁን “በሰለጠነው አለም” በታላላቅ ከተማዎች ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ሲወዳደር እጅግ የላቀ ሆኖ ይታያል። እነርሱ በጋርዮሽ ሲኖሩ ካለ ምንም ቁስ አካላዊ ግንኙነት ነው፤ በመንፈሳቸው አንድነትን መሥርተዋል።

እግዚአብሔር አስርቱት ትእዛዛትን እንድንከተል ቢያዘን፥ በመጀመሪያ ፈጣሪያችንን እንድናወቅና እንድናምነው፤ ቀጥሎም ለኛው ለራሳችን መሻሻያ ሆኖ፥ በምድር ላይ ጥሩ ኑሮ እንድንኖር እና፥ በኋላ ከርሱ ጋር እንድንሆን ነው (እምነት)። አስርቱ ትእዛዛትን ስንከታተል ቆይተን፥ ክርስቶስም ከመጣ ጀምሮ፥ በርሱ ሁላችንም በመንፈስ አንድ የመሆንን ምሥጢር መማራችን፥ ምድራዊ ኑሮአችን እንዳው በከንቱ ሆኖ እንደማይቀር ያረጋግጥልናል። በአንጻሩ፥ እስካሁን ድረስ ተመራማሪዎች ከዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ላለመላቀቅ ሲሉ ይደከማሉ።

ተመራማሪዎች ሲመለከቱ ቺምፓንዚን፥

ሁኔታውን፥ ከሰው ጋር መመሳሰሉን፥

ዘራችን ነው አሉ፥ የሁላችን፥

ግን ቢፈልጉ፥

ንዑስ ዝንጀሮ - ንዑስ ሰዎች - መሰሎቻችንን፥

ሰው ወይንም ዝንጀሮ ብቻ ሆነው ተኘኙ፥

እነ ኒአንደርታል ወይንም እነ ክሮ ማኞን።

አፈር መዛቅ፥ አጥንት ፍለጋ ሲሰለቻቸው፥

“በቃ ይኸው ነው የዘር ግንዳችን” ሆነ ድምዳሜው።

ልጆቹ ሁሉ ሲከዱት፥ እርሱ ብቻውን ቀረቶ እንዳያዝን፥

ዘመድ አገኘ፥ ያሰበለትን፥

በይመስላል ብቻ የሚቃዥውን፡፡
ሳይንስ ተብሎ በታላቅ ድፍረት፥
ተደረደረ ብዙ እውነት መሳይ እውቀት፥
ግርግዳ ሆነ ለሃይማኖት፡፡
ሰውም ሲጎዳ፥ በማን ፈጠረኝ ጭንቀት፥
የማይደረስበት ሲሆን ምሥጢሩ፥ የፈጣሪን ሥራ መረዳት፥
የዘመኑ ፈሊጥ ሆነ፥ ወደ እምነት ከማምራት ወደ ክህደት፡፡
እግዚአብሔር ሲያስበን ለመንግሥቱ፥
በደስታ እየዘመርን እንዳንዘጋጅ ለምጽአቱ፥
ጊዜአችን ጣደፍ ጣደፍ ብሎ ሄደ - ኮበለለ በከንቱ፡፡

## ምድራዊነታችን ብቻውን አያዛልቀንም

እስካሁን የቀረቡት ሃተታዎች ሁሉ የሚያመሩት፥ ምድራዊነታችን ብቻውን እንደማያዛልቀን፥ ካለ መንፈሳዊነት ምድራችን፥ ሰብአዊነትም ጤና እንደሚያጣ ነው፡፡

በቀጥታም ሆነ በተለየ መንገድ ስለ እግዚአብሔር መኖርና ኃያልነት ለእውነት ስንል እንደመሰከርን ሁሉ፥ ምድራዊ ኑሮአችን በሰማያዊ ተስፋ እየታደሰ፥ ሰላማችንን አግኝተናል፡፡ ሰው ቢሞት የማይሞተው (የማይሸነፈው) መንፈሱ ስለሚቀር፥ ለዚህ መንፈስ ማደሪያነት የሚያገለግል ምድራዊ አካል ካልኖረለት፥ የግድ ሰማያዊ አካል (ፍጽምተ አካል) መኖር አለበት፡፡ የሕያው መንፈስ ዘለአለማዊ የመኖሪያ ሥፍራ አካላዊ አለም ካልሆነ፥ የግድ ሰማያዊ አለም መሆን አለበት፡፡

መንፈሳውያንም ይህንን አካላዊ አለም እርግፍ አድርገው በየቀኑ በሚኖሩት ሕይወት፥ በእጅ የማይዳሰሱ መላእክትን እንደሚነኩና እንደሚዳሰሱ አድርገው በድርሳናቸው የሚደግሙት፥ ለነርሱ ሰማያዊ አለም እውን ስለሆነ ነው፡፡ ይህም በብርሃነ ሕሊና መጓዝ፤ እራስን በማይታይ አለም ውስጥ መክተት፤ ከመላእክት፥ ከጻድቃንና ከቅዱሳን ጋር ፈጣሪ አምላክን እያመሰገኑ በሰማያዊ አለም መኖርን ከዚሁ ከምድር ሆኖ መለማመድ ነው፡፡ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት እንዲህ ያለውን መንፈሳዊ ባህል ያለማምዳል፡፡

በምድርም ሆነ በሰማይ፥ ሲመላለሱ የማናያቸው አካላዊ ያልሆኑ ሕያዋን አይጠፉም፡፡ እግዚአብሔር ብቻውን አይኖርም፤ እርሱን እንደማናየው ሁሉ፥ ሌሎቹንም መናፍስት አናያቸውም፡፡ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ የሚጠጋው ጥሩ

መንፈስ አይታጣም። በጻድቃን ትይዩ ኃጢአተኞች፥ አስማተኞችና ጠንቋዮች እንደሚኖሩ ሁሉ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ሲርቅም የሚጠጋው መጥፎ መንፈስ ይኖራል፤ ለዚህም ነው በሁለት አለም መካከል ንኪኪ መኖር አለበት የምንል።

በዚህ አለም ላይ (በጠፈርም ቢሆን) ሁሉ ነገር ሊሆንም ላይሆንም እንደሚችል፤ ምንጊዜም የያንዳንዳችን አስተሳሰብ (የኛ ኃይል) በጠፈር ሁሉ እንደሚሳተፍ ሁሉ፤ አንድን ነገር እንዲሆን ወይንም እንዳይሆን የምናደርገው እኛው ራሳችንም ልንሆን እንደምንችልም እናስበው። የእኛ ሕልውና የተጠበቀ የሚሆነው ከምድራችን፥ በጠፈር ውስጥም ከሚገኙት ጋር ሁሉ በስምምነት ስንኖር ነው።

በሳይንስ ባዶ የምንለው ጭራሽ ባዶ አለመሆኑን ከተረዳን፥ ከአካላዊው ሞገድ የሚረጭ ምንድነው? እያልን በራሳችን ላይ ጥያቄ ስናበዛ፥ የመንፈስን ነገር ሳናስበው ማለፍ አይሆንልንም። ስለዚህ "ሁለት አለማት መኖር አለባቸው፤ አለዚያማ እንዴት ይሆናል?" ብለን ስንጠይቅ ነው ጥልቅ ምርምር ውስጥ የምንገባ።

ሰዎች እርስ በርስ ይግባቡ ዘንድ ቋንቋ እንደተሰጣቸው ሁሉ፥ መንፈስ የተባለውም ቃል ሁለት አለማት እንዲተዋወቁ (እንዲገናኙ) የሚያደርግ ሆኖልናል። እስካሁን ድረስ (ለወደፊትም) በአካል የማይገለጸው ሁሉ መኖሩን የሚናገር መንፈስ በሰዎች ሕሊና እየገባ ሃይማኖታችንን እውን አድርጎልናል። ይህም ይቀጥላል።

ይህ የሚታየው ሁሉ ይጠፋል፤ የማይታየው ነው ዘለአለማዊው። ከዚሁ ከምናየው ከአካላዊው የተለየ፥ ሌላ አካላዊ ያልሆነ አለም የለም ማለት እግዚአብሔር የለም እንደማለት ይቆጠራል። እግዚአብሔር የለም ስንል ደግሞ ብዙ ጽንሰ ሃሳቦች ይደመሰሳሉ። አንዳንድ ቁልፍ ሃሳቦችን እየሰነዘርን የተነጋገርባቸው፥ አንዱ ካለ ሌላውም ይኖራል ከሚል ስነአመክኖአዊ አመለካከት በመነሳት ነው። በዚህ ስነአመክኖአዊ አመለካከታችን፥ እስካሁን ድረስ ከሳይንስ ድጋፍ እንጂ ቅዋሜ አላጋጠመንም።

የሰውን የምድራዊነቱን ታሪክ በአካላዊ ማስረጃ እያረጋገጡ የጻፉ ብዙዎች ቢሆኑም፥ በግምትም ሆነ በትክክል ከነዘመኑ የሚታወቀው የቅርቡ ብቻ ነው። ከልዩ ልዩ መጻሕፍት ጋር በማመሳከር የተውጣጡ የዘመናት እርከኖችንም፥ ካሁኑ ዘመን ወደኋላ እየቆጠርን አስፍረናል (አባሪውን ይመለከቷል)።

ሕዝቦች ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ፥ ሲበተኑና ሲሰባሰቡ እንደቆዩ ሁሉ፥ ሰብሳቢያቸውን (እምነታቸውን) አግኝተዋል። ካሁን በኋላ የመበተን ክስተት ይዳከማል፤ የመሰባሰብ ክስተት ያይላል። በአሁኑ ዘመን እኛ ኢትዮጵያኖችም በአለም ዙሪያ ተበትነናል። ፖለቲካ እንደበተነን፥ ምድራዊ የሆነው ሁሉ እንደለያየን፥ የሕብረተሰብን መንፈሳዊ ጤንነት የሚጠብቅ መድኃኒት - የመንፈሳዊነታችን ኃይል

እያጠጋጋን ነው ያለው። ስለ መንፈሳዊነታችን በተነጋገርን ቁጥር እርስ በርሳችን እየተቀራረብን ነው የመጣነው። በጉልሁም ቢሆን በረቂቁ፥ ግለሰብ ለሕብረተሰብ፥ ሕብረተሰብም ለግለሰብ - አንዱ ለሌላው ሲያስብለት፥ ይህ ነው መንፈሳዊ አንድነት ማለት፤ የሁሉንም ስሜት የሚጠብቅ - ፍቅር የሚገለጽበት ደስተኛ ሕይወት።

ለሳይንስም ለሃይማኖትም ማእከላዊ ኃይል ሊሆን ይችላል እግዚአብሔር። የክርስቶሳዊነት አላማው በሰዎች መካከል ልዩነቶችን በፍቅር ደምስሶ፥ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ መኖር ነው። ማን አለን ማእከላዊ ሰብሳቢ ለእኛ (ለእስላሞች ፥ ለክርስቲያኖች፥ አይሁዶች፥ ለሂንዱዎቸች..ወዘተ) ካለ እግዚአብሔር?

በምድር ላይም ጥሩነት በፍቅር ይቀሰቀሳል። ካለ ፍቅር ወደ ሰማያዊ አለም ተሸጋግረን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሰማያዊ አንድነትን ለመመሥረት አንችልም።

መጀመሪያ የነበረ፥ በኋላም ያው የርሱ የሆነ አንድ ቃል፥

የርሱና እሱው የሆነ አንድ ማዕከል፥

ወደር የሌለው እፍጋታ፥ ታላቅ የመንፈስ ኃይል።

የሰው ልጅ የድኅነትን ምልከት ሲያስተውል፥

በፍቅር ስበት መቀራረባችን ሲቀጥል፥

ሁሉም በእግዚአብሔር ፍቅር ሲጠቃለል..

ከእንግዲህ አያቋርጥ መመልከታችን፥

መልከ ሰማይን - የእግዚአብሔርን የዙሪያውን፥

የጻድቃን፥ የመላእክቱን፥ ከዚያው ነውና መሄጃያችን፥

መሰባሰቢያ ጽዮናችን።

## እኛ ምን እናቆይላት ለምድራችን?

እጅግ በተቃለለ መንገድ ስንመለከት፡- ሁሉን ነገር ሊያሳውቀን የሚችል፥ በውስጣችን ሰማያዊነት እያለ፥ ምድራዊነት ማወቁን ሲደበቀብን፥ እናም በምድራዊነታችን ምክንያት ማወቅ የሚገባንን ማወቅ ሳንችል ስንቀርና ቶሎ ማወቃችን ግዴታ ሲሆን፥ የዛን ጊዜ አለማወቃችን ይጎዳናል፥ እስከሞትም ሊያደርሰን ይችላል።

ታዲያ ይህንን ጉዳይ አተልቀን ብናየው፥ ሞት ካለ ምክንያት ስለማይመጣና፥ ቶሎ ለመምጣት ምክንያት እንዳይኖረው ለማድረግ ስንልም የምናደርገው ይኖራልና፤ እስቲ “እኛ ምን እናቆይላት ለምድራችን?” ብለንም እናስብ።

የሰው ሥራ ሲያረጅና ሲሞት፥ ያ የመጨረሻው እንደሚሆን፥ የእግዚአብሔር ሥራ ግን ከእርጅና እና ከሞት በኋላ እንኳን የመጨረሻው እንደማይሆን ቀደም ሲል ጠቅሰናል። እንግዲያውስ፥ በጠፈር እስከዛሬና ለወደፊት የከሰሙ ከዋክብት፥ ለአካላዊ ሕያዋን ፍጥረት እንደሚዘጋጁና ለእኛም ምድራችን ምግብ እንደሆነችን ሁሉ፥ የጸሐይ ብርሃን ቢጠፋ፥ ምድሪቱም ከርሷ ጋር ብትጠፋ፥ ሰውም ከምድር ቢሰናበት፥ ያ የመጨረሻው እንደማይሆን አውቀናል።

እንዳው ለማስተዋል ያህል፥ የጠፈር አካላት በመሆን (በመኖር) ይህንን ያህል ሲቆዩ፥ እነርሱ በውስጣቸው የታገሏቸውን ጸረ አካላት ልብ ይሏል። ክፉ አሳቢነት እና አሉታዊነት የሰው ልጅ በምድር ለመኖር የሚያበቃውን የመጨረሻውን ትንሹን እውቀት እንኳን ሳይቀር በመስረቅ ወደ ሞት የሚዳርጉ ናቸው። (በተጨማሪ ከምድራዊነታችን ባሻገር - በሁለተኛው መጽሐፍ - "ቅራኔዎች፥ ከጠፈር እስከ መሬት" በተሰኘ የተጻፈውን ግጥም ይመልከቱ)።

በጠፈር ያለ ሁሉ እርስ በርሱ የሚያያዝ ከሆነ፥ የጠፈር ታሪክ እኛንም ይመለከተናል ካልን፥ ከእንግዲህ የሰብአዊነት ሞት ከምድራችን ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው የሚሆነው። እና፥ ሰብአዊነት (ግለ ሰብም ቢሆን) ብዙ ለመቆየት ከውስጡ ጥሩ አሳቢነትን እና አዎንታዊነትን (optimism and positivity) እያጎላ፥ ክፉ አሳቢነትን እና አሉታዊነትን (pessimism and negativity) እየቀበረ መሆን አለበት። በመንፈሳዊነት ጥሩ አሳቢነትና እና አዎንታዊነት የበላይ ሊሆን ይችላል። ጥሩ አሳቢነትና እና አዎንታዊነት የበላይ ሲሆን፥ ምድሪቱ በጎ ትሆናለች፥ የሰውም ልጅ ኑሮ ይሻሻላል።

ስለ ፍጥረታችን እና ስደቶቻችን ጉዳይ ስናወሳ፥ ከሳይንሳዊ ፍልስፍና ወደ መንፈሳዊ ፍልስፍና በመሸጋገር - የሰዎች ምድራዊ ኑሮ ካለ መንፈሳዊነት፥ ሰላማችንን የሚያሳጣን መሆኑን በመጠቆም ነው። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ስለ ተለያዩ ሥልጣኔዎችም እናስበው። ሁሉን ነገር ሊያሳውቀን የሚችል፥ በውስጣችን ሰማያዊነት እያለ፥ ምድራዊነት ማወቁን ቢደበቅብንም፥ ልዩ አይነት ሥልጣኔን ሳያመጣልን አልቀረም። ግን ሥልጣኔ አንድ አይነት ብቻ ነው ወይ? የዚህ የዘመኑ ሥልጣኔ መንፈሱ ምድራዊ ነው ወይንስ ሰማያዊ።[66]

---

[66] እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት በሚል ርዕስ በምዕራፍ ስምንት ያለውን ግጥም - ከምድራዊነታችን ባሻገር ሁለተኛ መጽሐፍ ላይ ይመለከቷል።

ከፉ እሳቢዎችና እና አሉታዊያን ጠፍቶ በማጥፋት ነው የሚያምኑት። ሆኖም፥ የሰብአዊነት፥ የምድራችንም ሕይወት ይህንን ያህል የቆየው፥ አንድም በጥሩ አሳቢዎችና በአዎንታውያን ብርታት ነው (ተመስገን)።

የሰብአዊነት፥ የምድራችንም ሕይወት ይህንን ያህል የቆየው፥ አንድም ይህ ዛሬ የምናየው አካላዊ ሕያው የሆነ ሁሉ፥ "ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ - በውስጡ የራሱን ሕልውና በሚጠብቅለት ለዘለአለም ሕያው በሆነ በሰማያዊነቱ" ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ማንም ሰው ለጥሩነት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በተለያየ መንገድ የሰብአዊነትን መንፈስ ያሳድገዋል። ግማሽ ሰውነቱን በቡቱቱ የሸፈነ፥ ከቆሻሻ ሥፍራ ምግብ የሚለቅም፥ አይምሮውን የሳተ ሰውም፥ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ፥ ይህ ሰው ሲሞት በቋሚ ሰው የሚታሰብበት - ጥሩነቱ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያገናኘዋል።

ሰብአዊነት እድሜው በሚሊዮን ዓመታት ቢቆጠር፤ የሰው ልጅ ሕይወት እንደ ውሃ ጎርፍ ቢመሰል፤ እንዲሁም ከሰብአዊነት ውስጥ የአንድ ግለሰብ እድሜ በሰማንያ ዓመት ቢተመን፤ ያ ዛሬ ተወልዶ ነገ የሚሞት ሕጻንም ለሰብአዊነት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

እኛ የዛሬዎቹ፥ እኛ የትላንትናዎቹ፥ እኛ የነገዎቹ ባንድ ላይ ተጠቃለን በሕያውነት ምንጊዜም አለን፤ ስለዚህ፥ ሕጻኑ ለምክንያት ተወልዷልና፥ ለምክንያት ይሞታል፤ ሕጻኑ በምድር ላይ መፈጠሩን እንኳን ሳያውቅ ቢሞትም፥ ሰብአዊነት ያውቃል። የሞተውም ያልሞተውም፥ ለወደፊት የሚወለደውም - ሁሉም እኛው ነን።

ከተፈጠሩ ጀምሮ ብዙ ዓመታት የማይኖሩትንና የሚኖሩትን ባንድ ላይ አጠቃለን ብንመለከተው (ሰብአዊነትን እንደ ውሃ ጎርፍ ብናስበው)፥ የእድሜ መርዘምና ዓመት መቁጠር እንኳን ምንም ትርጉም አይሰጥም። ታዲያ፥ እኔ - እኔ እያሉ በራስ ላይ ማተኮር ምንድነው? ግለሰባዊነት ከሕብረተሰባዊነት ጋር አብሮ እንዲዘልቅ የሚያደርጉትን ሁሉ በአዎንታዊነት ብንመልከት፥ ለዚች ለምድራችን ለሰብአዊነትም እናስባለን፤ ስናስብ፥ እድሜችንን ሁሉ ለራሳችን ብቻ ከማድረግ አልፈን ለጋራ ጥቅም እናውለዋለን። ይህ የጋራ ንቃት ከጋራ ጥፋት ሊያድን ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች ገና ከልጅነታቸው የራሳቸውን ኑሮ ሳይኖሩ፥ ለሌላው ብቻ እየደከሙ (በመንፈሳዊ ግልጋሎት ወይንም በሌላ በሕብረትሰባዊ ተሳትፎ) ሕይወታቸውን መስዋዕት ያደርጋሉ። ምንድነው የመንፈሳዊነት ፍልስፍና? መኖራችን ሁላችንንም እንደየአቅማችን ለሰብአዊነት መስዋዕትነት እንድንበቃ ካላደረገ። የሰዎች

መስዋዕትነት በሚዋደዱ ቤተሰቦች በየጊዜው ይከሰታል፤ መንፈሳዊ ሆኖ መኖርና መስዋዕትነት የማይነጣጠሉ ናቸውና።

የክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት ባጠቃላይ ሰብአዊነትን ወደ ጥሩ ለመለወጥ ካልሆነ፥ ለምን አስፈለገ? ዘለአለማዊ ሕይወት ከአካላዊው ሰብአዊነት ምን ያገኝ? የአንድ መንፈሳዊ ሰው የመጨረሻ አላማው፥ የሰብአዊነትን መንፈሳዊ ጎኑን በማሻሻል አለምን የተሻለ መኖሪያ ሥፍራ ከማድረግም አልፎ፥ ለመጪው አለም የሚያዘጋጅ ካልሆነ፥ የእኛ የእያንዳንዳችን መንፈሳዊ ሕይወትም ተደማምሮ አጠቃላይ ሰብአዊነትን ጥሩ ካላደረገው የመንፈሳዊነታችን ጥቅሙ ምንድነው?

በምድር ላይ መከራ እንደ ፈተና ሆኖ፥ የደጋጎች መስዋዕትነት ከምንጊዜውም በበለጠ የሚፈለግበት ጊዜ ይመጣል። በምድር ላይ የሰው መፈጠር፥ ሰው ለሰማይ መንግሥት ተስማሚ እንዲሆን ከሆነ፤ መስዋዕት መሆን ያለበት ሰው ሁሉ መስዋዕት ይሆን ዘንድ ግዴታ ነው። በአለም ታዋቂነት ያገኙ ሁሉ የተወሰነ መስዋዕትነትን አሳይተዋል። መስዋዕትነት ወደ መንፈሳዊነት የሚያመራ ከፍተኛ የእድገተ ሕሊና መመዘኛ ነው። ፍቅርም እራስን መስዋዕት  እስከማድረግ ያደርሳል።

“እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።” ዮሐ. 15፡12 - 14

አንባብያን ሆይ! በዚህ አለም ላይ ብዙ ሰዎች በሰማያዊ እውነትና በምድራዊ እውነታ መካከል ይንገላታሉ፤ የምድራዊነት መጨረሻው ምድራዊነት ቢሆን ይመረጣል? ወይንስ የምድራዊነት መጨረሻው ሰማያዊነት ቢሆን ይመረጣል?

ምድር ትጠፋለች፤ አካልም አፈር ይሆናል። ለዘለአለማዊና ለማይጠፋው መንፈሳዊ ሕይወታችን ምን እናድርግ? ታዲያ፥ እኛ ምን እናቆይላት ለምድራችን? የሰማዩ መንግሥት ከምድርም እንዲሆን (ምድራዊት ምድራችን ሰማያዊ እንድትሆን)፥ እኛ ምን እናድርግ በበኩላችን? መልሱም ተነግሯል፤ ተጽፏል፤ ተሰብኳል።

ሌሎች የሚያደርጉትን ብቻ ስንከተል የራሳችንን የፈጠራ ችሎታ በገዛ ራሳችን አናጥፋው። ከኛ ዘንድ የመነጨ አንድ አዲስ ነገር ቢገኝ፥ መጻፍና ማውራት አንፍራ።  የራሳችን ከራሳችን የፈለቀ የሆነውን ሁሉ አናቃለው። መንፈሳዊነትን እየተውን ምድራዊነትን ብቻ እየተከታተልን ከቆየን፥ ከራሳችን መገንጠላችን ነው።

እውነት በጊዜ ውስጥ እጅግ እየሰተስፋፋና እየጎላ ይሄዳልና፤ በአፍም በጽሑፍም የተላለፉ መንፈሳዊ እውቀቶችና ምክሮች ሁሉ፥  በጊዜ ውስጥ ለሕዝቦች ሁሉ መዳረሳቸው አይቀርም። እኛ የተገነባነው በአካል ቢሆንም፥ በውስጣችን መንፈስ አለን። ስለዚህ፥ከቀን ወደቀን እውቀታችን በአካላዊ አለም እየጎለመሰ ሲሄድ፥ ይህ

እውቀታችን መንፈሳዊነታችንን እንዳይደብቅብን እንጠንቀቅ። "ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፤ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ።" መዝ. 49፡15

መንፈሳዊነት የጎደለው ሕይወት እና መሪ የሌለው ወታደር አንድ ናቸው። በኑሮአችን ሁሉ መንፈሳዊነት የበላይ ሆኖ መምራት አለበት፤ እንደሚጠፉ እንስሶች እንዳንሆን። እውር ሆኖ ለተወለደ ሰው፥ በአይን ስለሚታይ ቁሳቁሶች በቋንቋ ገልጾ ማስረዳት እንደማይቻል ሁሉ፤ የእግዚአብሔርን ማንነቱን ለማወቅና ለማሳወቅ የሚቻለው ማንም ሰው አይኖርም።

ስለ መንፈስ ጉዳይ፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ መላእክት፥ ባጠቃላይ ስለ ሰማያዊው አለም ማንም ሰው ከተፈቀደለት ውሱን እውቀት በላይ ማወቅ አይችልም። ለማመን ማወቅ ካስፈለገን እና፥ "ካላወቅን አናምንም" የምንል ከሆነ፥ ምንጊዜም ሳናውቅ መኖራችን ነው። ግን አንድ ምርጫ አለን፤ ይኸውም አስቀድሞ ማመን ነው። አስቀድሞ ያመነ፥ የእምነቱን ያህል የሚገለጥለት ሰማያዊ እውቀት ይኖራል። አስቀድሞ ማመን እና የሚከተለውን መጠበቅ ይሻላል፤ አስቀድሞ በመጠራጠር ሁሉን ነገር ከማጣት።

የሚያምን ሰው ካለ ሥጋ ተጽእኖ የሚከተለውን መንፈሳዊነቱን እያየ ይመሰክራል፤ ከማመን ጋር ልዩ እውቀት ይገለጻልና። በጊዜ ውስጥ ውሸት ሁሉ እየወደቀ ሥፍራውን ለእውነት እየለቀቀ ሲሄድ፥ ውሸት ረግፎ ሲያልቅ፥ እውነት ብቻ ይቀራል። የዛን ጊዜ የማያምን፥ አምኖም የማያውቅ አይኖርም።

በማንኛውም እውነት በሆነ ነገር (በሳይንሳዊ እውነት፤ በመንፈሳዊ እውነት..) ጸንቶ መቆየት ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን፤ በእውነት ጸንቶ የቆየ ጸሎቱም እንደሚሰምርለት አንጠራጠር። ካመንን፥ ከፈለግን፥ ከጠየቅን፥ ከጸለይን፥ ምንጊዜም ቅዱስ መንፈስ ካጠገባችን ሆኖ ይራዳናል (ይህም መጽሐፍ አንድ ምስክር ነው)።

የሰብአዊነት እድገቱ (ይህ ሰው የመሆን - የማሰብና የመተሳሰብ ፍጥረታችን)፥ "ለመጨረሻው ጊዜ" እያሰናዳው ነው ያለው እንጂ፥ ሄዶ ሄዶ ካንድ ሥፍራ ሲደርስ በድንገት አይቀጭም፤ የሚያስብልን አምላካችን ከምድራዊነታችን አላቆ ከዚያ ሳያሻግረን አይተወንም። የማንም ሃይማኖት ከማንም ሃይማኖት አይበልጥም - አያንስም። የሚያበላልጠው ምድራዊ አመለካከታችን ብቻ ነው[67]።

ሂንዱም ሆነ አይሁድ፥ እስላምም ሆነ ክርስቲያን፥ የሁላችንም መጥፎነት ከውስጣችን ሲጠፋ (ከምድራዊነታችን ስንላቀቅ)፥ የዛን ጊዜ አንድ እንሆናለን። ግን እስከዛው፡- በእግዚአብሔር ቤት እስክንገናኝ ድረስ፥ አብረን እንኑን እና እርስ

[67] በአራተኛው መጽሐፍ የበለጠ ይብራራል።

በርሳችን እየተማማርን እንቆይ። ከዚህ አለም ውጥረት፥ ጸብና ጭቅጭቅ፥ ንትርክና ክርክር፥ ከውጣ ውረዱ፥ ከሃዘንና ከብስጭቱ፥ ወዘተ. ሁሉ ባሻገር ክርስቶስን መስሎ ማደር የሚችል ጻድቅ መሬትን ይወርሳልና፤ በጸሎትና በሥራችን ሁሉ መንፈሳዊነታችንን በማጠናከር ወደ እውነት - ወደ እግዚአብሔር እንጠጋ።

ለሁላችንም አንቀሳቃሽ መንፈስ አለን፤ በምድራዊነታችን የጎደለብንን ሁሉ አሟልተን ወደ ፍጹማዊነት እንጠጋለን - ምድራዊት ምድራችንን ሰማያዊ የምናደርጋት እኛው ነን።

ከነልዩነቶቻችን ደስ እንዲለን የሚያደርግ ጊዜ ይመጣል። በእውቀታችን እንኩራ፤ እንመካ፤ እንንቀፍ፤ እንሳደብ፤ እንዝለፍ፤ ትችት እናብዛ፤ እንፍረድ። በፍቅር መንፈሳዊ አንድነታችንን እንገንባ። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን።

ከእንግዲህ መጪው ጊዜ በጣም አስፈሪና አስከፊ ቢሆንም፥ በግራና በቀኝ ከሚታየው የሰዎች እልቂት በስተጀርባ ሰብአዊነት በማያቋርጥ ጉዞ ወደፊት ይገሰግሳል፤ ውሸት በያለበት ሲረግፍ፥ እውነት በምትኩ ሲያብብ፥ መጨረሻው ጥሩ ይሆናል። ስለዚህ፥ ለተሻለ ሕይወት እንዘጋጅ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ አይለየን። እግዚአብሔር የርሱን ፈቃድ አውቀን እንደፈቃዱ እንድንሠራ ያድርገን። ሁላችንንም ለመንግሥተ ሰማይ ያብቃን።

በእውነት ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጹምና ኃያል፥
ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ነው።

አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣሪ አምካችን ታላቅ ምስጋና ይድረሰው።
አሜን።

**ተፈጸመ**

የሚከተለውንም "ከምድራዊነታችን ባሻገር" አራተኛውን መጽሐፍ በቀጣይ እንዲያነቡ ተጋብዘዋል።

# የቃላት ትርጉምና ተጨማሪ ማብራሪያ

አገረ ከዋክብት:

በአንድ የጠፈር ክልል ውስጥ ማንኛውንም አካል (ከዋክብት፥ ጨረቃ ወዘተ..) በውስጡ ያቀፈ (galaxie)።

የከዋክብት ሰልፍ ወደ አንድ የተወሰነ የጠፈር ስፍራ (እፍጋታ ወደበዛበት አካባቢ) ጠምዘዝ ይላል። በዚህም ምክንያት (?) የአገረ ከዋክብት ቅርጾች አራት አይነት ናቸው። እነርሱም፦ ክባዊ ጥምዝዝ (spiral)፥ ነጠላ ጥምዝዝ (barred spiral)፥ ዘርጋ ያለ ሉል (elliptical) እና መርጸ ቢስ (irregular) ናቸው።

ሁለንተናዊ ግንኙነት:

የሁሉ ነገር እርስበርስ መያያዝ (መዛመድ)፥ በአካልና በመንፈስ።

ሃይድሮጂን:

ከንጥረነገሮች ሁሉ በይዘቱ ዝቅተኛ የሆነ፥ ባለ አንድ ኢሌክትሮን እና አንድ ኑክሊየስ። (hydrogen)

ሕይወት አልባ:

ሕይወት የሌለው (non living thing)

ህዋስ:

ዝቅተኛው (የመጨረሻውና ትንሹ) ባለ ሕይወት አካል፤ዝቅተኛው የሕይወት ክፍል።

አንድ ህዋስ በውስጡ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ፕሮቲኖች በህዋሱ ሽፋን (cell membrane) ውስጥ አቅፎ ይይዛል።

በፕሮቲን ውስጥ ያሉ ኬሚካሎች እንደ ሰንሰለት የተያያዙ አሚኖ አሲድ የተባሉ ናቸው። የአንድ ህዋስ የሕይወት ተግባራት በጠቅላላ ከዲ ኤን ኤ ጀምሮ እስከ ፕሮቲን ግንባታ ድረስ በዚሁ የሕይወት ህዋስ ውስጥ ይካተታል።

ልውጠ አለቶች:

በሙቀትና በግጋት የተለወጡ ጥንታውያን አለቶች (metamorphic rocks)

መንትያ ፍጥረት፡

እራሱን የመሰለ ፍጥረት። ክሎን - clone

የአንድ ዕጽ አካል መልሰው ቢተክሉት፥ የሚበቅለው አዲስ ዕጽ እና የመጀመሪያው ዕጽ በተፈጥሮ ጠባያቸው አንድ አይነት ይሆናሉ። በውስጣቸው የሚኖረው ዲ ኤን ኤ አንድ አይነት ይሆናል።

ክሎን ማድረግ በገበሬዎች ዘንድ ቀደም ብሎ የታወቀ ነው። ዶሊ የተባለችው በግ ግን በክሎን የተገኘች የመጀመሪያዋ እንስሳ በመሆ‘ ነው የተደነቀችው።

መስሎ ማደር፡

መስሎ መኖር፤ እራስን በራስ ለመለወጥ የሚያስችል ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ስምም ሆኖ ለመኖር የሚያበቃ ለፍጡራን ሁሉ የተሰጠ መመሪያ። (mutation)

መካነ አራዊት፡

የተለያዩ አራዊቶች ከተፈጥሮአዊ መኖሪያቸው ተወስደው የሚኖሩበት ውሱን ሥፍራ (zoo)

በራሂ፡

ጂን (gene) በኬሚካሎች የተመዘገበ ወሳኝ አካላዊ መልከ ጠባይ።

ባዶነት፡

በውስጡ ምንም ነገር የሌለበት። (vacuum)

ብርሃን፡

ከጸሐይና ከከዋክብት የሚፈነጠቅ ጨረር ሁሉ ብርሃን ይባላል። ሆኖም፥ ከሩቅና ከተለያዩ ከዋክብት ወደ መሬት የሚደርሰው ብርሃን የተለያየ ነው። ብርሃን በሞገድ መልክ የሚጓዝ ሆኖ ሳለ፥ በጸሐይ ብርሃን ውስጥም የተለያዩ ሕብረ ቀለሞች የሚታዩት፥ የሞገዶቹ ርዝማኔ (wave length) የተለያየ በመሆኑ ነው።

የሰዎች የማየት ችሎታ ለሰው አይን በሚያመች የሞገድ ጠባይ ብቻ የተወሰነ ስለሆነ፥ ባለ አጭር ሞገድና ባለ ረጅም ሞገድ ከሆኑት

ሞገዶች መካከል ያለው (ይኸውም የጸሐይ ብርሃን) ብቻ ነው በአይምሮአችን ተቀርጾ የምንገነዘበው (የሚታየን)።

ብርቅነት፡

አንድ ቁጥር እጅግ ትልቅ በሆነ ቁጥር ሲካፈል ወደ ዜሮ የሚጠጋ እጅግ ትንሽ ቁጥር እንደሚሆን፤ ይህንን ትንሽነት - ወደ አንድ ነጥብ (ዜሮነት) መጠጋት የሚገልጽ። (singularity)

ቁስ አካል ሁሉ ተሸማቆ የሚጠፋበት፤ የጽልመተ ጥልቀትን (black hole) ማእከል የሚገልጽ ስለሆነ፥ ይህም ጽልመተ ጥልቀት በብርቅነት ይገለጻል።

አንዳችነት፡

የጠፈር አካላት እርስ በርስ ሲደራረቡ የሚፈጠረው ታላቅና ግዙፍ አካል - የብርቅነት ተቃራኒ። ከመጨረሻ የጠፈር መሰብሰብ በፊት፥ የጠፈር አካላት ሲናወጡ፥ ወደ ኃይል የማይለወጡ አካላት ሁሉ እርስ በርስ ሲጠጋጉ (ሲጋጩ ወይንም ሲደራረቡ) የሚፈጠር ታላቅ የአካል ክምችት፤

“ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ..” ማቴ. 24:29 ከሚለው ጋር ያመሳስሏል (ሃሳባዊ)።

አንድሮሜዳ፡

ለኛ አገረ ከዋክብት የሚቀርበው (ጎረቤታችን) አገረ ከዋክብት ነው። የብርሃን ጨረር ከአንድሮሜዳ ወደ ምድራችን ለመድረስ 1.5 ሚሊዮን ዓመት ይፈጅበታል።

አልፋ ሴንቱአሪ፡

ለኛ የሚቀርበው የኮከብ ስም ነው። የብርሃን ጨረር ከአልፋ ሴንቱአሪ ወደ ምድር ለመድረስ 4 ዓመት ይፈጅበታል።

አምሳለ ከዋክብት፡

ጎላ ጎላ ብለው በደረቅ አይን የሚታዩትን ከዋክብት በመስመር በማያያዝ የሚገኝ ቅርጽ። (constellation)

አቶም፡

ዝቅተኛው የአካል ክፍል (atom)። ማንኛውም አካል በአተሞች የተገነባ ነው። የአቶሙን ማዕከላዊ ሥፍራ (ኑክሊየስ) የሚይዙት

ፕሮቶኖችና ኒውትሮኖች ሲሆኑ፥ ዙሪያውን ደቂቃን አካላት - ኣያሌ ኤሌክትሮኖች እንደ ደመና ይከቡታል። ፕሮቶን ኢሌክሮኖችን የሚስብ ሲሆን፥ ይዘቱም የአንድ ኢሌክትሮንን ሁለት ሺህ ጊዜ ይሆናል።

ኒውትሮን በይዘቱ ፕሮቶንን ትንሽ ይበልጠዋል፥ ግን ኢሌክትሮኖችን የመሳብ ችሎታ የለውም።

እሳት ወለድ አለት፡

ከእሳተ ገሞራ የተገነባ አለት። (volcanic rock)

እፍጋታ፡

በአካል ውስጥ የሚገኝ ይዘት (mass) በተለያዩ ሥፍራዎች (መሬቶች፥ ጨረቃዎች..) ስበት (gravity) አንጻር ሲገመት እፍጋታ (density) ይባላል። ለምሳሌ የአንድ ሰው እፍጋታ ከመሬት ይልቅ ጨረቃ ላይ አነስተኛ ነው፤ ይዘቱ ግን የትም ሆነ የት አይለወጥም።

አዲስ ግኝት፡

ከሁን በፊት ያልተደረሰበትን በምርምር ማግNeት። (discovery)

አዛሂት፡

እንደ መስተዋት የሚያብረቀርቅ ማዕድን። (quartz)

ዑደት፡

ዙረት። (cycle)

ታላቅ መኮማተር፡

የጠፈር መዘርጋት ሲያቆም፤ ጠፈር ሲሰበሰብና ሲሸማቀቅ። (the Big Crunch)

ታላቅ ቦግታ፡

አንድ ትልቅ ኮከብ ሊጠፋ ሲል (ከመክሰሙ በፊት) ከፍተኛ ብርሃን ይረጫል። ይህ ታላቅ ቦግታ ሱፐርኖቫ (supernovae) ይባላል። የኒውትሮን ከዋክብት የሚፈጠሩት ከሱ÷ርኖቻ በኋላ ነው። ብርሃን ወደ ውጪ ከጸሐይ ብርሃን መቶ እጥፍ ሆኖ ሲረደ፥ ይህ የብርሃን መረጨት እንደ ፍንዳታ ቢሙጠርም፥ ኮከቡ

ሲለማቀመ ፍንዳታው ወደ ውጪ (explosive) ሳይሆን ወደ ውስጥ ነው የሚሆን።

(emplosive)

ከሱፐርኖቫ ብዙ መቶዎች ወይም ብዙ ሺዎች ጊዜ የሚበልጥ ፍንዳታ ሃይፐርኖቫ (hypernovae) ይባላል። እጅግ ትልመ ኮከብ ሲፈነዳ ፍንዳታውም ወደ ውስጥ ሲሆን (emplosive) አተሞች ሳይቀሩ ጥፍት ይሉና ጽልመተ ጥልቀት ይፈጠራል።

ቴሌስኮፐ፡

የሩቁን አመርበና አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር። ታላቁ የጠፈር ቴሌስኮፕ የኸብል ቴሌስኮፕ ይባላል።

ክፍት፡

ወደ ውስጡ ማንኛውንም ነገር (ሙቀትንም) የሚያስገባ፤ ወደ ውጪም የሚያስወጣ። (open system)

ኮከብ፡

የራሱ ብርሃንና ሙቀት ያለው የጠፈር አካል።

ኩአርክ፡

በፕሮቶኖችና በኒውትሮኖች ውስጥም የሚገኙ እጅግ ደቂቅ የሆነ አካል። (quark)

ኩአዛር፡

በጠፈር ውስጥ እጅግ እሩቅ ከሆነ ሥፍራ፥ እጅግ በጣም የሚያበሩ እንደ ኮከብ ያሉ ናቸው። (quazar)

ኑትሪኖ፡

ጠፈር ሲዘረጋ የነበሩ ደቂቀ አካላት ናቸው። ኒውትሪኖ እና ጸረ ኒውትሪኖ ስለማይጠፋፉ፥ ኒውትሪኖዎች አሁን በጠፈራችን (በመሬትም) ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል።

ንድፈ ሃሳብ፡

አስተያየት፤ በማስረጃ የሚረጋገጥ ሃሳብ። (theory)

ንጥረ ነገር፡

ማንኛውም ቁስ አካል የተገነባበት መሥራች ነገር፤ በአተሞች የተገነባ የአካል አይነት። ንጥረ ነገር (element)። ለምሳሌ፡- ብረት፥ መዳብ፥ ኦክሲጂን፥ ሃይድሮጂን።

ንፍቀ ክበባት፡

ሁለቱ የሉል ክፍሎች (hemispheres)፥ መሬትን ለሁለት የሚከፍል - የደቡብ እና የሰሜን ንፍቀ ክበብ። (southern and northern hemispheres)

ቁስ አካል፡

አካል (matter)፥ በአካለዊ አለም የሚገኝ፥ ማንኛውም ቦታ የሚይዝ፥ በንጥረ ነገሮች የተገነባ ነገር።

ቅሪተ አካል፡

ከጊዜ ብዛት ወደ ድንጋይነት የተለወጠ የሕዋሳት ቅርጽ። (fossil)

ይዘት፡

በማንኛውም አካል ውስጥ የሚካተት ነገር ሁሉ። (mass)

የኖራ ድንጋይ፡

ከካልሲዩም እና ከካርቦኔት የተገነባ ድንጋይ። (limestone)

የኮስሞስ ጨረር፡

ከሌሎች አገረ ከዋክብት ወደ እኛ አገረ ከዋክብት እንዲሁም ወደ መሬት የሚገቡ ጨረሮች። (cosmic rays)

የሁኔታ አድማስ፡

በብርቅነት ዙሪያ ያለ የስበቱ ክልል የሚያዋስነው የኃይል ክልል። (event horizon)

የጸሐይ ጭፍሮች፡

በጸሐይ ስበት ክልል የሚዞሩ እንደኛ መሬት ያሉ አካሎች (planets - ፕላኔቶች)፥ ምድር እና መሰሎቿ።

ፕላኔቶች በጨለማው ጠፈር ቢያበሩም የራሳቸው የሆነ ብርሃን የላቸውም። ከፕላኔቶችና ከጨረቃዎች የሚመጣ ብርሃን ስለማይርገበገብ ከከዋክብት በቀላሉ ይለያሉ።

እንደ እሳት የሚርገበገቡ የሚመስሉት (twinkle) ከዋክብት ናቸው። ግን ተርገብጋቢው የምድር አየር ነው እንጂ፥ የከዋክብት ብርሃን አይደለም።

የጠፈር ደንጋዮች፡

በየጊዜው ከጠፈር ወደ መሬት እየበረሩ፥ አልፎ አልፎም መሬትን የሚመቱ የከሰሙ - እጅግ ጥቃቅን የከዋክብት ሽርፍራፊዎች።

ጅራታም ኮከብ (comet) የተባሉትን እንደ ጠፈር ደንጋዮች መቁጠር ይቻላል። የጠፈር ደንጋዮች የምንላቸው (meteorites) ብዙውን ጊዜ ብረት፥ ኒኬል፥ እና ካርቦን ይኖራቸዋል።

የጠፈር ደንጋዮች ከምድር ላይ ያረፉ እንደሆን፥ እንደየመጠናቸው አነስተኛ ወይም ትልቅ ጉርጓድ ይፈጥራሉ።

አንድ የጠፈር ደንጊያ በበሃ ደንጊያ ላይ ያረፈ እንደሆን፥ የዝናብ ውሃ በጉርጓዱ ገብቶ ድንጋዩን እየሸረሸረ ዋሻ እና ኢንቁፍቱዎች (sink holes) በቶሎ እንዲፈጠሩ ያደርጋል።

የጠፈር አይኖች፡

በዚህ መጽሐፍ ጽልመተ ጥልቀቶችን (black holes) እንደ የጠፈር አይኖች በመውሰድ፥ ከሰው አይን ብሌን ጋር በማመሳሰል፥ አንዳንድ ባሕረ ሃሳቦችን ገነባን እንጂ፥ ጠፈር አይን አለው ለማለት አደለም (ቢኖረውስ ማን ያውቃል)።

የማገናዘቢያ ምስል:

ንድፈ ሃሳቦችን በተቃለለ መንገድ ማስቀመጥ። (simulation)

የአሸዋ ድንጋይ፡

እንደ አዛሂት (quartz) ጠጣር በሆነ አሸዋ የተገነባ ድንጋይ። (sandstone)

የብርሃን ዓመት፡

የብርሃን ጨረር በሰኮንድ 300,000 ኪሎ ሜትር እየተጓዘ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚደርስበት የርቀት ልክ፤ የከዋክብት ርቀት መግለጫ። light year

የንብብሮሽ ሕግ፡

አንድ ነገር በሌላው ላይ ከተቀመጠ፥ መቀመጫው አስቀድሞ ሳይኖር ተቀማጩ አይኖርምና፤ በዝቅጠ አለቶች ጥናት መሠረት ከታች ያለው ዝቅጠ አለት ከላይ ካለው ያረጃል ይባላል፤ የመሬት መገለባበጥ ከሌለ። (law of superposition)

ጨረር ረጪዎች (ተለዋዋጭ ንጥረ ነገሮች)፡

ከተወሰነ እድሜ በኋላ ወደ ሌላ ንጥረ ነገር የሚለወጡ ንጥረ ነገሮች (radio active elements)።

የአንድ ንጥረ ነገር ማእከላዊ ሥፍራ (ኑክሊየስ) ባለበት የማይረጋ ከሆነ፥ ከውስጡ እጅግ ደቂቃን አካሎች እየተፈተለኩ ይወጣሉ (ጨረሮች ይረጫሉ)። በዚህን ጊዜ የአጠቃላይ አቶሙ ውስጣዊ ጠባይ ይለወጣል። የአተሞቹ ጠባይ ሲለወጥ ንጥረ ነገሩም ይለወጣል። እንዲህ አይነት ተለዋዋጭ ጠባይ የሚያሳይ ንጥረ ነገር ጨረር ረጪ (radio active) ይባላል።

ጨረር ረጪ ንጥረ ነገሮች ለመለወጥ መበስበስ ከመጀመራቸው በፊት (መነሻው አነሰም በዛም) የነበራቸውን የአቶሞች ይዘት ግማሹ በስብሶ የሚያልቅበት ጊዜ የጊዜ መለኪያ ሆኗል። ለምሳሌ፡ - ዩራኒየም - 238 ግማሽ አካሉ የሚበሰብሰው በ4.5 ቢሊዮን ዓመታት፤ ካርቦን - 14 በ5730 ዓመታት ውስጥ ነው።

ዘለአለማዊ ቁጥር፡

የማይቆጠር፥ ወሰን የሌለው ቁጥር።

ዘለአለም፡

ምንጊዜም፥ ለሁሉ ጊዜ፥ ለጊዜ ወሰን የሌለበት።

ዝግ፡

ከውስጡ ማንኛውንም ነገር (ሙቀትንም) ወደ ውጪ የማያስወጣ ከውጪም ምንም ነገር የማያስገባ። የከፍት ተቃራኒ። (closed system)

ዝቅጠ አለት፡

በውሃ ውስጥ ቆይቶ የዘቀጠ አፈር ከጊዜ ብዛት ወደ አለትነት ሲቀየር፤ ከባህር የዘቀጠ አለት። (sedimentary rock)

ዲ ኤን ኤ፡

ሕይወት መስራች ኬሚካል።

ባለ ሕይወትም ሆነ ሕይወት አልባ፥ በአተሞች ቅንጅት የተገነባ ነው።

የተወሰኑ አተሞች ባንድነት ሲሆኑ ሞሌኩል ይሆናሉ።

በአንድ የዲ ኤን ኤ ሞሌኩል ውስጥም ብዙ መወጣጫዎች እንዳሉት ባለ ሁለት ጥምዝዝ መንሰላል የመሰለ ከአተሞች ተገንብቷልና፤ ይኸ ነው ዲ ኤን ኤ የተባለ።

በአንድ የሰው ህዋስ (cell) ውስጥ ዲ ኤን ኤዎች ባንድነት ታጭቀው እንደ ዘንግ አይነት ቅርጽ ይመሠርታሉ፤ ይህም ክሮሞዞም ይባላል።

በሰው የሕይወት ህዋስ (cell) ውስጥ 46 ክሮሞዞሞች ይገኛሉ። በየክሮሞዞሙ ውስጥ የተለያዩ ውስጣዊ ጠባዮችን የሚወስን ጂን የተባለ ኬሚካል ይገኙበታል። በያንዳንዱ ክሮሞዞም ውስጥ ከሺህ የሚበልጡ ጂኖች ይገኛሉ።

ዳይናዞር፡

ከምድር ገጽ የጠፋ ጥንታዊ አውሬ። ዳይናዞሮች በአይነትና በትልቅነት የተለያዩ ናቸው። እጅግ ትልቅ የተባለው ብራኪዮዛውሩስ ይባላል። ይህም በቁመቱ 20 ሜትር፥ በርዝመቱም 30 ሜትር፥ በክብደቱም እስከ 100 ቶን (224,000 ኪሎግራም) የሚመዝን ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል። ዳይናዞሮች የነበሩበት ዘመን ከዛሬ 230 ሚሊዮን ዓመታት ጀምሮ እስከ ዛሬ 65 ሚሊዮን ዓመታት ድረስ (ለ165 ሚሊዮን ዓመታት) ነው ተብሎ ይገመታል።

ጅራታም ኮከብ፡

ባለ ዘርፋም (ጅራታም) ኮከብ። (comet)

በልምድ ኮከብ ተባለ እንጂ፥ ይህም የጠፈር ደንጋይ ነው።

ጉተታ፡

ወደ ውስጥ የሚስብ፤ በማንኛውም አካል ውስጥ ከሚገኝ ከኢሌክተሮ ማግኔቲክ እና የኑክሊያር ኃይሎች የሚመነጭ

የጥብቅብቆሽ ክስተት - ከጉተታ የሚመጣ መሰብሰብ። በጉተታ ክስተት ውስጥ የስበት (gravity) ኃይልም ይኖራል።

ግሉኦን፡

በጠፈር ውስጥ ያሉ አካላትን የሚያገናኝ (የሚያያይዝ)።

ኤተር የተባለውም እንዲሁ በጠፈር ውስጥ ይኖራል።

አካሻ የተባለውም በፍልስፍና ተመሳሳይ መሆኑ ነው።

ግፊት፡

ወደውጪ የሚያስወጣ ኃይል። ግፊት ከሙቀት ኃይል ይመነጫል።

ጸረ አካል፡

የአካል ተቃራኒ። (anti matter)

ጸረ አካል ከአካል የሚለየው በተቃራናዊ ጠባዩ ብቻ ነው። በአካል የተገነባ ብርጭቆ በጸረ አካል ከተገነባ ብርጭቆ ምንም ልዩነት አይኖረውም። ነገር ግን በጸረ አካላት ውስጥ የኢሌክትሮኖችና የፕሮቶኖች ጠባዮች በተቃራኒነት ስለተቀመጡ፥ በጸረ አካል የተገነባ ብርደቆ በአካል የተገነባውን ብርጭቆ ቢነካው ሁለቱም ብርጭቆዎች በታላቅ ፍንዳታ ይጠፋፋሉ።

አንድ ኢሌክትሮን እና አንድ ፖዚትሮን ቢጋጩ፥ ሁለቱም ይጠፋፉና በነርሱ ምትክ የጋማ ጨረር ብርሃኑን ያስተጋባል። እኛ ግን ይህንን ጨረር በአይናችን ለማየት አንችልም። ሆኖም ይህንን ፍሬ ሃሳብ በመጠቀም፥ በጋማ ጨረር ፎቶግራፍ የሚያነሳ PET Scanner (Positron Emission Temography) በህክምና አለም ውስጥ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ ነው ያለው።

የአካል እና የጸረ አካል መጠፋፋቶች በጠፈር ውስጥ በታላላቅ ቦግታዎች ሲካሄዱ፥ እስከ ምድራችን የአየር ክበብም ሲደርሱ እየተመለከትን፥ ጸረ አካላት ሲጠፉ እኛ ብቻ ተረፍን ማለት ይከብዳል። በጸረ አካላት የተገነባ ሌላ ጠፈር ቢኖር ማን ያውቃል።

ከጠፈር ወደ መሬት የሚገቡ ጸረ አካሎች (ፖዚትሮኖች) መሬትን በየጊዜው እንደሚጎበኟት ይታወቃል። በጠፈር ውስጥ በአንድ ወገን ከዋክብት፥ ጸሐዮችና ጨረቃዎች፥ እንዲሁም እኛና መሰሎቻችን በአካል እንደተገነባን፥ በጸረ አካላትም የተገነቡ

ሌሎች ከዋክብት፥ ጸሐዮችና ጨረቃዎች፥ እንዲሁም እኛና መሰሎቻችንን በመምሰል የተገነቡ ሊኖሩ ይችላሉ።

በአካል የተገነባ ደበበ በአካል በተገነባ ምድር ከተመላለሰ፥ በጸረ አካል የተገነባ ደበበም በጸረ አካል የተገነባ ምድር ውስጥ ሊመላለስ ይችላል። ግን ሁለቱ ደበበዎች ሲገናኙ እጅ ለእጅ ባይጨባበጡ ይሻላል፤ እንዳይጠፋፉ። “የአካልና የጸረ አካል መገኘት እድል መሳ ለመሳ ሊሆን ይችላል።” (Close Franc, 2009)

ጽልመተ ጥልቀት፡

በጠፈር ውስጥ በጨለማነቱና በከፍተኛ የስበት ኃይሉ የሚታወቅ ሥፍራ። (black hole)

ብርሃን የሞገድ (wave) እና የቅንጣት (particle) ጠባያትን በቅንጅት የያዘ በመሆኑ፥ በከፍተኛ ስበት (gravity) ሊጠለፍ ይችላል። ታዲያ፥ ይህ በጠፈር ጥቁር መስሎ የሚታይ ሥፍራ ጥቁር የሆነበት ምክንያቱ፥ ብርሃን ሁሉ ወደ ማዕከላዊው ባዶ የጨለማ ሥፍራ በታላቅ የስበት ኃይል ስለሚሰርግ ነው። የሚያርፍበት፥ ወይም የሚገጨው ነገር ስለሌለ፥ እንዲሁ ጭልጥ ብሎ ስለሚጠፋ፥ ጽልመተ ጥልቀት ተባለ። ግን የሚሄድበት ቢኖረው ማንም አያውቅም።

ጠፈር፡

ማንኛውንም አካል (ከዋክብት፥ አገረ ከዋክብት፥ ጨረቃ ወዘተ..) በውስጡ ያቀፈ።

ጥምል የጋስ - ጢስ፡

ከምድር ሲታይ እንደጢስ የሚመስል፥ እነ ፎቶን፥ ኢሌክትሮን እና ኒውትሪኖ ያሉበት። (nebulae)

ፎቶን፡

ሁለት አንድ አይነት ግን ተቃራኒ የሆኑ ደቂቀ አካላት ሲጋጩ እነርሱ ተጠፋፍተው የሚቀረው ኃይል ፎቶን ይባላል። ለምሳሌ፥ ኢሌክትሮንና ጸረ ኢሌክትሮን ሲጋጩ፥ ሁለቱም ጠፍተው በምትካቸው ፎቶን ይፈጠራል።

ፍጽምተ አካል (ሚሻክል)፡

ንጽረ አካል፥ የሰማይ አካል።

በሰማይ ቤት አንድ ነገር ከሌላው መለየቱን የሚገልጽ ብለን፥ ከምድራዊ አመለካከታችን ወጣ ለማለት እንዲረዳን፥ በአካል (በቁስ አካል) ትይዩ፥ በሌላው አለም ላለው ሁሉ "እንደ አካል የሆነ ነገር" ቢኖር ተብሎ ለሚታሰብ፤ ሰማያዊ አካል ለምንለው በአማራጭነት የተጠቀምንበት ቃል ነው።

ፍጽመምተ አካል በሰማያዊው አለም፥ ልክ እንደኛው አለም ለሰማያውያን ቁልጭ ብሎ ከኛ ሃሳብ ውጪ በራሱ ሕልውና የሚጸና ነው።

በሃይማኖት የምናስበው ከግለሰቦች የአስተሳሰብ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ ሰማያዊው አለም ልክ እንደምናስበው ሊሆን አይችልም።

የመንፈስ አካሉ ቢባል፥ "መንፈስ ደግሞ ምን አካል ይኖረዋል?" ይባላል። አካል የሚለውን ቃል ጭራሹኑ አስወግዶና ሌላ አዲስ ቃል አውጥቶ መጠቀም ይሻል ይሆናል በማለት "ሚሻክል" የሚል ቃል አውጥተን ተጠመመናል (በዚህ መጽሐፍ)።

ሆኖም፥ አዲስ ቃል ሲወጣ አብሮት ሌላ ሃሳብ እንዳይጋብዝ፤ የሰው ልጅ ቶሎ የሚገባው ከሚያውቀው (ከአካል ጋር) ሲዛመድለት ስለሆነ፥ ፍጽምተ አካል - ንጽረ አካል - የሰማይ አካል እያልን በነኚህ ድርብ ቃላትም መጠቀም አስፈለገ።

ከላይ የቀረቡት የቃላት ትርጉሞችና ተጨማሪ ማብራሪያዎች በመጽሐፉ የተገለጹትን ለማብራራት ያህል ስለሆነ፥ ለሁለንተናዊ ግልጋሎት የሚውሉ የቃላት ትርጉሞችን ከሌላም ሥፍራ ያመሳክሯል።

# አባሪ

# የጊዜ እርከኖች

**<u>የስነ ምድር (ጂኦሎጂ) የጊዜ እርከኖች</u>**

- ሕይወት አልባ ፕሪካምብሪያን (Precambrian)- ዘመነ አርኪያን (Archean) - ከ4600 ሚሊዮን ዓመታት እስከ 2500 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ - አካላዊ ሕያዋን ያልታዩበት።
- ባለ ሕይወት ፕሪካምብሪያን ዘመነ ፋነሮዞይክ (Phanerozoic) - ከ2500 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ እስከ 570 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ - እጅግ ጥቃቅን አካላዊ ሕያዋን በጥቂቱ የታዩበት።
- ቀዳማይ ሕይወት (Paleozoic) - ከአምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ዓመት አካባቢ እስከ ሁለት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመት አካባቢ - አካላዊ ሕያዋን በብዛት የታዩበት።
- መሐል ሕይወት (Mesozoic) ከሁለት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመት አካባቢ እስከ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዓመት አካባቢ - በመሬትም በባህርም ሕይወት የተበራከተበት ዘመን - ዳይናዞር የተባለ የመሬት ግዙፍ እንስሳ የኖረበት።
- ደኃራይ ሕይወት (Cenozoic) ከስልሳ ሚሊዮን ዓመት አካባቢ እስከ ዛሬ ድረስ - ከመሬት እንስሳት መካከል ዝሆን፥ ጎሽ፥ አንበሳና ነብር፥ ዝንጀሮና ፕጣ፥ በባህር ውስጥም ላርክ የተባለው አሳ በሊታ የታዩበት።

**<u>የሰብአዊነት የጊዜ እርከኖች</u>**

- ዘመኑ የማይታወቅ - ሰማያዊ ሰው (“አዳምና ሔዋን”) ከሚሻክላዊነት ወደ አካላዊነት የተሸጋገሩበት፥
- መቶ ወይም ሁለት መቶ ሺህ ዓመታት - እስከ አሁን - ሥጋዊ ሰው (“አዳምና ሔዋን”) በመሬት ላይ።

- በግምት ከ100 ሺህ ዓመታት፥ አካባቢ - እስከ 10 ሺህ ዓመት አካባቢ ድረስ - የተለያዩ ስደቶች በተለያዩ ሥፍራዎች፡-
  - በግምት ከ53 ሺህ ዓመታት ጀምሮ - ስደት ከአፍሪካ ወደ አውስትራሊያ፥
  - በግምት ከ40 ሺህ ዓመታት ጀምሮ - ስደት ወደ አውሮፓ፥
  - በግምት ከ15 ሺህ ዓመታት ጀምሮ - ስደት ወደ ሰሜን አሜሪካ።
- ከ10 ሺህ ዓመት በፊት - በራድ ዘመን ሳይለቅ፥ በአንዳንድ ሞቃት ሥፍራዎች አካባቢ - በባህር ዳርቻዎች፥ በሳሃራ ሜዳማና ለም ሥፍራዎች ለተወሰኑ ዓመታት (ምናልባት ለአንድ ሺህ ዓመታት) ሰዎች ሳይሰደዱ የኖሩበትና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑበት (ከኖህ በፊት የነበረ ሥልጣኔ)፤ የጥንታውያን ኢትዮጵያውያኖችም ሥልጣኔ።
- 10 ሺህ ዓመት አካባቢ ጀምሮ እና የኖህ ዘመን (የጥፋት ውሃ) ተብሎ ከሚታሰበው ዘመን አካባቢ - ኢትዮጵያውያን የሄኖክ ዘሮች - የኖህ ቤተሰቦች፥ በአንድ ወጥ ዘራቸው ወደ ሰሜንና ወደ ምሥራቅ (ወደ ቱርክ ወይንም ወደ ኢራክ..) ተሰደው ሳለ፥ በሦስት የዘር ቀለም መለያ - በሦስት ዘሮች በግልጽ የታዩበት።
- ከ10 ሺህ ዓመት አካባቢ ጀምሮ እስከ 6 ሺህ ዓመት አካባቢ - ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራዎች የተዛመተ፥ የሰሜን አፍሪካውያን ከፍተኛ ሥልጣኔ፤ የአውሮፓውያንም ግብርና (6500 ዓመታት አካባቢ)።
- ከ6 ሺህ ዓመት አካባቢ - እስከ 4 ሺህ ዓመት አካባቢ - የሳሃራ ድርቅ - የሰሜን አፍሪካውያን ስደት - ወደ አባይ ወንዝ መጠጋትና መሠልጠን (የግብጾች፥ ማለትም የሰሜን አፍሪካውያን - የኢትዮጵያውያን ሥልጣኔ - የፒራሚድ ግንባታ)፤ ከነባር እስያውያን ጋር የንግድ ልውውጥ - የእስያውያን የቀድሞው ሥልጣኔ፤ የደቡብ አውሮፓውያን የቀድሞ ሥልጣኔ፤ የሰሜንና የደቡብ አሜሪካውያን የቀድሞ ሥልጣኔ።

ከላይ የተጠቀሱትን ግምታዊ የጊዜ እርከኖች በመጽሐፉ ከተጠቀሱት ተፈጥሮአዊ ክስተቶች እና ታሪካዊ መረጃዎች ጋር ማመሳከር ይገባል።

# ዋቢ መጻሕፍት
## (ለአራቱም መጻሕፍት)


Abdullah Yusuf Ali (Translation by), 2002: **The Qur'an**, Published by Asir Media.

Bartusiac Marcia (edited and with Introduction), 2006: **Archives of the Universe**, Vintage Books, A Division of Random House, INC. New York.

Bhaktivedanta Swami Prabhupada A.C (His Devine Grace), 1972, 1983: **Bhagavad Gita As it is,** The Bhaktivedanta Book Trust

Charles Darwin, 1958: **The Origin of Species**, Signet Classics.

Close Frank, 2009: **Anti Matter,** Oxford University Press.

Coogan Michael D., 2003: **World Religions,** Duncan Baird Publications, London.

Davidson Basil, 2005: **Africa in History**; Touchstone, Rockfeller Center, New York, N.Y.

Drage Hale Rosemary, 2004: **Understanding Christianity**, Duncan Baird Publishers, London.

Ehrlich Carl S., 2003: **Understanding Judaism**, Duncan Baird Publishers, London.

Elain Murray Stone, 2004: **A Saint and His Lion, the Story of Tekla of Ethiopia,** Paulist Press.

Hammond, 2002: **Concise Atlas of World History**, 6$^{th}$ Edition, Map Makers for the 21$^{st}$ Century; HarperCollins Publishers.

Hausman Gerald, 1997: **The Kebra Nagast**: St. Martin's Press, New York

Hawking W. Stephen and Leonard Mlodinow 2010: **The Grand Design**; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 1988: **A Brief History of Time**, From The Big Bang to Black Holes; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 2005: **The Theory of Everything**, Fate of The Universe; Phonix Books.

Houston Drusilla Dunjee, 2007: **Wonderful Ethiopians of The Ancient Empire**; Nuvision Publications, LLC, Sioux Falls, SD, USA.

Jackson G. John, 1939 And 1985: **Ethiopia and the Origin of Civilization**; Nuvision Black Classic Press, Baltimore, MD. USA.

John Brockman (Editor), 2010: **This Will Change Everything**, Ideas That Will Shape The Future; Harper Collins Publishers, New York, NY. 10022.

Laszio Ervin, 2006: **Science and The Enchantment of The Cosmos**; The Rise Of The Integral Vision Of Reality, Inner Traditions, Rochester Vermont.

Leslau Wolf, 1976: **Concise Amharic Dictionary**, Amharic - English, English - Amharic, Otto Harrassowitz – Wiesbaden, Commercial Printing Press, Adds Ababa, Ethiopia

Mary and John Gribbin, 2003: **From Atoms to Infinity**; Icon Books.

Muhaiyaddeen Bawa M.R., 1987, revised 2004: **Islam and World Peace, Explanations of a SUFI,** The fellowship Press, Philadelphia, PA.

Oldstone Moore Jennifer, 2003: **Understanding Confusianism**, Duncan Baird Publishers, London.

Rana Fazal & Ross Hugh 2004: **Origin of Life**; Navpress, Colorado Springs, CO80920.

Ross Hugh 2010: **Beyond the Cosmos**, **What Recent Discoveries in Astrophysics Reveal About the Glory and Love of God,** 2010:Signalman Publishing, Orlando, Florida.

Southwood, Richard 2002: **The Story of Life**, Oxford University Press.

Steinberg Milton, 1975: **Basic Judaism**, Harcourt Brace Jovanovich, Publishers. San Diego, New York, London.

Vorilhon Claude, 1983፡ **Le Livre Qui Dit La Verite**

Wallis Budge (1932): **The Kebra Negast,** Oxford University Press, London, Humphrey Milford.

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ ***ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ***፥ አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ ኢታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)፥ 1978፤ ***ገድለ አቡነ አረጋዊ፥*** ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘጋጅ)፥ 1992፤ ***መልክአ ሚካኤል በአማርኛ፥*** ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘጋጅ)፥ 1964፤ ***መዝሙረ ዳዊት ወጸሎታት ዘነቢያት ወመዐልየ ዘሰለሞን***፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1951)፤ ***የኢትዮጵያ ታሪክ*** 2ኛ መጽሐፍ።

ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት (አሳታሚ)፥ 1990፤ **ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው**፥ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አቡነ ሽኑዳ 3ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ (ውርስ ትርጉም በዲያቆን ታደሰ ወንድም አገኘሁ)፥ 1993፤ **የንስሐ ሕይወት፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ፥ 2009፤ **በአዲስ መሠረት ላይ የነበረው ጥረት፥** Washington D.C. 20018 USA.

አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፥ 1998፤ **ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት፥** ኅትመተ ብራና ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥** እና ሌሎች ግለ-ወጎች።

ብሩህ ዓለምነህ፥ 2010፤ **የኢትዮጵያ ፍልስፍና የዘርርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ (ከነሐተታቸው)**

ኢንተርናሺናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፥ 2001፤ **መጽሐፍ ቅዱስ፥** አዲሱ መደበኛ ትርጉም፥ International Bible Society.

ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ 1991፤ **ትምህርተ መለኮት፥** ሁለተኛ እትም፥ ንግድ ማተሚያ ቤት ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

ዓባይነህ ካሴ፥ 1992፤ **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥** ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንደኛ መጽሐፍ፥ አሳታሚ ማሕበረ ቅዱሳን፥ አዲስ አበባ።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1992፤ **አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፥** ሁለተኛ እትም።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1995፤ **ሚሊንየም እንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት፥** Revised Edition.

እሸቱ ታደሠ ወንድም አገኘሁ (ዲያቆን) እና ደጀኔ ሽፈራው በላቸው (ዲያቆን)፥ 1991፤ **ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

ወሰኔ ይፍሩ፤ አዘጋጅ፤ 1990፤ **ሄኖክ**፤ በየዓመቱ የሚታተም የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት፥ 1101 S.W. Washington St. Suite 129 Portland, OR 97205

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (አሳታሚ)፥ 1980፤ **መጽሐፍ ቅዱስ፥** የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፥ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም

ማተሚያ ቤት ታተመ፥ United Bible Societies Africa Regional Centre, Nirobi, Kenya

የጥንት ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1983፤ **ተአምረ ማርያም፥** አንደኛ መጽሐፍ፥ አዘጋጅና አከፋፋይ ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ፥ አዲስ አበባ።

የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1946፤ **ገድለ ተክለ ሃይማኖት፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ዲበኩሉ ዘውዴ፥ 1986፤ **ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና**፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ጥዑመ ልሳን ካሳ (ሊቀ ካህናት - ርዕሰ ደብር)፥ 1981፤ **ያሬድና ዜማው፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።